# የሕላዌ እንቆቅልሽ

(ፍልስፍናዊ ነገረ መለኮት)

ትርጉምና ዝግጅት፦ ማንደፍሮ ማሩ

የደራሲው መብት በሕግ የተጠበቀ ነው። ጸሐፊውን በጽሑፍ በማስፈቀድ ለሽያጭ
ሳያውሉ ሙሉውን ማባዛትና ማሰራጨት፣ እንዲሁም መተርጎም ይቻላል።

ካልተጠቀሰ በስተቀር፣ የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅሶች የተወሰዱት ከቀዳማዊ ኀይለ ሥላሴ
(ቀ/ኀ/ሥ) እትም (1962 ዓ.ም) የተወሰዱ ናቸው።

ሁሉም ዓመታት እንደ አውሮፓውያን አቆጣጠር (እ.አ.አ.) ናቸው።

© ፪ሺህ ፲፭ ዓመተ ምሕረት

አዲስ አበባ፣ ኢትዮጵያ።

***

# The Riddle of Existence

(Philosophical Theology)

Translation & Preparation: Mandefro Maru

© September 2022 G.C.

የገጽ ሽፋንና የውስጥ ገጽ ንድፍ፦ ዶጋሊ ዲዛይን

አሉላ ጌታሁን | +251 920393813 | alu2get@gmail.com

# የሕላዌ እንቆቅልሽ

## The Riddle of Existence

(ፍልስፍናዊ ነገረ መለኮት)

ክርስቲያን ኤግዚስቴንሻል ፈላስፎች እና የሥነ መለኮት ሊቃውንት በሕይወት ሁነኛ ጭብጦች ላይ ያቀረቡት ዲስኩር።

# ማውጫ

## የሕላዌ እንቆቅልሽ

መቅድም ........ vi

የተርጓሚው ማስታወሻ........ viii

**መጽሐፍ 1**

(የጊዜ ምስጢር)

1. ዘለዓለማዊ አሁን ........ 12
2. የምወደው መልካም፤ የማደርገው ክፉ........ 29
3. መርሳት እና መረሳት........ 43
4. መንፈሱ በመሐላችን........ 58
5. መዳን........ 71
6. ሰው እና ምድር........ 81
7. በሁሉ አመስግኑ........ 96
8. በሽተኞችን ፈውሱ፥ አጋንንትን አስወጡ........ 108
9. ብቸኛ መሆን እና ለብቻ መሆን!........ 119
10. የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ........ 135
11. የእግዚያብሔር ፍለጋ........ 149
12. የእግዚያብሔር ስም........ 161
13. ጥበብ........ 172

**መጽሐፍ 2**

(የክብር ሽማ)

1. ሴቷ እና ወንዱ ........................................ 184
2. ቁጣ እና እርቅ ........................................ 225
3. የክብር መጎናጸፊ ........................................ 247
4. የጸሐፊዎቹ የሕይወት ታሪክ ........................................ 268

# መቅድም

መጻሕፍት እና እኔ ጓደኛሞች የሆነው ከልጅነት ነው፤ ከቄስ ትምህርት ቤት ጀምሮ። ደግሞም እድለኛ ነኝ፤ መጻሕፍትን እንድወድ እና እንድቀርብ ባደረጉኝ ሰዎች ዙሪያ ነው ያደኩት። ከልጅነቴ ጀምሮ በዚህ አቅጣጫ በሕይወቴ ውስጥ አስተዋዕፆ ያበረከቱ ሰዎችን ስም ዘርዝሬ አልጨርስም። አያቴን ግን ሳልጠቅስ ብቀር በሕይወት ውስጥ ውለታ ቢስ እሆናለሁ። መደበኛ ትምህርት ያለመማሩን ቁጭት፣ በእኔ መማር ውስጥ ማዳን ፍለጋው ነበር። በተለይ የቤተ ክህነት ትምህርት እንድማር የነበረው ጉጉት። ስለዚህ አያቴ መማርን ብቻ ሳይሆን ሥነ መለኮታዊ ሐሳቦችን ለማጠራቀም ብቻ የተፈጠረ የሚመስል ጭንቅላት እኔ ውስጥ ሰርቷል።

አያቴ በላይ መኮንን ዋሴ ጓሉ ይባላል። የቄስ ቤተሰብ ልጅ ነው። የእርሱን እምነት፣ ማሕበራዊ፣ ፖለቲካ እና ግላዊ የሕይወት ምልከታ ከልጅነት ብዙ ጠጥቻለሁ። እኔ የፍልስፍና እና የሥነ ጽሑፍ ፍቅር አከልኩበት። ሞላ መሰለኝ።

ሌላው ግን በኢመደበኛ መንገድ መደበኛ የሆነ የሥነ መለኮት፣ የቤተ ክርስቲያን ታሪክ፣ የታላላቅ ሰዎች ሕይወት የተግባራዊ ክርስትና ጽንሰ ሐሳቦችን ገና የመጀመሪያ ደረጃ ተማሪ እያለሁ በየእለቱ በሚባል ደረጃ ያቋደሰኝ ሰው አለ። ልጅ እያለሁ መንፈሳዊ አባቴ፣ ስጎረምስ ወንድሜ፣ ጉርምስናን መሰናበቻ ጫፍ ላይ ሳለሁ ወንድሜ፣ አሁንም ጓደኛዬ፤ ዘሪሁን ተካ ነው። ዘሪሁን ተካ ይባላል። አያቴ የኦርቶዶክ ቤተ ክርስቲያን ዲያቆን እንድሆን እንደናፈቀ፣ ግን እንደማልሆን ገና በጠዋቱ እንዳረጋገጠ አለፈ። ዘሪሁን የቤተ ክርስቲያን መጋቢ እንደምሆን እምነት እና ፀሎቱ ነበር። እኔም ለመስበክ ወደ ኋላ የማልል ተጠባቂ ወንጌላዊ እመስል ነበር እኮ! መጋቢም አልሆንኩም። የምሆንም አይመስለኝም።

ነገር ግን ውስጤ ከእነዚህ ሁሉ ምንጮች ፈሶ ወደ ውስጤ የሞላው የእግዚብሔር ቃል፣ የሥነ መለኮት እና የክርስትና መልዕክት ፍቅር እርቆ አያውቅም። ልቤ በዝምታ ውስጥ፣ በማይሰማ ሹክሹክታ ይህን ዓለማ እና ግብ እንዳገለግል ሳትወተውተኝ ቀርታ አታውቅም። እኔ ደግሞ ማገልገሉ ሳይሆን የጠበበ እና ሊታገልባቸው ከሚገባቸው ነገረ ጉዳዮች የራቀ፣ የክርስትና መልዕክት እና ዓለማ በአንድ መንደር ያጥራል ካልኩት ተቋማዊ ክርስትና የራቀ አገልግሎት እንዴት ሊኖር ይችላል በሚለው ላይ እንደተብሰለሰልኩ አለሁ።

እና ምንም ሳልሰራ ዘመኔን ልጨርስ!? ውስጤ ጭቅጭቅ ነው። ይሔ መጽሐፍ ከብዙ ምክንያቶች ዋነኛው የውስጤን ጭቅጭቅ ዝም ለማሰኘት ነው። እና ምን በማድረግ የውስጤን ጭቅጭቅ ዝም ላሰኝ?! መልካም፣ አስቀድመው የክርስትና መልዕከት ተቋማዊ እና ባሕላዊው ክርስትና እንዳስቀመጠው ሳይሆን፣ የሰው ልጆች ጉዳይ ሆኖ ከዘላለም ግብ አንፃር የማይታይ ምን ነገር የለም የሚለውን ሐሳብ ያንሸራሸሩት እና ከዚህ ሐሳባቸው ወይን ጠጥቼ የረካሁባቸውን የክርስቲያን ፈላስፎች እና የሥነ መለኮት ሊቃውንትን ሥራ በተቻለ መጠን የአማርኛ አንባቢ ሊረዳቸው በሚችል መልኩ በመተርጎም እና ጥቂት ማብራሪዎችን በማከል ለምን አልጀመርም የሚለው አማራጭ የሌለው ሆኖ አገኝሁ።

ሌላው ዕለት በዕለት በተለይ ከዚህ በፊት የህትመት ብርሃን ያየ ምን ሥራ የሌላቸውን የሚፈታተን ነገር የሃርድ ኮፒ ህትመት ነው። ብዙ ጊዜ መፅሀፍ መተርጎም ወይም የራሴን ወጥ ሥራ ማሰብ እፈልግና ከምተውበት ምከንያት አንዱ ህትመት ነው። የማይሞከር ለምን አልሞክርም በሚል በPDF መልክ ለምን ለአንባቢ አላቀርብም የሚለው ሚዛን ደፍቶ ተገኘ። በዚህ ብቻ እንደማይቆም ተስፋ አደርጋለሁ።

# የተርጓሚው ማስታወሻ

በዚህ መፅሀፍ የአራት ክርስቲያን ፈላስፋ፣ ሥነ መለኮት ምሑራን እና አሳቢዎችን ሥራ ወደ አማርኛ ተርጉሚያለሁ። የፖል ቲሊች ሰፊውን ቦታ የወሰደ ነው። The eternal now በሚል የሰራውን ሥራ ሙሉ በሙሉ በሚባል መልኩ ተርጉሜዋለው። ይሄ ሥራው መጀመሪያ በብዙ ዩኒቨርዚቲዎች እና ኮሌጆች እየተገኘ በዋና ዋና ጉዳዮች ላይ የሰጠው ሌክቸሮች እና ስብከቶች ስብስብ የያዘ ነው። ሌላው የራይኖሆልድ ኒቡር ሥራ ነው። Discerning the Signs of the Times ከሚለው ሥራው ውስጥ "እኔ ቁጣ እና እርቅ ብዬ" የመለስኩትን Anger and reconciliation የሚለውን መርጬ ወደ አማርኛ መልሼዋለው። ሌላው Man in revolt ከሚለው ሥራው ውስጥ Man and Woman የሚለውን ክፍል ከኢሚል ብሩነር ወስጄ፣ "ሴቷ እና ወንዱ" በሚል ወደ አማርኛ መልሼዋለው። መጨረሻ ላይ "የክብር መጎናጸፊ" በማለት የተረጎምኩት የታዋቂውን እና አሁንም ድረስ ተወዳጅነቱ ያልበረደው የሲ.ኤስ.ሊውስን ሥራ ነው። The weight of Glory ከሚለው ሥራው ውስጥ የመፅሐፋም ርዕስ የሆነውን ራሱን The weight of Glory ወደ አማርኛ መልሼዋለው።

እንደ እውነቱ የነዚህ ፈላስፎች፣ የሥነ መለኮት ምሁራን እና አሳቢዎች ሥራ ከመተርጎም ማብራሪያ መሥራት ተመራጭ ነው። ወደ አማርኛ ቋንቋ ለመመለስ የሚያዳግቱ ጽንሰ ሐሳቦችን፣ ማብራሪዎችን እና የአንባቢውን የከዚህ በፊት ሥራዎቻቸውን ቅድመ ንባብ የሚጠይቁ በመሆናቸው። ስለዚህ በተቻለኝ መጠን ሐሳባቸውን ያስተላልፋል ብዬ ያሰብኩትን መንገድ በመፈለግ ለመሥራት ጥረት አድርጊያለሁ። ለምሳሌ ቁልፍ ቃላትን በሌላ የአማርኛ ምትክ ቃል ከመተርጎም በአረፍተ ነገር ማብራራት ተገቢ ነው ብዬ ስላመንኩ የቁልፍ ቃሉን ሐሳብ በረዘመ አረፍተ ነገር አብራርቻለሁ። ቁልፍ ቃሎችን ብቻ ሳይሆን አረፍተ ነገር በአረፍተ ነገር ለመተርጎም የሚዳግቱ ፍልስፍናዊ እና ሥነ መለኮታዊ ግልፅነት የሚጎድላቸውንም ሰፋ አድርጌ ለማስረዳት ሞክሪያለሁ።

ሌላው የደራሲዎችን ሥራ ሊረብሽ ይችላል ብዬ በማሰቤ ተጨማሪ ማብራሪያ የሚስፈልጋቸውን ሐሳቦች በህዳግ እና በመጣጠፍ መልክ አስቀምጫለሁ። በመጨረሻ ደግሞ ደራሲዎቹን እና የሰሯቸውን ዋና ዋና ሥራ የሚዘረዝር የሕይወት ታሪካቸውን የደራሲዎቹ ሕይወት በሚል ከ New Encyclopedia ላይ ወስጄ ተርጉሜ አቅርቢያለሁ። ለምሳሌ New Encyclopedia ፖል

ቲሊችን አንዳንድ ቦታ እና በአንዳንድ ሥራዎቹ ላይ ትርጉም የለሽ እና ልክ ያልሆነ ማብራሪያ ይሰነዝርበታል። ሌላ ጭቅጭቅ ስለሆነ ቆርጬ አውጥቼዋለው። ማን ናቸው ምን ሰሩ፣ የሚለውን ፍንጭ እንድታገኙ እና ለተጨማሪ ንባብ እንዲገፋፋችሁ በሚል በሚመች መልክ ነው የተረጎምኩት። በተረፈ የእነዚህን ጸሐፊዎች ሥራዎች ያነበበ New Encyclopedia የሕይወት ታሪካቸው እና ስለሥራቸው ያነሳው ነገር ውሃ የሚቋጥር፤ ለመተዋወቅ ያህል የሚጠቅም መሆኑን ይመሰክራል። መልካም ንባብ!

ከአንድ አመት በፊት የህላዌ እንቆቅልሽ በሚል ርዕስ ፍልስፍናና ስነ መለኮትን አጣምረው የፍጥረትን ፈጣሪና ፍጥረቱን በተመለከተ ያሉ ርዕሰ ጉዳዮች ላይ በሰሯቸው የፍልስፍና እና የስነ-መለኰት ስራዎች  አንቱታ ያተረፉ የክርስቲያን ፈላስፎችን ስራ በተቻለ መጠን ሊያስተላልፋ የፈለጉት ሀሳብ ለአማርኛ አንባቢ እንዲመች አድርጌ  በመተርጎም በሶፍት ኮፒ ለገበያ አቅርቤ፣ ከገመትኩትና ከጠበቅኩት ብዙ እጥፍ የሚሆን ተቀባይነትን አግኝቶ ነበር። ነገር ግን በጊዜው የብዙዎቹ ጥያቄ የነበረው ‘እባክህን ወደ ወረቀት ህትመት ይምጣልን’ የሚል ነበር። በጊዜው ለእኔ ያ የሚሆንበት እድል የሚኖር መስሎ ስላልታየኝ ሃርድኮፒ የሚታተም አይመስለኝም የሚል ምላሽ በመስጠት ቆይቼ ነበር።

እየደር ግን የሰው ጥያቄና እኔም መፅሐፉ በሃርድኮፒ የመታተሙ አስፈላጊነት እየታየኝ ስለመጣ ቀጥታ ወደ ደራሲው የመጻሕፍት ቤት ባለቤት አቶ ወንዱ ዘወዱ ጋር በቀጥታ በመሄድ ስለመጽሐፌ ሕትመት ጥያቄ አቀረብኩ፡ ፡ ወንድዬ በፍጹም ፍቅርና ወንድማዊነት ደስ ብሎት ለማሳተም ፍቃደኛ እንደሆነ ገልጦልኝ የሕትመቱ ስራ ተጀመረ። በዚህ በሁለተኛው የመጽሐፉ ሕትመት ላይ አስቀድሜ ላመሰግን የሚገባው ሰው ካለ ያ አንድ ሰው፥ የደራሲው መጻሕፍት መሸጫ መደብር ባለቤት አቶ ወንድሙን ነው። ወንድዬ፥ እግዚያብሔር አንተን፣ ባለቤትህ ሃናን እና ልጆችህን ይባርክ፡፡ ለቅን ልብህ ባለእዳ ነኝ! ከፋዩ ጌታ እንደሆነ ከመማፀን ጋር!

ሌላው በዚህ ቦታ ላመሰግነው የምፈልገው ወዳጄን ዳዊት ፀጋዬን ነው፡፡ የአርትኦቱን ስራ ጥንቅቅ አድርጎ ሰርቶልኛል፡፡ መጽሐፍ መተርጎምም ይሁን የራስን ወጥ ስራ መስራት ዓላማ ያለው ሰው አርታኢ የሆነ የሚወደው ጓደኛ እግዚያብሔር እንዲሰጠው መፀለይ ነው፡፡ ገጣሚ እና ጋዜጠኛ ዳዊት ፀጋዬ ጓደኛዬ ነው ለማለት እኮራለሁ! ዴቪ  እንደምወድህ አንተ ታውቃለህ!

በመጨረሻም በዚህ ስፍራ ላመሰግነው የምፈልገው አሉላ ጌታሁንን ነው። አሉላ ለእኔ መፅሐፍ ከቨር ብቻ አይደለም የሰራው፤ ከመጀመሪያው ጀምሮ ያዘበራረቅኩትን ነገር ቅርጹን ማስተካከል፣ ፊደላቱን ማረም፣ ቅደም ተከተሉን ማስያዝ፥ ሁሉንም ዓይነት መከራ የጫንኩት በአሉላ ላይ ነው! አመሰግናለሁ! ጓደኛዬ! ስለ ቅንነትህና መሰጠትህ ምስጋናዬን ማቅረብ እፈልጋለሁ! በእኔ ስልቹነት አንተ ባትኖር ይህ ስራ ምን ሊመስል እንደሚችል አልገምትም! አመሰግናለሁ!

“በእውን ምንድን ነው የምፈልገው !ለድርጊቴ አስፈላጊ ካልሆነ በቀር አሁን ማወቅ ያለብኝን ነገር አይደለም የምፈልገው። ማድረግ ያለብኝን ነው ማወቅ የምፈልገው። ፍላጎቴ፣ አላማዬን ማወቅ እና እግዚአብሔር ምን እንዳደርግ እንደሚፈልግ መረዳት ነው። ቁልፉ ጉዳይ፣ የእኔን እውነት መፈለጉ ላይ ነው። ልኖርለት ወይም ልሞትለት የምፈልገውን ሐሳብ ማግኘት ነው።”

***- ሶረን ኪርክጋርድ***

# መጽሐፍ አንድ

## (የጊዜ ሚስጥር)

# 1. ዘለዓለማዊ አሁን

*“አልፋና ኦሜጋመጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ።”*

*ራእይ 21፡6*

እኛ ቋሚ አይደለንም። እኛ የምንኖርበት ዓለም ቋሚ አይደለም። ሁሉ ነገር ቋሚ አይደለም። እኛ እና እኛ በምንኖርበት ዓለም ውስጥ ያለ ነገሩ ሁሉ አንድ ቀን ከመኖር ወደ አለመኖር ይመጣል። እንዲህ እንዲሆን ደግሞ ፍጥረት ካለመኖር ወደ መኖር ከመምጣቱ በፊት የተወሰነ ውሳኔ ነው። እጣ ፈንታ ነው። የሰው ልጅ ሆነ ግዑዙ ዓለም፣ ዛሬ ያየነው ነገር ነገ ከቦታው አይኖርም። ይህ ሂደት የሚያስተላልፈው መልዕክት “ያንተም ጉዞ አንድ ቀን ያበቃል፤ መጨረሻ አለህ” የሚል ነው። አንዳንድ ክስተቶች ደግሞ፣ ሁሉ ነገር ማበቂያ እንዳለው ከሌላው ጊዜ በተለየ እንድናስታውስ የምንገደድባቸው ክስተቶች ናቸው። ለምሳሌ ለረጅም ዘመን ከኖርንበት ቦታ ለቀን ወደ ሌላ ቦታ ስንሄድ፣ ጥብቅ ቁርኝት ከነበረን እና መቼም አንለያይም ብለን ከምናስብበት ጓደኝነት እና ሕብረት ስንቆራረጥ፣ እጅግ የምንወደው እና የምንቀርበው ሰዉ ከእኛ በሞት ሲለይ፤ ለካ ሁሉም ነገር ማብቂያ አለው የሚለው እውነት ወገግ ብሎ ይታየናል። አንዳንዱ ደግሞ ቋሚ የሆነ ነገር እንደሌለ የሚረዳው፣ የደከመበት እና የሮጠለት ህልሙ፣ ከምንም ነገር በላይ አብልጦ የሚሳሳለት ተስፋው እንዳልሆነ ሲሆን ነው። ሌላው ደግሞ ይህንን ድምጽ የሚሰማው ከዕድሜ ነው። እድሜው ሲገፋ እና ጉልበቱ ሲዝል ለካ ሁሉም ነገር “ያበቃል” የሚለው ይገለጥለታል። በመከር ወቅት በሚታየው ነጭናጫ እና ጨፍጋጋ የተፈጥሮ ገጽታ በኩል ሁሉ ነገር በጊዜው ከቦታው እንደማይገኝ የሚያስተውልም ሰው አለ። በአጭሩ ከመኖር ወደአለመኖር የመምጣት ሂደት፤ ለእያንዳንዳችን የሚያስተላልፍልን መልዕክት፤ “አንተም አንድ ቀን ሩጫህ ያበቃል የሚል ነው።”

አንድ ቀን መጨረሻችን እንደሚሆን፤ በማንኛውም ጊዜ ሩጫችን እንደሚያበቃ በሚያስታውሰን ድምጽ በምንናወጥበት ወቅት፣ “በውኑ መጀመርያ እንዳለን እንዲሁ፣ መጨረሻም አለን ማለት ምን ማለት ነው?

ምንድነው መጀመርያ? መጨረሻ ማለት ምንድን ነው? ከመወለዳችን ወይ መኖር ከመጀመራችን በፊት "ካልነበርንበት" ጨለማ መጥተን "ከዚህ በኋላ ወደማንኖርበት"? ጨለማ እንጣደፋለን ማለት ነው?" እያልን የጭንቀት ጥያቄዎችን እናዥጎደጉዳለን። ቅዱስ ኦግሰቲን እነዚህ ጥያቄዎች ቀርበውለት፣ ከእነዚህ ጥያቄዎች ጋራ በአእምሮ ውስጥ ሲታገል ያገኘቸውን መልሶች በፀሎት መልክ ለመመለስ ሞክሯል። እና ደግሞ እንደዚህ ማድረጉ፤ ምን ያህል ጸጋ የበዛለት ሰው እንደነበር ማሳያ ነው። ምክንያቱም ጸሎት ማለት ጊዜአዊ ከሆነው ዓለም ወደ ዘለዓለማዋ ዓለም ጭኖ በሚያሻግር መርከብ ላይ መሳፈር ማለት ነው። ጸሎት ማለት ራስን ወደ ዘላለማዋ ዓለም በሚያሻግር መርከብ አሳፍሮ ወደ ዘላለም መዝለቅ ማለት ነው! ጊዜ ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ መልሱን ማዋቅ የምንችለው ደግሞ "ጊዜን" በዘላለም ብርሀን በኩል ስንመለከት ነው። በዛ ውስጥ ሆንን ካልሆነ በስተቀር በሌላ በማንኛውም መንገድ ልንረዳው አንችልም። አንድ ሰው በአንድ ነገር ላይ ውሳኔ ለመስጠት ወይም ስለነገሩ ለመናገር ብቁ ለመሆን በሆነ ያህል እና መጠን ከዛ ነገር ጋር መቆራኘት፣ የዛ ነገር አካል መሆን አለበት። አንድን ነገር ለመኮነንም ሆነ ለማፅደቅ በከፊል የነገሩ አካል መሆን፤ በከፊል ደግሞ ከነገሩ ውጪ መሆን ግድ ነው። ሙሉ በሙሉ በጊዜ ብቻ የታጠርን ሆነን ቢሆን ኖሮ፣ ወደ ዘላለማዊው ዓለም በመዝለቅ የዘላለማዊ ዓለም አካል ለመሆን አንችልም ነበር። በጸሎት፣ በተመስጦ እና በሐሳብ ወደ ዘላለማዊው ዓለም ተሻገርን እዛ የሚሆነው ነገር ለመከታተል አይቻለንም ነበር። ስለ ዘላለማዊው ዓለም ምንም አይነት ግንዛቤ ልናገኝ አንችልም ነበር። እንደሌሎቹ ፍጥረታት የጊዜ እስረኞች፤ በጸሎት፣ በተመስጦ እና በሐሳብ ወደ ዘላለማዊው ዓለም መጓዝ የማንችል ቢሆን ኖሮ የጊዜ ትርጉም ምንድን ነው ብለን መጠየቅ አንችልም ነበር። ነገር ግን የሰው ልጆች ስለሆንን ቀድሞውንም የዘላለማዊ ዓለም አካል እንደሆንን፣ እውነተኛው ቤታችንም ዘላለማዊ ዓለም እንደሆነ እናውቃለን። ጊዜ ጉሮሮአችን ላይ ሽምቀቆ አስገብቶ፤ ከዘላለም እንደነጠለንም እናውቃለን። በዚህም እኛ የሁለቱም አካል ነን። የጊዜም፤ የዘላለምም።

# 1.

ስለ ጊዜ በምንናገርበት ወቅት ያለፈ ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ እና የወደፊት ጊዜ በሚል በሦስት መንገዶች እንናገራለን። ስለጊዜ ስንናገር በእንደዚህ አይነት ሦስት መንገዶች እንደምንናገር አፋን ያልፈታ ልጅ እንኳን ይገነዘባል፤ ነገር ግን አንድም ጠቢብ ጊዜ በውስጡ የሰወረውን ሚስጥር ዘልቆ መረዳት አልቻለም። ስለ ጊዜ ስንናገር በነዚህ ሦስት የተለያዩ መንገዶች እንደምንናገር ትውስ የሚለን እንኳን "አንድ ቀን መጨረሻህ ይመጣል፣ በምድር የመቆያ ጊዜህም ያበቃል" የሚለውን ድምፅ ስንሰማ ነው። ሌላው ጊዜ ሚስጥር እንደሆነ በውስጡ ውስብስብ ነገሮችን እንዳቀፈ ገብቶን ትኩረት እንድንሰጥ ከእንቅልፋችን የሚቀሰቅሰን የወደፊት ጊዜ (the future) ነው። ጊዜ ከጀመረበት ተነስቶ ወደ ሚያበቃበት ይገሰግሳል። የሚሄደው የፊቱን እያየነው። የእኛ የጊዜ መረዳት ግን በተቃራኒ ነው። ስለ ጊዜ ማሰብ ስንጀምር "መጨረሻዬ ምን ይሆን፣ ሩጫዬ እንዴት ባለ ሁኔታ ይደመደማል፣ ከመንገድ ተሰናክዬ እወድቅ ይሆን ወይ ከሚል ጭንቀት" ፤ ከመጨረሻው እንጀምራለን። ያለፈውን ጊዜ እና የአሁኑን ጊዜ አጥርተን የምንመለከተው፣ የወደፊት ጊዜ በሚሰጠን ብርሃን ውስጥ ነው። እስቲ ስለ ወደፊቱ ጊዜ እና ለመጨረሻችን የምናደርገው አሰሳ ላይ ትኩረታችንን እናድርግ። ሁለት ነገሮች ቅድሚያ ሰጥተን እንመለክት። አንደኛው የወደፊት ጊዜን በተመለከተ ነው። ሁለተኛው በወደፊት ጊዜ ውስጥ ሆነን ምን ሊሆን እንደሚችል ስንብሰለሰልበት ስለነበረው የመጨረሻው ምዕራፍ ነው።

የወደ ፊት ጊዜ (The image of the future) በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ግራ አጋቢ እና እርስ በርሱ የሚቃረን ስሜት ይፈጥራል። በአንድ በኩል አንድ ሰው ስለወደፊቱ ጊዜ ሲያስብ ልቡ በደስታ ሊሰክር ይችላል። ይሆናል ብሎ የሚጠብቃቸው ነገሮች በደስታ ያስፈነጥዙታል። የወደፊት ጊዜን የመሰለ ነገር የለም። አንድ ሰው በምድር ሲኖር በሕይወቱ ሊያከናውናቸው የሚፈልጋቸውን ነገሮች እንደሚያሳካቸው እርግጠኛ የሚሆነው ከፊቱ ነገ የሚባል ተስፋ ስላለ ነው። ዛሬ ያላከናወናቸው ነገሮች ሐዘን እና ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዳይከቱት፤ ነገ የሚባል ቀን ጉልበት ይሆነዋል። የወደፊት ጊዜ እጅግ ታላቅ ነው! የሰው ልጅ ሕይወት ያልያዘውን እንደያዘ ቆጥሮ ትርጉም ባለው መንገድ እንዲኖር ያደረገው የወደፊት ጊዜ ነው! በሰው ሕይወት የወደፊት ጊዜ የሐሴት ምንጭ ነው። አንድ ሰው በነገ ውስጥ፥ ህልሙን ሁሉ ሊያሳካ የሚችልበት እድል አለው። የሰው ልጅ በወደፊት ጊዜ ውስጥ የተበላሸ፣ የፈረሰ እና የማይፈለግ ነገር፤ ለማረም፣ ለማደስ

እና ለማስተካከል ሌላ እድል ያገኛል። አንድ ሰው በወደፊት ጊዜ ውስጥ የተተረፈረፈ ሕይወትን በሕይወቱ መለማመድ ይችላል። አንድ ሰው፥ በነገ ውስጥ አዲስ ነገር መፍጠር ይችላል። ይህ አዲስ ነገር ሥራ ሊሆን ይችላል። ይህ አዲስ ነገር ከአሮጌ አስተሳሰብ እና አኗኗር ወጥቶ አዲስ ሕይወት መኖር ሊሆን ይችላል። ይህ አዲስ ነገር አንድ ሰው ግለሰባዊ እድገት የሚያመጣበት ሊሆን ይችላል። ትላንትና ከያዝናቸው፣ ዛሬ ደግሞ በእጃችን ላይ ካሉ ነገሮች ይልቅ በወደፊት ጊዜ ውስጥ ይሆናል ብለን የምንጠብቀው የሚሰጠን ተስፋና ደስታ በቃላት አይገለጽም። በተለይ በወጣትነት ወቅት የወደፊቱን ለመያዝ ያለው እሩጫ አስደማሚ ነው። በልበ ሙሉነት እና ብርታት ወደፊት እንገሰግሳለን። የወደፊት ጊዜ ሕይወትን በብሩህነት የሚሞላ ታላቅ ነገር ነው!

ነገር ግን በወደፊት ጊዜ ውስጥ ተስፋና ደስታ ብቻ አይደለም ያለው። የወደፊት ጊዜ የያዘውን ተስፋ እና ደስታ የሀዘን ጨርቅ የሚያለብስ፤ ስለነገ ያለንን ተስፋ፣ በነገ ውስጥ ይሆናል ብለን የምናስበውን ነገር እንድንጠራጠር እና እንዳናምን የሚያደርግ ጨፍጋጋ የሆነ መልክም አለው። ይሆናል ብዬ ያልኩት መልካም ነገር ሳይሆን መጥፎ ነገር ቢሆንስ፣ ባልደረስኩበት ነገ ውስጥ በሕይወቴ እንዲሆን የማልፈልገው ነገር ቢከሰትስ? የሚል ጥያቄ ያናውጠናል። ነገ በትክክል ምን ሊሆን እንደሚችል በእርግጠኝነት ማወቅ አለመቻላችን ጭንቀትን ይወልዳል። ስለ ወደፊት ጊዜ ስናስብ በተስፋ እና ደስታ መቦረቅ ብቻ ሳይሆን ከጭንቀትም ጋር እንታገላለን። ወደፊት እንይዘዋለን ያልነው ነገር እየዘገየ፤ በወደፊት ውስጥ ቶሎ ይደርሳል ያልነው ነገር እየራቀ በሄደ ቁጥር፣ ስለ ወደፊቱ ያለን ደስታ አብሮ እየደበዘዘ ይሄዳል። ሌላው የወደፊት ጊዜ ብዙ አይደለም። አጭር ነው። ዕድሜያችን እየጨመረ ሲሄድ፤ አለን ብለን የምንለው የወደፊት ጊዜ ርዝመቱ እየቀነሰ ይሄዳል። ወደ እድሜያችን መጨረሻ ስንደርስ ደግሞ የማይቀረው እርጅና ከተስፋችን እና ከምንጠብቀው ነገር ፈጥኖ ሲመጣ፤ አለን ብለን የምንለው “የወደፊት ጊዜ” አንድ ጉርሻ እንኳን አይሆንም። የወደፊት ጊዜ ባንድ እጁ ተስፋ እና ደስታ እንደያዘ በሌላ እጁ ደግሞ ሥጋትና ጭንቀት ተሸክሟል። በመጨረሻም ከተሸከመው እጅግ አስፈሪ ከሆነ ጨለማ ጋር፣ ምናልባትም የሕይወት ዘመናችን እሩጫ በሚዛን ሲመዘን በኪሳራ ፍርድ ውስጥ የሚወድቅበት፣ ዳግም ሌላ ነገር ለመሆን ሌላ እድል የማናገኝበት፤ ፍጻሜያችን ፈጥኖ ከች ይላል። በእያንዳንዱ ቀን ነገ የሚባል ቀን ብቻ ሳይሆን ያለን፤ በእያንዳንዱ ቀን የነጋችን እድሜ እየጠረ ይሄዳል። በወደፊት ጊዜ ውስጥ ተስፋ ብቻ ሳይሆን ተስፋ ማጣት አለ። በወደፊት ጊዜ ውስጥ ነገ በሕይወታችን ስለሚሆነው መልካም ነገር እያሰብን ሐሴት ማድረግ

ብቻ ሳይሆን፤ ነገ በሕይወታችን ውስጥ ላይሆን ስለሚችለው መልካም ነገር እያሰብን መጨነቅም አለ። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ የወደፊቱ ጊዜ መልክ በተዘበራረቀ ገጽታ የተሞላ ነው።

የወደፊት ጊዜ በውስጡ ማንም የማያመልጥበትን የፍጻሜ ቀን ይዟል፤ በወደፊት ጊዜ ውስጥ ተስፋ እና ሥጋት ተቀምጧል። ከዚህ በመነሣት ሰዎች ስለወደፊት ጊዜ ያላቸው ምላሽ እና አመለካከት ምንድነው? የወደፊት ጊዜ በውስጡ ለያዛቸው ነገሮች እንዴት ነው ምላሽ የምንሰጠው? ብዘዎቻችን ስለወደፊቱ ጊዜ ያለን ምላሽ፤ ወይም የወደፊት ጊዜ ስንል የሆነ አንዳች ነገር ለማግኘት በጉጉት እየተጠባበቅን፣ ልንይዘው እየሰራን፣ ተስፋ እያደረግን እና፣ እየተጨነቅንበት ስላለ ቀን ማለታችን ነው። ሁላችንም በሚባል መልኩ የወደፊት ጊዜ ምንድነው ለሚለው ጥያቄ፤ ወይም የወደፊት ጊዜ ሲባል በአዕምሮአችን ላይ የሚከሰተው ምስል ያልያዝነውን የምንይዝበት፣ ያልደረስንበት ቦታ የምንደርስበት፣ ያላገኘነውን የምናገኝበት በቅርብ እርቀት ያለ ቀን ማለት ነው። ይህን በምናደርግበት ጊዜ፥ እጅግ ሩቅ ስለሆነው የወደፊት ጊዜ ከማሰብ ራሳችንን እንገድባለን። ያልደረስንበት ቦታ ስለምንደርስበት፣ ያላገኘነውን ስለምናገኝበት የወደፊቱ ጊዜ የምናስበውን ያህል፤ እኛው ራሳችን የምናበቃበትን "የወደፊት ጊዜ" ላለማየት አይናችንን እንሸፍናለን። "በጊዜ" ውስጥ ለነበረን ሩጫ መደምደሚያ ስለሆነው ቀን፥ የወደፊቱ ጊዜያችን ማብቂያ ወቅት "ማሰብን" ከንቃተ ኅሊናችን ቆርጠን እናወጣዋለን። ምናልባት እስትንፋሳችን ስለሚቆምበት ቀን ማሰብ ካላቆምን በስተቀር ባለን ቀሪ ጊዜ "መኖር" አንችል ይሆናል። እንደዚያ ካላደረግን የኅሊና እረፍት ማግኘት አንችል ይሆናል። ስለዚህም ነገ ሟች ነኝ የሚለው ሃሳብ በእለት እለት ኑሮአችን ላይ መጥፎ ጥላ ስለሚያጠላ፣ ሁል ጊዜ ነዋሪ እንደሆነ ሰው፣ ስለ ወደፊቱ ጊዜ ስናስብ በወደፊት ጊዜ ውስጥ ስለምንደርስበት እና ስለምንጨብጠው ነገር ብቻ እናስባለን። ለመኖር ማድረግ ካሉብን ነገሮች መካከል አንዱ የምድር ቆይታችን የሚያበቃበትን ቀን ማሰብ ማቆም ነው። በዚህም ምክንያት "ሩጫችን ስለሚደመደምበት ቀን" አናስብም። ነገር ግን ሁልጊዜ ሞትን በመፍራት፣ የምድር እርምጃችን የሚቆምበትን ቀን ባለ ማሰብ መኖር፣ የመኖርን ትርጉም እንዳንረዳ ጋሬጣ ይሆናል። ስለ ፍጻሜያችን ለማሰብና ለማሰላሰል ፍቃደኞች ካልሆንን የሕይወትን ከፍታና ዝቅታ፣ ጣዕም እና ምሬት በተገቢው መንገድ ቀምሰን፣ መጋፈጥ ያለብንን ተጋፍጠን መኖር የሚገባንን ሳንኖር እንቀራለን። ሰው ደግሞ ሕይወትን መኖር ያለበትን ያህል ካልኖረ፤ በቁሙ ሞቶ ነበር ይባላል እንጂ ሌላ ምን ትርጉም አለው?

በወደፊታችን አንድ ቀን ውስጥ የተሰወረ፣ ይህች ፀበል ከእኔ ትለፍ ልንለው የማንችለው፤ እስትንፋሳችን የሚቋረጥበትን "ቀን" ማወቅ ብንችል ምላሻችን ምን ይሆን ነበር? እንሸከመዋለን!? እግሮቻችን ሳይናወጡ መቆም ይችላሉ? የሞታችንን ቀን ማወቅ ውስጥ ያለውን ጭንቀት እና ድንጋጤ፣ ከጨለማም የከፋውን ጨለማ ወደሚጋፈጥ ብርታት ለውጠን በሞት ፊት፣ በቀናችን መጨረሻ ፊት መቆም እንችላለን? ወይስ ያችን ቀን ያወቅን ሰዓት ወደ ተስፋቢሥነት ባሕር ውስጥ ራሳችንን እንወረውራለን? ወይስ ተስፋ በሌለው ነገር ላይ ተስፋ እናደርጋለን? ወይስ ደግሞ ትከሻችን ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሆነ ነገር በመሆኑ "እስትንፋሳችን ስለሚቆምበት ቀን" ያገኘነውን እውቀት አዕምሮአችን ሊያስታውስ ወደማይችልበት መቃብር ወስደን እንቀብረዋለን? ስለ መጨረሻችን፣ ያለውን ሐቅ ለመርሳት መሞከር ራሱን በተለያዩ መንገዶች ይገልጣል።

ብዙ ሰዎች ከዚህ ምድር የሚሰናበቱበት ቀን እንደሚመጣ ቢያስታውሱም ግን ያ ቀን በጣም ሩቅ ነው። ምድርን ጠግበው ሲበቃቸው ማድረግ የሚፈልጉትን ሁሉ አድርገው፣ ማሳካት የሚፈልጉትን ሁሉ አሳክተው ሲጨርሱ የሚመጣ ነገር ነው። በዛሬ እና በመጨረሻ ቀን መካከል የሚያጓጓ እና የሚያረጋጋ ረጅም እድሜ አለ። እናም የመጨረሻው መዘግየቱ፣ ገና ምን "አይቼ መሆኑ" እጅግ ወሳኝ ነው። በእድሜ የገፉ እና በምድር ቆይታቸው መጨረሻ ላይ የሚገኙ ሰዎች እንኳን ቢሆኑ የሚያስቡት እንደዚህ ነው። ለሰው ሁሉ ያለምንም ልዩነት የሚሞትበት ቀን ረጅም ነው። ገና ነው። ምክንያቱ ደግሞ የመጨረሻው ደቂቃ ብዙ የሚዘገይ አይደለም የሚለውን እውነት መሸከም ስለማይችሉ ነው።

ብዙ ሰዎች ደግሞ በዚህ መንገድ "የሞትን ቀን" ሃሳብ ለማምለጥ መሞከር ራስን ማታለል መሆኑን ፈጥነው ይገነዘባሉ። ስለዚህ አሁን አልሞትም ብዙ ቀን አለኝ በሚለው ተስፋ ከመረጋጋት ይልቅ ከሞት በኋላ ሕይወት እንደሚቀጥል ተስፋ ያደርጋሉ። ከሞት በኋላ ሕይወት ይቀጥላል በሚል እምነት ውስጥ ይሸሸጋሉ። በምድር ሲኖሩ የተነፈጉትን ነገር ሁሉ የሚያገኙበት ወይም የሚያሳኩበት መቋጫ እና ማብቂያ የሌለው፣ ሰላምና እረፍት የሞላበት ዘላለማዊ ቀን እንዳለ እርግጠኞች ናቸው። የወደፊት ጊዜን በተመለከተ ያለው ገዢ ሃሳብ ይህ ነው። ውስብስብ ስላልሆነ ለሚሰማዉ ደስ የሚል ለመቀበል የሚቀል ሃሳብ ነው። ነገር ግን ይህ አስተሳሰብ የሰው ልጅ መጨረሻ አለው የሚለውን ሃሳብ ይክዳል። የሰው ልጅ መጨረሻ አለው ስንል በምድርም ይሁን ከዚ ውጪ፣ በሆነ ቀን ካለመኖር ወደ መኖር እንደ መጣ፤ በሆነ ሌላ ቀን ደግሞ ከመኖር ወደ

አለመኖር ይመጣል። ዘላለማዊ ማንነት የለውም። ከሞት በኋላ የሚቀጥል ሌላ ሕይወት አለ የሚለው አስተሳሰብ ይህን መሠረታዊ ኩነት የሚክድ ነው። ሰው መጨረሻ እንዳለው ይክዳል። ይህ አመለካከት ፍጡር መሆናችንን፣ ጊዜን ካበጀው ወጥተን እንደመጣን እንዲሁ ጊዜን ወደ አበጀው እንደምንመለስ አይቀበልም። በዘላለም ውስጥ ጊዜ የሚባል ነገር እንዲኖር ያበጀው እርሱ፤ በሰዓት፣ በቀን እና በዓመታት ተቆጥሮ የሚያልቅ ቀንን ደግሞ የኛ ጊዜ እንዲሆን እንደሰጠን አይቀበልም። ከሞት በኋላ ሕይወት ይቀጥላል የሚለው አስተሳሰብ፤ ዘላለምን ተቆጥሮ በማያልቅ ቀን ይተካል።

ነገር ግን ሰዓቱ፣ ቀኑና አመታቱ የማያልቅ የወደፊት ጊዜ አለ ማለት ትርጉም አልባ፣ መዳረሻ አላማ የሌለዉ ነገር ነው። ዝም ብሎ መቀጠል ብቻ። ራሱን ዝም ብሎ የሚደጋገግም ነገር። ይህ የሚጨንቅ የሲኦል መልክ ነው። ክርስትና ፍጻሜን በተመለከተ ያለውን ጉዳይ ለመፍታት የሚሞክርበት መንገድ ይህ አይደለም። ክርስትና ይህንን አያስተምርም። ክርስትና ዘላለም ካለፈው ጊዜና ከወደፊት ጊዜ ውጭ ሆኖ ያለ ነገር ነው ብሎ ያስተምራል። “አልፋና ኦሜጋ መጀመሪያውና መጨረሻው እኔ ነኝ”

ክርስትና “ጊዜ” ከመነሻ ቦታ ወደ መደምደሚያ እንደሚሮጥ እውቅና ይሰጣል። እናም እኛም ወደዚያ መጨረሻ እንደምንሄድ ያስተምራል። ለእኛ የተሰጠን ቀን ደግሞ ስንወለድ ጀምሮ ከሞት በኋላ የሆነ ቦታ የሚቀጥል ሳይሆን “የሆነ ቀን ጀምሮ የሆነ ቀን ላይ የሚያበቃ” እንደሆነ ያስተምራል። እኛ እንድንኖርበት የተሰጠን ቀን ማብቂያ፣ ፍጻሜ አለው ማለት ነው። ብዙ ሰዎች “ከዚህ በኋላ ስለለው ሕይወት” ወይም “ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት” በተሳሳተ መንገድ ሲናገሩ ይደመጣል። መጽሐፍ ቅዱስ ከዚህ በኋላ ሰላለ ሕይወት ወይም ከሞት በኋላ ስላለ ሕይወት አልተናገረም። በቅዳሴአችን እንኳን ዘላለማዊነት “ማብቂያ የሌለው ዓለም” ተብሎ ተተርጉሟል። ዓለም ግን ገና ከፍጥረቱ፥ ማብቂየ እና መደምደሚያ ያለው ነገር ነው። ያለ ሞኛሞኝነት እና ህልም አለኝ በሰማይ አስተሳሰብ፥ እውነታውን መናገር የምንፈልግ ከሆነ ስለ ዘላለም ሰናወራ ከቁጥር እና ከቀናት ብዛት ጋር አያይዘን መናገር የለብንም። ምክንያቱም ዘላለም ማለት የማይቆጠር ቀን ማለትም አይደለም። ወይም ደግሞ ቁጥሩ እንደ ሰማይ ከዋክብት እንደ ሞድር አሸዋ የበዛ የሰው ልጅ ቆጥሮ የማይደርስበት ብዙ ቀን ማለት አይደለም። ስለዘላለም ስናስብ ከዚህ ምልከታ መውጣት አለብን። የወደፊት ጊዜ ሚስጥር መልስ የሚያገኘው በዘላለም ውስጥ ብቻ ነው። ምናልባት

ስለዘላለም ስንናገር የጊዜን ምስል እንደምሳሌ ወስደን ልንናገር እንችላለን። ነገር ግን ጊዜን የወሰድነው ስለዘላለም የሆነ ፍንጭ ለማግኘት፣ እንደ ምሳሌ እንጂ ዘላለም ማለት “ጊዜ ነው” ማለታችን እንዳልሆነ ከረሳን፤ ራስን በራስ የማታለል እና ቀጥ¨አምባሩ የጠፋ አመለካከት ውስጥ እንወድቃለን። ከጊዜ በኋላ ሌላ ጊዜ የለም! በጊዜ ውስንነት ውስጥ እንድንኖር የተፈቀደልን ሕይወት ካበቃ በኋላ፤ የሚቀጥል ሌላ ሕይወት የለንም። ነገር ግን ከጊዜ ውጪ የሆነ ዘላለማዊነት አለ።

# 2

“አሁን ወደሌለ” ነገር ግን በወደፊት ጊዜ ውስጥ ወደ ምንደርስበት አንዳች ነገር እንገሰግሳለን። እና ደግሞ “ከዚህ በኋላ ከማይኖር”፣ ተመልሰን ወደ ኋላ ሄደን ከማንደግመው፣ አንዳች ነገር ወጥተን መጥተናል። አሁን “እኛ” የሆነውን የሆነው እኛነታችንን ካገኘንበት ማንነት የተነሳ ነው። መጨረሻ እንዳለን እንዲሁ፥ እኛነታችን የጀመረበት “ቀንም” ነበር። ሌላው ደግሞ የእኛ ያልነበረ ወይንም እኛ ያልነበርንበት ጊዜ ነበር። የእኛ ያልነበረ ወይም ደግሞ እኛ ስላልነበርንበት ጊዜ በዕድሜ ከገፉ ሰዎች ሰምተናል። ከታሪክ መጽሐፍት አንብበናል። ሌላው ደግሞ ምንም ነገር ከመጀመሩ በፊት የነበረ ጊዜ ነበር። የአሁንና የወደፊት ጊዜን በመተው፣ እኛ ያልነበርንበትን እና ምንም ነገር ከመጀመሩ በፊት የነበረን ጊዜ ወደ ኋላ ሄደን ቀኖቹን በምናባችን እንቆጥራለን። እኛም ሆንን ሌላ ሰው ስለነዚህ ወደኋላ ስለነበሩ አመታት ምን ይመስሉ እንደነበር ማንም ሊናገር አይችልም። ግን እንዲሁ ዝም ብለን፣ ሁሉ ነገር ከመጀመሩ በፊት የነበሩ፣ ለቀናቸው ፍጻሜ የሌላቸውን በቢሊዮን የሚቆጠሩ አመታትን ወደኋላ ሄደን በመቁጠር በምናባችን እናያቸዋለን። በትላንትና ውስጥ ስፍር ቁጥር ያልነበራቸው አመታት ነበሩ ብለን በምናባችን ወደኋላ እንሄዳለን። በርግጥ “ልንገኝ የማንችልበት”ን፣ ያልነበርንበት ጊዜ፤ ምን ሊመስል ይችላል ብለን በምናባችን ማውጣትና ማውረድ ይከብደናል። ልክ እንዲሁ በወደፊት ጊዜ ውስጥ የሆነ ቀን ላይ “ስለምንገኝበት ቀን” በምናባችን ማውጣትና ማውረድ አስቸጋሪ ነው። ነገር ግን ብዙ ጊዜ “ሰዎች ስላልነበርንበት” ወይንም “ስላልተፈጠርንበት”፣ ከመወለዳችን በፊት ስለነበረ ስፍር ቁጥር ስላልነበረው ጊዜ ብዙ ግድ አይሰጠንም። ብዙውን ጊዜ ከመወለዳችን በፊት የነበረው ነገር አያስጨንቀንም። አስተሳሰባችን የተዋቀረው እንዲህ ነው፦ አሁን እና ዛሬ በሕይወት አለን። ይሄ የእኛ ጊዜ ነው። “የእኛን” ጊዜ ማጣት አንፈልግም፤ መኖር አለብን ! በሚል ነው። ብዙውን ጊዜ፥ ከመወለዳችን በፊት “ምን ነበርን?” ብለን አንጠይቅም። በዋናነት የምንጠይቀው፥ ከሞት በኋላ ስላለው ሕይወት ነው። ነገር ግን ስለመጀመሪያችን ሳንጠይቅ እና ሳናውቅ፣ ስለመጨረሻችን መጠየቅና ማወቅ ይቻላል ወይ? አራተኛው ወንጌል የሚቻል አይደለም ይለናል። ስለ ክርስቶስ ዘላለማዊነት ሲናገር፣ ወደ ዘላለማዊነቱ እንደሚመለስ ብቻ ሳይሆን፤ ከዘላለም ወጥቶ እንደመጣም ሲናገር “እውነት እላችኋለሁ፥ አብርሃም ሳይወለድ እኔ አለሁ” ይላል። ያለፈ ጊዜ ካረፈበት ወይም እኛ ትላንትና የምንለው ጊዜ ከሚገኝበት ውጪ ካለ የጊዜ አቅጣጫ መጥቷል። የእኛ የጊዜ እሳቤ ከሌለበት ዓለም ወጥቶ ያለፈ ጊዜ፣ የአሁን ጊዜ፣ እና የወደፊት ጊዜ ማዕቀፍ ወደሚገኝበት ወደ እኛ ዓለም

መጥቷል ማለት ነው። እርሱ (ክርስቶስ) እኔ አብርሃም ሳይወለድ በፊት ነበርኩ ሲል ይሰሙት የነበሩት ሰዎች በታሪክ ውስጥ ስለሚገኝ ትላንት እየተናገረ መስሎአቸው በትክክል ሳይረዱት ቀርተዋል። ራሱን አብርሃም ከመወለዱ በፊት ጀምሮ እስካሁን ድረስ የነበረ በእድሜ የገፋ ብዙ መቶ ዓመታት  የኖረ ሰው ነኝ ብሏል ብለው አመኑ። ይህ ሰው አእምሮው በሽተኛ ነው እንዴ በሚል ራሳቸውን ብስጭት ውስጥ ከተቱ። ይሄ ሰውዬ ጤነኛ ነው እንዴ አስብሏቸል። እርሱ ግን ከአብርሃም በፊት "ነበርኩ" (I was) አይልም፤ ይልቁንም አብርሃም ከመፈጠሩ በፊት "አለሁ" (I am) ነው ያለው። እርሱ ይናገር የነበረው ከዘላለም ጊዜ ውጪ "ራሱ" ስለነበረው ጅማሬ ነው። ይህ የጊዜ ስሌት ደግሞ "ካለመኖር ወደ መኖር የመጣው ነገር ሁሉ" የጀመረበት ነው። ይህ ጅማሬ እንደ ሰማይ ከዋክብት እና እንደ ምድር አሸዋ ተቆጥሮ የማይደረስበት ቢሊዮን ዓመታት አይደለም ነገር ግን በዘላለም ውስጥ የእኛ ትላንትና የጀመረበት የመጀመሪያው ሰከንድ ነው።

የትላንትና ጊዜ ምስጢር ያለው በሁለት ነገሮች ውስጥ ነው። የእኛ የትላንትና ጊዜ ውስጥ ሁለት ቁልፍ ነገር አለ። የመጀመሪያው በእያንዳንዱ ቀን በምናሳልፈው ሕይወት ውስጥ "ያለፈው ጊዜ" አብሮን አለመሆኑ ነው። ሁለተኛው ደግሞ በእያንዳንዱ ቀን በምናሳለፈው ሕይወት ውስጥ 'ያለፈው ጊዜ' አብሮን መሆኑ ነው። የእኛ "ያለፈው ጊዜ" ዛሬም ከእኛ ጋር ነው። በተመሳሳይ መንገድ ደግሞ የእኛ "ያለፈ ጊዜ" ዛሬ ከእኛ ጋር አይደለም። የእኛ ያለፈው ጊዜ ዛሬ ከኛ ጋር ነው ስንል የዛሬ እኛነታችን ተሰርቶ የተጠናቀቀው በትላትናችን ነው። እኛ አሁን "ዛሬ" የሆነውን የሆነው ትላንትናችን "እንድንሆን ባደረገን"፣ በሰራን መጠን ነው። በእያንዳንዱ የሰውነታችን ሕዋስ ውስጥ፥ በፊታችን ገፅታ ላይ በሚታየው ባሕርያችን፥ በእያንዳንዱ የነፍሳችን እንቅስቃሴ፥ "ያለፈው ጊዜያችን"፥ ዛሬ በምንኖረው "የአሁን ጊዜ ውስጥ"፥ ግልፅ ሆኖ ይታያል። በዚህ መንገድ "ትላንትናችን" (our past) "ዛሬያችን"

(Our present) ውስጥ አለ።

አንዳንድ ወቅቶች፣ በታሪክ ውስጥ የሚከሰቱ አንዳንድ የዘመን ምዕራፎች፣ ያለፈው ዘመን "ትላንትና፣ ያለፈ የምንለው ነገር" በዛሬ ውስጥ ያለሚቋረጥ እንደሚሰራ ምስክር ናቸው። ያለፈው ጊዜ በዛሬ ላይ ያለውን ተጽዕኖ ከእኛ ይልቅ በደንብ ያውቃሉ። በልጅነት ያሳለፍነው የሕይወት ልምምድ፣ እና አስተዳደግ በባሕርያችን ላይ ያለውን ተጽእኖ እናውቃለን። በእድሜያችን በመጀመሪያዎቹ ዓመታት የተከሰቱ ክስተቶች ጥለውት የሄዱትን ጠባሳ እናውቃለን። አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ጥንት ለግሪክ የሰቆቃ ወግ ፀሃፊዎች (Greek tragedians) እና

ለአይሁድ ነብያት ሚስጥር ያልነበሩ ነገሮችን እንደ አዲስ ከተቀበረበት አውጥተን አውቀናል። ትላንትና እነርሱ ያውቁት የነበረ ዛሬ እኛ እንደ አዲስ ያወቅነው ነገር፤ ያለፈው ጊዜ በዛሬያችን ውስጥ እንደሚሰራ ነው። ያለፈው ጊዜ በረከቱንም መርገሙንም ይዞ በዛሬያችን ውስጥ ህያው ነው። ሁልጊዜ ትላንትና ስንል በረከትንም መርገምንም የተሸከመ ቀን ማለታችን ነው። ይህ ያለፈ ጊዜ በረከትና መርገም ለግለሰቦች ብቻ አይደለም ከሀገርም አልፎ ተርፎም ለአህጉር የሚሆን ነው።

ታሪክ ካለፈው ጊዜ፣ ከቅርሶቻችን የተገኘ ሕያው ነገር ነው። የዛሬን ሁኔታ እና የነገን አካሄድ ይወስናል። የአውሮጳ ሐገሮች ክብር፥ ረጅም ዘመን የዘለቀው፣ ተዘልቆ የማያልቀው የበለፀገ ባሕላቸው ነው። ነገር ግን የዚህ ባህል በረከት የተነጣጠሉ እና ራሳቸውን የቻሉ አገሮች ለመሆን ባደረጉት የእርስ በርስ ጦርነት ካመጣው እርግማን ጋራ የተደባለቀ ናቸው። እነዚህ ደም አፋሳሽ ትግሎች ከአንድ ክፍለ ዘመን ወደ ወደሌላ ክፍለ ዘመን የተሻገሩ እና ብዙ ጊዜ አውሮፓን ራሷን በራሷ የማጥፋት ጠርዝ ጋ ያደረሱ ነበሩ። አሜሪካንን እንመልከት! አጭር በሆነው የሀገርነት ታሪኳ ውስጥ የተቀበለችው በረከት ቃላት የማይገልጡት፤ እንዴት ታላቅ ነው! ነገር ግን፥ ገና እንደ ሐገር ከቆመችበት ቀን አንስቶ እስካሁን እና ወደፊት ለሚመጣ ብዙ አመታት የሚቆይ የእርግማን የታሪክ ቁጥቋጦ በሥራ ላይ ነበር። እና እነዚህ ነገሮች ለብዙ አመታት እርግማን ሆነው ይቆያሉ። ለምሳሌ፥ በሐገሪቷ ውስጥ ብቻ ሳይሆን፥ ከራሷ ድንበር ውጭ ካሉ ሕዝቦች እና ሐገሮች ጋር በምታደርገው ግንኙነት፥ ከዘር እና ዘረኝነት ጋር በተገናኘ ያለውን ጉዳይ መጥቀስ እችላለሁ። “የአሜሪካውያን የአኗኗር ዘይቤ” ከትላንትናችን የመጣ፣ ያገኘነው በረከት ነው። ነገር ግን የወደፊት ጊዜአችንን ሥጋት ላይ የሚጥል እርግማንም ነው። በወደፊት ጊዜያችን ላይ አደጋ እንደደቀነም ይቆያል።

የሀገሮችን እና የአህጉራትን ህልውና፣ በተለይ ደግሞ ከሁሉም ነገር በላይ በአጠቃላይ የሰውን ልጅ ህልውና አደጋ ላይ የሚጥለውን የትላንትን እርግማን ማስወገጃ መንገድ አለ? ከባለፈው ጊዜ ተንከባለው የመጡ ነገሮች በዛሬ ያችን ላይ ያላቸውን አቅም እንዲያጡ፣ ለኣንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ጠቅልለን በነገ ማህደር ውስጥ ማስቀመጥ እንችል ይሆን? እንደግለሰብ ያለፈው ጊዜ በዛሬ ላይ አቅም እንዳይኖረው ማድረግ ይቻላል። አንድ ሰው በትክክል እንዳስቀመጠው የአንድ ግለሰብ የባሕሪ ጥንካሬ የሚወሰነው፣ ጠንካራ ሰብእና ተላብሷል ወይም አልተላበሰም ብለን ለመናገር የምንችለው፣ የ ግለሰብ በነገ ማህደር ውስጥ

መከተት ያለባቸውን ጉዳዮች ምን ያህሉን ትላንትና ውስጥ ከቶ ወደፊት እየሄደ ነው በሚለው ነው። የአንድ ግለሰብ “ትላንትና”፥ “ዛሬም” ያን ግለሰብ አንቆ ለመያዝ ኋይል እንዳለው የማንክደው ሀቅ ቢሆንም፥ ነገር ግን ያ ግለሰብ ራሱን “ከትላንትናው” መለየት ይችላል። ካለፈው ጊዜ ተጽዕኖ መላቀቅ ይችላል። ስሆነ ያህል ጊዜ ያህል እንኳን ቢሆን፤ “ትላንትናውን” ከዛሬው ላይ ጎትቶ በማንሳት፥ ወደ “ትላንት ማህደር “መወርወር ይችላል። እንደዛም በማድረግ ያለፈው ጊዜ በዛሬ ላይ እንዳይሠራ ባለበት ማስቀረት ይቻላል። ’ከዛሬያችን” ላይ አንስተን “ወደትላንት” የወረወርናቸው ነገሮች፥ ተመልሰው ሊመጡ እና “ዛሬያችንን” ድል ሊነሱት፣ ሊቆጣጠሩት ይችላሉ። ነገር ግን ይሄ ሁሌ ከመሆን የማይቀር የግድ የሆነ ነገር አይደለም። ማምለጥ፣ ማለፍ እና መሻገር በማይቻል መልኩ፥ ያለፈው ሕይወታችን ሰለባዎች አይደለንም። ያለፈውን፥ እንዳለፈ ነገር ብቻ ሆኖ እንዲቀር ማድረግ እንችላለን። እውነተኛ ንስሀ ማለት ስለተሳሳትነው ነገር፣ ስለአጠፋነው ጥፋት፣ እና ስለአደረግነው መጥፎ ተግባር እንባ አውጥቶ ማልቀስ፥ በሐዘን መቆራመድ ማለት አይደለም። ነገር ግን ያለፈው ጊዜ “ትላንትና”፣ ከዚህ ወዲህ “በእኛ ዛሬ ላይ” ምንም ዓይነት ተጽኖ እና ሀይል እንዳይኖረው አድርጎ ወደ አለፈው ጊዜ ለመወርወር የነፍስ፣ የሥጋ እና የመንፈሳችንን ሁለንተናዊ ተሳትፎ ያካተተ ድርጊት ነው። ንስሃ ማለት የአለፈው ጊዜ ቅሪቶችን ከእኛነታችን ላይ ለመነጠል በሙሉ ሀይላችን የምንፈጽመው ከትላንት የመላቀቅ ድርጊት ነው።

ልክ እንደ ግለሰብ ሁሉ አንድ ህዝብ ከትላንትናው እርግማን ለመላቀቅ ተመሳሳይ ነገር ማድረግ ይችላል? አንድ ሕዝብ ወይም ማንኛውም ማኅበራዊ ቡድን እውነተኛ ንስሐ መግባት ይችላል? ካለፈው እርግማን ራሱን መለየት ይችላል? የአንድ ሐገር ተስፋ የረፈው ከትላንት እርግማን ለመላቀቅ በመቻል እና ባለመቻል ውስጥ ባሉ ዕድሎች ላይ ነው። የእሥራኤልና የቤተ ክርስቲያን ታሪክ ይህንን ጉዳይ በተመለከተ ሁለት ነገሮችን ያስተምረናል። አንደኛው ከእሥራኤል እና ከቤተ ክርስቲያን ታሪክ እንደምናየው ከትላንትና እርግማን በንስሃ መላቀቅ ይቻላል። ሌላኛው ግን ከትላንትና እርግማን በንስሃ የመላቀቅ ድርጊት ብዙጊዜ የመከሰት ዕድሉ ጠባብ እንደሆነ እና ያንን ማድረግም በቃላት መግለጽ ከሚቻለው በላይ ከባድ መሆኑን ነው። ለአንድ ህዝብ ከትላንትና እርግማን በንስሃ ለመላቀቅ በመሞከሩ ውስጥ ያለውን ጥልቅ ህመም ለመሸከም ከባድ ይሆንበታል። የአሜሪካም ሕዝብ እንደ ቤተ ክርስቲያን እና እሥራኤል ንስሐ የሚገባ፥ ይሁን አይሁን ማንም አያውቅም። ነገር ግን የዚህ ሕዝብ የወደፊት እጣፈንታ፥ ያለፈውን የታሪክ ጠባሳ እንዴት ይታከማል በሚለው እና ካለፈ ታሪክ ወደዛሬ የመጡ

እርግማን የሆኑ ቅሪቶችን ነቅሎ በመጣል ላይ የተመሠረተ እንደሆነ እናውቃለን፡፡

ካለፈው ጊዜ ጋር በተገናኘ በእያንዳንዱ የሰው ልጆች ሕይወት ውስጥ ያለው ትግል እንደቀጠለ ነው፡፡ ባለፈው ጊዜ ምክንያት በረከት እና እርግማን ትግል እንደገጠሙ ናቸው፡፡ አሁን እኛ ባለንበት ዘመን፣ ባልነቃው የአዕምሮአችን ጓዳ (unconscious strivings) ስላሉ ፍለጋዎቻችን የስነ-ልቦና ሳይንስ የደረሰበትን እድገት መሠረት አድርገን ስለምንመለከት፣ ባለፈው ጊዜያችን ውስጥ ከበረከት ይልቅ እርግማኑ የበዛ እንደሆነ የማየት ዝንባሌ አዳብረናል፡፡ በልጅነታችን ወቅት ከወላጆቻችን ጋር ስለ ነበሩን ጊዜያቶች፣ ስለአለን ትዝታ ስንናገር ብዙ ጊዜ ስላሳደረቡን የልጅነት መጥፎ ተፅዕኖ፥ አስበው ባላደረጉት እና ከፍቃዳቸው ውጪ በእኛ ላይ ካስቀመጡት እርግማን (የልተጋባ ባሕሪ እና ድርጊት) ጋር ብቻ የተያያዘ ነው፡፡ በብሉይ ኪዳን የወላጆች ትዝታ ከበረከት ጋር እንዳይነጣጠል ሆኖ የተጋመደ ነበር፡፡ ልጆች በየትኛውም ዓይነት በረከት ይባረኩ፤ ምክንያቱ ወላጆቻቸው እንደሆኑ ያምኑ ነበር፡፡ ስለወላጆቻችን ያለን ትውስታ፥ “ወላጆቼ እንዲህ እና እንዲያ ሲያደርጉኝ ስለነበር፥ የእርሱ ቀጥታ ውጤት በሕይወቴ ላይ ይህን አመጣ እናም ልቀይረው የምችለው ወይም በቀላሉ የሚተወኝ አይደለም” ከሚል አስተያየት ጋር የታጀበ ነው፡፡ ብዙዎቹ በአእምሮ ህመም የሚሰቃዩ ሰዎች፥ ያለፈ ሕይወታቸውን በተለይም የልጅነት ጊዜያቸውን እንደ እርግማን ብቻ ነው የሚያዩት፡፡ እውነት ነው ብዙ ጊዜ ብዙዎች የሚሰቃዩት ከወላጆች በተላለፈ መጥፎ ነገር ነው፡፡ ነገር ግን አንድ ነገር መርሳት የለብንም፣ እርሱም ይህ ሁሉ መጥፎ ነገር ከወላጆቼ የመጣብኝ ነው፣ ከእነሱ የወረስኩት ክፉ ነገር ነው ሕይወቴን ያመሳቀለው ብለን ስንናገር፤ ምንም አይነት በረከት ከእነርሱ ዘንድ መጥቶ ባይሆን ኖሮ ዛሬን ልመኖር እና ነገን ለመጋፈጥ አንችልም ነበር፡፡ ከእነርሱ እርግማን ነው የወረስኩት ከምንለው ከወላጆቻችን የመጣ በረከት ባይኖር ኖሮ፥ አሁን መኖር እና ነጋችንን በጥቂቱም ይሁን በብዙ መጋፈጥ አንችልም ነበር፡፡

በዚህ ዘመን ብዙ ወንዶችና ሴቶች ልጆች “ባለፈው ጊዜ” ውስጥ በሕይወታቸው በሆነ ነገር ምክንያት ያለምንም እረፍት ፍሬ የማያፈራ ከንቱ ልፋት፣ ከንቱ ትግል እያደረጉ ይገኛሉ፡፡ ይህንን ግጭት ሃኪም ሊፈታው ሊያድነው አይችልም፡፡ ምክንያቱም የትኛውም ህክምና የሚሰጠው መድሀኒት ያለፈውን ጊዜ ሊለውጥ አይችልም፡፡ አንድ ነገር ብቻ ይህንን ማድረግ ይችላል፡፡ በትላንትናችን ውስጥ ከሆነ በረከትና እርግማን ውጭ ያለ በረከት ይህንን ግራ መጋባት ሊፈታ ይችላል፡፡ ሊለወጥ የማይችል የሚመስለውን ያለፈውን ጊዜ የሚለውጠው በረከት ነው፡፡ በእርግጥ

ይህም በረከት ቢሆን ይህንን እውነት ሊለውጥ አይችልም። ይህም የማይለወጠው እውነት፦ የሆነው አንድ ጊዜ ሆኗል፤ እንደሆነው ሆኖ ባለበት ለዘላለምም ይቀጥል። ነገር ግን በባለፋው ጊዜ የሆነው ነገር አሁን ለእኛ የሚሰጠን ትርጉም ዘላለማዊ በሆነው በእርሱ ሊለወጥ ይችላል። የዚህ ለውጥ ስም ደግሞ የ"ይቅርታ" ሕይወት ልምምድ ይባላል። "ስለትላንትናችን" ያለን መረዳት፣ ግንዛቤ እና "ስለትላንትናችን" የምንለው በምሬት የተሞላ ነገር፥ በጠቅላላ "ትላንትና ስለሆነው ነገር ያለን አተረጓጎም" በይቅርታ ከተቀየረ፥ በወደፊት ጊዜያችን ላይ ያለው ተፅዕኖም ይቀየራል። "የትላንት ትውስታችን" በውስጡ ይዞት የነበረው እርግማን ተጠርጎ ይጠፋል። "ትላንትናችንም"፣ ያለፈውም ጊዜም፤ ይቅርታ ባለው የመለወጥ ኃይል አማካኝነት ለበረከት ይሆናል።

እንግዲህ ወዳለፈው ጊዜ፣ ወደ ትላንትና ዞር ብለን ስንመለከት የምናገኘው በረከት እና እርግማን ብቻ አይደለም። አንዳንድ ጊዜ በትላንትናው ውስጥ በረከትም እርግማንም የሌለበት ጊዜ አለ። ባዶነትንም የተሸከመ የትላንትና ጊዜ አለ። ወደትላንትናችን ዞር ብለን ስንመለከት፥ በሕይወታችን ውስጥ የምንፈልገውን ሁሉ እናገኝበት የነበረበትን "የትላንት ጊዜ" እናስታውሳለን። እነዚያን ጊዜያት በደንብ እናስታውሳለን። በርግጥ አሁን የተትረፈረፈው ነገር ጠፍቶ፣ የነበረውም ደስታ ተኖ አሁን ምንም የለም። የዚያን ጊዜ ሙላት እና ድሎት ወደ ባዶነት ተቀይሯል። ባዶ ትዝታን ብቻ ፈጥሮ ጠፍቷል። ደስታ፣ ስኬትና ባለ ነገር መመካት ድንገት የመትነን ጠባይ አለው። ዛሬ ከእኛ ጋር ባይሆንም፣ ዛሬ ላይ ቆመን እንደ እርግማንም፣ እንደበረከትም አናያቸውም። እንዲሁ በትላንት ውስጥ ተውጠዋል። ላይመለሱ ሄደዋል። ቀጣይና ዘለዓለማዊ በሆነው ሕይወታችን ላይ የሚያሳድሩት ክፋም ሆነ በጎ ተጽዕኖ የለም። በሕይወታችን ውስጥ፣ ጥቂት ነገር ቢሆን እንኳን በዚህ ፍርድ ውስጥ የማይካተት፣ በረከትም እርግማንም ያልሆነ፣ ምን ይኖራል ብለን ራሳችንን እንጠይቅ።

## 3

“የወደፊት ጊዜ” ምስጢር እና “ያለፈ ጊዜ” ምስጢር “በአሁን ጊዜ” ምስጢር ውስጥ ተዋህደዋል። የእኛ ጊዜ፥ ማለትም “እጃችን ላይ ያለ ቀን” የምንለው፤ የእኛ “መገኘት” (presence) ያለበትን ቀን ነው። ነገር ግን መገኘት (presence) እንዴት ሊኖረን ይችላል? የ”አሁን ጊዜን” በማሳብ ላይ ሳለን፥ ብን ብሎ አይጠፋም? የ”አሁን ጊዜ” እንቅስቃሴው የማይቆም፣ በትላንት ጊዜ እና በወደፊቱ ጊዜ መልስ ያለ ድንበር (moving time boundary) አይደለምን? ነገር ግን ይህ የጊዜ ድንበር የሚንቀሳቀስ ድንበር ነው። የምንቆምበት ድንበር አይደለም። “ከዚህ በኋላ የማይኖር” የትላንት ጊዜ ብቻ እና “አሁን የሌለ” የወደፊት ጊዜ ብቻ ቢኖረን ኖሮ፥ ምንም ነገር አይኖረንም ነበር። ስለአሁኑ ጊዜ ማውራት አንችልም ነበር፥ “አሁን” የእኛ ጊዜ አይኖረንም ነበር። በአሁን ውስጥ የእኛ ህልውና (presence) አይኖርም ነበር።

ሚስጥሩ አሁን እኛ “የአሁን ጊዜ” አለን። እና ደግሞ ከዚህም ልቆ “በአሁኑ ጊዜ” ውስጥ ስለነገ ስለምናቅድ፣ የወደፊት ጊዜ ገና ከመድረሱ ዛሬ የእኛ ሆኗል። ደግሞም የትላንት ጊዜም የእኛ ነው። ምክንያቱም “በዛሬ” ውስጥ ስለምናስታውሰው። ያለፈው ጊዜ በትዝታ በእኛ ውስጥ ህያው ስለሆነ ትላንትና ትቶን የጠፋ ነገር ሳይሆን ዛሬም የእኛ ነው። በዛሬ ውስጥ “ያለፈ እና የወደፊት ጊዜ “አብሮ አለ። ትላንትና እና ነገ ከእኛ ጋር ነው። መቼ? ዛሬያችን ውስጥ። ነገር ግን ስለጊዜ ስናስብ መጨረሻ የሌለው የጊዜን ፍሰት ካሰብን “የአሁን ጊዜ” የሚባል አይኖርም። “የአሁን ጊዜ ምንድን ነው?” የሚለው እንቆቅልሽ፥ ከእንቆቅልሾች ሁሉ እጅግ ጥልቅ ነው። እናም “ትላትናን፣ ዛሬን እና ነገን” በውስጡ አካቶ ከያዘው እና ከ” ትላንትና፣ ዛሬ እና ነገ” ክበብ ውጪ ካለው፣ ጊዜን ሁሉ በአንድ ጨፍልቆ ከያዘው ከዘላለም ከሚመጣ በቀር የጊዜን እንቆቅልሽ ማንም አይፈታም። በየትኛውም ወቅት “አሁን” ወይም “ዛሬ” ስንል የጊዜን ፍሰት ለራሳችን እናቆማለን እንጂ፤ ጊዜ በየቅፅበቱ መሄዱን ቀጥሏል። ነግቶ ዛሬ የምንለውን ቀን ስናይ ደስ ይለናል። እና ዛሬ ባየነው ቅጽበት ዛሬነቱ እንዳበቃ ግን ግድ አይሰጠንም። ለምሳሌ ዛሬ አስር ኪሎ ግራም ወርቅ ቢሆን የተቀበልነው፤ በተቀበልነው ቅጽበት ዘጠኝ ይሆናል። እኛ መጉደሉ ግድ አይሰጠንም። ዝምብለን በአሁኑ ጊዜ ውስጥ እንኖራለን። እኛ እንኳን ባናስተውለው በየቅፅበቱ ባለው አዲስ የአሁን ጊዜ፣ ሌላ የአሁን ጊዜ እየታደሰ ይሰጠናል። ወይንም እኛ የምናየው የሚጎድለውን የወርቁን ኪሎግራም ባይሆንም እጃችን ላይ ያለው ወርቅ ኪሎግራም በፍጥነት ሲቀንስ እጃችን ላይ ወርቁ

እንዳይጠፋ ቶሎ ቶሎ በቦታው ይተካልናል ማለት ነው። ይህም ሊሆን የቻለበት ምክንያት እያንዳንዱ የጊዜ ፍሰት መዳረሻው ዘላለም ጋ ስለሆነ ነው። የጊዜን ፍሰት ባለበት እያቆመ የዛሬ ጊዜ እንዲሆን አበጅቶ የሚያቀርብልን ዘለዓለማዊው የሆነው እርሱ ነው። አላፊ የሆነ “የአሁን ጊዜ” የእኛ እንዲሆን የሚሰጠን በእርሱ ዘንድ “የአሁን ጊዜ” ዘላለማዊ የሆነው ነው። የምንኖረው፥ ጳውሎስ ለዕብራውያን በፃፈው ደብዳቤ ላይ እንዳስቀመጠው፥ “ዛሬ ሳለ”በሚለው ማዕቀፍ ብቻ ነው። ሁሉም ሰው እንደጨርቅ በሚጠቀለለው አላፊ “አሁን” ውስጥ ያለውን የ” ዘላለም አሁን” አይገነዘብም። ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ይህ መረዳት በሀይለኛ ወደ ንቃተ ኅሊናችን፣ ወደ አዕምሮችን ጓዳ ጥሶ ይገባል። ስለ ዘላለም እርግጠኝነትን ይሰጠናል። ከእኛ መረዳት ውጪ ስለሆነው የጊዜ አቅጣጫ ስለ ዘላለም እርግጠኝነትን ይሰጠናል።፣ እኛ ወደምናወቀዉ ጊዜ ሰንጥቆ ስለሚገባው እና ለእኛ “የሆነ ቦታ ጀምሮ የሆነ ቦታ የሚያበቃ ጊዜ” ስለሰጠን፤ ስለ ዘላለም እርግጠኝነትን ይሰጠናል።

ይህን የጊዜ አቅጣጫ የማይረዱ፣ እና ግንዛቤው የሌላቸው ሰዎች “በአሁን ጊዜ ውስጥ” ያለውን የዕረፍት እድሎችን ያጣሉ። የዕብራውያን መልእክት እንደሚገልጸው፣ ወደ መለኮታዊ ዕረፍት ፈጽሞ አይገቡም። በትላንትናቸው ተይዘዋል። ራሳቸውን ካለፈው ጊዜ መነጠል አይችሉም። ወይም ደግሞ፥ ዛሬን ትተው በወደፊት ጊዜ ውስጥ ተሸሽገዋል። እናም ከዛሬ ዕረፍት ውጪ ናቸው። የጊዜን ፍሰት የሚያቆም እና የአሁኑ ጊዜ በረከትን ወደ ሚሰጠን የዘላለም እረፍት አልገቡም። ይህ በጊዜያችን ውስጥ በጣም ጎልቶ የሚታይ ባሕሪ ነው። በተለይም በምዕራቡ ዓለም እና በተለይም በዚህ ሀገር (አሜሪካ) ውስጥ። “በዛሬ ውስጥ” ለመኖር የራስን ህልውና ለመቀበል፥ ድፍረት የለም። ምክንያቱም ከዘላለም አቅጣጫ ጋር ስለተጠፋፋን።

“እኔ መጀመሪያና መጨረሻ ነኝ” ይህ የተባለው በጊዜ እስርቤት ውስጥ በባርነት ላለን ለእኛ ነው። መጨረሻ ያለን፥ እና ከመጨረሻችን ጋር ለምንፋጠጥ ለእኛ ነው። ከትላንትናችን ማምለጥ ለማንችል ለእኛ ነው። የምንኖርበትን ዛሬን ለምንፈልግ ለእኛ፣ ጊዜ በተባለ የተወሰነን እና በጊዜ ባርነት ውስጥ ለምንኖር ለእኛ “መጀመሪያና መጨረሻ እኔ ነኝ” ብሎናል። እያንዳንዱ የትላንት ጊዜ፣ የአሁኑ ጊዜ እና የወደፊት ጊዜ የምንለው የጊዜ ሰሌዳ የራሱ የሆነ ምስጢር አለው። እያንዳንዱ የጊዜ ሰሌዳ የራሱ በቂ ጭንቀት አለው። ደግሞ እያንዳንዱ የጊዜ ቀመር፥ በሕይወት ውስጥ መነሳት ወዳለበት የመጀመሪያም የመጨረሻም ወደሆነ

ጥያቄ ይመራናል። እና ለዚህ ጥያቄ አንድ መልስ ብቻ አለ! ዘለዓለማዊው እርሱ! ጊዜን ሁሉ ጠቅልሎ የሚውጠውን ኀይል የሚልቅ ኀይል አለ! ዘለዓለማዊው እርሱ! የነበረውና ያለው፣ የሚመጣውም መጀመሪያውና መጨረሻ የሆነ! እርሱ ለትላንትናችን ይቅርታ ይሰጠናል፣ እርሱ ለሚመጣው ድፍረት ይሰጠናል። እርሱ በዘላለም መገኘቱ ውስጥ ዕረፍትን ይሰጠናል።

## 2. የምወደው መልካም፤ የማደርገው ክፉ

*“የምወደው መልካም፤ የማደርገው ክፉ የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም። የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኀጢአት ነው እንጂ።”*

*ሮሜ 7፡19-20*

“የማልወደውን ክፉን ነገር አደርጋለሁና ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።” ይህ የጳውሎስ ንግግር የእኛን ተፈጥሮ በትክክል የሚገልጽ ንግግር ነው? በጎ ነገር ለማድረግ በመፈለግ እና የፈለጉትን በጎ ነገር ለማድረግ ባለ ፍቃደኝነት መካከል ያለው ክፍተት፣ በጳውሎስ ሐሳቦች ውስጥ እንደተገለጡት የሰማይ እና የምድር ያህል ልዩነት ያላቸው ናቸው? የምፈልገውን በጎ ነገር አደርጋለሁ፣ የማልፈልገውን እኩይ ነገር ደግሞ አላደርግም በማለት፤ ሰዎች በእኛ ላይ ለሚያቀርቡት ክስ ጆሮአችንን እንደፍናለን? ምናልባት ጳውሎስ ድቅድቅ ከሆነ የጨለማው ጉልበት ያዳነንን ፀጋ ታላቅነት ለማጉላት ስለፈለገ፣ በሰው ልጅ ውስጥ ያለውን እኩይነት እጅግ አጋኖት ቢሆንስ? እነዚህ ጥያቄዎች ክርስትናን በሚነቅፉ ሁሉም ቡድኖች የሚነሱ ጥያቄዎች ናቸው። ግን ደግሞ በተቺዎች ብቻ ሳይሆን ራሳችንን ክርስትየን ብለን በምንጠራ ወይም ቢያንስ ክርስትና ሁኑ ያለንን ለመሆን የምንፈልግ ሁላችንም የምናነሳው ጥያቄ አይደለም ወይ? በመሠረቱ አንድ ሰው ሁልጊዜ በሕይወቱ ፈጽሞ ሊያደርገው የማይፈልገውን እኩይ ነገር ያደርጋል፤ የሚፈልገውን በጎ ነገር የማድረግ አቅም የለውም ብለን አናምንም። አንዳንድ ጊዜ ማድረግ የምንፈልገውን መልካም ነገር በማድረግ እንደተሳካልን እናውቃለን። ለምሳሌ ሲኦል ቢገባ ግድ ለማይለን ሰው ፍቅርን አሳይተን፣ ራርተን እናውቃለን። ለሥራችን መሳካት ስንል ጊዜአዊ የሆነን የማይረባ ነገር በመተው በሥነ ሰርዓት ኖረን እናውቃለን። ለምሳሌ እኛን አደጋ ላይ የሚጥል እንደሆነ ብናውቅም ከክፋዎች ጋር አልተባበርም ብለን በክፋት ፊት ፀንቶ የመቆም ድፍረት አሳይተን እናውቃለን። እነዚህን መሰል የሞራል ከፍታ ላይ የሚያስቀምጡንን በጎ ነገሮች ያልተገበርን ቢሆን ኖሮ፥ እኩይ የሆነው ምግባራችን ከቁጥር በበዛ ነበር። “የሰው ልጅ ፍጹም በሆነ የሀጢያት ግዛት ውስጥ ነው፥ በራሱ አንዳችም በጎ ነገር ማድረግ

አይችልም” “The total depravity of man” የሚለውን ትምህርት የሚያምን እና የሚሰብክ ሰባኪ ቢሆን እንኳን፣ በርሱ ውስጥ ያለውን መልካምነት እንዲታይ የማይፈልግ፥ በበጎ ምግባሩ የማይኮራ የምታውቁት አለ? ምናልባትም ጳውሎስ (ከእኔ የሆነ አንዳች በጎ ነገር የለም የሚለው እምነቱ ስር የሰደደው) ራሱ በአንዳንድ በጎ ድርጊቶቹ ኩራት ሳይሰማው አይቀርም። ቢያንስ ለቆሮንቶስ ሰዎች በጻፈው ደብዳቤ ላይ ስለደረሰበት መከራ እና በአገልግሎት ስለአለው እንቅስቃሴዎቹ እንደሚመካ በጨረፍታም ቢሆን ሊነግረን ሞክሯል። እርግጥ ነው የሰራሁት በጎ ምግባር በሚለው ነገር መመካቱን፣ ሞኝነት ብሎታል። እኛስ ቢሆን ትምክህታችን ሞኝነት መሆኑን ከመናገር ወደኋላ እንላለንን? እንደዛም ሆኖ በበጎ ምግባራችን መመካታችንን አናቆምም። በሌላ መልኩ ደግሞ “የምንመካበት ነገር አንዳች የለም ብለው የሚያምኑ፥ ከላይ ሲታይ ንግግራቸው ትህትና ቢመስልም፥ ምናልባት ጤና በማጣት፣ በአዕምሮ መቃወስ እና ‘በእኔ ውስጥ አንዳች በጎ ነገር የለም’ የሚል የዝቅተኝነት ስሜት አመለካከት ስላላቸው ቢሆንስ? ምናልባትም ደግሞ፥ ያሉበት የተስፋ መቁረጥ ጥልቀት የሚያስመካቸው ዓይነት ይሆናሉ። በራሳቸው ስቃይ የሚደሰቱ ይሆናሉ። ማንም ሰው ስለራሱ ጥቂትም ብትሆን በጎ አመለካከት እና በራስ መተማመን ሳይኖረው መኖር አይችልም። “በሕይወቴ ከስቃይ ውጪ አንዳች ነገር የለም፥ አንድም ነገር አሳክቼ አላውቅም” እያለ ራሱን የሚኮንነውም ቢሆን ይህንንም የተቋቋምኩት እኔ ሆኜ ነው የሚል አመለካከት ስለ ራሱ ካላዳበረ በጥንካሬው ካልተመካ መኖር አይችልም።

ነገር ግን ለምንድን ነው የጳውሎስን ንግግር በቀላሉ ወዲያ አሽቀንጥረን የማንጥለው? “ዳሩ ግን የምወደውን በጎውን ነገር አላደርገውም።” ለሚለው የጳውሎስ መግለጫ በመስማማት ጭንቅላታችንን የምንነቀንቀዉ ለምንድን ነው? ምክንያቱም እነዚህ ንግግሮች ምን ያህል እኩይ ወይም በጎ ነገር የምታደርግ ነህ አይደለህም የሚል ማወዳደሪያ የሚሰሩ እንዳልሆኑ፣ ነገር ግን መላው እኛነታችንን የሚመለከት፣ እንደሰው ስንኖር ስላለንበት ሁኔታ አንዳች ነገር የሚያሳይ፣ በ እኛነታችን ፈራጅ፣ አላማና ምንጭ በሆነው በእርሱ፣ በዘላለም አምላክ ፊት ስንቆም እንዴት እንደምንታይ የሚመለከትን ጉዳይ የሚያወሩ እንደሆኑ ስለሚሰማን ነው። ከኛ ፈቃድና ምርጫ ውጪ፥ በሌላ ኃይል ቁጥጥር ውስጥ መሆናችን፣ ሰው ሆነን በመፈጠራችን ብቻ የሆነብን አጣብቂኝ ሁኔታ ነው። ይህ ኃይል ከእኛ አልመጣም ነገር ግን በኛ ውስጥ አለ። በውስጣችን ቢኖርም እንጠላዋለን፥ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ በውስጣችን መኖሩን በደስታ እንቀበላለን። በዚህ ኃይል እንደነቃለን። ከዚህ ኃይል ጋር ድብብቆሽ እንጫወታለን። ለዚህ ኃይል

እንገዛለን። ነገር ግን ደግሞ ይህ በውስጣችን ያለን ኀይል የሚቋቋምና በቁጥጥር ውስጥ የሚያደርግ ሌላ ሀይል ከውጪ መጥቶ ካላስመለጠን በቀር እንደሚያጠፋን እናውቃለን። ሊያጠፋን የሚችል ሀይል እንደሆነ እያወቅን እንኳን፤ ሁሌም በአግራሞት እንደተሞላን ነው። እንደውም በሆኑ ወቅቶች ይህ ኀይል እንደፈለገ ቢያደርገን፣ በዚህ ሀይል አደጋ ውስጥ ብንወድቅ ራሱ ምንም የማይመስለን፣ እንደውም ያ ጥፋት እንዲያደርስብን የመፈለግ የተደበቀ ሞኞት አለን። ጳውሎስ ወደ ራሱ ሲመለከት እንደዚህ አይነት ማንነት ያለው ሆኖ ራሱን አይቷል። ራሱን ያገኘው እንደዚህ ዓይነት ሰው ሆኖ ነው! ብዙዎቻችን ራሳችንን ያገኘነው እንደዛ ዓይነት ሰው ሆነን ነው!

ወላጆች፣ አስተማሪዎች ሰባኪዎች እና በአጠቃላይ ራሳቸውን ክርስትያን ብለው የሚጠሩ ሁሉ እለት በእለት “መልካም ሰዎች እንድንሆን” እና ለእግዚአብሔር ፈቃድ እንድንገዛ ያሳስቡናል። ነገር ግን ለብዙዎቹ የእግዚአብሔር ፈቃድ ማለት፣ ለራሳቸውም ሞኞት የፈጠሩትን ሥርዓትና ሕግ ከምንም ነገር በላይ አክብረን እንድንኖር ከሚያስገድዱን ማሕበረሰባዊ ቅቡልነት (በማሕበረሰቡ ውስጥ አንቱ የሚባሉ ሰዎች) ካላቸው ቡድኖች ሐሳብ የተለየ አይደለም። እንደ እነርሱ ከሆነ፣ እነርሱ በጎ የሚሉትን ለማድረግ ፈቃደኞች ከሆንን፣ በርግጥም ማሳካት እንችላለን፣ ደግሞ አሁን እና በሚመጣው ዓለም የምንሸለምበት ጉዳይ ይሆናል። ከሁሉም በላይ ግን እንዳሉት ካደረግን በመጀመሪያው በዚሁ በምድር ሽልማት አለን።

አንድ ሰው ከጊዜ ወደ ጊዜ ይህ አይነቱን ስብከት ከቁምነገር የሚቆጥረው ሰው እየቀነሰ፣ በስብከቱ ልከኝነት ላይ ጥርጣሬ እየየለ በመምጣቱ እግዚአብሔርን ማመስገን ይችላል። ስለ ሰው ልጅ ማንነት በትክክል የሚያስገነዝብ እና ለሰው ልጅ ችግር መፍትሔ የሚሆን ሃሳብ አይደለም። አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ሕይወትን በቁምነገር ከሚወስዱ ወገን የሆኑ ሰዎች እንደ ሰው ሲኖሩ ስላሉበት ትክክለኛ አጣብቂኝ ሁኔታ ሊኖራቸው ስለሚገባ ንቃተ ኀሊና ዓይኖቻችን እየበሩ ነው። ሰው ማለት ምን ማለት ነው? ለምንድነው ወደ ግራና ቀኝ የሚላተመው? ለሚለው ጥያቄ መልሱ የት ጋ ነው ያለው የሚለውን ወደ መገንዘብ መጥተዋል። እንደውም እየንዳንዱ የጳውሎስ መልዕክት ዓረፍተ ነገር ጣቱን የሚቀስረው በአደባባይ የቅድስና ካባ በለበሱ ነገር ግን ውስጣዊ ማንነታቸው ስለራሳቸው የሚሉትን በማይመሰክር ሰዎች ላይ ነው። እንደውም እነዚህ ሰዎች ከማንም በላይ፣ ነኝ ከሚሉት እና ከሚያደርጉት በጎ ምግባር በተቃራኒ ሳይወዱ በግድ እንዲሄዱ

በሚያስገድድ ሀይል ተጠርንፈው የተያዙ ሆነው አይቷቸዋል። እነዚህ ሰዎች ደግሞ እኛ ነን። ከእኛ መካከል በጎን ነገር የማይሻ፣ መልካም ነገር ለማድረግ የማይፈልግ በዚህ በጎ ምኞት ያልተሞላ ማን አለ? ነገር ግን ራሳችንን በተሻለ እና በጥልቀት ወደማወቅ ብንመጣ፣ ከፍጥረታችን ማን እንደሆንን ብንረዳ፤ አለን የምንለው አንዳንድ መልካም ምግባራችን የምርም መልካም እንዳልሆነ መጠርጠር እንጀምራለን። እንደውም ከቶ ምን እንደሆነ ያላስተዋልነው እንግዳ የሆነ እኩይ ኂይል ከውስጣችን ሆኖ እየነዳን እናገኘዋለን።

በመልካምነታቸው ስማቸው በየቦታው የሚነሳ ነገር ግን ከመልካምነታቸው ስር የተሸሸገ እኩይነት ስለሚገኝባቸው ሰዎች ብዙ ማብራሪያ ማቅረብ አስፈላጊ አይደለም። የሥነ አዕምሮ ባለሙያዎች እና ሌሎች በዚህ ጥናት ዙሪያ የተሰማሩ ብዙ ያሉለት ነገር ስለሆነ እዚህ መድገም ተገቢ አይደለም። አሁን ስላለንበት ዘመን ሃየሲያን ብዙ ነቀፋ ቢያቀርቡም፥ በዘመናችን ውስጥ ሊጠቀስ ከሚችል ገንቢ ነገር አንደኛው፥ ሰዎች ስለሚያደርጓቸው ድርጊቶች ከጀርባ ያለው እውነተኛ ፍላጎታቸው ምን እንደሆነ፥ ከራሳቸውና ከሌሎች ሰዎች በቋሚነት ለመሸሸግ የማይችሉበት ዘመን መሆኑ ነው። ወደዚህ ግንዛቤ ለመድረስ ጥቅም ላይ የዋሉ ዘዴዎችን በተመለከተ ምንም ነገር ልናስብ እንችል ይሆናል ነገር ግን የተገኘው ግንዛቤ በራሱ አድናቆት የሚቸረው ነው።

ሁለንተናውን ለሥራው በመስጠት እና በዛም ስኬታማ እየሆነ ያለ ሰው እየሰራ ያለው ሥራ በእርግጥም በጎ ሥራ ስለመሆኑ እርግጠኝነት ሊሰማው ያልቻለበት ጊዜ ነው። ለሥራው ያለው ትጋት እና መሰጠት ምናልባት በሕይወት ውስጥ ሊያደርጋቸው ከሚገቡ ትክክለኛ ነገር መሸሻ፣ ከሁሉም በላይ ደግሞ ራሱን ከመስማት እና ከማየት መሸሻ መንገድ ሊሆን እንደሚችል ከዚህ በኋላ ከራሱ መሸሸግ አይችልም።

ልጆቿን ከምንምና ከማንም በላይ አብልጣ የምትወድ እናት፥ ፍቅሯ ጤነኛና እውነተኛ ይሁን አይሁን እርግጠኛ ለመሆን አስቸጋሪ የሆነበት ጊዜ ነው። ስለልጆቿ ሁለንተናዋ እድገት ያላት ጭንቀት ምናልባት ለእነርሱ ካላት እውነተኛ ፍቅር የመነጨ ላይሆን ይችላል። መውጣት እና መግባታቸውን፣ መነሻ እና መድረሻቸውን ለመቆጣጠር፥ እርሷ በምትፈልገው እና በሚያስደስታት መንገድ እንዲሆን ለማድረግ እንደሆነ የሚያሳይ፥ የጥልቅ ፍላጎቷ መገለጫ ሊሆን ይችላል። ወይም ደግሞ ከሕይወቷ ውስጥ እንዳች ነገር ጠርጎ ቢወስድላት የሆነ ነገር ይሰማታል። እና እናት የመሆን ሸክሟ በወገድ የመፈለግ ስሜት በውስጧ አለ።

ያ ስለልጆቿ በውስጧ የተፈጠረው መጥፎ ስሜት ለፀፀት ዳርጎታል። ስለዚህም ያ እጅግ ከመጠን ያለፈ ስልጆቿ የምታሳየው ፍቅር “እኔ ልጆቼን የምወድ እናት ነኝ እንደዛ የማስበው እኔ አይደለሁም። እኔ ልጆችን በጣም የሚወድ ልጆቼ ደስታዬ እንጂ ሸክም ያልሆኑብኝ ይሄ ነኝ እያለች” ከውስጧ ካለው መጥፎ ስሜት ጋር የምታደርገው ትግል መገለጫ ሊሆን እንደሚችል ከዚህ ወዲህ ከራሷም መደበቅ አትችልም።

ሰዎች ከሚያደርጉት ድርጊት በላይ ድርጊቱን እንዲያከናውኑ የሚገፋቸው ውስጣዊ ፍላጎት ከድርጊቱ በተጻራሪ ሊሆን የመቻሉ ዕድሉ ሰፊ ነው። ለምሳሌ ባሕላዊ፣ ማሕበራዊ እና ሐይማኖታዊ መሠረት ያላቸውን ሕግጋትና ሥርዓት አክብሮ የሚኖረውን ሰው ሁሉ ልናሞግሰው አንችልም። ምናልባት የዚህ መልካምነታቸው የጀርባ አንቀሳቃሽ ጉዳይ፣ ሲወርድ ሲዋረድ በመጣው ነባሩ የሥነምግባር ሕግጋት ላይ አብዮት ተነስቶ ወደ አዲስ ዓይነት አኗኗር ላለመሄድ ካላቸው ጥልቅ ፍርሃት የመነጨ፥ እና አብዮት እንዳይነሳ ለመከላከል ሊሆን እንደሚችል ስለምናውቅ ነው። ምክንያቱ ደግሞ ቀድሞውንም ሌሎች ነባር በሆነው ሥርዓት ላይ የለውጥ ጥያቄ አንስተው ስለነበር! እነዚህ ሰዎች በመሠረታዊነት አብዮቱን እንጂ ያልፈለጉት የሚያደርጉትን ነገር የሚያደርጉት ወደውት አይደለም። በሌላ መልኩ ደግሞ ነባሩን ሥርዓትና ሕግጋት ለመለወጥ የሚጋፈጡ ሁሉ ጀግኖች እያልን ልናሞግሳቸው አንችልም። ምናልባት እንደዚህ አይነት ሰዎች፣ የለውጥ ኀይል እና ለውጥ ለማምጣት ዋጋ የሚከፍል ሰው የሆኑበት ምክንያት፣ ለነበሩ ባህል ግዴለሽነትን እና የማሕበረ ሰብን መሠረቶች ማፍረስን የሚያበረታቱ ቡድኖችን ሃሳብ አለመከተል ኋላቀርነት ስለሚመስላቸው እና ከቡድን ተፅእኖ ተላቀው ትክክለኛ ለሆነ ነገር ፀንቶ ለመቆም ደካማ ስለሆኑ ሊሆን ይችላል። ጀብደኝነታቸው የደካማነታቸው መሸፈኛ ሊሆን እንደሚችል እናውቃለን።

በእነዚህ እና በሌሎች ለመቁጠር በሚያታክቱ እንደ ናሙና ከወሰድናቸው ምሳሌዎች እንዳየነው፥ የሆነ ኀይል በውስጣችን እንዳለ እና ይህም ኋይል ፈቃዳችንን እርስ በርስ እንደሚያጋጭ በተግባር ማወቅ ችለናል። ፈቃዳችን እርስበርስ እንዲቃረን እና በጎውን ተግባር ለክፉ መሻት ማስፈጸሚያ እንድናውል የሚገፋ ኀይል በውስጣችን እንደተቀመጠ ከልምድ ተገንዝበናል።

የዚህ ኀይል ስም ሀጢያት ይባላል። ባለንበት በዚህ ዘመን፥ በክርስትያኖች ዘንድ ይሁን ክርስትያን ባልሆኑት ዘንድ ይህንን ቃል መጥራትን የመሰለ ነቀፋ

የሚያስከትል አደገኛ ነገር የለም። በሁሉም ዘንድ ለማለት በሚያስችል መልኩ ኀጢአት የሚል ቃል ሲጠራ ላለመስማት ጆሮን የመድፈን የልብ ድንዳኔ አለ። አሁን ኀጢአት የሚለው ቃል፥ የቀድሞ መፈራቱን እና ያገኝ የነበረውን ትኩረት ያጣ ቃል ነው። ለአንዳንዶቻችን ሀጢያት የሚለው ቃል አንዳች ቂላቂል የሆነ ሃሳብ የተሸከመ ነገር ይመስለናል። ከዚህም የተነሳ ከቁም ነገር ልንወሰደውም የሚገባ ቃል ሳይሆን፥ ሳቅ በውስጣችን የሚፈጥር የመዘናኛ ቃል ነው። ሌሎች ደግሞ አሉ፥ ኀጢአት በሚለው ቃል ውስጥ ያለውን ፍሬ ሐሳብ ከቁምነገር የሚወስዱ እና እነሱን ይሁን ወይም ሌላን ሰው በኀጢአተኝነታቸው መውቀስ ወይንም ሀጢያት ከሚለው ቃል ጋር አስታኮ ማንሳት፥ በሰብአዊ መብትና ክብር ላይ የተደረገ ጥቃት አድርገው ይቆጥሩታል። በእነርሱ አይን ሰውን በዛ ቃል መጥራት ከባድ ወንጀል ነው። ሀጢያት ፈጽመሃል በሚል ምክንያት የተቀጡ እና መከራ የደረሰባቸው ሰዎች ደግሞ፥ ኀጢአት የሚለውን ቃል ሲሰሙ ቀድሞ በአዕምሮቸው የሚከስተው ምስል፥ የሚፈልጉትን ነገር እንዳያደርጉ የከለከሉአቸው እና ማድረግ የማይፈልጉትን ደግሞ እንዲያደርጉ ያስገደዱአቸውን ሰዎች ምስል ነው። ከዚህም የተነሳ፥ እኔን ጨምሮ፥ ክርስቲያን መምህራን እንኳን ሳይቀሩ ኀጢአት የሚለውን ቃል ላለመጥራት ሀፍረት አፋቸውን ሸብቦታል። ቃሉ ሲጠራ በሚሰሙ ሰዎች ዘንድ ምን የህል የተዘበራረቀ እና ደስ የማይል ምስል እንደሚሰጥ እናውቃለን። በተቻለን አቅም ቃሉን ከአካባቢያችን ለማጥፋት ወይም ሌላ የማይጎረብጥ ቃል እንዲተካው ለማድረግ እንሞክራለን። ነገር ግን ሀጢያት የሚለው ቃል እንግዳ የሆነ መለያ ማንነት አለው። የቱንም ያህል ከአካባቢያችንን ዞር ብናደርገው ሁልጊዜ ተመልሶ ይመጣል። ልናመልጠው በጭራሽ አንችልም። የቱንም ያህል የምንጠላው መልክ ቢኖረውም፤ ደጋግሞ መከሰቱ ይቀጥላል። ስለዚህም ከማደባበስ፥ ነገረ ጉዳዩን በጥልቀት መመልከትና እውነት ኀጢአት ማለት ምን ማለት ነው ብሎ መጠየቅ የተሻለ ነገር ነው። ይህንን ለራሴ ጭምር ነው የምለው።

ሐጢያት ማለት ትርጓሜው “የቅዱሥነት ካባ የደረቡ ሰዎች”፣ አንድ ነገር በትክክለኛው መንገድ አለማድረግ፣ ማድረግ የነበረብንን እና ማድረግ እንችል የነበረውን መልካም ነገር አለማድረግ ነው ብለን እንድናምን እንደፈለጉት ማለት አይደለም። ሀጥያት ማለት እነዚህ ሰዎች ነው ብለን እንድንቀበል እንደሚፈልጉት አይነት አይደለም። የጢጥያት ትርጉም እነርሱ እንደሚሉት ቢሆን ኖሮ፥ ኀጢአት ከሚል ስም ይልቅ፣ አስደንጋጭ ያልሆነና ግራ አጋቢ ምስል የማይከስት “የሰው ድካም” የሚለውን ቃል መጠቀም ይቻል ነበር። እንዲያውም የእነርሱ ኀጢአት ምንድን ነው ለሚለው የሰጡት ፍቺ፥ ሀጢያት ማለት ይህ ማለት አይደለም

ለሚለው መልስ ይሆናል። እና የሀጢያትን አጋንንታዊ ኀይል፣ በውስጣችን ያደረገውን እና በኛ ዘርያ አልፎ የሰራው በተጨባጭ ላየን ሰዎች፥ ሀጢያት ምንድን ነው ለሚለው የሰጡት ብያኔ አስቂኝ ነው።

ስለዚህ ፊታችንን ወደ ጳውሎስ ማዞር ሊኖርብን ነው። ወይም ደግሞ ምናልባትም በዶኦስቶቪስኪ የልብ ወለድ ሥራዎች ውስጥ ወደምናገኘው ኢቫን ካራማዞቭ ወደተባለ ገፀ ባሕሪም መመልከት ይኖርብናል። ወይንም ደግሞ በቶማስ ማን ዶ/ር ፋውስተስ በሚለው የልብወለድ ሥራ ውስጥ በአጋንንት እና በዋናው ገጸ ባሕሪው መካከል የተካሄደውን ውይይት መመልከት ይኖርብናል። ሀጢያት ምንድነው የሚለውን በድንብ የምንማረው ከእነዚህ ከላይ ከጠቀስናቸው ሥራዎች ነው። እንደገና ደግሞ ምን አልባትም በናዚ አና ፋሺዝም አጋንንታዊ ሀይል በአእምሮ ሊገመት በማይችል ዘግናኝ መንገድ ድምጥማጧ የጠፋው የባስክ ትንሽዬ መንደር ከሆነችው የጊሃሪንካ የፒካሶ ሥዕል አማካኝነት ሀጢያት ምንድነው የሚለውን እንማራለን። ምናልባትም በቲያትሮቻችን ውስጥ ያሉ ገጸ ባሕርያትን ከሞሉ የእኩይ እና የፀፀት ምስሎች የኀጢአትን ትርጉም እንማራለን። ወይም በልብ ወለድ ሥራዎቻችን ውስጥ የተደበቁ ፍላጎቶችን የማሳየት ሥራ ተበራክቶ ስለምናገኝ፣ ኀጢአት ምንድነው የሚለውን በዚያ በኩል መማር እንችላለን። ሀጢአት ምንድን ነው ለሚለው ትክክለኛውን ትርጉም ለመረዳት፥ ከአብያተ ክርስቲያናት አጥር ውጪ እና ጥልቀት ከሚጎድለው የሰባኪዎቻችን ዲስኩር ተሻግረን፤ ወደ አርቲስቶችና ጸሐፊዎች በመሄድ እነሱን መጠየቅ ተገቢ ነገር ነው። ትኩረት የሚሻ ጉዳይ ነው። እጅግ አስፈላጊ ጉዳይ ነው። ነገር ግን አሁንም አንድ ሌላ ሀጢያት ምንድነው የሚለውን ልንማር የምንችልበት ሁነኛ ቦታ አለ፥ ያ ሁነኛ ቦታ ደግሞ የራሳችን ልብ ነው።

ጳውሎስ ሀጢያት የሚለውን ቃል በብዙ ቁጥር ኀጢአቶች ብሎ የጠራበት ጊዜ የጣት ቁጥር አይሞላም ነገር ግን ሁልጊዜ በነጠላ ቁጥር ሀጢያት እያለ ነበር የሚጠራው። ጳውሎስ በመልእክቱ ውስጥ ሀጢያት የሚለው ዓለምን፣ አዕምሮን፣ ግለሰቦችን እና ሀገርን የሚገዛውን የኀጢአትን ኀይል ማለቱ ነው።

ኀጢአት ሲባል ይህንን እንደሚመስል በዚህ መልኩ ባለው ምስል አስባችሁ ታውቁ ይሆን? መጽሐፍ ቅዱስም ሃጢአት ምን እንደሚመስል የሳለልን በዚህ መንገድ ነው። ይህ መጽሐፍ ቅዱሳዊ የኀጢአት ምስል ነው። ነገር ግን ምን ያህል ክርስቲያኖች እና ክርስቲያን ያልሆኑ ይህንን ምስል አይተውታል? ብዙዎቻችን በቤት፣ በትምህርት ቤትና በቤተ ክርስቲያን አንድ ሰው ሊያደርገው ስለሚወደው ነገር፥

ነገር ግን ቢፈልግም ያን ማድረግ እንደሌለበት እንደተማርን እናስታውሳለን። እና ቢፈልግም እንኳን ማድረግ እንደሌለበት የተነገረውን ነገር ካደረገ ሐጢያት ሰርቷል ማለት ነው። እንደገና ደግሞ ማድረግ ስለሚገቡን ነገር ግን እኛ ልናደርጋቸው ስለማንፈልጋቸው ነገሮች እንደተነገረን እናስታውሳለን። እና አድርጉ የተባልነውን ካላደረግን ሀጢያት ሰርተናል ማለት ነው። የአድርግ አታድርግ ዝርዝር መመሪያዎችን የያዙ መዝገቦች ነበሩን። በዚያ የአድርግ አታድርግ መመሪያ መሠረት ካልኖርን፣ የተባልነውን ካልተከተልን፤ ሀጢያት ፈፀምን እንላለን። ሆነም ቀረም፣ ወደድንም ጠላንም፣ በየዕለቱ አንድ ወይም ሁለት ኀጢአቶችን እንሰራለን። እንደገና ደግሞ ከልባችን በሙሉ ፈቃደኝነት በየዕለቱ የምንሰራቸውን የሀጢያት ብዛት ለመቀነስ የተቻለንን እንሞክራለን። ስለ ሃጢአት ያለን ምስል ይሄ ነበር። ምናልባትም አሁንም ስለሀጢያት ያለን ምስል ይህ ነው። እጅግ ደካማ፣ ጥቅም የሌለው እና ግልጽነት የጎደለው ምስል ነው። እናም ሀጢያት የሚለው ቃል ተገቢውን ትኩረት እንዳያገኝ እና ውይይት እንዳይደረግበት ዋናው ምክንያት ይህ የኀጢአት ምስል ነው።

“የምሥራቹ ቃል” እያልን የምንጠራውን ዋነኛውን የክርስትና መልእክት ማለትም ወንጌልን በትክክል ለመረዳት የመጀመሪያው እርምጃ፥ ሃጢያት ማለት “ይህንን እና ያንን መጥፎ ድርጊት ማድረግ ነው።” የሚለውን የአድርግ አታድርግ የሃጢአት ዝርዝር የተፃፈበትን መዝገብ ማስወገድ ይሆናል። ከዚህ ዓይነቱ የኀጢአት ምስል ጋር የተጣበቁ፥ እና ይህን የሃጢያት ትርጓሜ እንደ ትክክለኛ ትርጉም የሚቀበሉ ሰዎች፥ የምሥራቹ ቃል ዋና መልእክት “በምንም መንገድ

ተቀባይነት የሌለውን መቀበል” (the message of acceptance of the unacceptable) ማለት ነው የሚለውን እውነት አሜን ብሎ ለማመን እራሴን ወገቤን የሚሉ ናቸው። አድርጌዋለሁ ብለው የሚቀበሉት እና የሰሩት ትንሽ ሃጢአት በአንድ በኩል። ደግሞ አለን የሚሉት ትንሽ ጽድቅ በሌላ በኩል ሆነው “የሰው ልጅ በሃጢያት የወደቀ ነው። አንድም ጻድቅ የለም። ግን ደግሞ የሰው ልጅ በማዳኑ ፀጋ እንዲሁ ይፀድቃል።” ለሚለው መልእክት ስሜት አልባ አድርጓቸዋል። ይሄ መልዕክት ይቆረቁራቸዋል። በእኔ ውስጥ አንዳችም ጽድቅ የለም ፍፁም ሀጥያተኛ ነኝ በማለት የሆኑትን ማንነት ተቀብለው በራሳቸው ላይ ለመፍረድ ድፍረቱን አያገኙም። ከዚህ የተነሣ ያለእነርሱ አንዳች ሰራ እንዲሁ በፀጋው በርሱ ዘንድ ተቀባይነት ማግኘታቸውን ለመቀበል ብርታቱ የላቸውም።

ሆኖም ከሃጢያት ጋር ደም እስከማፍሰስ ታግለው ያዩ ሰዎች ኀጢአት ማለት ይህንን እና ያንን ስህተት የመፈጸም፣ በየዕለቱ የምንሰራቸው ጥፋቶችና

መተላለፎች እና የተዘረዘሩ ህጎችን ከመተላለፍ ያለፈ ነገር መሆኑን የሚያውቁ ሰዎች፣ በየቀኑ የምንሰራቸው ጥፋቶችና ሰህተቶች ራሳችን ከራሳችን የመነጠላችን፥ በውስጣችን ያለ ግጭት መገለጫዎች መሆኑን ይገነዘባሉ። ሃጢአት በእኛ ውስጥ አድሯል። ይቆጣጠረናል። እናም ማድረግ የማንፈልገውን ነገር እንድናደርግ ያደርገናል። በውስጣችን መሰንጠቅ ይፈጠራል። እናም ራሳችንን የማንመስል ሌላ ፍጥረት ያደርገናል። የማንነት ቀውስ ውስጥ ይከተናል። ጳውሎስ ይህን በውስጣችን ያለ መከፋፈል ሁለት ጊዜ ጽፎታል። “የማልወደውን የማደርግ ከሆንሁ ግን ያን የማደርገው አሁን እኔ አይደለሁም፥ በእኔ የሚኖር ኀጢአት ነው እንጂ።” ይህ ውስጣዊ ግጭት በሕይወታቸው ዋጋ ያስከፈላቸው፥ እንዴት የልተጠበቀና አስደንጋጭ ሊሆን እንደሚችል ያውቃሉ። የሆነ ሃሳብ ወደ አዕምሮአችን ይገባል፥ ቃላት ከአንደበታችን ይፈሳል፥ ድንገት እና ያለምንም ማስጠንቀቂያ አንዳች ነገር አድርገን እንገኛለን። ያደረግነውን ነገር ዞር ብለን ስናይ ደግሞ፥ እንዲህ ዓይነት ስሜት ይሰማናል “ይህንን አይነት ነገር ያደረግኩት እኔ ልሆን አልችልም። እንደዚህ አይነት ነገር ላደርግ የምችል ሰው አይደለሁም። ምን እንደሆነ ልለየው የማልችለው፥ የሆነ ነገር በላዬ ላይ መጥቶብኝ ነው። ከመቀበል ውጪ አማራጭ የለኝም። ተሳስቻለሁ። ጥፋትን አጥፍቻለሁ። በርግጥ ነገሩን የፈጸምኩት እኔ ነኝ። ግን ያን ጥፋት ያጠፋው “እኔ”፣ ለእኔም እንግዳ እኔነቴ ነው። እውነተኛው እኔነቴ ይህ አይደለም። ትክክለኛው ውስጣዊ ማንነቴ ግን አይደለም። ይልቅ እኔ የማላውቀው የሆነ ኀይል ተቆጣጥሮኝ ነበር። አሁን ያወቅኩት ነገር ቢኖር ይህንን እኩይ ሰራ እንድሰራ ያስገደደኝ ሀይል ከሩቅ ቦታ ወደ እኔ የመጣ ሳይሆን ነገር ግን በውስጤ ያለ ኀይል ነው።”

ስለ ኀጢአት የምናውቀው በርግጥ ይህን ነው? ወይስ ከሆነ የሕይወት መንገራገጭ በኋላ ይህን እውቀት እንቀብረዋለን? ወይስ አሁንም ቢሆን በጎ ካልሆነ አኗኗር ራሳችንን በማራቅ በአንጻራዊነት ጥሩ ሰዎች የሚያሰኘንን የቤተሰብ፣ የማሕበረ ሰብ እና የሥራ ቦታ ህጎችን በማክበር በገነባነው መልካም አኗኗር የምንደገፍ ነን? በዚህ ማንነታችን ምክንያት ቅዱስ እና ንጹህ ሰው የሆንን መስሎ ይሰማናል? እንዲህ አይነት ሕይወት ስላላቸው ለሚረኩ ሰዎች ጳውሎስ የጻፈው ቃል ከንቱ ድካም ነው። እንደሰው ያሉበትን ትክክለኛ ሁኔታ ለመጋፈጥ የማይፈልጉ ናቸው። ነገር ግን ወደዱም ጠሉም አንድ ተጨማሪ ነገር በሕይወታቸው ውስጥ ሊሆን ይችላል። ይህም እግዚአብሔር ራሱ በትክክል ማን እንደሆኑ ያውቁ ዘንድ በኀጢአት ውስጥ እንዲነከሩ ሊጥላቸው ይችላል። ይህ ንግግር በድፍረት የተሞላ ንግግር ሊመሰል ይችላል። ነገር ግን ጥልቅ የሆነ መንፈሳዊ ልምምድ ውስጥ ያለፉ

ሰዎች የነገሩን ይህን ነው። የተናገሩት በዚህ መንገድ ነበር። እሱ ራሱ በሐጢያት ጭቃ ውስጥ ወርውሮ ከጣላቸው በኋላ፤ መልሶ ደግሞ የወደቀን በሚያነሳው እና በሚያድስ እጁ ከውድቀት እረመጥ አውጥቷቸዋል። በዚህ ሁኔታ ውስጥ ካለፋ በኋላ፣ ሁልጊዜ ሲያመልጡት የነበረውን ትክክለኛ ማንነታቸውን ጥርት ባለ ሁኔታ አይተዋል። እናም ከእውነተኛው ማንነታቸው መደበቅ ስላበቃ፣ ፍፁም በሆነ ሁኔታ ራሳቸውን ክደው፣፣ መልሱን ክርስትና ብቻ የሚሰጣቸውን ጥያቄ ጠይቀዋል። ይህ ከክርስትና የሚገኝ መልስ፤ "ራስን በመጥላት እና እኛነታችንን ባለመቀበል የሚመጣን ተስፋ መቁረጥ የሚያሸንፍ' ተቀባይነት የሌለውን የሚቀበል ኋይል አለ የሚል ነው። እንግዲህ ከዚህ አንጻር ካየነው በብዙ ድካምና ሀጢያት ውስጥ ማለፍ እውነተኛውን እና ውስጠኛውን እኛነታችንን እንድናውቅ በመለኮታዊ አሰራር ዕቅድ ውስጥ የተዘረጋ መንገድ ነው ብለን መውሰድ እንችላለን።

ቀጥለን ልክ ጳውሎስ እንደጠየቀው እንጠይቃለን:- ይህ ኀይል በውስጣችን መኖሪያ ስፍራ እንዲያገኝ ያደረገው ነገር ምንድን ነው? የጳውሎስ መልስ ሀጢያት በእኛ ውስጥ መሸሸጊያ ስፍራ ሊያገኝ የቻለው በብልቶቻችን ምክንያት ነው ይለናል። እንደገና ደግሞ ይህንን ስፍራ ሲጠራ"ሥጋ" እና አንዳንድ ጊዜ ደግሞ "ለሞት ታልፎ የተሰጠ ሥጋ" እያለ ይጠራዋል። ነገር ግን ይህንን ኀይል የሚቃወም ሌላ ጉልበት ሌላ ሀይል በውስጣችን አለ። "ሥጋን" የሚቃወመው ኀይል ደግሞ የእኛነታችን መሠረት የሆነው ውስጣዊ ማንነታችን (የእኛን ሃሳብ፣ ስሜት፣ እምነት፣ እሴት እና ስለራሳችን የምናውቀውን እውቀት አካቶ የያዘው የሰውነታቻን ክፍል)፣ አእምሮአችን እና መንፈሳችን ነው። አሁን በኛ ዘመን ያሉ ምሁራን የሰው ልጆችን በተመለከተ ለሚያደርጉት ጥናት የሚጠቀሙትን ቋንቋ ለመረዳት ከባድ እንደሆነው እንዲሁ፥ ጳውሎስ የሚለውንም ለመረዳት ቀላል ነገር አይደለም። ነገር ግን በአንድ ነገር እርግጠኞች ነን። ይህም ጳውሎስና ከሱ ጋርም ጠቅላላ የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እና የክርስትና አስተምህሮ፥ ሥጋ የለበሰውን አካላችንን አንድም ቦታ ላይ እኛ ከእግዚአብሔር፣ ከጉኡዘ ከምንኖርበት ዓለም እና ከእኛነታችን ለመነጠላችን ተጠያቂ ሲያደርጉን አናገኝም። ከእኛነታችን አንደኛው ክፍል ማለትም፥ አካላችን፣ ሥጋችን እና ብልቶቻችን ብቻ በሐጢያት የተበከሉ፥ ደግሞ ማለትም ውስጣዊ እኛነታችን፣ አእምሮአችን እና መንፈሳችን ሀጢያት የሌለበት የማንነታችን ክፍል አይደሉም። ውጫዊና ውስጣዊ ማንነታችን በጠቅላላ ሁለንተናችን፣ እያንዳንዱ የአካላችን ሴል፣ ሥጋና መንፈስ የሆነው እያንዳንዱ የአእምሮአችን እንቅስቃሴ፤ ለኀጢአት ኀይል ተገዝ ነው። መልሰው ደግሞ እነዚሁ ውጫዊና ውስጣዊ እኛነታችን የኀጢአትን ኀይል ከላያቸው ላይ ለመስበር ይታገላሉ። ራሳችን በሰራነው ሀጢያት

የመክሰሳችን ሀቅ የሚያሳየው፥ በእውነተኛው ማንነታችን በትክክል ማን እንደሆንን አሁንም ግንዛቤ እንዳለን እና ያ እውነተኛ ማንነታችንን መሆን እንደምንፈልግ ነው። የሆነ ነገር ካጠፋን በኋላ ምን እንዳሳሳተኝ እንጃ እንጃ እኔ እንዲህ አይደለሁም ብለን ለራሳችን ይቅርታ የማድረጋችን ተጨባጭ ሃቅ የሚያሳየው፥ ከእውነተኛ ተፈጥሮአችን ለመነጠላችን እውቅና ለመስጠት አለመቻላችንን ነው። ላጠፋነው ጥፋት የሚሰማን ሀፍረት የሚያሳየው አሁንም ቢሆን “የእኛ ትክክለኛ ማንነት ሌላ እንደሆነ” እንደምናውቅ ነው።

ልክ ከሰው ልጅ አካል በራሱ ቅዱስ እና ንፁህ የሆነ ክፍል እንደሌለ እንዲሁ፤ ከሰው ልጅ አካል በራሱ እኩይ የሆነ አካልም የለም። ይህንን እውነት ቸል የሚል የትኛውም ክርስቲያናዊ አስተምህሮ፤ ክርስትና ካገናፀፈን አብርሆት የጎደለ ነው። ከዚህ አንጻር ቤተ ክርስቲያን በታሪክ ውስጥ ይቅር የማይባል ስህተት ፈጽማለች። ሰዎች በደለኝነት ሊሰማቸው በማይገባ ጉዳይ በበደለኝነት ስሜት እንዲሰቃዩ፣ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ እንዲዳክሩ በማድረግ በሰው ልጆች ላይ ላደረሰችው ጥፋት ሃላፊነቱን ልትወስድ ይገባል። ክርስትያኖች፥ ሕይወት ያለው ነገር ለመባዛት እና ዘሩን ለመተካት በተፈጥሮ የታደለውን የሩካቤ ሥጋ ፍላጎትን፣ በራሱ ሀጢያት በማለት በየምስባኮቻቸው፣ በትምህርት ቤት እና በቤተሰብ መሃል ሲጠሩ እና ሲያስተምሩ ነበር። ከሩካቤ ሥጋ ጋር በተገናኘ የሰው ልጅ ያለበትን “ከተፈጥሮ የተዘበራረቀን ሁኔታ” መሠረት በማድረግ ክርስትና ያላስተማረውን ትምህርት በየቦታው ሲያደርሱ ነበር። በሁሉም ሕይወት ውስጥ ያለውን የፆታ ልዩነት እና የሩካቤ ሥጋን በተመለከተ ያለውን ጉዳይ እጅግ በማጋነን አረማዊ በሆነ መንገድ የሁሉ ነገር ማጠንጠኛ አድርገውት ነበር። የሰው ልጆች ከሩካቤ ሥጋ ጋር በተያያዘ ያለባቸው ችግር እንዳለው ሆኖ፤ መንፈሳዊ ማንነታችንም ችግር እንዳለበት እሙን ነው። ነገር ግን ለቤተ ክርስቲያን ለረጅም ጊዜ የሩካቤ ሥጋ ያህል ትዕቢትና ቸልተኝነት ትኩረት የሚሹ አደገኛ ነገር አይደሉም። ቤተ ክርስቲያን በሰዎች አእምሮ ውስጥ “ሀጢያት” ሲባል የሩካቤ ሥጋ ሀጥያት ብቻ ከፊት ለፊታቸው ድቅን እንዲል አድርጋ ስላለች። እንዲህ አይነቱ የሩካቤ ሥጋን የሕይወት ኋይል በዚህ መጠን ማስተጋባት በራሱ የጤነኝነት እጦት ነው። እንደዚህ ዓይነቱ አስተምህሮና ስብከት ጳውሎስ በመጽሐፍ ቅዱስ የሳለልንን የሀጥያት ሥዕል በሌላ የሚቀይር ሥዕል ነው። ጳውሎስ ኀጢአትን እንድንረዳ በት ካስቀመጠልን ምስል ጋር የሚጋጭ ምስል ነው። እጅግ በጣም የከፋው ደግሞ ይህ አይነቱ ስብከት፣ ሀጥያት የሚለውን ቃል ከሩካቤ ሥጋ የአንድ ሳንቲም ሁለት ገጽታ አድርጎ ማስቀመጥ ያመጣው ተጽዕኖ፣ ቆጥረን በማንዘልቃቸው ሰዎች ሕይወት ውስጥ በባዶ ሜዳ የበደለኝነት ስሜት

እንዲሰማቸው አድርጓል። የም የበደለኝነት ስሜት ከጥርጣሬ ወደ ጭንቀት፣ ከጭንቀት ወደ ተስፋ መቁረጥ፣ ከተስፋ መቁረጥ ለማምለጥ ወደ አዕምሮ በሽታ እንዲጓዙ ትልቁን ሚና ተጫውቷል። እና ብዙዎቹን ደግሞ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ራሳቸውን የማጥፋት ስሜት ውስጥ ከቷቸዋል።

እና አሁንም ቢሆን ስለ ሀጢያት የሚሰበከው እንዲህ አይነት ስብከት የመጣቸው መዘዞች ግልጽ ናቸው። በርግጥ ጳውሎስ ከሩካቤ ሥጋ ጋር በተገናኘ የሚፈጸመውን እርኩሰት፣ ሀጢያት የሰው ልጆችን እንዴት እንደተቆጣጠረ የመጨረሻው መገለጫ እንደሆነ አሳይቶናል። እኛ እንደ ክርስቲያን፣ ተፈጥሮን ሀጥያት ብለን በማርከስ እና የሐፍረት ምክንያት እንዲሆን በማድረግ፣ አሁን ያለው ሁኔታ እንዲፈጠር ከፍተኛውን ሚና ተጫውተናል ወይስ አልተጫወትንም ብለን ጠይቀን እናውቃለን? ከዚህ በስህተት ከተሞላ እና ሐጢያትን በተዛባ መንገድ ስሎ ካስቀመጠ መረዳት የተገኘው ውጤት፤ ተቃርኖ እና ግጭት ነው። ተፈጥሮ እንኳን ከሚያስተምረው ተጨባጭ ሀቅ ጋር ይጋጫል። ከተጨባጩ ሀቅ ጋር ብቻ አይደለም ነገር ግን መጽሐፍ ቅዱስ የሰው ልጅ ማንነቱ ውስጥ አለ ብሎ ከሚያስተምረው ችግር ውጭ የሆነ ችግር በመፍጠር ከቅዱስ መጽሐፍም ጋር ይጋጫል። ሀጥያትን በትክክል እንዳንረዳ አድርጎናል።

ስለ ሀጢያት መስበክ አደገኛ ነው። ምክንያቱም ስለኀጢአተኝነታችን እያሰብን መጨነቅ ሊያስከትል ይችላል። ምናልባትም ፈጽሞ ስለ ሀጢያት አለመስበክ ይመረጣል። እኔ ራሱ በዚህ ጉዳይ መስበክ አለብኝ የለብኝም እያልኩ ሳመነታ ብዙ ዓመት ቆይቻለሁ። ነገር ግን ኀጢአተኝነት እየጨመረ እንዲመጣ ያደረጉ የተዛቡ አስተሳሰቦችን ለማስተካከል አንዳንዴ ደፋር እርምጃዎችን መውሰድ ይጠይቃል። ምክንያቱም የተሳሳቱ አስተሳሰቦችን ያለማቋረጥ የምናስተናግድ ከሆነ፤ ያልተገባ ኑሮ የመኖር እድላችን ሰፊ ነው። በተሳሳተ ጎዳና መጓዛችን የማይቀር ጉዳይ ይሆናል።

በኀጢአት ላይ ማተኮር የሚያስከትለውን አሉታዊ ውጤት ማሸነፍ እንደሚቻል አምናለሁ። ሐጢያትን መቋቋም በሚያስችለን ብርሃን በኩል በተዘዋዋሪ መንገድ የምንመለከት ከሆነ ብቻ ነው። በኀጥያት ላይ በማተኮር የሚመጣን አሉታዊ ውጤት እንድናሸንፍ የሚያስችለን፤ እንደገና ወደነበርንበት መመለስ ነው። እንደገና ወደነበረንበት መመለስ የነጠለንን ነገር እንድናሸንፍ ያደርገናል። ሀጢያት ማለት በእግዚአብሔር ሕይወት ውስጥ ካለን ተሳትፎ መሸሽ ማለት ነው። እኛነታችን ከተገኘበት እና እንደገና ከምንመለስበት ሕይወት ጋር ያለንን

ሕብረት መበጠስ ማለት ነው። ሀጥያት ማለት እኔነትን የሁሉ ነገር መጀመርያ እና መጨረሻ ማድረግ ማለት ነው። እኛነታችንን የሁሉ ነገር ማጠንጠኛ እና ግብ አድርጎ ማስቀመጥ ማለት ነው። ሃጢያት ሁሉን ነገር ለራሳችን እንድናግበሰብስ የሚያደርግ በሁሉም ሰው ውስጥ ያለ አንቀሳቃሽ ሞተር ነው። ራሳቸውን በመግዛትና በጭምትነት ለመመላለስ ጥረት በሚያደርጉት ላይ እንኳን ሥራውን ይሰራል። ግን ይህንን ሙሉ በሙሉ ማወቅ የምንችለው ከራሳችን በላይ የሆነ የሕይወት ደረጃ ላይ በሆነ ያህል መጠን ስንደርስ ነው። እርሱነቱን ካጣ በኋላ መልሶ ያገኘ ራስን ማጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ በጥልቀት ያውቃል። እንደገና ወደ እግዚአብሔር ሕይወት ተመልሰን ከእግዚአብሄር ሕይወት ተነጥለን የነበርንበትን ሕይወት የምንመለከተ ከሆነ፣ ከጭንቀትና ፍርሃት ነጻ ወጥተን ራሳችንን እናገኘዋለን። ስለ ሀጢያት መናገር እንችላለን። ምክንያቱም ሃጢያት በኛ ላይ ያለው ኃይል ተሰብሯል።

በርግጥ የኀጢአት ኃይል ከእኛ እና በእኛ ጉልበት አይሰበርም። ጳውሎስ የኀጢአትን ኃይል በመልካም ሥራችን ከላያችን ላይ ለመስበር መሞከር ማለት የእግዚአብሔርን ሕግ በራሳችን ኃይል ለመፈጸም እንደመሞከር ነው በማለት ይገልፀዋል። የእግዚአብሔርን ሕግ በአእምሯችን፣ በውስጠኛው እኛነታችን ውስጥ ያለው ሕግ ማለት ነው። የዚህ ሙከራ ውጤት የሚሆነው ውድቀት፣ በደለኝነት እና ተስፋ መቁረጥ ነው። ህጉ በውስጡ ከያዘው ትዕዛዛትና ክልከላዎች ጋራ፥ እኩይ ምንድነው የሚለውን ለመረዳት እና እኩይን ባለበት ለማቆም ጥቅሙ እንዳለ ሆኖ፥ ሕጉን ባወቅንበት ቅጽበት ሕግ መተላለፍም አብሮ ይወለዳል። ቅዱስ ጳውሎስ በቅኔያዊ ለዛ ባማረ እና ሥነልቦናዊ መረዳቱ ጥልቅ በሆነ ቋንቋ ሲናገር “በሰውነታችን የብልት ክፍሎች ውስጥ የነበረው ኀጢአት፥”አታድርግ አድርግ”የሚለውን የሕጉን ቃል ሰምቶ እስከሚነቃበት ወቀት ድረስ በጥልቀ እንቅልፍ ውስጥ እንዳሸለበ ነበር” ይለናል። ሀጥያት ህያው እንዲሆንና ሥራውን እንዲሰራ የግድ መጠቀም የሚችለው ትእዛዛቱን ነው። ክልከላዎች የተኛን ፍላጎት ከእንቅልፍ ይቀሰቅሳሉ። ሕጉ የአጥያትን ኃይል ይቀሰቅሳል እና “ይሄ ነገር ሀጢአት ነው?”የሚል ንቃተ ኅሊና ይፈጥራል። ነገር ግን የኀጢአትን ኃይል መስበር አይችልም። የሀጥያት ኃይል ሊሰበር የሚችለው፥ የኀጢአትን ኃይል የሰበረውን መልእክት፥ በሁለንተናችን ማለትም በሥጋ፣ በነፍስና በመንፈስ ስንቀበል ብቻ ይሆናል። ያን ጊዜ የኀጢአት ኃይል በውስጣችን ይሰበራል።

የሐጢያት ምስል ቀፋፊ፣ በመከራ የተሞላና የሃፍረት ምስል ነው። በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ድራማ እና ግለቱ በማይበርድ እንቅስቃሴ የታጀበ ምስል

ነው። ከእኛ የሚልቁ ኀይሎች የሚፋለሙበት የጦርሜዳ ሆነን የምንታይበት የእኛው ምስል ነው። ሀጢያት የሰውን ልጆች ጥቁር እና ነጭ፤ መልካም እና እኩይ ብሎ አይከፋፈልም። ሐጢያትን እንዳታደርግ እያለ ጣቱን ቀስሮ እንደሚያስፈራራ ባለስልጣን ሆኖ አይገለጥም። ነገር ግን በዚች ትንሽ ፕላኔት በምድራችን ውስጥ በአካላችን እና በአዕምሯችን ውስጥ የሚከሰት ነገር ግን አሻግሮ አንድ እጅግ ወሳኝ የሆነ ጉዳይ እንዳለ የሚጠቁም ነገር ነው። ሃጢአት የሰው ልጅ በአጽናፈ ዓለም ውስጥ በእያንዳንዱ ደቂቃ ወሳኝ የሆነ ነገር ወደ ሚከሰትበት ደረጃ ይዞ የሚወጣ ነገር ነው። የሰው ልጅ በሐጢያት መኖር ምክንያት ውስብስብ ከሆኑ መንፈሳዊ፣ ሥጋዊ እና ዘላለማዊ ከሆኑ ጉዳዮች ጋር ወደሚታገልበት ሕይወት ለመግባት ይገደዳል። ይህ ክስተት ደግሞ ህልውና ላለው ሁሉ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሆነውን ትርጉም የሚያገኝበት ወሳኝ ነገር ነው። በእያንዳንዳችን፣ በእኛ ውስጥ እና በእኛ ዙሪያ፣ እንደዚህ ዓይነት ውሳኔዎች ይከሰታሉ። እያንዳንዷ በየደቂቃው ውስጥ የምንወሥናት ውሳኔ ከፍ ያለ ነገር የያዘች ነች። ይህ የተሸከምነው ቀንበር ነው። ተስፋ መቁረጥ የሚያገኘን በዚህ ነው። ታላቅነታችንም በዚህ ውስጥ ነው።

# 3. መርሳት እና መረሳት

*“ነገር ግን አንድ ነገር አደርጋለሁ፤ በኋላዬ ያለውን እየረሳሁ በፊቴ ያለውን ለመያዝ እዘረጋለሁ፥”*

*ፊሊፒሲዩስ 3፡13*

ጳውሎስ በመልዕክቶቹ ውስጥ ስለ ግል ሕይወቱ ከተናገረባቸው ቦታዎች አንዱ የሆነው እና፥ በዚህ መልዕክት ውስጥ ተጽፎ የምናገኘው ስለ ራሱ የሕይወት ልምምድ የሚያወሳው ቃል ይህንን ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል። ሊረሳ ፈልጎ የነበረው ምንድን ነው? በዛውም ምንድን ነው የምንረሳው? እና ማስታወስስ ያለብን ምንድን ነው?

ግን ደግሞ እነዚህን ጥያቄዎች አንስተን ስንጠይቅ፥ እጅግ የሚያናውጥ ሌላ ጥያቄ ወደ አዕምሮአችን ይመጣል፦ መረሳት ማለት ምን ማለት ነው? ለነገሮች፥ ሕላዌ ላለው ነገር መረሳት የሚያመጣባቸው ነገር ምንድን ነው?ከማንነታችን ከፍሎ፣ ወይም ሙሉ ለሙሉ፥ ወይም ደግሞ ለተወሰነ ጊዜ ያህል ብንረሳ፥ በእኛ ሕይወት ውስጥ ምን ትርጉም የመጣል? ለዘላለም እንረሳ ይሆናል የሚለው ሃሳብ በሕይወታችን ውስጥ የሚፈጥረው ስሜት ምንድነው? ሰባኪው፥ ሙታን “መታሰቢያቸውም ተረስቶአልና” “ፍቅራቸውና ጥላቻቸው ቅንዓታቸውም በአንድነት ጠፍቶአል”፥ መዝሙረኛው ደግሞ ጨምሮ ‘ይኖሩበት በነበረበት ቦታ፥ ከዚህ ወዲያ እዚህ እንደነበሩ አይታወቅም” የሚለውን ቃል ስንሰማ ውስጣችን ይህንን ቃል እንዴት ይረዳዋል? ተቋቁመን መስማትስ እንችላለን?

“መርሳት” የሚለው ቀላል ቃል፣ ወደ ሕይወት እና ሞት፣ ጊዜ እና ዘላለምን በተመለከተ ወደ አለው እንቆቅልሾች ዘንድ ይዞን ይሔዳል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በብዙ ቦታ ተጠቅሶ እናገኘዋለን። “መርሳት እና ማስታወስ” እጅግ አስደናቂ የሆነ በሰው ልጅ ውስጥ አምሳለ እግዚያአብሔር የተገለጠበት ማንነት ነው። በእኛ ውስጥ፥ አምሳለ እግዚያአብሔር እንዳለ ከሚገለጥበት አስደናቂ ባሕሪ መካከል “መርሳት እና ማስታወስ” ዋነኛ ነው። አሁን፥ መርሳት እና ማስታወስ፥ ደግሞም

መረሳት ምን ማለት እንደሆነ የተዘጋውን ሳጥን ከፍተን፣ ውስጠ ሚስጥሩን መፈተሽ ላይ እናተኩራለን። አስቀድመን ማወቅ ያለብን ነገር ይህን ውስጠ ሚስጥር ፈትሸን በቃላት ለማስረዳት ቃላት ደካማ እንደሆኑ፣ የማስተዋል አቅማችን የቱንም ያህል አስደናቂ ቢሆን፣ እድሜ ዘመናችንን ብንመረምር፤ ተረድተን የማናጠናቅቀው መሆኑን መገንዘብ አለብን። ነገር ግን "የመርሳት" እና የ"ማስታወስ" ን ሚስጥር ለመረዳት የማንሰንፍ ልበ ብርቱዎች መሆን ይጠበቅብናል። አስቀድመን "መርሳት" እና "ማስታወስ" የሚለውን ጊዜ ወስደን እንይ። ቀጥለን "መረሳት" እና ምናልባትም "መታወስ" የሚለውን እናያለን።

# 1.

ሕይወት መቀጠል የሚችለው፣ ያለፈው አልፏል ብለን፣ ከዛሬአችን ላይ “ከትላንትና ለዛሬ” የተላለፈን ሸክም ስናስወግድ ብቻ ነው። ዛሬን ላይ፣ የትላንት ጉዳይ ይዘን የምናመነኝክ ደካሞች ከሆንን፣ ሕይወታችን “ነገ የሚባል አዲስ ቀን የሌለው”፣ ተስፋ ቢስ ነው። በትላንት ጣጣ ውስጥ በባርነት ተይዞ የሚማቀቅ ሕይወት ይሆናል። አዲስ ነገር ብንፈልግ እንኳን በሕይወታችን አይሆንም። አንለቅም ብለን የያዝነው አሮጌ ነገር እንኳን ባለበት አይቆይም። ዛሬ አሮጌ የምንለው ነገር በአንድ ወቅት አዲስ ነገር ነበር። አሁን አሮጌ ሆኗል። ለአዲሱ ነገር ደግሞ ቦታ መልቀቅ ግድ ነው። ስለዚህ አንለቅም፣ አንተውም ያልነው አሮጌው ነገር እንኳን አብሮን ሊሆን ላይሆን ይችላል። አዲስ ነገር የማንቀበል ከሆነ ባዶ ነው። አሮጌውም ቢሆን አብሮን አይሆንም። እድሜ ዘመናችንን ይዘነው የምንጓዘው አሮጌው ነገር እንኳን ከሕይወታችን በኖ የሚጠፋ ይሆናል። በሕይወታችን ውስጥ የትላንቱን ወደ ትላንት ትተን የማንጓዝ ከሆነ፣ ሕይወታችን ምንም ጠብ የሚል ነገር የሌለው፣ በማይቻል ነገሮች የተሞላ ይሆናል። ሰቀቀን እና ስቃይ ነው። ይህን ለመረዳት ተፈጥሮን ማየት ጥሩ ነው። የእያንዳንዱን እፅዋት እና እንስሳ፣ ከመነሻው እስከ ፍጻሜ ያለውን የእድገት ሒደት ብንመለከት፣ ተፈጥሮ ለመጪው ቦታ እንዲኖር አሮጌውን የምታስወግድበት ኋይል እንዳላት እናያለን። ግን ይህን ስንል ሁሉም ነገር፣ የትላንት የተባለ ሁሉ ተወግዶ፣ ከዜሮ ይጀመራል እያልን አይደለም። ይልቅ አዲስ መጪው ወደፊት እንዲሔድ ወይም እንዲያድግ፣ የሚነሳበት መሠረት ስለሚያስፈልገው ከትላንት፣ ከአሮጌው ለአዲሱ አስፈላጊ የሆነው፣ ባለበት ቦታ ይቀጥላል። ሁሉም አይነት እድገት ዛሬ የደረሰበት ደረጃ ለመድረስ፣ የተከፈለውን ዋጋ የሚያሳይ፣ ሁልጊዜ ቆሞ የሚታይ ምልክት አለው። አንዳንዴ ይህ ምልክት ለዕድገት ተብሎ የተከፈለን ዋጋን የሚያሳይ ቁስልም ይሆናል። ሕይወት ገፍታም ቢሆን የራስዋን መታደስ እውን ለማድረግ፣ ትላትናዋን እና ያለፈችበትን ውጣ ውረድ እርስ በርስ ታፋጫለች። በትላንት ውስጥ የሆነውን ከመሸሸ፣ ፊት ለፊት በመጋፈጥ እና ወደፊት እንዳይመጣ መንገድ በመዝጋት፣ ከፊት ብሩህ ቀን እንዲመጣ ታደርጋለች። በዚህ የእድገት ሒደት የሰው ልጅም ሕይወት ከነገሮች ጋር ሁሉ የተዋሃደ መሆኑን እናያለን። ሕይወት ያላቸው ነገሮች ይህን መንገድ ተገነዘቡም አልተገነዘቡም፤ ይህ ሕይወት ባላቸው ሁሉም ላይ፣ በሁሉ ጊዜ እና በሁሉም ቦታ የሚሰራ የሕይወት ሕግ ነው።

ስለዚህ ጉዳይ ግንዛቤ ሊኖረው የሚችለው የሰው ልጅ ብቻ ነው። ሰዉ

“ከትላንትናው” እንዳይጠፋ የፈለገውን “ማስታወስ በሚባል ማህደር ውስጥ ያስቀምጣል። መልሶ ደግሞ፣ ከትላንትና ወደ ትላንት መወርወር ያለበትን “መርሳት” በሚባል ጆንያ ውስጥ ወደ ኋላ አርቆ ይወረውረዋል። በሁሉም የእድገት ሂደት ውስጥ የሚከሰተው፣ እንዲህ አይነት ተመሳሳይ ነገር ነው። አንድ ህፃን በአካል እና በመንፈስ የሚያድግበት መንገድም ይህ ነው። መጥፋት የሌለበትን ነገር ወደነገ ይዞ ይቀጥላል። ወደ ቀጣዩ መሄድ የሌለበትን ነገር ወደኋላ ይጥላል። ያስታውሳል፤ ይረሳል። በሁሉም የጤናማ ዕድገት ሒደት ውስጥ፣ በሁለቱ መካከል ያለው ሚዛን በአግባቡ የሚጠበቅ ከሆነ፣ ሕይወት እለት በእለት ወደ አዲስ ነገር የሚሄድ እና የሚሻሻል ይሆናል። ከትላንትናችን ላይ ከሚያስፈልገው እና ከምንችለው በላይ ተሸክመን ወደ ዛሬ ማምጣት የለብንም። በሌላ መልኩ መርሳት ከነበረብን ጥቂቱን ብቻ የምንተው ከሆነ፣ የእድገታችን መንገድ አባጣጎርባጣ ይሆናል። በውስጡ ከያዘው ቀላል ከሚመስል ጉልበት እና ትውስታዎቹ ጋራ ትላንትናችን ነጋችንን የመጫን ኋይል አለው። ይሄ ለሁላችንም ግልፅ ነው።

በሁለንተናችን አንዳንድ ክፍተቶች መሀል ተሰግስገው የምናገኛቸው መቅረት የነበረባቸው የትላንት ነገሮች አሉ። አንዱ መተው፣ መርሳት የነበረብን የልጅነት ጠባይ ነው። ነገር ግን ጎልምሰን እንኳን እንዳለቀቀን እና በተለያየ ወቅት በእኛ ላይ ሲንፀባረቅ እናገኛለን። በእድገታችን መንገድ ላይ የሆነ ቦታ ተቆርጠው መቅረት ነበረባቸው። አሁንም አብረውን ያሉ የልጅነት ጠባዮች፣ ወደፊት እንዳንገሰግስ ነፃነታችንን ገድበው፣ ትልቅ እንቅፋት እንደሆኑ አሉ። አለፍ ብሎም የተወለጋገደ አግድም ያደገ ሰው ያደርጉናል። በልጅነታችን የነበሩ አሁንም በድርጊታችን እና በንግግራችን ውስጥ ከሚገኙ፣ ልማዶች መካከል አንዳንዶቹን እናንሳ። በዚህ በጉልምስናችን ዘመን ያለ “አኩራፊነት” እና ምክንያታዊነትን በመቃረን “በቃ ምንም ነገር ይሁን አልፈልግም” ባይነት አንዱ ነው። በቂ ምክንያት በሌለው ነገር ሁሉ ዱላ እና ጠብ ወዳጅነት ሌላው የህፃንነት ጠባይ ነው። ልጆች ሳለን “ከተጨባጩ ዓለም ብዙ ማይል የራቀ ስለራሳችን እና ስለምንኖርበት ዓለም ያለን ግንዛቤ” አሁንም አብሮን መኖርንም መጥቀስ እንችላለን። አሁንም አቅፈን የያዝነው በእድሜ ብስለት መወገድ የነበረበት “ተፈፃሚነት የሌላቸው ሞኛ ሞኝ መሻቶች እና መሠረት የሌለው ጭንቀት” እርሱም ከትላንት የመጣ ዛሬ መኖር ያልነበረበት ነው። ጨምረን እንነይ ካልን፣ አሁንም በዚህ በጉልምስናችን “ልክም ይሁን አይሁን” የተንጠላጠልንበት የእናት አባቴ የምንለው የአኗኗር ዘይቤ ሌላው ነው።

ያለ ምንም በቂ ምክንያት፥ አሁን ካለንበት የእድገት ደረጃ አንፃር መኖር ያልነበረበት፥ ከልጅነታችን ጀምሮ በውስጣችን የተቀመጠ ለተለያዩ ነገሮች ያለን ጥላቻም ሌላው ሳንጠቅስ የማናልፈው የጨቅላነት ባሕሪ ነው። በሕይወታችን መረሳት የሚገባቸውን ጉዳዮች ለመርሳት ሞቶ የነበረ ጊዜ አጋጥሞን ነበር። ቢሆንም ድፍረት አጣን። በርግጥ የረሳናቸው ነገሮች አሉ። ቢሆንም ነገሩ ራሱ ከአዕምሮአችን ተኖ፥ መረሳቱ የማይቀር ነገር ነው የረሳነው። ብንረሳም ብናስታውሰም ክፋም ይሁን በጎ ተጽዕኖ የሌላውን ነገር ነው የረሳነው። እንደውም እረሳን ከምንል ራሱ ከትውስታችን ጠፋ የሚለው ልክ ነው። አቅደን እና አስበን መርሳት የነበረብንን ጉዳዮች አሳድረናቸው አሁን ለመርሳት ብንፈልግ እንደዘገየን ግልፅ ሆኖልናል።

በትወልድ ቅብብል ከትላንት የወረደውን ሁሉ ዛሬም ተሸክመን ካልኖርን የሚሉ፥ የትላንቱን ለትላንት መተው ዳገት የሚሆንባቸው ሐገሮች አሉ። ሲወርድ ሲዋረድ የመጣውን ነገር ሁሉ ሳይከለስ ሳይበረዝ መቀጠል አለበት በሚል ግትርነት ብዙ ነገር ያጡ ሐገሮች አሉ። በዚህም ግትርነት ሳቢያ ዘመን ካመጣው ሊቀበሉት ይገባ ከነበረው አዲስ ነገር ራሳቸውን አገደሉ። የትላንት የታሪክ፣ የባህል እና የአኗኗር ቀንበር አዲስ ቀናቸውን፣ አዲስ ዘመናቸውን አጨለሙ። እናም ለውርደት እና ሽንፈት ታልፈው ተሰጡ። እና አንዳንድ ጊዜ ቤተ ክርስቲያን ሌሎች ሀይማኖቶችን ጨምሮ መጣል፣ መተው እና መርሳት የነበረባቸውን ብዙ ኮተታኮተት ይዘው፥ መተው ከነበረባቸው ጥቂቱን ብቻ ትተው አሁን ድረስ መዝለቅ ነበረባቸውን ብለን እንጠይቃለን። በርግጥ የሰው ልጆች ከገነባቸው እድሜ ጠገብ ብዙ አይነት ተቋሞቻቸው ውስጥ እንደ ሀይማኖት መርሳት የሚገባን ነገር ለመርሳት ዳገት የሚሆንበት የሰው ልጆች ተቋም የለም። እግዚያአብሔር የትላንቱ የመነሻችን አምላክ ብቻ አይደለም ነገር ግን የአዲሱ ነገር፣ የመዳረሻችንም አምላክም ነው። እርሱ እግዚያአብሔር የጥንቱንም እንዳበጀው የአዲሱ ነገርም ፈጣሪ ነው። እርሱ ለፍጥረት ሁሉ መኖሩ የሚታወቅበትን ህልውና ሰጥቶታል።

ምንም እንኳን ህልውና ያለው ነገር ሁሉ መነሻ ቢኖረውም በሌላ መልኩ ደግሞ ህልውና ያለው ነገር ወደፊት ይጓዛል። ስለዚህ ፍጥረት ሁሉ መረሳት ያለበትን መርሳት እንዲችል የመርሳትን ስጦታ ተቀብሏል። ይህን የመርሳት ስጦታ በአግባቡ ተጠቅማ መተው እና ወደትላንት ማህደር ውስጥ መከተት ያለበትን፣ ማስወገድ ያለባትን ጉዳይ የማታስወግድ ቤተ ክርስቲያን መሆን የሌለባትን ትሆናለች። እና ሁሉም በየዘመናቱ በወደቁበት ወጥመድ ውስጥ ትወድቃለች። ክብሯ የሆነው

የእግዚያአብሔር ህልውና ሽሽቷት እራሷን በራሷ የምታመልክ ባዶ ስብስብ ትሆናለች። ይህ ማለት ግን፣ የመርሳትን ፀጋ ትለማመድ ሲባል ያላትን ነገር ሁሉ ትተው ማለት አይደለም። ማንነቷን ትርሳ ሁሉን ነገር እየጣለች ከአዲስ ትጀምር ማለት አይደለም። ለቤተ ክርስቲያን ብቻ አይደለም ነገር ግን ለግለሰብም ሆነ ለሀገር መርሳት ማለት መለያን ቀለምን ማንነትን ማጥፋት ማለት አይደለም። ስማችንን፣ መለያችንን እና የማንነታችንን መገለጫ እንድንረሳ አልተጠየቅንም። በተለይ ቤተ ክርስቲያን መሠረቷን እንድትረሳ ፈፅሞ የተገባ አይደለም። ነገር ግን በዛ መሠረት ላይ የደራረበቻቸው ብዙ ልምምዶች እና ባህሎችን እየተወች የማትሄድ ከሆነ ነገዋን ታጣለች።

ነገር ግን ፍጥረት ሁሉ፣ የሰውን ልጅ ጨምሮ የሚኖረው ወደኋላ በመጣል ብቻ አይደለም። ጠብቆ ማቆየትም አለ። መርሳት ልክ ነው ግን መርሳት ብቻ አይደለም፤ ማስታወስም አለ። ማስታወስ አለመቻል ብዙ ጥፋት እና ጉዳት እንደሚያስከትለው እንዲሁ፤ መርሳት አለመቻልም ጥፋት እና ጉዳት ያመጣል። አንድ እድሜ ጠገብ ዛፍን ብንመለከት የሚያሳየን ነገር አለ። የመጨረሻ የእድገቱን ጣራ የሚወሥነው መጀመሪያ የተዘራው ዘር ነው። ዛሬ ያ ዛፍ ትልቅ ከሆነ በኋላ ያ የመጀመሪያ ዘር የት ነው? ዛሬም ያ ዛፍ ቆሞ መታየቱ ያ የመጀመሪያ ዘር እንዳልጠፋ ምስክር ነው። አንድ እንስሳ ሀ ብሎ ሕይወትን ሲጀምር እና ድክ ድክ ሲል ምግቡን እንዴት እንደሚያገኝ ራሱን ከአደጋ እንዴት እንደሚጠብቅ የተማረውን ዛሬ ትልቅ ሲሆን ከረሳ በሕይወት መቆየት አይችልም። ለሰው ልጅም ህጉ ያው ነው። አንድ ህፃን ሲወለድ ብቻ ሳይሆን በኋላ በአዕምሮ እና በአካል ሲበስልም የህፃንነቱ መሠረት አይጠፋም። እንደሱ ካልሆነ እና ሁሉን ከዜሮ የሚጀምር ቢሆን ኖሮ ራሱን በራሱ የዘነጋ ይሆን ነበር። ይህ መርህ ለሁሉም ማሕበረ ሰብ እና ቡድኖች ይሰራል። አዲስ ነገር በሚል ጥድፊያ መዘዞ ምን እንደሆነ ሳንመረምር ወደፊት መገስገስ፣ የትላንት እና አሮጌ ነው የተባለውን ሁሉ እየነቃቀሉ መጣል በኋላ ጣጣው ከባድ ነው። ቀለም እና ቅርፅ የሌለው፣ ክብር የራቀው፣ ባዶ እና ነገው የወደፊቱ የተነጠቀ መሆን ነው። አሮጌውን ነገር ያረጀ ያፈጀ ያሉትን ልምምድ ለመርሳት ባላቸው ከፍተኛ ፍላጎት፥ ጫራሹንም ምንጫቸው፣ መሠረታቸው ምን እንደሆነ ከአዕምሮአቸው መዝገብ የተፋቀ አብያተ ክርስቲያናት አሉ። ከትላንትናቸው የተቆራረጡ ወግ እና ባሕላቸውን ሁሉ ጠርገው ያጠፉ ሐገሮች አሉ።

ምናልባትም በዚህ ረገድ ጎልተው ከሚታየት መካከል ዋነኛ ምሳሌ የምትሆነን አሜሪካን ነች። መሠረቱ እየሩሳሌምና አቴንስ የሆነውን የስልጣኔያችንን

ምንጩ ለመርሳት፥ ሙሉውን የውቅያኖስ ውኀ እንደ መርሻ መዳህኒትነት የጠጣን ሕዝቦችን ነን። በአንድ በኩል ከአይሁድ እና ከክርስትና፤ በሌላ በኩል ከግሪክ የፈለቀውን የስልጣኔአችንን አስተሳሰብ እና ዕይታ አሽቀንጥረን ለመጣል ያስችለናል፤ ለመርሳት ይረዳናል ብለን ያልነውን ሁሉ ጠጥተን የሰክርን ነን። እየተናገርኩ ያለሁት ከትላንት ስለወሰድነው ምሑራዊ ዕውቀት አይደለም። ከእዚህ አንፃር ጉድለት የለብንም። እየተናገርኩ ያለሁት ይህንን ሐገር ወደፊት ለማራመድ ካለው ጥድፊያ የተነሳ፥ ዛሬ የሆነውን እንድንሆን ያበቁንን የትላንት መሠረት ሁሉ፥ ከስሩ ነቅሎ ለመጣል እያደረግን ስላለው ነገር ነው። ከማንኛውም ህዝብ በተለየ ህዝባችን አንድ ነገር ሙጥኝ ብሎ ይዞ ባለበት የሚቆም አይደለም። ምንም ነገር ይሁን የመተው አቅሙ እጅግ ከፍተኛ ነው። ነገር ግን ይህ ጠንካራ የመርሳት ችሎታችን ከማስታወስ ችሎታችን ጋር ሚዛኑን የጠበቀ አይደለም። ሁልጊዜ ማስታወስ ባለብን ጉዳይ ላይ ደካማ በመሆናችን፥ ሚዛናችን የተወላገደ ነው። ምናልባትም ለፖለቲካ እና መንፈሳዊ ኑሮ ላይ ለመውደቃችን ዋና ምክንያት ይህ ሳይሆን አይቀርም። እንደህዝብ ማንነታችንን ከጣልን፣ ከረሳን ውድቀት እንደሚገጥመን ግልጽ ነው።

## 2.

መርሳት ማለት ሕይወት ራሷን ወደ ተሐድሶ፣ ለተሻለው ነገር የምትገፋበት መንገድ ነዉ በለን ወስደናል። እንግዲህ እንደርሱ ከሆነ ምንድን ነዉ መርሳት ያለብን፤ እንዴት ነው የምንረሳው? ወደፊት ያለውን ለመያዝ ከፍተኛ ጥረት ውስጥ በነበረበት ጊዜ የረሳው ነገር ምንድን ነበር? አንደኛው ፈሪሳዊ እና የክርስትና አሳዳጅ ሆኖ ያሳለፈውን ሕይወቱን ለመርሳት ከፍተኛ ጉጉት እንደነበረው ግልፅ ነው። ነገር ግን በእያንዳንዱ ደብዳቤዎቹ ውስጥ ያሰፈራቸው ቃል ያን ሕይወቱን እንዳልረሳ ማረጋገጫ ይሰጡናል።

እንደው በግርድፉ ስንመለከት የተለያዩ አይነት የመርሳት አይነቶች እንዳሉ እናያለን። በተፈጥሮ የትላንቱን ቀን እና በትላንቱ ቀን ውስጥ ያደረግናቸውን ነገሮች መርሳት የመጀመሪያው ነው። እንድናስታውስ ግድ የሚለን ነገር ካለ፣ አንዳንዶቹን ዛሬም እናስታውሳቸው ይሆናል። ነገር ግን ቀስ በቀስ ከአዕምሮአችን ውስጥ ይጠፋሉ። የቀኑ ውሎአችን ከአዕምሮአችን እንደጤዛ ተኖ ይጠፋል። አስፈላጊ የሆነው ነገር ብቻ ከትውስታ ማህደራችን ላይ ይቀራል። ከዚህ አንፃር በሕይወታችን ውስጥ አብዛኛዎቹ ቀናቶች በመርሳት ውቅያኖስ ውስጥ ሰምጠው የሚጠፉ ናቸው። ልክ በአካላችን ውስጥ ያለዉ የደም ዝውውር በራሱ ሂደት እንደሚሰራ፣ እንዲህ አይነት ተፈጥሯዊ የመርሳት ሂደት፣ የእኛን ድጋፍና ትብብር ሳይፈልግ እንዲሁ በራሱ የሚከናወን ነው።

ለብዙዎቻችን እንግዳ ያልሆነ ሌላ አይነት የመርሳት ገጽታ ደግሞ አለ። ለምሳሌ ስለሆነ ነገር ማስታወስ ብንፈልግና ነገር ግን የምናስታውሰው ነገር ቁስላችንን የሚያመረቅዝ እና ችግር ውስጥ የሚከተን አይነት ቢሆን በውስጣችን ያለ አንዳች ነገር ያንን ጉዳይ ከማስታወስ ይከለክለናል። የሆኑ ጥቅማጥቅሞችን እናገኛለን ነገር ግን ውለታ ለመመለስ የምናደርገው ነገር እንደሌለን ባወቅን ጊዜ “እንግዲህ አልሞት” በሚል ብሂል ነገሩን በመርሳት እንገላገላለን። የፍቅር ግንኙነታችን የሰመረ እንዲሆን አሟልተን እንድንቀርብ የተጠየቅነው ነገር ከአቅማችን በላይ የሆነ በመሆኑ፤ የቀድሞዉን ፍቅር ረስተናል። ውስጣችን ያለውን ጥላቻ አምቀን ብንይዝ፣ በውስጣችን እንዲያድግ ብንተወው ለአዕምሮ መታወክ ይዳርገናል፤ የቀድሞዉን ጥላቻ ረስተናል። የውስጥ ህመማችንን ትተናል ምክንያቱም አሁንም የቁስሉን ጥዝጣዜ መሸከም ስለማንችል ነው። የበደልን ክስ ተሸክሞ መኖር አቅማችን ስለማይችል፤ የቀድሞዉን በደል እረስተናል። በርግጥ

ይህን መሰል መርሳት፥ ባጋጣሚ መንግድ ላይ ያገኘነውን ሰው፥ በነጋታው ማግኘት አለማግኘታችንን እንደምንረሳው ወይም በቀን ውስጥ ሻይ ወይ ቡና መጠጣት አለመጠጣታችንን እንደምንረሳው አይነት ተለምዶአዊ መርሳት አይደለም። አስበን እና ፈቅደን የምናደርገው ነገር ነው። ልንቋቋመው ያልቻልነውን ነገር በመርሳት ከፊታችን ዞር እናደርገዋለን። በውስጣችን በመቅበር እንረሳዋለን።

ተለምዶአዊው የሆነው መርሳት በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ የሚገጥሙንን ጥቃቅን ነገሮች በውስጣችን ከማከማቸት ነፃ ያወጣናል። ነገር ግን አንዳንድ ነገሮች በግድ አምቀን እና አፍነን ብንረሳ ነጻነትን አናገኝም። ምናልባት ለጊዜው ካለንበት ስቃይ እና ህመም የተላቀቅን ሊመስል ይችላል። እንዲህ ዓይነቱን መርሳት መርሳት አንለውም። በዚህ መንገድ በመርሳት ለሕይወታችን የምናመጣው ጥቅም የለም። ምክንያቱም ትውስታው በውስጣችን ተቀበረ እንጂ አልጠፋም። አልተውንም። አልረሳንም። በሕይወታችን የእድገት ጎዳና ላይ ብቅ ያለ ተጽእኖ ማሳረፉን ይቀጥላል። አንዳንዴ ደግሞ ከታሰረበት በውስጣችን ካለው እስር ቤት በሩን ገንጥሉ እየወጣ ሁለንተናችንን ለህመም ይዳርገዋል፤ ይገጨናል።

ግን ደግሞ ሌላ አይነት መርሳት አለ። ሐዋርያው ጳውሎስ በሕይወቱ አንደተለማመደው የነገረን አይነት መርሳት። ይህ ጳውሎስ በህይወቱ አይቶ የሚመሰክረው መርሳት ነጻ የሚያወጣን፥ ከፀፀት እና የበደለኝነት ትውስታ ሳይሆን፥ ነገር ግን በዛሬያችን ላይ ይዞት ከሚመጣው ህመም ነው። ይህ ዓይነቱ መርሳት ከጥንት ጀምሮ ይጠራበት የነበረ አንድ ግሩም ስም አለ። ይህም ስም ንስሀ ተብሎ ይጠራል። በርግጥ ባለንበት ዘመን ንስሃ የሚለው ቃል የተቆራኘው፥ ትላንት የሰራነውን በደል አለቅጥ አጋነን በማየት፣ ራስን በመክሰስ ማለቃቀስ እና ለውስጥ ጭንቀት ጊዜያዊ ምቾት መፍጠር ከሚለው ሃሳብ ጋር እንጂ፤ ነፃነትን የሚሰጥ የመርሳት መንገድ ከመሆኑ ጋር አይደለም። ከመጀመሪያው ትርጉም ወስደን ንስሐ ማለት ምን ማለት የሚለውን ብናይ፤ ንስሐ ማለት ቀኝ ኋላ ዞር ማለት ነው። የተሳሳተውን ጎዳና ወደኋላ በመተው፣ ወደትክክለኛው መንገድ ገብቶ ወደፊት መሄድ ማለት ነው። ንስሀ ማለት የጥፋተኝነት ስሜታችንን በውስጣችን በማመቅ ሳይሆን፥ ጥፋተኛ እና በደለኛ መሆናችንን በማመን፥ “የቀደመውን በደልህን አልቆጥርም፥ እስከ ማንነትህ ተቀብዬሀለው” የሚለውን የምህረት ቃል በመቀበል፤ የበደለኝነትን ሕመም እና ክስ ወደኋላ መጣል ነው። ዝም ብሎ መተው የለም። ቀድመን ንስሐ መግባት አለብን። ንስሐ መግባት ከቻልን፤ መተው እንችላለን። መርሳት አስፈላጊ ነገር ስላልሆነ አይደለም፣ ጭንቀትን ሊሸከመው

ያልቻለውን በውስጣችን ስላመቅነው ስለአደፋፈነው አይደለም። ነገር ግን በደለኝነታችንን ስለአመንን እና ያለ ፀፀት እና ክስ ያለፈው አልፏል ብለን ከእውነታው ጋር መኖር ስለቻልን ነው። በደላችን ለዘላለም የተረሳ በመሆኑ ነው። ምንም እንኳን ትላንት በሕይወቱ ያለፈው ነገር ሁልጊዜ ከእርሱ ጋር የሚኖር ቢሆንም ጳውሎስ ከኋላው ያለውን ነገር የረሳው በዚህ መንገድ ነበር።

ይህ ዓይነቱ መርሳት ለግል ግንኙነታችን ወሳኝ ነው። ቢሆንም ውጤታማ የሚሆነው ደግሞ ይቅርታ በመስጠት፥ ደጋግሞ ይቅርታ በማድረግ ውስጥ እንጂ ከዛ ውጪ በሌላ ሊሆን የሚችል አይደለም። ይቅርታ ማድረግ የተፈፀመውን ጥፋት ማስታወስን ግንዛቤ ውስጥ ያስገባል። በሌላ መንግድ ደግሞ ያስታወሡነውን ለመርሳት ዝግጁም ያደርጋል። ግን ይህ መርሳት ትላንት የነበረውን የአየር ሁኔታ እንደረሳነው አይነት መርሳት አይደለም። “የሆነውን እያንዳንዱን ነገር አስታውሳለሁ ነገር ግን በፈቃዴ፣ አምኜበት ትቻለሁ፣ እረስቻለሁ” የሚለውን ታላቅ ቃል በውስጡ ይዞ ነው። እንደዚህ አይነት መርሳት ከሌለ፥ የሰው ልጅ ግንኙነት ጤናማ ሆኖ ሊቆይ አይችልም። አሁን እየተናገርኩ ያለሁት እጅግ መልካም ስለሆነው ይቅርታን የመጠየቅ እና የማድረግ ተግባር በተመለከተ አይደለም። እሱ አይነት ይቅርታ “እንዳጠፋ የተሰማው ሐፍረት ይዞት እና አንገቱን አቀርቅሮ ይቅርታ የሚልበት”፤ የተበደለው ይቅርታ እንዲያደርግ የሚለመንበት ነገር ግን “በደል ባለመፈፀም ያገኘውን የሞራል የበላይነት እያውለበለበ ይቅርታን ሲያሻው የሚሰጥበት እና የሚወስድበት” በየቀኑ በልጆች እና በወላጆች መካከል፣ በጓደኛሞች መካከል፣ በባል እና ሚስት መካከል የሚደረግ ተለምዱአዊ የሆነ፣ ትኩረታችንን የማይሻ ነገር ነው።

እኔ እያልኩ ያለሁት የጎዳንን እና በሕይወታችን ውስጥ መራራ ነገር ያደረገውን ሰው ለመቀበል፥ ያደረገብንን በደል ለመርሳት፣ በሁኔታዎች የማይለወጥ ይቅርታን ለማድረግ ፍቃደኛ የሆነ ሰው ስለመሆን ነው። ይህ አይነቱ ይቅርታ በደልን የመዘንጋት ጉዳይ ሳይሆን፥ እጅግ የላቀ ያለፈን የመተው፣ የመርሳት አቅም ላይ የመድረስ ምልክት ነው። ሌላኛውን ሰው በመበደላችን ምክንያት ከፊታችን ተደቅኖ የነበረው ጋሬጣ ተነስቶ ወደኋላ የሚወረወርበት ነው። በዚህም ግንኙነታችን ለአዲስ ነገር የተከፈተ በር ያለው ይሆናል። ትላንትና የተደረገውን በደል የምናስታውስ ቢሆንም ያለፈው አልፏል ብለን ስንተው ይቅርታ ይባላል። መኖር የምንችለው በአንድ ነገር ብቻ ነው፥ ያ መኖር የምንችልበት ምክንያት ለበደላችን ይቅርታን ስላገኘን፤ ለዘላለምም ስለተረሳ ነው። ማፍቀር የምንችለው በአንድ ምክንያት ብቻ

ነው፤ ያ ብቸኛ ምክንያት ይቅርታ ስናደርግ እና ይቅርታ ሲደረግልን ነው።

## 3.

በመጽሐፍ ቅዱስ ንባባችን ጳውሎስ ከፊቱ ያለውን ለመያዝ የሚሮጥ ሰው እንደሆነ እናውቃለን። ለእኛ ግን ዋናው ነገር ከኋላው ያለውን እየተወ ከፊቱ ያለውን ለመያዝ የሚዘረጋ ሰው መሆኑ ማወቁ ብቻ ሳይሆን፥ ይህ ሊይዘው ወደ ፊት የሚዘረጋለት ነገር ምን እንደሆነ መመርመርና ማወቅ ነው። ምክንያቱም አእምሯችን አስቀድመን ካነሳነው "መርሳት እና ማስታወስ" ከሚለዉ ውይይታችን ለየት ያለ የ" መርሳት" አይነት እንዳለ ወደ መገንዘብ የሚመጣው በዚህ መንገድ ነው። ይህ ቀድሞ ካነሳነው የ" መርሳት" አይነት ለየት ያለ የ" መርሳት" አይነት፥ አንድ ቀን እኛው ራሳችን "እንረሳለን" የሚል ነው። እኛ ነገሮችን እና ሁኔታዎችን "ስናስታውስ እና ስንረሳ" እንደነበረው እንዲሁ እኛም አንድ ቀን "ከሚረሱ እና ከሚታወሱ" ነገሮች መካከል አንዱ እንሆናለን። ይህንን ሃቅ መገንዘብ እንዳለ ሆኖ በሌላ መልኩ ደግሞ እኛ ራሳችን እንደምንረሳ ማሰብ አእምሮችንን የሚያናውጥ፥ መሸከም የማንችለው ነገር ስለሆነ ባለን አቅም በውስጣችን እንቀብረዋለን። በዚህ ጉዳይ የተፃፉ የሥነጽሑፍ ሥራዎቻችን የሚያሳዩት ደግሞ ሌላውን ገፅ ነው። በዚህ ዘሪያ የተፃፉ ጠቅላላ የሥነጽሑፍ የፈጠራ ሥራዎችን ብንመለከት እንደ ደሀው ሁሉ ባለጠጋውም፣ እንደማንኛውም ሰው ነገስታትም፣ እንደ ደካማው ሁሉ ብርቱ የሆነውም አንድ ቀን ሞት እንደሚጠራው፥ "መረሳት" እጣ ፈንታው እንደሆነ በሚተርኩ እና በሚያስታውሱ ታሪኮች የተሞሉ ናቸው። ያም ቢሆን ለእኛ ሞት የሚባል የቀጠሮ ቀን እንዳለብን ማሰብ ራሱ እንደ ሞት ነው።

እናም የሞታችን ቀን የሚያስታውሰንን ማንኛውንም ነገር እና የትኛውንም ሐሳብ የሚያስረሳ ነገር ሁሉ እናደርጋለን። እንኳንስ ስለምንሞትበት ቀን፥ ሟች መሆናችንን ማሰብ ራሱ አንፈልግም። መረሳት እንፈራለን። እንደ ማይሞት እንደማይረሳ ሰው እንኖራለን። ያም ሆኖ እንደምንረሳ አንድ ቀን ሟች እንደሆንን ማድበስበሳችን የሚፈይደው ምንም ነገር የለም። ሁሌም አብሮን የሚኖር በሥጋችን ተሸክመን የምንዞረውን ሟች የመሆናችንን እውነት ማስወገድ አይችልም። በሕይወት እንዳለን እንዲሁ አንድ ቀን ደግሞ እንደማንኖር እናውቃለን። ሟች ነኝ የሚለውን ጭንቀት ማስወገድ አይቻልም። በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ እንዲህ ዓይነቱ ሟች የመሆናችንን እውነታ ለማድበስበስ የምናደርገው ጥረት ትንሽ እንኳን ውጤታማ የማይሆንባቸው ጊዜያት አሉ። እነዚያ ጊዜያት

ወደ ሕይወታችን ሲመጡ፥ “የምረሳበት” ዘላለም ደግሞ የማልታወስበት ቀን ይመጣል ማለት ነው? ብለን ራሳችንን መልሰን እንጠይቃለን። “ነገ እኔም ሟች ነኝ” የሚለውን በማወቅ መነሻ ምክንያት፥ ዛሬን በፍርሀት የሚያየውን በውስጣችን ያለውን ጭንቀት በግልጽ መጋፈጥ እንጀምራለን። ሟች መሆንን ማወቅ ጭንቀት ነው። መረሳት አስፈሪ ነገር ነው። ሟች መሆናችንን በማወቃችን ብቻ ወይም ሟች መሆናችን የወለደው ጭንቀት ማለት፥ አንድ ሰው አሁን በአካል ሥጋ ካለበት እውነታ፥ በኋላ ደግሞ ነፍሱ ከሥጋው ስትለይ፥ ለዘላለም እንደሚረሳ ማወቅ የሚያመጣው ጭንቀት ማለት ነው።

ሁሉም ሕይወት ያለው ነገር አሁን ያለበት የመኖር እዉነታ ተቀይሮ፥ ወደ አለመኖር እንዲሄድ በፍፁም አይፈልግም። አሁን ያለበት ሁኔታ፥ ዘላለም የሚኖር ባይሆን እንኳን፥ በሌላ አዲስ ቅርፅ ቢሆን ህልውናውን አግኝቶ ለመኖር ይፈልጋል። ማንም ወደ ነገ ማህደር ውስጥ ተወርውሮ እንዲረሳ አይፈልግም። ይህን የመረሳት መጥፎ ስሜት፥ ወደ መረሳት ማህደር ውስጥ የመወርወር እውነታን በአስፈሪ ድባቡ የሚገልፅ ምልክት የቀብር ሥነሥርዓት ነው። እንግዲህ ቀብር ማለት ከዚህ ወዲህ ስለማንኛውም ነገር፥ እየሆነ ስላለው ሁኔታ አለማወቅ፣ ከምድር ፊት ፍጹም መወገድ ማለት ነው። የኢየሱስ ከሞት የመነሳት ታላቅነት የሚገባን እና ትርጉም የሚሰጠው በእምነት መግለጫ ውስጥ በምናገኘው “የተቀበረ” በሚለው ቃል ውስጥ ነው። “በዚህ የመቃብር ስፍራ ነበር” ነገር ግን ተነስቷል የሚለው ሃሳብ ምን እንደተሸከመ ስለተረዳን የተቀበረ በሚለው ቃል ውስጥ

ያለውን ታላቅ ነገር እናያለን።

ሌላው ከዛሬ ነገ እሞታለው ከሚል እውቀት የሚመጣ ጭንቀት ምን ማለት ነው የሚለውን ለመመለስ የሚሞክር መሠረተ ቢስ የሆነ እይታ አለ። ይህም ከዛሬ ነገ እሞታለሁ የሚል ጭንቀት ማለት፥ የሰው ልጅ ወደ ሞት አፋፍ ሲቀርብ የሚያልፍበትን ስቃይ እና ጣር የመፍራት ጭንቀት ነው የሚል እይታ ነው። እውነት ነው በሞት አፋፍ ላይ በምንሆንበት ጊዜ በቃላት የማይገለጥ ስቃይ እና ጣዕር ውስጥ እናልፋለን። ነፍሳችን ከሥጋችን በቀላሉ አትላቀቅም። ነገር ግን ሞታችን ቀለል ያለ፣ ስቃይ ያልበዛበት ሊሆን ይችላል። በብዙ ጣዕር ብቻ ሳይሆን ያለምንም ጣዕር ነፍሳቸው ከሥጋቸው የምትለኝ ሰዎች አሉ። ስለዚህ ከዛሬ ነገ እሞታለው ከሚል እውቀት የሚመጣ ጭንቀት የሞት ጣዕርን፣ እና ስቃይ የመፍራት ጭንቀት አደለም። ከዛሬ ነገ እሞታለው ከሚል እውቀት የሚመጣ ጭንቀት፤ መርሳትን ከማሰብ የሚመጣ ጭንቀት ነው።

የሰው ልጅ ይህን ሃሳብ መሸከም ችሎ አያውቅም። የሰው ልጅ መረሳትን ላለመቀበል የሚያደርገዉ መፍጨርጨር፥ ግሪኮች ክብር ምንድነው የሚለውን ሲፈቱ መረሳትን ማሸነፍ ነው ከሚለው ጋር መሳ ለመሳ ይሄዳል። ዛሬም በእኛ ዘመን ተመሳሳይ ነገር እናገኛለን። መረሳትን ለማሸነፍ "ለታሪክ የሚሆን ነገር ሰርቶ ማለፍ "አንዱ መንገድ እንደሆነ የጋራ ስምምነት ይዘናል። አንድ ሰው ከቻለ የመታሰቢያ አዳራሾችን ይሠራል ወይም የመታሰቢያ ምግባረ ሰናይ ድርጅት ያቋቁማል። በዚህ ምክንያት ከሞትኩ በኋላ በሚወዱኝ፣ በሚጠሉኝ እና በሚያደንቁኝ ሰዎች ብቻ ሳይሆን ከትውልድ ትውልድ ለመታሰቢያ በሰራኋቸው ሥራዎች ላይ ለመጀመሪያ ጊዜ ስሜን በሚያውቁ ሰዎች ጭምር እታሰባለው ብሎ ማሰብ ትልቅ መፅናናት ይሰጠናል። ሕይወት ትርጉም ያለው እንዲሆን ያደርጋል። አንዳንድ ስሞች ከትውልድ ወደ ትውልድ እየተላለፉ ሲታወሱ ይኖራሉ። ይህን ተስፋ ባለቅኔው በብዕሩ በኩራት ተሞልቶ "የምድር ላይ ቆይታው አሻራ እስከ ዓለም ፍጻሜም ድረስ ቢሆን አይጠፋም." በማለት ከትቦ እናገኛለን። እውነት ነው ከዚህ ምድር በሞት ብንለይ እንኳን አሻራዎቻችን ህያው ምስክር ሆነው ይኖራሉ ነገር ግን እኛ ራሳችን በአካል ሥጋ የለንም። ስማችን ይንፀባረቅባቸዋል እንጂ ስማችን አይደሉም። የም ሆነ ይህ ከመረሳት አይታደጉንም።

ከመረሳት ሊታደገን የሚችል ምን አለ? አንድ እርግጠኛ የምንሆንበት ከመረሳት ፍርሃት ከሚከስትብን ነፍስን እረፍት ከሚነሳ ጭንቀት የሚያድነን ብቸኛ ነገር፥ ዓለም ሳይፈጠር በእርሱ ፊት በመታወቃችን እና በዘላለም ውስጥ ታውሰን እንደምንኖር ማመናችን ነው። አንረሳም። ልንረሳ አንችልም። ምክንያቱም ካለፈ እና ከወደፊት የጊዜ ሰሌዳ ባሻገር ለዘላለም በፊቱ ስለምንታወቅ ፍፁም አንረሳም።

ዓለም ሳይፈጠር በርሱ ዘንድ ስለታሰብን፥ በዘላለም ዘመናት ውስጥ በፊቱ የምንታወስ ስለሆንን ልንረሳ አንችልም። ነገር ግን ራሳችንን መርሳት እንችላለን። ከዘላለም በፊት የታወቀውን እና የታሰበውን እውነተኛ ማንነታችንን መርሳት እንችላለን። በሕይወት ጎዳና ላይ ስንጓዝ ከመደምደሚያ፥ ከፍጻሜ አንፃር በየሰዓቱ የሚያጋጥሙንን አብዛኛዎቹን ነገሮች እረሳን ወይ አልረሳን ወይም ማስታወሳችን ያን ያህል አስፈላጊ አይደለም። ዋናው ነገር ራሳችንን አለመርሳት ነው። ከሁሉም በላይ ረብ ያለው ነገር ከማልማትም ከማጥፋትም መብት ጋር በእጆቻችን የተሰጠንን ማንነታችንን አለመርሳት ነው። የማይደገም፣ ልዩ፣ ግሩም እና ድንቅ ሆኖ የተበጀውን ማንነታችንን አለመርሳት ነው። እንዲህም ሆኖ እውነተኛ ማንነታችንን

ልናጎሳቁል፥ ትኩረት በተነፈገ ሁናቴ ውስጥ ልናስቀምጥ እና ሊሆን የሚገባውን እንዳይሆን በእሥራት አቆይተነው ይሆናል። በሌላ ጎኑ ደግሞ በየዕለቱ ለእውነተኛው ማንነታችን ትኩረት ቢኖረን፣ በዘላለም ዘመናት ውስጥ ያለውን ቦታ የተገነዘበ እንዲሆን ካደረግን፥ ገና በእናታችን ማህጸን እንዳለን እንደምንታወቅ፤ ወደፊትም እንደማንረሳ እንገነዘባለን። የእኛ እውነተኛ ማንነት ምንጩ የፍጥረት መሠረት ከሆነው ከእርሱ ነው። እኛነታችንን ካለመኖር ወደ መኖር ያመጣው፤ በኋላም የሚመለሰው ወደርሱ ነው።

በመለኮት ፈቃድ ህልውናውን እንደያዘ በዘላለም ዘመናት ውስጥ እንዲኖር የተመረጠ ፈጽሞ አይጠፋም። ከዘላለም ወጥቶ መጥቷል፤ ወደ ዘላለም ይመለሳል። ይህን የምናገረው ስለአንድ ሰው ሳይሆን ስለሰው ሁሉ ነው። በአጽናፈ ዓለሙ ዉስጥ ከእግዚአብሔር ሁሉን አዋቂነት የተሸሸገ የማይታወቅ ምንም ነገር የለም። በመጨረሻም ይህ የታወቀ ነገር ሳይጠፋ ይኖራል። ዛሬ በማይቆጠር እና በማይለካ መስመር ላይ ወዲህ እና ወዲያ የሚሉ አተሞች፥ ከቢሊየን አመት በፊት በማይቆጠር እና በማይለካ መስመር ላይ ሲንቀሳቀሱ የነበሩ አተሞችን ጨምሮ መነሻቸው አንድ ቦታ ነው። የ አንድ ቦታ አንድ ጊዜ በቃሉ ይሁን ብሎ ሁሉን ወደመኖር ያመጣበት ቀን ነው። ፍጥረት ሁሉ ያን ጊዜ ጀመረ፣ አሁንም አለ። ወደፊትም የሚኖረው ይህ በቃሉ ይሁን ተብሎ ያን ጊዜ ወደመኖር የመጣው ፍጥረት ነው። ስለዚህ አንድ ነገር ተረሳ ስንል ፍፁም በሆነ ሁኔታ ተመልሶ ላይገኝ ደብዛው ጠፋ ማለታችን አይደለም። ከዓይኖቻችን እና ከትዝታ ማህደራችን ሊሰወር ይችላል። ነገር ግን ትላንት፣ ዛሬ እና ነገ በፊቱ በማይለዋወጡ በመለኮት ፊት በዘላለም ዘመናት ስፍራቸው ላይ እንዳሉ አሉ። አንድ ጊዜ በቃሉ ወደ መኖር የመጡ ነገሮች ተመልሰው ወደ አለመኖር አይመጡም። ፍጹም የሚጠፋ ከዘላለም ዘመናት ማህደር ውስጥ የሚፋቅ ምንም ነገር የለም።

እኛም ካለመኖር ወደ መኖር ከመጡ ነገሮች ሁሉ ጋር በመለኮት ሕይወት ውስጥ አንድ ላይ አብረን እንኖራለን። ይህ በዘላለም ዘመናት ውስጥ ሳይጠፋ የሚኖር ነገር አንድ ጊዜ በቃሉ ይሁን ብሎ ወደመኖር ሲያመጣው እንዳይጠፋ የወሰነው ነገር ሁሉ ነው። በእኛም ውስጥ ሆነ በእኛ ዙሪያ፥ በዘላለም ዘመናት ውስጥ እንዲኖር ያልተወሰነ ነገር፥ ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ መረሳት ማህደር ውስጥ ይወረወራል።

“የመጨረሻው ፍርድ” ማለት፥ በሁሉም ነገሮች ላይ እንደሚደረገው ሁሉ፥ በእኛም ወስጥ በዘላለም ዘመናት ውስጥ እንዲኖር ያልታሰበ ጊዜያዊና ረብ

የሌለው ነገር ሁሉ፥ በዘላለም ዘመናት ውስጥ እንዲኖር ከተወሰነው እውነተኛ ማንነታችን እንዲነጠል ይደረጋል። እኛ በፍጹም አንረሳም። ነገር ግን ከእኛነታችን ውስጥ የምንወደው፣ የምንሳሳለት በመጓጓት የያዝነው ነገሩ ሁሉ ከዘላለም ዘመናት ፊት ተፍቆ፥ ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ወደ መረሳት ማህደር ይጣላል። አሁን እንኳን እንዲህ አይነቱ የመጨረሻ የፍርድ ሂደት በሕይወታችን እያንዳንዱ ቅፅበት ውስጥ እየተከናወነ ያለ ነገር ነው። ነገር ግን የዚህ የመጨረሻው ፍርድ አሰጣጥ ሂደት በጊዜ ውስጥ የተሸሸገ እና በዘላለም ዘመናት ውስጥ ብቻ የሚገለጥ ነገር ነው። በእያንዳንዱ ቀን እውነተኛ ማንነታችን ያልሆነ ነገር የቱንም ያህል ብንፈልግ እና ብንወድ በመለኮት የፍርድ ዙፋን ፊት እየቀረበ፥ በመለኮት በማይታዩ እጆች የመነጠል ጥበብ፥ ከእኛ ላይ እና ከእኛ ውስጥ እንዲነጠል ይደረጋል። . ለዘላለም ሊረሳ የተገባ ነገር ግን በእኛ ውስጥ ያለውን"የማይጠፋውን ማንነታችንን" እያራቆተ ያለን ማንነት፥ ወደ ነገ እንወርውረው፥ ወደመረሳት ማህደር ውስጥ እንጣለው። እውነተኛ ማንነታችንን ወደሚያንፀባርቀው እና በዘላለም ዘመናት ውስጥ የማይጠፋውን ለመያዝ እንገስግስ።

# 4. መንፈሱ በመሐላችን

*“ብቃታችን ከእግዚአብሔር ነው እንጂ፥ በገዛ እጃችን እንደሚሆን አንዳችን እንኳ ልናስብ ራሳችን የበቃን አይደለንም፤ እርሱም ደግሞ በመንፈስ እንጂ በፊደል ለማይሆን ለአዲስ ኪዳን አገልጋዮች እንሆን ዘንድ አበቃን፤ ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።”*

*2ተኛ ቆሮ 3፡5-6*

## 1.

ሐዋርያው ጳውሎስ ሲፅፍ እንዲህ ይላል “ራሳችን የበቃን አይደለንም”። በእውኑ ይህ “እኛ” የተባለው ማን ነን? እርሱ “እኛ” ሲል ራሱ ሐዋርያው ጳውሎስ እና ከእርሱ ጋር የሚሰሩትን ማለቱ እንደሆነ ግልፅ ነው። በተጨማሪም፥ ጳውሎስ ይህን ኪዳን ሲጠራው፥ በእግዚያአብሔር እና በሰው መካከል የተጀመረ አዲስ ሕብረት ነው ይላል፤፥ ከዚህ አዲስ ሕብረት ደግሞ በሰው ልጅና በሚኖርባት ዓለም ከዚህ በፊት ያልነበረ አዲስ ፍጥረት ተገኝቷል ጳውሎስም አገልጋይ የሆነበት ይህ ኪዳን ነው እናም “እኛ” የሚለው፥ “አዲሱን ኪዳን” ለማገልገል የተገቡትን ሁሉ የሚያካትት ነው።

የቱንም ያህል ያልተሟላ ይሁን፥ በዚህ አዲስ ኪዳን ውስጥ የተሳተፈ ሁሉ፥ ለዚህ ኪዳን አገልጋይ ለመሆን ብቁ ነው። ነገር ግን በዚህ አዲስ ፍጥረት ውስጥ የተካተተው፣ የተሳተፈው ማን ነው ብለን ስንጠይቅ፥ ወዲያው መልስ የሌለው ጥያቄ እንደሆነ እንደርስበታለን። ማንም ሰው፥ ወደሌላው ሰው ውስጠኛ ሰውነት “የእርሱነቱ ቅድስተ ቅዱሳን” ግብቶ መመልከት አይችልም። ወደራሱ ልብ እንኳን ሙሉ በሙሉ ዘልቆ ገብቶ ማወቅ አይችልም። ስለዚህም ማንም በእርግጠኝነት በዚህ “ሁሉን ነገር አዲስ ባደረገው” ኪዳን ውስጥ፥ እከሌ የተባለ ሰው ተካፍሏል ብሎ መናገር አይችልም። ስለ ራሱ እንኳን ቢሆን እንደዛ ማለት አይችልም። ደግሞ የሌላ “እከሌ የተባለ ሰው” ሕይወት የቱንም ያህል የተዛባ ይሁን፥ አንድ ሰው ተነስቶ “ስለእዛ ሌላ ሰው” ሁሉን አዲስ ባደረገው ኩነት ውስት በጭራሽ አልተሳተፈም

እናም የዚህን አዲስ ሕይወት ዓላማ ለማገልገል፣ ብቁ አይደለም ብሎ መናገር አይችልም። በእርግጠኝነት ማንም ስለ ራሱ ይህን መናገር አይችልም።

ምናልባት አሁን በእኛ ጊዜ በዚህ የመጨረሻ ሃሳብ ላይ ማለትም ራሳችንን እና በዙሪያችን ያሉት ሰዎችን ጨምሮ፣ አዲሱን ፍጥረት ለማገልገል የበቃን እንደሆን እና ካህናት የመሆናችን ጥሪ ለማሳካት በጋራ መደጋገፍ እንድንችል አቅማችንን ማዳበር ላይ አጽንኦት መስጠት ይበልጥ አስፈላጊ ሊሆን ይችላል። ባለፉት ጥቂት አመታት፣ ብዙ ሰዎች፣ በተለይም የቤተ ክርስቲያን ንቁ ተሳታፊ ምዕመናን፣ በሌሎች ላይ ለመፍረድ እና ሌሎች ምን ማመን እንዳለባቸው እና እንዴት እንደሚኖሩ መመሪያ ለመስጠት የበቁ እንደሆኑ የሚሰማቸው ወቅት ነበር። ዛሬ ይህን አይነት አመለካከት እብሪት እንደሆነ እናውቃለን። በተለይ በመካከለኛ እድሜ እና በወጣቱ ትውልድ፣ በሌላው ላይ ከመፍረድ “እኔስ መች የበቃሁ ነኝ” የሚል አስተሳሰብ እና ግንዛቤ የዳበረበት ወቅት ነው። ራሳችንን ብቁ እንዳልሆንን ወደመቁጠሩ እና አዲሱን ፍጥረት ከማገልገል ወደመሸሽ እናዘነብላለን። እኛ በዚህ አዲስ ኪዳን ውስጥ ስፍራ እንደሌለን፣ በዚህ ሕይወት እንዳልተካፈልን እና ለሎችንም ወደዚህ ተሳትፎ፣ መካፈል ማምጣት እንደማንችል ይሰማናል።

አንዳችን ለሌላችን ካህናት ነን በሚለው ውስጥ ያለውን ክብር እና ቀንበር አንቀበልም። ብዙ ጊዜ ይሄ የሚሆንበት ምክንያት እጅግ ለላቀው ጥሪአችን ግድየለሽ ከመሆን የሚመጣ ነው። ነገር ግን እኩል በኩል፣ ወደ እንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ የምንገባው ደግሞ፣ በራሳችን ላይ ተስፋ በመቁረጥ፣ በጥርጣሬ፣ በባዶነት ስሜት እና በበደለኝነት ነው። “ሁሉን አዲስ ካደረገው ኩነት” ሙሉ በሙሉ፣ እስከመጨረሻው እንደተወገድን ይሰማናል እና ሌሎች ወደዚህ ሕይወት ክብር እንዲመጡ መርዳት አንችልም።

ሌላው ቀድመን ያነበብነው ክፍል የያዛቸው ሌሎች ሀሳቦች፣ ማለትም “ብቃታችን ከእግዚያአብሔር እንጂ ከእኛ አይደለም” የሚለው እና “እግዚያአብሔር ከልባችንም ይልቅ ታላቅ ነው” የሚለው፣ እጅግ አጽናኝ የሆነው ቃል፣ ተግባራዊ ይሆን ዘንድ ግድ ነው። እና ከራሳችን አልፈን፣ ከእኛ እጅግ የሚልቀውን እርሱን ብንመለከት፣ እኛው ራሳችን እርዳታ በሚያስፈልገን ወቅት እንኳን ሌሎችን ለመርዳት እንደተጠራን፣ በቅፅበት ማወቅ እንጀምራለን። እናም በሚያስደንቅ ሁኔታ! ራሳችን ሌሎችን መርዳት የሚችል ሰው ሆኖ እናገኘዋለን። ከእኛ ያልሆነ ኋይል በእኛ አልፎ ይሰራል። ምናልባትም፣ እኛው ራሳችን በታላቅ ጭንቀት በነበርንበት ወቅት፣ ቃላት ከውስጣችን፣ ከእኛ ጥልቅ ከሆነው የማንነታችን ክፍል ተነስተው፣ ወደ ሌላ

ሰው የውስጥ ክፍል፣ “የእርሱነቱ ቅድስተ ቅዱሳን”ወደሚገኝበት፣ ቃላት ወደ ማይገልጠው “ጭንቀቱ” ውስጥ ዘልቀው ገብተው በመግጨት፣ ያ ሰው አዲስ ሁኔታ፣ ከጭንቀት ወደ መረጋጋት ውስጥ እንዲገባ የረዱትን ወቅቶች እናስታውስ ይሆናል።

ምናልባት የአንድ ሰው ድርጊት፣ ይህው ሰው ሕይወቱ ቀጥ ባለ መንገድ እየሄደ እንዳልሆነ የምናውቀው ሰው ክህነታዊ አገልግሎት የሚያነቃ እና የፈውስ ተፅዕኖ በሕይወታችን ሲፈጥር እናስታውስ ይሆናል። በእኛ ውስጥ እንደነበረ ነገር ግን የእኛ ኃይል እንዳልሆነው እንዲሁ፤ ይህ ከእርሱ የወጣው ኋይል የእርሱ አልነበረም፣ ነገር ግን በእርሱ ውስጥ ነበር። በዚህ የአዲስ ፍጥረት አገልግሎት ውስጥ፣ ሌሎች ወደዚህ አዲስ ፍጥረት እንደሚጡ፣ አስታራቂ የመሆንን ኋላፊነታችንን በእብሪት አንያዘው። ከእኛ በላይ ማን አለ አንበል። ይህን ስል እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቤተ ክርስቲያን ማለቴ ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ አንዳችን ለሌላችን ካህናት እንድንሆን የተሰጠንን አደራ አቅልለን አንያዝ፣ እንደ ተራ ነገር አንጣለው። በየትኛውም ምክንያት ይሁን ! በራሳችን ላይ ተስፋ ቆርጠን ወይም ለተጠራንበት ታላቅ ጥሪ ግዴለሽ በመሆን፣ ብቻ በየቱም ምክንያት፣

አንዳችን ለሌላችን ካህናት የሆንበትን ጥሪ አንጣለው። ብቃታችን ከእኛ የሆነ ሳይሆን፣ ከማንም ሰው የሆነ ሳይሆን፣ ወይም ከየትኛውም ተቋም የሆነ ሳይሆን፣ ከቤተ ክርስቲያናችን እንኳን የሆነ ሳይሆን ከራሱ ከእግዚያአብሔር ነው የሚለው ቃል ትምክህተኝነትን የሚገድል እና ከተስፋቢሥነት የሚታደግ ነው። እናም ከእርሱ ከእግዚያአብሔር የመጣ ከሆነ የመንፈሱ ህልውና መገኘት በመንፈሳችን ውስጥ ነው ማለት ነው።

# 2.

መንፈስ የሚለውን ቃል ስንሰማ ምን ማለት እንደሆነ ይገባናል። መንፈስ ማለት ከእኛ ያልሆነ፣ ነገር ግን በእኛ ውስጥ ያለ "አሁን ሁሉን አዲስ ላደረገው ኩነት" አገልጋይ እንሆን ዘንድ፣ የሚያበቃን ኃይል ማለት ነው። ክርስቲያን ለሆኑም ላልሆኑም ሰዎች፣ በክርስትና ውስጥ ከምንጠቀማቸው ንግግሮች ውስጥ "መንፈስ ቅዱስ" የሚለው ቃል ግር ያሰኛቸዋል። በትክክልም ለመረዳት ሲቸገሩ ይስተዋላል። ብዙ ጊዜ መንፈስ ቅዱስ፣ እንደ ርዕሰ ጉዳይ ሆኖ በስብከት ውስጥ አይነሳም፣ በሃይማኖታዊ ትምህርቶች ውስጥም ችላ የተባለ ነገር ነው። የመንፈስ ቅዱስ በዓል የሆነው፣ የባዕለ ሃምሳ ክብረ በዓል ምን ማለት እንደሆነ ከብዙ ሰዎች አዕምሮ ሊጠፋ ለጥቂት ተቃርቧል። ልዩ የሆነ የመንፈስ ቅዱስ ቀባት በላያችን ላይ ፈሷል፣ ድንቅ እና ተዓምራትም እናደርጋለን እያሉ የሚናገሩ ሰዎች ጤና የነሳቸው እንደሆኑ ይቆጠራሉ፤ እና በርግጥ ብዙ ጊዜ ትክክል ነው። "መንፈስ ቅዱስ" የሚለውን ቃል በሥርዓተ አምልኮ ጊዜ ስንጠቀም፣ ከወትሮው ከምናወራውና ከምናስበው በጣም የተለየ ነገር፣ እያወራን እና እያሰብን እንደሆነ እንዲሰማን ያደርጋል። ነገር ግን፣ በመንፈስ ቅዱስ የመነካት የሕይወት ልምምድ፣ እንደ መውደድና እንደ መተንፈስ ሁሉ፣ "አለ፣ የለም ብለን" የማንጠራው፣ ማንም ሰው ሊለማመደው የሚችለው እውነታ ነው።

ስለዚህ መንፈስ የሚለውን ቃል ለመጠቀም ሐፍረት ሊይዘን አይገባም። የቱንም ያህል፣ በመንፈሳችን ውስጥ የእግዚያአብሔር መንፈስ መገኘት የሕይወት ልምምዳችን ያላደገ እና ደካማ የሚባል እንደሆነ ብንገነዘብም፤ በውስጣችን እና በእኛ ዙሪያ ላለው የመንፈሱ መገኘት ሙሉ በሙሉ ንቁ መሆን አለብን። መንፈስ ቅዱስ፣ ከመለኮት የሆነውን መንፈስ ማለት የእግዚያአብሔር መንፈስ በመንፈሳችን ውስጥ ሲገኝ ማለት ነው። መንፈስ ማለት፣ የሆነ ሚስጥራዊ ንጥረ ነገር ማለት አይደለም፤ ከእግዚያአብሔር የሆነ ክፍል ማለት አይደለም። ራሱ እግዚያአብሔር ነው፣ ነገር ግን በመንፈስ ሲገኝ፣ ሁሉን ነገር ካለመኖር ወደመኖር በሚያመጣ አስገኚ እግዚያብሔርነቱ፣ የታሪክን አቅጣጫ በሚመራ እና በታሪክ ወሳኝ ወቅት ራሱን በሚገልጥ እግዚያብሔርነቱ ሳይሆን፣ በማሕበር እና በግለሰቦች ሕይወት፣ በሚይዝ እና በሚደግፍ ማንነቱ፣ ለታላቅ ሥራ በሚያነሳሳ እና ፍፁም ሌላ አድርጎ በሚቀይር እግዚያአብሔርነቱ ነው።

ከሁሉ አስቀድሞ መንፈስ ኀይል ነው፤ የሰውን መንፈስ ካለበት ከፍ አድርጎ

በማነሳት፣ የሰው መንፈስ ሊደረስበት ፈልጎ ወደ አልደረሰበት የሚነዳ ኀይል፣ ከስጦታዎች ሁሉ የሚልቀው ስጦታ የሆነው የፍቅር ኋይል፣ ስለ ሕላዌ ምንነት እንድንረዳ ነገሩ ራሱን ለእኛ ክፍት የሚያደርግበት የእውነት ኀይል፣ እና የቅዱሱ እርሱም የነገር መጀመሪያ እና መደምደሚያ የሆነው፣ የህለውናው መገለጥ ኋይል ነው።

እንደገና ደግሞ፣ እንዲህ ልትል ትችላለህ፦ “እኔ ይህን ኀይል አላውቅም። እንደዚህ አይነት የሕይወት ልምምድ ውስጥ አልፌ አላውቅም። እኔ ሃይማኖተኛ አይደለሁም። ወይም ቢያንስ ክርስቲያን መኖን ነበረብኝ ግን እኔ ክርስቲያን አይደለሁም እና በእርግጠኝነት ይህ መንፈስ በውስጤ የለም። ከንግግርህ የምረዳው፣ የሆነ የሚያስጨህ የሚያስፈነድቅ ነገር ሳይሆን አይቀርም፤ እኔ ደግሞ እርጋታ እወዳለሁ። መለኮታዊ ሚስጥርም ይመስላል፤ እኔ የተሰወረን ነገር ወደ ብርሃን ለማምጣት ነው የምሞክረው። ራስን መስዋእት፣ መሰጠት የሚጠይቅ ነገርም ነው መሰለኝ፤ እኔ እንደሰው መድረስ ከምችልበት ለመድረስ እና ማሳካት የምችለውን በራሴ ለማሳካት እፈልጋለሁ” ልትለኝ ትችላለህ። ለዚህ መልሴ እንዲህ የሚል ነው። በእርግጥ፣ በብዙዎቻችን ሕይወት ውስጥ ላይከሰት ይችላል፣ ነገር ግን መንፈሳዊ ኋይል፣ አንዳንድ ሰዎችን እጅግ በሚያስፈነድቅ የሐሴት እና ደስታ ሁኔታ ውስጥ ይከታቸዋል። አንዳዶቹን ደግሞ፣ አብዛኞዎቻችን እናድርገው ብንል እንኳን አቅሙ ወደሌለን አይነት፣ ሰውነትን መስዋዕት አድርጎ ወደማቅረብ ሕይወት ሊወስዳቸው ይችላል።

ለአንዳንዶቹ ደግሞ፣ ለብዙዎቻችን እንደሰማይ የራቀንን፣ እጅግ ጥልቅ የሆነ የሕላዌን “ቅድስተ ቅዱሳን” በአስተውሎት የመዘለቅ አብርሆት ሊሰጣቸው ይችላል። ነገር ግን በእንዲህ ያለ መልኩ በሌሎች የመሥራቱ እውነታ በእኛም ውስጥ መንፈሱ እየሰራ እንደሆነ ላለመቀበል የምናደርገውን ማንገራገር ትክክል አያደርገውም። በዚህ መልክ በእኔ ስለማይሰራ፣ እኔ ውስጥ እየሰራ አይደለም ብለን ለመናገር ምስክር አይሆነንም። ያለምንም ጥርጥር፣ መንፈሱ በየትኛውም ስፍራ በሚሰራበት ጊዜ፣ ጥቂትም ቢሆን ራስን መስዋዕት አድርጎ የማቅረብ ቁጥቋጦ አለ፣ የቱንም ያህል ደካማ ቢሆንም በመንፈሱ ሐሴት የማድረግ እርሾ አለ፣ ምናልባትም ብልጭ ብሎ የሚጠፋ አይነት ቢሆንም የሕላዌን “ቅድስተ ቅዱሳን” በአስተውሎት የመዘለቅ አብርሆት ዘር በውስጣችን አለ። እናም እነዚህ ጥቂት በመንፈሱ ኋይል በሕይወታችን የሆኑ ነገሮች ህልውናው በሕይወታችን እንዳለ ለማስረገጥ በቂ ናቸው።

ነገር ግን የመንፈሱ ህልውና ሌሎች የሚታወቁ እና ማንም ሰው በቀላሉ ሊለያቸው የሚችል መገለጫዎች አሉት። እራሳችሁ “ይህ አይነቱ ልምምድ በሕይወቴ ውስጥ አለ፥ ካለ በምን ያህል ደረጃ?” እያላችሁ እየጠየቃችሁ ሳለ፤ እኔ ደግሞ አንዳዶቹን ልዘርዝራቸው። መንፈስ ቅዱስ ለአንድ ሰው በለሆሳስ ድምፅ፥ ሕይወቱ ባዶ እና ትርጉም የለሽ እንደሆነች፥ ግን ደግሞ ባዶነቱን ሊሞላለት እና ድንዛዜውን ድል ሊነሳለት፥ አዲስ ሕይወት በአንተነትህ ውስጠኛው ክፍል በር ላይ ቆሞ እየጠበቀህ ነው እያለ በማያቋርጥ ድምፅ በመንገር በውስጡ ሊሰራ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰው በቀኑ ክፋት ውስጥ ካለው አፀያፊ ድርጊት ተቃርኖ ወደከበረው ነገር እንዲገሰግስ የማንቃትን ሥራ በውስጡ ሊሰራ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ፥ በዙሪያው እና በራሱ ውስጥ የፈራረሰ እና የተበላሸ ነገር ቢኖርም እንኳን፥ አሁንም የቀናውን ነገር እንዲመርጥ፣ ለሕይወት “እሺ” እንዲል፣ በጤነኛው መንገድ እንዲጓዝ ብርታት በመስጠት በሰውዬው ውስጥ ሊሰራ ይችላል። መንፈስ ቅዱስ አንድ ሰው ሌላውን ሰው እጅግ እንደጎዳው፣ እንዳሳዘነው ሊገልጥለት፥ ግን ደግሞ ያው መንፈስ፥ ከበደለው ሰው ጋር ዳግም መልካም ግንኙነት እንዲኖረው የሚደርግ ቃል ሊሰጠው ይችላል።

ቅዱሱ መንፈስ አንድን ሰው እና ሁላችንንም፥ በጣም የምንጠላውን፥ ኖረም ሞተም ምንም የማይመስለንን ሰው፥ በመለኮታዊ ፍቅር እጅግ አብልጠን የምንወድ ሊያደርገን ይችላል። ቅዱሱ መንፈስ፥ የሕይወትህ ዓላማ እንደሆነ ወደምናውቀው እንድንገሰግስ ሐኬተኝነታችንን ድል ሊነሳው፣ እና ነውጥ የሞላውን እና ድባቴ ስሜታችንን ወደ መረጋጋት እና ወገግ ወዳለ ቀን ሊለውጠው ይችላል።

መንፈስ በእኛነታችን ውስጥ፥ ቅርባችን፣ ጓደኞቻችን እና ወዳጆቻችን በሆኑ ላይ በስውር ካስቀመጥነው ጥላቻ እና በድለውናል በምናላቸው ላይ ደግሞ በአደባባይ ልናደርግ ከምናስበው በቀለኝነት፥ ነፃ ሊያወጣን ይችላል። በምናባችን የፈጠርነው፥ ምክንያት የሌለው ጭንቀታችንን እንድንጥል እና በመኖር ውስጥ ያለን ጭንቀት እንደ አመጣጡ እንድንጋፈጥ ብርታት ሊሰጠን ይችላል። መንፈስ፥ ሕይወታችን ሊሄድ ወደሚገባበት አቅጣጫ እንዲሄድ ድንገት፥ ግንዛቤ እንዲኖረን፣ መነሳሳት ውስጥ እንድንገባ ሊያደርገን እና ሁሉን ነገር እንደገና እንደ አዲስ (አመለካከታችንን፣ ልምምዳችን እና የለመድነውን ነገር ሁሉ ወደሚያስቀይር) እንድናይ፥ አይናችንን ሊያበራ ይችላል። መንፈስ በተለመደው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ውስጥ ሳለን፤ እንዲሁም ባለንበት ጥልቅ ሀዘን ውስጥ ደስታን ሊሰጥን ይችላል።

መንፈስ፥ ውስጣችንም፣ ዙሪያችንም ሲቀዘቅዝ እና የስሜት ድብታ ውስጥ

ስንገባ፥ ከዛ ሁኔታ እንድንወጣ ሊረዳን ይችላል እና ደግሞ ለምንወዳቸው ሰዎች የነበረን ፍቅር ሲጠፋ መልሰን እንድናገኘው፥ ጥበብንና ብርታትን ሊሰጠን ይችላል። መንፈስ ወደ ግራ መጋባት እና ጭንቀት ሊወረውረን ይችላል፥ መልሶ ደግሞ ሕይወት ሙሉ በሙሉ ፊቷን እንዳዞረችብን በተሰማን እና እኛው ራሳችን እኛነታችንን ሙሉ በሙሉ በጣልን ወቅት፤ እስከ ሆነው ማንነት ሙሉ ሰው እንደሆንን፣ ነጋችን በተስፋ የሞላ እንደሆነ አንድንቀበል እርግጠኝነትን ሊሰጠን ይችላል። በመንፈስ ህልውና ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ሊኖረው የማይችለው አይነት የፀሎት ሕይወት ሊሰጠን ይችላል። ድምፅ አውጥተን ሆነ በፀጥታ የምንፀልየው ፀሎት እኛን ህልውናችንን ካገኘንበት ከመለኮት ጋር እንደገና መገናኘት አንድችል የሚያደርግ ፀሎት ከሆነ በእኛ ውስጥ እና በእኛ አልፎ የሚሰራው የመንፈስ ሥራ ነው። ፀሎት ማለት ውስን የሆነው እኛነታችን ወደ ምንጩ፣ መነሻው ለመመለስ ያለው መንፈሳዊ ርሃብ ማለት ነው።

መንፈሱ በህልውናው ከእኛ ጋር እና በእኛ ውስጥ እንደተገኘ ምልክት የሚሆኑ የመንፈስ ቅዱስ ሥራዎች አሉ። እነዚህን መገለጫዎች በአዕምሮአችን እንየዝና፥ አሁን መንፈሱ ከእኔ ጋር የለም ብሎ አፋን ሞልቶ ሊናገር የሚችል ማን ነው? አንድ ሰው፥ ሌላን ሰው አፋን ሞልቶ፥ ያ ሰው መንፈሱን በውስጡ የተሸከመ አይደለም፥ ሊል የሚችል ማን ነው?ምልክቶቹ ብስለቱ እና እድገቱ ጥቂት ሊሆን ይችላል ነገር ግን ማንም ከመካከላችን ስለራሱ ከዚህ በላይ የሚናገር አለን?

አንድ ሰው የመንፈስን መገኘት፥ ከምንተነፍሰው፣ ዙሪያችንን ከከበበን፣ ቅርባችን ከሆነው እና በውስጣችን ያለው ሕይወት እንዲሰራ ከሚያደርገው አየር ጋር ማነጻጸር ይቻላል። ይህ ንፅፅር ልክ እንደሆነ የሚያስረግጥልን ብዙ ነገር መጥቀስ እንችላለን። በብዙ ቋንቋዎች “መንፈስ” የሚለው ቃል፥ እስትንፋስ ወይም ነፍስ ማለት ነው። አንዳንድ ጊዜ ንፋሱ፥ አውሎ ንፋስ፣ ታላቅ እና አውዳሚ ይሆናል። አብዛኛው ጊዜ ወደግራ እና ቀኝ ይነፍሳል፥ መገኘቱ አለ፥ ግን ማንም አያስተውለውም።

በተመሳሳይ መንገድ፥ መንፈስ ሁልጊዜ አለ፥ የሚንቀሳቀስ ኀይል ነው። አንዳንድ ጊዜ ከቁጥጥር ውጪ በሆነ የፈንጠዚያ እና የደስታ ማዕበል ግለሰቦችን እና ሕብረቶችን ያጥለቀልቃል። ብዙ ጊዜ ግን በፀጥታ ውስጥ ይሰራል፥ ወደ መንፈሳችን ዘልቆ ይገባል እና መንፈሳችንን ንቁ ያደርገዋል። አንዳንድ ጊዜ በታላቅ የታሪክ ክስተት ላይ ወይም በግለሰብ ሕይወት ውስጥ ይገለጣል። ነገር ግን ብዙ ጊዜ፥ በስውር ነውጥ እና ጩህት በሌለበት፥ በዕለት ዕለት ሕይወታችን መካከል፥ ከሰዎች

እና ከምድር ጋር በምናደርገው ጉድኝት ውስጥ ይሰራል። አንዳንድ ጊዜ ተፈጥሮን ብቻ በመጠቀም፣ አንዳንድ ጊዜ የሃይማኖት ማሕበሮችን እና ያላቸውን መንፈሳዊ እንቅስቃሴ በመጠቀም ይሰራል። እና ደግሞ ብዙ ጊዜ ሰዎች ሃይማኖታዊ ስፍራ ወይም ሃይማኖታዊ ነው ብለው በማያስቡት ነገር መሐል ራሱን ይገልጣል፤ መገኘቱ ይታወቃል:::: ልክ እንደነፋስ መንፈስም ወደፈቀደበት ይነፍሳል! እርሱ በሕግ እና ውስን በሆኑ ዘዴዎች ቁጥጥር ውስጥ የሚያዝ አይደለም! ከሰዎች ጋር ያለው ግንኙነት፥ በሰዎች እና በሚያደርጉት ነገር ላይ የተመሠረተ አይደለም። መንፈስን በራሳችን ውስጥ፣ በግለሰቦች ውስጥ እና በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንኳን አስገድደን እንዲሰራ ልናደርገው አንችልም።

ምንም እንኳን ቤተ ክርስቲያንን የመሠረታት እርሱ ክርስቶስ ራሱ ከመንፈስ ቢሆንም ደግሞም አዎን በእርሱ በኩል የተገለጠው የመንፈስ ኃይል የመንፈስ ቅዱስ ህልውና መገለጥ የመጨረሻ ጣሪያው ነው፤ ነገር ግን መንፈስ ቅዱስ በቤተ ክርስቲያን ጣሪያ ስር የታሰረ ወይም በማናቸውም የተገደበ አይደለም። ቅዱስ መንፈስ በቤተ ክርስቲያን አጥር ወይም በማናቸውም የታጠረ የተገደበ አይደለም። መንፈሱ በሰዎች መንፈስ ውስጥ በማንኛውም ሰው ሁኔታ ውስጥ ለመሥራት የሚከለክለው ነገር የሌለ የነፃነት መንፈስ ነው። እና እርሱ እንደወደደ እንዲሰራ ሰዎች እንዲያውቁ ያሳስባል። መንፈስ የሆነው እግዚአብሔር፥ ሁልጊዜ ለሰዎች መንፈስ ቅርብ ነው።

ነገር ግን ታዲያ መዝሙረኛው ለምን "መንፈስህን ከእኔ ላይ አትውሰድ!" በማለት ይጸልያል? አሁን ባለንበት ዘመን በሥነ ጽሑፍ እና በሥነ ጥበብ ሥራዎች ውስጥ ደጋግሞ እየተጠቀሰ ያለ እና ከሁሉም በላይ ደግሞ ስፍር ቁጥር የሌላቸው ሰዎች በግል ሕይወታቸው ውስጥ እየሆነ ላለው ነገር ዋነኛ ምክንያት እንደሆነ የሚጠቅሱት ቃል "እግዚያአብሔር ፊቱን ሰውሯል" የሚል ነው። እና ለምንድን ነው ዛሬ በእኛ ዘመን "እግዚያአብሔር ፊቱን ሰውሯል" እያልን የምንናገረው? የቅዱሱ መንፈስ መገኘት አለ የሚለውን መልዕክት፤ እግዚያአብሔር ፊቱን ሰውሯል ከሚለው መልዕክት ጋር እንዴት ነው የምናስታርቀው? "ፊቱን ስለሰወረው" አምላክ፥ ፊቱን የሰወረበት ምክንያት ምንድን ነው? ብዬ በመጠየቅ አንድ ነገር ልበል። በልባችን ድንዳኔ ምክንያት፣ በግድየለሽነታችን ምክንያት፣ ከልባችን የሆነ ነገር ስለሌለን አስመሳዮች ስለሆንን፣ ቅንነት በጎደለው የማያባራ ጥያቄአችን ምክንያት፣ ወይም ተገቢነት በሌለው ወይም በአጓጉል ጥርጣሬያችን ምክንያት ብለን መልስ ልንሰጥ እንችላለን።

እነዚህ ሁሉ መልሶች የተወሰነ እውነት አላቸው፣ ግን በቃ ይሄ ብቻ ነው ብለን እጃችንን አጣምረን እንድንቀመጥ የሚያደርጉ ብቻኛ መልሶች አይደሉም። እግዚአብሔር ፊቱን እንዲሰውር የሚያደርገው ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ የመጨረሻው መልስ እግዚአብሔር ራሱ ነው የሚል ነው!

ቅዱሱ መንፈስ፣ ከጥቂት ሰዎች ሕይወት ብቻ ሳይሆን፣ ነገር ግን በሆነ ዘመን እና ወቅት፣ እግዚያአብሔር ከብዙ ሰዎች ፊቱን እንዲሰውር የማድረግ ሥራ ይሰራል። እና አሁን የምንኖርበት ዘመን፣ እግዚያአብሔርን የምናውቀው ፊቱን በሰወረ እግዚያአብሔርነቱ ነው። ነገር ግን፣ እግዚያአብሔር ፊቱን እንደሰወረ ስንገነዘብ፣ ስለእርሱ አለመኖር ያለን እውቀት፣ አሁን ከሕይወታችን እንደጠፋ፣ በአንድ ወቅት ግን የእኛ እንደነበረ አንዳች ነገር ወይም አንድ ሰው ይኖርበት የነበረ ቦታ፣ አሁን ባዶ ሆኖ በሚሰማ ስሜት እናውቀዋለን። በዚህ መንገድ አሁንም የእርሱ መኖር ግንዛቤ አለን። እግዚያአብሔር ሁልጊዜ ወሰን በሌለው ቅርበት ቅርባችን ነው፤ ደግሞም ወሰን በሌለው እርቀት ከእኛ እሩቅ ነው። እርሱን በሙላት የምናውቀው፣ እነዚህን ሁለቱንም ገፅታዎች በሕይወታችን ስንለማመድ ነው።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ፣ ስለ እሱ ያለን ግንዛቤ ጥልቀት የሌለው፣ የልምድ፣ ሞቃት ወይም ቀዝቃዛ ያልሆነ፣ እጅግ አብዝተን ከመላመዳችን የተነሳ ምንም የደስታ ስሜት የማይሰጠን ሲሆን፣ እጅግ ቅርባችን ሆኖ ሳለ እርሱ እሩቅ እንደሆነ አድርገን ስንቆጥር፤ እርሱ ያንን ጊዜ ፊቱን ከእኛ ይሰውራል። ይህ ሲሆን ቅዱሱ መንፈስ ህልውናውን ከእኛ አይወስድም። ነገር ግን የእግዚአብሔር መንፈስ እግዚአብሔርን ከአይናችን ይሰውረዋል። በቅዱሱ መንፈስ ላይ የሚደረግ የትኛው ተቃውሞ፣ የትኛውም ቸልተኝነት እና የትኛውም አይነት ጥርጣሬ ቅዱሱን መንፈስ ገፍቶ እንዲሄድ ሊያደርገው አይችልም። ነገር ግን ሁልጊዜ ህልውናው በመካከላችንም እያለም ቅዱሱ መንፈስ ራሱን ከእኛ ይሰውራል ይህም ማለት እግዚያአብሔርን ከእኛ ይሰውራል ማለት ነው።

እናም ቀጥሎ ቅዱሱ መንፈስ፣ ዓይኖቻችንን ገልጦ፣ እግዚአብሔር ፊቱን ከእኛ እንደሰወረ እና በውስጣችን ማደሪያው የነበረ ስፍራ ባዶ እንደሆነ ያሳየናል። ቅዱሱ መንፈስ ለዘመናችን እና ቁጥራቸው እጅግ ለበዛ በዘመናችን ላሉ ሰዎች እግዚያአብሔር ፊቱን እንደሰወረ እና በእግዚአያብሔር እንዲሞላ በውስጣችን የሚጮህውን ባዶ ቦታ አመላክቷል። እና ምናልባት ፊቱን የሰወረው እርሱ ፊቱን ሊመልስ እና ለእርሱ የተገባውን በእኛ ውስጥ ያለውን ቦታ ይ ሊቆጣጠር፣ ህልውናው እንደገና ወደ ውስጠኛው ማንነታችን ጥሶ በመግባት በእውነት ማን

እንደሆንን እንድንገነዘብ ሊያነቃን፣ ሊያናውጠን እናም እንደሌላ ሰው አድርጎ ሊለውጠን ይሆናል። ይህ የሚከሰተው ልክ እንደ ማዕበል መምጣት ዓይነት ይሆናል፤ የቅዱሱ መንፈስ ማዕበል፤ በተከማቸበት አንድ ቦታ ታምቆ አልንቀሳቀስ ያለውን፤ የመንፈሳዊ ሕይወታችንን አየር ያናውጠዋል፤ ቀጥሎ መዕበሉ ፀጥ ይላል፤ ተመልሶ ደግሞ ሌላ አይነት ደለል ይከማቻል። በመንፈስ ያለ ሕይወት፤ የመውረድና የማውጣት፤ የሆነ ጊዜ የሚቆም፤ ሌላ ጊዜ ደግሞ የሚሄድ ሕይወት ነው፤ ይህ ማለት እግዚአብሔር ፈቱን ሰውሮብንም ወይም በመገኘቱ ብንረሰርስ፤ ሁለቱም የሕይወት ልምምድ የአንዱ የመንፈስ ሰራ ነው።

# 3.

አሁን በውስጣችን፣ የህልውናው መገኘት ምልክት የሆነውን፣ ከዛ ውስጥ ምልክት እጅግ ታላቅ የሆነውን ምልክት ልንገራችሁ። ጳውሎስ “ፊደል ይገድላልና መንፈስ ግን ሕይወትን ይሰጣል።” ሲል በተናገረው ቃል ውስጥ፣ በተሻለ ሁኔታ ተገልጦ እናገኛለን። በአንድ ሰው ውስጥ፣ የመንፈሱ ህልውና በሙላት እየሰራ ነው የምንለው፣ ከሕግ ቀንበር ነፃ አውጥቶት በመንፈስ ወደሆነ ነፃነት ከወሰደው ነው። ይሄ ልክ የሞት ፍርድ ተሸሮ እስረኛው አዲስ ሕይወት እንዲኖር ሁለተኛ እድል ሲያገኝ አይነት ነው። እነዚህ ቃላት፣ በንግግር የማይገለጥ፣ በርግጥ ጥቂቶች ብቻ ተለማምደውት ያለፉት ሆኖም ግን እኛ ሁላችን ይህ አይነቱ የሕይወት ልምምድ ሊኖረን የሚችል፣ እጅግ ጥልቅ የሆኑ መንፈሳዊ ልምምዶችን ተሸክመዋል። ይህ ጥልቅ መንፈሳዊ ልምምድ እንደ ፖል፣ አውጉስቲን እና ሉተር ባሉ ሰዎች ኀይለኛ አብዮት በማሥነሳት፣ መንፈሳዊ ዓለምን ለውጧል። በዚህም አብዮት በኩል የሰው ልጆችን ታሪክ ቀይሯል። ጥያቄው እኛ እንደዚህ አይነት ጥልቅ ልምምድ ሊኖረን ይችላል ወይ ነው።

መጀመሪያ ሁላችንም ገዳይ የሆነው የፊደል ሕግ ኀይል አንቆ የያዘን እጁ እየተሰማን ነውን፣ በአስርቱ ትዕዛት ውስጥ የተፃፈው የፊደል ሕግ ወይም ይህ የፊደል ሕግ ስፍር ቁጥር በሌለው ሁኔታ በመጽሐፍ ቅዱስ እና በታሪክ የተብራራው ትርጓሜውን ጨምሮ ያለውን ትእዛዛት ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን በማሕበረ ሰብ እና በወላጆቻችን የስልጣን ብዕር፣ ከህፃንነታችን ጥልቅ በሆነው በእኛነታችን ክፍል ተጭኖብን፣ አሁን ደግሞ በአዕምሮአችን ውስጥ በመገለጥ፣ በምንሰራው እየፈረደብን፣ ከሁሉም በላይ በማንነታችን አንተ እንዲህ ነህ እንዲያ አይደለህም እያለ እየፈረደብን ያለውን፣ ከመንፈስ ሳይሆን ከፊደል የሆነው ሕግ የመግደል ኀይል፣ በትክክል ተሰምቶናል? ማንም ሰው ከዚህ በውስጣችንም በውጪም ከተፃፈ የፊደል ሕግ ድምፅ ማምለጥ አይችልም። እና ይህን ድምፅ ዝም ለማሰኘት ከሞከርን፣ ጆሯችንን በዚህ ድምጽ ላይ ለመዝጋት ስንሞክር፣ ቅዱሱ መንፈስ ራሱ እነዚህን ሙከራዎቻችንን ያከሽፋል።

በዘላለም ዓለም አይን ፊት፣ ማን እንደሆንን እና ምን መሆን እንዳለብን፣ እውነተኛው እኛነታችን የሚጮህውን ጩህት እንድንሰማ፣ ልንደፍን የሞከርነውን ጆሮ ይከፍተዋል። በእኛ ላይ ከተላለፈው ከዚህ ፍርድ ማምለጥ አንችልም። ቅዱሱ መንፈስ ራሱ፣ ሕግ፣ ትእዛዛቱን በመጠቀም፣ ከቶም ከዛ ድምጽ ማምለጥ

እንዳንችል ያደርገናል። መንፈስ ቅዱስ አስቀድሞ በሞት ጥላ ውስጥ እንድናልፍ ሳያደርገን ሕይወትን አይሰጥንም። አዎን! እርግጥ ነው! እጅግ አስፈሪ በሆነው ምስሉ፥ የፊደል ሕግ የመግደል ኃይል አለው። መጥፎ ነገር ይመጣልኛል ብለን የምንለውን ነገር በኛ ላይ በመጫን፥ ማድረግ ያለብንን ና ማድረግ የምንፈልገውን በማድረግ የምናገኘውን ደስታ ይገድላል። ከነገሮች እና ሰዎች ጋር ባለን ግንኙነት የምናምነውን እና የምናስበውን የመመለስ ነፃነታችንን፥ የሕጉን ፅላት በፊታችን በማስቀመጥ ይገድላል። የጊዜውን የዘመኑን ጥሪ የመስማት፣ የሌሎች ሰዎች ድምፅ የሌለው ድምፃቸውን የመስማት እና ዛሬ እና አሁን በዙሪያችን ባለው ነገር ውስጥ የመኖር ችሎታችንን ይገድላል። ብሳሳትስ በሚል ጭንቀት የሚመራውን ኅሊናችንን አሽንፈን፥ ማድረግ የሚገባንን የማድረግ ድፍረታችንን ይገድላል። ይህን የፊደል ሕግ ከምር ወስደው የሚከተሉትን፥ እምነት እና ተስፋቸውን በመግደል ራስን ወደመኮነን እና ተስፋ መቁረጥ ወስዶ ይጥላቸዋል።

ከዚህ ከተፃፈ የፊደል ሕግ ማምለጫ መንገድ የለም። መንፈስ ቅዱስ ራሱ አመቻማቾች፣ ግማሹን የሚፈጽም፣ ግማሽ ትዕዛዛቱን የምንጥስ ከመሆን ይከለክለናል። መንፈስ ቅዱስ፥ ወደ ቸልተኝነት፣ መረንነት ወይም ብዙ ጊዜ እንደምናደርገው፥ እኔ እኮ ጥሩ ነኝ ወደሚል የራስ ፅድቅ ለመሸሸግ ስንሮጥ፥ ራሱ ወደ ሚገድለው ፊደል እንድንመለስ ከፊታችን ይቆማል። ነገር ግን መንፈስ ራሱ ተመለስ ብሎ ሲጠራን፣ ሕይወት ሊሰጠን እንጂ በተፃፈው ሕግ ውስጥ እንድንያዝ አይደለም።

ቅዱሱ መንፈስ የሚሰጠንን ሕይወት እንዴት ልንገልጸው እንችላለን? በሁሉም ዘንድ የታወቀ፣ በራሱ በጳውሎስ፣ እና ከእርሱ በኋላ በተነሱ ታላላቅ የቤተ ክርስቲያን ሰባኪዎችና አስተማሪዎች ሲነገሩ የነበሩ ብዙ ቃላቶችን መጠቀም እችላለሁ። ከፊደል ሕግ ነፃ የሚያወጣን የቅዱሱ መንፈስ ሥራ ነፃነት ነው ማለት እችላለሁ። ወይም ደግሞ የእርሱ ሥራ እምነት ነው ማለትም እችላለሁ። ወይም ደግሞ የእርሱ ሥራ ተስፋ ነው ማለት እችላለሁ። እና ከሁሉም በላይ ደግሞ የቅዱሱ መንፈስ ሥራ ፍቅርን መፍጠር ነው። በዚህ ፍቅር ሕግ ሁሉ ወደ ሙላት እና ፍጻሜ መጥቷል። በተመሳሳይ፥ የፊደል ሕግ የመግደል ኃይል በዚህ ፍቅር ተሸንፏል። ነገር ግን እነዚህን ቃላት ብጠቀም ፊቱን የሰወረው እግዚያአብሔር ጥላ ዳግም በላያችን ላይ እንዲያጠላ እና አሁን እንዲህ መናገር እንደማንችል እንድንገነዘብ ሊያደርገን ይችላል። እንደዛ ያደረግን ቀን፤ ነፃነትን ከልቅነት ጋር እናምታታለን፣ እምነትን ከስሜት መጋለብ ጋር እናምታታዋለን፣ ተስፋን ተጨባጭ ያልሆነን ነገር አይን

አንጋጦ ከመጠበቅ ጋር እናምታታለን እና እኔ የመንፈስን መፍጠር በተመለከተ ስጠቀም እጅግ አብዝቼ የምወደው ፍቅር የሚለውን ቃል ነው እሱ ደግሞ “ፍቅር” ማለት የልቅ ስሜት ግልቢያ አድርገን ልንተረጉመው እንችላለን።

ቅዱሱ መንፈስ አዲስ ቃል ሊሰጠን ይገባል ወይም ደግሞ ቀድሞ የነበረውን ቃል እውነተኛውን ሕይወት ለመግለጽ የሚችሉ አድርጎ፥ ሊያድሳቸው ይገባል። መጠበቅ አለብን። ያ እንዲሆን መፀለይ አለብን። በግድ፣ በጉልበት አናመጣቸውም። ነገር ግን በኑሮአችን የሆነ ወቅት ሕይወት ምን እንደሆነ እናውቃለን። ሕይወት ታላቅ እና ቅዱስ፣ ጥልቅ እና የተትረፈረፈ፣ የሚያስፈነድቅ እና የተረጋጋ፣ በጊዜ የተገደበ እና የተምታታ፣ እና ሙላቱን በዘላለማዊነት ያገኘ መሆኑን እናውቃለን። እግዚአብሔር ፊቱን በሰወረበት ጊዜ፥ ሁኔታውን ለመግለፅ ቃላት አቅም ቢያጥራቸው፣ መንፈስና ሕይወት ያለ ወሰን የተገለጡበትን የእርሱን መልክ፥ ቃል ሳንናገር እና ድምጽ ሳናሰማ መመልከት እንችላለን።

# 5. መዳን

*“ከክፉም አድነን እንጂ ...”*

*ማቴዎስ 6፥ 13*

በጌታ ጸሎት ውስጥ ያለው የመጨረሻው ልመና “ከክፉ አድነን” በሚል ቅርፅ ተቀምጦ እናገኘዋለን። ትርጉሙ የተሳሳተ አይደለም ነገር ግን ከዋናው ቅጂ “ክፉ ከሆነው ከእርሱ አድነን” ከሚለው ጥልቀት ጋር የሚቀራረብ አይደለም። እስቲ ስለእነዚህ ጉዳዮች፥ በተለይ “ማዳን” ስለሚለው አንድ ቃል እናሰላስል።

ክርስትና በትክክለኛው ማንነቱ የድነት ሀይማኖት ተብሎ ተጠርቷል። እና “ክርስቶስ” ደግሞ መዳንን ለሚያመጣው፥ ለአዳኙ የተሰጠ ሌላ ቃል ነው። ድነት፣ ማዳን እና አዳኙ፥ በብሉይም ሆነ በአዲስ ኪዳን፥ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ስፍር ቁጥር ለሌላቸው ጊዜያት፥ በታላላቅ የሥነ መለኮት ሊቃውንት ሥራዎች፥ በክርስቲያን ባለቅኔዎች ዝማሬዎች ውስጥ፥ በቅዳሴና በስብከት፥ በቤተ ክርስቲያን የእምነት መግለጫዎች ውስጥ፥ በእምነት ማፅኛ ማስተማሪያ መፅሐፎች እና ከሁሉም በላይ በግል የጸሎት ወቅት፥ ብዙ ጊዜ ጥቅም ላይ የሚውሉ ቃላት ናቸው። ልክ እንደሌሎች ጥቂት ቃላት፥ የክርስትናን አስተሳሰብ እና ሕይወት ዘልቀው ገብተዋል። ታዲያ እንዴት አጭር በሆነ፥ የስብከት ቦታ እና ሰዓት ውስጥ ስለእነዚህ ጉዳዮች መናገር ይቻላል?

ምናልባት የማይቻል ነገር ይሆናል! ግን እንደዚያም ቢሆን መስበኩ እጅግ አስፈላጊ እንደሆነ አስረግጬ ልናገር። ምክንያቱም ትክክለኛ ትርጉማቸው፣ በእነዚህ ቃላት በኩል መተላለፍ ያለበት መልዕክት፣ ከነአካቴው የመጥፋት ደረጃ የሚደርሰው እና በሰው ልጆች ላይ የሚያመጡት ተጽዕኖ የሚዘነጋው እነዚሁ ቃላት ናቸው። የሚቻል ከሆነ እንዲህ ያሉ ቃላት እንደገና መወለድ አለባቸው። እና ዳግም መታደስ የማይችሉ ከሆነ፥ በባህል ለረጅም ጊዜ ተጠብቀው የቆዩ ቢሆኑም መተው አለባቸው። ነገር ግን፥ የመጀመሪያ ትርጉማቸውን እና ኀይላቸውን እንደገና ለመመለስ ያለው አንድ መንገድ ብቻ ነው። እርሱም እነዚህ ቃላት፥ ለሕይወታችን

ምን ማለት እንደሆኑ እና በፍጻሜውም እጅግ አስፈላጊ የሆነ ሊያስተላልፉ መቻል አለመቻላቸውን፥ ራሳችንን በመጠየቅ ነው። ይህ በክርስትና ሐይማኖት ውስጥ ለምንጠቀማቸው፥ ለምሳሌ እግዚአብሔር እና ክርስቶስ፣ መንፈስ እና ቤተ ክርስቲያን፣ ኀጢአት እና ይቅርታ፣ እምነት፣ ፍቅር እና ተስፋ፣ የዘላለም ሕይወት እና የእግዚአብሔር መንግስት ለመሳሰሉት ቃላት እና ቋንቋዎች ሁሉ የሚሰራ ነው። ስለእያንዳንዳቸው ቃላት መጠየቅ ያለብን ነገር፥ እነዚህ ቃላት፥ የሕይወታችን ጥልቀት ውስጥ ዘልቀው፣ በማይደረስበት የእኛነታችን ክፍል በመግባት፥ ነክተውናል ወይስ አልነኩንም ብለን ራሳችንን መጠየቅ አለብን። አንድ ቃል በእኛ ዘመን እጅግ ወሳኝ ለሆኑ ጉዳዮች ግድ ለሚላቸው ብዙዎች ሰዎች ትርጉም የማይሰጥ ቃል ከሆነ የመጀመሪያውን ኀይሉን ካጣ፣ እንደገና ጥቅም ላይ መዋል የለበትም። ወይም እንደገና የቀድሞ መሰል ጉዳዮችን የማስተላለፍ ኀይሉን እስኪያገኝ መነሳት የለበትም።

ምናልባት ድነት፣ ማዳን እና አዳኝ የሚሉት ቃላቶች ራሳቸው የመዳን እድል ሊኖራቸው ይችላል። ከምንጩ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ ጥቅም ላይ ሲውሉ፥ ጥልቅ ትርጉም እና ለውጥ የሚያመጣ ጉልበት ነበራቸው። ነገር ግን፥ የ ማንነታቸው በዘመናት አዋራ ተሸፍኗል እና በዘልማድ አፍ ላይ እንደመጡ ከመጠራታቸው ብዛት ትርጉም አልባ ሆነዋል። እንግዲያውስ፥ የማይቻለውን ነገር ለማድረግ እንሞክር፣ እናም በዚህ ሰዓት “ነገረ ድነትን” የሃሳባችን መዳረሻ ይሁን።

በጌታ የፀሎት ትምህርት፥ 7ተኛው ልመና፥ ድነት ምንድን ነው ለሚለው፥ ሁለት የተለያዩ ምስሎችን ይጠቀማል፣ እርሱም “ማዳን” እና “መታደግ” የሚሉት ናቸው። ድነት የሚለው ቃል፥ በላቲን ሳልቩስ ከሚለው የተገኘ ሲሆን፥ ፍችውም ፈውስ እና ሙሉ መሆን ማለት ነው። አዳኙ የታመመውን እና የተጎሳቆለውን “ይፈውሳል እና ሙሉ” ያደርጋል። በግሪክ የፈውስ አምላክ አስክሊፒየስ አዳኝ ተብሎ ይጠራ ነበር። ኢየሱስ ራሱን ለህመምተኞች እንጂ፥ ለጤነኞች ያልመጣ ሀኪም ብሎ ይጠራ ነበር።

ማዳን ማለት አሁንም፥ መታደግ፣ የተያዘን ማስለቀቅ፣ ነጻ ማውጣት ማለት ነው። ይህ ደግሞ ሌላ ምስል ነው፥ በባርነት ውስጥ ነን። በባርነት ውስጥ አስሮ ያቆየን ደግሞ፥ በዓለም ውሰጥ የነገሮች ሁሉ መዛባት እና ሁሉን የማጥፋት ምልክት፥ ክፉ የሆነው እርሱ ነው። አዳኙ ደግሞ በማንነቱ ክፉ የሆነውን እርሱን እና ኀይሉን ያሸነፈ ነው። ሮሜ ምዕራፍ ስምንት ላይ ባቀረበው ታላቅ የድል መዝሙር ውሰጥ፥ ከጳውሎስ የበለጠ፥ እጅግ ግሩም እና ጥልቅ በሆነ ሁኔታ “አንዳቸውም

ይህን ዓለም የሚገዙ የአጋንንት ሀይላት ቢሆኑ ከእግዚአብሔር ፍቅር ሊለዩን አይችሉም" በማለት የአዳኙን የአሸናፊነት ምስል የተጠቀመ ማንም የለም።

ማዳን ማለት ከበሽታ መፈወስ ነው፤ ማዳን ከባርነት እሥራት ነፃ ማውጣትም ነው። ሁለቱ አንድ ናቸው። አንድነታቸውን በምሳሌ ላቅርብ። እንደታመመ አምኖ ሕይወትን የማይጋፈጥ፣ በአዕምሮ ህመም ወይም በሥነ ልቦና ችግር ውስጥ ያለ፣ አንድ ሰው አለ እንበል። ነገር ግን ህመሙን በዝርዝር ከገለጥን፣ ራሱን ከእጃቸው ፈልቅቆ ማውጣት ካልተቻለው፣ ከአቅሙ በላይ በሆኑ ኀይላት ስር ተቀፍድዶ እናገኘዋለን። አዲስ ኪዳን በሚገልፀው ቃል፣ እርሱ በአጋንንት የተያዘ ነው። በእርሱ ውስጥ በሽታ እና ባርነት አንድ ናቸው። እና በተወሰነ ደረጃ፣ ይህ የሁላችንም ሕይወት ነጸብራቅ ይሁን አይሁን እንጠይቃለን። ደግሞ ሆኖ ከሆነ፣ በምን መልኩ ፈውስ ያስፈልገናል ብለን እንጠይቃለን። ነፃ መውጣት የሚያስፈልገን ከየትኛው ነገራችን ነው? መዳን ለእኛ ምን ትርጉም ሊኖረው ይገባል?

በብዙዎች ምናብ እንደተሳለው፣ ድነት ማለት ከሲኦል አምልጦ ወደ መንግስተ ሰማይ መፍለስ ማለት አይደለም። ወይም እጅግ ደካማ በሆነ እና በተለመደው አጠራር፣ ከሞት በኋላ ያለ ሕይወት ማለት አይደለም። አዲስ ኪዳን ስለ ዘላለማዊ ሕይወት ይናገራል፣ እናም የዘላለም ሕይወት ከሞት በኋላ የሚቀጥል ሕይወት ማለት ግን አይደለም። የዘላለም ሕይወት፣ በጊዜ ክበብ ውስጥ የሌለ ማለትም ከትላንት፣ ከዛሬ እና ከወደፊትም ጊዜ ውጪ የሆነ ነገር ነው፣ ወጥተን የመጣንበት፣ አሁን በህልውናው ውስጥ እየኖርን ያለንበት እና ተመልሰን የምንገባበት ነው። ሁልጊዜ በቦታው ያለ ነገር ነው። እኛ የተገኘንበት እና በነፃነት እንድንካፈል በእርሱ የተወሰንበት መለኮታዊ ሕይወት ነው፤ ዘላለማዊ የሆነ እግዚአብሔር ብቻ ነውና። ለጢሞቴዎስ በተፃፈው ደብዳቤ ላይ እግዚአብሔር "እርሱ ብቻ የማይሞት ነው" እንደሚል፣ የሰው ልጅ የማትሞት ነፍስ ያለው፣ ኢ ሟቲነትን የእርሱ ርስት አድርጎ ሊመካ አይገባም። አይችልም። እኛ እንደማንኛውም ፍጥረት ሟች ነን፣ ከሁለንተናችን ጋር ሟች ነን፤ አካል እና ነፍሳችንን ጨምሮ፤ ነገር ግን ደግሞ በምድር ላይ ከመኖራችን በፊት፣ በጊዜ ሜዳ ውስጥ እየኖርን ሳለ እና የምድር ቀናችን ተቆጥሮ ካበቃ በኋላ፣ በእነዚህ ሁሉ ወቅት እኛ ግን በዘላለም ሕይወት ውስጥ ተሰውረን ነበር። መኖሪያችንን በዘላለም ውስጥ አድርጎልናል።

እዚህ እና አሁን፣ በጊዜ ሜዳ ውስጥ እና ከዚያ ውጪ በመለኮታዊ ሕይወት ውስጥ በነፃነት እንድንካፈል አስቀድሞ የተወሰነ ከሆነ፣ አንቆ ከያዘን እጆቹ እንድንለቀቅ የምፀልይበት፣ ክፉ የሆነው እርሱ ማለት እንግዲህ ከዘላለም

በፊት እንኖርበት ዘንድ የተወሰነልን የሕይወት እጣፈንታ እንዳናከናውን ባሪያ አድርጎ የያዘን ኀይል ነው ማለት ነው። እኛ እንድንካፈልበት ከተፈቀደልን የዘላለም ሕይወት የነጠለን ከፊታችን የቆመ ግንብ ነው። እናም በእርሱ ምክንያት ከዘላለም ሕይወት ተካፋይነት በመለየየታችን አሁን እኛ ሁለንተና እና በምንኖርባት ዓለም ያለው ህመም ሊኖር ችሏል። ይህ ባሪያ የሚያደርግ ኀይል ድል በተነሳ ቁጥር ሁሉ፣ ግድግዳው በፈረሰ ቁጥር፣ እና በሽታ በተፈወሰ ጊዜ ሁሉ ድነት ይሆናል ማለት ነው። ይህን ማድረግ የሚችል አዳኝ ይባላል። ደግሞ ይህን ማድረግ የሚችል፥ ከእግዚአብሔር በቀር ማንም የለም። በሰንሰለት የታሰሩት ራሳቸውን ነፃ ማውጣት አይችሉም። የታመሙ እንዲሁ ከቶም ራሳቸውን መፈወስ አይችሉም። ከተያዝንበት ባርነት ሙሉ በሙሉ የሚያስለቅቀን፣ ከበሽታችን ሙሉ አድርጎ የሚፈውሰን ኀይል የሚመጣው፥ እኛ ከቆምንበት፥ ከዘላለም ሕይወት ከነጠለን ግንብ፥ ወዲያ ማዶ ካለ ስፍራ የሚመጣው ነው። ይህ ማዳን እና መታደግ በሚሆንበት በማንኛውም ጊዜ፥ በእኛ ጊዜያዊ እና ሟች በሆነ ሕላዌ መካከል፥ የመለኮት ሕይወት፥ በዘላለም ዓለም ውስጥ ያለው እርሱ፥ ተገለጠ እንላለን። ሁሉም ነጻ አውጪዎች፣ ሁሉም ፈዋሾች በእግዚአብሔር ተልከዋል። ነጻ የሚያወጡት እና የሚፈውሱት፥ ከዘላለም ከሆነው ከእርሱ በተሰጣቸው ኀይል በኩል ነው።

እነዚህ ፈዋሾች እነማን ናቸው? እነዚህ አዳኞች የት አሉ? የመጀመሪያው መልስ የሚሆነው፦ "እዚህ ናቸው፣ እነሱም አንተ ነህ!" የሚል ነው። እያንዳንዳችሁ፥ ካህናት ተደርጋችሁ ለተሾማችሁት ለሌላ ሰው፥ ነጻ የማውጣት እና የመፈወስ ኃይል ተቀብላችኋል። ሁላችንም፥ አንዳችን ለሌላችን ካህናት እንድንሆን ተጠርተናል። የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብንሆንም፥ ደግሞም ሐኪሞች ነን። ሐኪሞች ብንሆንም፥ ደግሞም የምናፅናና ነን። ደግሞ አጽናኝ ብንሆን፣ ነፃ አውጪዎችም ነን። ስፍር ቁጥር የሌላቸው መጠናቸው እና አይነታቸው የተለያዩ የማዳን ጸጋ አግልግሎቶች አሉ። ክፋ የሆነው እርሱ እጅግ ብርቱ በሆነ እጅ፥ በብዙ ነገር ባሪያ ስላደረጋቸው በእነርሱ በኩል አልፎ የሚሰራው የማዳን ኀይል፥ ከውስጣቸው ወደ መጥፋት የተቃረበ ቁጥራቸው የበዛ ሰዎች አሉ። በሌላ በኩል ደግሞ፥ የማዳን ሥራ የተገለጠባቸው፥ በእነርሱ አገልግሎት ቁጥራቸው የበዛ ሰዎች፥ ተፅዕኖው ከትውልድ ትውልድ የተሻገረ፥ ነጻ የመውጣት እና የፈውስን ኀይል በሕይወታቸው የተለማመዱባቸው፥ እጅግ ታላላቅ የሆኑና በታሪክ የሚጠቀሱ ሰዎች አሉ።

ብዙዎቻችን በዚህ በሁለት አይነት ሰዎች መካከል ውስጥ ነን። ክርስትና የማዳን ጸጋን ያለ ገደብ የሚያይበት፥ በአጋንንት ኀይሎች ላይ ወሳኝ ድልን

የተቀዳጀ፥ ዘለዓለማዊ ከሆነው የነጠለንን የበደለኝነት ግንብ ያፈረሰ፣ በሰው እና በሚኖርበት ምድር ውስጥ አዲስ ኩነት ወደ ብርሃን ያመጣ፥ ሁልጊዜ ፈውስ በእጁ ያለ አንድ አዳኝ አለ። እርሱን አዳኝ ብለን ብንጠራው በእርሱ በኩል ድነትን ያደረገ እግዚያአብሔር መሆኑን ማስታወስ አለብን። እና ከመለኮት የሆነው መዳን ለሰው ልጆች ሁሉ እንዲሆን፥ ራሳችንን ጨምሮ፥ እግዚያአብሔር አልፎ የሚሰራባቸው ብዙ ነጻ አውጪዎች እና ፈዋሾች አሉ። እግዚአብሔር ዓለምን፥ በየትኛውም ቦታ እና በማንኛውም ጊዜ በእነርሱ በኩል ለሌላው ትድግና የሚሆኑ ሰዎች፥ ያለ ፈውስ ኋይል አይተዋትም።

አሁን ይህ ሁሉ ለራሳችን ሕይወት ምን ማለት ነው? እኛ ይህን አይነት የማዳን ኀይል መቼ እና የት ነው በሕይወታችን የተለማመድነው? ነፃ የወጣነው እና የተፈወሥነው መቼ እና የት ነው? ብለን ቀድመን አንስተነው የነበረውን ጥያቄ ደግሜ መጠየቅ አለብኝ።

ስለ ኢየሱስ በተነገሩት የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች ውስጥ ሁሌም ከሚታወሱት ክስተቶች ውስጥ አብዛኛው ክፍል የፈውስ ታሪኮች ናቸው። በእነዚህ የፈውስ ታሪኮች ውስጥ ሦስት አይነት ፈውሶች ሆነዋል፦ በአካል ሥጋ የታመሙ ሰዎች በቀጥታ ከበሽታቸው የተፈወሱበት፣ በአካል ሥጋ ታመው ይቅርታ እና ፈውስ ያገኙ እና የአዕምሮ ህመም ያለባቸው፥ ህመማቸው በአጋንንት መያዝ ስለነበር፥ ከአጋንንት እሥራት ነፃ የወጡ ናቸው። እጅግ በሚያሳዝን መልኩ ብዙ ስብከቶች እነዚህ ታሪኮች ስለህመም፣ ጤና እና ፈውስ ከዛም ደግሞ አዕምሮአችን እና ሥጋችን በማይነጣጠል ሁኔታ የተሳሰረ ስለመሆኑ ሊያሳዩን የሚችሉትን ጥልቅ እና መሠረታዊ መረዳት ከማሳየት ይልቅ የእነዚህን ታሪኮች ድንገታዊ የሆነውን ተዓምራታዊ ፀባይ ላይ መናገር የተኩሩ ናቸው። እነዚህ ታሪኮች አዳኝ ተብሎ በተጠራው በእርሱ የተፈጸሙ የድነት ታሪኮች ናቸው። በታሪኮቹ ውስጥ ማዳን ማለት ፈውስ ማለት እንደሆነ ግልፅ ነው። ቤተ ክርስቲያን ከመልዕክቶቿ ውስጥ፥ ይህን ክፍል በትክክል ተረድታ ቢሆን ኖሮ፥ በሃይማኖት እና በሕክምና ሳይንስ መካከል ያለው አሳዛኝ ግጭት፥ ፈጽሞ ላይኖር ይችል ነበር።

በሁለቱም ውስጥ፣ በቤተ ክርስቲያን እና በሕክምና፥ የማዳን ኀይል በሥራ ላይ ነው። ዛሬ የሕክምና ሳይንስ እና የአዕምሮ ህክምና የሚያደርገውን ተአምራት ብንመለከት፣ ክፉ ከሆነው ከእርሱ በሕይወታችን በአንዱ አቀጣጫ ነፃ መውጣታችን ተፈፅሟል እና አሁን በዘላለም እና በሚጠፋ ሕይወት መካከል ያለው ግድግዳ በአንድ በኩል ተቀደ ክፍት ሆኗል እናም በሐኪም ወይም የአእምሮ

አማካሪ በኩል ለአንድ ሰው የመዳን ቀን ሆኗል ብለን መናገር የሚገባን ደረጃ ላይ ነን። እንደማንኛውም አዳኝ፥ የማዳንን ሥራ እያከናወነ ያለው ሐኪም ወይም የሥነ ልቦና ባለሙያ ለተፈጥሮ እና ለሰው ልጅ በጊዜ እና በቦታ በመለኮት መግቦት መገኘት ውስጥ በተሰጠ የፈወስ ኀይል መጠቀሚያ በመሆን ነው።

ግን ይህ ዓይነቱ ፈውስ እና ነፃ መውጣትም ቢሆን የራሱ ውስንነቶች አሉት። በኢየሱስ የተፈወሱ ሰዎች እንደገና ታመዋል። ወደማይቀረው የሥጋ ሞትም ሔደዋል። ኢየሱስ እንዳስጠነቀቀው፥ ከአጋንንት ስቃይ ነጻ የወጡ፥ ምናልባት ወደ ባሰው የአዕምሮ ህመም ውስጥ ገብተዋል። በህክምና አማካኝነት ከህመማችን ድነን ግን ዳግም እንደምንታመመው ሁሉ፥ ተዓምራትም በጊዜ የሆነ ወቅት ውስጥ ዘለዓለማዊ ሕይወት ማዳኑ የሚታይበት ነው።

እንዲሁም፣ የአካል እና የአእምሮን ፈወስ በተመለከተ፥ በሁለተኛነት የምናስቀምጠው ውስንነት አለ፦ ይህም መፈወስ ያለበት ሰው ያለው አመለካከት፥ ፈውስን ሊከላከል ይችላል። ከክፋው የመዳን ፍላጎት ከሌለ ነፃ መውጣት የለም!የፈውስ ኀይልን ሳንናፍቅ ፈውስ የለም! ከዘላለማዊ ሕይወት የነጠለን ግንብ የሚፈርሰው መሻቱ ካለን ብቻ ነው፣ እርሱም ቢሆን ፈውሱን ይዘው የሚመጡትን የምናምናቸው ከሆነ ብቻ ነው። ለፈውስ ምክንያት የሆኑ ሰዎችንም ማመን ማለት በዘመናችን በእምነት ፈውስህን ተቀበል የሚሉትን ማለት አይደለም። እሱ ራስን ወይም ሌላውን ሰው በሳይኪክ ኀይል የማንፃት ወይም የመመተት ጥሩ ማሳያ ነው። ለፈውስ ምክንያት የሆኑ ሰዎችንም ማመን ማለት፥ በየትኛውም ጊዜ ከእንደዚህ አይነት አርነት የማውጣት ሥራ ጋር ፊት ለፊት በተገናኘን ጊዜ ሁሉ፥ ከክፋ እጅ አርነት ለመውጣት ልብን ክፍት ማድረግ ማለት ነው።

እንደዚህ አይነት ክፍት ልብ ሁልጊዜ አይገኝም። ከጤንነት ይልቅ በሽታን፤ ከነፃነት ይልቅ ባርነትን ልንመርጥ እንችላለን። ላለመፈወስ እና ነፃ ላለመውጣት የምንሻበት ብዙ ምክንያቶች አሉ። ደካማ የሆነ ሰው በአካባቢው፣ በቤተሰቡ እና በጓደኞቹ ላይ ፍላጎቱን የሚፈፅምበት ኀይል ያገኛል። ይህ ሁኔታ እምነትን እና ፍቅርን ሊያጠፋ ይችላል ነገር ግን ደካማነት ይህንን ስልጣን ለሚያመጣለት ሰው እርካታን ይሰጣል። ብዙዎቻችን ሳናውቀው በባል ወይም በሚስት ላይ፣ በልጆቻችን ላይ፣ በወላጆቻችን ላይ፣ በጓደኞቻችን ላይ እና በተለያዩ ቡድኖች ውስጥ የምናደርገው ይህን በድካማችን አሳበን መቆጣጠር አይደለም ወይስ ነው ብለን ራሳችንን እንጠይቅ። ነፃነትን የማይፈልጉ ሌሎች አይነት ሰዎችም አሉ። ምክንያታቸው ነፃ ከወጡ እና ከተፈወሱ፣ ጤንነት እና ነፃነት ተጨባጩን ዓለም እንዲጋፈጡ እና እንደ

ሰው የሕይወትን ቀንበር እንዲሸከሙ ማለትም በኋላፊነት እየወሰኑ እንዲኖሩ ግዴታ ውስጥ ይከታቸዋል። እናም የዚህ ፍራቻ በበሽታ እና በእሥራት ውስጥ መሆንን እንዲመርጡ ያደርጋቸዋል።

ይህ በተለይ በአእምሮ መታወክ እና የድብርት ባርነት ውስጥ ባሉ ሰዎች ላይ በተጨባጭ እናየዋለን። በርግጥ፥ ልክ በአካለ ሥጋ በተለያየ በሽታ እንደሚሰቃዩ ሰዎች፥ በአዕምሮ መረበሽ እና ድብርት ውስጥ ያሉም ሰዎች እንዲሁ ይሰቃያሉ፥ ነገር ግን ከስቃዩ በላይ በሌላው ላይ ያገኙት የመደመጥ፣ በስስት እና ጥንቃቄ የመያዝ፣ የሚደረግላቸው እንክብካቤ፣ ማባበል እና ያለ ሐላፊነት መኖር፥ በአጭሩ በሰው ላይ የሚያገኙት ኋይል እና ሐላፊነትን መሸሽ፥ ስቃዩን ችለው እንዲኖሩ ካሳ ይሆንላቸዋል። ስለዚህ ከድነት እና ፈውስ ይልቅ በሌላው ላይ ያገኙት ኋይል እና ሐላፊነትን መሸሽ የበለጠ አስፈላጊ ሆኖ ይታያቸዋል። ስለዚህ ራሳቸውን ከማዳን ኃይል ይነጥላሉ። በመጀመሪያ ለእነርሱ ይህ የማዳን ኃይል መሆን ያለበት፥ የሥጋ ወይም የአእምሮ ድነት እንዲያገኙ ፍላጎት እንዲኖራቸው፥ ልባቸውን የሚከፍት፣ የሚያዘጋጅ ነው።

ነገር ግን ኢየሱስ እንኳን ከብዙዎች፣ ምናልባትም ከአብዛኞቹ አድማጮቹ ጋር ፈውስን ይህን ማድረግ አልቻለም። እናም አንድ ሰው፥ የእያንዳንዱ ፈዋሽ እና ነጻ አውጪ የመጀመሪያ ሥራ፥ ሊያድናቸው በሚፈልጋቸው ሰዎች ውስጥ ያለውን፥ የበሽታ እና የባርነትን ፍቅር መስበር ነው ማለት ይችላል።

አሁን ደግሞ በዚህ ዓለም ውስጥ ስንኖር በጊዜ እና በቦታ የተወሰንን በመሆናችን ምክንያት የመጣውን ሌላ አይነት የባርነት እና የነጻነት ቅርፃችን እንመልከት። በቴክኖሎጂ ጉዳይላይ ከተነገሩት እና እኔ ራሴ በተቃውሞ ከተናገርኩት በተቃራኒ፣ ተፈጥሮን ቴክኒካል በሆነ መንገድ በመቆጣጠራችን ስለተገኘው የማዳን ኃይል መናገር እፈልጋለሁ። ይህ ዓይነቱ ተፈጥሮን በሳይንስ እድገት መቆጣጠር መቻሉ ከፍተኛ ደረጃ ላይ በደረሰበት እና በተመሳሳይ ጊዜ ኀጂ እና አጥፊ ገጽታዎች ከመቼውም ጊዜ በላይ በገሃድ እየታዩ በመጡበት ወቅት በዚህ ጉዳይ ላይ መናገር ድፍረት የሚጠይቅ ነው። ማንኛውም ቴክኒካል፣ ሳይንሳዊ ፈጠራ ሰውን ከእንስሳነት ደረጃው አንስቶ ከፍ ያደርገዋል፣ ከብዙ አድካሚ እና አሰልቺ ሥራዎች ነፃ ያወጣዋል፣ በጊዜ እና በቦታ የተገደበውን እንቅስቃሴውን አሸንፎ ወደ አሻው ቦታ እንዲበር ያስችለዋል፣ የተፈጥሮ አንድ አካል በመሆኑ ከማይቀርለት ስፍር ቁጥር ከሌላቸው ትልቅ እና ትንንሽ ክፋ ነገሮች ለምሳሌ አላስፈላጊ ሞት እና ህመም ይታደገዋል።

እነዚህን የቴክኖሎጂ ውጤቶች ገፍተው ከጣሉ በኋላ በአካል ሥጋ እና በአዕምሮ ሲጎዱ እንደገተነዘቡት አዳዲስ ቴክኖሎጂዎች ሰውን የማዳን ኳይል አላቸው። በቴክኖሎጂ ውስጥ የማጥፋት አቅምም እንዳለ እናውቃለን። በየጊዜው እየደገ የሚሄደው አዳዲስ የቴክኖሎጂ ፈጠራ፥ በምድር ላይ ያለውን ሕይወት ሁሉ ለማጥፋት እና የዓለም ፍጻሜን ለማምጣት እንደሚችል እናውቃለን። በተጨማሪም ጥልቅ እና ዘላቂ በሆነ መልኩ ስናየው ደግሞ የሰውን መንፈስ ድነት ከማግኘት ሊያርቀው እንደሚችል እናውቃለን። ሰው ራሱን ወደ ነገሮች እና ቁሳቁሥነት እንደሚቀይረው እናውቃለን። ቢሆንም በዚህ የሳይንስ እየደገ ታላላቅ ስኬቶችን ማስመዝገብ ውስጥ፣ አላፊ በሆነው ምድር ላይ ዘላለማዊ የሆነ ድንቅ ነገርን አግኝተናል። ስለ ማዳን ኳይል እና ስለ ድነት ስንናገር የሳይንስ እድገት እና የቴክኖሎጂ ፈጠራዎች ቸል ሊባሉ አይችሉም።

በጥንት ዘመን ታላላቅ የፖለቲካ መሪዎች አዳኞች ተብለው ይጠሩ ነበር። በውስጣቸው ያሉ ሕዝቦችን እና ቡድኖችን ከመከራ፣ ከባርነት እና ከጦርነት ነፃ አውጥተዋል። ይህም ሌላው የፈውስ ዓይነት ነው። የመጽሐፍ ቅዱስን የመጨረሻ መጽሐፍ ቃል የምታስታውሱ ከሆነ ቅኔያዊ በሆነ የቋንቋ አገላለፅ "..የሕይወት ዛፍ ነበረ፥ የዛፉም ቅጠሎች ለሕዝብ መፈወሻ ነበሩ።" ይላል። ሕዝብ እንዴት ሊፈወስ ይችላል? አንድ ሰው ከውጭ ገዢዎች ወይም ከውስጥ ጨቋኞች ነፃ ሊወጡ ይችላሉ ሊል ይችላል። ግን ሊፈወሱ ይችላሉ? ድነት ሊሆንላቸው ይችላል? ነቢያት መልሱን ይሰጣሉ፦ ሕዝብ ሊፈወስ፣ ድነት ሊያገኝ የሚችለው አንድ ሕዝብ በትክክል እንደሆን የተጠራበትን የሚወክሉ ጥቂት ሰዎች፣ ጥቂት ቡድኖች ካሉ ነው። እነዚህ ጥቂቶች ሊሸነፉ እና ላይደመጡ ይችላሉ። ነገር ግን መንፈሳቸው ሀገርን የሚጎዱ፣ የሚያጠፉ እና የሚያፈርሱ እርኩሳን መናፍስትን የመቋቋሚያ ሀይል ይሆናሉ።

በአንድ ሐገር ውስጥ እና በአንድ ሕዝብ ውስጥ ስለ የማዳን ኳይል ጥያቄ ከተነሳ፥ በፕሮፓጋንዳ የሚፈጠረውን ጭንቀት፣ በማስፈራሪያ የሚደራጀውን መንጋነት ወይም በድንቁርና የሚቀሰቀሰውን ጥላቻ ለመቋቋም እና ለመቃወም ፈቃደኛ የሆኑ፥ ጥቂቶች፣ እጅግ በጣም ጥቂቶችም ቢሆኑ እንኳን፥ አሉ ወይ የሚል ጥያቄ ነው። የዚህች ሀገር (እርሱ ይኖርባት የነበረውን አሜሪካንን ማለቱ ነው) የወደፊት እጣ ፈንታ እና መንፈሳዊ እሴቶች፥ እንደ እነዚህ ያሉ ጥቂት ሰዎች ወይም ቡድኖች በሕዝብ አስተሳሰብ እና ድርጊት ላይ በሚያሳድሩት በጎ ተፅዕኖ ላይ እንጂ፥ በአቶሚክ መከላከያ የሚጠበቀ እና ከትውልድ ትውልድ የሚተላለፉ አይደሉም።

የተደገፋት የአቶሚክ ኋይላችንን አይደለም።

ይህ ለአጠቃላይ ለሰው ልጆች በሙሉ የሚሰራ እውነት ነው። በአንድ ሐገር ውስጥ ይሁን ወይም ብዙ ሀገሮችን የሚያዳርስ፣ የሰው ልጆች የወደፊት ሁኔታ የሚወሰነው፣ የሰው ልጆችን ከሚመጣባቸው የመጥፋት አደጋ መታደግ በሚችሉ ቡድኖች ነው። በሰው ልጆች ውስጥ፣ እርስ በርስ፣ አንዱ ለሌላው መድሃኒት የመሆን ኋይል አለ። ነገር ግን በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ራስ በራስ የመጠፋፋት የተደበቀ መሻት አለን። የጥፋት ኋይል ወይም የመታደግ ኋይል፣ የትኛው ወገን እንደሚያሸንፍ በእያንዳንዳችን ምርጫ ላይ የወደቀ ነገር ነው። የሰው ልጅ፣ በዚህ ወይም በሚቀጥለው ዓመት፣ በሕይወት ስለመቀጠሉ ምንም መለኮታዊ ተስፋ የለም። ነገር ግን የሰው ልጅ፣ በዚህ ወይም በሚቀጥለው ዓመት በሕይወት ስለመቀጠሉ፣ በአንተ ወይም በእኔ ውስጥ በሚከናወነው መድሃኒት የመሆን ኀይል ላይ፣ የወደቀ ሊሆን ይችላል። (የማሕበራዊ ፍትሕ፣ የዘር እኩልነት እና የፖለቲካ ጥበብን በተመለከተ ከእኛ በአንዳንዶቻችን በኩል በሚሰራው መድሃኒት የመሆን እና የነፃነት የማምጣት ጸጋ መጠን ላይ የተመሠረተ ሊሆን ይችላል።) አብዛኛዎቻችን፣ ለራሳችን፣ በእኔ ውስጥ በሚሰራው የማዳን ኋይል የሰው ልጅ ሊጠፋም ሊለማም ይችላል ወደሚል እምነት ካልመጣን በስተቀር፤ መጥፋቱ አይቀርም።

ነገር ግን የዚህ የማዳን ኋይል መጠቀሚያ መሳሪያ ለመሆን፣ መጀመሪያ እኛው ራሳችን መዳን አለብን። ከመለኮት ሕይወት የነጠለን ግድግዳ መፍረስ አለበት። እኛን ከመለኮት ሕይወት የለየን ግድግዳ እንዳይፈርስ፣ በህመም እና በክፋው ባርነት ስር እንድንቆይ የሚያደርገን አንድ ነገር አለ። እርሱም አሁን እና ዛሬ ዘለዓለማዊው ሕይወትን፣ ድነትን በሕይወታችን እንዳንለማመድ የሚከለክለን፣ በውስጣችን ያለው መነጠል እና በደለኝነት ነው። በእኛ ላይ የተላለፈው እና እኛም በኅሊናችን ውስጥ አዎን ብለን የተቀበልነው የፍርድ ቃል፣ ተስፋ የመቁረጣችን እና የህመማችን ምክንያት ነው። (ፓል ቲሊች ይህን ሐሳብ ሲያሰፍር ህመም ለሚለው ቃል የተጠቀመው የኤግዚስተንሻሊዝም አባት ተብሎ የሚወደሰውን የሶረን ኪርክጋርድን በብዙዎች ዘንድ የምትወደስ መጽሐፍ ርዕስን ነው sickness unto death. የሰው ልጅ የነቃውና እና ያልነቃው የአዕምሮው ክፍል እና ሁለንተናው ምን እንደሆነ የተዳሰሰበት ድንቅ መጽሐፍ ነው። sickness unto death ከመፅሐፉ ጥቅል "ሐሳብ ለመሞት በመፈለግ እና ለመሞት ባለመቻል" በሥነ ልቦናችን የሚፈጠር ጭንቀት እና ተስፋ መቁረጥን ያመለክታል።

ፖል ቲሊች ደግሞ በዚህ ቦታ ለዚህ ሁኔታ የዳረገን በእኛ ላይ ያለው በደላችን

እና በበደላችን የተፈረደው እኛም አዎን ብለን የተቀበልነው ለህመማችን ወይም ለመሞት በመፈለግ እና ለመሞት ባለመቻል ሁኔታ ውስጥ የከተተን የፍርድ ቃል ነው ይለናል) እናም ከሕይወት ጋር ለመስማማት፣ ከዚህ ሁኔታ ልንፈወስ ግድ ይላል። ከክፋው እሥራት ነፃ የወጣ ሕይወት፣ የተፈወሰ አዲስ ሕይወት ነው። በጌታ ጸሎት ውስጥ ያሉት፣ የመጨረሻዎቹ ሁለት ፀሎቶች ማለትም በደላችንን ይቅር በለን እና ከክፋ አድነን እንጂ የሚሉት፣ በእውነቱ ተመሳሳይ ልመና ናቸው። የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ ናቸው። ኢየሱስን፣ አንተ ክርስቶስ ነህ ብለን ከጠራን፣ አዳኛችን ነው ካልን፣ በእርሱ ውስጥ እኛን እስከማንነታችን በመቀበል የሚፈውስ እና ደግሞ በእርሱ ማንነት ውስጥ ያለ አዲስ ፍጥረት በማሳየት ከታሰርንበት ነፃ የሚያወጣ ኀይል አይተናል ማለት ነው። በዚህም አዲስ ፍጥረት ምክንያት ከራሳችን ጋር፣ ከምንኖርባት ዓለም ጋር እና ምንጫችን ከሆነው የመለኮት ዓለም እና እኛነታችን ጋር እርቅ ሆኗል።

እና የመጨረሻው ጥያቄ ማን ይድናል፣ ማን ነፃ ይወጣል፣ ማን ይፈወሳል? የሚል ነው። አራተኛው ወንጌል እንዲህ ይላል፦ ዓለም፣ እኛ ቀድሞ ወጥተን የመጣንበት፣ በኋላም የተለየንበት፣ ደግሞም ዳግም ከምንመለስበት ዘላለም ጋር፣ ዳግም አብሮ መሆን ለሆነው ነገር ሁሉ (ለተፈጠረው ሁሉ)፣ ቃል ተገብቶለታል። ድነት ያገኘነው እንደ ግለሰብ ብቻ ሳይሆን፣ ከሁሉም ጋር በአንድነት እና ከአጽናፈ ዓለሙ  ሁሉ ጋር ነው። የእኛ ነፃ መውጣት፣ በባርነት የተያዙትን ባሉበት እንዲሆኑ የሚተው አይደለም። የእኛ መፈውስ፣ ለዓለም ሁሉ የሚደረገው የታላቁ ፈውስ አካል ነው። ስለዚህ አባታችን ሆይ በሚለው ፀሎት ውስጥ የምናገኘው ሁለቱ ፀሎት ማለትም ከክፋው አድነን፣ እና መንግሥትህ ትምጣ! የሚባሉት ፀሎቶች አንድ አይነት ናቸው። ይህ መንግስት፣ ነፃ የወጣው እና የተፈወሰው የእርሱ ፍጥረት ነው። ከጊዜ ተነስተን ወደ ዘላለማዊነት ስንመለከት፣ ተስፋ የምናደርገው ይህ ነው። አድነን፣ ፈውሰን፣ የሚለው ጩሀት፣ እየንዳንዳችን ከሰው ልጆች ሁሉ ጋር፣ በአንድነት እና ከመላው አጽናፈ ዓለሙ ጋር በህብረት ሆነን የምንጮህው ጩህት ነው። መለኮታዊው መልስ ይህ ነው፦ ከእኔ የተለየው፣ የእኔ ነውና ወደ እኔ እመለሳለሁ። በፊት እንዳደረኩት እና ወደፊትም እንደማደርገው፣ ዛሬ ነጻ እያወጣኋችሁ ነው። ዛሬ፣ “ነጻ እያወጣኋችሁ፣ እየፈወስኳችሁ ነው” የሚለውን እነዚህን ቃላት ስትሰሙ እሺ በሉ! የመዳንን ኀይል አትቃወሙ!

# 6. ሰው እና ምድር

*የጣቶችህን ሥራ ሰማዮችን ባየሁ ጊዜ፥ ጨረቃንና ከዋክብትን አንተ የሠራሃቸውን፥ ታስበው ዘንድ ሰው ምንድር ነው? ትጐበኘውም ዘንድ የሰው ልጅ ምንድር ነው? ከመላእክት እጅግ ጥቂት አሳነስኸው፤ በክብርና በምሥጋና ዘውድ ከለልኸው። በእጆችህም ሥራ ሁሉ ላይ ሾምኸው፤ ሁሉን ከእግሮቹ በታች አስገዛህለት፥*

*መዝ 8፡3-6*

## 1.

ከገል ቲሊች ሥራዎች ጋር የምናደርገውን ቆይታ እንቀጥላለን። በዚህኛው ክፍል ሥነ መለኮት እና ፍልስፍናን በማጣመር፥ ሰው ከምድር ጋር ስላለው ትስስር አዕምሮን ሰቅዞ በሚይዝ መንገድ እይታውን ያካፈለበት ሥራ እንመልከት። ፅሑፉንም ሲጀምር እርሱ በነበረበት ጊዜ አንቱ የተባሉ የሳይንሱ ዓለም ተወካዮች፥ በአይነቱ አዲስ የሆነ ምርምር እንዲካሄድ ጠይቀው እንደነበር ያነሳል። ይህም አዲስ ምርምር “ህልውናን የማቆየት ሳይንስ” (science of survival) ብለው ጠርተውት እንደነበር ይነግረንና ይህን ሲሉ ይላል “ግለሰቦችን፣ የሆኑ የማሕበረሰብ ክፍሎችን፣ ሐገሮችን ወይም ጎሳን ማለታቸው አይደለም። እሱን ማለታቸው ቢሆን ሲባል የቆየ ነገር ስለሆነ ምንም አዲስ ነገር አልነበረውም” በማለት የእርሱን ትኩረት ሊስብ የቻለውም የምርምር ጥያቄ አጀንዳ “የሰውን ልጅ በጥቅሉ፣ ወይም ስልጣኔ ያስገኘውን የሰው ዘር ወይም በአጠቃላይ በዚህ ፕላኔት ላይ ያለው ሕይወትን ማትረፍ” ማለታቸው ስለነበር ነው። በጸሐፊው ዘመን የነበሩ የሳይንሱ ዓለም ሰዎች፥ የሰው ልጅ በምድር ላይ የመኖር እድሉ እየተመናመነ እንደሄደ ጥርት ባለ ሁኔታ አይተዋል።

እነዚህ ሰዎች ያቀረቡት ሃሳብ ገል ቲሊች “በሰው ልጅ ታሪክ፥ ከዚህ በፊት ከተፈጠረ አንድ ክስተት ጋር፥ ያም በብሉይ ኪዳን እና በብዙ ሐገሮች አፈታሪኮች ፣ ተረቶች እና የእሳት ዳር ወጎች ውስጥ ከሚገኘው የ“ታላቁ የጥፋት ውኃ” ታሪክ ጋር ብቻ የሚመሳሰል ደረጃ ላይ መድረሳችንን የሚያሳይ ምልክት ነው። “ነው

ካለን በኋላ "በእኛ ሁኔታ ና በጥፋት ውኃው መካከል ያለው ብቸኛው ልዩነት" ምን እንደሆነ ሲያስቀምጥ "በእነዚህ ታሪኮች እንደምናየው ሰዎች መለኮትን በማስቆጣታቸው እግዚያአብሔር በምድር ላይ ያለውን ሕይወት ሁሉ እንዳጠፋ

እናውቃለን።

የዘፍጥረት መጽሐፍ እንደሚገልጸው፦ "እግዚአብሔርም ሰውን በምድር ላይ በመፍጠሩ ተጸጸተ፥ በልቡም አዘነ። እግዚአብሔርም፥ የፈጠርሁትን ሰው ከምድር ላይ አጠፋለሁ፥ ከሰው እስከ እንስሳ እስከ ተንቀሳቃሽም እስከ ሰማይ ወፍም ድረስ፤ ስለ ፈጠርኋቸው ተጸጽቼአለሁና አለ።" ይላል በቀጣዩ ቁጥር ላይ ግን የሚተርፍ ቅሪት ይኖር ይሆን ለሚለው ጥያቄ ምላሽ ይሰጣል "ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ።" በእርሱ በኩል ተፅፎ እንደምናነበው የሰው ልጅ ብቻ ሳይሆን ሕይወት ካለው ፍጥረት ሁሉ እንስት እና ተባዕት ሕይወት በምድር ላይ እንዲቀጥል እንዲተርፉ መደረጉን እናያለን። እናም ልዩነቱ "ዛሬ ግን በምድር ላይ ለሕይወት መጥፋት ወይም መትረፍ ቁልፉ በሰው ልጅ እጅ ላይ የወደቀ መሆኑ ነዉ" ይለናል። ስለዚህም "እንደመዝሙረኛ ሐሳብ" ይላል ጸሐፊው "እግዚያአብሔር ከመላእክት በጥቂቱ አሳንሶታልና! በሁሉ ላይ እንዲገዛ ስልጣን ያለው የሰው ልጅ፥ ሕይወትን የማዳን ወይም የማጥፋት ኋይል በእጁ ላይ።" ወድቋል።

ጸሐፊው አሁን ምድር ከሰማይ በመጣ ቁጣ እንደማትጠፋ ነገር ግን ምድር በሰው እጅ ልትጥፋ እንደደረሰች አመላክቶናል እናም "ሰው ለዚህ አዲስ ሁኔታ ምን ምላሽ ይሰጣል? ምን ምላሽ እንሰጣለን? ምን ምላሽ መስጠት አለብን?" በማለት ጥያቄ ያቀርብልናል። ከዚህ ወዲያ "ምድር እና እኛ" ያለን ግንኙነት ከዚህ በፊት እንደነበረው፥ የሰው ልጅ መመራመሪያ፣ ጥበባዊ ምናቡን የሚቀሰቅስ፣ ሳይንሳዊ ጥናት የሚካሄድበት፣ ወይም ተፈጥሮን ለመቆጣጠር የሚታገልባት ነገረ ጉዳይ መሆኗ አብቅቷል ይልና "አሁን ምድር ለሰው ልጅ መሠረታዊ ሥጋት እና እንቅልፍ የምትነሳ የጭንቀቱ ምክንያት ነች።" ይለናል። ምናልባት ጸሐፊው የነበረበት ዘመን የቀዝቃዛው ጦርነት ወቅት ስለነበር እና የኒኩሌር መሳሪያ መገኘቱ፥ በእርሱ እድሜ ከተካሄደው የሁለተኛው የዓለም ጦርነትም የከፋ ምድርን ሙሉ ለሙሉ የሚያጠፋ አዲስ ክስተት መኖሩ እጅግ እንዳሳሰበዉ በሚያሳብቅ ሁኔታ "የነገሩን እጅግ አሳሳቢነት ለማድበስበስ የቀቢፀ ተስፋ ሙከራ እናደርጋለን። ነገር ግን የዘመን ተጋሪዎቻችንን በተለይም የወጣቱን ትውልድ አእምሮ በጥልቀት ስንመረምር፣ በአጠቃላይ በማንነታቸው ውስጥ ሰርጎ የገባ ሥጋት እናገኛለን። ይህ

ፍርሃት ከጥቂት አሥርተ ዓመታት በፊት አልነበረም።” በማለት በጊዜው የነበረውን ሁኔታ ካሳየን በኋላ፣ “ለመግለጽ አስቸጋሪ ነው እያለ ጭንቀቱን ያካፍለናል። እሱ የነበረበትን ዘመን” ልክ በየዕለቱ በማያቋርጥ ድምጽ ከዛሬ ነገ ጠፋህ የሚል ማስፈራሪያ በምትሰማበት ሁኔታ ውስጥ እንደመኖር ነው።” በማለት ይገልፀዋል።

ጸሐፊው የነበረበትን ዘመን ከሁሉም ሁኔታ እጅግ የከፋ ያደረገው ደግሞ የሆነ መከራ የሚያመጣ አደጋ መኖሩ ሳይሆን፣ አደጋው “የማይቀረው ዓለም አቀፍ እና የአጠቃላዩ ሕይወት መጥፋት አደጋ ነው። “የሚለውን እንድናሰምርበት ያደርገናል። ምናልባት ጸሐፊው ይህን ሲናገር በጊዜው የነበረው ትልቁ ሥጋት፣ ከዛሬ ነገ በሶቭየት ሕብረትና በአሜሪካ መካከል የኒዩክለር ውጊያ ሊካሄድ ይችላል የሚለውን ሥጋት በአዕምሮ ይዞ ይሆናል። በጊዜው ታዳያ ሰዎች፣ ለእንዲህ ያለው ፍርሃታዊ ስሜት ያላቸው ምላሽ በሁለት ነገር ዙሪያ የጠነጠነ ነበር። እንደ ጸሐፊው ሃሳብ ለዚህ ሁኔታ የመጀመሪያዎቹ ሰዎች ምላሽ ያለውን ሥጋት የሚያስረሳቸው ነገር ማድረግ ነው። ካለው ሥጋት መሸሸጊያ የሚሆናቸው ደግሞ፣ በመግብ እና መጠጥ፣ በመዝናኛ እና ጓደኛ፣ በመስሪያ ቤት፣ በቤተሰብ እና በመሳሰሉት እንቅስቃሴዎች ውስጥ ተግተው በመሥራት ከዛ በሚያገኙት የስኬት ዋስትና ውስጥ ይደበቃሉ። ይህም ስለአጠቃላዩ በምድር እየሆነ ስላለው ነገር እንደይሰሙ ወይም እንዳይጨነቁ ከለላ ይሆናቸዋል። ሁለተኛዎቹ ደግሞ፣ የሰው ልጅ በጥበብና በእውቀቱ በመታገዝ ምድርና ከምድር ውጪ ያሉትን አካላት መቆጣጠር መቻሉን መሠረት አድርገው በምድር ላይ ሊመጣ ያለውን ጥፋት ለመቆጣጠር ሰው የሚሳነው ነገር እንደሌለ ስለሚያምኑ፣ እጅግ የተጋነነ በሰው ልጅ ስልጣኔ ላይ ያላቸው መተማመን እየታየና እየተሰማ ያለው ሥጋት ከሰው ቁጥጥር ውጭ እንደማይሆን እርግጠኛነት ውስጣቸው ስለጨመረ፣ በዚህ ምልከታቸው ከሥጋት እና ጭንቀት ያመልጣሉ ይላል።

ጸሐፊው “አብዛኞቻችን እንዲህ እርስ በርሱ የሚጣረስ ምላሽ በራሳችን ውስጥ ተፈጥሮ አይተናል። ቀድሞ በምድር ሁሉን ሰጪነት፣ ሕይወትን የመጠበቅ እና የማቆየት ኋይል የነበረን ነፍስ ያላወቀ ልጅ በእናቱ ደረት ላይ ያለውን አይነት መተማመን አሁን ጠፍቷል። ከእንግዲህ ምድር አትሸከመን ይሆናል። እኛው ራሳችን ምድር እኛን የመሸከም ሥራዋን እንዳትወጣ እንከለከላት ይሆናል። ሁለተኛ የጥፋት ውኃ እንደማይመጣ ለቃልኪዳን ይሆን ዘንድ ለኖህ እንደ ተሰጠችው ቀስተ ደመና ዓይነት ለእኛ ምንም አይነት ሰማያዊ የቃል ኪዳን ምልክት አልተሰጠንም። በሰው ሰራሽ ችግር ምክንያት ለሚከሰት የጥፋት ውሃ ጎርፍ አሁን እንደቀድሞ በውሃ

ሳይሆን፥ በእሳት እና በአየር ለሚሆነው የሰው ሰራሽ “የጥፋት ውሀ” ጎርፍ ምንም ዋስትና የለንም” የሚል ሐሳብ አለው።

ፖል ትሊክ “እንደዚህ አይነት ሐሳቦች፣ አሁን ስላለንበት ስለዚህ ሁኔታ ክርስትና ምን ይላል፥ ስለምንገኝበት አጣብቂኝ ምን ምላሽ አለው የሚል ጥያቄ እንዲነሳ በር ይከፍታሉ።”ይልና ጥያቄው እንደማይቆም፥ ይልቁንም “በዚህች ፕላኔት ላይ ስላለው ሕይወት፣ ስለ መጀመሪያው እና ስለ መጨረሻው እንዲሁም ሰው በምድር ላይ ስላለው ስፍራ ምን ይላል? ከአጽናፈ ዓለሙ ግዙፍነት አንጻር የምድርን አስፈላጊነት፣ እና የሰው ልጅ የታሪክ ትእይንት በተመለከተ ምን ይላል? ከአዕምሮ በላይ ለሆነ “የማይታሰብ የጊዜ ርዝመት” ካለው አጽናፈ ዓለም ጋር ሲነፃፀር ለዚች ለእኛዋ ፕላኔት፣ ለምድር እና በእርሷ ላይ ላለው ሕይወት ‘ስለተሰጠው “አጭር የቆይታ ጊዜ” ምን ይላል? ብለን ለመጠየቅ እንገደዳለን ይለናል።

ነገር ግን ይላል ጸሐፊው “ብዙ ጊዜ ይህን መሰል ጥያቄዎች በእኛ በክርስቲያኖች ስብከት እና ትምህርት ውስጥ እምብዛም አይነሱም።” ይልና “የክርስትና ማዕከላዊ የትምህርት ጭብጦች የሚያጠነጥኑት በሥነ ፍጥረት፣ ውድቀት፣ ድነት እና ነገረ ፍጻሜ ላይ”ቢሆንም “ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ዋነኛ ያልሆኑ ጉዳዮች ድንገት ብድግ ብለው በዋና ዋና የእሳቤ ሥርዓት መካከል ጣልቃ በመግባት፥ ማዕከላዊ ቦታን የሚቆጣጠሩበት ጊዜ አለ። ይህ የሆነበት ንድፈ ሐሳባዊ ምክንያት ኖሮ ሳይሆን እነዚህን መሰል ጥያቄዎች የብዙ ሰዎች የሕይወት እና የሞት ጉዳይ ስለሚሆኑ ነው። “በእኛና በምድር መካከል ስላለው ግንኙነት ማሰብን እንደሚገባን ያሳስባል። “እንዲህ አይነት እንቅስቃሴዎች” ይላል ፀሃፊው፥ በኛ እና በምድር መካከል ስላለው ግንኙነት የሌላ ነገር ትኩረት ተሻምቶ ማቅረቡ ጥያቄ ሊፈጥርብን አይገባም የሚለውን ለማስመር “በሰው ልጆች ታሪክም ውስጥ ይሁን በክርስትና ታሪክ ውስጥ ብዙ ጊዜ ተከስተዋል።” ይለናል። እናም ይላል ጸሐፊው “እንዲህ አይነት ነገር በሆነበት፣ በተከሰተበት በየትኛውም ጊዜ በሁሉም ደረጃዎች የነበረን የክርስትናን የአረዳድ ባህል እንደቀየረው ሁሉ የሰው ልጅ ራሱን የሚያይበትን እይታም በሁሉም መንገድ ቀይሯል።”

ጸሃፊው እሱ በነበረበት ዘመን የነበረው አደጋ እንዳለ ሆኖ፥ ተስፋ ሰጪ ነገርም እንደነበረ ሲያመለክተን “የሰው ልጅ ከምድር እና ከአጽናፈ ዓለሙ ጋር ያለው ዝምድና ለሚመጡት ረጅም ዘመናት ሐላፊነት በሚሰማቸው እና አስተዋይ በሆኑ ሰዎች ዘንድ ዋነኛ የትኩረት ነጥብ የሚሆንበት ጥሩ አጋጣሚ ባለው ጊዜ ላይ

እንገኛለን።" በማለት ይናገራል።

ተስፋውን ሲያስቀምጥ ደግሞ "ይሄ በእውነት የሚሆን ከሆነ፣ በርግጠኝነት ከዚህ ወዲህ ክርስትና በሰውና በመሬት መካከል ስላለው ግንኙነት አስተማማኝ የሚመስል ግን ያልሆነ፣ መደላድል ወደሰጡት ጥያቆዎች እና መልሶች ሄዶ መሸሸግ የሚችል አይሆንም።" ይልቁንም "ልክ ቀድሞ እኛ ያነሳናቸውን አይነት ጥያቄዎች፣ አዳዲስ እና መልስ ያልተሰጣቸውን ጥያቄዎች ወደ ማሰሰ አዲስ ነገር ከመሞከር ወደማይመለሰው እጅግ ወደመጠቀ የሰው ልጅ መንፈስ ፍለጋ ውስጥ ተገፍቶ ለመግባት ይገደዳል። ነገር ግን እነዚህ ጥያቄዎች በተመሳሳይ ሁኔታ ይላል ጸሐፊው "ወደዘለዓለማዊው አቅጣጫ፣ ወደምንጩ፣ ወደ ሰው ልጅ እና እርሱ የሚኖርባት ዓለም ግብ የሚጠቁሙ ናቸው።" ይላል።

"በርግጥ አሁን ያለንበት አጣብቂኝ ሁኔታ የተፈጠረው በዋናነት በዚህ ክፍለ ዘመን በተገኘው ሳይንሳዊ እና ቴክኒካል ዕድገት ምክንያት ነው። ቢሆንም በዚህ ሳይንሳዊ እድገት ላይ ቅሬታ ማቅረብ ሞኝነት፣ እንዲሁም ከንቱ ልፋትም ነው። እነዚህ ሳይንሳዊ እድገቶች የሰው ልጅ በተፈጥሮ ካገኘው ሕይወት እጅግ የላቀ እና የረቀቀ አዲስ ዓለም ነው። ቀድሞ በተፈጥሮ ያለውን ብቻ እየተጠቀመ ከሚኖርበት ሕይወት ያሻሻለው ዓለም ነው። እነሆ ሳይንስ በመካከላችን ሆነ እናም ኑሮአችንን፣ ሐሳባችንን እና ስሜታችንን በሁሉም አቅጣጫ ለወጠው፣ በምናውቀው መንገድ፤ እንደውም በውል እንኳን ባልተገነዘብነው መንገድም ጭምር ቀየረው።" ብሎ ምክንያቱን ያቀርብና በሳይንስ እድገት ምክንያት በዘመኑ የተከሰተውን ሲያስረዳ "በዚህ ዘመን ያሉ ተማሪዎች ከእነርሱ በፊት የነበሩ ትውልዶች እንደነበሩት አይነት አይደሉም። በዚህ ዘመን ያሉን ተስፋዎች እና ጭንቀቶች በመካከላችን ላሉ በዕድሜ ለገፉ ሰዎች እንኳን እንግዳ ናቸው። ሁለት ትውልዶችን በመቶ አመት ክፍተት ብናወዳድራቸው እኛን ከእነርሱ የሚለየን እርቀት እጅግ ትልቅ ነው።" በማለት ያስቀምጣል።

"አሁን የምናየው ፈጣን የሆነ እድገት እና ለውጥ የመጣው በዋናነት በሳይንስ እና ሳይንስ ባስገኛቸው የፈጠራ ሥራዎች የመጣ ነው።" ካለን በኋላ ስለዚህ "ሳይንስ ይህን አይነት ተዓምር ካሳየን ዘንድ ስለ ሰው ልጅ፣ ስለሚኖርበት ምድር፣ እና ስለአጽናፈ ዓለሙ ሁሉ እውነተኛ እና የመጨረሻው መልስ የሚኖረው ሳይንስ አይደለምን? በማለት ፈታኝ ጥያቄ ከፊታችን ያስቀምጣል። ጥያቄውን ይቀጥላል "ከዚህ ወዲህ" የሳይንስ ተዓምር እያለ ማለቱ ነው "ሐይማኖት ምን የሚጨምረው ነገር አለ? እንደውም እንደእውነታው ሐይማኖት በእነዚህ ጉዳዮች

ላይ የራሱን ምላሽ ለመስጠት በሚሞክርበት ጊዜ በሳይንሳዊ ጉዳይ ጣልቃ እየገባ እንቅፋት አልሆነምን በዚህም ምክንያት ሰሚ አላጣምን?" መልስ እንድናዘጋጅ ይጋብዘናል። እንዲህ አይነቱ አካሄድ ትላንት የነበረ ነው፣ እና አሁንም እየተከሰተ ያለ ነገር ነው። አዎ ገብቷል ! የሃይማኖት በሳይንስ ጎዳይ ጣልቃ እየገባ እንቅፋት መሆኑ ትላንትም ሲከሰት ነበር፤ ዛሬም በእኛ ዘመን ይከሰታል የሚለውን ከመለሰ በኋላ ነገር ግን ይላል "ነገር ግን ነገሩን ከስር መሠረቱ ብንመለከት በሳይንሳዊ ሥራ ውስጥ ዘው ብሎ የማይመለከተውን ጉዳይ የሚፈተፍተው ሃይማኖት በራሱ ሳይሆን አንድ ነገር ከምር ወስደው ማሰብ ሞት መስሎ በሚታያቸው፣ እና ዜይቤያዊ የሃይማኖት ቋንቋን ረቂቅ ከሆነው ምሑራዊ የምርምር ጽንሰ ሐሳብ ለመለየት ፍቃደኛ ያልሆኑ ጭንቀታም እና ወገኛ የሃይማኖት ሰዎች ናቸው።" በማለት ሃይማኖት በራሱ እንደ ነገረ ጉዳይ የሳይንስ እንቅፋት እንዳልሆነ ያስቀምጥል

በዚህ እንቅፋትነት "ከተራው ምዕመን አንስቶ እስከ የነገረ መለኮት ሊቃውንት ድረስ ያሉ" ተሳታፊ እንደሆኑ ይወቅሳል። ያኔ በእርሱ ዘመን እንኳን "በብዙ ክርስትና ባለባቸው ዓለም ክፍሎች እንዲህ ዓይነቱን የተዛባ አመለካከት እና ሃይማኖትን አላግባብ መጠቀም ተወግዷል።" በማለት ደስታውን ይገልፃል። ቢሆንም "እዚህ ላይ አንድ ሰው ሐይማኖትን መሠረት አድርጎ ስለ ሰው ልጅ እና ስለሚኖርበት ምድር መናገር እና ማስተማር ይችላል።" ካለ በኋላ ነገር ግን "ይሄን ታዲያ ሲያደርግ በሳይንስ ላይ ለመጨመር ወይም ለመቀነስ፣ ታሪካዊ ዕውቀት ላይ የሆነ ነገር ለመጨመር ወይም የቱንም ያህል ከለመድነው መንገድ የወጣ ቢሆን ሳይንሳዊ መላምት ላይ ክልከላ ለማድረግ ከማሰብ አይደለም፤ መሆንም የለበትም።

'ስለዚህ ጥንቃቄ ያስፈልጋል' በማለት ምክሩን ይለግሳል።

ፓል ቲሊች "እንግዲህ ይህ ከሆነ፥ ክርስትና በዚህ ምድር ላይ የሰው ልጅ ስላለበት አጣብቂኝ ሁኔታ ምን ይላል? ራሱ መልስ ሲሰጥ "ይህን ተመሳሳይ ጥያቄ፥ ክርስትና ከመጀመሩ ከብዙ መቶ አመታት በፊት የተፃፈው መዝሙረ ዳዊት፥ በምዕራፍ ስምንት ላይ በማያሻማ መንገድ እና ውበት በተላበሰ መንገድ ጠይቋል።" ይለናል። ጥያቄው ወደ ሁለት ነገር የሚያመለክት ጥያቄ መሆኑን በመጥቀስ። ዳዊት በመዝሙር ውስጥ "በአንድ በኩል በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ከዋክብት እና ሌሎች ፍጥረታት ጋር ሲወዳደር የሰው ልጅ ምን ያህል የውሃ ጠብታ ያህል እንደሆነ ያመለክታል። እና ደግሞ በሌላ በኩል የሰው ልጅ ያለውን እጅን በአፍ ላይ የሚያስጭን ታላቅነት፣ የሰውን ልጅ ክብር እና ግርማ፣ በፍጥረት ሁሉ ላይ

ገዢ መሆኑን እና ከራሱ ከእግዚያአብሔር ጋር አምሳያነት እንዳለው ያሚያመለክት ጥያቄ" አቅርቧል በማለት የመዝሙረኛው ሐሳብ ምን እንደያዘ ያሳየናል። ጨምሮም "እንደዚህ አይነት ሐሳቦች በተደጋጋሚ በመጽሐፍ ቅዱስ ተጠቅሶ አናገኝም። ድንገት ስናገኛቸው ግን ልክ ዛሬ የተፃፋ አይነት ስሜት ይሰጡናል።" ይለናል።

በዘመናዊ ሳይንስ አማካኝነት አጽናፈ ዓለሙ መታወቅ እና መጠናት ከጀመረበት ጊዜ እና እጅግ ግዙፍ መስላ ትታየን የነበረችው ምድር በከዋክብት እና ጨረቃ እና የሰማይ አካላት የተከበበቻ ትንሽ ነገር መሆኗ ከተደረሰበት ጀምሮ፤ የሰው ልጅ አጽናፈ ዓለሙ ምን ያህል ግዙፍ እንደሆነ እና ምድር ደግሞ እንዴት ትንሽ እንደሆነች ሲያስብ ግራ መጋባት ተሰምቶታል። በወይን ጠጅ እንደሰከረ እንደመንገዳገድም ብሏል። በማለት ሳይንስ ዳዴ ሲል የሰው ልጅ ምላሽ ምን እንደነበረ ያስቃኝናል። እናም ይለናል ፀሀፊው "ከአጽናፈ ዓለሙ ማዕከላዊ ቦታ ምንም ጥቅም ወደሌለው አንድ ጥግ የተወረወረ አይነት ስሜት ሆኖበታል። ከጭንቀቱም ብዛት እነዚህን ጥያቄዎች ለመጠየቅ ተገዷል።" ይልና፥ የሰው ልጅ የሁሉ ማዕከል እና ከዚህ ምድር ውጪ ሌላ ፕላኔት እንደነበረ በማያውቅበት ዘመን፥ የሕይወት መነሻ ና መዳረሻ ይህች ምድር ብቻ ትመስለው ነበር። ከዚህም የተነሳ ከምድር ውጪ ሌሎች ፕላኔቶች እንዳሉ ሲያውቅ ምድር አላት ብለው ይሉ የነበረው ዓለማስ ምን ይሆናል የሚል ግራ መጋባት ውስጥ እንደገባ በዝርዝር ያነሳል።

"ሰዎች ከዚህ በፊት እንደነበራቸው የሚያምኑበት ታላቅ ዓላማስ? የሰው ልጅ በተፈጥሮው የእግዚአብሔር አምሳል ያረፈበት ነው የሚለውሰ? ክርስትና የሰው ልጅ ሁሉ መዳን የሚፈፀምበት መንገድ ነው የሚለው የእርሱ ታሪክስ? በአዲስ ኪዳን የአጽናፈ ዓለሙ ጌታ ተብሎ የተጠራው ክርስቶስ አሁን ሳይንስ ከደረሰበተ ግኝት ጋር እንዴት ነው የምናዛምደው? በመጽሐፍ ቅዱስ ቋንቋ በአደገኛ ነውጥ ፀሀይ፣ ጨረቃ እና ከዋክብት ይወድቃሉ ተብሎ ስለተገለፀው የታሪክ ፍጻሜ ምን ማለት ይቻላል? አሁን ከተደረሰበት ተጨባጭ ሁኔታ አንፃር ስለ ምድር አስፈላጊነት እና ስለ ሰው ክብር ባለበት ፀንቶ የሚቀረው የቱ ነው? ከዚህም በላይ ድሮ እኛ ብቻ እና ለእኛ ብቻ የሚመስሉን ነገሮች በሌሎች ፕላኔቶች የመኖር እድል ስላላቸው ማለትም በእነዚህም አካላት የእግዚያአብሔር አምሳል ሊገለጥ፣ በእግዚያአብሔር ሐሳብ ውስጥ ስፍራ ሊኖራቸው፣ የክብር እና የግርማ ዘውድ ያጎናፅፋቸው ከሆኑ ክርስትና ስለሰው ልጅ ታሪክ ያለው እና የሰው ልጅ ታሪክ ዋና

ማዕከል የክርስቶስ መገለጥ ነው የሚለው እይታ ትርጉም ምንድን ነው?” በማለት የጥያቄ መዓት ማዥጎድጎዱን ፖል ቲሊች በፅሑፉ ያሳየናል፡፡

ትላንትና የተነሱ እነዚህ ጥያቄዎች “በንድፈ ሃሳብ ብቻ የተቀመጡ ጥያቄዎች አይደሉም፡፡ ከምናባችን በላይ እጅግ ግዙፍ ከሆኑ ከዋክብቶች ውስጥ በዚህች በአንዷ ኮከብ ላይ እንደመስፈሩ ሰው ራሱን እንደሰው ልጅ እንዲረዳ የሚያግዙት ወሳኝ ጥያቄዎች ናቸው፡፡ እናም በክርስቲያናዊ አመለካከት ውስጥ እንደሆኑ ለሚሰማቸው ሰዎች ብቻ ሳይሆን የክርስትና መልዕክት የማይቀበሉት ነገር ግን ከክርስትና ጋር በታሪክ ትርጉም እና በሰው ሕይወት የመጨረሻ ፋይዳ ላይ ያለውን እምነት የሚጋሩትን ጭምር አዕምሮ የሚያናውጡ ጥያቄዎች ናቸው፡፡” በማለት ጥያቄዎቹ ከድንጋጤ የተጠየቁ ቢሆንም ጥልቀት ያላቸው መሆናቸውን ይነግረናል፡፡

በድጋሚ፣ ምንም እንኳን ከረጅም ዘመን በፊት የተፃፈ ቢሆንም፣ መዝሙር ስምንት “ከእግዚአብሔር ትንሽ አሳነስኸው በእጆችህም ሥራ ላይ ሥልጣን ሰጠኸው፡፡” እያለ ሲናገር በቅርቡ የተፃፈ ነው የሚመስለው፡፡ ይህንንም ሲናገር በእንስሳት እና በሌሎችም ፍጥረታት ላይ ያለውን የገዢነት ስልጣን ምሳሌ አድርጎ ነው፡፡ “ነገር ግን” ይለናል ፖል ቲሊች “ዘመናዊው ቴክኖሎጂ ተፈጥሮን በሁሉም ዘርፎች መቆጣጠር እንዲችል ባደረገው ጊዜ ግን ‘ከእግዚአብሔር ትንሽ ያነሰ’ የሚለው ሐረግ ሙሉ ትርጉሙ ምን ማለት እንደሆነ በትክልል መረዳት ችለናል፡፡ የሰው ልጅ በፈጠራቸው ፈጣን የሆኑ ዘመናዊ የትራንስፖርት እና የመገናኛ መረቦች እና ሌሎች ግኝቶች፣ ጊዜን እና ጠፈርን መቆጣጠር መቻሉ፣ ‘ለውስንነቱ ባሪያ አድርጎት የነበረውን ገመድ መበጠስ እንዲችል አድርጎታል፡፡’ በቦታ እና በጊዜ የተወሰነ ተፈጥሮውን ማሸነፍ አስሮት የነበረውን የውስንነትን ገመድ ከእጆቹ እና እግሮቹ ላይ ማውለቅ ችሏል፡፡

ከሰዓታት ባነሰ ጊዜ ከአንድ ቦታ ወደሌላ ቦታ መሄድ፤ የፈለገውን ማምረት ችሏል፡፡ ፖል ቲሊች ”አንድ ወቅት ለመለኮታዊ አካላት በመተት ኋይል ወይም በድንቅ እና ተዓምር ካልሆነ በቀር የሚሆን እንዳይደሉ ይታሰቡ የነበሩ ነገሮች ከሰው ልጅ የቴክኒክ ኋይል እና እድገት የተነሳ በቀን ተቀን ሕይወት ውስጥ የሚገኙ ተራ ጉዳዮች ሆነዋል፡፡” ይለናል፡፡ በአንድ ወቅት አማልክት ካልሆኑ በቀር በሰማይ በሮ፣ በምድር ነድቶ ወይም በባሕር ሐገር የሚያህል ነገር ተሸክሞ የሰው ልጅ በቀናት እና በሰዓታት ውስጥ ከምድር ጫፍ ወደ ምድር ጫፍ መጓዝ መቻሉ የማይታሰብ ነበር ማለቱ ነው፡፡ ጸሐፊው “አሁን የሰው ልጅ በሳይንስ አማካኝነት ከደረሰበት

ደረጃ ተነስተን" ይላል "ከዘማሪው ጋር፥ የሰው ልጅ ከእግዚአብሔር በጥቂቱ ያነሰ ፍጡር እንደሆነ ቢሰማን፥ እንደውም እንዳንዶቻችን ከእግዚአብሔር ጋር እኩል እንደሆንን ማሰብ ብንጀምር፥ ከዚህም አልፎ ሌሎች ደግሞ በአደባባይ፥ የሰው ልጅ በጥቅሉ በአዕምሮው ሥራው እግዚአብሔርን ሙሉ በሙሉ ተክቷል ብለው ቢናገሩ" ልንገረም አይገባም ይለናል።

ጸሐፊው "አሁን እዚህ ጋ ከአንድ አስገራሚ እውነት ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን፦ "ይለንና ይህም፥ ሳይንስ ተፈጥሮን መቆጣጠሩ፣ የአጽናፈ ዓለሙን እና የፕላኔቶችን ሚስጥር መግለጡ፥ የሰውን ልጅ "በዓለም ላይ ከነበረው ማዕከላዊ ስፍራ ገፍቶ ወደ ዳር የጣለው እና ወደ ኢምንትነት ዝቅ ያደረገው ክስተት መልሶ ደግሞ በምድር እና ከምድር ክበብ ውጪ ባለ ሰፍራ የአማልክትን ቦታ ወደሚስተካከል ከፍታ አውጥቶታል።" ብሎ ይነግረናል።

ጸሐፊው ትንተናውን ይቀጥልና "ለዚህ ተቃርኖ መልስ ይኖር ይሆን? መዝሙረኛው የሚለውን በጥሞና እናድምጥ። መዝሙረኛው ሰው በሁሉ ላይ ገዢ ነው፤ ከእግዚአብሔርም በትንሽ ያነሰ ነው የሚል ነገር አይናገርም። መዝሙረኛው ሲናገር "በእጆችህ ሥራ ላይ ሥልጣን ሰጠኸው፥ ከእግዚአብሔርም ትንሽ አሳነስከው" ይላል፥ ይህ ማለት የሰው ልጅ ትንሽነትም ሆነ ታላቅነት ከራሱ የመነጨ አይደለም ማለት ነው። ነገር ግን ከዚህ ንፅፅር ውጪ የሆነ አንዳች ነገር አለ ማለት ነው። "ጸሐፊው፥ ከላይ ባሰፈረው ሐሳብ ብዞዎች እንደሚተረጉሙት መዝሙረኛው፥ ሰው የሁሉ ገዢ እና ከመላዕክት/አማልዕክት በጥቂት ያነሰ ነው ሳይሆን የሚለው፥ በሁሉ ላይ ገዢ እንዲሆን እና ከመላእክት በጥቂቱ ያነሰ ያደረገው እግዚአብሔር ነው የሚለውን አፅንኦት ይሰጣል። ይቀጥልና "ሰውም ከሌሎች ፍጥረታት ሁሉ ጋር፥ ሁሉን ነገር ከእግሩ በታች ካስገዛለት ከእርሱ ዘንድ ወጥቶ መጥቷል፥ ህልውናውን አግኝቷል። የሰው ልጅ መሠረት ለአጽናፈ ዓለሙ ሁሉ ከዋክብቱን ጨምሮ ምንጫቸው ከሆነው ከአንድ ምንጭ፣ ከእግዚአብሔር ዘንድ ነው። ፍጥረታት በራሳቸው ሳይሆን ህልውናቸውን ካገኙበት ከእርሱ ታላቅነትን ተቀብለዋል። የቱንም ያህል ጥቃቅን ቢሆን፥ ለሆነው ነገር፥ አተሞች፣ እፅዋት እና እንስሳትም ሁሉ፤ ጥቃቅንነትን የሰጣቸው ምንጫቸው የሆነው እርሱ ነው፤ የቱንም ታላቅ ቢሆኑ፥ ሰውን እና ከዋክብቱን ጨምሮ፣ ታላቅ ያደረጋቸው የፈጠራቸው ነው። በራሱ ትንሽነትንም ሆነ ታላቅነትን የያዘ የለም።

ምንም ጥቅም ለማይሰጥ ኢምንት ለሆነው ነገር፥ ወሳኝ መሆንን፣ አስፈላጊነትን ይሰጠዋል። ለእያንዳንዱ ሰው እና ለሰው ልጅ በአጠቃላይ የሕይወትን

አስኳል፥ የም አስፈላጊነትን ይሰጣል። ይህ መልስ ትንሽ ነኝ በሚል ስሜት ያለንን ጭንቀት ጸጥ ያደርጋል፣ በሌላ መልኩ ደግሞ ታላቅ ነኝ የሚል ኩራታችንን ያጠፋል። ይህ መልስ መጽሐፍ ቅዱሳዊ ብቻ አይደለም። ይህ መልስ ክርስቲያናዊ ብቻ አይደለም። ይህ መልስ ሃይማኖታዊ ብቻ አይደለም። እንደው ሰው ያለንበትን መውጫ የሌለው ችግር ማለትም የራሳችን ፈጣሪ እኛ እንዳልሆንን እና በዚህ ምድር የኖርነው በእኛ ምርጫ እንዳልሆነ እየተገነዘብን ስንመጣ ይህ እውነት ሁላችንንም የሚመለከት ስለሁላችንም የሚያወራ እንደሆነ ይታወቀን ይጀምራል።

እኛ ካለመኖር ወደ መኖር የመጣነው እና ያበጀን አጽናፈ ዓለሙን፣ ምድርን እና በላዩ ላይ ያለውን ሁሉ ደግፎ በያዘ ኋያል ነው፤ ነገር ግን ፍጥረትን ደግፎ ከያዘው ኋይል ጋር ስንተያይ ኢምንት ነን" ካለ በኋላ "ቢሆንም ይህን ኋይል ማወቃችን ብቻ ከፍጥረታት መካከል ታላቅ ያደርገናል።" በማለት ንቃተ ኀሊና ሰውን ከፍጥረታት ሁሉ የተለየ አድርጎታል የሚለውን እርሱም እንደሚስማማ ያስቀምጣል። አሁንም ከቲሊች ጋር የጀመርነውን ጉዞ እንቀጥልና ከታች በስፋት ስለምድር እና እኛ ያለውን ሐሳብ እንስማ።

## 2.

አሁን ደግሞ በጥፋት ውኃው ታሪክ ውስጥ "ሰውን በመፍጠሬ ተፀፀትኩ" የሚለውን አምላካዊ ቃል መለስ ብለን እንመልከት። ይህ አምላካዊ ቃል፥ በአስተሳሰባችን ውስጥ ከምድር እና ከሰው ልጅ ጋር በተገናኘ፥ ፍርድ፣ ተስፋ አለማድረግ እና ሰቆቃ የመሳሰሉትን ቃላት ያስተዋውቀናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፣ ወይም በሌላ የጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ከዚህ ሐሳብ የበለጠ ተደጋግሞ የተነሳ ጭብጥ የለም። ምድር በተደጋጋሚ ጊዜ፥ የሰው ልጅን ጨምሮ ሁሉንም ሕይወት ያላቸውን ፍጥረታት እና ሰቆቃውንም ጨምሮ፥ በታሪክ ውስጥ የተከሰተው ሀዘንና መጥፎ ነገር ሁሉ ከእርሷ በመገኘቱ ምክንያት፥ ስፍር ቁጥር ለሌላቸው ጊዜያት በሰው ልጅ ተረግማለች። ምድርን መክሰስ ባህል እየሆነ እንደሄደ በምናየው እና በምንሰማው ነገር ውስጥ ሁሉ መመልከት እንችላለን። በርግጥ ለምን እንዲህ እንደሆነ ለመረዳት አይከብድም። በሁሉም የጥበብ ማንፀባረቂያዎቻችን፣ በልብ ወለድና በድራማ ሥራዎቻችን፣ በሥዕልና በሙዚቃ፣ በፍልስፍናዊ አስተሳሰብና ስለ ሰው ተፈጥሮ በሚገልጡ ነገሮች ሁሉ እንከሳታለን።

ነገር ግን በዋነኛነት ሊሰመርበት የሚገባው፥ በተበታተነ ወይም በታመመ አዕምሮ ውስጥ በመሸሸግ፣ በአደንዛዥ ዕፆች እና ሌሎች አስካሪ በሆኑ ዘዴዎች አማካኝነት ሕይወት ማለፍ ከሌለባት በላይ ወይም ሕይወት መሆን ከሌለባት በታች በኀይል በማስገደድ፣ ወይም አሰልቺነት እና እንደ ፋብሪካ ዕቃ አንድ አይነት የመሆን ዕፅ በሆነው የመንጋ ኑሮ ውስጥ በመግባት፥ ሕይወትን በተገቢው መንገድ መሄድ አለባት የሚለውን የተቀበሉትን በማጣጣል፥ በማናናቅ በዝምታችን ውስጥ የምናደርገው ክስ ነው። በእነዚህ ሁሉ መንገዶች በዚህ አጽናፈ ዓለም እና ፕላኔት ላይ ያስቀመጠንን፥ መዝሙረኛው "የክብርና የምሥጋና ዘውድ ጫንህለት" የሚለውን እጣፈንታ እናማርራለን። ነገር ግን ብዘዎቻችን ያንን ክብር ልናስወግደው እንናፍቃለን እና ያ የክብር እና የምሥጋና ዘውድ ባልኖረን ብለን እንመኛለን። በደመነፍሳዊ ፍላጎት እርካታ ተወሥነው፣ ስለራሳቸውም ሆነ ስለሚኖሩበት ዓለም ሳያውቁ እንዳሉት እንስሳት፤ እኛም ምነው እንደ እንስሳት በሆንን ብለን እንናፍቃለን።

በጥፋት ውሃ ታሪክ ውስጥ ሰውን በመፍጠሩ የተፀፀተው እና ከምድር ፊት ሊያስወግደው የወሰነው እግዚአብሔር ነው። አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ግን ራሱን ከምድረ ገጽ ለማጥፋት ኀይል ያለው ሰው ነው እና ሁል ጊዜ ደግሞ ከነአካቴው

ከሰውነቱ የመነጠል ምኞት ተሞልቶ፥ ሰው ሆኖ በመፈጠሩ የሚፀፀተው ራሱ ሰው ነው። በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ አብረን ከምናሳልፋቸው ሰዎች ከምንገነዘበው በላይ በቁጥር ብዛት ያላቸው ግለሰቦች አእምሮ ውስጥ ይህን መሰል ፍላጎት እየተመላለሰ ነው፥ እና ምናልባት በተወሰነ ደረጃ፥ ስናውቀው፥ እኔም የሚሰማኝ እንደ እናንተ ነው በሚል ምላሽ ውስጣችን ከውስጣቸው ሳይናበብ አይቀርም። በሰው ልጅ ሙሉ ቁጥጥሩ ውስጥ የዋለችው ምድር፥ አንድ ቀን የሰው ልጅ መኖር የሚፈልግበት ቦታ መሆኗ የሚያበቃበት ሁኔታ ሊፈጠር ይችል ይሆን? የሰው ልጅ አጥብቆ በኀዋ ምርምር ሳይንስ ፍቅር የመውደቁ ምክንያት ምድርን ለአንዴ እና ለመጨረሻ ጊዜ ጥሎ ለመጥፋት ድብቅ በሆነው የአዕምሮው ክፍል ውስጥ ያለው ፍላጎት መገለጫ ይሆን? ምንም እንኳን ለእነዚህ ጥያቄዎች ትክክለኛ መልስ ባይኖርም በሰው እና በምድር መካከል ያለውን ግንኙነት በተመለከተ የሰው ልጅ ያለውን የተሳሳተ በምድር የመተማመን ስሜት እንደገና እንዲያጤን የሚያስገድዱ በመሆናቸው መጠየቅ አለባቸው። በጥንቱ ዘመን ይነገር የነበረው “የሰው ልጅ በዚህ ምድር ላይ መፃተኛ ነው” የሚለው የጥበብ ቃል በእነዚህ ጥያቄዎች ውስጥ መንፀባረቁን ማየት እንችላለን እና ዛሬም ሥጋ ለለበሰ ሁሉ ተፈፃሚ የሚሆን ነው።

የሰው ልጅ ራሱ በምድር ላይ እንግዳ፣ መናኝ ነው። እናም ይህ የእንግድነት፣ የመናኝነት ጉዞ የሚያበቃበት ጊዜ ይኖራል፣ በውል በማናውቀው ሩቅ የወደፊት ጊዜ ውስጥ፣ ወይም ምናልባትም በቅርብ ጊዜ ያበቃል። ክርስትና የሰው ልጅ ታሪክ ቆይታ ምን ያህል ጊዜ እንደሆነ ምልክት አይሰጥም። የጥንቷ ቤተ ክርስቲያን በነበረችበት ክፍል ዘመን ውስጥ የፍጻሜ ዘመን እንደሚሆን ስትጠብቅ ነበር። በዚያን ወቅት የነበሩ አማኞች በተስፋ አሁን የዘመን ፍጻሜ ይሆናል ብለው ሳይሆን ሲቀር እጅግ አዝነው ነበር። ምድር ግን ቀጠለች። በአሁኑ ዘመናዊ ዓለም የመጨረሻው ዘመን የሚሆንበት ዓመት ማለቂያ ለሌለው ጊዜ እረዝሟል። ዛሬ ደግሞ ሳይንቲስቶች የሰው ልጅ ታሪክ ገና ወደፊት ለሚሊዮኖች አመታት ሊቀጥል እንደሚችል ይናገራሉ። በሚሊዮኖች የሚቆጠሩ ዓመታት ወይም በሺዎች የሚቆጠሩ ዓመታት ወይም ነገ፥ አናውቅም! ምድር በየቱም ጊዜ ትጀምር እና በየቱም ጊዜ ፍጻሜዋ ያብቃ የእኛ ዋና ጥያቄ የዚህ ታሪክ ትርጉም ምንድን ነው? የሚለው ነው። አሁን እኛን እኔ እና አንተን እንዴት እንደሚነካን እየጠየቅን አይደለም፣ ነገር ግን አጽናፈ ዓለሙን እና የአጽናፈ ዓለሙን የመጨረሻ አላማ እንዴት እንደሚነካ ነው። አሁን፣ እኛ እኔ እና አንተን እንዴት እንደሚነካን እየጠየቅን አይደለም፣ ነገር ግን  አጽናፈ ዓለሙን እና የ አጽናፈ ዓለሙን የመጨረሻ አላማ

እንዴት እንደሚነካ ነው።

በብሉይ ታሪክ ውስጥ እግዚአብሔር ሰውን በመፍጠሩ ሲፀፀት እናነባለን። ይሄ ማለት እግዚአብሔር ሰውን በፈጠረ ጊዜ ነገሮች ካሰበው ዓላማ ውጪ ሊሄዱ እንደሚችሉ እያወቀ ነው ማለት ነው። አንድ ነገር ለመሥራት ስንነሳ፥ የስራው ያለመሳካት ዕድልም አብሮ የሚታሰብ እንደሆነ እናውቃለን። የሰውን ልጅ መፍጠር ስኬታማ አለመሆኑን በመገንዘቡ፤ የተበላሸውን የሚያስተካከልበት አዲስ መንገድ መጀመሩን እናያለን። ይሁን እንጂ አሁንም የተጀመረው አዲስ የማስተካከል ሥራ፥ ውድቀት እንደማይገጥመው፥ በምንም ዓይነት መንገድ መተማመኛ የሚሰጠን አናገኝም።

ከጥፋት ውሃ ታሪክ ተነስተን ስንናገር፥ ያ ወቅት ምድር ለመጀመሪያ ጊዜ መለኮታዊ ፍርድን በሰዉ ላይ የፈፀመችበት ወቅት ነው። አሁን ባለንበት ዘመን ግን፥ ፍርዱን በራሱ ላይ የሚፈጽመው ሰው ራሱ ነው። ሰው ራሱን በራሱ እና ምድርን የሚያጠፋ ከሆነ፥ የሥነ ፈለክ ተመራማሪዎች ሲናገሩለት እና የሰው ልጆች ለዘመናት ሲያምኑት የነበረው፥ የምድር በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ልዩ እና ብዙ ጠቀሜታ ያለው ቦታ ላይ መቀመጥ፥ ምንም ረብ የለዉም ማለት ነው። እንግዲህ ምድር በሰው የምትጠፋ ከሆነ፥ ቀድሞ የነበራት ልዩ ሚና በከንቱ የተሰጣት ይመስላል።

እነዚህ ሃሳቦች ጠቃሚ እና ትኩረት ሊሰጣቸው የሚገቡ በመሆናቸው ችላ ልንላቸው አይገባም። እኔ እንደሚመስለኝ፣ በርግጥም እንዲህ ያሉ አስተሳሰቦች አስበው የሚራመዱ ሰዎች አደባብሰው የሚያልፍት አይደለም። ክርስትና ስለዚህ ጉዳይ ምን ይላል? እደግመዋለሁ፤ ስለሰው ልጅ የምድር ቆይታ ርዝመት ይሁን እጥረት ምንም የሚነግረን ነገር የለም። ከነገ ወዲያ ይቀጥላል ወይም በሳይንሳዊ አገላለፅ እንዴት የዘመን ፍጻሜ ይሆናል የሚለውን አይናገርም። እነዚህ ነገሮች ክርስትናን የሚያስጨንቁ ጉዳዮች አይደሉም። ክርስትና በመልዕከቱ የሚነግረን በምድር የሚሆነው ነገር የሚሆንበት ትርጉም ከክስተት ልቆ የሚሔድ መሆኑን እና ስለዚህም የምድር እድሜ ርዝመት ምን ያህል ነው ወይም መች ነው የሚያበቃው የሚለው በዘመን ፍጻሜ ለሚሆን ነገር፣ ከመደምደሚያው ትርጉም ጋር ምንም ተያያዥነት የሌለው እንደሆነ ነው። ነገር ግን ከዘላለም ግብ አንፃር ስናየው የምድር መቀጠል ወይም አለመቀጠል ያን ያህል አስፈላጊ እና አሳሳቢ አይደለም ብለን ደግሞ አንወስድም። ምንም እንኳን ከዘላለም ግብ አንፃር አስፈላጊ ባይመስልም በምድር የመቆየት ጊዜ ውስጥ ትርጉም ያለው ሐይወት እንዲኖረን እና እኛነታችንን የሚሰራበት ስፍር ቁጥር የሌላቸው እድሎችን ይሰጠናል። ስለዚህ እነዚህን እድሎች

ለመጠቀም ምድር እንድትቀጥል የምንችለውን ሁሉ ማድረግ አለብን።

ከምንም በላይ የሰው ልጅ ራሱን በራሱ የማጥፋት ተግባር፣ ነገ ምድር ከመኖር ወዳለመኖር ብትመጣ፣ ምድር እና በውስጧ የነበረው ሁሉ በከንቱ የነበረ አልነበረም። በአጽናፈ ዓለሙ የቢሊየን ዓመታት ዕድሜ ውስጥ ቢያንስ አንድ ፍጥረት ካለመኖር ወደ መኖር መጥቷል፤ ለዚህ ፍጥረት መገኘት ደግሞ በምድር ላይ ያለ ሕይወት ሁሉ አስተዋጽኦ አድርጓል እና በዚህ አንድ ፍጡር ላይ ደግሞ የፍጥረት ሁሉ ምንጬ የሆነው የመለኮት መልክ አለበት። ቢያንስ አንድ ወቅት፣ ሕይወት ያለው ነገር ተፈጥሮአል፤ ነገር ግን ደግሞ ሕይወት ያለው ነገር መፈጠር ብቻ ሳይሆን፣ በዚህ ሕይወት ባለው ነገር የሕይወት አላማና ግብ ተከናውኗል። የሰው ልጅ ታላቅነት መገኛ ምንጩ ከዚህ ነው፣ በግልጥና በስውር ሕይወትን እየከሰስን ያለን አንዳንዶቻችን፣ ለዚህ እውነት ራሳችንን ልንከፍት ይገባል። እጅግ አጭር በሆነው የሕይወት ቆይታችን እና አጭር በሆነው በሰው ልጆች ታሪክ ቆይታ፣ እና ምናልባትም እጅግ በጣም አጭር በሆነው የምድር መኖር፣ አንዳች ዘላለማዊ ትርጉም ያለው ነገር ተከናውኗል። የነገሮች ሁሉ ጥልቀት ማለትም መነሻና መድረሻ፣ ትርጉምና ግብ በአንድ ፍጥረት ውስጥ ተገልጧል። እና የዚያ ፍጥረት ስም ሰው ይባላል።

አንተና እኔ ደግሞ ሰዎች ነን! ይህንን መቀበል የማንችል ከሆነና፣ መሆን የነበረበት እንደዛ ነው የሆነው ግን ሌላ ነው በሚለው አቋማችን የምንፀና ከሆነ፣ የሰው ልጅ በእኩይ የተሞላ ነው፣ ምድርም በሰው ልጅ በደል ረክሳለች፣ በየዘመናቱ የፈሰሰው የንፁሃን እንባ ለበቀል ወደ እግዚአብሔር ትጮሃለች በዚህም ምክንያት እግዚአብሔር እንኳን ሰውን በመፍጠሬ ተፀፅቻለሁ እስኪል ያስገደደ ነው የምንልም ከሆነ ለአፍታ ደግሞ ቆም ብለን "ኖኅ ግን በእግዚአብሔር ፊት ሞገስን አገኘ።" የሚለውን ደግመን እናሰላስል። ይህ አንድ ሰው በያንዳንዱ ሰው ውስጥ ያለ አንዳች ነገር ይወክላል፤ ያም ነገር የሰው ልጅ እስከ ጉድለቱ እና ጥፋቶቹ፣ የመለኮት ባሕርይ ተካፋይ እንደሆነ ያንፀባርቃል። የክርስትና መልእክት እዚህ ጋ አያቆምም። የክርስትና ምልክት ይህ ነው:- እግዚአብሔር ያለምንም እንከን መልኩን በፍፅምና ያገኘበት አንድ ሰው አለ፤ ለሰው ልጅ ሁሉ በእግዚአብሔር ፊት የሚቆመው እርሱ ነው። በዚህ ምክንያት የእግዚአብሔር ልጅ፣ ክርስቶስ ተብሎ ተጠርቷል። በሰው ልጅ የረከሰችው ምድር፣ በሰው እጅ በኩል ነፅታለች ደግሞ ተቀድሳለች። ' ፐል ቲሊች፣ የሰው ልጅ ምድርን የሚያነፃትና የሚቀድሳት እንዴት ነው የሚለውን ሲመልስ፣ "በአንድ ሰው እርሱም በክርስቶስ በተገለጠው፣ በሁሉም ዘመንና በሁሉም ቦታ በሰው ልጆች ሁሉ ውስጥ በሚሰራው፣ የፈውስ፣ የሙላት፣ የፍቅር እና የባርኮት

መለኮታዊ ሀይል ነው" ይላል። "የሰው ልጅ ታሪክ የጨለማ ብቻ ያልሆነበት፥ አስፈላጊም እንዲሆን ያደረገው ይህ ነው። የሰውን ልጅ ለመቀበል እራሷን ስታዘጋጅ የነበረችው የምድርንም ቆይታ አስፈላጊ ያደረገው ይህ ነው። ምድርን አምጦ የወለደው የአጽናፈ ዓለሙ አስፈላጊነት ይህ ነው።" ይለናል።

እና ደግሞ የአጽናፈ ዓለሙ አስፈላጊነት ለምድር ብቻ አይደለም፥ ፍጥረት ሁሉ ደግሞ ለሰው ልጅ ብቻ ተብሎ የተቀመጠ አይደለም። ሌሎች የሰማይ አካላት፣ ሌሎች ታሪኮች፣ ሌሎች የሕይወት ሚስጢራዊነት የተገለጠባቸው ፍጥረታት ሊተኩን ይችላሉ። የእውቀት ማነስ፥ ወይም የተሳሳቱ አመለካከቶቻችን፤ አስተሳሰባችን ከምድር፣ ከራሳችን የሰው ልጆች ታሪክ እና ክርስትናን ጭምር አልፎ ወደሌላኛው ዓለም እንዳያይ ገደቦችን ልናደርግበት አይገባም። ሳይንስ እና ባለቅኔው ደግሞ በምናብ፥ ይህንም ገደብ አልፈው ሌላውን ዓለም መመልከት ጀምረዋል። ክርስትናም የእነሱን አርአያነት ለመከተል መፍራት የለበትም። ከዚህ ባሻገር ክርስትና ገንዘቡ ያደረገው፥ የመለኮት ኋይልና ክብር ከምድር ወይም ከሰው እና ከአጽናፈ ዓለሙ የትኛውም ክፍል እና ግዛት ገደብ የሚሻገር፥ ተቆጥሮ የማያልቅ ካለመኖር ወደመኖር የማምጣት ፈጠራም ማለት እንደሆነ ማሳየት አለበት።

# 7. በሁሉ አመስግኑ

*“ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ ሳታቋርጡ ጸልዩ፤ በሁሉ አመስግኑ”*

*1ኛ ተሰሎንቄ 5፡16-18*

## 1.

“በሁሉ አመስግኑ” እነዚህን ቃሎች በዚህ ወቅት ትኩረታችንን አድርገን የምናሰላስልባቸው ቃሎች ናቸው። በሁሉ እንድናመሰግን፥ ምክርና ማሳሰቢያ ያስፈልገናል? አመሰግናለሁ የሚለው ቃል፥ በቋንቋችን ውስጥ ዕለት በዕለት ጥቅም ላይ ከሚውሉ ቃሉት መካከል ዋነኛው አይደለምን? ለጥቂት ተግባር እንኳን አመሰግንሃለሁ እንላለን። ለኛና ለተግባራችን ለሚቀርብ ሙገሳ አመሰግናለሁ እንላለን። ከልባችንም ይሁን፣ አይሁን አመሰግናለሁ እንላለን። አመሰግንሃለሁ የሚል ቃል፥ ተሰምቶን ይሆን ፥ ከአፋችን የማይጠፋ የልማድ ቃል ነው። ስለዚህ አመሰግናለሁ ስንል ከልባችን ከሆነ፥ ጠንካራ የሆነ ቃል እና ከልባችን መሆኑን የሚያሳይ መንገድ መጠቀም መጀመር አለብን። ሃይማኖተኛ የሆኑ ሰዎችን፥ ምዕመናኑ ሊሆኑ ይችላሉ ወይም አገልጋዮች፥ ጎረቤቶቻቸውን ባገኙት አጋጣሚ ሁሉ አመሰግናለሁ እንደሚሉት፥ ለእግዚአብሔርም ተመሳሳይ የሆነ የማያቋርጥ ምሥጋና ለማቅረብ ዝንባሌ አላቸው።

እንዲህ ዓይነት ነገር፥ ለሰዎችም ሆነ ለእግዚአብሔር ማድረግ ያስፈለገን፥ ለምን እንደሆነ ከጀርባ ያለውን ምክንያት መጠየቅ ግድ ይላል። ለምን ምሥጋና ማቅረብ አስፈለገ? ምሥጋና መቀበልና መስጠት ማለት ምን ማለት ነው? በእለት ተእለት ሕይወታችን እንደግለሰብ፥ እና በሃይማኖታዊ ሕይወታችን በየቀኑ የምናደርገው ድርጊት፥ ወይም የምንጠቀመው አመሰግናለሁ የሚል ቃል፥ ከበስተጀርባ ያዘለውን ትርጉም በትክክል በመረዳት፥ ረብ ከሌለው፣ አእምሮ ከጎደለው ድግግሞሽ አውጥተን፥ ከፍ ባለ ስፍራ ልናስቀምጠው እንችላለን? ይህን አድርገን የምናሳይ ከሆነ፥ ያቺ “አመሰግናለሁ” የምትል ቀላል ቃል፥ በውስጣዊ

ማንነታችን ምን እንደሆን እና ስለ አለማችን የምትነግረን ብዙ ነገር እንዳለ እንደርስበታለን። ሁሉ ሰው ከአፍ የማይነጥላት፥ ግን ደግሞ አላግባብ ጥቅም ላይ እየዋለች ያለች አንድ ቃል በእኛነታችን ጥልቀት ውስጥ ላለ ደረጃ መገለጥ ልትሆን ትችላለች።

አመሰግናለሁ ማለት ሁልጊዜ የማሕበረሰብ ወግና ሥርዓት ብቻ አይደለም። ከእውነት በሆነ፣ ከልባችን በሚፈልቅ ሰሜት፥ ምሥጋና የሚቀበለው ሰው ያንን ምሥጋና ከእኛ ፈለገው፣ አልፈለገው፥ አንድን ሰው አመሰግናለሁ ከማለት ውጭ፥ ሌላ ምንም ማድረግ የማንችልበት ሁኔታ ውስጥ እንገባለን። አንዳንድ ጊዜ ስሜታችን ያሸንፈናል። እና ለተደረገልን ነገር ለማመስገን፥ ቃላት ባጣ አንደበት እናመሰግናለን እንላለን። ይህ እንዲሁ የአፍ ምሥጋና አይደለም። በዚያ ቅጽበት እንደዚያ ይሰማናል። ሆኖም፣ ከጥቂት ጊዜ በኋላ፣ ትንሽም ቢሆን ባዶነት ወይም ውርደት ሊሰማን ይችላል። ዝም ማለት ይኖርብኝ ነበር እንላለን። በአንዳንድ ወቅቶች ደግሞ፥ በሆነ ወቅት ውለታ የሚከብድብን ጊዜ አለ።፣ ነገር ግን፥ በውጫዊ ሁኔታዎች ምክንያት፣ ወዲያውኑ አመሰግናለሁ ለማለት እድሉን አላገኘንም።

በውጤቱም፣ ምሥጋናችንን በአካል ሳንገልፅ ልንረሳው እንችላለን፣ እና ውለታ ወደዋለልን ሰው ጆሮ አይደርስም፤ በጭራሽ አይሰማም። ኢየሱስ፥ አሥር ለምጻሞችን በፈወሰበት ታሪክ ላይ ተመሳሳይ ሁኔታ ተከስቷል። ሁሉም ስላደረገላቸው ነገር ሳያመሰግኑት፣ የዋለላቸውን ውለታ ሳያስቡ አይቀርም፣ ግን አመሰግናለሁ ለማለት ከመካከላቸው አንዱ ብቻ ነው ወደ ኢየሱስ የተመለሰው። ኢየሱስ በዚህ በጣም ተገርሞ ነበር። በቀሩት ደግሞ ተበሳጨ።

ውስጣችን ጥልቅ በሆነ ስሜት የሚሞላው፥ ምሥጋናችንን እና አድናቆታችንን ለመግለጽ ፍላጎት ሲኖረን ብቻ ሳይሆን፥ እንዳች መልካም ነገር ሰርተን ወይም የልግስና ምግባር የፈጸመን እንደሆን፥ በምላሹ ምሥጋና ለመቀበል ከፍተኛ ፍላጎት አለን። አንድ ሰው ለዚህ አስተዋጽኦችን እኛን ማመስገን ሲያቅተው፥ ብዙ ጊዜ በውስጣችን የባዶነት ስሜት ይሰማናል። ይህንን ባዶነት የሚሞላ ምሥጋናን እንጠብቃለን፣ ነገር ግን በማይመጣበት ጊዜ፣ የሆነ ነገር እንደጎደለ ይሰማናል። በሚገርም ሁኔታ፣ ልክ እኛም ከመጠን ያለፈ ምሥጋና ካቀረብን በኋላ ሐፍረት እንደሚሰማን፥ ከመጠን ያለፈ ምሥጋና ወይም ውዳሴ ሲቀርብልን ደግሞ ምቾት አይሰማንም። ያን ምሥጋና ለመቀበል በውስጣችን ምንም አይነት ቦታ የለም እና ወደመጣበት እንገፋዋለን። እንዲህ አይነት ስሜት እንደተሰማን በንግግራችን ገለፅነውም አልገለፅነውም። ያለ ውስጣዊ ተቃውሞ ምሥጋና መቀበል በጣም

ፈታኝ ሊሆን ይችላል። እንደ “ምንም ማለት አይደለም፤ ተቀብያለሁ “እና “እባክህ፥ ችግር የለም” ያሉ አገላለጾች፥ ሰዎች ሳያንገራግሩ ምሥጋና እንደማይቀበሉ የሚያሳዩ ምሳሌዎች ናቸው። ምሥጋናን ላለመቀበል ቀላሉ አገላለጽ “ማለት አያስፈልግም” የሚለው ሲሆን ሆኖም ግን በተመሳሳይ ጊዜ ምሥጋናውንም እንቀበላለን።

በቀላሉ ምሥጋናን ለመስጠት ወይም ለመቀበል፥ የምናሳየው ማንገራገር ከሌሎች ጋር ስለ አለን ግንኙነት እና ሰው በመሆናችን ስለ አለንበት ተፈጥሯዊ” አጣብቂኝ” ሁኔታ፥ አንዳች ነገር ያስተምረናል። በማንኛውም ጊዜ ምሥጋናን ስንሰጥ ወይም ስንቀበል፣ አንድን ሰው እንቀበላለን ወይም እንገፋለን ማለት ነው፣ እና እነሱም በተመሳሳይ መንገድ ይቀበሉናል ወይም ይገፉናል ማለት ነው። ምሥጋናን በመቀበልና እና በመግፋት ሂደት፥ ሰውየውን ራሱ የመቀበልና የመግፋት ሂደት እንደሆነ ብዙ ጊዜ አይታወቅም። በሁለቱም ወገኖች አይታወቅም። ቅፅበታዊ እና በእኛነታችን ንቁ ባልሆነው ኅሊና ውስጥ የሚካሄድ ሂደት ነው። ካወቅን ስሜቱ ሊሰማን ይችላል እና “በደስታ ወይም በሀዘን”፥ “በሃፍረት፣ ወይም በኩራት”፥ ወይም የእነዚህ ስሜቶች ጥምረት በያዘ ሁኔታ ምላሽ ልንሰጥ እንችላለን። እጅግ ቀላል የሆነው “አመሰግናለሁ” የሚል ቃል የጠብ እና ሽሽት ምክንያት ሊሆን ይችል ነበር። እጅግ ቀላል የሆነው “አመሰግናለሁ” የሚል ቃል፥ አንድ ሰው በእኛ ውስጥ ስፍራ እንዲኖረው ከሚያደርገው ሙከራ ራሳችንን የምናርቅበት አዋጭ መንገድ፣ ወይም አንድ ሰው በእኛ ውስጥ ስፍራ እንዲኖረው የምናደርግበት መንገድ መገለጫ ሊሆን ይችላል። እጅግ ቀላል የሆነው “አመሰግናለሁ” በሚል ቃል ውስጥ የምናመሰግነውን ሰዉ፥ አንተ በእኔ ውስጥ ፍጹም አታስፈልግም ማለትም ሊሆን ይችላል። የልባችንን በር ከፍተን ማስገባትም ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ምን አልባት ብዙ ጊዜ እንደሚሆነው፥ አመሰግንሃለሁ በማለት ውስጥ “የምናመሰግነው ሰዉ” ለኔ ግድ አይሰጠኝም የማለት ጨዋነት ያለው መንገድ ሊሆን ይችላል።

መዝሙር ምዕራፍ 50 ላይ “ለእግዚአብሔር የምሥጋናን መሥዋዕት ሠዋ” እና “ምሥጋና የሚሠዋ ያከብረኛል” ይላል። አሁን በዚህ ስፍራ፥ የምሥጋና ትክክለኛ ትርጉም፥ ጉልህ በሆነ ሁኔታ ቀርቦ እናገኘዋለን። ምሥጋናን ማቅረብ መስዋእትነት ነው። በዚህ ዐውደ የ”ምሥጋና”ን ቀጥተኛ የትርጉም ስሜት መረዳት ይቻላል። ምሥጋና የሚገለጸው በመስዋዕትነት ድርጊት ውስጥ ነው። ውድ ዕቃዎች ከተለመደው የአገልግሎት ዓላማቸው ወጥተው፥ ለአማልክት እንደ መስዋዕት ተደርገው ይሰጣሉ። ይህ ሰው ራሱን እንዳልፈጠረ እውቅና ሲሰጥ ማለት ነው። በእውነት የእሱ የሆነ ምንም ነገር የለም። እኛ ያለ ምንም ነገር፥ ራቁታችንን ወደ

ዓለም መጥተናል እና ያለ ምንም ነገር ጥለነው እንሄዳለን። ሰው ያለው ነገር ሁሉ የተሰጠው እንጂ ከራሱ የሆነ ምንም ነገር የለም። የምሥጋና መስዋእትን በመሠዋት፣ ስለ እጣ ፈንታ፣ ፍጻሜው ምን እንደሆነ ያለውን ግንዛቤ ያሳያል። ከተሰጠው ውስጥ የተወሰነውን ያቀርባል፣ ምንም እንኳን ያቀረበው ነገር እንኳን የእውነት የእርሱ ባይሆንም። ምሥጋናን በመስዋዕት፥ ውሱን ህልው እና ጊዜያዊ የሆነ ፍጡር መሆኑን ራሱ ምስክር ሆኖ ይቀርባል። ማንኛውም ልባዊ ምሥጋና፥ የመስዋእት ተግባር፥ ውስን ፋጡር የመሆናችንን እውነታ መቀበልን ያካትታል። ምሥጋናን በእውነት መግለጽ የሚችል ሰው ፍጡር መሆኑን ይቀበላል፣ ይህንንም ሲያደርግ፣ የተለየ ሃይማኖት ባይከተልም መንፈሳዊ ነው። በተጨማሪም፣ ምንም ሳያንገራግር ልባዊ ምሥጋና የሚቀበል ሰው በሳል ሰው ነው። የራሱንም ሆነ የሌሎችን ሰዎች ውስንነት ያውቃል። ደግሞ በዚህም ምሥጋና የመለዋወጥ የጋራ ተግባር ውስጥ ሁለቱም ግለሰቦች ፍጥረት መሆናቸውን እየመሰከሩ እንደሆነ ያውቃል።

# 2.

ለሌሎች ከልባችን የሆነውን ምሥጋና በምናቀርብበት ጊዜ ሁሉ፥ ማንን እንደምናመሰግን እና ለምን እንደሆነ እናውቃለን፣ ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ፥ ያንን ምሥጋና እንዴት እንደምናቀርብ ጭንቅ ይሆንብናል። እንዲሁ ደግሞ ከመሬት ተነስተን፥ ምሥጋና የምናቀርብባቸው ጊዜያትም አሉ። እንደዛ እንድናደርግ ምክንያት የሆነ ሰው፥ ወይንም የተለየ ነገር አልተፈጠረም። በዚህ ጊዜ ምሥጋና የምናቀርብለት ማን ነው የሚለው ጠፍቶን ሳይሆን፥ ማንም ስለሌለ ምሥጋናው በውስጣችን የሚገላበጥ ነው። እንዲሁ ምሥጋና እናቀርባለን። ይህ ዓይነቱ ምሥጋና የሚመጣው በእኛ ሕይወት ውስጥ አንድ ታላቅ ያልተለመደ ነገር ስለተፈጸመ አይደለም። ነገር ግን፥ ምክንያት የሌለው ምሥጋና የማቅረብ ልምምድ ሕይወታችንን ይሞላዋል። ሰው ሆነን በመፈጠራችን፥ በእኛነታችን ምክንያት ምሥጋና እናቀርባለን። ሰዉ የመሆን ኀይልና ክብር ውስጥ እንድንሳተፍ ተደርገን ስለተፈጠርን በምሥጋና እንሞላለን። ይህ ሁኔታ፥ በደስታ ስሜት ውስጥ የመገኘት ሁኔታ ነው። ከደስታ ስሜት በላይ ነው። ከሚሄድ እና ከሚመጣ የደስተኝነት ስሜት በላይ ነው። ይልቅ ዘላቂ ሆኖ እኛነታችን ውስጥ ይከርማል። ይህ የምንገባበት የደስታ እና የሐሴት ሁኔታ፥ ምሥጋና ማቅረብ እንዳለብን፥ እንድንገነዘብ የሚያደርገን ጥልቅ የደስታ ሁኔታ ነው። ሆኖም ግን ይህንን ምሥጋና ወስደን የምንሰጠው ምንም ነገር፥ ማንም የለም። እናም በውስጣችን የምሥጋና ስሜት ተሸክመን በዝምታ እንሆናለን። በፀጥታ ውስጥ ምሥጋና በውስጣችን

ይፈሳል።

ይህንን ምሥጋና ለምንድነው ወደ እግዚአብሔር የማናቀርበው ብላችሁ ትጠይቁ ይሆናል። ክርስትያን በሆኑት ሆነ፣ ክርስትያን ባልሆኑት፤ በሚያምኑት ሆነ በማያምኑት ዘንድ፥ በውስጣቸው የተፈጠረውን ሁኔታ የሚገልጽ ወይም የተረዳ ጥያቄ አይደለም። በርግጥ ውስጣቸው በምሥጋና ተሞልቷል። እያመሰገኑ ነው። ነገር ግን በፀሎት በኩል ወደ እግዚአብሔር የሚያቀርቡት ምሥጋና አይደለም። ለምንም እና ለማንም ያልሆነ ነገር ግን፥ አመሥጋኝነት ብቻ በውስጣቸው ሞልቷል። ምናልባት ምሥጋና በተሞላ ፀሎት፥ መስዋዕታቸውን ይዘው ወደ እግዚአብሔር እንዲያቀርቡ ቢነገራቸው፤ ውስጣቸው የሞላውን የምሥጋና፣ ስሜት ሊያጠፋው ይችላል። ያለ ትእዛዝና መመሪያ ውስጣቸው የፈጠረውን ነገር፥ እንደአመጣጡ እንዳያስተናገዱ፥ እንቅፋት ማስቀመጥ ነው።

ሁላችንም በሆነ ጊዜ በሕይወታችን ሊሆን የሚችል ይህን አይነት ሁኔታ፥ የምንደኘው እንዴት ባለ ሁኔታ ነው? እግዚአብሔርን ተመስገን ካላልን፥ እዉነተኛ ምሥጋና አይደለም በማለት እንናገር? ጳውሎስ እንደገለጸው ራሳችንን “እግዚአብሔርን እየወቁ እንደ እግዚአብሔርነቱ አላከበሩትም ወይም አላመሰገኑትም” እንደተባለ እንደ አረማውያን ህዝቦች ሆነናል ብለን ራሳችንን እንገልጻለን? በጭራሽ እንደርሱ አናደርግም። ምንም እንኳን በንግግር እግዚአብሔርን ተመስገን ባንልም፥ በአመሥጋኝነት የተሞላ ልብ፥ እግዚአብሔርን ያከብራል። የማያምን እንኳን ቢሆን አመሥጋኝ ልብ ካለው፥ አለማመኑ አብቅቷል። ከምንም ተነስቶ፥ በሕይወት ውስጥ በመገኘቱ የሚያቀርበው ምሥጋና ወይንም በውስጡ የሚሰማው ምሥጋና፥”ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ!” ለሚለው የመጽሐፍ ቅዱሳችን ምክር መታዘዝ ችሏል ማለት ነው።

የመጽሐፍ ቅዱስ ምንባባችን “ሁልጊዜ ደስ ይበላችሁ፣ ያለማቋረጥ ጸልዩ፣ እና ስለ ሁሉም ነገር አመስግኑ።” ይላል። እንደዚህ ከሆነ፥ ይህን ክፍል ለመረዳት ቀላል ነው። ነገር ግን “በፍፁም ሀዘን አይሰማህ፣ ሁልጊዜም ቀንና ሌሊት ፀልይ እና የምሥጋና ቃል አውጣ!”ማለቱ በጭራሽ አይደለም። ኢየሱስ ይህ ራሳችንን በእግዚአብሔር ላይ በግድ ለመጣል የሚደረግ ዘዴ፥ ሃይማኖት መሆን ያለበትን እንደ ማዛባት ወይም ማበላሸት ነው በማለት ገልጾታል። ታዲያ በዚህ ምንባብ ውስጥ ያሉ ማበረታቻዎች፥ ለማስተላለፍ እየሞከሩ ያሉት ትክክለኛው መልእክት ምንድን ነው? እያሉ ያሉት፥ አፋችንን እየከፈትን በመፀለይ ልናሳየው ወይም ላናሳየው ብንችል እንኳን፥ ጸጥ ያለ የምሥጋና ስሜት ውስጥ መሆን ማለት ነው። ዘወትር ከእርሱ የምንፈልገውን ወይም ስለ አደረገልን ነገር፥ ለእግዚአብሔር መንገር አይጠበቅብንም። ሁልጊዜ በምናደርገው ነገር ሁሉ፥ በመንፈስ ከእግዚአብሔር ጋር ለመገናኘት ሁልጊዜ መነሳት አለብን። እሱ ህልውናውን፥ ከህልውናችን ፈጽሞ አይጠፋም። እኛ ባናስተውለውም፥ እርሱ ሕይወት በሚያበዛ መንገድ፥ ሁል ጊዜ በሁሉም ሰው ሕይወት ውስጥ፥ በህልውናው ይገኛል። ነገር ግን በፀጥታ ውስጥ ሆነን በምሥጋና ስንሞላ፥ መገኘቱ ይሰማን ይጀምራል። ብዘ አመሰግንሃለሁ የሚሉ ቃላትን በመደርደር ብቻ ሳይሆን፥ ለእሱ ክፍት በመሆን ከፍ ያለ የሕይወት ልምምድ ውስጥ ልንገባ እንችላለን።

አንድ ሰው ይጸልይ እንደሆነ በተጠየቀ ጊዜ። “ሁልጊዜ እና በጭራሽ አልፀልይም” ሲል መለሰ። መለኮታዊ መገኘት እንዳለ ተረድቷል። ነገር ግን ይህንን መረዳት ለማሳየት ጸሎትን እና የምሥጋና ቃላትን እምብዛም አይጠቀምም።

እርሱ የመለኮትን ህልውና በሕይወታቸው ስላልተለማመዱ አመሰግንሃለሁ የሚል ቃል ከአፋቸው ከማይወጣቸው ወገን አይደለም። እና እግዚአብሔርን ማወቅ ማለት እርሱን ያለማቋረጥ መጥራት ማለት ነው ብለው ከሚያምኑት ወገን አልነበረም። አንድ ሰው፥ ከእግዚአብሔር ጋር ሲነጋገር፥ የሚያወጣቸው ቃላት ከፍ ካለ፣ አብዝቶ ከሚያመሰግን እና ጸጥ ካለ የአእምሮ ሁኔታ መውጣት አለበት ብሎ የምን ነበር። ሌላ አንድ ሰው፥ በእግዚአብሔር እንደሚያምን ተጠየቀ እና እርግጠኛ አይደለሁም ነገር ግን አንድ ጥሩ ነገር ካጋጠመው የሚያመሰግነው የሆነ ኀይል ቢኖር እንደሚፈልግ ተናገረ። ልክ እንደ መጀመሪያው ሰው፣ ይህኛውም ጠንካራ ፣ ምሥጋና የማቅረብ ስሜት ተሰምቶት ነበር።

ነገር ግን ይህኛው ስሜቱን በቃላት ለመግለጽ እና በቀጥታ በንግግር ምሥጋና ለማቅረብ ፈልጎ ነበር። ሁለቱም ሰዎች የሚገልጹልን፥ እግዚአብሔርን ማመስገን በፀጥታ ውስጥ የሚከወን ከፍ ያለ ሕይወት ሊሆን እንደሚችል፣ እና ደግሞ ለእግዚአብሔር በቃላት የምሥጋና መስዋት ለመስዋእት ፍላጎት ሊሆን እንደሚችል ነው።

በእነዚህ ሁለት አመሰግናለው የማለት መንገዶች፣ ከእግዚአብሔር ጋር በሁለት የተለያዩ መንገዶች ግንኙነት እንደምናደርግ ማየት እንችላለን። በአንድ በኩል እርሱ፥ አመሰግንሃለሁ ብዬ ላወራው የምችል ቀርቤ የሆነ፥ “ሌላ እና ከሌላ” ነው። በሌላ በኩል ከእኔ እና ከሁሉም በላይ የሆነ፥ ከቶም ልቀርበው እና ላናግረው የማልችል፥ “ሌላ እና ከሌላ” ነው። ነገር ግን በፀጥታ ውስጥ በምሥጋና ስሆን ራሱን ሊገልጥልኝ ይችላል።

አንዱ እና ታላቁ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ ይዞ የመጣው ነገር፥ እኛ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕብረት፥ ያለማቋረጥ ጸሎቶችን በመድገም ወይም በአምልኮ ሥርዓቶች በመሳተፍ፣ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ወይም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ በምንሠራው ወይም በምንናገረው ነገር የሚመሠረት ሳይሆን፥ እግዚአብሔር እንዲሁ እንደተቀበለን በማወቅ ውስጥ ሰላምና ደስታን ማግኘት እንደሆነ መገንዘቡ ነው።

# 3.

የምናመሰግነው ለምን ጉዳይ ነው? ምሥጋና መስጠት ገደብ ይኖረው ይሆን? የመፃፍ ቅዱስ ምንባባችን እንደዚህ ይላል"በሁሉ አመስግኑ" ይህ ማለት በሁሉ ነገር ውስጥ ማለት ነው። ለሁሉ ነገር አመስግኑ ማለት ግን አይደለም። ይልቅ በሁሉም ሁኔታዎች ውስጥ ምሥጋና አቅርቡ እያለ ነው። ምሥጋና ለማቅረብ ምንም ዓይነት ገደብ የለም ነገር ግን አንድን ሰው በምን ጉዳይ ነው የማመሰግነው ለሚለው ገደብ አለው። ይህ ጥያቄ ሰዎች በየቀኑ በሚያጋጥሚቸው ተግዳሮቶች ላይ አዲስ መረዳት እንዲኖረን የሚረዳን ጥያቄ ነው።

በ1ኛ ጢሞቴዎስ ምዕራፍ 4:4 እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን። "እግዚአብሔር የፈጠረው ሁሉ መልካም ነውና፥ ከምሥጋናም ጋር ቢቀበሉት የሚጣል ምንም የለም" በእነዚህ ቃላት ምሥጋና አዲስ ሚና ተሰጥቶት እናገኛለን። በእግዚአብሔር የተፈጠረውን ሁሉ ቅዱስ ያደርጋል። ምሥጋና አንድን ነገር የተቀደሰ የማድረግ ተግባር ነው። የዚህ ዓለም የሆነን ነገር ወስዶ ወደ ቅዱሱና መንፈሳዊው ግዛት ያንቀሳቅሳል። በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እና ከቤተ ክርስቲያን ውጪ፥ ያሉ "አጓጉል፣ እንግዳ እና መናፍስታዊነት" የተጠናወታቸው ሊለውጡት እንደሚሞክሩት፥ ወደ ሆነ ልዩ ነገር፥ አንዳች ነገር ወደሚያመጣ ኋይል አይለወጥም። ነገር ግን መለኮትን ለመወከል ከፍ ብሎ ይቆማል። ፀጋን ይዞ ይመጣል።

ስለዚህም የዕለት ምግባችንን ስንመገብ፥ ስለሰጠን ምግብ በምናመሰግንበት ወቅት፥ ፀጋህ አይጓደል እንላለን። በዚህም የሰጠንን ምግብ እንቀድሰዋለን። ምግብ ብቻ አይደለም፤ በምሥጋና የተቀደሰ ትርጉም ያለው ነገር ይሆናል። በፍጥረት ውስጥ ያለ ነገር ሁሉ የተቀደሰ መሆን ይችላል። የምሥጋና ምክንያት ሊሆን ይችላል ማለት ነው። ከዚህ አንፃር ካየነው ምሥጋና ለማቅረብ የሚገድበን ምንም ነገር የለም። ስለሰጠን ጤነኛ አካል እና አዕምሮ ምሥጋና ልናቀርብ እንችላለን። ስላልነቃው ውስጠኛው የእኛነታችን ክፍል፤ ሁሉን መቃኘት ስለሚችለው የኅሊናችን ክፍል ምሥጋና ማቅረብ እንችላለን። ስለ ምድር እና ሞላዋ ማመስገን እንችላለን። ላለው ነገር ሁሉ እና ሕይወት ስላለው ነገር ሁሉ ምሥጋና ማቅረብ እንችላለን። የሰው ልጆች ስላበጇቸው ነገሮች ሁሉ ምሥጋና ማቅረብ

እንችላለን። ስለነዚህ ሁሉ ምሥጋና ማቅረብ እንችላለን።

ታዲያ ይህን ስናደርግ ለተፈጠረው ነገር ሁሉ፣ ተፈጥሮን እና በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን ነገር፣ ሰዎች የሰሯቸውን እና ሃይማኖታዊ የማይመስል የሚሉትን የሚጠሉ ወግ አጥባቂ፣ ምድር ከንቱ ነች የሚሉ እና እግዚአብሔር የፈጠረውን ዓለም የሚያማርሩ ባሉበት ነው። በንፁህ ኅሊና ምሥጋና ልናቀርብበት የምንችለው ነገር ሁሉ ከምሥጋና የተነሳ ልዩ ይሆናል። የተቀደሰ ይሆናል። ይህ እውነት መሠረታዊ የሆነ ሥነ መለኮታዊ መረዳት ብቻ አይደለም። ነገር ግን አንድን ነገር ለመቀበል ወይም ለመተው እርግጠኞች መሆን በማንችልበት ወቅት፥ ተግባራዊ የሆነ የመመዘኛ መስፈርት ነው። ስለዚህ ጉዳይ ላመሰግንበት እችላለሁ ብለን የምንጠይቅበት ነው። አንድን ነገር ከተቀበልን በኋላ ለተቀበልነው ነገር ምሥጋና ማቅረብ እንችላለን። በምሥጋናችንም ፍጥረት መልካም እንደሆነ ምስክር እንሆናለን ማለት ነው። በእውነት ከልባችን ምሥጋና ያቀረብንበትን ጉዳይ ልዩ እናደርገዋለን። እንቀድሰዋለን። እና ከመጣበት ቅዱስ የሕይወት ምንጯ ጋር እናገናኘዋለን። እና የፕሮቴስታንት እምነት ተከታዮች ሊወስዱት የሚገባውን አደጋ እንኳን ለመውሰድ አንፈራም፤ ኅሊናችን ስህተት ውስጥ ሊወድቅ ይችላል እና መጣል ያለበትን ልንቀበልም እንችላለን። ግን ቢሆንም ምሥጋና እናቀርባለን!

በፍጥረት ውስጥ፥ ምሥጋና የማናቀርብበት አንዳች ነገር የለም። ምሥጋና ለማቅረብ ገደብ የለም። ነገር ግን በሕይወታችን ውስጥ ገደቦች የሉም? በታማኝነት ስንናገር፥ ላለንበት ተስፋ መቁረጥ፣ ለገጠመን አደጋ እና በሽታ ምሥጋና ማቅረብ እንችላለን? እነዚህ ሁኔታዎች በደረሱብን ቅፅበት ምንም ነገር ማድረግ አንችልም። እዚህ ጋ ከልክ በላይ አጉል መንፈሳዊ መሆን፥ ወደ ውሸታም እና አስመሳይነት እንዳይከተን ልንጠነቀቅ ይገባል። እንደዚህ አይነት መጥፎ ነገሮችን መቃወም ጥሩ ነው። እንደሰው መከራን ከሕይወታችን ማስወገድ እንፈልጋለን። ተፈጥሮአዊ ስለሆነ። ከአቅማችን በላይ ሆኖ መከራ ውስጥ ስንሆን በሕይወት እና ባመጣብን ነገር እንቆጣለን። እንማረራለን። እና ማመስገን የሚል ሃሳብ እንኳን የማይመጣበት ከባድ የአካል እና የአእምሮ ህመም ውስጥ የምንሆንበት ጊዜያት አሉ። ዳዊት በመዝሙራቱ ውስጥ ከመከራው ጥልቀት ውስጥ ሆኖ ወደ እግዚአብሔር ሲጮህ ሲጣራ እናያለን። ምሥጋናን ግን ከአፉ አላወጣም! ይሄ እውነተኛ መሆን። መሬት ላይ ያለውን ነገር አለመካድ! ይህ በሕይወታችን ያለውን የእግዚአብሔርን ህልውና ከመረዳት የሚወጣ እውነተኝነት ነው። ሁላችንም በሕይወታችን ውስጥ መጥፎ ገጠመኞች ያጋጠሙን ይመስለኛል። በኋላም ወደ ጥሩነት የተቀየሩ፣ እና በኋላ ከልባችን የምሥጋናችን ምክንያት ሆነዋል።

በደለኞች እንድንሆን ወይም መልካም እንድንሆን ላደረጉን፣ ለሰራናቸው ጥሩ እና መጥፎ ሥራዎች ምሥጋና ማቅረብ አንችልም። የጥፋተኝነት ስሜት እንዲሰማን ወይም ለፈፀምነው ስህተት ተጠያቂ ለሚያደርገን ነገር ምሥጋና ማቅረብ የለብንም። በተጨማሪም፣ መጀመሪያ ላይ ያመሰገንበት ጉዳይ፣ በበደላችን ምክንያት ወደ ክፋ ነገር የሚቀየርበት ጊዜ ሊኖር ይችላል። ጥሩነታችን ስለሚያስመሰክሩ በውስጣችን ስላሉ ነገሮች ምሥጋና አናቀርብም። የፈሪሳውያን ስለበጎ ሥራቸው ራሳቸውን የሚያመሰግኑበት ልምድ፣ ለምን ጉዳይ ምሥጋና ማቀረብ እንደሌለብን እና እንዳለብን፣ ጥሩ ምሳሌ ይሆነናል። በእውነቱ ስለሰራናቸው በጎ ሥራዎች ምሥጋና ለእግዚአብሔር በምናቀርብበት ጊዜ እየመሰገንን ያለነው፣ ራሳችንን እንጂ እግዚያብሔርን አይደለም። ስንቶቻችን ይሆን እግዚአብሔርን እያመሰገንን እየመሰለን ለራሳችን ምሥጋናን የምንሰዋ! አንድ ሰው ራሱን ማመሰግን የለበትም! ለራስ የሚሰጥ የምሥጋና መስዋዕት፣ ምሥጋና አይደለም! ለራስ ምሥጋና ማቅረብ ዋጋ የለውም! ለምሳሌ ጠንክረን ሠርተን ስናጠናቅቅ ወይም ከትልቅ ትግል በኋላ አንድ ነገር ስናሳካ የምናቀርበው የምሥጋና ቃል እና የምሥጋና ፀሎት፣ አንዳንድ ጊዜ ድብቅ ራስን የማመስገኛ መንገድ ሊሆን ይችላል።

ምሥጋና ማቅረብን በተመለከተ ጥያቄ በአእምሮአችን ይዘን፣ መጽሐፍ ቅዱስን ማንበብ፣ በተለይም የመጨረሻዎቹን የመዝሙረ ዳዊት ሦስት ቁጥሮች ማንበብ፣ እጅግ አስገራሚ ልምምድ ነው። አንድ ሰው፣ እነዛን ክፍሎች በሚያነብበት ጊዜ፣ የመዝሙራቱን ጸሐፊዎች ጨምሮ፣ የሁሉም የሰው ልጆች ሀዘን እና መከራ በተጻፈበት በዚህ መጽሐፍ ውስጥ፣ አንዱን ገፅ ጨርሰን ወደ ሌላ ገጽ ስንሄድ፣ ለእግዚአብሔር በሚቀርብ የምሥጋና መስዋዕት ሞልቶ ያገኛቸዋል። በ ጸሐፊዎቹ ሕይወት ውስጥ መከራና ችግር ቢኖርም ከምሥጋና ግን ያገዳቸው ነገር አልነበረም። እያነበብናቸው፣ በመከራና በአስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ እንኳን፣ ምሥጋና ማሰማት እንደሚቻል እየተሰወረብን ስለመጣ በሌላ ዓለም ያለን ያህል ሊሰማን ይችላል። ልክ እንደ እነርሱ በመከራ ውስጥ ምሥጋናና ውዳሴን ማቅረብ ተራራ መውጣት ሊሆንብን ይችላል። እግዚአብሔርን ማወደስ፣ ማመስገን እንኳን እንዳለብን ላይሰማን ይችላል። ስለ አለንበት ችግርና መከራ መብሰልሰል ላይ እናተኩራለን። ውዳሴ ለማቅረብ እና ለማመስገን ምክንያት የምንለው ነገር እንዳለ አይታወቀንም። ከግዴታ ተነስተን፣ እግዚአብሔርን ማመስገን እንደለብን ተሰምቶን ለማመስገን ስንሞክር፣ ወይም በቤተ ክርስቲያን አገልግሎት በፀሎት እና ምሥጋና ፕሮግራም ስንሳተፍ፣ ከእውነተኛ ስሜታችን የወጣ ነገር እንደሆነ

አይሰማንም፡፡ ውስጣችን ሌላ፤ ላያችን ሌላ እንደሆነ ይሰማናል፡፡ ይህ ውዳሴን እና ምሥጋናን በትክክል መግለጽ አለመቻል፥ የዘመናችን ሃይማኖታዊ ልምምድ የተለመደ ገጽታ ነው፡፡ የእውነት በመከራ ውስጥ እንኳን እንዴት ነው ምሥጋና የማቀርበው የሚለው ይሰወርብናል፡፡ ይህ ስሜት በሕዝቡ ብቻ ሳይሆን፥ በብዙ የዘመኑ ሰባኪዎች፣ የሃይማኖት ሊቃውንት፣ ባለቅኔዎች እና ፈላስፋዎች ተገልጦ እናገኘዋለን፡፡ ሲያስተላልፉት እናያለን፡፡ . እኛ ራሳችንን ጨምሮ፥ ብዙ ሰዎች የሚሰማቸውን በዚህ ሁኔታ ስለሚገልጹ በእነዚህ ግለሰቦች ላይ መፍረድ የእኛ ድርሻ አይደለም፡፡ ብዙውን ጊዜ በራሳቸው መንፈሳዊ ስቃይ የተነሳ እነዚህን ስሜቶች በሐቀኝነት ለሚገልጹት ሰዎች ልናመሰግናቸው ይገባል፡፡ ችግራቸውን እንጂ ምሥጋናን ማቅረብ ስላልተሰማቸው ልንገስፃቸው አይገባም፡፡ እኛም ልምዶቻቸውን ወይም ስሜቶቻቸውን እንካፈላለን፡፡ በዚህ መልክ የራሳቸውን ሃሳብ እና ስሜት ሲገልጹ፥ የእኛን ሃሳብ እና ስሜት ያስተላልፋሉ፡፡ ብዙ ጊዜ ከጥልቅ መንፈሳዊ ህመም ተነስተው፥ ራሳቸውን በዚህ መንገድ ለሚገልፁ ሰዎች ምሥጋና ማቅረብ አለብን፡፡

በቀደመው ቤተ ክርስትያን ውስጥ ያሉ ሰዎች፥ አረማዊነት በገነነበት ዓለም፥ በተዘበራረቀ እና ተስፋ በሌለው ሁኔታ፥ ስለበራላቸው የወንጌል ብርሃን ምንያህል በጋለ ስሜትና ፍጹም መሰጠት እግዚአብሔርን ያመሰግኑ እንደነበር ከታሪክ ስናነብ፥ አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ነገሩ የተለየ መሆኑ ግልጽ ነው፡፡ እግዚአብሔር ስለሰጠን ስጦታ፥ ማለትም ስለ ክርስቶስና ቤተ ክርስቲያን፥ ስናመሰግን ልክ እንደነ እርሱ ተመሳሳይ የሆነ የጋለ ስሜት እና አድናቆት በውስጣችን አለ ወይ? ማን ነው ከልቡ ለዚህ ጥያቄ “”አዎ” ብሎ ሊመልስ የሚችል?

በተጨማሪም፥ ለተሃድሶ የተዋደቁ የተሐድሶ አባቶች፥ ዳግም በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እግዚአብሔር ኀጢአተኞችን እንደሚቀበል እና ያለምንም የሰው ሰራ ይቅር እንደሚል፥ ተሸፍኖ የነበረውን እውነት በማግኘታቸው ምን ያህል እግዚአብሔርን ያመሰግኑ እንደነበር ስናነብ፤ አሁንም በእኛ እና በእነርሱ መካከል ልዩነት እንዳለን ይሰማናል፡፡ በእነርሱ ውስጥ የነበረውን ለዚህ እውነት ግድ የመሰኘት ነገር በእኛ ውስጥ አለ? ማን ነው ከልቡ አዎ የሚለው? ስለዚህ አሁን እየሆነ ስላለው ነገር እውነቱን ስለሚናገሩ ሰዎች ምሥጋና ማቅረብ አለብን፡፡

ነገር ግን አንድ የምንፅናናበት ቃል አለ፦ ሁሌም አብሮን ከሚሆነው፥ ከእግዚአብሔር መገኘት የምንነጠል አይደለንም፡፡ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን

ሁሉ፥ የእርሱን መገኘት መለማመድ እንችላለን። ለእግዚአብሔር መገኘት ክፍት ሆኖ ለመቆየት በመምረጥ፣ ልባችን በምሥጋና እና በውዳሴ ሊሞላ ይችላል። ቃላት ሳናወጣ እንኳን፥ በልባችን ምሥጋና በማቅረብ እና በውዳሴ ሊሞላ ይችላል። በሌላ ጊዜ ደግሞ፥ አንደበታችን በምሥጋና እና የውዳሴ ቃላት ሊጥለቀለቅ ይችላል። ነገር ግን ይሄን ቃል መናገር ወይም አለመናገር ህልውናውን ለመገንዘብ አስፈላጊ አይደለም። የዘመኑ ሃይማኖታዊ ሪቫይቫይ ተብሎ የሚጠራውን እንቅስቃሴ ከፊት ሆነው የሚነዱ ሰዎች፥ ከልባችን ልንቀበለው ወደማንችለው፥ ዝም ብሎ ቃል ወደመደጋገም ፀሎት እና የምሥጋና ሥነ ሥርዓት እንድንመለስ ወይም በግድ ራሳችንን ነቅንቀን ደስታ እና ምሥጋና በውስጣችን የመፍጠር ልምምድ ውስጥ እንድንገባ ወደሚያደርግ ነገር፥ እንዲመልሱን ልንፈቅድ እና ልንከተላቸው አይገባም። ነገር ግን፥ ሕይወታችንን በየቀፅበቱ፥ ማለትም እዚህ እና አሁን፥ ለተሸከመው፣ በክንዱ ለሚደግፈው፥ በተፈጥሮ እና በክርስቶስ መልዕክት በኩል ለመጣው ኋይል፥ ልባችንን እንደከፈትን እንኑር። በውስጣችን ላለው የመሆን ኋይል፣ ሐይወት፥ በፀጥታ በተሞላ የአመሥጋኝ ማንነት እንሞላ ዘንድ፥ ውስጣችን ክፍት እንደሆነ እንቆይ! እና ከዚያ ምናልባት፥ ዳግም በእውነት እና በታማኝነት ምሥጋና እናቀርብ ዘንድ የምሥጋና ቃል፣ የመስዋዕት ቃል፣ እና የሚቀድስ ቃል ከአንደበታችን ሊወጣ ይችላል!

# 8. በሽተኞችን ፈውሱ፣ አጋንንትን አስወጡ

*"ድውዮችን ፈውሱ፤ .....አጋንንትን አውጡ"*

*ማቴዎስ 10፡8*

ፖል ትሊች ይህንን ዲስኮርስ የሰጠው፣ እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር በ1955 በኒዮርክ፣ ለዩኒየን ቴዎሎጂካል ሴሚናሪ የሰነ መለኮት ምሩቃን ተማሪዎች ነበር። ንግግሩንም ሲጀምር ተመራቂዎችና ወዳጆች በሚል ነበር። እኛም ከዚህ ንግግር ዋናውን ፍሬ ነገርና ለኛ የሚሆነውን ለመውሰድ ዘልቀን እንግባ።

ፓል ቲሊች፣ ኢየሱስ አንድን አገልጋይ ከፊቱ ቀድሞ እንዲሄድ የፈውስ ሀይል ሰጥቶ ሲልከው፣ የመጀመሪያ ችግር የሚሆነው የተላከበት ህዝብ ጋ ሲደርስ፣ ህዝቡ ፈውስ እንደማይፈልግ ከአፋቸው ሰምቶ ያወቀ ጊዜ ነው ይለናል። አገልጋዩ ኑሯቸውን የተቆጣጠረውን አጋንንት ሊያስወጣ እንደመጣ ሊናገር ይችላል። ነገር ግን ይላል ፖል ትሊች፣ ልክ ኢየሱስ ላይ አድርገውት እንደነበረው በአገልጋዩ ይስቃሉ፣ አገልጋዩ ራሱ አጋንንት እንዳለበት ከመናገር ወደኋላ አይሉም። ይህ ሁኔታ እንደሚገጥመው ምንም ጥርጥር ሊገባው አይገባም።

ስለዚህ የአንድ አገልጋይ የመጀመሪያ ድርሻ ፈውስ ማካሄድና አጋንንትን ማስወጣት ሳይሆን ሰዎች በትክክል ስላሉበት ሁኔታ እንዲገነዘቡ ማድረግ ነው። ሰዎች ሕይወታቸው በምን አይነት አጣብቂኝ ውስጥ እንዳለ እንዲያውቁ ሊደረግ ይገባል። እንደዛ ካልሆነ አገልግሎት ተስፋ አስቆራጭ እንደሆነ ሲጠቁም፣ ከዚህ በፊት ከዚህ ትምህርት ቤት ሥነ መለኮት አጥንተው ወደ አገልግሎት የተሰማሩ ከሥራው ክብደት የተነሳ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ገብተዋል። ወይ አገልግሎት ሙሉ ለሙሉ ትተዋል አሊያም ደግሞ ራሳቸውን ጤነኛ አድርገው የሚቆጥሩትን ብቻ እያገለግሉ ነው በማለት ይነግረናል። ነገር ግን ወደ አገልግሎት የተሰማሩበት ዓላማ ጤነኞችን ማገልገል ሳይሆን በሽተኞችን መፈወስ፣ በሽተኞችን ብቻ ሳይሆን በሽተኛ እንደሆኑ ያላወቁትንም ጭምር እንደሆነ ረስተዋል በማለት ያስገነዝበናል። በእርሱ እይታ ሰዎች በትክክል ስላሉበት ሁኔታ ማንነታቸውን እንዲያውቁ እንዲነቁ ማድረግ

ቀላል አይደለም። ቢሆንም ግን በርግጠኝነት እግዚአብሔር ከተኙበት እንዲነቁ የሚሠራበት የራሱ መንገድ አለው።

ራሳቸውን እንደ ጤነኛ የሚቆጥሩትን፣ ዉጫዊ እና ውስጣዊ የሆነው ነገራቸውን ሁሉ ተረጋግቶ ካለበት በማናጋት ፣ወደ ጨለማና ተስፋ አስቆራጭ ሁኔታ ውስጥ ይከታቸዋል። ተደላድለው የተቀመጡበት መሠረት ለሁለት በመክፈል በትክክል ማን እንደሆኑ ራሳቸውን እንዲያዩ ያደርጋቸዋል። እነርሱ ማን እንደሆኑ የማያውቁ እውራን መሆናቸው ይገለጥላቸዋል። እኛ ግን ሰዎችን እንደዛ ማድረግ አንችልም፣ እኛኑ ራሱ እንደዛ ማድረግ አንችልም። ነገር ግን እግዚአብሔር እኛን ራሱ እንደዚ አይነት ሁኔታ ውስጥ ሲከተን፣ ለምን ዓላማ እንደዛ እንዳደረገ ከተገነዘብን ለተደረገው ነገር ሁለንተናችን ልንከፍት እንችላለን። ጸሐፊው እግዚአብሔር እኛን ወደ ጨለማ እና ተስፋ መቁረጥ የሚከተን ለሌሎች ፈውስ ምክንየት የምንሆን መሳሪያዎች አድርጎ ሊሰራን ነው ይለናል።

ቀጥሎም ይህን መሞከር የአንድ አገልጋይ የመጀመሪያ የሥራ ድርሻ ነው እና ደግሞ ምን አልባትም ከሥራዎቹ እጅግ ከባዱ ሥራ ነው። ነገር ግን አገልጋዩ ለዚህ ፈውስ መሳሪያ የሆነው እርሱ ብቻ እንደሆነ ሊሰማው አይገባም። ሁሉም ሰው ለፈውስ ምክንየት ነው። አንዱ ለሌላው፤ ሌላው ለአንዱ የፈውስ መሳርያ ነው ይላል። ለዚህ ምስክር የሚያደርገው ቀና ብለን ከተመለከትን በየጊዜው ያለ ቤተ ክርስቲያንና ያለ አገልጋይ በሰዎች ሕይወት ውስጥ ፈውስ የመኖሩን እውነታ ነው። ፓል ቲሊች፣ ኢየሱስ ለደቀመዛሙርቱ በሽተኛ የመፈወስ እና አጋንንት የማስወጣት ሀላፊነት የመስጠቱ እውነታ የሚያሳየው፣ ይህን ነገር የማድረግ ልዩ ችሎታና መብት ለአገልጋይ መሰጠቱን አይደለም። እያንዳንዱ ክርስቲያን የፈውስና አጋንንትን የማስወጣት ኀላፊነት ተሰጥቶታል። ስለዚህም እያንዳንዱ ክርስቲያን ከሌላው ክርስቲያን ጋር ወይንም አንድ ሰው ከሌላ ሰው ጋር በሚያሳልፈው የግንኙነት ወቅት ይህ ስጦታ በውስጡ እንዳለ ከምር መውሰድና ለፈውስ ምክንየት መሆን ይገባዋል በማለት ይሞግታል። እያንዳንዱ ሰው ለሌላኛው ሰዉ ክህነታዊ ኀላፊነትን እንዳለበት ማወቅና ክህነታዊ ኀላፊነቱን መወጣት የግድ ይለዋል። ምክንየቱም ለአገልጋይ ብቻ የተሰጠ ምትሃታዊ የሆነ አገልጋይ ሲኖር ብቻ የሚከሰት የፈውስ ኀይል የለም።

አንድ የቤተ ክርስቲን አገልጋይ በቤተ ክርስቲያን ውስጥ መስበኩ፣ ማስተማሩ እና ቅዱስ ቁርባን ሥርዓት ማካሄዱ ይሄ ኀይል እንዲኖረው አያደርገውም። ነገር ግን በቤተ ክርስቲያን ውስጥ እንዲያገለግል ተመርጦ እንደተቀመጠ አገልጋይ፣ ለ ፈውሰና አጋንንትን ለማስወጣት ለቤተ ክርስትያን

የተሰጠውን ኀይል ወክሎ ይቆማል።

ወንጌል ለመጀመሪያ ጊዜ በተሰበከበት በሐዋርያት ዘመን፥ አጋንንትን ማስወጣት እና በሽተኛ መፈወስ ይታይ የነበረ ወሳኝ ክስተት ነበር። በኛ ዘመን አስፈላጊነቱ እምብዛም የሆነውና የጠፋው ለምን ይሆን? እኔ እንደማምነው ይላል ፐል ቴሊች፥ ፈውስ እና አጋንንትን ማስወጣት የሚለውን ቃል በተሳሳተ መንገድ በመረዳታችን ነው። አሁን ለእኛ ፈውስ ማለት በየድንኳኑ እና አዳራሽ ወስጥ "ከመቅፅበት ከበሽታ መዳን እየተባለ" የሚካሄደውን የማጂክ ኀይል የሚመስል ፈውስን ነው። በእርግጥ እንደዚህ ዓይነት ነገሮች ይከሰታሉ። ከመቅጽበት ሰዎች ይፈወሳሉ። እዚህና በመላው ዓለም መሰል ነገሮች ይከሰታሉ። እንደዚህ አይነት ክስተቶች አሉ፤ በክርስትያኖች መካከልም ይፈጸማል። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን እንደዚህ አይነት ነገሮችን ማካሄድ የቤተ ክርስትያን እና የአገልጋዮች ድርሻ አይመስለኝም የሚል ስሜት ሊሰማት መቻሉ ትክክል ነው። ቤተ ክርስቲያን ፈውስ የምታከፋፍል፥ የኢየሱስ ስም ደግሞ የሆነ በሽታ ለመፈወስ የሚውል ፎርሙላ አድርጎ ማቅረብ ልክ አይደለም። ይሄ ድርጊት ክርስቶስን ለከንቱ ዓላማ መጠቀም ነው ይለናል። ያም ቢሆን በመግቢያችን የጠቀሥነው የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል፥ ለሁሉም ጊዜ የሚሰራ ቃል ነው። ቃሉ ክርስቶስ እንደ ክርስቶስ ማን እንደሆነ የምንረዳበት፣ የምናውቅበት ቃል ነው። በሽተኞችን መፈወስ እና አጋንንትን ማስውጣት የሚለው ቃል፥ በኢየሱስ ክርስቶስ ስም ውስጥ ያለዉን ኑሮአችንን፣ አዕምሯችንን እና አካላችንን የተቆጣጠሩትን የአጋንንት ሐይላት ድል የሚነሳ ኀይል እንዳለ የሚያሳይ ቃል ነው።

እኔ እንደማምነው ይላል ፐል ቴሊች፥ የክርስቶስን ወንጌል መልእክት ለሌሎች ለማድረስ ከምንጠቀምባቸው የተለያዩ መንገዶች በተሻለ፥ ይህ መንገድ በዘመናችን ያሉ ሰዎችን ለመድረስ እጅግ ውጤታማ የሚያደርግ መንገድ ነው። በዚህ መንገድ የምሥራቹን ቃል በቀላሉ ሊረዱት ይችላሉ። በአለማችን ውስጥ ባሉ በእያንዳንዱ ሀገር ውስጥ፥ ባለፋት ክፍለ ዘመናት በነበሩ ሰዎች መሀል ታይቶና ተሰምቶ ባልነበረ ሁኔታ በዚህ ዘመን እኩይ፣ የክፉ ኀይል ስለመኖሩ ከፍተኛ የሆነ ግንዛቤ አለ። ለምሳሌ ይላል ፐል ቴሊች ዘመናችንን ጠቅለል አድርገን እንመልከት "በሽተኞች እንጂ ጤነኞች ባለ መድኀኒት አያስፈልጋቸውም የሚለውን የኢየሱስ ክርስቶስን ምፀታዊ ንግግር በዛ ዘመን ለሆኑ ቡድኖች የዋለ ቃል ነበር፥ አሁን ግን ይህ የቃል የማይመለከተው ጤነኝነት የሚሰማው፥ ነገር ግንበሽተኛ ያልሆነ በእኛ ዘመን የለም በማለት ይሞግታል። ይህንን መልዕክት የሚቃወሙ ቁጥራቸው የበዛ

መሆኑ እንዳለ ሆኖ፥ እንደታመምን፤ ሁለንተናችን ጤነኛ እንዳልሆነ እናውቃለን። የእኛን ጨምሮ፥ የዘመን ተጋሪዎቻችን መልክት ዋና ማጠንጠኛ እና በጉባኤያችን እና ከጉባዔዎቻችን ውጭ ባሉ በብዙዎች በጉጉት የሚጠበቀው መልዕክት የፈውስ ኀይል እንዳለ የሚያውጀው የምሥራቹ ቃል ነው።

የፈውስ አገልግሎት፥ የፈውስ አገልጋይ ነኝ የሚለውን ሰው፥ የሕይወትን ተፈጥሮ እና የሰው ልጆች ያሉበትን ሁኔታ የመረዳት፥ ጥልቅ እይታ ያለው እንዲሆን ግድ ይለዋል። ብዙ ጊዜ ሰዎች ትዕግስታቸው እንደ ተሟጠጠ በሚያሳብቅ ሁኔታ ውስጥ ሆነው “በእግዚአብሔር አሠራር ውስጥ በሽታችን ፈውስ ካለው፥ ቀድሞውን በሕላዌ እና ግኡዝ በሆነው ዓለም ውስጥ፥ እግዚአብሔር በሽታን ለምን አስቀመጠ ብለው ይጠይቃሉ። በፖል ቲሊች እይታ ይህ ጥያቄ ተፈጥሮአዊ ጥያቄ ነው። ግን ደግሞ ለብዙዎቻችን ከእምነት ማሰናከያ የሆነ ጥያቄም እንደሆነ ይቀበላል። በኋላም ይህ ጥያቄ እግዚአብሄር በአበጀው ዓለም ውስጥ “የዕኩይ መኖር እንቆቅልሽ” ጋር ፊትለፊት እንድንላተም ያደርገናል። ይህም በመሆኑ ይለናል ፖል ትሊች፥ ከሌሎች ጥያቄዎች በበለጠ ዘወትር ይህንን ጥያቄ ለመመለስ የራሳችንን ጥረት ማድረግ ይጠበቅብናል። እና ሚስጥር ነው በሚል ከለላ ይህንን ጥያቄ ከፊታችን ዞር ማድረግ በፍጹም አይገባም። በርግጥ ሚስጥር የሆነ ነገር አለ። እኛ የማንደርስበት መለኮታዊ የሆነ ሚስጥር አለ። በዛ ላይ ደግሞ አሁንም እኩይ ምንድነው ለሚለው፥ ሙሉ መልስ እንደሌለ እና ዕኩይ ሚስጥር መሆኑ የማይካድ እውነታ ነው በማለት ያስቀምጣል።

በፖል ቲሊች ሌሎች ሰራዎች ውስጥ በተደጋጋሚ እንደምናገኘው በዚህ ሥራ ውስጥም የአንድን ነገር ውስብስብ ገጽታዉን እንድንረዳ መንገዶችን ያሳየናል። እናም በእርሱ ሐሳብ መሠረት መብራራትና መነገር የሚቻለውን ማብራራት እንድንችል፥ ሚስጥር የሆነውን ደግሞ በሚስጥራዊነቱ ቦታ በተገቢዉ ለማስቀመጥ ጥልቅ እይታ ያላቸው ሰዎች ሆኖ የመገኘቱ ግዴታ እኛ ላይ የወደቀ ነው። ምክያቱም እኩይ በመለኮት ሥርዓት ውስጥ ሚስጥር ብቻ ሳይሆን የተገለጠም ነገር ነው። ራሱ የእኩይ መኖር ሕይወት ታላቅነትንና አደጋንም አካቶ የያዘ መሆኑን የሚገልጽ ነገር ነው። ህመም ሊያገኘው የሚችለው፥ ህመም ሊያገኘው ከማይችለው በብዙ ነገር የተሻለ ነው። ጥፋትም ልማትም የማይካሄድበት ሕይወት ባለበት የቀረ ይሆናል። ሊታመም እና ሊጎዳ የማይችል በውስጡ ለውጥ እንዳይካሄድ በማንነቱ ዉስጥ አቅም የለም። ምንም እንኳን ኋላ ነፃነቱ ወደ ባርነት ቢቀየርም፥ ቀድሞ ነፃነት የነበረው ብቻ ራሱን ለአጋንንታዊ ኋይል ማስገዛት ይችላል። የነፃነት ስጦታ ለባርነት

ታልፎ የመሰጠት አደጋንም በውስጡ ይዟል።

የተትረፈረፈ ሕይወት ስህመም የመዳረግ አደጋንም አቅፏል። የሰው ሕይወት የተትረፈረፈ ነው፥ መቋጫ የሌለው ውስብስብ ነው፣ እና ለአቅሙም ገደብ የለውም። ይህ ማንነት ድህነት ባጎሳቆለው ሰው ውስጥ እንኳን አለ። የሰው ልጅ ሕይወት ለበሽታ የተጋለጠ ነው። ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ በአንድ ሰው ሕይወት፥ ሁልጊዜ ባለበት ሆኖ በሕብረት ሊያዝ የሚገባው፥ ወደ ተለያየ አቅጣጫ የሚሄድ እና እርስ በርስ የሚጋጭ ፍላጎት አለ። ጤንነት ማለት በአካላዊ ወይም በአምሮአዊ ወይም በመንፈሳዊ ሕይወታችን ውስጥ የተዘበራረቀ የማይታረቅ ነገር አለመኖር ሳይሆን፥ ችግሮች እንዳሉ ሆነው ሁለንተናችን እርስበርስ ተያይዞ እንዲሰራ የሚያደርግ ኃይል አለመኖር ነው። ፈውስ ማለት ሁለንተናችን ተበታትኖ ከነበረበት እንደገና በአንድነት ለመሥራት ሲዋሃድ ማለት ነው። “በሽተኞችን ፈውሱ” ማለት ምን ማለት ነው ለሚለው ፖል ቲሊች ሲመልስ ከውስጣቸው የጠፋውን የሁለንተና ውህደት እንደገና መልሰው እንዲያገኙ ማገዝ ነው ይላል። ነገር ግን አንድ አገልጋይ ይህንን በሚያደርግበት ጊዜ፥ በራሳቸው ፈቃድና ስምምነት እንኳን ቢሆን፥ ሰዎችን ከሕይወት መትረፍረፍ በማጉደል እና ወደ ጉስቁልና ሕይወት በመጨመር መሆን የለበትም። በፖል ቲሊች አስተሳሰብ የሰው ልጅ ከመትረፍረፍ ሕይወት ሲጎድልና ወደ ጉስቁልና ሲወረውር ማለት፥ እንደ ሰው ማለፍ ከተገባው መንገድ ሲያፈግፈግ ማለት ነው። ማግኘትና ማጣት፣ ደስታና ሐዘን፣ በእምነት መሆንና በጥርጣሪ ውስጥ ማለፍ፣ መበርታት እና መድከምን ተጋፍጦ የማያልፍ ሰው መሆን ማለት ነው። አገልጋይ ፈውስ ሆነ ማለት የሚችለው በሽተኛው ለዚህ ተጋድሎ የበቃ እንዲሆን ካደረገው ብቻ ነው።

በሁለንተናችን ወስጥ ለበሽታ የተጋለጡ ብዙ ክፍሎች አሉ። ይህ ለሁላችንም ግልፅ ነው። ከዚህም የተነሳ በብዙ ሰው ውስጥ በህመም ላለመጠቃት፥ ቢቻል ለበሽታ የተጋለጠውን ነገር ሁሉ ቆርጦ ከላያችን ላይ መጣል የሚመኝ በራሱ በሽተኛ የሆነ ፍላጎት አለን። በበሽታ ፈርሃት የታመሙ በጣም ብዙ ሰዎች ማየት እንችላለን። ለዚህ መፍትሄ ብሎ ፖል ቲሊች ያቀረበው ኑሮዬ ይበቃኛል ማለት፥ በሁሉ ነገር ካለን ተሳትፎ መለስ በማለት በሆነ ያህል መጠን ዝቅ ያለ ሕይወት መኖር ጥሩ ነው የሚል ነው። አስፈላጊ ነው የሚል ነው። እንግዲህ ሁሉም በረከት እና ነጻነት፥ የተትረፈረፈ ሕይወት ውስጥ ያለውን ነገር ሁሉ ማግኘት፤ በረከት እርግማንን፣ ነፃነት ባርነትን፣ መትረፍረፍ መጉደልን፣ ማግኘት ማጣትን ይዞ የመምጣት አደጋ በውስጡ ስላለ፥ አንዳንዱን በበጎ ነገር መተው ግዴታ ነው። እንግዲህ በፖል ቲሊች አስተሳሰብ

ውስጥ በሆነ ያህል መጠን ዝቅ ያለ የሕይወት አኗኗር ለመመስረት አንዳንድ ጊዜ የሕይወትን ባለጠግነት መቀነስ አስፈላጊም ነው። ነገር ግን ይላል ፖል ቲሊች፥ ይሄ በራሱ ጤንነት አደለም። ክፉ ነገር ፈርቶ መልካሙን ነገር መተው አይደገፍም።

እንዲህ ዓይነቱ ነገር በአሁን ዘመን የተስፋፋ የአእምሮ በሽታ ነው። ነገር ግን ክፉ ነገርን ፈርቶ መልካም ነገርን ለመያዝ ከመዘርጋት መተው ወደ ትክክለኛ ነገር፣ ወደ ጤነኛነት የሚቀየረው፥ የተቆጠበ ሕይወት ለመኖር ብለን ያጣነውን ነገር ከፍ ባለ ደረጃ የምናገኘው ከሆነ ነው። መተዋችን ለምናገኘው ሌላ ሕይወት መሆን አለበት። ምናልባትም እጅግ በጣም ከፍ ላለ ማግኘት። ይህ በጣም ከፍ ያለዉ ደረጃ ከእግዚአብሔር ጋር ያለን ሕይወት ነው።

ፖል ትሊክ "ወደ ሕይወት ድሃነት ውስጥ መውረድ ፈውስ አይደለም። ነገር ግን የሕይወት መትረፍረፍ ሲሆን፥ አብሮ የሚመጣ የግጭት፣ የበሽታ እና የአጋንንታዊ እሥራት አደጋ አለ።" ይልና ወደ ተማሪዎቹ ዞር ብሎ ምን ማለቱ እንደሆነ ሲያብራራ። "በዚህ መረዳት ላይ በመደገፍ፥ አንድ በጣም አስፈላጊ የሆነ ምሳሌ እንመልከት፥ ለናንተ በጣም ዋነኛ የሆነ ነገር በርግጠኝነት በሽተኞችን እንደትፈውሱ እና አጋንንትን እንድታስወጡ የላከቻችሁ ቤተ ክርስቲያን ነች። ስለዚህ ስለላከቻችሁ ቤተ ክርስቲያን እንነጋገር። የብዙ ቤተ ክርስቲያን፣ አብያተ ክርስቲያናት እና ጉባኤዎች ችግር ሊሆን የሚችለው፥ በሽታን ወይንም ችግርን ወይንም ውጥንቅጥን ለመሸሽ የሚሞክሩት እነዚህን ችግሮች የሚያመጣውን ነገር ቆርጦ በመጣል ነው።" ይልና ነገር ግን ይህንን ችግር የሚያመጣው ያው ነገር የሕይወትን ታላቅነት የሚያፈራ ነው በማለት ይደመድማል። ጤንነት ማለት የችግር አለመኖር አይደለም የሚለውን ለማስረገጥ ሲያስረዳም "አደጋ መጋበዝ የምትፈራ፣ ችግር፣ ህመም ወደ ውስጧ እንዳይገባ ፈተና የምትሸሽ ቤተ ክርስቲያን፣ አጋንንታዊ ተፅዕኖ እንኳን ቢሆን በመካከሏ እንዲገኝ ፈቅዳ እርሱን መጋፈጥ የምትሸሽ ቤተ ክርስቲያን፣ በሽተኛን የመፈወስ እና አጋንንትን የማውጣት አቅም የላትም።

ሁሉ ነገር አልጋ ባልጋ የሆነላት፣ ዘና ያለች፣ እድገቷም እንደ ኤሊ ቀርፋፋ በሆነች ቤተ ክርስቲያን የሚኮራ እያንዳንዱ አገልጋይ፥ በዚህች ቤተ ክርስቲያን ያሉ ምዕመናን ጤነኞች እንዳልሆኑ እንዲያውቁ ማድረጉን እና በሽታቸውን ካወቁ ወዲያ፥ የመፈወሳቸውንም እውነታ ለመቀበል ድፍረትን እንዳስታጠቃቸው ማድረግ አለማድረጉን መጠየቅ አለበት። ይልና እርሱ በነበረበት ዘመን በሰው ልጆች የመንፈሳዊ ሕይወት እና እውቀት እድገት ላይ ከፍተኛ የሆነ መነቃቃት የፈጠሩ ከቤተ ክርስቲያን አጥር ውጪ የነበሩ ሰዎች መሆናቸውን በማመልከት፥ "በሁሉም

አቅጣጫ ባለ የሰው ልጆች መንፈሳዊ ሕይወት ጋር በተገናኘ የታየ ታላላቅ ሥራዎች እና ዕይታዎች ያለማቋረጥ የዳበሩት እና እየዳበሩ ያሉት ከቤተ ክርስቲያን አጥር ውጪ ለምን እንደሆነ መጠየቅ አለበት” ብሎ የቤተ ክርስቲያን ተቀጣሪ አገልጋዮችን ይሞግታል። መለስ ብሎ ደግሞ በጊዜው ይሄን ዲስኮርስ ሲያደምጡ ለነበሩት፥ “የባህል እድገት በሚፀባረቅባቸው የፈጠራ ሥራዎች እና ትዕይንቶች ውስጥ እንደምንመለከተው፥ በተለይ ካለፋት አስር ዓመታት ጀምሮ ባለው ጊዜ፥ የሰው ልጅ ፈውስ የሚሻበት፥ የሚታይ እና የማይታይ በሽታ እንዳለበት ያለው ግንዛቤ ትልቅ እመርታ አሳይቷል በማለት ይናገራል።

አንድ አዕምሮ ሰቅዞ የሚይዝ ጥያቄ ደግሞ ያቀርባል “እነዚህ ሰዎች ማለትም ሰዎች በአጋንንት እሥራት ውስጥ እንዳሉ ያዩ እና በተለያዩ የጥበብ እና የባህል ሥራዎች ውስጥ ያንን ሃቅ የሚንፀባርቁ፥ ከእሥራት ለመፈታት ወደ ቤተ ክርስትያን፣ ወደ እናንተ ወደ አገልጋዮች የማያዩት ቀድሞ በአዕምሮአቸው ውስጥ ባስቀመጡት ለቤተ ክርስቲያን እና ለአግልጋይ ባለቸው ጭፍን ጥላቻ ምክንያት ነውን? ወይስ ቤተ ክርስትያን እራሷ በውስጧ የፍውስ ኋይል እንደሌላት እንደደከመች አይተው ነው?”

ሌላው ከፖል ትሊች ዲስኮርስ ውስጥ የምናገኘው ሙግት “ኢየሱስ ደቀ መዛሙርቱን በሽታኛን እንዲፈውሱና አጋንንትን እንዲያስወጡ ሲልካቸው በአካል ሥጋ፣ በአዕምሮ እና በመንፈሳዊ ህመም መካከል ልዩነት አላስቀመጠም።” የሚለውን ነው። “ነገር ግን እያንዳንዱን የወንጌል ገፆች እየገለጥን ብንመለከት” ይላል “ አብዛኛው የመጽሐፍ ቅዱስ ታሪኮች የሚያሳዩት፥ ኢየሱስ አንደኛው በሽታ ከሌላኛው በሽታ ጋር፥ የሥጋ በሽታ ከመንፈሳዊ በሽታ ጋር፥ እጅግ የተቆራኘ እንደሆነ ለማሳየት ሲጥር ያሳዩናል።” እና እኛም ይላል ፓል ቲሊች “በወንጌላት ውስጥ የምናገኛቸው ታሪኮች የሚያሳዩን የአካል ሥጋ ህመም፣ ከአዕምሮ እና መንፈሳዊ አካል ጋር፤ የሌላው ክፍል ከሌላኛው ጋር፥ እርስ በርስ የተሳሰረ እንደሆነ ነው።” እናም መጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ኢየሱስ ፈውስ ሲል፣ ነፃ መውጣትን ሲሰብክ አንድ የሆነ የተወሰነ የሰው አካል ፈውስ ማለቱ ሳይሆን፥ የሰው ሁለንተና ማለቱ ነው።

ፖል ቲሊች “ከቀደሙት ትውልዶች በተሻለ አሁን ባለንበት ዘመን ይህ የሰው ልጅ ሁለንተና እርስ በርስ የተቆራኘ እንደሆነ ማየት ችለናል” ይልና ቀጠል በማድረግ “ይህ ታላቅ ስጦታ ነው።” ካለ በኋላ፣ ይሰሙት ለነበሩ ተመራቂ ተማሪዎች “ብዘዎቻችሁ ደግሞ ይህን ስጦታ ለማካፈል ብዙ ዕድል እና አጋጣሚዎችን አግኝታችኋል። ከሁሉም በላይ የምሥራቹን ቃል እውነት እርሱም ሕግ እና ትዕዛዝ

እንደማይፈውስ ነገር ግን የህመምተኛውን ህመም እንደሚያባብስ ተምራችኋል። የሚያድነው የፈውስ ኀይል ስም ምን እንደሆነ ተምራችኋል። የሚያድነው የፈውስ ኀይል ስም ፀጋ "እንደሆነ አውቃችኋል ይላቸዋል። ቀጠል በማድረግም የፀጋን አስተምህሮ እሳቤ ድንበር በማስፋት በክርስትና እምነት ተከታዮች ዘንድ ብዙም ተቀባይነት የሌለው ወይም የማይነገር "ይሄ ፀጋ ሁሉም ሐኪም፣ ከቅጠላቅጠል መድሃኒት ይቀምሙ የነበሩ የጥንት ባሕላዊ ሐኪሞችም ጭምር የተደገፉበት የተፈጥሮ ፀጋ ሊሆን ይችላል፣ ይህ ፀጋ በባህል፣ በቅርስ እና በጋራ ምልክቶች የሰው ልጆች ሕይወት ደግፎ ያቆመ የታሪክ ፀጋ ይሆናል። ይህ ፀጋ በይቅርታ መልዕክት እና በአዳዲስ ክስተቶች የአጋንንትን ኀይል ድል ያደረገ የመገለጥ ፀጋ ሊሆን ይችላል።" የሚል ሐሳብ ያሰፍራል። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አንድነቱን፣ ጤናን፣ ሰላምን እና በጎ ነገር የመጡትን ሁሉ በዚህ ፀጋ ውስጥ ከቶ እንመለከታለን።

የእርሱን ሙግት ለማጠናከር ተማሪዎቹ በትምህርት ላይ በነበሩ ጊዜ ያገኙት እውቀት ዞር ብለው እንዲያዩ፣ ዞር ብለው ካዩ ደግሞ መልሱን እንደሚያገኙ ሲያሳስብ እንዲህ ይላል "ሌላ ደግሞ የአካለ ሥጋ የሚመስል በሽታ ስሩ የአዕምሮ ሊሆን ይችላል፣ የግለሰብ የሚመሽል በሽታ በተመሳሳይ መንገድ ማሕበረሰባዊ ሊሆን ይችላል። ይህንን ደግሞ ተምራችኋል። ግለሰቦችን ከበሽታ ከመፈወሳችሁ በፊት፣ አስቀድማችሁ ለበሽታቸው ከፍተኛ አስተዋጽኦ ካበረከተው ከያዛቸው ማሕበረሰባዊ አጋንንት ነፃ ሳታወጧቸው ግለሰቦቹን ካለባቸው በሽታ ልትፈውሷቸው በጭራሽ እንደማትችሉ ተምራችኋል። ከዚህ ውጪ፣ አካላዊም ሆነ አእምሯዊ፣ ግለሰባዊ እና ማሕበራዊ ህመም፣ የሰው መንፈስ ከመለኮታዊ መንፈስ የመነጠሉ ውጤት እንደሆነ እና የሰው ልጅ መንፈስ ከመለኮት መንፈስ ጋር ሳይስተሳሰር፣ ሕብረት ሳያደርግ የትኛውም ህመም እንደማይፈወስ፣ የትኛውም አይነት አጋንንት እንደማይወጣ ይህን ተጨባጭ እውነታ እንዳለ ግንዛቤ ጨብጣችኋል። ለዚህ ምክንያት ብቻ ይህን ካወቃችሁ ብቻ ፈውስ እንዳለ ለሚያበስረው መልዕክት አገልጋዮች ሆናችኋል።" በማለት ምክሩን ለግሷል።

ጨመር አድርጎም "ሐኪሞች መሆን አይጠበቅባችሁም፣ ሳይኮቴራፒስት መሆን አይጠበቅባችሁም፣ የፖለቲካ ለውጥ አራማጆች መሆን አይጠበቅባችሁም። ነገር ግን ፈውስ እና አጋንንትን የሚያሸንፍ ኀይል የሆነውን በክርስቶስ መልዕክት ውስጥ የተንፀባረቀውን የይቅርታ እና መርቆ የከፈተውን የአዲስ መንገድ እውነታ ማወጅ እና ወክላችሁ መቆም ይጠበቅባችኋል።" የሚለውን በማስገንዘብ "ሌሎች የፈውስ መንገዶችን ይኖሩ ይሆን ብሎ ነቅቶ

ማየትም ግድ ነው።" የሚል ምክሩን ይለግሰና፥ በእኔ አገልግሎት ወይም በእኔ ሐይማኖት ብቻ ካልሆነ ፈውስ የለም ከሚል አቋም ይልቅ፥ ሰዎች ፈውስና ሰላም ያገኙበት ከእኛ ውጪ የሆነ ነገር ካለ፥ መተባበር እንደሚገባ ያሳስብና ነገር ግን "የምትወክሉትን የሚተካ መሆን የለበትም። የምትወክሉትን የተጠራችሁበትን ጥሪ በሌላ መተካት የለባችሁም።" የሚለውን አፅንኦት እንዲሰጡት ያሳስባል።

አዳማጮቹ የነበሩት የሥነ መለኮት ተማሪዎች ወደ አገልግሎት ሲሰማሩ ሊረሱት የማይገባ ነገር እንዳለ ለማስገንዘብ "የክርስትናን መልእክት መወከል ትችላላችሁ?" በማለት ይጠይቅና፥ "ምናልባት ይህ ጥያቄ በዚህ ሰዓት ውስጥ የእናንተ አሳሳቢ ጥያቄ ሊሆን ይችላል" በማለት አዕምሮአቸውን ለማንበብ ይሞክራል። ይህን ጥያቄ ያቀረበበት ዋና ምክንያት፥ ሁሉም አገልጋይ በየዘመናቱ የሚጠይቀውን ጥያቄ እንዲጠይቁ ለማበረታታት ነበር "ደግሞ እኛ ሳንፈወስ ሌላውን መፈወስ እንችላለን ወይ ብላችሁ ልትጠይቁኝ ትፈልጋላችሁ? "በማለት ሊጠይቁት እንደሚፈልጉ እርግጠኝነት ስለተሰማው መልሱን "አዎ! ትችላላችሁ!ደቀመዛሙርትም ሆኑ እናንተ "መልካም፣ አሁን እኛ ተፈውሰናል ! በሉ ሌሎችን ደግሞ እንፈውስ!" ማለት ፍፁም አትችሉም።" በማለት ይመልሳል። እናም ይላል ፓል ቲሊች "ስለራሱ እንደዚህ የሚያስብ ካለ እርሱ ሌሎችን ለመፈወስ የበቃ አይደለም። ጤነኛ ስለሆንኩ ህመምተኞችን እፈውሳለሁ ብሎ ካሰበ ከጅምሩም ራሱን ከሌላው ነጥሏል። ለፈውስ መሳሪያ ሊሆን አይችልም።" እኛ ይላል "አንዳችን ለሌላችን ፈውስ የምንሆነው ሁላችንም ስላልተፈወስን ነው።" ስለዚህ "በችግር ውስጥ በህመም ላሉ ስታማክሯቸው እነርሱ ያሉበት አስቸጋሪ እና አጣብቂኝ ሁኔታ ውስጥ እናንተም እንዳላችሁ አሳዩ።" በማለት የአገልጋይ መሆን ድርሻ የቱ ጋ እንዳለ አሳይቷል።

"እና እንዲህ ብላችሁ ልትጠይቁኝ ትችላላችሁ፦ እኛው ራሳችን ከአጋንንት ሃይላት ጥቃት ነፃ ሳንወጣ ከሌሎች ሰዎች አጋንንትን ማስወጣት እንችላለንን?" የሚል ጥያቄ ካቀረበ በኋላ፥ አሁንም መልሱን ራሱ ይሰጣል። "አዎን ትችላላችሁ!!" ለዚህ ምክንያት የሚለው ደግሞ "በእናንተ ውስጥ አጋንንት የመሥራታቸውን እርሾ፥ እናንተም ከጥቃት ያመለጣችሁ ያለመሆናችሁን እስካላወቃችሁ ድረስ በሌሎች ውስጥ ያለውን አጋንንት ልትለዩ አትችሉም። በሌሎችው ውስጥ ካለው አጋንንት ጋር ልትታገሉ አትችሉም። ስሙን ስላወቃችሁ ብቻ ውገያ በማድረግ ያለውን ኀይል ልታዳክሙ አትችሉም።" ይላል። እንግዲህ ፓል ቲልች በሌሎች ሥራዎቹም ላይ እንደምናገኘው፥ የሚጠቀማቸው አንዳንድ ቃላት እና ሐሳቦች ቃል በቃል

የሚወሰዱ ሳይሆኑ፥ አንድ ሰፊ እና ውስብስብ ነገር ለመወከል ጥቅም ላይ የሚውሉ ናቸው። ለምሳሌ እዚህ ቦታ ላይ "በእናንተ ውስጥ አጋንንት የመሥራቱን እርሾ፥ እናንተም ከጥቃት የመለጣችሁ ያለመሆኑን እስካላወቃችሁ ድረስ በሌሎች ውስጥ ያለውን አጋንንት ልትለዩ አትችሉም" ሲል፥ እርሱ አጋንንት እያለ የሚጠራው የእኩይን መኖር ይሁን፤ ወይም ራሱ አጋንንትን (Demonic being) ምንም የምናውቅበት መንገድ የለም። ለእኛ በተመቸን ተርጉመን ከመውሰድ ውጪ። ቀጥለን የምናገኘው ሐሳብ ደግሞ እርሱ "አጋንንት" ሲል ምን ማለቱ ነው የሚለውን የእኛ የቤት ሥራ አድርጎ እንደተወው የሚያሳይ ይመስለኛል። "ሕይወታችሁ የሚንቀሳቀስ፣ ዉጤታማ፣ የሚፈጥር እና የፈውስ ምክንያት የሆነ ሕይወት መሆኑን እስከቀጠለ ድረስ፥ አጋንንት ነፍሳችሁን በጡጫ በመለጋት እና ለሁለት በመሰንጠቅ ባላችሁ እምነት፣ ሥራ እና በሁለንተናችሁ ላይ ጥርጣሬን ያልፈጠሩበት አንዳች የሕይወታችሁ ወቅት የለም። አልያም ይህን በሕይወታችሁ ማድረግ ካልተሳካላቸው ሌላ ነገር በማድረግ ይሳካላቸዋል። አጋንንትን በማስወጣት እና በሽተኞችን በመፈወስ በአገልግሎት ባላችሁ ስኬት፣ በራስ መተማመን እና ትዕቢት በነፍሳችሁ ውስጥ አስርገው በማስገባት ያሳኩታል።" ይለናል።

እንግዲህ በዚህ አጋንታዊ ሥራ፥ ሰው ሆኖ ዋጋ ያልከፈለ እና ያልተጠቃ አናገኝም። ነገር ግን ይህ አጋንንታዊ ጥቃት በእኛ ውስጥ ነው፤ ከውጭ ሆነው ነው ለሚለው ክርክር መፍትሄ ማበጀት የንግግሩ ዓላማ ስላልነበረ ባቀረበው ዲስኮርስ ውስጥ አናገኝም። የፖል ቲልክ ዲስኮርስ ማጠንጠኛ ከበሽታ እና አጋንንታዊ እሥራት ነፃ መውጣት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ማሳየት ስለነበር፥ አጋንንት የለብኝም ወይም በአጋንንት ጥቃት አልደረሰብኝም የሚል ሊኖር እንደማይችል ትዕቢትን እንደምሳሌ መጥቀሱን ይቀጥልና "ኢየሱስ ስለዚህ አይነት ትዕቢት ማስጠንቀቂያ ሲሰጥ "መናፍስት ስለተገዙላችሁ በዚህ ደስ አይበላችሁ፥ ስማችሁ ግን በሰማይ በመጻፉ ደስ ይበላችሁ" ብሏል።" በማለት በአገልግሎት ስኬት ከመጠን በላይ የመደሰትን አደጋ ያሳየናል። ስማችን እንኳን በሰማይ መፃፉ ለእኛ የሚሰጠን "እኔ እኮ" የሚያስብል ነገር እንደሌለ እንዳንዘነጋ፥ "ስማችሁ 'በሰማይ በመጻፉ' ደስ ይበላችሁ ማለት በሕይወት ዘመናችሁ ውስጥ ካስመዘገባችሁት የሕይወት ጥቁር ነገር፣ በላያችሁ ላይ ነቀፋ እያለባችሁም ቢሆን ማለት ነው በማለት ስማችን በሕይወት መዝገብ መፃፉ እንኳን አስመክቶን ለአጋንንት ጥቃት እንዳንጋለጥ ያስጠነቅቀናል። "ሐሳቤን ዋስትና በሚሰጥ ንግግር ልቋጨው።" በሚለው በንግግሩ መጨረሻ ያቀረበውን ሐሳብ፥ ስንመለከት እንዲህ ይላል "በምድር ላይ በሽተኞችን ለመፈወስ እና አጋንንትን ለማስወጣት እንደመጠራት ታላቅ ጥሪ የለም። ለዚህ

ሥራ በመጠራታችሁ ሐሴት አድርጉ!! ከዚህ አገልግሎት ጋር ተያይዞ በሚመጣው ሽክም ምክንያት ድባቴ ውስጥ አትግቡ። በዚህ ብቻ ሳይሆን ከእሥራት ነፃ ለመውጣት ከማይፈልጉት ጋር በምታደርጉት ምልልስ ባለው ሽክም ድባቴ ውስጥ አትግቡ። በጥሪያችሁ ደስ ይበላችሁ። የእናንተው ህመም እንዳለ ሆኖ፣ በእናንተ ውስጥ እና በቤተ ክርስቲያናችሁ ውስጥ ከአጋንንት ጋር ያለው ተጋድሎ መበርታቱ እንዳለ ሆኖ በጨረፍታም ቢሆን ሊፈውስ የሚችለው ምን እንደሆነ አይታችኋል።

በእርሱ እግዚያብሔር በአጋንንትና በበሽታ ላይ ያለውን ኀይል የገለጠበት፣ እርሱ በዓለም ያለው የፈውስ ኀይል የሚወከልበት፣ ዓለምን ደግፎ ያቆማት እና ወደ እግዚያብሔር ከፍ የሚደርጋት በእርሱ እንደሆነ አይታችኋል።” እናም “የእርሱ መልዕክተኞች ስለሆናችሁ ደስ ይበላችሁ! በምትሄዱበት ሁሉ ይህን ደስታ ሰንቃችሁ ሂዱ!!”

# 9. ብቸኛ መሆን እና ለብቻ መሆን!

*“ሕዘቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።”*

*ማቴዎስ 23፡14*

## 1.

በመጽሐፍ ተፅፎ እንደምናገኘው፥ “ብቻውን በዚያ ነበረ።” ይላል። እኛም ብቸኞች ነን። የሰው ልጅ ከፍጥረቱ “ብቸኛ” ነው። ሰው ብቸኛ የሆነው ሰው በመሆኑ ነው። በርግጥ በብዙም በጥቂቱም ፍጥረት ሁሉ “ብቸኛ” ነው። ወደ ሰማይ አንጋጠን ስንመለከት፣ እጅብ ብለው ሲጓዙ የምናያቸው ከዋክብት፣ ተሸካክመው እና ተደራርበው እየተጓዙ ቢመስለንም እንኳን፣ እያንዳንዱ ኮከብ ራሱን ችሎ፤ በድቅድቁ ጨለማ ውስጥ ብቻውን ይጓዛል። እያንዳንዱ ኮከብ እጅን በአፍ በሚያስጭን ጥልቅ “ብቸኛ” ነት ቋሚል። እንስሳትን እንመልከት፥ ወንድ እና ሴት፣ በቤተሰብ እና በቡድን ሆነው ተሰባስበው ይኖራሉ። ክፉንም ደጉንም በጋራ ያሳልፋሉ። እውነታው ግን እያንዳንዱ ብቸኛ ነው። እያንዳንዱ እንስሳ የእኔ በሚለው አካለ ሥጋ ተወስኖ፣ በዚያ ውስንነት፣ መጠን እና አቅም፥ ለራሱ ይኖራል፣ ለራሱ ይታገላል፤ እና ለራሱ ይሞታል። ብቸኛ! በቡድን፣ በመንጋ እና በቤተሰብ ውስጥ ቢኖሩም፥ ነገር ግን ሁሉም በራሱ የቆመ ደግሞም “ብቸኛ” ነው። በሕይወት መኖር ማለት በአካለ ሥጋ ውስጥ መኖር ማለት ነው። በአካለ ሥጋ ውስጥ መኖር ማለት፥ ከሌላው አካል ተለይቶ መኖር ማለት ነው። ተለይቶ መኖር ማለት ደግሞ፥ “ብቸኛ” መሆን ማለት ነው።

ይህ እውነታ ለሁሉም ፍጥረት ይሰራል። ነገር ግን ከሌሎች ፍጥረታት በተለየ በተጨባጭ “ብቸኛ” ነው የምንለው የሰውን ልጅ ነው። የሰው ልጅ ብቸኝነት የተለየ ነው። ሰው “ብቸኛ” ብቻ አይደለም፤ ነገር ግን “ብቸኛ” መሆኑንም ያውቃል። “ብቸኛ” መሆኑን ስለሚያውቅ የብቸኝነት ጉዳይን ያብሰለስላል።

ለምን "ብቸኛ" እንደሆነ ይጠይቃል፡፡ "ብቸኛ" ነቱን እንዴት እንደሚያሸንፍ የውጠነጥናል፡፡ ይመረምራል፤ መንገድ ይፈልጋል፡፡ አዎ! ለሰው ልጅ ብቸኝነት ሊሸከመው የማይችለው ቀንበር ነው፡፡ ቢሆንም ከብቸኝነቱ ማምለጥ አይችልም፡፡ እግዚአብሔር እንኳን ይህን የብቸኝነት ቀንበር ከሰው ልጅ ማንሳት ፍቃዱ አይደለም፡፡ ብቸኛ መሆን የሰው እጣፈንታ ነው፡፡

ስለ ሰው አፈጣጠር በሚያወሳው የብሉይ ኪዳን ታሪክ ውስጥ፣ "እግዚአብሔር አምላክም አለ፤ ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም" ተብሎ የተፃፈውን እናገኛለን፡፡ እናም እግዚአብሔር ከአዳም አካልን ወስደ ሔዋንን ፈጠረ፡፡ እንገዲህ ይህ ታሪክ የሚያሳየን፣ "ወንዱ እና ሴቷ" መካከል የአካል መለየየት እንዳልነበረ እና በመጀመሪያ አንድ እንደነበሩ ነው፡፡ ከተለያዩ በኋላ ደግሞ፣ አሁን መልሰው "አንድ" መሆን ይፈልጋሉ፡፡ ብቸኝነታቸው እንዳለ ሆኖ አንዱ የሌላው አካል እንደሆነ፣ ሌላኛቸው ደግሞ፣ "የሌላው አካል የእርሱ እንደሆነ" ይተዋወቃሉ፡፡ ምንም እንኳን እንደገና አንድ የመሆን ጥልቅ መሻት ያላቸው ቢሆንም፤ ነገር ግን እርስ በርስ እየተያዩ፣ "እሱ፣ ለእርሷ" ፤ "እርሷ፣ ለእርሱ" "እንግዳ ፍጥረት"፣ የማይመሳሰሉ እና ፍፁም የተለያዩ መሆናቸውን ይገነዘባሉ፡፡ በዚህ ታሪክ፣ እግዚያብሔር ወንዱ እና ሴቷ የማይነጣጠሉና አንድ የሆኑ ብቻ ሳይሆን፣ የተለያዩ እንደሆኑ እንዲያውቁ ሲያደርግ እንመለከታለን፡፡ ለምሳሌ "አትብሉ" የተባሉትን በልተው በተገኙ ጊዜ፣ አንድ የሆኑ ብቻ ሳይሆን "ብቸኛ" እንደሆኑ ያውቁ ዘንድ ሁለቱንም ያናገራቸው በየግል ነው፡፡ አታድርጉ የተባለትን ለምን እንዳደረጉ የጠየቃቸውም ለየ" ብቸኛ"፣ ብቻ ለብቻ በመነጠል ነው፡፡ ላጠፉት ጥፋት፣ እርግማኑን እና ሃፍረቱን የተቀበሉትም ለየብቻ ነው፡፡ የእርሱ ሌላ እርግማን ነው፤ የእርሷ ሌላ እርግማን ነው፡፡ ራሳቸውን ችለው ነው የቆሙት፡፡ ብቸኛ! የሴቷ መፈጠር እግዚአብሔር ያለውን መልካም ያልሆነ የብቸኝነት ሕይወት፣ የብቸኝነት ኑሮ ሙሉ በሙሉ የሚቀይር አይደለም፡፡ ከእርሷም መፈጠር በኋላ አዳም ብቸኛ ነው፡፡ የሴቲቱ መፈጠር፣ ለአዳም ረዳት ቢያስገኝለትም በዋናነት ዘፍጥረት ላይ የሆነው ነገር አንድ ከፍጥረቱ "ብቸኛ" ሆኖ ለተበጀ ሰው፤ ሌላ ከፍጥረቷ "ብቸኛ" ሆኖ የተበጀችን ሰው አጋር አድርጎ የመስጠት ሥራ ነው፡፡ ከእነርሱም አብራክ የሚወጣ ሥጋ ለባሽ ሁሉ በሕይወት ዘመኑ የሚኖረው "ብቸኛ" ሆኖ ነው፡፡

ታሪኩ እንደዚህ ቢሆንም አንዳንድ ጥያቄዎችን ግን ማንሳታችን አይቀርም፡፡ የሄዋን መፈጠር የአዳምን ብቸኝነት የአዳም መፈጠርም፣ የሄዋንን ብቸኝነት አልቀየረም? እግዚያብሔር ለአዳም ረዳት ስለፈጠረለት ለአዳም መልካም

አልሆነም? እግዚአብሔር "ብቸኛ" ለሆነው ሰው፤ ለብቸኝነቱ ፋይዳ የሌላት ሌላ "ብቸኛ" ሰው ነው የጨመረበት፤ ከዚህ የተሻለ ነገር አላደረገም? መጠየቃችንን እንቀጥልና፥ "ወንዱ፥ ከሴቷ"፣ "ሴቷም፥ ከወንዱ"፣ በሚያደርጉት ቁርኝት "ብቸኛ" ነት አይወገድም? መልሱ ይወገዳል የሚል ነው። ምንም ጥርጥር የለውም። ነገር ግን ይህ የሚሆነው እና "ብቸኛ" ነታቸው የሚወገደው፥ በሩካቤ ሥጋ ውህደት ውስጥ በሚሆኑበት ቅፅበት ብቻ ነው። በሩካቤ ሥጋ ወቅት ባለው ጥልቅ የሆነ የፍስሐ ስሜት፥ አንዱ በአንዱ ውስጥ ተውጦ፥ "ብቸኝነት" ለዘላለም ወደሚወገድበት የምናብ ዓለም ውስጥ ስለሚከት፤ ብቸኝነት የተወገደና የተሸነፈ እንዲመስል ያደርጋል። ግን ከዛች ክስተት በኋላ፣ ወሲባዊ እርካታው ካከተመ ወዲያ፣ እንደውም ከዚህ በፊት ተሰምቶ የማያውቅ ጥልቅ ለ" ብቻነት" ውስጥ ይገባል። እንደውም "እኔ" ነታቸው ከራሱ "እኔ" ነት ሲነጠል የ" ብቻነት" ነት ጎርፍ ሲወስድ ምን እንደሚመስል የሚታወቀው፤ የሚሰማው ብቸኛ ወቅት ያን ጊዜ ነው። ወንዱ ከሴቷ፣ ሴቷ ከወንዱ እቅፍ ሲወጡ። እንደውም አንዳንዴ ብቸኝነት እንኳን ሊሸነፍ፣ የተለያዩ መሆናቸው ከመጉላቱ የተነሳ "ምነው ተነስቶ ቢሄድልኝ" የሚያስብል የመጠየፍ ስሜት ውስጥ ይከታቸዋል። ሁለንተናቸውን አሳልፈው ከሰጡ በኋላ፣ መልሰው ደግሞ ነጥቀው ለመውሰድ መፈለግ እና መሻት ውስጥ ይገባሉ። ብቸኝነታቸውን ለመከላከል የሚያደርጉት ጥረት በሐፍረት ስሜት በኩል ራሱን ይገልጣል። "እኔ" ነታቸውን፣ ማለትም አዕምሮ እና አካላቸውን ከፍተው ከሰጡ በኋላ፣ መልሶ ደግሞ ሐፍረት ይሰማቸዋል። ይህ በሁላችንም ሕይወት የሚያልፍ ነው። ልክ አዳም እና ሔዋን ርቃናቸውን መሆናቸውን ባወቁ ጊዜ እንዳደረጉት እኛም እርቃናችንን ለመሸፈን እንሞክራለን። እናም በዛ "ጥልቅና፣ ፍፁም መዋሃድ" ወቅትም እንኳን ቢሆን፣ አይመስልም እንጂ "ብቸኛ" ነት ሳይነካ ባለበት አለ። በምንም ተዓምር አንዱ የሌላውን "ብቸኛ" ነት ማስወገድ አይቻለውም። የሰው የማንነቱ ማዕከል "ብቸኛ" ነት ስለሆነ። ማንም የማንንም ብቸኝነት ድንበር ጥሶ ወደ ውስጥ ዘልቆ አይገባም። ይህ ባይሆን ደግሞ አንዱ የሌላው አይሆንም ነበር፤ እርስ በርስ የሚረዳዳ የሚደጋገፋ አይሆንም ነበር። የሰው ልጅ ማሕበረ ሰብ የሚባለውም አይኖርም ነበር።

ለዚህም ነው እግዚአብሔርም ሰውን ከ" ብቸኛ" ነቱ ነፃ ሊያወጣው ፍቃዱ ያልሆነው። የሰው ታላቅነቱ፣ "ብቸኛ" ነቱ ነው፤ መኖሩ በራሱ ዙሪያ የጠነጠነ መሆኑ ነው። ከሁሉም ነገር ተለይቶ ብቻውን መሆን መቻሉ፣ ሁሉንም ነገር መልሶ በጥልቀት እንዲረዳ አስችሎታል። በምናብ፣ በእይታ እና በአሰላስሎት "ብቸኛ" ሆኖ፣ ሌላውን መቃኘት እና መመርመር በመቻሉ፣ ነገሮችን ማወቅ፣ መውደድ

እና መለወጥ ይችላል። እግዚአብሔር የሰውን ልጅ የምድር ገዢ አደረገው። መልሶ ደግሞ የተለየ እና ለ” ብቸኛ” ነቱም የተተው አድርጎ አበጀው። ስለዚህ ሰው በ” ብቸኛ” ነቱ ምክንያት አምሳለ እግዚአብሔር አለበት። እና ሲጠራውም “አቤት!”፣ “እነሆኝ!”፣ “እዚህ ነኝ!” ሊል የሚችል ፍጡር ነው። ብቸኛ በመሆኑም ጥያቄዎችን መጠየቅ እና መልስ መስጠት፣ እንዲሁም ውሳኔዎች መወሰን ቻለ። “ብቸኛ” በመሆኑም ከበጎ ወይም ከእኩይ ጎን በመሆን የመምረጥ ነፃነት አለው። ነፃ ሰው ማለት፣ በምንም እና በማንም የማይገረሰስ “ብቸኛ” የመሆን ማንነቱን ጠብቆ ያለ ሰው ማለት ነው። ብቸኝነቱን የማያሥነካ! “ብቸኛ” የሆነ፣ ብቻውን የሚቆም ብቻ እኔ ሙሉ ሰው ነኝ ማለት ይችላል። “ብቸኛ” መሆኑን መገንዘቡ ሙሉ ሰው ያደርገዋል። በርግጥ “ብቸኛ” መሆኑን መገንዘቡ፣ መልስ የሌለው ጥያቄ ያበዛበታል። ቢሆንም ብቸኝነት ለሰው ልጅ የታላቅነቱ ቁልፍ፤ ደግሞም ጫንቃውን ያጎበጠ ቀንበር ነው።

# 2.

ብቸኝነት ለሰው ልጅ የትልቅነቱ ቁልፍ፣ ደግሞም ጀርባውን ያጎበጠ ቀንበር እንደሆነ የሚያሳይ ሁለት ሐሳቦችን በቋንቋ ውስጥ እናገኛለን። አንደኛው የብቸኝነትን ህመም ለመግለጥ የምንጠቀመው “ብቸኛ መሆን” የሚለውን ሲሆን፣ በብቸኝነት ውስጥ ያለውን ክብር ለማሳየት ደግሞ የምንጠቀመው “ለብቻ መሆን” የሚለውን ሐሳብ ነው። በርግጥ እነኚህን የብቸኝነት ሁለት ገፅታዎች በዕለት ተዕለት ሕይወታችን አንለይም። ነገር ግን ይህን ልዩነት ያለማቋረጥ እየተገነዘብን መኖር አለብን። ቸልተኝነትን አስወግደን ይህን ልዩነት እየለየን በመኖር ሰው በመሆናችን በሕይወት ውስጥ የሚገጥመንን እንቆቅልሽ በጥልቀት መረዳት አለብን።

በመዝሙረ ዳዊት ምዕራፍ 25 “እኔ ብቻዬንና ችግረኛ ነኝና ፊትህን ወደ እኔ አድርግ ማረኝም።” እንዲህ የሚል ቃል እናነባለን። በዚህ ቦታ መዝሙረኛው ብቸኝነት በሚያመጣው ስቃይ እና ህመም ውስጥ እያለፈ እንደሆነ መመልከት እንችላለን። በርግጥ እርሱ እያለፈ የነበረበት ብቸኝነት ከምን የመነጨ እንደሆነ አናውቅም። ነገር ግን ብቸኝነት ሊከሰትበት የሚችልበትን ዘርፈ ብዙ ምክንያት ማወቅ እንችላልን። ሥጋ የለበስን ሁላችንም በአንድ ወይም በሌላ ምክንያት የሚመጣ ብቸኝነት በሕይወታችን አጋጥሞናል።

ብዙ ጊዜ በሕይወታችን ብቸኛ የመሆን ሁኔታ ውስጥ የምንገባው እና የብቸኝነት በረዶ በላያችን ላይ የሚወርደው በሕይወት መንገድ ላይ ብቸኛ እንደሆንን እንድንረሳ የረዱን ሰዎች በሞት ሲለዩን ወይም እንደበፊቱ አብረውን መሆን የማይችሉበት ሁኔታ በሚፈጠርበት ወቅት ነው። የቅርባችን እና የልባችን የሆኑ የቤተሰብ አባላት፣ የትዳር አጋሮቻችን፣ ልጆቻችን እና ከቤተሰብም በላይ ቅርባችን የሆኑ ሚስጥረኛ ጓደኞቻችን ሲለዩን ብቻ ሳይሆን አይደለም ነገር ግን “ጓደኞቼ እንዴት ያሉ ድንቅ ናቸው!?” እንድንል ያደረጉን ሕብረቶች ውስጥ ያሉ ሰዎች ሲለዩን ነው። በመስርያ ቤት ያፈራነው ቡድን ውስጥ ያሉ ድንቅ ሰዎች፣ በማያቋርጥ ማሕበራዊ ግንኙነት ወቅት ያገኘናቸው ሰዎች፣ እና መንፈሳዊ ሕይወት አብረናቸው ስንካፈል የነበሩ ሰዎች ከእኛ ሲለዩም በሕይወታችን ብቸኛ የመሆን ወቅት ይከሰታል። ብዙ ሰዎች እንዲህ ባለ ሁኔታ ምክንያት ብቸኛ የመሆን የሕይወት አጋጣሚ ሲገጥማቸው ቋሚ እና የማያቋርጥ መከፋት፣ ሆደባሻነት፣ ደስታ ማጣት እና ጥልቅ ድብርት ውስጥ ይገባሉ። በዙሪያችን እና በዓለም ላይ ያሉ ስፍር ቁጥር የሌላቸው የብቸኝነት ስቃይ ውስጥ የመሆን የሕይወት እጣ ፈንታ የወደቀባቸው ሰዎች የዝምታ ጩህት፣

ጩሀታቸውን ለማዳመጥ ፍቅር ግድ ብሎት ጆሮዎቹን የከፈተ ሁሉ ይሰማቸዋል።

እስኪ ደግሞ በመካከላችን በጓደኞቻቸው የተከበቡትን እንመልከት። ከጎረቤቶቻቸው ጋር የጉርብትናን ውብ ሙቀት የሚሞቁትን እንመልከት። በትውልድ ሐገር፣ በምድራቸው ያለ ሰቀቀን ወዲህ ወዲያ የሚሉ፣ በሚያስቀና የፍቅር ሕይወት ሐሴት እየደረጉ ያሉትን እንመልከት። ብቸኛ የመሆን ሁኔታ የማያውቃቸው፣ "ሌላው የሌለው ሁሉ ያላቸው" ን እንመልከት። በሕይወት ደስታ ውስጥ የሚዋኙ ሰዎችን እንመልከት። ከዛም ቀጥለን ይህን ጥያቄ እንጠይቅ፤ እውን እንዲህ ያሉ ሰዎች ከብቸኝነት ሕመም ነጻ ናቸው? ነው ወይስ ብቸኝነታቸው በከበቧቸው ሰዎች ተሸፍኗል? ከእነዚህ በወዳጅ ዘመድ ከተከበቡ፣ ሁሉ ከሞላላቸው ሰዎች፣ አንዱ እኔ ነኝ ብለን ራሳችንን መቁጠር ከቻልን ጥያቄውን በሚከተለው መልክ መመለሳችን ሳይታለም የተፈታ ነው።"በሰዎች በተከበብኩበት ሰዓት እና ደቂቃ ምንም አይነት ብቸኝነት አይሰማኝም፤ ነገር ግን ድንገት፣ ማንም ጎኔ የሌለ፣ ማንም ለእኔ ግድ የሌለው፣ ለራሱ ፍላጎት እንጂ ለእኔ ብሎ የሚፈልገኝ የሌለኝ ብቸኛ የሆንኩ እንደሆንኩ ይገለጥልኛል። ከ" ብቸኛ" ነቴ ጋር "ብቸኛ" መሆኔን ለማስታመም፣ እራሴን ከቡድኑ እነጥላለሁ፤ ፀጥ እላለሁ። ምክንያቱም ውጪዬ በሰዎች ከበባ፣ ውስጤ ደግሞ በብቸኛነት ስሜት እየተናወጠ ከማሳልፍ፤ ውስጤን እና ውጭዬን ማስማማት እፈልጋለሁ" እንላለን። አንዳንድ ሰዎች እንዲህ አይነት ነገሮችን እና የሰዎችን ይህን መሰል የሕይወት ልምምድ ስንሰማ ዘር ብለን "ባክህ ተወው! ዝም ብሎ ነው! እንዲህ አይነት ሰዎች ምንም እንኳን ሁሉ የሞላላቸው ቢሆኑም። የጎደላቸው ነገር የሌለ ቢመስልም። አጠገባቸው ባሉ ሰዎች እና ቡድኖች ሁነኛ ስፍራ እና ተደማጭነት ለማግኘት የሚበቃ ጠንካራ ማንነት የላቸውም። ራሳቸውን ጠንካራ ከማድረግ ይልቅ እኔ "ብቸኛ" ነኝ ብለው ይሸሻሉ። ምንም የጎደላቸው ነገር የለም! እንደዚህ አይነት ሰዎች የምክር ወይም የሥነ አዕምሮ እርዳታ ነው የሚያስፈልጋቸው" ብለን ማጣጣል የለብንም።

በርግጥ በራሳቸው ደካማነት እንዲህ አይነት ነገር የሚገጥማቸው ሰዎች፣ በብዙ የሰዎች ስብስብ እና ቡድኖች ውስጥ አሉ። ለእንደዚህ አይነት ሰዎች እርዳታ እና ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። ነገር ግን አሁን እያወራሁ ያለሁት በከበቧቸው ሰዎች ስለሚደመጡ እና ስለሚከበሩ፣ በገቡበት ቦታ የከበረ ስፍራ ስለሚይዙ እና በስብዕናቸው ጠናካራ ስለሆኑ ሰዎች ነው። ነገር ግን እንዲያም ሆኖ በብቸኝነት ወጀብ እና አውሎ ንፋስ ስለሚናወጡ ሰዎች ነው። ብቸኛ በመሆን መብረቅ ተመተው በጭንቅ ውስጥ ስላሉ ሰዎች ነው። እነዚህ ሰዎች ድንገት አጠገባቸው

ካለው ስብስብ ተነጥለው የሰው ልጅ ሕይወት የማይፈታ እንቆቅልሽ የሆነበት እና ሁልጊዜ ራሱን ለምን ግራ አጋቢ ሁኔታ ውስጥ እንደሚያገኝ ከምንጩ ወደመገንዘብ ይመጣሉ። እንዲህ ያለ ሁኔታ በሕይወታቸው ያለፈ ሰዎች የሕይወት ተሞክሮን “አንዳንድ ሰዎች ምንም እንኳ ሁሉን ነገር ጥርት ባለ መንገድ ሌላው ሰው እንዲገባው አድርገው ማስረዳት ቢችሉም፣ ነገር ግን “ሌሎች ሰዎች እኔ የምለውን አይረዱኝም” የሚል ስሜት ስለሚሰማቸው፤ በሰው ተከበው ሳሉም ጥልቅ ብቸኝነት ይሰማቸዋል፤ ይሄ ደግሞ ያለ ነው” በማለት አሳንሰን ማየት የለብንም። እንደዚህ አይነት ሰዎች መኖራቸውን ማንም ሊክድ አይችልም። ሌላው ደግሞ በተወሰነ መጠን “ሰው አይረዳኝም” የሚል ጠባይ ቢያሳዩ እውነታቸው አይደለም ወይ? ሰው ሰውን ይረዳዋል ወይ? እንኳን ሌላ ሰው እኛስ ራሳችንን እንረዳለን ወይ?የሰው ልጅ ጥልቅ ማንነት፣ ከላይ ከላይ በምናየው እና ሰውየው በሚያሳየን አንድ እና ሁለት ነገሮች ላይ ተንተርሰን ‘ይህ የሆነው በዚህ ምክንያት ነው’ ብለን የምንተነትነው አይደለም። በርግጥ በራሳቸው ምናብ ፈጥረው “እኔ የተለየ ማንነት እና ግንዛቤ አለኝ፤ ስለዚህ ሰዎች ትኩረት ሊሰጡኝ እና ሊያደምጡኝ ይገባል” የሚሉ ሰዎች፣ በተለያዩ ሰዎች ውስጥ ያለውን ትክክለኛ ነገር ለመረዳት የምናደርገውን ጥረት ገደል የሚከቱ ሰዎች አሉ።

እነዚህ ሰዎች “በችሎታዬ እና ከሁሉ የተለየሁ በመሆኔ እንዲህ አይነት ቦታ ይገባኛል” ብለው ጠብቀው ያነን ቦታ በሚያጡበት ጊዜ፣ ብቸኛ ወደመሆን እና ራሳቸውን ወደ ማግለል ይሄዳሉ። ይህ ሃቅ እንዳለ አንክድም። እንደዚህ አይነት ሰዎችም እርዳታ ያስፈልጋቸዋል። ምንም የተለየ ነገር ሳይኖራቸው፣ እንዲሁ ከሜዳ ተነስተው “ሰው ለምን ስፍራ አልሰጠኝም” ብለው የሚያኮርፉ ሳይሆኑ፣ ካላቸው የከበረ ማንነት የተነሳ የሚደመጡ፣ ስፍራ የሚሰጣቸው እና ተናግረው ሰው የሚረዳቸው፤ ነገር ግን በዚህ ብቸኛ የመሆን አስፈሪ የሕይወት ዓለም ውስጥ የሚኖሩ ሰዎች አሉ። በዚህ ብቸኝነት ሳቢያም ከተለምዷዊው የዕለት ተዕለት እንቅስቃሴያቸው እና ከሰዎች ጋር ካላቸው ግንኙነት ዞር ብለው፣ ከአዕምሮ መረዳት በላይ ወደሆነው “ለምን የሰው ልጅ ሁልጊዜ ራሱን አስቸጋሪ ሁኔታ ውስጥ ያገኛል?!” ለሚለው ጥያቄ መልስ ወደሚያገኙበት መነሻ ቦታ ዘልቀው ይገባሉ። ብቸኝነትን ይጋፈጣሉ። ብቻቸውን ከ” ብቸኛ” ነት ጋር ይፋጠጣሉ።

ሌሎች በጣም ብዙ ሰዎች ለማፍቀር እና ለመፈቀር ከፍተኛ ዋጋ ቢከፍሉም፣ ማድረግ የሚችሉትን ሁሉ ቢያደርጉም በምላሹ ፍቅር የሚለግሳቸው በማጣታቸው እና ፍቅራቸው በመገፋቱ ምክንያት ብቸኝነት የሚሰማቸው አሉ።

እንደዚህ አይነት ብቸኝነት ወይም በዚህ ምክንያት የሚመጣ ብቸኝነት፣ በግድ ጎትተን በራሳችን ላይ የምናመጣው ብቸኝነት ነው። እንዲህ አይነት ብቸኝነት ውስጥ ያሉ ሰዎች ከሌላ ሰዉ ፈቃድና ፍላጎት መንጭቶ እንደስጦታ ሊገኝ የሚችለውን የፍቅርን በረከት፥ ሌላው እነርሱን የማፍቀር ግዴታ እንዳለበት የሚሰማቸውና፣ መፈቀርን እንደ መብታቸው የሚቆጥሩ አይነት ሰዎች ናቸው። እንዲህም ስለሚያስቡ የፈለጉት እና ይገባኛል ያሉትን ፍቅር ከፈለጉት ሰው ሲያጡ በምላሹ ራሳቸው በራሳቸው ላይ ጎትተው ባመጡት የብቸኝነት ዓለም ውስጥ ቁርፍድ ብለው ይቀመጣሉ። ከዛም አልፈው “አፍቅሬው አላፈቀረኝም”፥ “ፈልጌው አልፈለገኝም” ያሉት አካል ላይ ምሬት ያዳብራሉ፣ ሰላም ይነሳሉ እና የበቀል እርምጃ ይወስዳሉ። እንዲህ አይነት ሰዎችን ቀርበን ስለ አሉበት ሁኔታ ምን እየደረጉ እንዳሉ ብንመለከት ለብቸኝነታቸው መድሃኒት የማይፈልጉ እና በብቸኝነታቸው ስቃይ የሚደሰቱ እንደሆኑ በቀላሉ ማወቅ እንችላለን። እንዲህ አይነት ሰዎች የምድርን ፊት ሞልተዋል፤ ዕልፍ ዓዕላፋት ናቸው። አሁን በዘመናችን ለተባባሰው የአዕምሮ ቀውስ በዚህና መሰል ምክንያት በመጣ ብቸኝነት ውስጥ ያሉ ሰዎች ከፍተኛውን ድርሻ ይዘዋል። እነዚህ ሰዎች ከምንም በላይ ከፍተኛ ድጋፍ ያስፈልጋቸዋል። እነዚህ ሰዎች በቀላሉ በክፋ መንፈስ ኀይል ጥርስ ውስጥ ገብተው የሚታኙ ናቸው። ከሌላው ሰው ብቻ አይደለም የሚነጠሉት፤ ነገር ግን ራሳቸውን ከራሳቸው ነጥለው እጅግ አደገኛ ጉዞ የሚጓዙም ሰዎች ናቸው።

እና ማፍቀር ካፈቀሩት አካል ምላሽ መጠበቅ ተገቢ የሆነ ነገር እንጂ በሃፍረት የሚያሸሽ ነገር አይደለም። ይህ ቢሆንም በርግጥም የተገፋ፣ ተስፋ አድርጎ “ተስፋው” የበነነ፥ ያፈቀረውን በማጣት ሕይወት ውስጥ ያለፈ አለ። በዚህ የማፍቀር እና ምላሹ በጎ እንደሚሆን ተስፋ በማድረግ ሕይወት እያለፉ ያሉ ሰዎች ስላፈቀርኩ ልፈቀር፣ ስለወደድኩ ልወደድ፣ ስለፈለኩ ልፈለግ ብለው ግዴታ አያስቀምጡም። ግን ለማፍቀሬ ምላሹ “ፍቅር ነው” የሚል እጅግ ትልቅ ተስፋ አላቸው። በሌላው ላይ ተስፋ ማድረግ ስብራትን ያመጣል። ከሌላው ወገን እነርሱ በፈለጉት መንገድ የሚሆን ነገር እንደሌለ ሲያውቁ ይሰበራሉ። በሌላው ላይ የተደገፈ “ፍቅር” አይዘልቅም። መውደድም መዋደድም ማብቂያ አለው። አንዳንዴ እንዳይታደስ ሆኖ ሊጠፋም ይችላል። በዚህ ምክንያት የሚመጣ “ብቸኝነት” ደግሞ ከሌላው ጋር የነበረን የተለመደውን የግንኙነት ገመድ ይበጣጥሳል። መገፋፋት ና ግጭት ሳይኖር፤ መነጣጠል ና መለያየት ይከሰታል። ያም ሆነ ይህ ግን በብቸኝነት ዉስጥ የሚማቅቁት ለፍቅራቸው ምላሽ ፍለጋ ሲኳትኑ የነበሩ ናቸው። ብቸኛ የሚሆኑት እነርሱ ናቸው። ከሌላ አቅጣጫ ወይም ሰው የመጣ ፍቅር፣ ወይም

በራሳችን ውስጥ ያለ የፍቅር ኀይል ይህን ሸክም ከእኛ ሊያነሳልን አይችልም። የሕይወት ክፍታ ይህ ነው፦ አፍቅሮ እና ያፈቀረውን ለማግኘት ፈልጎ ነገር ግን ለፍቅሩ ተመሳሳይ ምላሽ ያላገኘ፣ "ነፍሱ" ግን "ከምሬት እና ቁጣ" የነፃች፥ አፍቅሮ ባለመፈቀሩ የሚመጣበት ስብራት፣ ሥጋ በለበሰ ሁሉ ላይ የሚደርስ አስቸጋሪ የሕይወት አጣብቂኝ ለመጥፊያው ሳይሆን ከፍ ወዳለ እና አዲስ የሕይወት ልምምድ ውስጥ መግቢያ መንገድ ይሆንለታል።

በመጨረሻም ብቸኛ መሆን ከሁለት አቅጣጫ በግራ እና በቀኝ በመምጣት ሕይወታችንን ይከባል። ይህ ሲሆን ጉሮኖ ገብተን እንደበቅም፤ ደግሞም ሮጠን አናመልጠውም። አንደኛው ከበደለኝነት የሚመጣ "ብቸኛ" ነት ሲሆን ሁለተኛው ወደማይቀረው ሞት ልንሔድ በተቃረብንበት ወቅት ያለ "ብቸኛ" ነት ነው። እኛው ራሳችን "ህያው በሆነ፣ ለመኖር እና ለማፍራት በተሰጠን" እኛነታችን ላይ በደል ፈፅመን ስናበቃ፥ በበደል ያመጣነውን ጉዳት ማንም ከእኛ ላይ ማስወገድ አይቻለውም። በድብቅም ይሁን በአደባባይ የፈፀምነው በደል የእኛው ጥፋት እና የእኛው ብቻ እንደሆነ እናውቃለን። ስሜቱ በአጥንታችን ዘልቆ ይገባል። ሆዳችን እያወቀ ለማድበስበስ ብንሞክርም፤ ለፈፀምነው በደል ማንንም ተጠያቂ ማድረግ አንችልም። ከበደለኝነታችን መሮጥ እና ማምለጥ አንችልም። ልንሸፍነው፣ ወደ ጓዳ ወርውረን ልንሰውረው አንችልም። እኛው ለብቻችን፤ ከበደላችን ጋር እንፋጠጣለን። ኋላም ይህ በፈፀምነው በደል ምክንያት የገባንበት "ብቸኛ" ነት ሁሉንም አይነት "ብቸኛ" ነት ጎትቶ ወደ ሕይወታችን ያመጣል። እናም ይህ አይነቱ ከበደለኝነት የሚመጣ ብቸኝነት እኛው በራሳችን ላይ ዳኛ ሆነን፥ ራሳችንን በመኮነን ራሳችን ላይ እንድንፈርድ ያደርገናል።

ቀጥሎ ደግሞ ነፍሳችን ከሥጋችን ልትለይ ባለው ሰዓት እና ደቂቃ በሕይወታችን የሚሆን በቃላት የማይገለፅ የ" ብቸኛ" ነት ኑባሬ ነው። ከሞት ደጃፍ ላይ ሆነን የስንብት ሰዓታችንን እየጠበቅን በብቸኝነት ጥልቀት ውስጥ እንሰምጣለን። በዛች ሰዓት ከሌሎች ጋር ያለን የትኛውም ግንኙነት ያን የብቸኝነት ጥልቀት ሊያስወገድ አይችልም። በምድር ሩጫችን ማብቂያ ሰዓት፣ የምንም ነገር ከአጠገባችን መሆን፣ ሞታችንን ልንሞት እንደሆነ እና ተራችን ደርሶ እንደተጠራን የመሆኑን እውነት ሊሸፍን እና ሊደብቅ አይቻለውም። በነፍሳችን ፍጻሜ ሰዓት፥ በሞት ጣዕር ውስጥ ስንሆን ከአጽናፈ ዓለሙ እና በውስጡ ካለው ነገር ሁሉ እንቆረጣለን። "ብቸኛ" መሆናችንን ረስተን መኖር እንድንችል አድርገውን የነበሩ ሁሉ ይለዩናል። ግዑዙም፥ ሕይወት ያለውም ከእኛ ይነጠቃል። ይህን "ብቸኛ" ነት ማን

ይቋቋማል?

## 3.

ብቸኝነት የሚሸነፈው ለብቻ መሆንን መሸከም በሚችሉ ብቻ ነው። ሰው ስለሆንን “ለብቻ መሆንን” የምንፈልግበት ከተፈጥሮ የሆነ መሻት አለን። “ለብቻ በመሆን” ከጫጫታ እና ከግርግር ዞር በማለት ማን እንደሆን እና ምን እንደምንሆን ለማወቅ እንፈልጋለን። ለመረዳት እንፈልጋለን። ይህ ለብቻ የመሆን ፍላጎት ጤነኛ ፍላጎት ነው። “ለብቻ” ችን መሆን የፈለግነው “ከጭንቅ እና ከፍርሃት” ከሌላው ሽሽት ሳይሆን “ከደስታ እና ብርታት” የተነሳ ነው። ከራሳችን ጋር “ለብቻ ለመሆን” ካለን መሻት ነው። “ለብቻ”፥ በፀጥታ ውስጥ መሆንን የምናገኝበት እና የምንለማመድበት ብዙ መንገድ አለ። እነዚህ ብዙ አይነት መንገዶች ሃይማኖታዊ መንገዶች ተብለው ሊጠሩ ይችላሉ። ሐይማኖታዊ መንገዶች ስንል በሆነ የእምነት ማሕበር ጥላ ውስጥ መሆንን የሚያመለክት አይደለም ነገር ግን የመለኮት መገኘት የትኩረታችን ማዕከል ሲሆን እና በልባችን ለመለኮት መገኘት ስፍራ ያለን ስንሆን፣ የምናልፍባቸው መንገዶች ማለታችን ነው። አንድ ፈላስፋ “ሃይማኖት ማለት ሰው ብቻውን በሚሆንበት ጊዜ የሚያስበው፣ የሚናገረው እና የሚያደርገው ነገር ነው” እንዳለው ከሌሎች ሰዎች ጋር ተሰባስበን የምናደርጋቸው ሃይማኖታዊ እንቅስቃሴዎች ልባችን ውስጥ የሌለ፣ ከብዙሃኑ ጋር ለመመሳሰል የምናደርገው ጥረት ሊሆን ይችላል። “ዞር” ስንልና “ለብቻ” ችን ስንሆን ማድረግ አይደለም ማሰብም የምንጠላውን ነገር በሐይማኖት ሰዎች መሐል ስንሆን ሰዎችን በመፍራት ወይም ለአንዳች ጥቅም እናደርገዋለን። ሃይማኖት ለብቻችን ስንሆን የምንሆነው ነው።

ከእነዚህ ሐይማኖታዊ መንገዶች አንዱ ከተፈጥሮ ዝምታ ጋር አብረን ለማሳለፍ ያለን ፍላጎት ነው። ድምጽ ሳናወጣ ከዛፎቹ ጋር እናወራለን፤ ከደመናት ጋር እንላፋለን፤ ከባሕር ሞገዶች ጋር እንጫወታለን። እነርሱም በተራቸው ከአንደበታቸው ቃል ሳይወረውሩ፣ ዛፎች ቅጠላቸውን በማራገፍ፣ ደመና ወዲህ እና ወዲያ በመጓደድ፣ የባሕር ማዕበል በአስገምጋሚ እንቅስቃሴ ምላሽ ይሰጡናል። ለብቻችን ስለሆንን! ይህ አይነቱ ለብቻ መሆንም ቢሆን የሚቆየው ለተወሰነ ጊዜ ያህል እንጂ ለዘለቄታው አይደለም። ለዚህም ምክንያት አለ። ለብቻችን ከተፈጥሮ ጋር ስንጨዋወት በቆየን ቁጥር፣ የተፈጥሮ ድምፅም ቢሆን በአዕምሮአችን የተሸከምነውን ጥያቄ ሊፈታ እንደማይችል፣ እና ዘላለም ከተፈጥሮ ጋር ለብቻችን

መቆየት እንደማያዛልቅ እንገነዘባለን። ከተፈጥሮ ጋር የምናሳልፈው የፀጥታና “ለብቻ የመሆን” ጊዜ መልካም ቢሆንም መልሶ ብቸኛ፣ ምንም እና ማንም አብሮት የሌለ ሰው ስሜት ይፈጥርብናል። ሮጠን ወደ ሰው ልጆች ዓለም፣ ተሰባስበን ወደ ምንኖርበት፣ ወደ ጫጫታው እንመለሳለን።

“ለብቻ መሆንን” የጥበብ ሥራዎችን በማንበብ ውስጥም ማግኘት ይቻላል። በግጥም ስንመሰጥ፣ ሙዚቃ ስናዳምጥ፣ የሥዕል ሥራዎችን ስንመለከት እና በንፁህ ልቦና በጥልቀት በምናሰላስልበት ጊዜ “ለብቻ” የመሆንን በረከት እናገኛለን። በብዙ ሰዎች መካከል በ” ብቸኛ” ነት ስሜት ከመሰቃየት፥ በብዙ ሰዎች መሐል ሆነን ቢሆን እንኳን፤ የውጪው ጫጫታ ወደ ውስጣችን ገብቶ የማይረብሸን “ለብቻ መሆንን” የምንችል እንሆናለን። ራሳችንን ሳናገል እና በመጎዳት ምክንያት ከሰው ሳንሸሽ፤ “ለብቻ መሆንን” መልመድ ከሚወረወርብን ቀስት የሚጠብቀን ጋሻ ነው። ነገር ግን ኑሮ ትርጉም ወደሌለው፣ ሁሉም ተናጋሪ ወደሆነበት እና ልናስወግደው ወደማንችለው ወደ ዕለት ተዕለት ሕይወት ይመልሰናል። ኑሮ ለብቻ ከመሆን በረከት አውጥቶ ወደ ብቸኝነት ቅዝቃዜ ውስጥ መልሶ ይወረውረናል። መልሶ ደግሞ በግርግር “ብቸኛ” ነታችንን ማስረሻ ነገር ያለብሰናል።

አሁን መጨረሻ ላይ ያነሳነው ሐሳብ በሁሉም ቦታ እና በሁሉ ዘመን ያሉ የሰው ልጆች ያለባቸውን የሕይወት ተግዳሮት የሚመለከት ነገር ብቻ ሳይሆን፤ በተለይ አሁን ያለንበትን ዘመን በተለየ ሁኔታ የሚገልፅ ነው። ካለፉት ትውልዶች በበለጠ ሁኔታ አሁን ያለንበት ጊዜ፥ ብዙ ሰዎች ከግርግር እና ከበርቻቻ ወጥተው በእርጋታ መቀመጥ፣ ለ”ብቻ መሆንን” የሚፈሩበት ዘመን ነው። ነገር ግን በግርግር እና ጩኸት መሐል እጅግ አስፈሪ በሆነ “ብቸኛ” ነት የሚሰቃዩበትም ዘመን ነው። ሰው ሁሉ በሌላው ለመወደድ፣ በሰው ለመከበብ፣ የሆነ ቡድን አካል ለመሆን፣ ሁነኛ ሰው ለመሆን፣ የማይቆፍረው ጉድጓድ የሌለበት ጊዜ ነው። ደግሞ የዚህ ዘመን የአኗኗር ዘይቤም፣ እንደዚ መሆንን የሚያስገድድ እና ብኩንነትን የሚደግፍ ነው። ሁሉም ነገር እና ሁሉም ቦታ በእርጋታ ለብቻችን መሆን እንዳንችል እና ለብቻ መሆንን እንዳንለምድ የሚያደርግ ከባቢ በመፍጠር የተካነ ነው። ይሄ ምን ያህል እንደታመምን ማሳያ ምልክት ነው። ያለው የማያቋርጥ ጫና እና ብኩንነት ለብቻ የመሆንን መሻት ከውስጣችን ሙልጭ አድርጎ ለማውጣት የሚታገል ነው።

ነገር ግን አንዳንድ ጊዜ ከበርቻቻው፣ ጩኸቱ፣ ግርግሩ፣ ከህዝቡ ጋር ግፊያው ተመችቶን ሳለ፥ እግዚአብሔር በግድ ከሰው መሐከል ነጥሎ አውጥቶ ለብቻችን ያደርገናል። እኛም በኋላ ላይ እግዚአብሔር ለብቻ እንድንሆን የወሰደን ስፍራ

ይመቸናል። ነብዩ ኤርሚያስ ሲናገር “በእጅህ ፊት ለብቻዬ ተቀመጥሁ።” ይላል። አንዳንድ ጊዜ እግዚአብሔር እጁን በላያችን ላይ ያከብዳል። ለብቻችን ካደረገን በኋላ ከብዙ ሰዎች ሊነጥለን በሚችል ፀጥታ፤ ለብቻ ሲኮን ብቻ የሚጠየቅ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል። እውነት ይህ ምንድን ነው? ይሄ እንዴት እውነት ተባለ? እውነትን እንዴት ላስተውላት? ብለን ጥያቆዎችን እንድናወጣ እና እንድናወርድ ይፈልጋል። ነገ ከፊታችን ሞት እና መከራ ቢመጣ ለመቀበል የማናመነታ ሰዎች የሚያደርገንን የፍትሕ ጥያቄ እንድንጠይቅ ያደርገናል። ይህም ለብቻ ሲኮን ብቻ በውስጣችን እያደገ የሚሔድ ነገር ነው። ነገ ሰዎች በእኛ ላይ አዋራጅ ንግግር እንዲናገሩ እና እንዲጠሉን የሚያደርግ ነገር ግን ሁሉም ሰው ከሚሔድበት መንገድ ወጥተን፥ እንቅፋቶችን ሁሉ አልፈን እንድንሄድ ይፈልጋል።

ይህም ለብቻ ሲኮን ብቻ የሚሆን ነገር ነው። ስለ እኛነታችን ከላይ ከላይ ብቻ የምናውቀውን ገለባ መረዳት በመናቅ የሕይወት ድብቅ ሚስጥር ግልጥልጥ ወደሚልበት ወደነፍሳችን ጥልቀት ገብተን እንድናስስ ይፈልጋል። ይህም “ለብቻ ሲኮን” ብቻ መገለጥ የሚችል ነው። ከእኛ መካከል በአንዳንድ የሕይወት ዘርፎች የፈጠራ ሥራ ለመሥራት የሚፈልጉ ይኖሩ ይሆናል። ነገር ግን ይህም ለብቻ መሆንን ይጠይቃል። በፅጥታ ውስጥ ሳንሆን የፈጠራ ሥራ መሥራት አንችልም። በአንድ ወቅት በፈጠራ ሥራ የተካንን የነበርን ብንሆን እንኳን፤ “ለብቻ የመሆን” ጊዜ ከሌለን በዛ የፈጠራ ክህሎት መቀጠል አንችልም። ለሰዓታት የፈጠራ ስልጠና ወስደን ከምናገኘው ክህሎት በላቀ አስበን እና አቅደን “ለብቻ መሆን” የፈጠራ ሐሳብ አመንጪነታችንን ያጎለብታል።

“ለብቻ መሆን” ስንጀምር፣ “ለብቻችን ስንሆን” የሚሆነው ምንድን ነው? ኢየሱስ በምድረ በዳ ስላሳለፈው “ለብቻ የመሆን” ጊዜ ማርቆስ የተናገረውን ተመልከቱ፣ “በምድረ በዳም በሰይጣን እየተፈተነ አርባ ቀን ሰነበተ፤ ከአራዊትም ጋር ነበረ፥ መላእክቱም አገለገሉት።” ብቻውን ሆነ። በዛ ለብቻው በሆነበት ሰዓት አጽናፈ ዓለሙ ሁሉ ከእርሱ በተቃራኒ ቆመ! የምድረበዳ አራዊት በዙሪያው እና በእርሱ ላይ አፈጠጡ። እርሱ ራሱ አብ አባቱን እንዲፈታተነው በሚፈልግ የክፋ ኀይል እና ለክፋ ኀይል እጅ እንዳይሰጥ በሚፈልግ የመለኮት ኀይል መካከል በሚካኼደው ጦርነት የአውደ ውጊያ ቦታ ሆነ። አያችሁ “ለብቻችን ስንሆን” ምን እንደሚሆን? ከራሳችን ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን። ከራሳችን ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን ስንል ምግብ ስንበላ፣ ውሃ ስንጠጣ፣ ከሰዎች ጋር ስንጫወት፣ እና ሥራ ስንሰራ ከምናውቀው “እኛነታች” ን ጋር አይደለም የምንገናኘው። ነገር ግን በሕይወት

ውስጥ “አዲስ ነገር በሚያደርግ” እና በሕይወት ውስጥ “መልካም ነገር” በሚያጠፋ ኋይል መካከል ውጊያ የሚካሔድበት ጦርሜዳ የሆነ “እኛነታችን”ን እናገኝዋለን። እግዚአብሔር እና ሰይጣን የሚፋለሙበት ሜዳ ከሆነው እኛነታችን ጋር ፊት ለፊት እንገናኛለን። ከመንጋ ከሰው ከበባ እና ጩህት፣ ተነጥሎ ለብቻ መሆን ቀላል አይደለም።

ለብቻ የመሆንን በምርጫ የሚገኝ መንገድ ማን ይሔድበታል? “ለብቻ መሆን” ለኢየሱስ እንኳን ቀላል አልነበረም። ሌላም ቦታ ላይ እንዲህ ተብሎ ተፅፏል “ሕዝቡንም አሰናብቶ ይጸልይ ዘንድ ብቻውን ወደ ተራራ ወጣ። በመሸም ጊዜ ብቻውን በዚያ ነበረ።” ምሽት ሲሆን፣ እየጨለመ ሲመጣ “የብቸኝነት” ህመሙ እየከፋ ይመጣል። ይህ ነፍስን በፍርሃት በሚከብብ የብቸኝነት ስሜት ቀኑን በሰላም ውለን፣ ሲመሻሽ ወይም በሕይወታችን የሆነ ወቅት ወይም የሕይወታችን ዘመን ወደ ፍጻሜው ሲመጣ ዘልቆ ይሰማናል። ኢየሱስ ሊጸልይ ወጣ። ብቸኛ ከመሆን ሕይወት “ለብቻ መሆን” እና “ለብቻ የመሆንን” የሕይወት ልምምድ ወደ ተግባር ለመቀየር ፀሎት ሁነኛ መንገድ ነውን? ከባድ ጥያቄ ነው። በቀላሉ የሚመለስ አይደለም። ብዙ የምንፀልያቸው ፀሎቶች እንዲህ አይነት ነገር ለማድረግ ኋይል ያላቸው አይደሉም። አብዛኛው ፀሎታችን ከጓደኞቻችን ጋር ተሰባስበን፣ እንደምንጯጯህው፣ በወሬ እንደምንጠመደው እግዚአብሔርንም በከንቱ ልፍለፋ በመጥመድ፣ የጩህታችን አካል ለማድረግ ነው። እንደውም በፀሎት ሰዓታችን ወደ አዕምሮአችን የመጣውን ሁሉ በመለፍለፍ “ለብቻ መሆን”፣ በጸጥታ እና እርጋታ መቀመጥ የሚገኝበትን እውነተኛውን መንገድ አበላሽተን ብቸኛ ከመሆን ማምለጫ እናደርገዋለን። ውስጣችንም፣ ውጪያችንም ፀጥ ብሎ እግዚአብሔርን አናዳምጥበትም። እንዲህ አይነቱን ፀሎት፣ የቤተ ክርስቲያን ደጃፍ የሚያዘወትሩ ምዕመናን እና አገልጋዮች በቀላሉ በየቀኑ የሚያንበለብሉት ነው። እንዲህ አይነት ፀሎቶች እግዚአብሔር እና ሰው ብቻቸውን ከሚገናኙበት ቦታ የሚወጣ ፀሎት አይደለም። የዘልማድ ነው። እንዲህ ያለው ፀሎት፣ ኢየሱስ ወደ ተራራ ወጥቶ የጸለየው አይነት ፀሎት አይደለም። ዝም ብንል መልካም ነበር። ሁሌ “ለብቻ መሆን” የምትጓጓው ነፍሳችን ቃል ሳታወጣ ከእግዚአብሔር ጋር እንድታወራ ብንተዋት እንዴት ጥሩ ነበር። ይህን ለማድረግ የተለየ ቀን እና ቦታ አያሻም። በሥራ በተወጠርንበት ቀን፣ በግርግር በተሞላ ቤት ውስጥ ባስ ሲልም በጣም አስቸጋሪ በሆኑ ውጪዊ ሁኔታዎች ውስጥም ሆነን ይህን ማድረግ እንችላለን። ይህን ደግሞ ማንም ሊወስድብን የማይችል፣ ለብቻ የምንሆንበት ጊዜ ይሰጠናል።

ለብቻ በምንሆንበት ጊዜ፥ የሚደረግልን አንዳች ነገር አለ። በ" ብቸኛ" ነት ቆፈን ሲጠቃ የሚታመመው ደግሞም ለብቻ በመሆን በሚመጣ እርጋታ እና ሰላም፥ ዕረፍት የሚያገኘው "የሁለንተናችን መሠረት የሆነው" እኛነታችን፥ ወደ መለኮታዊ ክብር ከፍ ብሎ በዛ የመለኮት ክብር ውስጥ መቀመጥ ይሆንለታል። እናም "እኛነታችን" ን ሳይጠፋ፤ ብቸኛነታችን ሳይወገድ በመለኮት ክብር ውስጥ እረፍት ይሆንልናል።

ምናልባት ከዚህ ቀደም ጠይቀነው የነበረውን እና በውስጣችን ሲብላላ የቆየውን ጥያቄ አሁን መመለስ እንችላለን። ለብቻ መሆን፤ ከሁሉ ነገር ተነጥሎ በፀጥታ መቀመጥ፥ ከራሳችንም ከሌሎችም ጋር የሚኖረንን ሕብረት ጤነኛ ያደርጋል። እንዴት እውነተኛ ሕብረት ለብቻ ከመሆን ውስጥ ያድጋል? አስቀድመን የሌላውን ሰው ሁለንተና በርብረን ማወቅ አንችልም የሚለውን አይተናል። የሌላው ሰው እሱነት የራሱ ብቻ ነው። በርግጥ ሊመስለን ይችል ይሆናል። ወደ እርሱነቱ፥ ወደ ሌላ ሰው ውስጠኛ ክፍል ዘልቀን ገብተን ስለ እርሱ ያለውን ነገር ማንነቱን ማየት አንችልም። ሌላ ሰው ወደ ሌላው ሰው "መንፈስ እና ነፍስ" ማዕከል መግቢያ በር የለውም። ሁልጊዜ ብቸኛ ነን። ሁሉም ራሱን ብቻ ይዞ የሚቆም ማንም የማይደርስበት ብቸኛ ነው። ነገር ግን ወደ ሌላ ሰው ብቸኝነት ውስጥ ገብተን ብቸኝነቱን ወደ ሕብረት የምንቀይርበት መንገድ አለ። መጀመሪያ ወደ እግዚአብሔር ህልውና እንገሰግሳለን በእግዚአብሔር ህልውና በኩል ወደሌላ ሰው "ብቸኝነት"፥ "እርሱነት" ውስጥ እንገባለን። ግን እንደዛም ሆኖ "እሱነቱ" የራሱ ብቻ ሆኖ የተፈጠረበትን ማለትም "የምንም እና የማንም" ያልሆነውን ብቸኝነቱን ማስወገድ አንችልም።

ሕብረት ብቸኛነት ማስወገጃ፥ አንዱ የሌላውን እኔነት የሚያጠፋበት አይደለም። ነገር ግን "የሁሉ ብቸኝነት" በቦታው እንዳለ፤ ሁሉም ብቸኝነቱን ይዞ፥ ሰው ሁሉ "የማንም እና የምንም ሳይሆን" ወዶ እና ፈቅዶ እሱነቱን ከፍቶ ወደሚያካፍልበት ሕብረት ይዞት ይመጣል። በዚህ መንገድ ሁሉም ሰው የሚያርፍበት ሕብረት ያገኛል። በዚህ መልክ፥ ፍሬው የማረ፤ ሕብረትና ማሕበረ ሰብ ይፈጠራል። ለሌላው ያለን ፍቅርም ከቀዘቀዘበት ሁኔታ፥ ዳግም የሚወለደው ለብቻ በመሆን ውስጥ ነው። ከግርግሩ ዞር ብለን በእርጋታ አንድ ቦታ መቀመጥ ስንችል፤ ለብቻ መሆን ውስጥ ቆይተን ስንመለስ፥ በፍቅር ተትረፍርፈን በመንፈስም እና በአካል ከእኛ የተነጠሉትን ለብቻችን በሆንበት ቦታ በትውስታ እና ናፍቆት በልባችን ውስጥ ቦታ እንሰጣቸዋለን። አስቀድመን ነፍሳችን ውስጥ ቀጥለን፥

በአካል አብረናቸው መሆን እንችላለን። ለብቻ መሆን የሚችል ከሌላም ሰው ጋር አብሮ መሆን ይችላል። እናም በአካል ከእኛ የተነጠሉንን የምናገኛቸው ለብቻ በመሆን ውስጥ ብቻ ነው። ለብቻ መሆን ውስጥ ባለንበት ወቅት፥ በፀጥታ እና በእርጋታ በተቀመጥን ጊዜ የእኛነታችን ማዕከል ክፍት ነው። ያም ስለሚሆን በአካል የተነጠሉንን ዳግም በአካል ከማግኘታችን በፊት ከውስጣችን፣ ከእኛነታችን ያራቀውን “እነርሱነታቸውን” ወደ “እኛነታችን” እጃቸውን ይዘን እንገባለን።

በልባችን ውስጥ አብረውን ይሆናሉ። አንድ ተሰባሪ ሰው ከሌላ ተሰባሪ ሰው የለያየው ግድግዳ ፈርሶ አልፎ መገናኘት የሚችለው፥ ለብቻ መሆን ውስጥ በምናገኘው የመለኮት ሕልውና ነው። በዘላለም አምላክ ሕልውና ነው። ፍቅራችንን ለማሳደግ እና ሕብረታችንን ለማጠንከር 24 ሰዓት ጊዜ ወስደን ስንጫዋወት እና ስናወራ ብንውል የማናገኘውን ብርቱ መዋደድ እና የማይሰበር ሕብረት፤ አንድ ሰዓት ለብቻ በመሆን ውስጥ ስናሳልፍ እናገኘዋለን። በዛ ለብቻ በሆንበት ቦታ የእኛነታችን በር ከፍተን የምንወደውን ሰው እርሱነት ወደ እኛነታችን በማስገባት እናገኘዋለን። ለብቻችን ሆነን የምናስበው፣ ህልውናውን ከእኛ ጋር እንዲሆን የፈቀድንለት ሰው ብቻ እውነተኛውን ፍቅራችንን ይካፈላል። ወደሌላው የምንቀርበው ለብቻ በመሆን ውስጥ ነው። ወደ ዘላለም ሕብረት፥ ወደተራራው ይዘናቸው የምንሔደው በዚህ መንገድ ነው።

ደግሞ የዘላለም አምላክ ለብቻ መሆንን የተፈጥሮአችን አንዱ አካል ሲያደርግ ያን ሊያደርግ የፈለገበት ለብቻ የመሆን ውስጠ ሚስጥር ምንድን ነው? በማለት ጥያቄ መጠየቅ እንችላለን። መልሱ ይህ ነው። በውጥረት እና ዕረፍት ማጣት፣ በግርግር እና ጭንቀት በተሞላው በዚህ ሥጋ ለባሽ ተሰባሪ ሰው መንገድ ላይ ዘላለማዊው የሆነው የመለኮት ሕልውና መገኛ ለብቻ መሆን ብቻ በመሆኑ ነው። በክርስቶስ በኩል በሚያበራው የእግዚአብሔር ዘላለማዊ ሕልውና የተለየናቸውን ሰዎች እና ነገሮች ሁሉ የሚያካትት ነው። ተቀይመን እና ተቆጥተን ሮጠን የተደበቅንበት ስፍራ አይደለም። ማንም እና ምንም የሌለን በብቸኝነት ብርድ፣ ብቸኛ በመሆን ሕመም የምንሰቃይበት ሳይሆን “ለብቻ የመሆን” የእርጋት እና የእረፍት ልምምድ ሕይወት ነው። ከግርግሩ ወጥተን፣ ለብቻ ወደ መሆን ውስጥ የምንገባው ሁሉን ነገር አጥተን ሁሉን ነገር ጥለን ባዶ ሆነን ነው። ከብቻ መሆን ዓለም ወደ ተለምዷዊው ዓለም ስንመለስ በሁሉ ነገር ባለጠጎች ሆነን እንመለሳለን።

እንግዲህ “ለብቻ መሆን”፥ ውስጥ ለመሆን አናመንታ። ደፋሮች እንሁን። ግርግሩን ትተን፥ ወደፀጥታው እንዝለቅ። በዛ፥ ዘላለማዊውን እንገናኘዋለን፤ በዛ የተለየናቸውን እና የተነጠልናቸውን፥ በተዘረጋ እጅ እና በፍቅር ማቀፍን እናገኛለን። በዛ እኛን ሲፈልገን የነበረውን “እኛነታች” ንን እናገኘዋለን። ለብቻ መሆን፤ ከብቸኝነት መዳኛ።

# 10. የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ

*“ላለው ይሰጠዋልና፤ ከሌለውም ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።”*

*ማርቆስ 4:25*

አንድ ቀን በመካከላችን በሊቅነቱ እጅግ የተመሰገነ የሰራ ባልደረባዬ ሊያናግረኝ ፈልጎ ወደኔ መጣ። አንዳች አስደንጋጭ ዜና እንደያዘ ወይም መርዶ እንደሰማ ሰው በፊቱ ላይ የመረበሽ ስሜት ነበረው። “እኔ በግሌ እስከዛሬ ከተነገሩ ሀሳቦች እጅግ ኢ-ሞራላዊ እና ኢ-ፍትሓዊ እንደሆነ የምቆጥረው ሃሳብ አዲስ ኪዳን ውስጥ ተጽፎ ይገኛል።” አለኝ። ቀጥሎ አሁን የምንመለከተውን ክፍል ከመጽሐፍ ቅዱስን ከፍቶ አነበበ “ያለው ይጨመርለታል” ይላል። ያን የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል እያነበበ በሄደ ቁጥር፥ ቁጣው እየጨመረ ሲሄድ ፊቱ ያስታውቅ ነበር። “ከሌለውም ያው ያለው እንኳ ይወሰድበታል።” እንደጨረሰ መፅሐፉን ከደነ። ወደ እኔ ዞር ብሎ አሁን ይሄ ምን ማለት ነው በሚል አስተያየት አየኝ። ይህ ወዳጄ ብቻ አይደለም ነገር ግን ሁላችንም በዚህ ክፍል በተጠቀሰው ሃሳብ በርግጥ ግን ምን ማለት ነው በማለት ውስጣችን ጥያቄ ሳይፈጠርበት እንደማይቀር አምናለሁ። ይህ ለህቅ የዚህን ክፍል ግራ አጋቢነት ለመፍታት መፍትሄ ነው ብሎ ያቀረበው ኢየሱስ ይህን አይነት ንግግር አልተናገረም። ምናልባት ደቀመዛሙርት አጥርተው ባለመስማት ምክንያት ሌላ ነገር ብሎ ሳለ ይህን ያለ ስለመሰላቸው የሰነከሩት ሐሳብ ነው። ነገሩ ቢያበሳጭም ከቁም ነገር ሳንወስደው እንለፈው የሚል ነው።

እኛ ግን እንዲህ አይነት ማምለጫ በመፈለግ በቀላሉ ክፍሉን አጣጥለን ማለፍ አንችልም። ቢያንስ አራት ጊዜ በወንጌላት ውስጥ ተፅፎ እናገኛዋለን። ይህ እንግዲህ ምን ያህል በትኩረት የተጠቀሰ ቃል እንደሆነ መረዳት እንችላለን። ከዚህም በላይ የወንጌል ጸሐፊዎች ልክ እንደ እኛ ግራ የመጋባት ስሜት ተሰምቷቸው እንደነበር ግልጽ ነው። ለእነርሱም ቢሆን ይህ ሐሳብ የእንቅፋት ድንጋይ ሳይሆንባቸው አልቀረም፤ እና “አይ እንዲህማ ሊል ፈልጎ አይደለም በሚል” በተለያየ መንገድ ሊተረጉሙትም ሞክረው ይሆናል። ምናልባትም ይህ ሐሳብ በቀላሉ እንዲገባቸው ሊያደርግ ይችላል የተባለ ማብራሪያ ሁሉ ተመልክተው አላረካቸው

ይሆናል። የሆነ ሆኖ በተለይ ይህ ከኢየሱስ አፍ የወጣ ንግግር፥ እኛ ሁላችንን ለሰው ልጆች በየዘመናቱ አልፈታ ካለ ዋነኛ ምናልባትም ደግሞ ህመሙ አጥንት ስር ዘልቆ ከሚሰማ የሕይወት እንቆቅልሽ ጋር ወስዶ ያላትመናል። ይህም እንቆቅልሽ በሕይወት ውስጥ እኩልነት የሚባል ነገር አለመኖር ነው።

የእኛም እርግጠኝነት፣ ይህንን እንቆቅልሽ እንፈታለን ብለን ተስፋ አለማድረጋችን ብቻ ነው። መጽሐፍ ቅዱስ ይህን እንቆቅልሽ አይፈታም። ሌሎች ታላላቅ ሃይማኖቶች ይህን እንቆቅልሽ መፍታት አቅም የላቸውም። የትኛውም አይነት ፍልስፍና ይህን እንቆቅልሽ ለመፍታት አንዳች ጉልበት የለውም። ነገር ግን አንድ ማድረግ የምንችለው ነገር አለ። የኢ እኩልነትን እንቆቅልሽ ጥልቀትና ስፋት ማሰስ እንችላለን። የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ ሳይፈታ ባለበት ቢኖር እንኳን፤ ከዚህ እንቆቅልሽ ጋር የምንኖርበትን መንገድ መፈለግ እንችላለን። እንዴት አብረን እንደምንኖር መንገድ መፈለግ እንችላለን ብለን ስንል፥ ይህ እንቆቅልሽ የሕይወትን ትርጉም እና መንገድ እንዳያሰናክል የሚከለክል እይታ እና አስተሳሰብ ይኖረናል ማለት ነው።

እውነት ግን ምንድን ነው ያለኝ ብለን ራሳችንን ጥያቄ ከጠየቅን በኋላ በቁሳቁስ እና በሚታዩ ነገሮች ብዙ የተሰጠን ሰዎች ሆነን ራሳችንን እናገኘው ይሆናል፥ ለምሳሌ ብዙ የልብ የሆኑ ጓደኞች ያሉን፥ በትምህርታችን ስኬታማ የሆንን፥ የምናደርጋቸው ነገሮች የምናደርግበት መርህ እና ሞራል ያለን ሰዎች ሆነን ራሳችንን አግኝተን ይሆናል። ስለዚህ እነዚህ ብዙ የተሰጡን ነገሮች ስላሉን ተጨማሪ ብዙ ነገር እንደሚሰጠን መጠበቅ እንችላለን። በሌላ መልኩ ደግሞ እኛ ያሉን መልካም ነገሮች፣ ስኬቶች እና ችሎታዎች የሌላቸው ሰዎች ያቿ ያለቻቸው ጥቂት ነገር ተጨምራ እንደሚወሰድባቸው ርግጠኛ መሆን እንችላለን። ከዚህም በላይ፣ በኢየሱስ ምሳሌ መሠረት፣ አንድ ብቻ መክሊት ካለው ተወስዶ  አምስት ወይም አሥር መክሊት ላላቸው መሰጠት አለበት። እነሱ የበለጠ ድሆች ስለሚሆኑ የበለጠ ሀብታም እንሆናለን ማለት ነው። ሕጉ ይህ ነው። እና እንደዚህ አይነት ኢፍትሓዊነትን ልንቃወም እንችላለን። ቢሆንም ግን ሕይወት በኢ እኩልነት የተሞላ መሆኑን አንክድም። ይህን ሐቅ ልንክደው አንችልም፣ ነገር ግን ተገቢ የሆነ ጥያቄ ልንጠይቅ እንችላለን፤ በእርግጥ አለን ብለን የምናምነው ከእኛ ሊወሰድ የማይችል ነገር አለን? ይህ ጥያቄ የሚያናውጥ ነው። ልብን የሚያርድ በጭንቀት የሚሞላ ጥያቄ ነው፥ በሉቃስ ወንጌል ላይ ደግሞ የባሰ ከብዶ እና ጎልቶ እናገኘዋለን። ሉቃስ እንዲህ ይላል

"ከሌለውም ሁሉ፥ ያው ያለው የሚመስለው እንኳ ይወሰድበታል።"

ምናልባት እኛ አሉን ያልናቸውን ብዙ ነገሮች “ላለው ይጨመርለታል” በሚለው ውስጥ የማይገቡ “ብዙ ያለን” የሚመስሉ ግን የሌሉ ነገሮች ይሆናሉ። ምናልባት ደግሞ በምስኪኑ ሰው ዘንድ ያለችው “ጥቂት ነዉ ያለው የተባለው ነገር” ላለው ይጨምርለታል በሚለው ውስጥ የሚመደብ የሚበዛ ነገር ይሆናል። ኢየሱስ ስለመክሊት በሰጠው ምሳሌ ውስጥ ይህን ሐሳብ ሲያስረግጥ እናገኛለን። ለማትረፍ ወጥተን ቢከስር እንኳን፣ አፋችንን ሞልተን አለኝ ልንለው የምንችለውን ነገር አውጥተን ጥቅም ላይ ያዋልነው መክሊትን ብቻ ነው። በትርፍ ይሁን በኪሳራ እንዲያድግ ከማድረግ ይልቅ ከእንቅብ በታች ሸሽገን አለን ብለን የምንኮራበት ነገር የቱንም ያህል ብዙ ቢሆን የሚቆጠረው ከሌለው ያለው እንኳን ይወሰድበታል ከሚለው ጥቂት ነገር ጋር ነው። እናም ከእኛ ይወሰዳል። ድንገት ስንባንን እንዳጣነው እስክናውቅ ድረስ ቀስ እያለ ከአይናችን ይሰወራል። ምናልባትም ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ ከሸሸግንበት ስንፈልገው ላይመለስ ሄዷል።

እስቲ ይህን መርህ ወደ እኛ ሕይወት አምጥተን እንይ። አጭር ወይም እረጅም ሊሆን ይችላል። ዞር ብለን በትዝታ የራሳችንን ሕይወት ብንቃኝ ያለን የሚመስሉን ነገር ግን ያልነበሩን እና ከኛ የተወሰዱ ብዙ ነገሮች አሉ። በርግጥ አንዳንዶቹ የጠፉት በእጣፈንታ የሕይወት ውስንነት ባመጣው ምክንያት ነው። ስለሌሎች ነገሮች እድገት እና መሻሻል ብለን ትኩረት እና ጊዜ በማጣት የጠፋ ነገሮች አሉ። በልጅነታችን ሁላችንም የልጅ ትሁት እና ቅን ልብ ተሰጥቶን ነበር። ክፋ ደግ ያለማወቅ። ያ የልጅነት ቅንነት፣ ክፋ እና ደግ አለማወቅ የሚያገለግል እና የሚያድግ ነገር አይደለም። በአዕምሮ ሆነ በአካል እያደግን መሄድ የምንችለው ይህን የልጅነት ክፋ እና ደግ ያለማወቅ ልብ መስዋዕት በማድረግ ነው።

እንደሱም ሆኖ እንኳን አንዳንድ ጊዜ ምነው ክፋ እና ደግ ወደማላውቅበት ልጅነቴ በተመለስኩ የሚል ምኞት ያድርብናል። ግን አይመለስም ሔዷል። ልጅነት ተሸሯል። በወጣትነታችን የነበረን ግለት እና ለብዙ ነገሮች የሰነቅነው ህልም ነበር። በወጣትነት ትኩስ ጉልበት እና ዓላሚነት ተሰጥቶን ነበር። ነገር ግን በወጣትነታችን ለሁሉም ነገር ያለን ከፍተኛ የሆነ መነሳሳት አገልግሎት ላይ የሚውል እና የሚያድግ ነገር አይደለም። አይጨምርም። ለብዙ ነገሮች የነበረንን መነሳሳት እየተገራ ሔዶ ለጥቂት ነገር ብቻ ይሆናል። ለጥቂቱ ዕድገት ብዙውን ነገር እንሰዋለን። እነዛ ጥቂት ነገሮችንም በግለት ሳይሆን በስክነት እናደርገዋለን። እንዲህ አይነት መስዋዕትነት ሳንከፍል የሚመጣ ብስለት የለም። ነገር ግን አሁንም ቢሆን በወጣትነቴ እንደ ጀመርኩት በዚህ መንገድ ቀጥዬ ቢሆን፣ እነዚህን ነገሮች ለምን ተውኳቸው፣ ለምን

ይህን አደረግኩ፣ ያን ለምን አልሰራሁም በሚል ባባከናቸው እድሎች የመቆጨት ስሜት ሰውነታችን ይወረራል። የልጅነት የዋህ ልብና የወጣትነት ትኩስ ፍላጎት ነበረን፤ ላለው ይጨመርለታል በሚለው ውስጥ የሚካተት ነገር ስላልነበረ ኖሮን የነበረ ነገር ቢሆንም እልነበረንም። እንደ ጠዋት ጤዛ የሚጠፋ ነገር ነበር። ሕይወት እራሷ እነዚህ ነገሮች ከእኛ እንዲወሰዱ ግድ ትላለች። እነዚህን ነገሮች ይዞ ወደ ቀጣዩ የእድገት ደረጃ መሄድ አይቻልም ነበረና የሕይወት ሕግ ከውስጣችን አጠፋው።

ሌሎቻችን ደግሞ ሙዚቃ፣ ግጥም፣ ታላላቅ የሥነጽሑፍ ሥራዎች እና ድራማ በቀን ተቀን ውሏችን ውስጥ የማይጠፉ ምግባችን ነበር። የነፍሳችን ረሃብና ጥም የሚረካው በነዚህ ሥራዎች ውስጥ ነበር። የሕይወታችንን ምርጡን ዘመን ከእነዚህ ሥራዎች ጋር በመቆራኘት አሳለፈናል። ለራሳችን በእነዚህ ሥራዎች አማካኝነት ተለምደዊዉን የአኗኗር ሂደት የተሻገረ አስደሳች ህይወት ፈጥረን ነበር። ይህንን የመሰለ የሕይወት ልምምድ ነበረን ግን ደግሞ አሁን ከእንደዛ አይነት አኗኗር ከራቅን ዓመታት ነጉደዋል። በዘላቂነት በሕይወታችን ውስጥ እንዲሰፋ እና እንዲያድግ አልፈቀድንም። ለእነዚያ የጥበብ ሥራዎች የነበረን ፍቅር ከሞት የበረታ አልነበረም። እንዲሁ ደስታ የሚሰጠን ነገር ብቻ ነበር። ለነዛ ነገሮች የነበረን ፍቅር ሁሉን ነገር መስዋዕት እስከማድረግ የደረሰ ስላልነበረ ጠፋ። ስለዚህም ከእኛ ተወሰደ።

ብዙ ሰዎች በሕይወታቸው አንድ ወቅት ነገን ለመኖር እንዲጓጉ የሚያደርጋቸው ገፊ ሀይል የ አጽናፈ ዓለሙን እንቆቅልሽ ለመፍታት እና እውነትን ለመፈለግ እንደነበር ያስታውሳሉ። ወደ ኮሌጅ እና ዩኒቨርሲቲ ጥሩ ሥራ ለማግኘት፣ ከፍተኛ ደሞዝተኛ ለመሆን፣ በማሕበራዊ እና በኢኮኖሚ የክብር ስፍራ ለመያዝ ሳይሆን ለእውቀት በነበራቸው እጅግ ከፍ ያለ ጥማት ነበር። የሚያድግ፣ የሚበዛ፣ እና እለት በዕለት እየጨመረ የሚሄድ ነገር ነበራቸው። ነገር ግን ያንን ለማሳካት የሚያስፈልገው የነበረው መሻት “ውሃ ልጠጣ፥ ወይስ ሻይ ልጠጣ”ብሎ ከማማረጥ የዘለለ መሻት አልነበረም። እንደጥሩ ገበሬ አረሙን እየነቀሉ እና የዘሩትን ውሀ እያጠጡ በማሳደጉ ላይ ተገቢውን ያህል ሥራ ባለመሥራታቸው የነበራቸው የእውቀት ርሀብ ተክሉ ደረቀ። የነበራቸው ያቺ ጥቂት ነገርም ከነርሱ ተወሰደች። የተገኘውን ዕድል መጠቀምና ለእውነት ቸልተኛ መሆን፥ አንድን ነገር በጥልቀት መርምረን ለማወቅ የነበረን ስፍራ ወሰደ። ለእውነት የነበራቸውን ፍቅር አሽቀንጥረው በመጣላቸው አንዳንድ ገዜም ቢሆንም እንኳን ትክክለኛ

ነገር አይደለም ያደረኩት በሚል ስብራት ልባቸው መታመሙ አልቀረም። አንድ ጊዜ ከሕይወታቸው ጓዛን ጠቅልሎ እንዲወጣ የገፈተሩት እውነትን የመውደድ ልብ ዳግም ተመልሶ እንደማይመጣ ተረድተዋል።

ከሌላ ሰው ጋር ያለን ጥልቅ የሆነ ግንኙነት ትኩረት፣ ጊዜ እና ዋጋ መክፈል እንደሚያስፈልገው ጠንቅቀን እናውቃለን፤ አለበለዚያ እርስ በርስ ያለን ፍቅር አይዘልቅም። እና አንድ ጊዜ ያ ጥልቅ ግንኙነት ከተበላሸ መልሰን ልንይዘው አንችልም። ይህም አንዱ ለቁጥር የሚያታክቱ የሰው ልጅ አሳዛኝ ክስተቶች መነሻ የሆነው "ያለውን" ና "የሌለው" መሆን የሚታይበት ቅርፅ ነው። ሁላችንም በዚህ ውስጥ አልፈን ወይ በሌላ መንገድ እናውቀዋለን።

እና ደግሞ "ያለውና የሌለው" ከምንላቸው ነገሮች እጅግ መሠረታዊ የምንለው አንድ ነገር አለ። ያም መሠረታዊ "ያለውና የሌለው" አይነት "አለን ካልን የሚኖረን እግዚአብሔር ነው፥ ከሌለን የማይኖረን እግዚአብሔር" ነው። ምናልባት በልጅነታችን ወቅት፣ ምናልባት እድሜያችን ከፍ እስካለበት ጊዜ ከእግዚአብሔር ጋር የነበረን ሕብረት እጅግ ጠንካራ የነበረ ይሆናል። ህልውናው ከምንም ነገር በላይ ይሰማን የነበረበት ወቅትም እንደነበር እናስታውሳለን። ሁለንተናችን በመንፈሱ ህልውና የነበረበት፣ ልባችንን በፊቱ በፀሎት ያፈሰስንበትን፣ በቃሉ፣ በዝማሪ እና በተቀደሰ ስፍራ ከቅዱሱ ጋር እንጓደድ የነበረበትን የሕይወታችንን ወቅቶች በደንብ እናስታውስ ይሆናል። ከእግዚአብሔር ጋር ጥልቅ ሕብረት ነበረን። አሁን ግን ከእኛ ተወስዷል። ያንን ሕብረት በማሳደጉ ላይ ስኬታማ አልነበርንም እናም ቀስ በቀስ ከሕይወታችን ተነነ። የነበረችን ያቺ ጥቂት ነገር ያልነበረች ሆነች። "እንዲህ አልነበርኩም ዛሬ ግን ሆኛለሁ" የሚል ቁጭትን ብቻ በውስጣችን ትታ ሄደች። ቀስ በቀስ ደግሞ ግድየለሽነት፣ ሣር ቅጠሉን የሚረግም ኩናኝነት፣ እና ለእግዚአብሔር ለሆነ ነገር ባዕድነት ሕይወታችንን ወረረው። ይህ የሆነው ግን የሃይማኖታችንን አካሄድና ባህል በመጠራጠር የመጣ አይደለም። የሃይማኖትን አካሄድና ባህል መጠራጠር በእግዚአብሔር ነገር ከበለፀገ ሕይወት የሚገኝ ነገር ነው። ነገር ግን በአንድ ወቅት ለኛ የሞትና የሕይወት ጉዳይ ከነበረው ነገር ጀርባችንን ሰጥተን ዞር ስላልን ነው።

እነዚህ ሀሳቦች ከመጀመሪያው ረድፍ የሚቀመጡ የኢ እኩልነትን እንቆቅልሽ ለመረዳት የምንጓዝባቸው መንገዶች ናቸው። አንደኛው ላላቸው ለእነርሱ ይጨመራል የሚለው ነው። ነገር ግን አለኝ የሚሉት ነገር በእርግጠኝነት በቦታው እንዳለ ማሳየት መቻል አለባቸው። ይህም ማለት አለኝ የሚሉት ነገር

እየተጠቀሙበት እና እንዲያድግ እያደረጉት ከሆነ ብቻ አለኝ ማለት ይችላሉ። እናም ይጨመርላቸዋል። ኖሮ ጥቅም ላይ የማይውል እና የማያድግ ነገር ቢኖርም እንደሌለ ይቆጠራል።

## 2.

ነገር ግን አሁንም ቢሆን ኢ-እኩልነት ለምን ኖረ እና እንዴትስ ይፈታል የሚለውን ጥያቄ አልፈታንም። ነገር ግን ለጊዜው ይህን ጥያቄ እየጠየቅን እንቆያለን። አንዳንዶቻችን ገና ከማለዳ፣ ሕይወትን “ሀ” ብለን ከጀመርንበት፣ “በመክሊት ማትረፍ ወይም መክሰር” የሚባል ነገር ከማይታሰብበት ከልጅነታችን ወራቶች ጀምሮ፥ ሌሎች በእጦት ቀምበር ታስረው ባሉበት፥ የሞላልን እንዴት ሆንን፣ እንዴት ብዙ ተቀበልን? አንደኛው አገልጋይ አምስት መክሊት፣ ሁለተኛው ሁለት፣ ሦስተኛው አንድ መክሊት ለምን ይቀበላል? ለምንድነው አንድ ሰው እጅግ ጥልቅ በሆነ ድህነት ውስጥ፣ ሌላው ደግሞ በተትረፈረፈ ብልጽግና ውስጥ የተወለደው? ለእነዚህ ጥያቄዎች ብዙ ከተሰጠው ብዙ ይጠበቃል፤ ጥቂት ከተሰጠው ጥቂት ይጠበቃል የሚለው መልስ በቂ አይደለም። ምናልባት መልስ ካገኘንለት ብለን የምናወጣው እና ምናወርደው የኢ እኩልነት (እኩል አለመሆን) ጥያቄ መነሻው፥ በውጫዊ እና በውስጣዊ ነገር፥ ከስር መሠረት የነበረ ኢ እኩልነት (እኩልነት አለመሆን) ነው።

አንደኛው ሰው በመሆኑ ብቻ ብዙ ነገር ሊያደርግ የሚችልበት ሀይል ሲሰጠው፥ ሌላኛው ያልተሰጠው ለምንድነው? አንደኛው ብዙ ሊጠበቅበት ይችላል የምንለው፥ ብዙ እንዲጠበቅበት ያደረገው ነገር ለምን ተሰጠው፥ ጥቂት ሊጠበቅበት ይችላል የምንለውስ እንዲያ እንዲሆን፥ ለምን ጥቂት ተሰጠው? ይህንን ችግር በግለሰቦች መካከል ባለ ኢ እኩልነት (እኩል ለመሆን) ጋር ብቻ ሳይሆን በመደብ፣ በዘርና ዘር እና በሐገሮች መካከል ጋር በተገናኘ ከተመለከትን፥ በፖለቲካው መስክ ባለው የኢ እኩልነት (እኩል አለመሆን) ጥያቄ፥ እናም ከዚህም ጋር ተያይዞ ይህን ኢ እኩልነት (እኩል አለመሆን) ለማጥፋት ሰዎች የሞከሯቸውን መንገዶች ጨምሮ አብሮ ይነሳል።

በአብዛኛው በየጊዜው ለተነሡ አብዮቶች እና ለተቀሰቀሱ ጦርነቶች ዋናው ገፊ ምክንያት የኢ እኩልነትን እንቆቅልሽ ለመፍታት (እኩልነትን ለማምጣት) ያለው ፈቃደኝነት ነው። ነገር ግን ጦርነትም ሆነ አብዮት ለዚህ እንቆቅልሽ መልስ

መስጠት አይችልም። ምንም እንኳን ወደፊት በሂደት አብዛኛው ማሕበራዊ ኢ እኩልነት በእኩልነት ቁጥጥር ውስጥ ይወድቃል ብለን ብናስብም፣ እነዚህ ሦስት እውነታዎች በሁሉም ቦታና በማንኛውም ዘመን እንዳሉ ሆነው ይቆያሉ። አንዳች ሊለውጣቸው የሚችል ነገር አይመጣም። አንደኛው የችሎታ ልዩነት ነው። በሰዎች መካከል፣ በአካልና በአዕምሮ ችሎታ እኩል አለመሆን አለ። ሁለተኛው ነፃነት እና እጣፈንታ በሚፈጥሩት ሁኔታዎች ምክንያት የተፈጠረ ኢ እኩልነት (እኩል አለመሆን) አለ። በአንደኛው ግለሰብ ቸልተኝነትና ስንፍና ሳይሆን ነገር ግን የሚሆነውን ለመሆን የሚያስፈልገው ነጻነት ስላልነበረ እና እጣ ፈንታ አጋጣሚዎችን ስለከለከለው ከሌላኛው ሰው እኩል መሆን አልቻለም።

እንዲህ አይነት ሁኔታ ሁሌም ይኖራል። ሦስተኛውና የመጨረሻው ከእኛ በፊት የነበሩ አያት ቅድማያቶቻችን በአንድም በሌላ መንገድ፣ እኩልነትን የሚያጣጥሙበት ዕድል ሊያገኙ ባለመቻላቸው የተነሳ፣ ዛሬ እኛ ያለንበት ቦታ ድረስ የመጣ ከሌላው ጋራ በእኩልነት ለመቆም ያለመቻል፣ የፍትሕ ኢ እኩልነት (እኩል ያለመሆን) እውነታ መኖር ነው። ይህ የመጨረሻው የኢ እኩልነት (እኩል ያለመሆን) እውነታ፣ ከሁሉም የከፋና መፍትሄ ለማግኘትም የሚያደግት አይነት ነው። ዛሬ እኛ በሰራነው ተገቢ ያልሆነ ወይንም የዛሬ ሁኔታ በፈጠረው ችግር ምክንያት ሳይሆን፣ በቀደሙ ትውልዶች ተበላሽቶ እየተንከባለለ እኛ ዘንድ የደረሰ ስለሆነ፣ ያን እውነታ ተቀብለን ለመፍታት እንጥራለን እንጂ እንዴት እንዲህ ሊሆን ቻለ ብለን ለመሟገት አንችልም። አንድ በጭራሽ ማድረግ የሌለብን ነገር አለ! በዛሬ ውስጥ እጅግ ጥልቅ የሆነ እና የብዙዎችን ሕይወት ያመሳቀለ ችግር እየተመለከትን፣ ዛሬ የፈለገው ነገር ቢሆን ምንም ማለት አይደለም፣ ነገ በጎ ይሆናል ወደሚል፣ ራስን በማሞኘት እና ከተጨባጩ ሀቅ የተፋታ ሰው በማድረግ፣ ራሳችንን ቅዠት ውስጥ መክተት የለብንም። መኖር ካለብንም መኖር ያለብን አሁን ነው። ዛሬ ብለን በምንጠራው ቀን ውስጥ ያለውን ሕይወት መኖር አለብን። በቻልነው አቅም አሁን እና ዛሬ በሕይወት ውስጥ ያለውን የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ (እኩል ተጠቃሚ ያለመሆን ችግር) ለመፍታት መታገል ይገባናል።

ከብዙኀኑ ጋር የምንደመር ቁጥር ብቻ ሳንሆን ከሌላው የተለየን ግለሰብ መሆናችን፣ ሰው ሆነን የመፈጠራችን ክብር ነው። ይህ ማንነት ለእኛ ተሰጥቶናል እናም ጥቅም ላይ መዋል አለበት ደግሞ ስፍራ ሊሰጠው የተገባ ነው። አሁን በዘመናችን ትልቅ ተግዳሮት በሆነው መንጋነት፤ በተመሳሳሎሻዊ የተበከለ ውሃ ውስጥ ተወርውሮ መስጠም የለበትም። ከአንድ ሰው የሚጠበቀው የእያንዳንዱ

ሰው ግለሰብነት እና “ልዩ የመሆን” መብት ለመንጠቅ የሚደረግ ሙከራ መቆም ስላለበት ለዚህ የራሱን ሚና መጫወት ነው። ነገር ግን አንድ ሰዉ “ሰዎች በተፈጥሮቸው ልዩ ልዩ ፀጋ አላቸው፣ የኢ እንቆቅልሽ መፍትሄ ደግሞ ይህን የልዩነት ፀጋ መቀበል ነው” ወደሚል ድንዛዜ ውስጥ መግባት የለበትም። እንደ አለመታደል ሆኖ፣ ስር ሰዶ ያለውን ማሕበራዊና ፖለቲካዊ ኢ እኩልነትን (ሁሉንም እድሎች በእኩልነት አለማግኘት)፣ በተፈጥሮ ከተሰጠን ልዩ ልዩ ጸጋ ጋራ አንድ አይነት አድርጎ በተሳሳተ መንገድ መረዳት በብዙሃኑ ዘንድ እንዳለ የተገነዘቡ፣ በታሪክ ቅብብሎሽ የተመቻቸላቸውን መብትና ጥቅም ላለማሥነካት፣ የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ መፍትሔ እንደሌለው፣ ክፍና ዝቅ ማለት በተፈጥሮ ከማንነት ጋር ተያይዞ የሚመጣ እንደሆነ አድርገው የሚያቀርቡ ግራ ዘመም የማሕበራዊና የፖለቲካ ሊሂቃን አሉ።

“ዛሬ የማይቻል ነገር ነው። ነገር ግን ነገ ከነገ ወዲያ ሁሉም ሰው እኩል የሚሆንበት፣ ኢ እኩልነት የሚወገድበት ወቅት ይመጣል” ብለው እንደሚያምኑት እንደነዚያኛዎቹ እነዚህም፣ ጠቢብና ብልጥ እንደሆኑ ቢሰማቸው “ሞኝ እና በቅዠት ዓለም” የሚኖሩ ናቸው። ሆስፒታሎችን፣ የአዕምሮ ህሙማን መንከባከቢያ ስፍራዎችን፣ እስርቤቶችን፣ ደግሞም በዝቅተኛ ክፍያ እና ጥንቃቄ ማድረጊያ ያልተሟላበት የሥራ ቦታዎችን፣ የጦር ሰፈሮችን፣ በርሃብ እየተሰቃዩ ያሉ ሰዎችን፣ የቤተሰብ መፈራረስ፣ እና ከዚህም የከፋ ምስቅልቅል ሁኔታዎችን በየእለቱ ለሚመለከት እና በጆሮዎቹ የሚሰማ ሰው፣ “እጅግ ጎጂ እና ተፈጥሮአዊ ያልሆነውን የኢ እኩልነት እንቆቅልሽን”፣ እንደ ግለሰብም ይሁን ማሕበረ ሰብ እጅግ ጠቃሚ እና ተፈጥሮአዊ ከሆነው “ሰዎች በተፈጥሮ ፀጋ ከሌላው ይለያያሉ” ከሚለው ጋር አንድ አይነት አድርጎ በተሳሳተ መንገድ የሚረዳ ሰው ከዚህ በሽታው ሊፈወስ ይገባል። ’ኢ እኩልነትን” ከመቀበል ውጪ ምን ምርጫ አለ’ ከሚል ከንቱ ራስን የማፅናናት በሽታ መፈወስ አለበት።

# 3.

እስቲ አሁን ደግሞ የ" ኢ እኩልነት" (እኩል ያለመሆንን) እንቆቅልሽ ጠልቀን ለመፈተሽ የምናደርገው ሙከራ ለምን አንዳንዶቻችን የተሰጠንን ነገር በመጠቀም ባለን ነገር ላይ ጨመርን፣ ሌሎች ግን ለምን ያን ባለማድረጋቸው የተሰጣቸው መክሊት ተወሰደባቸው? የሚል ጥያቄ በመጠየቅ ወደ ሶስተኛ ደረጃ እናሸግረው። ለምንድነው እግዚአብሔር ለነብዩ በብሉይ ኪዳን ሲናገር ይህ ሕዝብ ለመለኮታዊው መልእክት ጆሮው እንዳይሰማ እና አይኑ እንዳያይ ተደርጓል ብሎ ለምን አለው? እና አንዳንዶች ነፃነታቸውን በኃላፊነት ተጠቅመው ማድረግ ያለባቸውን ሲያደርጉ፤ ሌሎች ደግሞ በራሳቸው በደል ምክንያት ለውድቀት ተዳርገዋል የሚለው መልስ በቂ ነውን? ከላይ ከላይ ሲመለከቱት ግልፅ ቢመስልም፥ እንዲህ አይነት መልስ አጥጋቢነቱ የሚሆነው በራሳችን ላይ ስንተገብረው ብቻ ነው። እያንዳንዳችን ለተሰጠን መክሊት መጨመር ወይም መጥፋት ተጠያቂ ራሳችን እንደሆንን መቀበል አለብን። ላጣነው ወይም ለጠፋብን ነገር ከኛ በስተቀር ማንኛውም አካል ወይም የትኛውም ነገር ተጠያቂ ማድረግ እንደማይገባን ኅሊናችን ራሱ ይመሰክራል።

ነገር ግን ዘግናኝ በሆነ የችግር ማዕበል የሚናጡትን ሌሎችን ሰዎችን በተመለከተ ይህ መልስ በቂ ሊሆን አይችልም። በቃል ሊነገር በሚከብድ ጭንቀት ውስጥ እያለፈ ያለ ሰው፥ ለእርዳታ ወደ እኛ ቢመጣ "እባክህን የተሰጠህን መክሊት ተጠቀምበት እንጂ፥ ለምንድን ነው እንዲህ የምትሆነው?!' ማለት አንችልም። እንደዛ መመለስ የተገባ አይደለም። ወደ እኛ የመጣበት ብቸኛ ምክንያትም መደረግ የሚገባውን ማድረግ ባለመቻሉ እኮ ነው!! ሆነው ያሉትን በመሆናቸውም ምክንያት በትልቅ ተስፋ መቁረጥ ውስጥ ያሉ ሰዎችን "እስቲ ራስህን ለውጥ" ማለት አንችልም። "ተስፋ የሚያስቆርጥ ሁኔታ ውስጥ" መሆን ማለት፥ የማንፈልገውን ማንነት ከራሳችን ላይ አሽቀንጥረን ለመጣል ያለመቻል ሁኔታ ውስጥ መሆን ማለት ነው። በዘሪያቸው ያለውን ክፉ ተፅዕኖ ማሸነፍ ባለመቻላቸው፥ ወንጀል እና ሰቆቃ የሞላበት ሕይወት ውስጥ የተዘፈቁ ሰዎችን "ከዚህ ነገር ለመውጣት ጠንካራ ልትሆን ይገባል! ከበረታህ ከዚህ ትወጣለህ" ልንል አንችልም። በዘር ማንዘር ውርስ ወይም ባደጉበት አካባቢያዊ ምክንያት የሚገጥማቸውን ተግዳሮት የሚያሸንፉበት ጥንካሬ የላቸውም። ጠንካራ መሆን ስላልቻሉ እንጂ መፍትሄው ጠንካራነት እንደሆነ አጥተውትም አይደለም። አሁን ከየት ያምጡት! በእርግጥ እነርሱም ልክ እንደ እኛ ሰዎች ናቸው፥ ነፃነትም ተሰጥቷቸው ነበር። ነገር ግን እጣፈንታ በአመጣባቸው ሁኔታ አግር ስር ወድቀው

ተገኙ። እጣፈንታ መንገዳቸውን ወሰነ።

ሌላው ደግሞ፥ ትላንትና በወሰኑት ውሳኔ እና ባደረጉት ድርጊት ምክንየት ዛሬ ላሉበት ሁኔታ ተጠያቂ እነርሱ እንደሆኑ መፍረድ ሆነ፥ በሌላ መልኩ ደግሞ 'እንድን ሰው፥ "አንተ ሳትሆን ሁኔታዎች ናቸው እንደዚህ ያደረጉህ፥ ምንም ማድረግ አትችልም፥ የሚያስጠይቅ ጉዳየ አደይደለም፥ ብለን መተማመኛ መስጠትም የእኛ መብት አይደለም። ፈራጅ አይደለንም፥ ለመፍረድ አንችልም። ሁልጊዜ በራሳችን ላይ ስንፈርድ እንኳን፥ ስለእኛ የሆነውን በትክክል ማወቅ የማንችል ፍጥረቶች ስለሆንን ፍርዳችን ፍጹምና ትክክለኛ እንዳልሆነ መርሳት የለብንም። ምክንየቱም እኛን ጨምሮ ሁላችንም ከዘላለም ፍርድ በታች ነን። ስለ ሁላችን ትክክለኛውን ፍርድ የሚሰጥ አለ። በዛ የዘላለም የፍርድ ወንበር ስር የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ (እኩል ያለመሆን ጥያቄ) መልስ ያገኛል። ነገር ግን መልሱ ያለው ከእኛ ዘንድ አይደለም። ስላለንበት "መዉጫ መግቢያ ም" ስለሌላው የሕይወት አጣብቂኝ የግድ ጥያቄ መጠየቅ ይኖርብናል። አዕምሯችንን የሚያታግሱ እና ውስጣችንን እረፍት የሚነሱ ጥያቄዎችን መጠየቅ አለብን፥ ለምንድነው እንዲህ ያለ መከራ ውስጥ የገቡት? እንዴት እኛ ምንም አልሆንም? አጠገባችን፣ ቅርባችን ሆነው በስቃይ ውስጥ ለሚያልፋት ደግሞ ይህንን ጥያቄ እንጠይቃለን፥ በእነርሱ ሕይወት ውስጥ ለደረሰው መከራ የሆነ ያህል ተጠያቂ ነን? ተጠያቂ ልንሆን እንችላለን ነገር ግን የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ ጥፋተኛነትን በማመን ባለማመን አይፈታም። ሃላፊነት የሚሰማውና ከራሱ ድንበር ተሻግሮ የሚያስብ ኅሊና ያለው ደግሞ በተጨማሪነት፥ እኛ በምቾትና በድሎት ውስጥ ስንኖር፥ እነዚያ በዚያ እርቀው ያሉ ለምን በስቃይ ውስጥ ይኖራሉ ብሎ ይጠይቃል። ለምን ተቸገሩ? ለምን አልተቸገርንም?

የራሴን ልጅ ጨምሮ፥ በሚሊዮን የሚቆጠሩ በአጭር የተቀጩ ህጻናት ፥ ሞት ከጨቅላነታቸው የወሰዳቸው ለምንድነው? ለምንድነው ልጄ፥ ወይም የሌላ ሰው ልጅ፥ ከመወለዱ ጀምሮ የአእምሮ ወይም የአካል ጉዳተኛ የሆነው? ጓደኛዬ ወይም ዘመዴ፣ ወይም የሌላ ሰው ወዳጅ ወይም ዘመድ፥ የአእምሮው መታወክ የገጠመው ለምንድነው? በዚህም የአዕመሮ መታወክ ምክንየት እንደሰው ህልሙን መኖር እና ማድረግ የሚፈልገውን በነፃነት ማድረግ ያልቻለው ለምንድነው? ከሰው በታች ለምን ሆነ? ወንድ ልጄ ወይም ሴት ልጄ ብዙ ተሰጥኦ እና አቅም የነበራቸው ቢሆንም መክሊታቸውን ያባከኑት እና መክሊታቸውን ጥለው ባዶአቸውን የቀሩት ለምንድነው? በእኔም ይሁን በሌላ በማንኛውም ወላጅ ላይ እንደዚህ አይነት ነገር የሚደርሰው ለምንድነው? ለምንድን ነው የዚህች ሴት ልጅ፣

ወይም የዚያ ወንድ ልጅ አእምሮ ውስጥ ያለ የመፍጠር ኀይል፥ በአምባገነን አባት ወይም መፈናፈኛ በማትሰጥ እናት ምክንያት እንደማይሆን የሆነው ለምንድን ነው?

እነዚህ ከላይ ያነሳናቸው ጥያቄዎች፥ እኛ ካለንበት ጋር የሚያገናኛቸው ነገር የለም። አሁን ይህ ለምን በእኔ ላይ ሆነ? ብለን እየጠየቅን ያለበት ጊዜ አይደለም። እግዚአብሔር አስቀድሞ በመከራ ውስጥ እንዲገራ እና ቀጥሎ ከእርሱ ጋራ ስር የሰደደ ሕብረት እንዲኖረው አድርጎ የኢዮብን ጥያቄ አልመለሰም። መለኮታዊ ፍትሕ ወዴት ነው፣ መለኮታዊ ፍቅር ወዴት ነው? የምንልበት የቆየ እና አንገብጋቢ ጥያቄ እያቀረብን አይደለም። አሁን የምንጠይቀው ከሞላ ጎደል ተቃራኒ ጥያቄ ነው፦ እኔ ለምን በዚህ ሁኔታ ውስጥ ሳልገባ ሌላው ለምን፤ በእኔ ያልደረሰ በሌላው ላይ እንዴት ደረሰ? መለኮታዊ መልስ ለመቀበል ኢዮብ የነበረው አቅም ባልነበራቸው ሰፍር ቁጥር በሌላቸው ሌሎች ሰዎች ላይ ለምን ደረሰ?። ኢየሱስ ራሱ የተጠሩ ብዙዎች ናቸው ነገር ግን የተመረጡ ጥቂቶች ናቸው ለምን አለ? እንደገና ደግሞ ይህ የሰው ልጆች ያሉበት የሕይወት አጣብቂኝ ነው በማለት አስቀመጠ እንጂ ለጥያቄው ምላሽ አልሰጠም። ከሰው ልጆች አብዛኛዎቹን ከመለኮታዊ ሕብረት አውጥቶ የሚጥልና በኋላም ለተስፋ መቁረጥ እና ራስን በራስ ወደማጥፋት የሚዳርግ ሆኖ ሳለ፥ ጥያቄ መጠየቃችንን እናቁም እና መለኮታዊውን ፍርድ በትህትና እንቀበል? ፍርድ በፍቅር ላይ ለዘላለም ያገኘዉን አሸናፊነት እንቀበል? አንችልም። ማንም የሰው ልጅ ይህን ሊቀበል አይችልም። ምናልባት እግዚአብሔር በምህረት ሳይሆን በፍርድ ስለ መገለጡ ስብከት ሊሰብክ እና ሌላውን በስብከቱ ሊያስፈራራ የሚችል ይኖራል። ነገር ግን ይህ ዓይነቱ ስብከት ሲሰብክ በፍፁም እርግጠኝነት ውስጥ ሆኖ እርሱም በዚያ ፍርድ ውስጥ እንደወደቀ፥ እና ከመለኮት ህልውና ወጥቶ ለዘላለም እንደ ተጣለ ተቀብሎ ካልሆነ፥ ስብከቱና ማስፈራራቱ እውነተኛ ሳይሆን ራስን በራስ ማታለል ነው። እርሱ ራሱ ለዘላለም ከምህረቱ ደጅ ውጪ ተጥሎ ማየት የሚችል ማን ነው?

እስካሁን በተመለከትነው ውስጥ ብዙ ነገሮችን ብንዳስስም፥ የተመለከትናቸው ነገሮች በዋነኛነት በሰው ልጆች መካከል ያለውን የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ መፍታት ሳይሆን፥ ስለነገሩ መያዝ ስላለብን ምልከታ አስተምህሮ የሚያቀርብ ብቻ በመሆኑ፥ ከክርስትና አስተሳሰብ ውጪ ድንበር በመሻገር "ይህ አሁን በምድር የምንኖረው ኑሮ የዘላለም እጣፈንታችንን የሚወሰን አይደለም" በማለት ከእኛ ለየት ያለ እይታ ያላቸውን መስማት ይኖርብን ይሆን? ይህን የተለየ አስተሳሰብ የሚያራምዱት እንደሚነግሩን ከሆነ፥ አስቀድመን አሁን ባለን አካል

ሥጋ ውስጥ ከመሆናችን በፊት፥ በሌላ ዓይነት ነገር ውስጥ እንኖር ነበር፥ ወደፊት የምንኖረው ደግሞ አሁን ከምንኖረው ኑሮ የሚያገኘውን ትርፍና ኪሳራ ይወስድና በዛ በመመስረት፥ አሁን የለበሥነውን አካል ስጋ የሚመስል፥ ከሞት በኋላ ተመልሰን የምንኖረው ሌላ ሕይወት አለ። (ይህ ከላይ የተጠቀሰው አስተሳሰብ በቡዲሂዝም እና መሰል ሃይማኖቶች ውስጥ የሚገኝ አስተሳሰብ ሲሆን፥ ዋነኛ አስተምህሮው አሁን ያለንበት አካል ሲሞት፥ ተመልሰን በሌላ አካል እንወለዳለን የሚል ነው። ለምሳሌ ደጋግመን ስንወለድ መልካም ነገር እያጠራቀምን፣ መጥፎውን እየቀነስን ስለምንሄድ ወይም የምንሄድ ከሆነ የሆነው ወቅት ላይ ፍፃምነት ላይ ስንደርስ፥ ደጋግሞ የመወለድን ሂደት በማስቆም ዘላለማዊነትን እንቀዳጃለን የሚል ነው) ይህ አስተምህሮ እውነተኛነቱን አምነው የሚከተሉት ሰዎች ያሉት አስተምህሮ ነው። ደግሞም ሙሉ በሙሉ ክርስትና የማያውቀው እንግዳ ትምህርትም አይደለም። ነገር ግን "ቀድሞ" በሚባለው ሕይወት ውስጥ ሆነ፥ "ወደፊት" በሚመጣው ሕይወት "ማን እንደነበርን" እና "እንደሆንን" ስለማናውቅ፥ ማወቅም ስለማንችል፤ ከቀድሞ ሕይወት አሁን፥ ከአሁን ወደፊት ደጋግመን ስንወለድ፥ ከፊተኛው ሕይወት ይልቅ በኋለኛው ሕይወት የተሻለ እየሆነ የመጣው እጣፈንታ የእኛ አይደለም። ምናልባት የሌላ ሊሆን ይችላል። ስለዚህ ይህ አስተምህሮ በሰዎች መካከል ያለ "የኢ እኩልነትን" እንቆቅልሽ ለመፍታት የሚቻለው አይደለም።

በመሠረቱ፥ ከጠቅላላው ፍጥረት ነጥለን፥ ጊዜያዊ እና ዘለዓለማዊ እጣፈንታው ምን ሊሆን ይችላል ብለን ስለ አንድ ነገር ብቻ የምንጠይቀው ጥያቄ ምንም አይነት መልስ አይኖረዉም። አንድ ቀን በጊዜና ዘላለም ውስጥ፥ ፍጥረት ሁሉ በተጠቃለለበት አንድነት፥ በሥጋ ለባሽ የመረዳት አቅም ልክ የሆነ፥ የኢ እኩልነትን እንቆቅልሽ የሚፈታ መልስ ሊኖር ይችላል። "ሥጋ ለባሽ ሊረዳ የሚችለው "መልስ ማለት ግን በሥጋ ለባሽ መካከል ያለ የ"ኢ እኩልነት" እንቆቅልሽ ሙሉ በሙሉ ይወገዳል ማለት ሳይሆን፤ "እንቆቅልሹ ለምን እንቆቅልሽ እንደሆነ የሚያስረዳ ምክንያት አግኝተን መኖር እንችላለን ማለት ነው።

በመጨረሻም ህልውናውን አግኝቶ ከወጣበት እና ዳግም ወደ ሚመለስበት የመለኮት ሕይወት፥ በሰማይ እና በምድር ያለ ፍጥረት ሁሉ በአንድነት ይጠቃለላል። በዚህ በአንድነት የመጠቅለል ሂደት ውስጥ፥ ፍጥረት ሁሉ፥ የሰው ልጅ እና የሰው ልጅ ያልሆነውም፥ ተሳታፊ ነው። በዚህ የመጠቅለል ሂደት ውስጥ አንዱ በሌላኛው ውስጥ፥ ሌላኛው በአንዱ ውስጥ ተሳታፊ ሆነው ስለሚገኙ፥ የተዘበራረቀ ነገር

ሳይሆን ፍፁም አንድ የሆነ ሆኖ ይቀርባል። በጉድለት ውስጥ ያለን በሙላት ውስጥ ባለት፣ በሙላት ዉስጥ ያለን በጉድለት ውስጥ ባለት እንካተታለን። ይህን የፍጥረት ሁሉ አንድነት ባወቅን ጊዜ፣ ከዚህ በፊት ስለ ነገሮች የነበረን እይታ እና መረዳት ሙሉ በሙሉ ይቀየራል። የሌሎች በእጦት ውስጥ የመሆን ተጨባጭ ሀቅ፣ እኛ በእጃችን ላይ ያለን ኀብት የምናይበትን ፀባይ እንድንለውጥ ያደርገናል። "የምፈልገው ነገር ስላለኝ የሚያስጨንቀኝ አንዳች ነገር የለም" ብለን ከተሸሸግንበት የደህንነት ዋስትና ነቅሎ በመውጣት፣ ከሌላቸው ጋራ የሌለን ካላቸው ጋር ያለን መሆናችንን ያስገነዝበናል። ይህ ግንዛቤ ደግሞ ሌሎች ስላሉበት አጣብቂኝ ሁኔታ ለመረዳት፣ ያለንን ለማካፈል፥ በሚያስፈልጋቸው ጊዜ ድጋፍ እንድንሆን እና ከራሳችን አልፈን ለሌሎች እንድንቆረስ ገፊ ምክንያት ይሆነናል።

ሌሎች በሀጢያት፣ በወንጀል፣ እና በመከራ ውስጥ መውደቅ እና እኛ ደግሞ መቆም መቻላችን ከተቀበልነው ፀጋ እንደሆነ እናውቃለን። ይህ የተቀበልነው ፀጋ ስለ እነርሱ ውድቀት ባለን አመለካከት ላይ ለውጥ ያመጣል። ከመመካት እና ከመታበይ ይልቅ፤ እኛም ሰው "ያላየው" "የተሰወረ" በደል እንዳለብን በኛ ያለው ፀጋ እንድናምን ያደርገናል። በተገለጠ ኀጢአት፥ በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት በመከራ ዉስጥ ያሉ ሰዎች እየከፈሉ ያሉት ዋጋ ለእኛም ጭምር ነው እንድንል ያደርገናል። እነርሱ በተግባር ባከናወኑት ወንጀልና ኀጢአት ወይም ባጋጠማቸው መከራ ሲሰቃዩ እኛ ደግሞ በፍጥረት አንድነት ውስጥ ባለን ማሕበርተኝነት ምክንያት አብረናቸው እንሰቃያለን። ይህም ማለት የእኛ ማግኘት፣ ሰላምና ጤና፥ ዕድለኞች እንደሆንን እንዲሰማን የሚያደርግ ነገር ሳይሆን፥ እኛም የሚሰቃየው አካል ሌላ ክፍል እንደሆንን የሚያስገነዝበን ነው። በዚህ ሂደት የአንዱ አካል ያልተጎዳና እና ያልታመመዉ ሌላ ክፍል እንደሆንን እናውቃለን።

ሌሎች ሙሉ ሰው ወደ መሆን ማደግ ሲችሉ ነገር ግን ከስኬት እና ከሞራል እድገት ኋላ መቅረታቸውን መገንዘባችን እኛን እንዴት ሙሉ ሰው ሆነን ለማደግ እንደቻልን ደግመን እንድናስብ ያስገድደናል። ገና በለጋ ዕድሜያቸው የሞቱትን ስናስብ፣ ገና ከልጅነታቸው ወይም በሕይወት ሩጫ መሐል ላይ መልካም ነገር ሁሉ ከእጃቸው የመለጣቸውን ስናስብ ፤ ወደ እኛ የግል ሕይወት እና ጤንነት ይዞት የሚመጣው ነገር አለ። ያም ይዞት የሚመጣው ነገር የማያቋርጥ አደጋ ነው። የእነሱ መሞት አሁን "እኛ ባንሞትም" ሞት በደጅ እንዳለ አውቆ መጨነቅን፣ እኛ "በተረጋጋ ሕይወት" ውስጥ ብንሆንም በእነርሱ ላይ በሆነዉ "የኑሮ መዘበራረቅ" "ነግ በኔ ነው" የሚል አደጋ መጠባበቅን ያመጣል። በሚገጥመን በእያንዳንዱ

የሞት መርዶ “አሁን ባንሞት” እንኳን ከእኛ የሆነ ነገር የሞተ ይሄዳል፤ በየዕለቱ የሆነ መጠን ያህል ከእኛ ላይ እየተነሳ ወደነበርነት ይለወጣል።

ይህ መልስ በቂ ስለሆነ ተረጋግተን መኖር እንችላለን? አዎ እንችላለን። ወደ አዲስ እና ልዩ የሆነ የሕይወት ልምምድ ላለመሄድ ራሳችንን አስረን ካስቀመጥንበት፣ ራሳችንን ነፃ ካወጣን በዛ ነፃ ባወጣንበት ነፃነት ልክ እንችላለን። ነገር ግን ማንም ሰው ከራሱ ነፃ መውጣት አይችልም። ከራሱ ነፃ የሚወጣው በእያንዳንዱ እና በሁሉ ነገር ውስጥ “የህልውናው መገኘት” እንዲሆን በሚፈቅድ ዘለዓለማዊ ሀይል ሲያዝ ነው። ዘለዓለማዊ ሀይል!እኛ የተገኘንበት እና ተመልሰን ወደ እርሱ የምንመለስበት፣ እኛን ለእኛ ከሰጠን እና እኛን ከራሳችን ነፃ የሚያወጣን ዘለዓለማዊ ሀይል! አንድ ሰው ራሱን ነፃ የሚያወጣው በዚህ ኀይል የተያዘ እንደሆነ ብቻ ነው። ያን ጊዜ ራሱን ከራሱ ነፃ ያወጣል። ይህ የክርስትና ትምህርት ዋና መልዕክት እና የመልዕክቱም ታላቅነት ሚስጥር ከዚህ ዘንድ ነው። ይህም እግዚአብሔር በመስቀል ላይ በክርስቶስ በኩል ራሱን እንደገለጠው በመከራችን ተመልካች ሳይሆን ተካፋይ ነው።

እርሱ ከዚህ ዓለም በጨቅላነቱ በሞት ከሄደው ጋር በሞቱ ተካፋይ ነው፣ እርሱ ወንጀለኛው በወንጀሉ በሚከፍለው ፍርድ ውስጥ ተካፋይ ነው፣ በአዕምሮ መታወክ ከሚሰቃዩት ጋር አብሮ ይሰቃያል፣ እርሱ በርሃብ እና በጉስቁልና ውስጥ ካሉት ጋር ይሰቃያል፣ ራሳቸውን በራሳቸው ጥለው ያልተገባ ዋጋ እየከፈሉ ካሉት ጋር እንኳን ዋጋ ይከፍላል። እግዚአብሔር በህልውናው የማይደርስበት የሰው ልጅ የሕይወት ክፍል እና መንገድ አንድም የለም። ከሰው ልጆች ሁሉ ውርደት የከፋው የመስቀል ሞት ውርደት፥ የክርስቶስ መስቀል የሚነግረን ይህን ነው። የኢ እኩልነት (እኩል ያለመሆን) እንቆቅልሽ በመካከላችን ያለው የደረጃ ልዩነት በመጥበቡ እና በመስፋቱ ወይም በሚጠፋበት ልክ መፈታት የሚችል አይደለም። የኢ እኩልነት እንቆቅልሽ የእግዚአብሔር መገኘት በእኛ ሕይወት እና በእያንዳንዱ ፍጥረት ሕይወት ውስጥ በሚሆንበት በዘላለም ውስጥ ብቻ የሚፈታ ጉዳይ ነው። ምንም እንኳን ይህን እንቆቅልሽ ለመፍታት የእኛ ውስን አዕምሮ ሊፈታው ከሚችለው ጣራ በላይ ቢሆንም፣ ነገር ግን የእግዚአብሔር ከምንታመመው ጋር ታማሚ፣ በእጦት ካለነው ጋር በእጦት፣ ከምንፈተነው ጋር በፈተና አብሮን እንደሚሆን እና አብሮን ተሳታፊ የመሆኑ እርግጥ የሆነው እውነታ የኢ እኩልነትን እንቆቅልሽ እንድንቋቋም ብርታት ይሰጠናል።

# 11. የእግዚያብሔር ፍለጋ

*“ያን ጊዜ ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተው ሸሹ።”*

*ማቴዎስ 26፡56*

## 1.

አንድ ቀን ምሽት የባችን “የህማማቱን ወቅት ማቲዎስ እንደተረከው” (Passion according to St. Matthew) የሚለውን መዝሙር እያዳመጥኩ፣ “ከዚያም ደቀ መዛሙርቱ ሁሉ ትተውት ሸሹ።” በሚለው ስንኝ እና በሙዚቃው ውበት ውስጤ ተነክቶ ነበር። ኢየሱስ በመስቀል ላይ የተናገረውን “አምላኬ አምላኬ ለምን ተውከኝ?” የሚለውን ቃል ታሳቢ ያደረገ ስንኝ ነው። በሰዎች የተተወ፣ሰዎች ሁሉ የተውት፥ በእግዚያብሔር እንደተተወ ይሰማዋል፡፡ በእርግጥ ሁሉም ሰዎች ትተውት ሄዱ። ከማንም በላይ ለእርሱ ቅርብ፣ የልብ የሆኑት በጣም እርቀው ሸሹ። ብዙ ጊዜ ኢየሱስ በመስቀል ላይ በተሰቀለበት ወቅት ስላለው ሁኔታ የምንገነዘበው ግንዛቤ ከእውነታው ጋር የሚጋጭ ነው። በአእምሮችን አንድ የሚያምር ሥዕል አለ፡፡  ስለመስቀል ላይ መከራው ስናስብ ወደ አዕምሮአችን የሚመጣው ያ የሥዕል ሥራ ነው። ስዕሉ የኢየሱስ የሚያምር ገላ ፣ በሚያምር እንጨት ላይ ተሰቅሎ፣ በሚስማር የተቸነከሩት እጆቹ ትንሽ ትንሽ ደም እያፈሰሱ፣ እናቱ እና ኢየሱስን ይወደው ነበር የተባለው ደቀመዝሙር እና ሌሎች ሴቶች ከመስቀሉ ስር ተሰባስበው፥ ኢየሱስ በእነርሱ እየተፅናና የሚያሳይ ስዕል ነው። ስለ መስቀል መከራው ስናስብ፥ በአዕምሮችን የሚከሰተው ያ ምስል ነው። እውነታው ግን ከዚህ የተለየ ነበር። ሁሉም ሸሽተውት ነበር። በርግጥ አንዳንድ ሴቶች በቅርብ እርቀት ሆነው ሁኔታውን ለመከታተል ደፍረዋል፤ ሞክረዋል። ሕይወቱ አና ሥራው ያበቃ፣ የተሰበረ በሚመስለው በዛ የመስቀል ላይ የስቃይ ሰዓት ውስጥ አብሮት የነበረው በቃላት የማይገለጥ ብቸኝነቱ ብቻ ነበር።

ስለ እነዚህ ደቀመዛሙርት ምን እና እንዴት እናስብ? መጀመሪያ ወደ

አዕምሮአችን የሚመጣው ጥያቄ ይህ ነው። እንዴት አንተ መሲህ ክርስቶስ ነህ ያሉትን፣ በሰው ልጆች ታሪክ ያልነበረ ወደፊትም የማይኖር አዲስ ዘመን ያመጣውን፣ ስለ እርሱ ሁሉን ትተው የተከተሉትን፣ እንዴት በጭንቅ ሰዓት ጥለውት ሄዱ? እንዴት ተውት? እኔ ግን የመዝሙሩን ስንኝ እና ዜማ ስሰማ ይህ ቃል እኛ ዘንድ እንዲደርሰ ባለውለታዎቻችን በመሆናቸው፣ ደቀመዛሙርቱ ላይ ከማዘን ይልቅ እገረማለሁ።በመከራ ቀን ጥለውት እንደ ሄዱ፣ እንደ ሸሹ አልሸሸጉንም። ይህ የፃፉት ሐሳብ በተነበበ ጊዜ ሁሉ የሚያስፈርድባቸው ሐቅ ነው። ነገር ግን ሐቁን በአጭር አረፍተ ነገር አስቀመጡልን። በወንጌላት ውስጥ ደቀመዛሙርት ጥፋተኛ እንደሆኑ የሚያሳዩ ብዙ ታሪኮች ተፅፈው እናገኛለን። ያለሚቋረጥ ኢየሱስን ሊረዱት ሲሳናቸው እናነባለን።

ልክ እናቱ እና ወንድሞቹ እንዳልተረዱት፣ ደቀመዛሙርትም አልተረዱትም፡ ፡እሱን ያለመረዳታቸው ጉዳይ ቀን በቀን እየጨመረ፣ እየጠነከረ በመጣ ቁጥር፣ ውስጡ ይጎዳ ነበር። አዕማድ ከነበሩ ደቀመዛሙርት መካከል፣ በሚመጣው ዓለም የክብር ስፍራ እና ስልጣን እንዲሰጣቸው ሲጠይቁት እናነባለን። ኢየሱስን የማይከተሉ ሰዎችን የሚኮንኑ ፅንፈኞች እየሆኑ ስለመጡ፣ ሲነቅፋቸው እናገኛለን። ኢየሱስ ጴጥሮስን “ሰይጣን” ብሎ ሲጠራው እናነባለን። ምክንያቱም፣ ኢየሱስ በአባቱ በአብ እንደተወሰነው መከራን ሊቀበል እና በመስቀል ሊሞት ወደ ኢየሩሳሌም እንዳይሄድ፣ ጴጥሮስ ሊያሳምነው በመሞከሩ ነበር። ጴጥሮስ በፈተና፣ በዛ የጭንቅ ሰዓት የኢየሱስ ደቀመዝሙር አይደለሁም ብሎ ካደ። እነዚህ ዘገባዎች አስገራሚ ናቸው። ኢየሱስ ለደቀ መዛሙርቱ ምን እንዳደረገ የሚሳዩ ናቸው። ላጠፉት ጥፋት ፍርድን እንዲቀበሉ እንጂ ራሳቸውን መልካም አድርገው እንዳያቀርቡ አስተማራቸው። ይህን መሰል ጥፋታቸውን የማያምኑ፣ የማይቀበሉ ከሆነ ደቀመዛሙርቱ ሊሆኑ እንደማይችሉ ነገራቸው። ደቀመዛሙርቱ የነበረባቸውን መሠረታዊ ድካም እና ጥፋት ከእኛ ሸሽገውት ቢሆን ኖሮ፣ ወንጌላችን አሁን የሆነውን አይሆንም ነበር። የክርስቶስ ክብርና የተከታዮቹ መከራ፣ እንዲህ እንደምናየው በግልፅ ተፅፎ አናገኘውም ነበር።

ከዚህ የምንማረው፣ በተመሳሳይ መልኩ የሰው ልጅ የራሱን ቆሻሻ ለመሸሸግ ያለው ፍላጎት ቆሻሻውን የበለጠ እንዲታይ እንደሚያደርገው ነው። ወንጌላት ተፅፈው ካለቁ በኋላ ከጊዜ ወደጊዜ እየሰፋ የመጣ (Later gospel traditions)፣ በኢየሱስ ዙሪያ ይነገሩ የነበሩ ታሪኮች፣ ባህሎች እና ወጎች ከባድ እና ስቃይ የበዛበትን የኢየሱስን ሕይወት የሚያሳዩ ምስሎችን፣

ለማለሳለስ እና ለንግግር የማይከብድ ለማድረግ ሞክረዋል። በርግጥ በተቋቋሙት የክርስቲያን ጉባኤዎች ላይ የሚታደሙ ምዕመናን ደቀመዛሙርቱ መሸሻቸውን፣ከደቀመዛሙርቱ መካከል ማናቸውም የጌታቸውን መሰቀል እንዳልተመለከቱ መቀበል ፣በእርሱ ስቀለት ወቅት በአካባቢው እንኳን እንዳልነበሩም ብሎ ለማመን ጫንቃቸው ሊሸከመው እንደማይችል ግልፅ ነው። ሸሽታቸው የቆመው፥ እርሱን ሸሽተው በተደበቁበት በገሊላ፣ በመከራና በተስፋ መቁረጥ ጊዜ ጥለውት የሄዱት እርሱ፣ በመካከላቸው ዳግም ከሙታን ተነስቶ ሲቆም ብቻ እንደነበር እውነታውን መቀበል አልቻሉም። አልፈለጉም።

ስለዚህ ሸሽተው ሳይሆን ኢየሱስ ራሱ ወደ ገሊላ እንዲሄዱ እንደነገራቸው ተፃፈ። አሁንም፥ ወደበኋላ በተጨመሩ ታሪኮች ደግሞ ደቀመዛሙርት ወደገሌላ እንዳልሸሹ ይልቁንም በኢየሩሳሌም እንደቀሩ ተነገረ። ገና ከጅምሩ ጀምሮ፥ ቤተ ክርስቲያን ይህን የደቀመዛሙርቱን ጥፋት ለማመን ከብዷታል። መቀበል አልቻለችም። ቤተ ክርስቲያን፥ በራሷ ላይ የተላለፈውን የትላንት እና የዛሬ የጥፋተኝነት ፍርድ መቀበል አቃታት። ደቀመዛሙርቱ በግልፅ፥ ሁላችንም ትተነው ሸሽተናል ብለው የተቀበሉትን ሐቅ፥ በቤተ ክርስቲያን ታሪክ ውስጥ ለመሸሽግ ተሞክሯል። ሆኖም የኢየሱስ ተከታዮች የሆኑት ደቀመዛሙርትን ጨምሮ፥ ስለ

ሁሉም የሰው ልጆች ያለው እውነት ይህ ነው፤ በመከራ እና ፈተና ቀን እንሸሻለን።

# 2.

ከእግዚአብሔር ሽሽት የምንጀምረው፥ የእርሱ መገኘት በተሰማን ቅጽበት ነው። ይህ የሽሽት ስሜት የሚገኘው በውስጠኛው የእኛነታችን ክፍል  በጨለመ ድብቅ ቦታ  ማለትም በህፃን ልጅ ማቆሚያ በሌለው ጥያቄ እና ፍለጋ ውስጥ፣ ጥርጣሬ እና ተስፋ መቁረጥ በረበበው ጉርምስና ውሰጥ፣ በአዋቂዎች መሻት እና ትግል ውስጥ እና  ግማሽ ንቁ በግማሽ ደግሞ ባልነቃው (half conscious being) ማንነታችን ውስጥ ነው። የሚታወቅበት ሁኔታ የለም፥ ግን ፍሬው ያፈራል። ነገር ግን በዚህ ሁኔታ ውስጥም ቢሆን እግዚያብሔር መገኘቱ አለ።በርግጥ እንደ እግዚያብሔርነቱ ሆኖ አይደለም።በዚህ ወቅት በእኛ ውስጥ ያለው የእግዚያብሔር መገኘት ምልክቱ ፥ እረፍት የለሽ የሚያደርግ የማይታወቅ ኋይል በውስጣችን እንዳለ መገንዘባችን ነው።

ነገር ግን በአንዳንድ ጊዜያት፥ እንደ እግዚያብሔርነቱ ሆኖ ይገለጣል። እረፍት የለሽ እንድንሆን ያደረገን በውስጣችን ያለው የማይታወቀው ኋይል፥ በእጆቹ መዳፍ የያዘን፣ ብንክደው የሚከዳን፣ እሺ ብንል የዘላለም መጠጊያችን የሚሆነን እርሱ ራሱ እንደሆነ፥ “እንደ ራሱ” እንደ እግዚአብሔርነቱ ሆኖ ይገለጣል። እንደዚህ ባሉ ጊዜያት እሱ እንደ እሱነቱ ለእኛ ሲገለጥ  ማለት በስውር ስንሸሽ ከነበረበት ስንያዝ ማለት ነው። ነገር ግን ስንሸሽ የተያዝነው ጨካኝ በሆነ ኋይል ሳይሆን ወዴት ነው የምትሄደው ብሎ በሚጠይቅ ትሁት በሆነ በእርሱ ነው። መልስ ሳንሰጥ፥ ሽሽታችንን የመቀጠል ነፃነት አለን። በደቀ መዛሙርቱ ላይ የሆነው ይህ ነው። መጀመሪያ ኢየሱስ  ወደ ራሱ በጠራቸው ወቅት ጥሪውን ተቀብለው ሰምተው መጥተው ነበር። ነገር ግን፥ እንደገና ለመሸሽም ነፃነት ነበራቸው። እናም የፈተና እና የጭንቅ ቀን በመጣ ጊዜ ከእርሱ ሸሹ። አሁን በቤተ ክርስቲያን እና በምዕመኖቿ የሚሆነው እንደዚሁ ተመሳሳይ ነገር ነው። በድብቅ ከሚሸሹበት የእርሱ ብርቱ እጅ አስቆመቻቸው እና ወደ እግዚያብሔር ህልውና መጡ። ነገር ግን እንደገና ለማምለጥ ነፃ ናቸው። እንደግለሰብ ብቻ አይደለም የሸሹት፥ ነገር ግን የነገዋን ቤተ ክርስቲያን እጃቸው ላይ ይዘው ነው የሸሹት። ራሳቸውን ብቻ ሳይሆን፥ ቤተ ክርስቲያንንም ተሸክመው ወደ ገሊላ እሮጡ። በተቻላቸው አቅም ሁሉ፥ እጅግ እሩቅ ወደሆነ ቦታ ቤተ ክርስቲያንን ይዘው ሸሹ። ዘለዓለማዊው ወደ ጊዜያዊው ዓለም ሰብሮ ከሚገባበት ወሳኙ ስፍራ፥ ዘለዓለማዊው ከጊዜያዊው ከሚገናኙበት ብቸኛ ቦታ፥ ማለትም ከእርሱ ህልውና ነጥለው ወሰዷት። ሰው በቤተ ክርስቲያን ውስጥ ሆኖ እንኳን፥ ከእግዚያብሔር ይሸሻል። ወደ የትም ንቅንቅ እንዳይል፥

በመገኘቱ ክብር የተያዘበት ቦታ ነው ተብሎ ከሚታሰብበት ስፍራ ሆኖም ይሸሻል። በህልውናው ውስጥ ሳለን፣ ከእርሱ እንሸሻለን።

## 3.

የፍጥረት መሠረት የሆነው እርሱ እግዚአብሔር ወደ አንድ ሰው ሕይወት ለመግባት ሲመጣ፣ ያ እግዚአብሔር ወደ ህይወቱ ሊገባ  የፈለገው ሰው ግን አንገብጋቢ ባልሆኑ ነገሮች ውስጥ ለመሸሽግ ይሞክር ይሆናል። እምቢ ቢል የመውጊያው ብረት በእርሱ እንደሚብስ ካስጠነቀቀው ብርሃን ለመሸሽ መደበቂያ ይሆነኛል ወዳለው ስፍራ ይሮጣል። ልክ ገሊላ ለደቀመዛሙርቱ ጥሩ መሸሸጊያ ቦታ መስሎ እንደታያቸው እኛም አስተማማኝ የሚመስሉን ብዙ መደበቂያ  ቦታዎች አሉን።

ምናልባት በዚህ ዘመን፣ ወደ እቅፉ ሊከተን ካለው የእግዚያብሔር ሕልውና ለመደበቅ በምንሮጥበት ጊዜ፣ በጣም ውጤታማ የሆነ መደበቂ ቦታ የሚሆነን፣ የእለት እንጀራችንን የምናገኝበት ሥራችን ነው። በጥንት ጊዜ ግን እንደዛ አልነበረም። የጥንቱ ሰው ለሥራ ስለነበረው አመለካከት፣ እግዚያብሔር አዳምን በረገመው ጊዜ በተናገረው “በፊትህ ላብ እንጀራን ትበላለህ” በሚለው ቃል ውስጥ እና በመዝሙር 90፣ ዳዊት ህይወታችን በምድር ላይ አጭር መሆኑን በተናገረበት “ነገር ግን ጊዜያቸው ድካምና ችግር ብቻ ነው” ባለው ቃል ውስጥ ጥሩ በሆነ ሁኔታ ተጠቃሎ ተቀምጧል። በኋላ ላይ የማህበረሰብ እድገት እየተወሳሰበ ሲመጣ፣ የጉልበት ሥራ ከነ አድካሚነቱ እና ብዘበዛው ለባሮች፣ ጭሰኞች እና ላልተማሩ ክፍሎች የተተወ ነገር ሆነ። የጉልበት ሥራ ደግሞ ጥቂት እድለኞች ትርፍ ጊዜያቸውን ማሳለፊያ አድርገው ከሚጠቀሙበት የፈጠራ ሥራ ተለይቶ እንዲታይ ሆነ። የመካከለኛው ዘመን ብለን በምንጠራው ዘመን በነበረው የክርስትና ህይወት ልምምድ፣ በተለይም በገዳማዊ ሕይወት፣ ሥራን እንደዋነኛ የመንፈሳዊነት መገለጫ እና አገልግሎት አድርገው ይመለከቱ ነበር። ነገር ግን አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ከሊቅ እስከ ደቂቅ ሁሉም የሰው ልጅ የሚኖርለት እና የሚሞትለት እጣ ፈንታ ሥራ ሆኗል። ሁሉም ሰው በስራ ላይ ተሰማርቶ ስለማይገኝ በተጨባጭ ያለው ነገር እንደምንለው ላይመስል ይችላል ፣ነገር ግን ከአቅም በላይ ካልሆነ በቀር ማንም ሰው ስራ አለመስራቱን እንደ መልካም ነገር እንደማይቀበለው ስናይ፣ስራ መስራት የሰው ሁሉ እጣፈንታ እንደሆነ በዚህ እናውቃለን።

ሥራ ሁሉ ነገር ነው። ከእያንዳንዳችን የሚጠበቅ ግዴታ ነው፣ ምርት ነው እና ፈጠራ ነው። በዘቅተኛ መደብ ላይ የሚገኙ ሰዎች የሚሰሩት የጉልበት ሥራ እና ለክፍያ ሳይሆን ትርፍ ጊዜን ለማሳለፍያ ጥቂት እድለኞች የሚሰሩት የአእምሮና የጥበብ ስራ የሚለው ልዩነት አብቅቷል። ሥራ ማለት፥ በአዳም ሐጢያት ምክንያት የመጣ እርግማን ነው ተብሎ ይታመን የነበረው፥ ከመጽሐፍ ቅዱስ እይታ የተወሰደ አስተሳሰብ፥ ተቀባይነቱ አብቅቷል። ሥራ እርግማን አይደለም። አሁን በዚህ ዘመን ሥራ ራሱ ሃይማኖት ነው። የዘመናዊ ኢንዱስትሪ ማሕበረሰብ ሃይማኖት ሆኗል። እና ሁላችንም በእጁ ውስጥ አለን። ባለመሥራታችን ምክንያት ከሚመጣ የርሃብ ቅጣት ማምለጥ ብንችልም እንኳን፥ በውስጣችን የሆነ አንዳች ነገር በሥራ ከመወጠር ባርነት እንድናመልጥ አይፈቅድም። ለአብዛኞቻችን ሥራ አስፈላጊ እና አስገዳጅነት ነገር ነው። እረፍት እንድናደርግ የሚፈቅድ ሁኔታ ቢኖር እንኳን፥ አዕምሯችን ባለመሥራታችን ፀፀት ውስጥ ይገባል። እናም እንደዚህ በመሆኑ፥ ሥራ መሥራት ግዴታ፣ በሥራ መወጠር አማራጭ የሌለው ነገር ተደርጎ መወሰዱ፥ በሥራ አመካኝተን ከእግዚያብሔር ለመሸሽ ጥሩ አማራጭ መንገድ ሆኗል።ከዚህ መንገድ ውጪ ሌላ የተሻለ መንገድ ያለም አይመስልም። ሥራ በመሠራት ሐላፊነትን በመወጣት የሚገኝን እርካታ እናገኝበታለን። አንድን ስራ ሰርተን ስንጨርስ “በጣም ጎበዝ ፥በጥሩ ሁኔታ አከናወንከው” የሚል መወደስ ከሌሎች እና ከራሳችን እናገኝበታለን። “ጎበዝ ሰው” እንባላለን። ከሥራ በምናገኘው ገንዘብ፥ ቤተሰባችንን እና የቤተሰባችንን አባሎች መደገፍ እና መንከባከብ እንችላለን።

በሥራ ላይ የምንሆን ከሆነ እለት በእለት ሊገጥመን ከሚችል ዘልዛልነት፣ ድባቴ እና ሥርዓተ ቢስ ከመሆን አደጋ እንተርፋለን። ሥራ ስንሰራ፥ ንፁህ ኀሊና እና ደስተኛ ሕይወት ይኖረናል። እናም አንድ ፈላስፋ በሽሙጥ መልክ እንዳለው፥ ከሥራ መልስ “ጥሩ እንቅልፍ” እንተኛለን። በተለይ ደግሞ፥ የፈጠራ ሥራ ተብሎ የሚጠራውን አይነት ሥራ የምንሰራ ከሆነ፥ አዲስ ነገር በማግኘት በሚመጣ ደስታ፥ ሕይወታችን ከፍተኛ በሆነ እርካታ የተሞላ ይሆናል። ምናልባት አንድ ሰው ስራ እኔ ከእግዚያብሔር የምሸሽበት መንገድ አይደለም ቢል እንዲህ በማለት እንጠይቀዋለን። እንደው አንዳንድ ጊዜ ጉድለት እና ሙላትህን፣ ኪሳራና እና ትርፍህን፣ ከቤተሰብህ እና ከራሰህ ጋር ባለህ ግንኙነት ደካማ እና ጠናካራ ጎንህን ለማወቅ በታማኝነት ተቀምጠህ ራስህን ስትፈትሽ ብዙ ጉድሎቶች እንዳለብህ ማስተዋል ቻልክ ነገር ግን እነዛን ጉድለቶች ከማረም ይልቅ ያለብህን ጉድለት በሥራህ ስኬት እና ትጋትህ ለማካካስ የሞከርክበት ወቅት የለም? የዘመናችን ፈሪሳዊ በታታሪነቱ፣ ወለም ዘለም ባለማለቱ እና በስኬታማ ሕይወቱ

የሚመካውን ያህል እንደቀድሞው ፈሪሳዊ ለሕግ በመገዛቱ እና በመንፈሳዊ ልምምዱ አይመካም። ልክ እንደጥንቱ ፈሪሳዊ የዘመናችንም ፈሪሳዊ ራሱን ከሌሎች እያስተያየ እንዴት "ጥሩ ደረጃ ላይ ያለሁ ሰው ነኝ፣ ውይ እንደ እከሌስ ከምኖር ሞት እመርጣለሁ" እንዲል ባደረገው ራሱን በሚያተልቅበት የትህምክት ሃጢያት ውስጥ የወደቀ ነው።

## 4.

በተወሰነ ደረጃ ተጨባጭ የሆነ፣ ወደ ተትረፈረፈ ሕይወት እንደሚመራን ተስፋ የሰጠን ሆኖም ግን ከእግዚአብሔር የምንሸሽበት ሌላም አይነት መንገድ አለ። ይሄ መንገድ ከኢየሱስ ምሳሌዎች አንዱ ከአባቱ ቤት ድርሻውን ይዞ የጠፋው ልጅ የሄደበት መንገድ አይነት መንገድ አይደለም። ጥልቅ አሳቢ በሆነ አዕምሮ እና ፍቅር በመነዳት፣ በተፈጥሮ ያሉትን አስደናቂ እና ቆንጆ ነገሮችን በማድነቅ እና በህይወት እና በመኖር ውስጥ ያሉ ነገሮችን ሁሉ በመቀበል ሊሆን ይችላል። እንዲህ መሰል ለሕይወት ያለ ስስት እና ናፍቆት፣ በታላቅነት ውስጥ ያለን አሳዛኝ ሁኔታ፣ በብርሃን ውስጥ ያለን ጨለማ፣ በደስታ ውስጥ ያለን ህመም እና በውበት ውስጥ ያለን አስቀያሚነት ላለማየት ዓይኖቻችንን መዝጋትን የግድ አይደለም። ብዙ ወንዶች እና ሴቶች፣ የተትረፈረፈ ሕይወትን ለመለማመድ ድፍረት ሊኖራቸው ይገባል። ነገር ግን ይህም ደግሞ፣ በጉልበት መዛል እና በሥራችን አመካኝተን እንደምናደርገው፣ ከእግዚአብሔር የመሸሻ መንገድ ሊሆን ይችላል። ሐሴት እና ፈንጠዝያ በሞላው ሕይወት ውስጥ፣ የተትረፈረፈ ሕይወት "ገደቡ የት ድረስ ነው" የሚለው አይታወቅም። እየተናገርኩ ያለሁት፣ ጥሩ ጊዜ ስለማሰለፍ፣ ራስን ደስተኛ ለማድረግ እና ለመዝናናትን ስላለው ፍላጎት ረብ የለሽ ዘዴዎች አይደለም።

ብዙ ጊዜ መዝናናትም ቢሆን ፣ ጭንቀት ለመቀነስና የዛለን ጉልበት ለማደስ በሚል የምንሸፋፍነው ሌላ አይነት ስራ ማለትም ሊሆን ይችላል፣ስለዚህ አንዳንድ ጊዜ መዝናናትም ከእግዚያብሔር የመሸሻ ሌላ መንገድ ነው። ሥራን በተቀላጠፈ ሁኔታ ለመስራት ለሆነ ያህል ጊዜ የመዝናኛ ጊዜ ማግኘትን የመሰለ አዋጭ መንገድ የሌለ በመሆኑ መዝናናት በሁሉም ዘንድ ድጋፍ አለው። ጭንቀትን እና በሥራ መሰላቸትን ለማስወገድ ተዝናንቶ ወደሥራ መመለስ እንደመድሃኒት የሚታዘዝ ነገር ነው። ነገር ግን እኔ እያወራሁ ያለሁት፣ በሐሴት በተሞላ ሕይወት ውስጥ መሳተፍን ነው።

እንዲህ አይነት ሕይወት ብርታት እና ሁሌም አፍላ መሆንን ይጠይቃል ነገር ግን ከእግዚያብሔር መሸሻ መንገድም ሊሆን ይችላል። በዚህ መንገድ የሚኖርን ሰው፥ በሞራል ዝቅጠት ውስጥ መድበን ልንነቅፈው አይገባም፥ ነገር ግን እረፍት የሌለው መሆኑን፣ እግዚአብሔርን ለመገናኘት ያለውን ፍራቻ ሊያውቅ ማድረግ ይገባል። በሥራ ተወጥሮ፣ ሥራው ላይ ብቻ ትኩረት አድርጎ የሚውል ሰው የቡርቃ እና የፌሽታ አኗኗር የሚኖረን ሰው ህይወት የከንቱነት ህይወት በማለት በበላይነት ስሜት ሊኩራራ አይገባም። በሕይወት ውስጥ ደስታን እያሳደደ የሚኖረው፥ በሥራ ውጥረት እሥራት ውስጥ ባለው ላይ መኩራራት የለበትም።

## 5.

በዘመናችን ሁለቱንም መንገዶች ገደብ እንዳላቸው የዩ፣ በሕይወታቸው ሁለቱንም የተለማመዱ ብዙዎች ናቸው። ለእነዚህ ሰዎች የተሳካ ሥራ ያለው ሰው መሆንም ሆነ ፤ በተትረፈረፈ የፈንጠዝያ አኗኗር ውስጥ መባከን ሁለቱም ትርጉም የለሽ የሆነባቸው ናቸው። እኔ እየተናገርኩ ያለሁት በጭንቀት እና በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ስላሉት፣ በሕይወታቸውን አንድ ወቅት ከእግዚያብሄር የሚያደርጉትን ሽሽት አቁመው የነበረ ግን በኋላ በዛው ሽሽታቸው ስለቀጠሉት የመለኮትን መኖር ስለሚጠራጠሩት እና ስለዋዜኞች ነው። በርግጥ አቁመውት የነበረውን ሽሽት የቀጠሎት በአዲስ ቅርፅ ነው። ይህም አዲስ ቅርፅ የማያቋርጥ ጥያቄ በማዥጎድጎድ እና እርሱን በመካድ ነው። በዘመናችን ስለ እንደዚህ አይነቶቹ ዕይታ እና እውነተኛ መሻት በከፍተኛ ሁኔታ ተብራርቶ እና ተተንትኖ የቀረበው በሥነጽሑፍ እና በጥበብ ሥራዎች ውስጥ ነው። በእርግጥ እነዚህ ሰዎች በሆነ ያህል ድጋፍ አላቸው። በማስመሰል ሳይሆን የምርም ተጠራጣሪዎች ከሆኑ አለማመን እና ተጠራጣሪነትን ተከትሎ የሚመጣ መከራ እውነተኝነታቸውን ያስረግጣል።

በተስፋ መቁረጥ ውስጥ ከሆኑ፣ ተስፋ መቁረጣቸው የምርም ከሆነ፣ እያለፉበት ያለው እጅግ አዳጋች የተስፋ መቁረጥ ሕይወት የራሳችንን ሁኔታ በደንብ የምንረዳበት ምልክት ይሆነናል። ሆኖም ግን እነርሱም ከእግዚያብሔር በመሸሽ ላይ ናቸው። እግዚአብሔር ሽሽታቸውን እንዲያቆሙ እና ወደ እርሱ ዞር እንዲሉ በበትር ሰብሯቸዋል። እግዚአብሔር መታቸው ግን እነርሱ አላወቁም። በአስተሳሰባቸው እና በአኗኗራቸው እሱን መካድ የመፈለጋቸው ጥልቀት፣ ከክህደታቸው ከሽሽታቸው ለትንሽ ጊዜም ቢሆን በእርሱ እንደተያዘ አመላካች ነገር አለው። በሥራ ስኬት ወይም በሕይወት መትረፍረፍ፣ ከእርሱም በሚገኝ የደስታ

በረከ ኖሮ “የሕይወት ምንጯን ከሳሾች” አይሆኑም ነበር። የሕይወት ምንጯን ይከሳሉ። ምክንያታቸው ምንድን ነው፤ ለእያንዳንዱ ሕይወት “ሕይወት መሆንን”

ከሚሰጠው ኋይል ስለሚሸሹ ነው።

## 6.

ከእግዚአብሔር መሸሽ ምን እንደሚመስል በህይወታቸው የምናይባቸው መጨረሻ ረድፍ ላይ ስለሚመጡ ሰዎች የማንላቸው አንዳንድ ነገሮች አሉ። ደቀመዛሙርት እንዳደረጉት እነዚህኛዎቹ ከመስቀሉ ሸሽተው አልሄዱም። ይልቁን ወደ መስቀሉ የተጠጉ ናቸው። በመስቀል የተቀበለውን መከራ ተመለከቱ፣ ምስክሮችም ሆኑ። በመስቀሉ ስራ ተቀደሱ። ከዚህ ሁኔታ የተነሳ ከደቀ መዛሙርቱም የተሻሉ ናቸው! በርግጥ የተሻሉ ናቸው? ከዚህ ሁኔታ ተነስተን የተሻሉ ናቸው ለማለት እንችላለንን? የሚጠፋው ከማይጠፋው፣ ዘላለማዊ የሆነው ዘላለማዊ ካልሆነው የተገናኙበት ወሳኙ ቦታ የሆነው መስቀሉ የትውፊታችን እና የባሕላችን ዋነኛ መገለጫ ወደ መሆን ከመጣ መንፈሳዊ ሀይሉን እንደያዘ የክርስቶስ መስቀል ሆኖ ይቀጥላልን? ምን አልባት ከመስቀሉ ስር አስጠግቶ ያቆየን የወላጆቻችን ባህል ስለሆነ ላይሆን ይችላል። ነገር ግን ድንገት በሕይወታችን የተከሰተ የመነካት ልምምድ ይሆናል። ለመጀመርያ ጊዜ ከመስቀሉ ጋር ፊትለፊት የተገናኘነው ወደ መስቀሉ ያመጣን ሀይለኛ ሰባኪ ወይም ወንጌላዊ ይሆናል! ይህን በመሰለ መንፈሳዊ መነቃቃት ውስጥ ባለንበት ሰዓት እንኳን ራሳችንን መጠየቅ ያለብን አንድ ጥያቄ አለ፥ እሱም መስቀሉ ስር በአክበሮት ተደፍቼ፥ በልቤ ግን ከ“መስቀሉ ስር መደፋቴን” ከመስቀሉ መሸሻ መንገድ አድርጌው ይሆን? ብለን መጠየቅ አለብን።

## 7.

ከእግዚአብሔር የምንሸሽበት መንገድ ምንም ይሁን፥ እርሱ ይቀድመናል፣ እንየዛለን። እርሱ ሲቀድመን እና ስንየዝ ያን ጊዜ ከተለምዶአዊው የአኗኗ ዘይቤአችን የያወጣን፥ አንዳችን ነገር  ወደ ሕይወታችን አልፎ ይገባል። ከባድ፥ ነገር ግን እጅግ ታላቅ የሆነ የሕይወት ልምምድ ነው!አንዱ ከሚሰራው ሥራ ይሰናበታል፥ እናም የሕይወቴ ትርጉም ጠፋ ብሎ ማሰብ ይጀምራል። አንዱ ድንገት የተትረፈረፈ፣

የደስታ የፈንጠዝያ የሚመስለው ሕይወት ባዶ ትርጉም የሌለው ይሆንበታል። ሌላኛው ሰው ዋዘኝነቱ ግድየለሽነቱ፣ የምር የሆነ ተስፋ የመቁረጥ ሁኔታ ውስጥ ሆኖ ሳይሆን፣ የተደበቀ እብሪተኝነት መሆኑን ሊገነዘብ ይችላል። አንዱ ደግሞ፣ በእግዚያብሔር ፊት በተመስጦ ሆኖ በሚያሰላስልበት ሰዓት እግዚያብሔርን በሃይማኖታዊ ስሜት እንደተካው ሊበራለት ይችላል። ይህ ሁሉ ሂደት ግን ቀላል አይደለም ከባድ ነው። ልክ በቢላ ተወግቶ እንደመቁሰል አይነት ነው። ነገር ግን ታላቅም ነው። ምክንያቱም በእኛ ውስጥ አዲስ የሕይወት ምዕራፍ ስለሚጀምር። ስንሸሽ! ከእርሱ ስንሸሽ እግዚያብሔር ያዘን ፤ የሆነ አዲስ ነገር በእኛ ውስጥ ሆነ!

በእርሱ ከምንሸሽበት ከተያዝን በኋላ፣ በእኛ ሕይወት የሚመጣው አዲስ ነገር፣ የቀድሞውን ኑሮአችንን አያስወግድም። ነገር ግን ከዚህ በፊት እናደርግበት እና እንኖርበት የነበረውን ምክንያት እና ይዘት በመለወጥ አዲስ ማንነት ይሰጠዋል። ይታደሳል። የዕለት እንጀራችንን የምናገኝበትን ሥራ መሥራታችንን እንቀጥላለን። መጀመሪያም እንደነበረው፣ የሥራ ሕይወት አድካሚ እና አስጨናቂ መሆኑ ይቀጥላል። እንደቀድሞ የዕለት እንጀራችንን የምናገኝበት ሥራ የቀናችንን አብዛኛውን ሰዓት መውሰዱ ይቀጥላል። ነገር ሥራ ከዚህ ወዲህ የሕይወት ትርጉም ከሥራ አናገኝም።

ሥራ የመሥራት ጥንካሪያችን ወይም ሥራ የመሥራት እድሎቻችን ከእኛ ሊወሰድ ይችላል። ነገር ግን የሕይወታችን ትርጉም ከእኛ አይወሰድም። የሕይወትን ትርጉም ከሥራ እንደማናገኘው እንዲሁ፣ ሥራም የሕይወትን ትርጉም ከእኛ ሊወስድ እንደማይችል እንገነዘባለን። ሥራ የራሱ የሆነ ሌላ ትርጉም አለው። ሥራ፣ በሕይወት ውስጥ ተሰውረው የተቀመጡ ወሰን የሌላቸው፣ ካለው ነገር አዲስ ነገር የማምጣት እድሎችን እውን እንዲሆን፣ የምናግዝበት ነገር ነው ማለት ነው። ሥራ መሥራት! ትንሽ የምንለው ሆነ ትልቅ የምንለው ሥራ ! የትኛውም ሥራ መሥራት ከሕይወት ራስን የመፍጠር ኋይል ጋር መተባበር ነው። እንደ ሰራተኛ በእኛ በኩል፣ አንዳች የማይነጥብ፣ የማይበላሽ፣ የሕይወት ጥልቅ ነገር በእኛ በኩል ይገለጣል። ሥራ እርግማን ወይም ግዴታ መሆኑ ቀርቶ የውስጣችን አቅም መገለጫ ይሆናል ማለት ነው። ይህ አንድ ሰው ከእግዚያብሔር የመሸሽ ሕይወቱ አብቅቶ፣ በህልውናው እጆች ሲያዝ የሚሰማው ስሜት ነው። ለጥቂትም ጊዜ ቢሆን ሥራ ከመሥራት ባሻገር ያለን ነገር የሚጠቁም ነው። ምክንያቱ ሥራ ማለት ይህ ስለሆነ፣ ሥራውም ይባርካል እና እኛም በሰራ በኩል እንባረካለን። መባረክ ማለት፣ ልንደርስበት የተገባውን መስመር ተከትለን፣ በእውነተኛው የእኛነታችን አቅጣጫ

ከፍተኛው ደረጃ ላይ ስንደርስ ማለት ነው።

የሆነ አንድ ሰው የተትረፈረፈ፣ የድሎት እና የፈንጠዝየ ሕይወት በራሱ ባዶ እንደሆነ፣ በሕይወቱ ውስጥ እያየው እና በዛ ባዶነት ውስጥ እያለፈ ሳለ እግዚያብሔር በመንገዱ ከተገናኘው የተትረፈረፈው ሕይወቱ ከእርሱ አይወሰድም። አሁንም ካለው የተትረፈረፈ ሕይወት፣ ታላቅ የደስታ እና የሀሴት ገዚያትን ማግኘቱን ይቀጥላል። ነገር ግን የሕይወቱን ትርጉም ከሚታይና ከሚዳሰስ ነገር ላይ አያገኝም ። የሚታዩ እና የሚጨበጡ ውጫዊ ዕድሎች ወይም በእርካታ እና በደስታ የተሞላ ኑሮ ለመኖር ያለ ውስጣዊ ዝግጁነት ሊጠፋ ይችላል። ነገር ግን የሕይወቱ ትርጉም አይጠፋም። ደግሞ አንድ ነገር ይገነዘባል፣ መትረፍረፍ እና በረከት የሕይወት ትርጉም መስጠት አይችልም። ደግሞም የሕይወትን ትርጉም ከእርሱ ሊወስድ እንደማይችልም ያስተውላል። በእርሱ እጆች ለተያዘ፣ ሸሽቱን ላቆመ ሰው ስለሕይወት መትረፍረፍ የሚያውቀው ነገር ቀድሞ ከሚያስበው የተለየ ይሆናል። ከዚህ በኋላ የተትረፈረፈ ሕይወት ማለት ተለያይቶት የነበረውን የሚያዋህድ፣ ያለውን የሚያካፍል እና የሚሰጠውን የሚቀበል የህያው ፍቅር ማሳያ ወደ መሆን ይለወጣል። ከእኔነት አውጥቶ ከፍ ያለውን ነገር ያሳየናል። ሕይወትን እንድንወድ ሁሉን ነገር ከዘላለም ግብ አንፃር እንድንመለከት የደርገናል ውስን ፍጡር መሆናችንን እና ያገኘነውን ሁሉ ተቀብለን እንደሆነ ያሳየናል።

አንድን ሰው፣ ተጠራጣሪነትን እና ተስፋ መቁረጥን ምክንያት አድርጎ ከሸሸበት እግዚያብሔር ሲያገኘው፤ ተጠራጣሪነቱ እና ተስፋ መቁረጡ የምር እንዳልሆነ እንዲያውቅ ሲያደርገው፣ ተጠራጣሪነቱን ከእርሱ አይወስድበትም። ተስፋ መቁረጥም የሕይወቱ ሥጋት ከመሆን አይቆምም። ነገር ግን ተጠራጣሪነቱ ወደ ተስፋ መቁረጥ እንዲመራ ሊያደርገው አይገባም። የሕይወትን ትርጉም ሊነጥቀው አይገባም። በዋዘኝነቱ ወቅት፣ ከሁሉም የተሻለ እንደሆነ ራሱን በሚቆጥረበት ወቅት እንደሚያምነው፣ የሕይወትን ትርጉም የሰጠው ተጠራጣሪነት አይደለም። በተስፋ መቁረጥ ሆኖ ያስብ እንደነበረው ደግሞ፣ ተጠራጣሪነት የሕይወትን ትርጉም ሊነጥቀውም አይችልም። በእግዚያብሔር ከሸሸበት ለተገኘ ተጠራጣሪነት ሌላ መልክ አለው። ተጠራጣሪነት ወደ “ማንነቱ ቅድስተ ቅዱሳን” እና ወደ ሁሉም ሕላዌ ውስጠኛ ክፍል ክፍል ዘልቆ የሚረዳበት መንገድ ይሆናል። ጥርጣሬ የአእምሮ ጨዋታ ወይም የምርምር ዘዴ መሆኑ ያቆማል። ከዛ ይልቅ ሕይወታችን ተደገፎ የቆመባቸውን፣ እንዲሁ የተቀበልናቸውን አስተሳሰቦች እና እምነቶች ደፍሮ የሚጠይቅ እና የሚሞግት መሳሪያ ይሆናል። በዚህም እነዚህ

አስተሳሰቦች ተራ በተራ ከላያችን ይራገፋሉ። እናም ይሄ ነገር ይሆናል። ከምር እና ከልብ ስለራሳቸው እና ስለዓለም ጥርጣሬ ያላቸው፣ ያው ጥርጣሬ እራሱ ወደ እርሱ ማለትም ከሚሸሹበት አስቀሞ ወደራሱ እቅፍ ወደከተታቸው ወደ እግዚአብሔር የሚወስደውን አቀጣጫ እንዲያገኙ ምክንያት ይሆናቸዋል። እናም የምር ከነበረው ጥርጣሪያቸው ጀርባ የእውነት ፍለጋ እንደነበር ይገነዘባሉ።

እናም አንድ ሰው በእግዚያብሄር ሲያዝ፣ ከእግዚአብሔር ይሸሽ የነበረው በአሃማኖተኝነት ካባ ስር ስለነበር ሃይማኖተኝነቱ የህይወትን ታላቅ ነገር አግኝቶ ከመለማመድ እንዳራቀው ፣ሃይማኖተኝነቱ ህይወት የሌለበት እንደሆነ እንዲረዳ ሲያደርገው ያንን እንዲገነዘብ መደረጉ ሐይማኖት ጥሎ እንዲሄድ አያደርገውም። በሃይማኖት መኖር ከእርሱ አይወሰድም። ነገር ግን አሁን ሃይማኖት የሕይወት ትርጉም ሊሰጠው እንደማይችል ይረዳል። ሃይማኖቱን የሚያጣበት ሁኔታ እንኳን ቢኖር የሕይወቱን ትርጉም ማጣት የለበትም። በእግዚያብሄር የተያዘ ማንኛውም ሰው ይሄ በሃይማኖት እና ያለሃይማኖት ከሚለው አልፎ የሚሄድ እይታ ያለው ነው። ሃይማኖቱን አጥብቆ የሚይዝ ከሆነ ደግሞ ለእርሱ በሀይማኖት መኖር ሌላ መልክ ይኖረዋል። ሕግ ሳይሆን መንገድ ሊሆን ይችላል፤ የነገር ሁሉ ፍጻሜ የሆነው የእርሱ ህልውና እርሱን ከሚሸሽበት አግኝቶ የያዘበት ሌላ መንገድ መንገድ ይሆናል። ሐይማኖት ብቸኛ መንገድ ግን አይደለም። ከሀይማኖት እሥራት ነፃ እንደሆነው እንዲሁ፣ ማንኛውንም ሃይማኖት ለመምረጥም ነፃ ነው። በሀይማኖት ውስጥ ይባረካል፣ ከሃይማኖት ውጪም ይባርካል። አሁን እርሱ ስለሕላዊ እውነታ አዲስ ወደሆነ የንቃትና የመረዳት ደረጃ ላይ ደርሷል።

ስለዚህ አትሸሹ! ለእግዚያብሄር ፍለጋ ለመገኘት ራሳችሁን ስጡ እና በእርሱ የተባረካችሁ ሁኑ!

# 12. የእግዚያብሔር ስም

*“የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ፤ እግዚአብሔር ስሙን በከንቱ የሚጠራውን ከበደል አያነጻውምና።”*

*— ዘጸአት 20፥ 7*

በዚህ ክፍል ውስጥ ያሉ ሌሎቹ ትእዛዛት ሕይወትን፣ ክብርን እና ንብረትን ስለመጠበቅ የተሰጡ ትዕዛዛት ሲሆኑ፥ሁለተኛው ትዕዛዝ ግን ብቻውን የያዘው ስሙን በከንቱ እንዳንጠራ የተሰጠውን ትዕዛዝ ነው፥ ይህ ከሆነ በዚህ ስም ውስጥ አንድ የተለየ ነገር መኖር አለበት። እርግጥ ነው፥ እግዚአብሔር ስሙን መጠበቅ አያስፈልገውም፥ ነገር ግን በከንቱ እዳንጠራ ስሙን ይጠበቃል። ትዕዛዙን የሚሰሙ፥ ትዕዛዙ ምን ያህል ከባድ እንደሆነ እንዲገነዘቡ ይህን አንድ ትዕዛዝ በሚተላለፉ ላይ ስለሚሆነው አስፈሪ ነገር ተጨምሮ ተነግሯል። ይህ የሆነበት ምክንየት ስሙ ሲጣራ የስሙ ባለቤት በተጠራበት በዛ ስፍራ ህልውናው ስለሚገኝ ነው። በጥንት ዘመን ሰዎች የአንድን ፍጡር ወይንም ነገር ድብቅ ስም ማወቅ ከቻሉ ያን ነገር በቁጥጥራቸው ስር ማድረግ እንደሚችሉ ያምኑ ነበር። ልክ እኛም በዚህ ዘመን፥ በእኛነታችን ውስጠኛ ክፍል ያልነቃውን ኀሊናችንን የሚውኩ እና ለአዕምሮ መረበሽ የዳርጉን ነገሮች በስማቸው ውስጥ የተሰወረውን ኀይል ሚስጥር ለማወቅ እንደምንጥረው፤ የጥንቱ ሰውም አማልክት እርኩሳን መናፍስትን ድል በመንሳት የሚታደጉን በመናፍሱቱ ስም ውስጥ ያለውን የኋይል ሚስጥር በማወቅ እንደሆነ ያምን ነበር።

በስውር ሊያሳኩ ስለፈለጉት ነገር አብርሆት ካገኘን፥ ኀይላቸውን መስበር ማዳከም እንችላለን። ሰዎች ሁልገዜ በዚህ ተመሳሳይ መንገድ፥ የእግዚአብሔርን ስም ለመጠቀም ይሞክሩ ነበር፥ ነገር ግን ይህን ያደርጉ የነበረው በስሙ ላይ ያለውን ኋይል ለመስበር ሳይሆን የስሙን ኋይል ለራሳቸው ዓላማ ለመጠቀም ነበር። ለምሳሌ የእግዚአብሔርን ስም በጸሎት ውስጥ መጥራት የእግዚያብሔርን ስም ለዓላማችን መሳካያ መሣሪያ ለማድረግ መሞከርን ሊያመለክት ይችላል። ስም በመጥራት አንድ ነገር ከሌላው ነገር የምለየው በምናወጣው ድምፅ ብቻ

አይደለም ነገር ግን ያ የምንጠራው ስም በውስጡ ሀይልን የያዘ በመሆኑ ነው፡ ፡ በዓይናችን የማናየው ነገር፥ ህልውናው በመካከላችን እንዲሆን ያደርጋል። የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ መጥራት ተገቢ ያልሆነው እና በከንቱ ለሚጠራ ጉዳት የሚያመጣበት ምክንያት ይህ ነው።መለኮት የሆነውን ጠርተን ሳይነካን አይተወንም። ስንጠራው ሰምቶ ካልፈወሰን፤ ይሰብረን ይሆናል። የእግዚያብሔርን ስም በከንቱ መጥራት የሌለብን ለዚህ ነው። የሃይማኖት አደጋው ይህ ነው። የሃይማኖት ተቃዋሚም መሆን እንኳን አደጋው ይሄ ነው። በሃይማኖትም በሃይማኖት አልባነት ውስጥ የእግዚያብሔን ስም ተገቢ በሆነ እና ተገቢ ባልሆነ መንገድ ጥቅም ላይ ይውላል።

እግዚአብሔር የሚለውን ስም መጥራት እንዴት አደገኛ ሊሆን እንደሚችል አንመልከት። በተለይ ደግሞ ስሙን አምኖ በማወጅ ውስጥ፣ በመካድ ወስጥ እና እግዚአብሔር ብሎ መጥራት ሞቻት የሚነሳ ነገር ሲሆንብን ሞቻት የማይሰጡ ሦስት አይነት ይዘት ያላቸውን መንገዶች ልናስቀምጥ እንችላለን። ከትህትና እና ከአክብሮት የተነሳ ስሙን ለመጥራት ሞቻት ማጣት፥ ከተጠራጣሪነት የተነሳ ሰሙ ለመጥራት ሞቻት ማጣት እና ከስሙ አስደናቂነት የተነሳ ስሙን ለመጥራት ማመንታት ናቸው።

በተለይ ያለፉት 15 ዓመታት ውስጥ በዚህች አገር፥ (ጸሃፌዉ በነበረበት ዘመን በአሜሪካ ውስጥ ከፍተኛ የሆነ ሃይማኖታዊ መነቃቃት ነበር። በዚች ሀገር ሲልም ይኖርባት የነበረችውን ምድር አሜሪካንን ማለት ነው።) የእግዚአብሔርን ስም ለመጥራት፣ ስለእግዚአብሔር ለማውራት ፈቃደኛ የሆኑ ሰዎች በከፍተኛ ሁኔታ የጨምሩበት ዘመን ይዞ ከመምጣቱ አንፃር ስንመለከት፥ ይህ ምሁር የተናገረው ንግግር እጅግ ጠቃሚና፤ የእኛም ትኩረት የተገባው ንግግር ነው። ምንም እንከን የማይወጣለት እጅግ በጣም አስደናቂ የሆነ መነቃቃት ነው፡፡ ሃይማኖተኝነት ሳይሆን ለእምነት ስፍራ የሰጠ፥ ሐይማኖትን በተመለከተ ግንዛቤ ወደዳበረበት መነቃቃት ውስጥ የገባንበት ነው። ይህ ክስተት የእግዚአብሔር ስም፥ ስም ብቻ ሳይሆን ከሁሉም የላቀ በመሆኑ፥ ስሙን ስንጠራ ማድረግ ስላለብን የጥንቃቄ አካሄዶች፣ የእግዚአብሔርን ስም ለመጥራት ሞቻት የማይሠጠን ነገር ሳይኖር፥ የእግዚአብሔርን ስም ወደ ምንጠራበት ሁኔታ ውስጥ ይመራናል ብለን ተስፋ እናደርጋለንን? ብቻ አፋችን ላይ እንደመጣ የመለኮትን ስም መጥራት የሚፈለግ ነገር ነውን? በጭራሽ አይደለም! እግዚያብሔር ስሙን በፍርሃትና በመንቀጥቀጥ የሚጠራዉን ልብ ይፈልጋል።

ሁሉም ሰው በሕይወቱ የሆነ ጊዜ የእግዚያብሔርን ስም መጥራት ወይም አለመጥራት እንዳለበት እንዲወስን የሚገደድበት ሁኔታ ውስጥ ራሱን ያገኛል።አንድ ቀን ሁሉም ሰው በድጋፍ ይሁን በተቃውሞ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ይኑርበት ወይም አይኑርበት እንዲወስን የሚገደድበት ሁኔታ ውስጥ የሚሆንበት ቀን ይመጣል። እያንዳንዱ ሰው ከሌላ ሰው ጋራ ሃይማኖታዊ ጉዳይን በተመለከተ መወያየት ይኑርበት አይኑርበት እንዲወስን የሚገደድበት ሁኔታ ውስጥ ራሱን ያገኘል። እንዲህ ዓይነቱን ውሳኔ ማድረግ ብዙውን ጊዜ አስቸጋሪ ነው። በአንዳንድ የሰዎች መሰባሰቦች መካከል ስንሆን የእግዚያብሔርን ስም ማንሳት እንደሌለብን፣ ከእነ አካቴው ስለሃይማኖት ነገር ከማውራት መቆጠብን ተገቢ እንደሆነ የሚሰማን ወቅት አለ። ምክንያቱም፣ በእነዚህ ሰዎች ፊት ያን ማድረግ አጉል ሃይማኖተኝነት እና የሰዎችን መብት መዳፈር ነው ብለን ስለምናስብ ነው። ነገር ግን ይህ አመለካከታችን ብዙ ጊዜ ግልጽ አይደለም። ምናልባት ይህንን የምናደርገው ተገቢ አይደለም ወይም የሰውን ስሜት የሚጎዳ ነገር ነው ብለን አስበን ይሆናል፣ ነገር ግን ዝምታችን ከፍርሃታችን የተነሳም ይሆን ይሆናል።አንዳንድ ጊዜ የእግዚአብሔርን ስም አለመጥራታችን ተገቢ ሆኖ ሳለ፣ ራሳችንን በፈሪነት እንከሳለን። ይህ አይነት ነገር የሚሆነው በእግዚያብሔር ስም በሚያምኑ ዘንድ ብቻ አይደለም ነገር ግን የእግዚያብሔርን ስም በመቃወም በሚጠሩት ላይም ጭምር የሚፈጠር ነገር ነው። ስለዚህ ትክክል እንሁን፣ አንሁን እርግጠኞች ስላይደለን ዝም እንላለን። ሁኔታው ራሱ እርግጠኛ የሚያደርግ አይደለም።

በስሙ የምናምን እንሁን ወይንም ሰሙን የምንክድ፣ የእግዚአብሔርን ስም በመጥራታችን ብቻ የተገለልን ወይም እንደ ሞኝ የታየን ሊመስልን ይችል ይሆናል። ነገር ግን የእግዚያብሄር ስም ሲጠራ ለመጀመሪያ ጊዜ ለሚሰማ ሰው ይዞለት የሚመጣ በረከት አለ፣ ያም በሕይወቱ ለመጀመሪያ ጊዜ የእግዚአብሔር ህልውና ይሰማዋል፡፡ ስሙን የሚሰማበት ያንቺ ሰዓት የሕይወቱ አቅጣጫ የሚቀየርበት ወሳኝ ሰዓት ሆና ለመታሰቢያ ትቀመጣለች። ደግሞም ምናልባት አስር ጊዜ የእግዚያብሄርን ስም በመጠራቱ ምክንያት ሃይማኖት የተባለን ነገር ሊጠላ የሚችል ሰው ይኖራል።በዚህም ምክንያት ያ ሰው ሃይማኖት ማለት የአምላክን ስም አላግባብ የሚጠቀም እና በከንቱ የሚጠራ ነገር ነው ብሎ ማሰብ ይጀምር ይሆናል። ማንም ሰው ከሌሎች እጅግ አብልጦ አንድን ሰው የሚቀርብ ወዳጅ ቢሆንም እንኳን የዛን ሰው ልብ ዘልቆ መረዳት አይችልም። ምንም ይሁን ምን በአንድ በኩል በድፍረት ለመናገር እና በሌላ በኩል ጥበብ በተሞላው መንገድ ዝም ማለት ባለብን ቦታ ዝም ለማለት ኋላፊነት መውሰድ አለብን። በስሙ ግርማ

መገረም የሌለው እና አክብሮት በጎደለው መንገድ የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ወይም የእግዚአብሔርን ስም መካድ ውስጥ ማንም ሰው ገፍቶ እንዲከተን ልንፈቅድ አይገባም። በስሙ በኩል እና በሰሞኑ ውስጥ ላለው የእግዚአብሔር ህልውና ያለን፤ ከአክብሮት የወጣ ፍርአት እና መቀጥቀጥ ከሕይወታችን መጉደል የለበትም።

ብዙ ሰዎች፥ ለልጆቻቸው ስለእግዚያብሔር ስም በሚያስተምሩበት ጊዜ ከፍርሀት እና አክብሮት የተነሳ ሰሙን ለልጆቻቸው ላለመንገር የመፈለግ ስሜት ውስጣቸው በመኖሩ ምቾት በማጣት ህመም ውስጥ አልፈዋል። ሎሎች ደግሞ ኋላቀርነት እና ጎጂ ነገር ነው ብለው በማመናቸው ለልጆቻቸው የእግዚያብሔር ስም መጥራት እንዳያውቁ ከልክለዋል ነገር ግን ይህን በማድረጋቸው ውስጣቸው በፍርሃት ስለተሞላ በምቾት በሚነሳ ስሜት ተሰቃይተዋል። ልጆችን በተፈጥሮ እና በታሪክ ውስጥ ስላሉ አብዛኛው ነገሮች ያለምንም ሐፍረት ወይም የምቾት ማጣት ስሜት ማስተማር ተፈጥሯዊ እንደሆነው፤ ልክ እንደዚሁ መለኮታዊ ነገሮችን ለልጆች ማስተማር ተፈጥሮአዊ ነገር ተደርጎ መወሰድ አለበት ብለው የሚያስቡ ወላጆች አሉ። ነገር ግን ብዙዎቻችን በእዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እንደ ወላጅ ልጆችን ስለመለኮታዊ ነገር ስናስተምር ምቾት የማይሰጥ፣ እንግዳ ነገር እንደሚሰማን አምናለሁ። ከአዋቂዎች ይልቅ ልጆች፥ ለእግዚያብሔር ህልውና ልባቸው ክፍት እንደሆነ ኢየሱስ ያውቅ ነበር። እኛም እናውቃለን።

ይሁን እንጂ መለኮታዊውን ስም በሆነውም ባልሆነውም በከንቱ የምንጠቀም ከሆነ የልጆቻችንን የተከፈተ ልብ ልንዘጋ እና ልጆቻችን በመለኮታዊው ስም ውስጥ ስላለው ጥልቅ ነገር እና ምሥጢር ሳይገነዘቡ እንዲያድጉ ልናደርጋቸው እንችላለን። ልጆች አይደሉ አሁን በዚህ ነገር መጥመድ ምን ይጠቅማል ብለን ይሁን ወይም ጭራሹኑ መለኮታዊ ነገርን ስለምንቃወም ይሁን ስለመለኮታዊ ነገር እንዳያውቁ ስሙን ከፊታቸው ለመሸሸግ ከሞከርን፣ ባዶነት የልባቸውን ስፍራ ሊይዝ እና በኋለኛ ዘመናቸው በሕይወታችን ውስጥ በጣም አስፈላጊ ከሆነው ነገር ነጠላችሁን ብለው ሊከሱን ይችላሉ። እንደዚህ አይነት አደጋ እንዳይኖር በዚህ መካከል ያለውን ትክክለኛውን መንገድ ለማግኘት በመንፈስ የተቃኘ ዘዴ አስፈላጊ ነው። የትኛውም አይነት ሙያዊ ክህሎት ሆነ የሰነ ልቦና እውቀት የእግዚያብሔርን ስም በሚጠሩበት ሰዓት ትህትና ፣ፍርሃትና እና መንቀጥቀጥ ያለበትን የወላጆችን እና የአስተማሪዎችን አዕምሮ ሊተካ አይችልም።በተለይ ደግሞ የእምነት ትምህርት የሚያስተምሩ አስተማሪዎች የእግዚያብሔርን ስም ሲጠሩ ትህትና፣ፍርሃትና

መንቀጥቀጥ የሚያውቅን ልብ ሊተካ አይችልም። ስለዚህ ወላጆች ፣ አስተማሪዎች እና የሃይማኖት መምህራን የእግዚያብሔርን ስም ሲጠሩ ትህትና ፣ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ ሊኖራቸው ይገባል።

ምንም እንኳን የእግዚአብሔርን ስም በከንቱ የሚጠቀሙ ሰዎች የሚያደርጉት ነገር ያልተገባ መሆኑን ባያውቁም ወይም ባያስጨንቃቸውም፤ ለእግዚያብሔር ስም በፍርሃት እና በአክብሮት የተሞላ ጆሮ ያላቸውን ሰዎች የሚስቆጣ ስሙን በከንቱ የመጠቀም አጉል ልማድ አለ። አሁን የምናገረው፥ እግዚያብሔርን ከማመን ወይም ከመካድ፣ ከአክብሮት ወይም ከንቀት ያልሆነ፥ እንዲሁ እንደ ኑሮ ዘይቤ የእግዚያብሔርን ስም በየአደደባባዩ መጠቀምን በተመለከተ ነው። ነገርዬው በመልካምም ሆነ በጥሩ ፍላጎት ይደረግ፥ የሰውን ፍላጎት ከሚሟላት ጋር የተገናኘ ነው።

በእግዚአብሔር ስም ውስጥ ያለውን ምሥጢር የተገነዘብን እና የተረዳን ወገኖች፥ ይህ ስም በመንግሥት ባለስልጣናት እና በፖለቲካዊ ንግግሮች መሀል፣ በጉባኤ እና ትልልቅ በሆኑ የእራት ግብዣ የፀሎት ሥነ ሥርዓቶች ወቅት፣ በዓለማዊና ሃይማኖታዊ ማስታወቂያዎች ላይ፣ በዓለም አቀፍ የጦርነት ፕሮፓጋንዳ መሐል፥ ስሙ ሲጠራ ውስጣችን በቁጭት እና በሐዘን ይሞላል። በርግጥ፥ ብዙ ጊዜ በዚህ መልኩ ስሙ መጠራቱ የሚወደስ ተግባር ነው። ምክንያቱም ሃይማኖተኛ አገር መሆናችን አመላካች ስለሆነ። እንደውም መመኪያ እና ኩራት ነው። የራስን ሐገር ከሌላው እያወዳደሩ፥ ኩራት እንዲሰማ ያደርጋል። ይህ መወገዘ አለበት? አዎ ሊወገዘ ይገባል ነገር ግን ማውገዝም ቀላል ነገር አይደለም። የመለኮትን ስም፥ በአደባባዮች ላይ በትክክለኛ መረዳት እና እውነት ላይ ተቁሞ፣ ለስሙ በሚገባ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ እና መንፈሳዊ ብልሃት ታክሎበት ከሆነ ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እንዲህ ያለው መንገድ የሚስቆጣ አይሆንም። ነገር ግን ብዙ ጊዜ የሚሆነው እንደዛ አይደለም። ለስሙ ክብር ላልሆነ ዓላማ፥

ጥቅም ላይ በዋለበት ጊዜ ሁሉ፥ የስሙ መጠራት ለከንቱ ነው።

# 2.

መለኮት የሆነውን የእግዚአብሔርን ስም እንዳንጠራ ሞቾት የሚነሳን እና ግራ መጋባት ውስጥ የሚከተን ሌላኛው መሠረታዊ ምክንየት ተጠራጣሪነት ነው።እግዚአብሔርን ስለምንጠራጠር ነው። ስለ ራሱ ስለ እግዚያብሔር ያለን እውቀት ሁሉ በጥርጣሬ የተሞላ መሆኑ ነው። እንዲህ አይነት መጠራጠር፣ ሁሉም የሰው ልጅ ውስጥ ያለ እና ተፈጥሮአዊ የሆነ ነው። እግዚያብሔር እንደማንኛውም በምድር ላይ እንደምናገኘው ቁስ አካል በቀላሉ የምንለየው፣ እንደማንኛውም ነገር በምርምር እና ጥናት የምናረጋግጠው ተጨባጭ እውነታ ቢሆን ኖሮ እርሱ እግዚያብሔር፣"እግዚያብሔር" አይሆንም ነበር።ጥርጣሬ ሳይሸነፍ እምነት ሊኖር አይችልም። እምነት የግድ አንዳች ነገርን በእኛ ውስጥ ማሸነፍ እና ተለምዷዊ የሆኑ ማስረጃ ሊገኙላቸው የሚችሉ ሂደቶችን ተሻግሮ መሄድ አለበት። ምክንያቱም እምነት እና  እውነት የሚገኘው ሳይንስ ማረጋገጫ ሊሰጥበት ከሚችለው ከባቢ ውጪ ካለ ነገር ነው። እምነት፣ ጥርጣሬን ድል የሚነሳ ብርታት ነው።

ሆኖም እምነት ጥርጣሬን ድል የሚነሳው ጥርጣሬን በማስወገድ ሳይሆን፣ ጥራጣሬን  የእምነት አንዱ ቅንጣት ክፍል አድርጎ ወደ ውስጡ በማካተት ነው።እናም በአንድ ነገር እርግጠኛ ሆኛለሁ። የቱንም ያህል እግዚያብሔርን ስር በሰደደ እምነት ብናምን ጥርጣሬም በውስጣችን አለ።ብዙ ጊዜ እንዲህ አይነቱን ጥርጣሬ በቀላሉ የምንለየው ነገር አይደለም፣ነገር ግን የእኛነታችን ጥልቅ ክፍል ውስጥ ተሰውሮ ተቀምጧል።  ከውስጣችን ብቅ እያለ፣ በእኛነታችን ላይ ተፅኖውን ያሳርፋል።በጣም በቅራባችን፣ ጠንካራ እና በምንም የማይናወጥ እምነት ያላቸውን ሰዎች እናውቅ ይሆናል ነገር ግን በአንዳንድ አስቸጋሪ ወቅት በእነዚህም ሰዎች ላይ በውስጣቸው ተሰውሮ የነበረ በእግዚአብሔር ላይ ያለ ጥርጣሬ ካለበት ብቅ ሲል ማየት ብርቅ ነገር አይደለም።

የሀይማኖት መሪዎች፣ በእምነት እና እምነት በማጣት መካከል በአዕምሮአቸው ውስጥ ስላው ትግል፣ በቀጥታም ሆነ በተዘዋዋሪ ሲናገሩ እንሰማለን። በሌላ ጎኑ ደግሞ ወገኛ እና ፅንፈኛ አማኞች፣ ጮክ አድርገው ከሚያሰሙት በእግዚያብሔር ላይ አለኝ ከሚሉት ጠንካራ እምነት ጀርባ፣ አፍነው የያዙት የጥርጣሬ ድምፅ ይሰማል። በውስጣቸው ተቀበረ እንጂ፤ ከማንነታቸው ውስጥ አልተወገደም።

በሌላ መልኩ ደግሞ ትርጉም ካልው ሕይወት የመሸሸ መገለጫ የሆነውን፣ የግልብ ሰውን እግዚያብሔር የለም ክህደት ስንሰማ፣ አብረን ደግሞ ከዚህ ክህደት ጀርባ፣ በጥንቃቄ ማንም እንዳያውቅ ተደርጎ የተሸፈነ ሐዘን፣ ተስፋ መቁረጥ የወለደው ጭንቀት እና ጩህት እንዳምጣለን። ይህ ተስፋ ቢስ ከመሆን የመጣ ጭንቀት ደግሞ፣ በእግዚያብሔር አለመኖር እርግጠኛ ከመሆናቸው የመጣ ሳይሆን፣ ክህደታቸውን ራሱ እንደሚጠራጡ ማሳያ ነው። እና ደግሞ፣ እግዚአብሔርን ለመካድ፣ ሳይንሳዊ አመክኒዮን ከሚደገፋ ሰዎች ጋር በምናደርገው ግንኙነት፣ ጎልቶ የምናገኘው አንድ ነገር፣ በክህደታቸው እርግጠኛ የሚሆኑት፣ ስለእግዚያብሔር የሚታመኑ ነገሮችን ፍርሽ ለማድረግ እስከታገሉ ድረስ ብቻ ነው። ክርክራቸው የቆመ ቀን፤ የክህደታቸው እርግጠኛነት አደጋ ውስጥ ይወድቃል።

በርግጥ፣ ብዙ ጊዜ የሚስቁት እና የሚተቹት፣ ያለ ዕውቀት በሆኑ ሃይማኖተኞች ዘንድ ስለ እግዚያብሔር በሚታመነው እና በሚነገረው እንቶ ፈንቶ ሀሳብ እና መተታዊ ልምምዶች ላይ ነው።ከዚህ አንፃር የሚሰነዝሩት ነቀፌታ ውሃ የሚቋጥር ነው።ይህም ሁኔታ የአሸናፊነት እና ከሁሉ የላቀ እውቀት እንደጨበጡ እርግጠኝነት ስለሚሰጣቸው በክህደታቸው እንደጸኑ እንዲቆዩ ያደርጋቸዋል።ይሁን እንጂ፣ በእውነት እግዚያብሔር ማን ነው ብለው መጠየቅ የጀመሩ ጊዜ፣ ማለትም በጠቅላላ ሕይወት ስላላው ትርጉም፣ በተለይ ደግሞ የራሳቸው ሕይወት ስላላው ትርጉም፣ የምርምር እና ጥናት ሥራቸው  የመጨረሻ ግብ ምን እንደሆነ በጠየቁ ጊዜ በራስ የመተማመን እና የእርግጠኝነት ወኔያቸውን ያጣሉ። ምክንያቱም ማንም ሰው፣እግዚአብሔርን በማመኑ ወይም እግዚያብሔርን በመካዱ ላይ ሙሉ በሙሉ እርግጠኛ  መሆን አይችልም። እግዚያብሔርን፣ በልቡ አምኖ በአፉ የሚመሰክረውም፣ ሙሉ በሙሉ  የሚክደውም፤ ሁለቱም ማለትም የሚያምነው ስለማመኑ የሚክደውም ስለመካዱ፣እርግጠኛ መሆን አይችልም።

እርግጠኝነት የእኛ የሰው ልጆች ማንነት አይደለም።ሰው የሆነው ማነታችን     በምንም ጉዳይ እርግጠኛ ነገር ላይ እንድንደርስ የሚያስችል አቅም እንዳይኖረንአድርጎናል። የእኛ ማንነት ጥርጣሬ ነው። ተጠራጣሪዎች ነን። እግዚያብሔር የካድን ወይም ያመንን ብንሆን ፣በዚህም ሆነ በዚያ ተጠራጣሪዎች ነን። ምናልባት ብዙ ጊዜ እንደሚታሰበው እና እንደሚታመነው ሳይሆን ፣ በመጠራጠር እና በእምነት መካከል ያለው ልዩነት፣ ያን ያህል ትልቅ አይሆን ይሆናል። እምነት እና መጠራጠር ስለሚቀያየጡ ምናልባት አንድ አይነት ሊሆኑ ይችላሉ።  የአንድ ሰው እግዚአብሔርን መካድ የምር እንኳን ቢሆን ”አግዚያብሔር

የለም"፣ ማለቱ ሊያናውጠን አይገባም። ሕይወትን የምር ለሚወስዱ ሁሉ ሊስደነግጣቸው የሚገባው የቸልተኝነት መኖር ነው። እምነትም መጠራጠርም የሌለበት ማንነት። አስደንጋጩ እሱ ነው። ቸልተኛ፣ ትኩስም በራድም ያልሆነ ሰው፥ እግዚያብሔር የሚለው ስም ሲጠራ "ግድ የማይለው ሰው"፥ በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ፥ የሕይወትን መሠረታዊ ጥያቄ ለመመለስ የሚታገል፥ ሰው መሆኑን "ሰውነቱን"የካደ ነው።ስለእግዚያብሔር፣ ስለእውነት ቸልተኛ ተኩኖ ሕይወትን የማወቅ ፍላጎት ሊኖር አይችልም።ካለም ከመሰረቱ የተበላሸ ነው።

ሁልጊዜ የእግዚያብሔርን ስም ስንጠራ ያለው ፍርሃት፣ ምቾት ማጣት የሚመጣው፥ በእምነት ጥልቀት ውስጥ ካለ ተጠራጣሪነት ነው።እንዲህ ያለ ፍረሃት፣ መቾት ማጣት፥ በነቃውም ባልነቃውም ኅሊናችን ውስጥ ሐቀኝነት የመኖሩ መገለጫ ሊሆን ይችላል። አንዳንዴ በውስጣችን የሆነ ነገር፥ "እግዚአብሔር"ለማለት ስንፈልግ "አቁም" ዝም በል ያለን ጊዜ፥ ለአንድ አፍታም ፀጥ ያልንበት ወቅት የለም? እንዲህ አይነቱ ወደ እግዚያብሔር "ልጣራ፤ ልተው" የሚል ማመንታት ራሱ፥ ለእግዚያብሔር ያለንን ጥልቅ ስሜት ሊገልፅ ይችላል። እንዲህ መሆናችን በራሱ፥ በእግዚያብሔር ስም ውስጥ ስላለው ኋይል የሚነግረን አንዳች ነገር አለ። ስሙን በመጥራት እና ባለመጥራት መካከል ስለሚያመነታውም ሰው፥ የሚነግረን አንዳች ነገር አለ። አንዳንድ ጊዜ፥ ብቻችንን በምንሆንበት ወቅት እግዚያብሔር የሚለውን ስም ለመጥራት እናመነታለን። ስለእግዚያብሔር ማሰብ እንኳን አንፈልግም። በፀሎት መንፈስ ውስጥ እንኳን፥ ድምፅ ሳናሰማ ከእግዚያብሔር ጋር ለማውራት፥ "በመፈለግ እና ባለመፈለግ" ውስጥ እንዋትታለን።

ምናልባት መፀለይ ያስተወን፣ በመወላወል ውስጥ የከተተን ተጠራጣሪነት ይሆናል። ከዚህም ባሻገር በእኛ እና በእግዚያብሔር መካከል ያለው የሰማይ እና የምድር ያህል እርቀት ስሙን ለመጥራት የምናመነታ ሊያደርገን ይችላል። እርሱ ከእኛ እሩቆ፥ መድረስ ከማንችልበት ቦታ ላይ የቆመ መስሎ ስለሚሰማን ከእርሱ ጋር ለማውራት አንደፍርም። ይህም ቢሆን የእግዚያብሔርን መኖር፣ የእግዚአብሔር ህልውና ከእኛ ጋር እንዳለ የመቀበላችን ማረጋገጫ ምልክት ነው ሊባል ይችላል። የመለኮትን ስም ለመጥራት ማመንታታችን፣ ስሙን መጥራት ምቾት ስላልሰጠን በፀጥታ ውስጥ መቆየታችን፥ የመለኮትን ሚስጥር ከመዳፈር ይጠብቀናል።

# 3.

የመለኮትን ስም "ስለመጥራት እና አለመጥራት" ስንነጋገር በሁለት ነገር ምክንያት ስሙን መጥራት እንደሌለብን ተነጋግረናል። አንደኛው፣ ከአክብሮት የተነሳ ስሙን አለመጥራት ተገቢ በመሆኑ ሲሆን፣ ሌላኛው ደግሞ ስሙ እንደማንኛውም ስም ስላልሆነ፣ "መጥራት አለብኝ ወይስ የለብኝም" በሚል እርግጡን ነገር ካለማወቅ እና ከሀቀኝነት የተነሳ ዝም ስለምንልበት ሁኔታ ተመልክተናል። ነገር ግን ከሁለቱም ሁኔታዎች ሌላ እጅግ መሠረታዊ የሆነ ስሙን የማንጠራበት ምክንያት አለ። ከአድናቆት፣ መገረም እና ከግርማው አስፈሪነት የተነሳ የመለኮትን ስም መጥራት እንደሌለብን ማወቅ ነው። እስቲ አንድ ጥያቄ እናንሳ ፣ ከዚህ የመጨረሻ ምክንያት የተነሳ ስሙን አለመጥራታችንን እግዚአብሔር ይወደዋልን?መለኮት ሚስጥር በዚህ ምክንያት ስሙን አለመጥራታችንን ከእኛ የሚጠብቅብን ነገር ነውን? በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ እንድንሆን ይፈልጋልን? በእርሱ እንድንደነቅ፣ እንድንገረም እና የግርማውን አስፈሪነት በህይወታችን እንድንለማመድ ግድ ይለናልን? የሕይወታችን ትርጉም የሚገኝበትን ዋነኛው ነገር እርሱም የእግዚአብሔርን ስም መጥራት ምክንያት እየደረደረን መተው አለብን? ስለእርሱ ሳናነሳ እና ስሙን ሳንጠራ መኖር አለብን፣ ዝም ማለት አለብን? መልሱ አይደለም ነው። እግዚየብሔር ራሱ ውስን ወደሆነው እኛነታችን ሰብሮ ሲገባ እና ራሱን ሲገልጥ፣ ማን ብለን ልንጠራው እንደሚገባ ስሞቹን አሳውቆናል። እነዚህን ስሞች መጠቀም እንችላለን። እርሱ እንድንጠራው በሰጠን ስሞች መጥራት አለብን። ዝምታ ኋይል የሚኖረው፣ በሌላኛው ወገን ያለው ሲናገር ፤ በዚህኛው ወገን ያለው ደግሞ ሲሰማ ነው። በዚህ መንገድ ከተረዳነው ዝምታ በራሱ የንግግር አካል መጥራት አለብን። ዝምታ ኋይል የሚኖረው፣ በሌላኛው ወገን ያለው ሲናገር ፤ በዚህኛው ወገን ያለው ደግሞ ሲሰማ ነው። በዚህ መንገድ ከሆነ ዝም ያልነው ይህ አይነቱ ዝምታ በራሱ የንግግር አካል ነው።

በእግዚያብሔ ፊት በስሙ ስንሰበሰብ ስሙን የመጥራት እና ዝም የማለት አስፈላጊነት እጅግ ወሳኝ ጉዳይ መሆኑን የምንረዳው ስሙን በአግባብ ከጠራን ስሙን መጥራታችን ለበረከት የሚሆንልን፤ ደግሞም በከንቱ ከጠራን የሚያስፈርድብን ጉዳይ በመሆኑ ነው። እኛ ስለእግዚየብሔር የሚነገርበት፣ ስሙ የሚጠራበት ጉባኤ ነን። እኛ ቤተ ክርስቲን ነን። ቤተ ክርስቲያን ማለት፣ ቅዱስ የሆነው የእርሱ ሚስጥር በመነደቅ፣ በግርማው ፊት በፍርሃት እና መንቀጥቀጥ በመሆን የምንለማመድበት ቦታ ነው። ነገር ግን ሕይወታችን፣ የሕይወታችን

ልምምድ እንዲህ ነውን? በግልም ይሁን በህብረት ባለን ፀሎት ስሙን በከንቱ እየጠራን ነው ወይስ በአግባቡ እየተጠቀምን ነው? ቁጥራቸው እጅግ የበዛ ከቤተ ክርስቲያን ቅጥር ውጪ ያሉ ሰዎች እንኳን የሚሰማቸው ስለ ስሙ ያለው ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ እኛን ይሰማናል? እንደ አገልጋይነታችን፣ በቅዱስ ቁርባን ውስጥ ያለውንመለኮታዊ መገኘት በምናገለግልበት ወቅት፣ በግርማው የማስደነቀ ክበር ይከበናል? ወይም፣ እንደ ቅዱሱ ቃሉ፣ ሥነ መለኮት አስተማሪነታችን፣ እርሱን ለሌሎች በትክክል ማስረዳት መቻላችን እርግጠኛ ነን? የመጽሐፍ ቅዱስ ጥቅስ ወይም የተመረጡ ፈጣን ቃላት በፀሎታችን ወቅት ከአፋችን ሲፈስ፣ በዚህ ሁሉ ውስጥ በቂ የሆነ፣ ከተቀደሰ ልብ  የወጣ ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ በውስጣችን አለ? የክርስቶስ ባለቤቶች እንደመሆናችን፣እርሱን ራሱን እንድንወርሰው ወራሽ ስላደረገን፣ ስለእርሱ ያለውን እውነት እናውቃለን  ብለን ስንናገር፣ ወይም የእርሱ ህልውና በሚገኝበት ቦታ ስንሆን፣ ወይንም ኋይሉን ለሌሎች ስናገለግል፣ ከእርሱ ጋር ባለን ሕብረት እንዳንላመደው፣ እንዳንዳፈር፣ ከአክብሮት የሆነውን  “ከቅድሱ የመራቅ”፣ እርቀት እንጠብቃለን? በዓለም ዙሪያ ሁሉ፣ በሰንበት ቀን በሚደረገው የአምልኮ ሥነ ሥርዓት ምን ያህል ለስሙ የሚሆን ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ አለ? ምን ያህል በግርማው መደነቅ እና መገረም ህያው ሆኖ በመካከላችን ይገኛል?

አሁን ቤተ ክርስቲያንን እና ምዕመኖቿን፣ አንተን እና እራሴን ጨምሮ፣ ድፍረት የተሞላበት ጥያቄ ልጠይቅ። በቤተ ክርስቲን ውስጥ፣ ስሙን አላግባብ በመጠቀማችን፣ ስሙን በመዳፈራችን ምክንያት ለቁጣው ፍርድ ይሆን ዘንድ ከጊዜ ወደጊዜ ስሙ እንዳይነሳ፣ ስለስሙ ማንም እንዳይናገር በማድረግ ራሱን እየገለጠ ሊሆን ይችላልን? በዚህ ዘመን የእርሱ ‘’መታወቅ’’ በመረሳትን ውስጥ ይሆን? አንዳንድ ጊዜ ሰዎች ስሙን እንዳይጠሩ በማድረግ፣ የስሙን ክብር እየጠበቀ ሊሆን ይችላል። የእግዚያብሔርን ቃል መናገርን በተመለከተ፣ ለቀድሞ ትውልድ በተፈጥሮ እንዳለ ነገር ቀላል የነበረ ስሙን የመጥራት ልማድ፣ ለዚህኛው ትውልድ ደግሞ ሰውሮበት ሊሆን ይችላልን?  እግዚያብሔር የለሽነት፣ በሰዎች የልብ ድንዳኔ ብቻ የሚመጣ ሳይሆን፣ ነገር ግን እግዚያብሔር በራሱ ‘’የአዎ አይ’’ አሰራሩ፣ ሃይለኛ ሰዎችን በማሥነሳት፣ በስሙ ተሰብስበው ነገር ግን ስሙን በከንቱ ባዋሉ ላይ የፍርድ እና ትችት ናዳ እንዲያወርዱ በማድረግ ስሙን በከንቱ ከሚጠሩ እግዚአብሔር የለሽ እንዲሆኑ አድርጓቸው ይሆን? ከቤተ ክረስቲያን ቅጥር ውጪ ያለው ዓለም፣ ዛሬ በሄድንበት ቦታ ሁሉ የሚገጥመን፣ በእግዚያብሔርን ነገር ላይ ያለው ዝምታ፣ ምናልባት ቤተ ክርስቲያን ስለእርሱ ስትናገር፣ ስሙን ስትጠራ፣ ከክብር በወጣ  ፍርሃት እና መንቀጥቀጥ ስለእርሱ ወደምትናገርበት፣ ወደቀድሞ

ቦታ የሚመልስበት መንገድ ሊሆን ይችላልን?

እንዲህ አይነት ጥያቄ መጠየቅ በራሱ፣ ምናልባት ድፍረት የተሞላ ድርጊት ይሆናል። በእርግጠኝነት ምንም አይነት መልስ ላይኖር ይችላል። ምክንያቱም እኛ መለኮት በመግቦቱ ውስጥ የሚሰራውን የሥራውን ባሕሪ አናውቅም። ነገር ግን፣ ምን መልስ ባይኖርም ጥያቄው በራሱ በቤተ ክርስቲያን ቀጥር ገቢ፣ በመቅደሱ ውስጥ ስሙን ሲጠሩ እንደቀልድ እንደማንኛውም ስም ለሚያዩት ሁሉ እንደማስጠንቀቂያ ሊሆን ይችላል።

ግላዊ በሆኑ፣ ማለትም እኔን በሚመለከት እና ግላዊ ከመሆን ባለፉ ጥቂት ቃላት፣ ይህን ሐሳብ ልቋጭ። ስለዚህ ትምህርት እያሰብኩ በነበርኩበት ሰዓት ስለእግዚያብሔር ስም ብቻ የሚያወሳ እንዳይሆን፣ ነገር ግን ስለራሱ ስለእግዚያብሔርም የሚናገር እንዲሆን ለማድረግ ሞክሪያለሁ። እንዲዚህ አይነት ሙከራ ላብራራ የሞከርኩትን “የእግዚአብሔርን የአምላክህን ስም በከንቱ አትጥራ” የሚለውን ቃል የሚጥስ፣ እኔን ከፍርድ ስር የሚያቀምጠኝ ነው። ይሔ በራሱ የተሸሞነሞነ፣ የእግዚያብሔርን ስም በከንቱ የመጥራያ ሌላ መንገድ ነው። እርሱ ራሱን ለእኛ የገለጠበትን ስሞች ብቻ አንስተን መናገር እንችላለን። እርሱ ራሱ፣ “ማንም ሊቀርበው በማይችል ብርሃን ይኖራል፤ አንድ ሰው እንኳ አላየውም ሊያይም አይቻለውም”።

# 13. ጥበብ

*“የጥበብ መጀመሪያ እግዚአብሔርን መፍራት ነው፤ ቅዱሱንም ማወቅ ማስተዋል ነው።”*

*ምሳሌ 9፡10*

## 1.

በዚህ ዘመን፥ በቤተ ክርስቲያን ስብከት እና ትምህርት ውስጥ፥ ጥበብ የሚለው ቃል ሲነገር አለመስማታችን እጅግ የሚያሳዝን ነው። “ጥበብ” የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በክርስትና ውስጥ ብዙም ትኩረት አለመሰጠቱ ያሳዝናል። በርግጥ፥ ሰዎች በተለያዩ ቦታዎች እና በፍልስፍና ውይይት መካከል ጥበብ የሚለውን ቃል ማንሳት አልተውም። ሆኖም ግን፥ የቃሉ  አስፈላጊነት እና ኀይል ሙሉ በሙሉ ጠፍቷል ማለት ይቻላል። ሰዎች፥ ጥበብ ማለት ወጣቱን ትውልድ ግድ የማይሰጠው፥ በእድሜ ገፋ ካሉ ሰዎች የሚገኝ  ፀጋ ብቻ አድርገው ያስባሉ። አሁን በዚ  ትውልድ ጥበብ የሚለው ቃል፥ ዘመን ያለፈበት ሲነገር ከማሳቅ የዘለለ ትርጉም የለውም።

ሰዎች ስለ ልምድ፣ ግንዛቤ እና እውቀት ሲያወሩ ይደመጣል። እርግጥ ነው፥ እነዚህ ቃላት ከጥበብ ጋር የተገናኙ እና ሁልጊዜም ደግሞ የእርሷ አካል ናቸው። ሆኖም ግን ከጥበብ ጋር  አንድ አይነት አይደሉም። ጥበብ ከእነዚህ ነገሮች የበለጠ ታላቅ ነገር ነው። ሁሉንም ሰው በሁሉም የእድሜ እርከን ወቅት ከማሰብ ጋር በተገናኘ ያለን ሕይወት በጥልቅ የሚነካ ነገር ነው። ጥበብ ምሪቅ ለዋጡ ሰዎች ብቻ አይደለም። ወጣቶችም ጥበብ የተላበሱ ሊሆኑ ይችላሉ። ደግሞ፥ በማንኛውም ዕድሜ ላይ ሞኝ ሰዎች ሊኖሩ ይችላሉ። በዚህ ጊዜ፣ ጥበብ ማለት ምን ማለት እንደሆነ እና ለምን በጣም አስፈላጊ እንደሆነ በተለይም ስለ ሕይወታቸው ጥሩ ምርጫ ማድረግ ለሚፈልጉ ወጣቶች ማካፈል እፈልጋለሁ።

ጥበብ ምን ማለት እንደሆነ፥ ስፋቱን እና ጥልቀቱን ለማወቅ፥ ያነበብነውን

የመጽሐፍ ቅዱስ ክፍል የፃፈልን ሰው፥ ጽንሰ ሐሳቡን ባየበት መንገድ ልናይ ያስፈልገናል። በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ፥ በብሉይ እና አዲስ ኪዳን፥ ጥበብ ምን ያህል ታላቅ እንደሆነ የሚገልጹ ብዙ ቃሎች አሉ። በብዙ ሃይማኖቶች ውስጥ፥ ጥበብ በብዙ ማወደስ እና ጥበብን አጥብቆ መፈለግ አለ። ጥበብ በሁሉም ቦታ እና ለሁሉም ሰው ሊኖረው የሚችል ነገር ነው። በዓለም ዙሪያ ባሉ ሰዎች መንፈሳዊ ሕይወት ውስጥ የጥበብ ህልውና አለ። ጥበብ በሰዎች ውስጥ ብቻ ሳይሆን በመላው አጽናፈ ዓለም ውስጥም ይገኛል። አጽናፈ ዓለሙ የተፈጠረው የጥበብ መገኘት ባለበት በመለኮት ኀይል ነው። ምሳሌ መጽሐፍን የጻፈው ሰው እና መፅሐፈ ኢዮብን የጻፈው ባለቅኔ፥ ጥበብ በፍጥርት ጊዜ ህልውናዋ ነበር የሚለውን ሐሳብ ያስተዋውቁናል። ዓለም ሳይፈጠር በፊት ጥበብ ከእግዚአብሔር ጋር ነበረች። ጥበብ "ሰማዮችን በዘረጋ ጊዜ አብሬ ነበርሁ፥ በቀላያት ፊት ክበብን በደነገገ ጊዜ፥" ነበርኩ ትላለች።

የእዮብ መጽሐፍ ጸሐፊ ደግሞ፥ ውብ በሆነ ቅኔ ስለጥበብ ሲናገር፥ "ለነፋስ ሚዛንን ባደረገለት ጊዜ፥ ውኆችንም በስፍር በሰፈረ ጊዜ፥ ለዝናብም ሥርዓትን፥ ለነጐድጓድ መብረቅም መንገድን ባደረገ ጊዜ፥ በዚያን ጊዜ አየት፥ ገለጣትም፤ አዘጋጃትም፥ ደግሞም መረመራት።" ይላል። የእነዚህ ቃሎች ትርጉም ልክ ከጎኑ ራሱን በራሱ ችሎ እንደቆመ ኀይል፥ እግዚያብሔርም፥ አብራው ጎኑ ያለችውን፥ ጥበብን የስሳል የሚል ነው። ከእርሷ ባገኘው እይታም ለዓለም ይህን ቅርፅ ሰጥቷል። በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ያለው ነገር ሁሉ በጥበብ የተሠራ ነው።

ይህንን እውነት፥ ከጥቂት ሳምንታት በፊት በሥነ ፈለክ፣ ፊዚክስ እና ባዮሎጂ መስክ፥ ትልቅ ስም ካተረፉ ከተለያዩ ታዋቂ ባለሙያዎች ጋር በተገናኙሁ ግዜ ማረጋገጥ ችያለሁ። እነዚህ ባለሙያዎች፥ በዙሪያችን ስላለው ስለምኖርበት ዓለም ያላቸውን እውቀት በማስፋታቸው በአጽናፈ ዓለም ውስጥ ስላለው ጊዜ ስለማይሸረው ጥበብ ያላቸውን ግንዛቤ ማሳደግ እንደቻሉ ገልፅውልኝ ነበር። እነዚህ ሊሃቃን፥ ጥበብ የማይሰጥ ወይም ማስተዋልን የማይጨምር የተለመደውን ነገር ግን መረጃን ብቻ የሚያቀርብ ሳይንስን የሚቀበሉ አይደሉም። እንደዚሁ የሰው ልጅ የተፈጥሮን ዓለም በመመርመር የሚያገኘውን ጥበብ ችላ የሚል እና የሚገፋ ማንኛውንም አይነት የሥነ መለኮት አመለካከት አይደግፋም።

በመካከለኛው ዘመን ማብቂያ፥ ሳይንሳዊ የምርምር ዘዴ ሀ ብሎ በተዋወቀበት በ13ኛው ክፍለ ዘመን አንድ አስተዋይ ሰው ይህንን ትንቢታዊ ንግግር ተናገረ"በዚህ አዲስ የምርምር ዘዴ፥ ሳይንስ ማደጉ ሳይታለም የተፈታ ነው ነገር ግን

ጥበብ እየኮሰመነ ይሄዳል" አለ። ለእርሱ ጥበብ ማለት፥ ዓለምንና ሕይወታችንን የሚቀርፁ መርሆዎችን መረዳት ማለት ነው። ትንቢቱ እንከን የሚወጣለት አይደለም። እንደ ተነበየው፥ ሳይንስ ጥበብን ድልነሳ! ለነገሮች ያለን ጥልቅ ዕይታ፣ የመረዳትን ቦታ እውቀት ተካ። አንዱን ከፍለ ለዘመን ጨርሰን ወደ ሌላው ክፍለ ዘመን ስንሻገር፥ ያለ ጥበብ የሆነ እውቀት፥ በውጭም ሆነ በውስጥ፥ ራስን በራስ ማጥፊያ መሳሪያ እንደሆነ ግልጥ ብሎ ታይቷል።

በዘመናችን ያሉ ወጣቶች፥ ይህንን በደንብ መገንዘባቸውን የሚያሳየው፥ ያለ ጥበብ የሆነ እውቀት ባዶ መሆኑን ባገኙት መንገድ ሁሉ እየገለጹ ነው።እውቀት ተብሎ የተማሯቸው ነገሮች በውስጣቸው የያዙትን ትርጓሜ ሳይረዱ፥ ስለ ተጨባጭ ነገሮች ብቻ መማር ብቻውን በቂ አይደለም ብለው የሚሞግቱ ሰዎች፤ እንዲሁም እውቀት ቢኖራቸውም ጥበብ ግን ስለሌለበት ባዶነት የሚሰማቸው ሰዎች፥ በትምህርት ሥርዓታችን ውስጥ ሆነ በማሕበረሰባችን ውስጥ እጅግ የሚያስፈልጉ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ሰዎች ቅሬታቸውን መግለፃቸው ይቀጥሉ! በዕድሜ የበሰሉ ሰዎች ጆሮአቸውን እስኪሰጧቸው ድምጻቸው ይሰማ! ይሁን እንጂ እነዚህ ቅሬታ አቅራቢ ሰዎች ጥበብን በመፈለግ ስም እውቀትን እና ምሁራዊነትን የሚንቁ የሚገፉ ከሆነ፥ በዕድሜ የበሰሉ ሰዎች እነሱን በቁም ነገር ለመመልከት ይከብዳቸዋል። ያም ሆነ ይህ በ'ድሜ የበሰሉ ሰዎች ባላቸው አቅም አና በተሰጣቸው ስጦታ ሁሉ ወጣቱ ትውልድ ወደ ጥበብ ለመሄድ በሚያደርገው ጉዞ ለመርዳት የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው። ጥበብ የሚፈልጉ ሰዎችን ለመርዳት የተቻላቸውን ሁሉ ማድረግ አለባቸው።

## 2.

ጠቢብ እንዲሁ በቀላል የምትገኝ አይደለችም። የጥበብ ህልውና በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ባሉ ክፍሎች ሁሉ ላይ የምትገኝ ቢሆንም  የመለኮት እንቆቅልሽ እና ሚስጥር እንደሆነች መቆየቷ ግን ይቀጥላል። የእዮብ መጽሐፍ እንዲህ ብሎ ይጠይቃል፥"ነገር ግን ጥበብ የምትገኘው ወዴት ነው? የማስተዋልስ ስፍራ ወዴት ነው? ሰው መንገድዋን አያውቅም፤ በሕያዋን ምድር አትገኝም። ቀላይ። በእኔ ውስጥ የለችም ይላል፤ ባሕርም። በእኔ ዘንድ  የለችም ይላል። …….ከሕያዋን ሁሉ ዓይን ተሰውራለች፥ ከሰማይ ወፎች ተሸሽጋለች። ጥፋትና ሞት። ወሬዋን በጆሮቻችን ሰማን ብለዋል።" ይህ ማለት፥ ጥበብ በሰዎች ልጆች የሚደረስባት አይደለችም ማለት ነው። ለጥበብ የሚቀርብ ወዳሴ ለሰው እና ለሀይሉ የሚቀርብ ውዳሴ አይደለም። የሰው ልጅ የመኖር ድምበር ማብቂያ፥  የማይታወቅ ጥልቅ ነገር እና ሞት ብቻ ወደ ጥበብ ይጠቁሙናል። ነገር ግን እነሱም ቢሆኑ ጥበብን አይሰጡንም። ባለቅኔው "የጥበብን ድምጽ ከሩቅ ስፍራ፥ በጭምጭምታ ሰምተዋል።"እንዳለው ነው። ጥበብ ምን ብልህነት ማለት አይደለም። ጥበብ ከብልህነት ይለያል። ጥበብ ማለት ምሁራዊ ልቀት ማለት አይደለም። አመክንዮአዊ አስተሳሰብ ከጥበብ ጋር አይተካከልም። ከሕይወት ይልቅ ሞት ስለ ጥበብ ብዙ ይናገራል። ስለ ጥበብ ከዕለት ተዕለት ሕይወታችን ይልቅ ከሞት የበለጠ እንማራለን። ሞትም ቢሆን የመጨረሻ የሚለው መልስ የለውም፤ የጥበብ እውቀት ከሞት አይመጣም።

ጥበብ፥ በዙሪያችን ባሉ ነገሮች ውስጥ ሁሉ ያለች ብትሆንም ለምን ስውር ሆነች?ጥበብን ማየት ለምን ይከብዳል? ምክንያቱ በሁሉም ሕያዋን ፍጥረታት ውስጥ እርስ በርስ የሚፋለሙ ሁለት ኀይሎች ስላሉ ነው። አንደኛው ኋይል ይፈጥራል። ሁለተኛው ያጠፋል። ነገር ግን ሁለቱም ከአንድ ሰፍራ ከፍጥረት መሠረት፥ ከመለኮት ምንጭ የወጡ ናቸው። የኢዮብ መጽሐፍ እንደሚነግረን "በሽምግልና ጊዜ ጥበብ፥ በዘመንስ ርዝመት ማስተዋል ይገኛል። በእግዚአብሔር ዘንድ ጥበብና ኀይል አለ፤ ለእርሱ ምክርና ማስተዋል አለው። እነሆ፥ ይፈርሳል፥ የፈረሰውም ተመልሶ አይሠራም፤ በሰውም ቢዘጋበት የሚከፍትለት የለም። እነሆ፥ ውኆቹን ይከለክላል፥ እነርሱም ይደርቃሉ፤ እንደ ገና ይሰደዳቸዋል፥ ምድሪቱንም ይገለብጣሉ። ኀይልና ጥበብ በእርሱ ዘንድ ናቸው፤ የሚስተውና የሚያስተው ለእርሱ ናቸው። መካሮችንም እንደ ዘረፋ ይወስዳቸዋል፥ ፈራጆችንም ያሳብዳል። …….. አሕዛብን ከፍ ከፍ ያደርጋል፥ እነርሱንም ያጠፋል፤ አሕዛብንም ያሰፋል፥

እነርሱንም ያፈልሳቸዋል። …….የንጉሱ ግርማ አያስደነግጥምን?” ሁሉም ሰው ሕይወት ውጣ ውረድ እንዳላት ያውቃል ነገር ግን ነገር ግን ባለቅኔው ከሕይወት ክስተቶች በስተጀርባ መለኮታዊ ምስጢር እንዳለ ያምናል። የእግዚአብሔር ጥበብ ከፍጥረት ሥራ ሆነ ከጥፋት በስተጀርባ ያለ ኀይል ነው። ይህ ብሉይ ኪዳን የደረሰበት እጅግ ጥልቅ የሆነ እይታ ነው። በአዲስ ኪዳን ውስጥ የነበሩ ሰዎችም ይህ ግንዛቤ ባይኖራቸው ኖሮ ኢየሱስ እርሱ ክርስቶስ ብለው የተከተሉት የደረሰበትን መከራ ለመቀበል ይቸገሩ ነበር። በሌላ ኋይል የሚገደ’ል፣ የሚሸነፍ አምላክ ለማሰብ አዕምሮአቸው አቅም አይኖረውም ነበር።

የለዚህም እውቀት፥ ጳውሎስ የገዛ ወገኖቹ የምሥራቹን ቃል እርሱም የክርስቶስን ወንጌል አሁን ለሌሎች ሰዎች ጥቅም ሲባል እንደማይቀበሉ በሚያሳዝን ሁኔታ ከተናገረ በኋላ፥ “የእግዚአብሔር ባለ ጠግነትና ጥበብ እውቀቱም እንዴት ጥልቅ ነው”በማለት መደነቅ አይችልም ነበር።

# 3.

እስቲ አሁን እንዲህ ብለን እንጠይቅ፦ እንዴት እንደዚህ አይነት ጥበብ ሊኖረን ይችላል? በምሳሌ መጽሐፍ ውስጥ ጥበብ እንዲህ ትላለች፦ "ሁልጊዜ በፊቱ ደስ ይለኝ ነበር፣ በሚኖርበት ዓለም ደስ ይለኛል፣ በዓለምም ደስ ይለኝ ነበር። የሰው ልጆች . . . አሁንም ልጆቼ ሆይ ስሙኝ . . . እኔን የሚያገኝ ሕይወትን ያገኛል። . . የሚጠሉኝ ሁሉ ግን ሞትን ይወዳሉ።" ጥበብን መፈለግ የሞት እና የሕይወት ጉዳይ ነው። ጥበብን ቸል ማለትም የሞት እና የሕይወት ጉዳይ ነው። እውቀትን አስመልክተን ይህ አንናገርም። እውቀት አስፈላጊ ቢሆንም ጽንሰ ሐሳቡን ወስደን ስንናገር ጥበብ የያዘውን ሁለት ተቃራኒ ተፈጥሮ የያዘ አይደለም። ብዙ የሚያውቁ ሰዎች ከእውቀታቸው የተነሳ ሕይወት የላቸውም። ብዙ የማያውቁ እና ለመማር የማይፈልጉ ሞትን ይወዳሉ ማለት አይደለም። ነገር ግን፥ ጥበብ የሞት እና የሕይወት ጉዳይ ናት። ምክንያቱም እርሷ ከእውቀት በላይ ስለሆነች። ከእውቀት ጋር ልትጣመር ትችላለች። ነገር ግን እራሷን ችላም ለብቻዋ መቆም ትችላለች። ጥበብ በጥናት እና ምርምር ብቻ በማይደረስበት ዓለም ውስጥ ተሰውራ ትኖራለች። ጥበብ የሕይወትን ትርጉም፣ ግጭቶቹን እና የተሸከመውን አደጋ፣ አዲስ ነገር የመፍጠር እና ያለውን የማጥፋት ኋይሉን፣ የመጣበትንና የሚመለስበትን ምንጭ በጥልቀት መረዳት ነው።

ጠቢቡ በስብከቱ፥ ጥበብን ለማግኘት የመጀመሪያው እርምጃ እግዚአብሔርን መፍራት እና ቅዱሱን ማወቅ እንደሆነ ይነግረናል። ይሁን እንጂ እነዚህን ቃላት በተሳሳተ መንገድ ልንረዳ እንችላለን። የሰባኪው ሐሳብ፥ የሚስፈራራ አምላክ እናምልክ ወይም ስለእግዚያብሔር የሚነገሩ ነገሮችን በጭፍን እምነት እንቀበል እያለ አይደለም። ይህን መሰል ምክር ወይም ትዕዛዝ ወደጥበብ ጉየ ሳይሆን ይልቁ ከእርሷ በብዙ እጥፍ ያርቀናል። ያነበብነው ክፍል እያለ ያለው አንድ ሰው፥ መደነቅ ውስጥ ከሚከተው፣ የሕይወቱን አካሄድ እና አመለካከት ከሚያስቀይረው፥ ከቅዱሱ ጋር ፊት ለፊት ካልተገናኘ በቀር ጥበብ ሊያገኝ አይችልም እያለ ነው። በሚያስደንቅ ሁኔታ ከጥበብ እድል ፈንታ ሳይቋደሱ የቀሩ ተድላ እና ፈንጠዝያ ወይም ኀይልን ሲያሳድዱ የሚውሉ እና የሚያድሩ ሰዎች ሳይሆኑ፥ በግርማው "መደነቅን የሚሞላውን"፥ ቅዱሱን ፊት ለፊት ፊፅሞ ያላዩ፥ በማስደንገጡ ሕይወታቸውን ያልዳሰሳቸው ነገር ግን ባዶነታቸውን በአዕምሮአቸው ልዕቀት የሸፈኑ ባለ ብሩህ አዕምሮ ሰዎች ናቸው። እንደነዚህ ያሉ ሰዎች፥ ባዶነታቸውን በእውቀት መደበቅ ይችላሉ። እውቀታቸው በአካዳሚክ እና

አካዳሚክ ባልሆነው ማህበረሰብ ውስጥ ጉልህ ሚና ቢጫወትም፥ ብዙ ጊዜ ግን በእነዚህ ሰዎች ውስጥ ጥበብ ሲንፀባረቅ አናይም። ዓለምን የፈጠረው ዘላለማዊ ጥበብ እነዚህን ሰዎች ሞኞች ይላቸዋል።

አንድ ሰው ከሕይወት እንቆቅልሽ ጋር ፊት ለፊት ከተገናኘ የጥበብ ምንጭ በር ጋር ደርሷል ማለት ነው። በናፍቆት እና በመደነቅ ከጥበብ ጋር ፊት ለፊት ሲገናኝ፣ ጥበብን ከመንገድ ሲያገኛት፥ የእርሱ ማንነት እና እርሱ ወጥቶ ከመጣበት "የማንነቱ መነሻ ምንጬ" ጋር ሰማይ ከምድር እንደሚርቅ ያለውን እርቀት በሕይወቱ ይገነዘባል። የማንነቱን ውስንነት ያውቃል። እናም "መጀመሪያ እና መጨረሻ" በሌለው በእርሱ ፊት፥ ምን ያህል ውስን መሆኑን ይገነዘባል። ወደጥበብ ለመጓዝ የራስን ውስንነት ማወቅ ወሳኝ ምዕራፍ እንደሆነ ይማራል። ሞኞች ግን እንደርሱ አይደሉም በውስንነታቸው ምክንያት በተቀመጠውን ገደብ ላይ እግራቸውን ያነሳሉ። በእውቀት እና በኋይል ያልተወሰኑ እንዲሆኑ ይመኛሉ። ብልህ ግን ውስንነቱን ይቀበላል። ብልህ ሰው እርሱ ፍጡር እንጂ ፈጠሪ እንዳልሆነ ያውቃል።

ነገር ግን ይህንን እውነተኛ ጥበብ ያስተዋሉ እና በዚህ እውነተኛ ጥበብ ምክንያት ጥበበኞች በሆኑ ሰዎች ውስጥ በብዙ ህመም እንኳን ቢሆን በላያቸው ላይ የተጫነ የውሸት ውስንነት ይወገዳል።፣ እውነተኛው መለኪያ፣ ተፈጥሮአዊ የሆነው ውስንነት ከተደበቀበት ይገኛል።። ጥበብ ድንበር ተሻግራ ወደ ሰዎች ስትመጣ የሚሆነው ይህ ነው። የሰው ልጅ፥ በጥበብ ዙሪያ የከተባቸውም ሁሉም የጽሑፍ ሥራዎች፥ ለዚህ እውነት ህያው ምስክር ናቸው። ጥበብ ማለት፥ ለውስንነታችን እውቅና መስጥት ማለት ነው። ጥበብ ማለት ገደብን ማወቅ ነው። ጥበብ ማለት በሁሉም የሕይወት ዘርፎች መካከል ባለው ግንኙነት ትክክለኛው ሚዛን ምን እንደሆነ ፈልጎ ማግኘት እና ያን ሚዛን ማስጠበቅን ማወቅ ነው። መገንዘብ ነው። ነገር ግን ይህን ስንል ከአዕምሮአችን ሊጠፋ የማይገባው። አንድ ሰው ጥበብን፥ በኋላ አደገኛ መዘዝ ይዞ ከሚመጣ፥ ጥበብን አሳስቶ ከመተርጎም ወይም የጥበብን ጽንሰ ሐሳብ ቀይሮ ከማቅረብ አደጋ ሊጠብቃት ይገባል። ጥበብን፥ "ከማላውቀው መልዓክ የማውቀው ሰይጣን ይሻለኛል" በሚል፣ ከወግ አጥባቂነት የተነሳ ወይም ግንዛቤ ከማጣት የተነሳ፥ ስር ነቀል ለውጥ ከማድረግ ወደኋላ ማፈግፈግ ጋር አጣምሮ ከመረዳት መጠበቅ ያስፈልጋል።

ለጊዜያዊ እና ለአጭር ጊዜ ጥቅም ከሚደረጉ ከሥነ ምግባር እና ትልቁ ምስል ጋር ግንኙነት ከሌላቸው "ልከክልህ እከክልኝ ድርድሮች" ጋር ጥበብን

ከማሳከር መጠበቅ ያስፈልጋል። የራስን ጥቅም ለማስጠበቅ ብልጣብልጥነት እና ማታለልን ተጠቅሞ አንዳች ውጤት ማምጣትን፥ ጥበብ ነው ብለን እንዳንገነዘብ መጠንቀቅ ያስፈልጋል። ይሄ ሁሉ ከቅዱሱ ጋር ፊት ለፊት ስንገናኝ፥ በግራማው መደነቅ ውስጥ ሳለን ካገኘነው ጥበብ እጅግ የራቀ ነው። ይህንን በደንብ ለመረዳት ለህዝባቸው አዳዲስ ሕግጋትን የሰጡ፥ አዲስ የአኗኗር ዘይቤዎችን ለመላው አህጉር ያስተማሩ ወደ ተፈጥሮ በረሃዎችም ሆነ ወደ ነፍሳቸው በረሃ ወርደው ብዙ እውቀትና ጥበብ ይዘው የመለሱ፥ በታሪክ እና በተለያዩ ባህሎች ውስጥ፥ በሁሉም ሰው ዘንድ ጥበበኞች ይባሉ የነበሩትን ታላላቅ ሰዎች ዞር ብሎ መመልከት የግድ ያስፈልጋል። ሁልጊዜ ስር ነቀል ውሳኔ ከማድረግ የሚቆጠቡ እና በህብረተሰቡ ውስጥ ከተለመዱ ነገሮች ጋር ተስማምተው ከሚኳዙ ሰዎች ላይ ጥበብ ሊገኝ አይችልም።

ተቀባይነት ካላቸው የሕብረተሰቡ አመለካከቶች እና እምነቶች ጋር በመስማማት "ጉልህ ምርጫዎችን"፥ ከማድረግ ከሚሸሹ እና ከሁኔታዎች ጋር አመቻምቸው ከሚኖሩ ግለሰቦች ዘንድ ጥበብ አይገኝም። ጥበብ የሰውን ልጆች ትወዳለች። ምርጫዋ ግን እስከ ስህተታቸው እና ሞኝነታቸው ወደ ጉያዋ የሚሮጡትን ነው። ጥበብ ሞኝም ብልህም ያልሆኑትን ግን ትንቃለች። አደጋን ተጋፍጠው በመውደቅ እና መነሳት ውስጥ በማለፍ የማይማሩ እና ጥበበኞች እንዲሆኑ በሚያደርጋቸው መንገድ የማይጓዙትን ትሸሻለች። እነዚህን ሰዎች እውነትም ሞኞች ትላቸዋለች። ምክኒያቱ የሕይወት ሚስጥር፣ እንቆቅልሽ ፊት ለፊት አግኝቶ አላናወጣቸውም። ከዚህም የተነሳ በመለኮት ጥበብ አሰራር ውስጥ፥ በመትከልና በመንቀል፥ በመፍጠር እና በማጥፋት ያለውን አንድነት ልዩነት ማየትና መረዳት ከቶም አችሉም።

ጥበብ ወደ ተማሩ ሰዎች ዘንድ ብቻ አትሄድም። ነገር ግን ወደ ሁሉም የሰው ልጆችትሄዳለች። ሁሉንም የሰው ልጆች  ለማግኘት ትሄዳለች። አንድ ሰው ታላቅ የሆነ ጥበብን ማየት ከፈለገ፥ የሚያስተውል የለም እንጂ ብዙ ጊዜ መገኛዋ በተራ ሕዝብ መሐል ነው። አብረን ከምንኖራቸው፣ ከሥራ ባልደረቦቻችን፣ በተጨናነቁ ጎዳናዎች ስናዘግም ድንገት ከምናገኛቸው ሰዎች መሐል፥ ጥበበኞች ሊኖሩ ይችላሉ። ጥበብ ከእናቶች እና ከመበልት ሴቶች ጋር ትሆናለች። ጥበብ ከታዳጊ ልጆች እና ወጣቶች ዘንድ ልናገኛት እንችላለን። ከእረኞች እና ሹፌሮች መካከል ትቀመጣለች። እጅግ ከተማሩት በእውቀት ከላቁ ዘንድም፥ ጥበብ ትገኛለች። ሁሉም ከጥበብ ማዕድ መቋደሳቸውን እንደሰው ውስን መሆናቸውን እና ለሁሉም

ነገር ገደብ እንዳለው፥ ፋይዳ ባለው መልኩ በመቀበል ያረጋግጣሉ።

ነገር ግን ውስንነቱን ሊቀበል የሚችል ማን ነው? ለሕይወት ተግዳሮቶች፣ ለሕመም፣ አልፎ ተርፎም ለሞት ታልፎ የተሰጠ መሆኑን ማን ሊቀበል ይችላል? በፈንጠዝያ እና እረፍት በሌለው መኳተን ራሳን በመጥመድ ጨርቅ ሳይሸፍን፥ የመኖር አንዱ ገፅታው ጭንቀት እና ጥልቅ ሐዘንም ጭምር ነው ብሎ ማን ሊቀበል ይችላል? የሕይወት እንቆቅልሽ ሚስጥራዊነቱ እጅግ ብርቱ በሆነ ሁኔታ የተገለጠበት የኢዮብ መጽሐፍ ውስጥ ለቀረቡ ወሳኝ ጥያቄዎች የተሰጠው መልስ ከጥያቄው ጋር ዝምድና የሌለው ነው። ለአንዱም ጥያቄ መልሰ ሲሰጥ መልሱ እንዲህ ይሆናል ተብሎ የተጠበቀውን አልነበረም።አንድ ሰው አስደንጋጭ እና አስፈሪነቱ፣ ውስብስብ እና ማለቂያ የሌለው ጥልቅ መሆኑን ቢረዳም፥ ልክ ኢዮብ እንደነበረበት ሁኔታ ውስጥ ቢሆንም እንኳን ውስንነቱ ያመጣበትን ውጣ ውረድ ሊቀበል የሚችለው ዘላለማዊ ጥበብን በመጋፈጥ ብቻ ነው። ከእርሱ ጋር ሙግት በመግጠም ብቻ ነው። በእውነት ቅዱስ ከሆነው ከእርሱ ጋር በግራማው መደነቅ ውስጥ ሆነን የሕይወትን ሁሉ ሚስጥር ፊት ለፊት ስናይ፣ በፊቱ ስንቆም ውስን መሆናችንን እንድንቀበል እና በዚህ መቀበል ውስጥ ደግሞ ጥበበኞች ወደመሆን የምንመጣበትን ብርታት እና ሀይል የሚሰጠንን አዲስ የሕይወት አቀጣጫን እንለማመደለን።

# 4.

ስለ ጥበብ በተጻፋ ጽሑፎች ውስጥ፥ ለዕለት ተዕለት ኑሮ የሚጠቅሙ ብዙ ልዩ የሆኑ መመሪያዎች ተሰጥተዋል። መጽሐፍ ቅዱስ በዚህ ምክር የተሞላ ነው። ሁሉም ተግባራዊ የሚሆኑት ከቅዱሱ ጋር ባለ ህያው ሕብረት በመሆኑ፤ ሁሉም መመሪያዎች እርስ በርስ የተያያዙ ናቸው። ሁሉም ውስጥ፥ ጥበብ ውስንነትን በመቀበል ውስጥ ትገለጣለች። ይህን ግንዛቤ በአዕምሮአችን ይዘን፣ ጥበብ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን እንዴት እንደምትገለጥ እንመርምር። ለቤተሰባቸው፥ በኋላ ሊሰበር የሚችል የሐሰት ጣዖታት ከመሆን በሚቆጠቡ እና የኀይላቸውን ወሰን በሚረዱ ወላጆች ላይ የጥበብ ህልውና ከእነርሱ ጋር ነው፡፡። የጥበብ ህልውና በልጆች ውስጥ ሊንፀባረቅ ይችላል። ልጆች የነፃነታቸውን መጠን ሲገነዘቡ፣ እና በወላጆቻቸው ላይ በሚያምፁበት ጊዜ እንኳን፥ ከትውልድ ትውልድ የተላለፈላቸውን ቅርስ እና ትውፊት የማይንቁ ሆነው ሲገኙ፥ ጥበብ በእነርሱ እንደፀደቀች ይታወቃል። እውነትን ሲያስተምሩም ሆነ ከተማሪዎቻቸው ጋር ባላቸው ግንኙነት፥ ውስን ሰው መሆናቸውን በሚገነዘቡ አስተማሪዎች፥ ጥበብ በእነርሱ ዘንድ እንዳለች ይታወቃል። በሚያስተምሩበት ጊዜ፥ በሚያካፍሉት እውቀት ውስጥ፥ ጥበብ እንዲያበራ ፈቅደው ይሁን አይሁን ያለሚቋረጥ ይመረምራሉ።

ከሚማሩት ማንኛውም ትምህርት በስተጀርባ ያለውን መርህ እና ያ መርህ ለሕይወታቸው ያለውን ፋይዳ የሚመረምሩ፣ የሚጠይቁ ተማሪዎች ጠቢባን ናቸው። የእውቀትን፣ የመማርን አስፈላጊነት እና ደግሞም ውስንነት፥ ከሁሉም ይልቅ ፍቅር ከእውቀት እንደሚልቅ የሚገነዘቡ ጠቢባን ናቸው። ከሴቶች ጋር ባላቸው ግንኙነት፥ እንደ ወንድ የስሜት እና እውቀት ገደብ እንዳላቸው የሚገነዘቡ ወንዶች፥ ጠቢባን ናቸው። ወንዶች፥ በሰው ልጅ ማሕበርተኙነት፥ እንደነሱ ሰው እንደሆኑ በመቀበል ለውስንነታቸው እውቅና የሚሰጡ ሴቶች ጠቢባን ናቸው። ወንዶችም ሆኑ ሴቶች ሁለቱም፣ ያለብስጭት፣ መበዳደል፣ ግጭት እና መከዳዳት፥ ነገር ግን ከዘላለም የሆነውን፥ የማይለዋወጥ እርሱን፥ ከመገንዘብ በመጣ የፍቅር ኀይል የሚቀባበሉ ከሆነ ብልሆች፣ ጠቢባን ናቸው።

ጥበብ እጅግ የሚያስፈልገን ወቅት ውስንነታችንን ለመቀበል እጅግ ከባድ ህመም በሚሆንበት ወቅት ነው።በወደቅን፣ በስህተት በተሰናከልን እና በሞኝነታችን ምክንያት ባደረስነው በደል በጥፋተኝነት ስሜት በምንሰቃይበት ሰዓት ጥበብ ያስፈልገናል። ለሰው ውድቀትን መቀበል ከባድ ነው። ምናልባትም

በምንሰራው ሥራ ሁሉ የሚገጥመንን ውድቀት መቀበል ከባድ ነው። ስህተትን አምኖ መቀበል እጅግ ከባድ ነው። በጓደኝነት ይሁን በትዳር በተጣመርነው ሰው ላይ የምንፈርደው ፍርድ ስህተት ሆኖ ሲገኝ ስህተትን መቀበል ከባድ ነው። እኛ ሁሌ ልክ ነን ብለን ስለምናምን ከልባችን የሚበልጠውን እርሱ ዘለዓለማዊውን ካላየን በቀር ለእኛ ለሰው ልጆች በደላችንን ለራሳችን እና ለሌሎች መናዘዝ እጅግ ከባድ ነው። ምንም እንኳን በመከራ አልፎ እና በህመም የተማረው ቢሆንም ይህን መሰሉ ጥበብ ያለው ሰው በእግዚአብሔር ዘንድ ካለው ዘለዓለማዊ ጥበብ ውድቀት ይሁን ስህተት፣ ወይም በደል አንዳች እንኳን ሊለየው እንደማይችል የውቃል።

የመጨረሻው ሊኖረን እና ልንቀበለው የተገባ ጥበብ ሞኝነታችንን እና የራሳችንን ጉድለት መቀበል ፤ እውነተኛ ጥበብ ሞኝነት ሆኖ በታሪክ የተገለጠበትን ቦታ መመልከት ነው። ያ ሞኝነት ሆኖ የተገለጠው እውነተኛ ጥበብ የክርስቶስ መስቀል ነው። እነሆ ለዘላለም ከእግዚአብሔር ጋር የነበረ ጥበብ፣ በመላው አጽናፈ ዓለሙ ወስጥ በህልውናው የሚገኝ እና የሰው ልጆችን የሚወድ ፍቅር በሙላት ተገልጧል። ያንን በሚከተሉ እና በሚመለከቱ ውስጥ ጥበብ እና እምነት አንድ ይሆናሉ።

# መጽሐፍ ሁለት

## (የክብር ሸማ)

# 1. ሴቷ እና ወንዱ

እኔ ማን ነኝ የሚለው ጥያቄ በሁሉም ቦታ እና በሁሉም ዘመን የሚነሳ የሰው ልጅ ጥያቄ ነው። በሁሉም ዘመን እና ቦታ ያለ ሰው ለእነዚህ ጥያቄዎች መልስ ነው የሚለውን በተለያየ መንገድ አቅርቧል። የሁሉም ሰው ጥያቄ ቢሆንም፣ ደግሞም ሁሉም ሰው የእኔ  የሚለው መልስ ቢኖረውም፤ ቅርፅ፣ ይዘት እና ትርጉም ባለው መንገድ ይህን ጥያቄ ሊመልሱልን የሞከሩት የሥነ መለኮት ሊቃውንት፣ ፈላስፎች፣ ፀሃፌዎች እና በዚህ መስክ የተሰማሩ ምሁራን እንደሆኑ ጥያቄ አያሥነሳም። እኛም ወጥና ትርጉም ያለው መልስ ይዘን እና የራሳችንን እይታ አክለን ስለ እኛነታችን ጥልቅ መረዳት እንዲኖረን ካስፈለገ፤ የእነዚህን ሊቃውንት እና ፈላስፎች ሥራ ዞር ብሎ መመልከቱ ግድ ይለናል። በዚህ ክፍል የኤሜል ብርነርን ከማንነታችን ክፍል አንዱ ስለሆነው ፆታ እና ፆታዊነትን አስመልክቶ ያቀረበውን ጽሑፍ እንመለከታለን።

## 1.1. ከተፈጥሮ የሆነውን ፆታዊ ልዩነት ስንዳስስ

የፆታና እና ፆታዊነት ፀንሰ ሐሳብ ላይ ትኩረታችንን ለማድረግ የምንገደድበት ዋናው ምክንየት ስለ አካለ ሥጋችን ማወቅ ግድ ስለሚለን ብቻ ሳይሆን፣ በዋነኛነት ከግለሰባዊነት ጽንሰ ሃሳብ ጋር የተቆራኝ በመሆኑ ነው። ፆታ እና ፆታዊነት ከተቃራኒ ፆታ ግንኙነት እና ዘር ከመተካት በላይ በዋነኛነት ግለሰባዊነት ምንድን ነው ከሚለውን ጥያቄ ጋር በብርቱ የተቆራኝ ጉዳይ ነው። ፆታ እና ፆታዊነትን በተመለከተ ሁለት አተያዮች፣ አንዳንዴ በመደጋገፍ ብዙ ጊዜ ግን እርበርስ በመቃረን፣ ከፊት ይቆማሉ። እነርሱም ሥነ ሕይወታዊ (Biological Perspective) የፆታ እና ፆታዊነት አተያይ እና ግለሰባዊነትን (Individuality) የምንረዳበት የፆታ እና ፆታዊነት አተያይ ናቸው። የዚህ ፁሑፍ ዋና ዓላማ ደግሞ ፆታ እና ፆታዊነት ከግለሰባዊነት ጋር ያስተሳሰረውን ጉዳይ በመመርመር ላይ ያተኩራል።

በዚህም ምክንየት ፆታ እና ፆታዊነትን መረዳት፣ ትኩረት ሰጠነው ወይም ነፈግነው ተፈጥሮአዊ ሂደቱን ተከትሎ የሚፈስ ወይም እንደትርፍ ጥናት የሚታይ

ሳይሆን “ሰዎች ራሳቸውን እና ማንነታቸውን እንዴት እንደሚገነዘቡ የሚታወቅበት፣ ከማንነት ጋር በጥብቅ የተቆራኘ ጉዳይ ነው። ፆታ እና ፆታዊነት ራስን ከመሆን ጋር የተሳሰረ ነው። አንድ ሰው እኔ ማን ነኝ የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ፣ እርሱነቱን የሚገልጡ ነገሮችን ማስቀመጥ ግድ ይለዋል። ስለዚህ አንድ ግለሰብ ከሌላው ግለሰብ ለመለየት እና ማንነታዊ መገለጫ ስንሰጥ የተገኘበትን ዘር ወይም ያለውን ሥነ ልቦናዊ መገለጫ ወይም አዕምሮአዊ ሥራውን እና ብቃቱን እንደምንጠቅሰው፤ ፆታም የማንነት መገለጫ ነው። የሰው ልጅ ግለሰባዊ ማንነቱ የሚለየው በዘሩ፣ በሥነ ልቦናው፣ በሰውነት አካሉ፣ በአዕምሮአዊ ችሎታው እንደሆነው እንዲሁ ሴት ወይም ወንድ የመሆኑ እውነታም የግለሰባዊ ማንነቱ መለያ ነው። ‘ሰው ማን ነው ስንል ጥቁር ወይም ነጭ፣ ሃብታም ወይም ድሃ ብለን ከምንለየው በላይ፤ ወንድ ወይም ሴት በሚለው ልዩነት ተከፍሎ የሚታይ ይሆናል። ’ በሰው መካከል ያለ አንድ እና መሠረታዊ ልዩነት ወንድ እና ሴት መሆን ብቻ ነው። ነገር ግን ይህን ልዩነት ወደጎን የምንገፋ ከሆነ፣ ሰው ማን ነው የሚለውን ጥያቄ ለመመለስ እንቸገራለን። ወይም መልሳችን ጎዶሎ ነው። ‘ምክንያቱም የፆታ ልዩነት ግለሰባዊነት ከሚያካትታቸው ሁሉም ነገሮች አልፎ የሚሄድ ጥልቅ ነገር በመሆኑ ነው።

የፆታዊነት ጥያቄ አንድን ግለሰብ ከሚገልጡ ነገሮች ሁሉ መሠረታዊ እና ከፊት የሚመጣ ጉዳይ ነው። ሰዎች እኔ ማን ነኝ ሲሉ ወደ አዕምሮአቸው ከሚመጣላቸው የዘር፣ የሃይማኖት፣ የፀባይ፣ የሥራ እና ችሎታ መገለጫቸው በላይ የማንነታቸው መገለጫ ፆታዊ ማንነታቸው ነው። ይህ ብቻ ሳይሆን እነርሱም እራሰቸውን ለመረዳት ሌላውም እነርሱን ለመረዳት ፆታዊ ማንነታቸው ግምት ውስጥ መግባት አለበት። ፆታዊነት ደግሞ አንድን ሰው ከሌላ ሰው መለየት ከመያስችሉን ፀባዮች በላይ የሆነ ማንነት ነው። የሰውን ልጅ ልዩነት ከሚያሳዩን ብዙ ነገሮች የበለጠ ‘በወንድና በሴት መካከል ያለው ልዩነት የሰውን ልጅ አንዱን ከሌላው በመለየት እና በመረዳት ረገድ ጉልህ ሚና’ አለው። “የሰው ልጆችን ጨለምተኛ እና ብሩህ ነገር የሚታየው፣ ድብቅ እና ግልፅ፣ ጥቁር እና ነጭ፣ ድንቅ ጭንቅላት ያለው ወይም ደካማ ተብለው ይከፈላሉ ብለን ለመናገር አንደፍርም ነገር ግን የሰውን ልጅ ልንከፍልበት የምንችለው እርግጠኛ የሆነ ነገር ሴት እና ወንድ የመሆናቸውን ነገር ነው።” እነዚህ ልዩነቶች እንደ ሰው ስንኖር የምንኖርበትን መሠረታዊ ምክንያት የሚነኩ ነገሮች ናቸው። ከዛም ‘አልፈው እንደ ሰው ያለንን ማንነት እና የምንኖርበት ዓለማ የሚነኩ ነገሮችም ናቸው። አንድ ሰው በሚኖርበት እድሜ መጠየቅ ያለበት ጥያቄ በሕይወቴ የሚገጥመኝ እና  የማከናውናቸው ነገሮች እንደ አንድ ወንድ እና

እንደ አንድ ሴት ምንድን ነው?’ የሚለውን የሚመለከት ጥያቄ ነው። ምክንያቱም ፆታ የአንድ ሰው ማንነት እና ድርጊት የሚፈቅዱ እና የሚከለክሉ ነገሮች በመሆናቸው ነው።

አንድ ሰው፣ ሰው ስለሆነ ብቻ በማንኛው ጊዜ ተነስቶ የፈለገውን ማድረግ አይችልም። በፆታ ልዩነት ውስጥ ማድረግ የሚችላቸው እና የማይችላቸው ነገሮች አሉ። ፆታ እና ፆታዊነት ይህን ያህል ጠልቆ የሚሄድ ነገር ነው። “እና ይህ ልዩነት ሄዶ ‘የማንነታችንን እና የሕይወታችንን አላማ’ በቀጥታ ይነካል።” በሥነ ምግባር ጥናት ውስጥ ትዳር ዋነኛ የትኩረት አቅጣጫ መጠናት ያለበት የውዴታ ግዴታ እንደሆነው ሁሉ፣ የፆታ ጥያቄን የመመለሱ ጉዳይ አንትሮፖሎጂን የሚመለከት ወሳኝ የሆነ ጉዳይ ነው። ነገር ግን፣ የፆታ ልዩነት መኖር አስፈላጊነቱ ለፈላስፎች ብቻ ሳይሆን (ገና ከጅምሩም ወንዱን ብቻ ማዕከል አድርገው ሲያሰላስሉ ለኖሩት) ነገር ግን ለባለቅኔዎች፣ ተረት ፈጣሪዎች እና ፀሀፊዎችም ጭምር አስፈላጊ ነው። በዚህ ዘሪያ ላለ ያልተመለሰ ብዙ ጥያቄ መፀሀፍ ቅዱስ የሚለው ነገር አለ ወይም የሚለውን መመልከት ወሳኝ ነገር ነው። “መጽሐፍ ቅዱስ ስለዚህ ችግር የሚናገረው የተለየ ነገር አለው?” የሚል ጥያቄ ተገቢነት ያለው ጥያቄ በመሆኑ መልስ ልንሰጥበት ይገባል።

“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ፤ በእግዚአብሔር መልክ ፈጠረው፤ ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው።” ይህ በጣም ቀላል እና ቀጥተኛ የሆነ ኀይለኛ እና እጥር ምጥን ያለ መግለጫ፣ በውስጡ ምን ያህል ጥልቅ እንደሆነ እና የት ድረስ የሚሄድ ሐሳብ እንደተሸከመ ላናስተውል እንችላለን። ነገር ግን ይህ ቀላል የሚመስል ቃል “አፈ ታሪኮችን፣ ድነት የሚገኘው በእምነት ሳይሆን ግለሰቡ ስለመለኮት ባለው እውቀት ነው የሚድነው የሚለውን የኖስቲዝም ጽንሰ ሀሳብን፣ ተጠራጣሪ አመለካከትን፣ ሥጋን በከንቱ የመጨቆን ከንቱ ኟይማኖተኝነትን፣ አምልኮተ ግብረ ሥጋ ግንኙነትን እና የፆታ ፍርሃትን ገደል የከተተ” ቃል ነው።

“እግዚአብሔርም ሰውን በመልኩ ፈጠረ” የሚለውን ሐሳብ” ወንድና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው” ከሚለው ጋር ማዋሃድ አግራሞት እና ሳቅ የሚያጭር የሞኝነት ቃል ይመስላል “ነገር ግን በጠቅላላው፣ የሰው ልጅ ራሱን ለመረዳት ባደረገው ታሪክ ውስጥ ይህ መግለጫ ለመጀመሪያ ጊዜ የቀረበው አንድ ጊዜ ብቻ እና በዚህ ቦታ ነው። ይህ ባይሆን ኖሮ የሰው ልጅ በሺ መንገዶች ይህ ሐሳብ የሚቃረን የሆነ ነገር ማለቱ አይቀርም ነበር።” የሰው ልጅ አንዳንዴ ስለዚህ ጉዳይ ጥቂት ይላል። ሌላ ጊዜ ብዙ ነገር ይናገራል። ደግሞ በሌላ ወቅት በችግሩ አንድ አካል ላይ አብዝቶ ያተኩራል።

በሌላ ጊዜ ደግሞ መልሶ ይህ አይነቱ ችግር በመኖሩ ራሱ ይቆጣል። መጽሐፍ ቅዱሳችን እንደ እግዚያብሔር ቃልነቱ፣ በዚህ በሁለቱ ሐሳቦች ብቻ፣ ማለትም ሰውን በአምሳሉ ፈጠረው የሚለው እና ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው በሚለው ከሌሎች መፅሐፎችም ልቆ ይቆማል።

በዚህ አንድ ቃል ምክንየት ብቻ በእነዚህ ሁለት መግለጫዎች፦ እግዚያብሔር ሰውን በመልኩ ፈጠረ እና ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው በሚለው መካከል ትስስር እና ግንኙነት አለ ማለት ነው። እኛም ስለዚህ እውነት በጥልቀት በምናሰላስልበት ወቅት፣ ጥቂት ወይም ደግሞ ከመጠን አልፈን እንዳንናገር በጥልቀት ማሰብ አትራፊ ነው።

ሕይወት ያለውም ሆነ የሌለው ሁሉ የተፈጠረው  ወንድ እና ሴት ሆኖ ነው  ሚለው አመለካከት የተሳሳተ ነው። ሴላቸውን በመከፋፈል የሚራቡ እና በፆታቸው የማይለዩ ሕይወት ያላቸው ነገሮች አሉ። ደግሞ ሌሎች ፍጥረታት በአንዱ ውስጥ ሁለቱምን ጾታ አካተው የያዙ አሉ ። ሰው ወንድ እና ሴት በሆኑ ፍጥረታት ምድብ ውስጥ እንጂ፣ ከዚህ ውጪ ባሉ ፍጥረታት ውስጥ መሆን የለበትም ተብሎ አስቀድሞ የተወሰነ ውሳኔ የለም። ሰዎች ለመራባት የግድ ጥንድ መሆን ከሚያስፈልጋቸው እንስሳት ጋር መመደብ እንዳለበት ተወስኖ እንደነበር እርግጠኛ ሆነን መናገር አንችልም። የሰው ልጅ ከአጥቢ እንስሳት ቢመደብም ሥነ ሕይወታዊ ተፈጥሮው ቶሎ ስለሚለማ እና የዘሩን ፍሬ በጥንቃቄ ስለሚይዝ ከአጥቢ እንስሳት ሁሉ የላቀ ነው ልንል እንችላለን። ከእንስሳት በተለየ የሰው ልጆች ወላጆች በትዳር ይጣመራሉ፤ ልጆችም በዘላቂነት ከወላጆቻቸው ጋር ይኖራሉ። ከአጥቢ እንስሳት በተለየ የሰው ልጅ ብቻ ወደ ምድር ለሚያመጣው ልጅ በዘላቂነት የሚቆይ መኖሪያ ያዘጋጃል፤ በዘላቂነትም የወለደውን ልጅ ይመግባል። ለሰው ልጅ ትዳር እና ቤተሰብ በተፈጥሮአዊ ዕቅድ መስመር ላይ የሚሄድ ነገር ብቻ ሳይሆን፤ ሞራላዊ ተቋምም ነው። ተፈጥሮ እንደመራው እና ስሜቱ እንደፈለገ ባገኘው አጋጣሚ እና በማንኛው ጊዜ ወደ ጥምረት ውስጥ አይገባም። ተፈጥሮአዊ  እና ዘር የመተካት ፍላጎት ከሚሟላት የዘለለ ጥልቅ ጥምረት ነው። በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ፣ ተፈጥሮ ያዘጋጀው የጥምረት ዓላማ እና ትርጉሙ ምን እንደሆነ የሚታወቀው አንድ ወንድ ከአንድ ሴት በሁለንተናዊ ግንኙነት አንድ በሚሆኑበት ትዳር ውስጥ ነው። ከዚህ የምንረዳው የሰው ልጅ ግብረ ሥጋዊ ግንኙነት ደመ ነፍሳዊ ብቻ እንዳልሆነ ነው።

ከተግባሩ እና ሁለንተናውን ከሚገልጹ ባሕርያት አንፃር ካየነው የሰው

ልጅ በዋናነት ተፈጥሮአዊ ማንነቱ ፆታዊ ነው። ነገር ግን ነገር ግን የዚህ የፆታዊ ተፈጥሮአችን መገለጫ ማንነት፣ እንደ የምግብ መፍጫ ሥርዓት “ያለ እርሱ መኖር አንችልም” የምንለው ሙሉ በሙሉ ደመነፍሳዊ አይደለም። ፆታ እና ፆታዊነት (sex and sexuality) የሴትን እና የወንድን በአጠቃላይ ያላቸውን አካላዊ በተጨማሪም ሁለንተናዊ ተፈጥሮ እና የባሕሪ መገለጫ ምን ይሆን የሚለውን ለመወሰን የሚያግዝ ነው። የሰው ልጅ መላው ሰውነቱ፣ አካለ ሥጋው፣ ከፆታዊ ተግባር ጋር የተሳሰረ ወይም በዛ ቀጥተኛ ተፅኖ የሚያርፍበት እንደሆነው እንዲሁ፤ አእምሯዊ እና መንፈሳዊ ባሕርያቱም በተመሳሳይ መልኩ ከዚህ የፆታዊነት ተግባር ጋር ቀጥተኛ ትስስር አለው። በተቃራኒው፣ የሰው ልጅ መንፈሳዊ እና አዕምሮአዊ ብስለት እና እድገት በሁሉም ፆታ እና ፆታዊነት (sex and sexuality) ተግባሩ ላይ ተገልጦ ይታያል። በሌላ አባባል የሰው ልጅ መንፈሳዊ እና አዕምሮአዊ ብስለት እና እድገት፣ ፆታና ፆታዊነትን የሚበይንበትን እና የሚተገበርበትን መንገድ ጤነኛና ጤነኛ ያልሆነ ተብሎ እንዲከፈል ወሳኝ ሚና ይጫወታል። ስለዚህም የሰው ፆታዊ ተፈጥሮ እንደ እንስሳት ደመነፍሳዊ አይደለም። እንደውም የሰው ልጅ በደመ ነፍስ የሚመራ ፆታ እና ፆታዊ ማንነት የለውም። የሰው ልጅ የፆታዊነት ተፈጥሮ እና ተግባር በአንድም በሌላ መልኩ ከፍቅር ጋር የተሳሰረ ነው። ይህ መሠረታዊ ገፅታ ደግሞ የሰውን ልጅ “የፆታ እና ፆታዊነት” ተግባር አጋንንታዊ ወይም መንፈሳዊ ያደርገዋል።

እንስሳት ፍቅርን አያውቁም። ማሰብ ስለማይችሉ። ማፍቀር ምንም ማለት እንደሆነ አይረዱም። ከሁሉም በላይ ግን እንስሳት ፍቅር በሁለት አካላት መካከል ያለ ግላዊ ሕብረት እንደሆነ ማወቅ አይችሉም። አሁን እኛ ኋላቀር እና የጥንት ዘመን ሰዎች የምንላቸው እንኳን የእንስሳ አይነት የፆታ እና ፆታዊ ተግባር አልነበራቸውም። በአንድም በሌላም ቅርፅ ቢሆን ፆታ እና ፆታዊ ተግባራቸው ሥነ ምግባር እና ግለሰባዊ ፀባይ አለው። የፆታ እና ፆታዊ ተፈጥሯችን ጋራ በተያያዘ በውስጡ የፍቅር ትስስር እንዳይኖረው ማጥፋት እና ሥነ ምግባራዊ ዘር እንዳይኖረው ማድረግ የሰው ልጅ ተፈጥሮ አይፈቅድም። የሰው ተፈጥሮ አይደለም። ምናልባት ይህ የሚሆነው እየፈረሰና እየጠፋ ባለ ስልጣኔ፣ እየወደቀ ባለ ማህበረሰብ ዉስጥ ነዉ። ነገር ግን ይህን የፍቅር እና የሥነ ምግባር ሐሳቦች ማህበረሰብ የፈጠራቸው እና እውነተነት የሌላቸው ናቸው ብለው የሚያስቡ ሰዎች አሉ። ገና ስልጣኔ ባልደረጀበት እና የሰው ልጅ ፍራፍሬ እየለቀመ በሚመገብበት ዘመን የመጀመሪያው የሰው ልጆች ማህበረሰብ ውስጥ የነበረው ተፈጥሮአዊ አኗኗር ድንቅ እና ውብ ነው የሚል ስሜታዊ እና ከእውነት የራቀ እይታ አለ።

በየትኛውም ዘመን ለኖረ ሰው የሚሰራ እና አይናችንን እንጨፍን ካላልን በቀር ገሐድ የወጣው እውነት “በፆታዊነት ተግባራችን ውስጥ ሰብዓዊነታችን እንዳለበት ሁሉ እንስሳትም የሌላቸው ከተፈጥሮ ውጪ የሆነ እና አጋንንታዊ ገጽታ ከሰው ልጅ ባሕሪ ጋር አለ። “ነገር ግን ሰው ንቃተ ኀሊናው እየበሰለ እና ራሱን አብዝቶ እያወቀ ሲመጣ ፆታ እና ፆታዊነት በማንነቱ ውስጥ ያለ ትልቅ እንቆቅልሽ እንደሆነ መገንዘብ ይጀምራል። ለሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊነት በደስታ እና ህመም፣ በብርሃን እና ጨለማ፣ በነፃነት እና ባርነት፣ እጅግ ስውር እና ሚስጥራዊ በሆነ ገመድ የተሳሰረ የሕይወት ልምምድ ነው። ይህ ሰዋዊ ልምዳችን ነገሮችን ከሁለት አቅጣጫ ወደመመልከት ይመራናል፦ ፍጥረት እና ሐጢያት።

## 1.2. መለያየት፣ ሃፍረት እና ናፍቆት

እግዚያብሔር ሰው ወንድ እና ሴት አድርጎ ፈጠራቸው የሚለው የመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ ኤንድራጂነስ[1] ስለ ሴት እና ወንድ አመጣጥ አፈታሪክ ከሚናገረው ሙሉ በሙሉ የሚቃረን ነው። ከዚህም የተነሳ በክርስቲያን አዕምሮ ውስጥ ገብቶ ተሰራፍቶ ለመቀመጥ ቦታ የሚያገኝ አስተሳሰብ አይደለም። ነገር ግን ክርስቲያኖች ይህ መሰል አስተሳሰብ ሊቀበሉ ከቶም እንደማይችሉ አትኩሮት

1 የኤንድራጂነስ አፈ ታሪክ ስለ ጾታ አመጣጥ የሚያወሳ አፈ ታሪክ ነው። ታሪኩን ይጻፉልን ጸሐፍት በግሪክ ሀገር በአቴንስ ከተማ የሚኖሩ አቴናውያን፣ አንድ ቦታ ተሰባስበው ስለ ፍቅር ምንነት ባሕሪና ተፈጥሮ ያደረጉት ውይይት በተከተበበት የፕላቶ ሲምፖዚየም በሚለው የፈጠራ መጽሐፍ ውስጥ ይገኛል ይላሉ። በዚህ አፈ ታሪክ ውስጥ ከተናጋሪዎቹ መሃል አንዱ የሆነው አሪስቶፋነስ ሰዎች ገና ሲፈጠሩ ከአፈጣጠራቸው ኤንድራጂነስ የሆነ አፈጣጠር እንደነበረ የተፈጠሩት ለተሰበሰቡት ሰዎች ይተርካል። እነዚህ ኤንድራጂነስ ክብ ነበሩ። አራት ክንዶች፣ አራት እግሮችና ሁለት ፊት ነበራቸው። በጣም ኀያላን ስለነበሩ አማልክትን ያስፈራሩ ስለነበር ዜኡስ የተባለው አምላክ ለሁለት ከፈላቸው። ቀድሞ አንድ የነበሩት ሁለቱ ግማሾች፣ ከተነጣጠሉ በኋላ ዳግም ለመጣበቅ አንዱ እርስ በርስ መፈላለግ ጀመሩ። እርስ በርስ ሲገናኙ እጅግ በተነፋፈቀ ስሜት ሆነው እንደገና አንድ ለመሆን ይጥራሉ። ኤንድራጂነስ አፈ ታሪክ ፍቅርን እና ሙሉ መሆንን ፍለጋ ምን ማለት እንደሆነ የሚተርክ ምሳሌያዊ አፈ ታሪክ ነው። ይህ አፈ ታሪክ የሚያስተምረን እኛ ሁላችን ሌላኛ ግማሻችንን የምንፈልግ ያልተሟላን ፍጡራን መሆናችንን ነው። ግማሽ አካላችንን ስናገኝ እውነተኛ ፍቅርና ደስታ ማግኘት እንችላለን። ኤንድራጂነስ አፈ ታሪክ በተለያዩ መንገዶች ይተረጎማል። አንዳንዶች ስለ ሰው ልጅ አመጣጥ እውነተኛ ታሪክ አድርገው ይመለከቱታል። ሌሎች ደግሞ የጎደለንን የጣነውን ነገር የመፈለግ ምሳሌ አድርገው ያዩታል። ሌሎች ደግሞ በተቃርኖ ውስጥ ያለ አንድነት ምሳሌ አድርገው ይወስዳሉ። ጠቅለል አድርገን ስንመለከት በግሪክ አፈታሪክ ውስጥ ኤንድራጂነስ ግማሽ ወንድ እና ግማሽ ሴት የሆነ ፍጡር ነበር ማለት ነው። በዜኡስ አምላክ እንደተፈጠሩ እና የመጀመሪያዎቹ የዓለም ነዋሪዎች እንደነበሩ ይነገርላቸዋል። በስተመጨረሻም ዜኡስ የተባለውን አምላክ በማስቆጣታቸው ኤንድራጂነስ ወደ ወንድና ሴት ለሁለት ተከፍለዋል። በፕላቶ ፍልስፍና ውስጥ ደግሞ የነፍስ ምልክት ሆነው እናገኛቸዋለን። ፕላቶ ነፍስ በመጀመሪያ ኤንድራጂነስ እንደሆነ ያምን ነበር ይላሉ። ነገር ግን ነፍስ ወደ ሰው አካል ውስጥ በገባች ጊዜ ለሁለት ልትከፍል ችላለች። ፕላቶ አንደኛው ከፋይ ወንድ ሁለተኛው ከፋይ ደግሞ ሴት ሆነ ብሎ ይነግረናል። እናም ያለማቋረጥ እንደገና አንድ ለመሆን ጥረት ያደርጋሉ ብሎ ይናገራል።

በሂንዱይዝም ሃይማኖት ውስጥ ኤንድራጂነስ የሺቫ አምላክ ምልክት ነው። እና ሺቫ ብዙውን ጊዜ በግማሽ ወንድ እና በግማሽ ሴት ይመሰላል። ሺቫ እንደ ወንድ እና ሴት፣ ጥሩ እና ክፉ፣ እና ሕይወት እና ሞት ያሉ የተቃራኒ ነገር አንድነት ይወክላል ይባላል። አንድሮጂን በታሪክ ውስጥ በተለያዩ መንገዶች የተተረጎመ ጥልቅ ሃሳብን ለመግለጽ ጥቅም ላይ የዋለ ምልክት ነው።

ሊሰጥበት የሚገባው ጉዳይ ነው። ምክንያቱም አሁንም "ሁለት ፆታ መኖሩ የውድቀት ውጤት ነው ብለው የማመን ዝንባሌ ያለው የኖስቲሲዝም[2] አስተሳሰብ ዳግም እየንሰራራ በመሆኑ ነው። ይህ አስተሳሰብ የግሪክ እና የአረማዊ ህዝብ አስተሳሰብ እንጂ መጽሐፍ ቅዱሳዊ መሠረት የለውም። ከመጽሐፍ ቅዱስ ይልቅ በግሪክ እና በአረማዊ ምንጮች ላይ የተመሠረተ ሃሳብ ነው። ነገር ግን ከዚህ የጥንት የኖስቲሲዝም አስተምህሮ ጀርባ አስፈላጊ የሆነ አስተምህሮ እንዳለ አንክድም። ከሰው ልጅ የሕይወት ልምምድ ውስጥ ተመልክተን መመስከር እንደምንችለው ፆታ እና ፆታዊነት በውስጡ ከፍጥረት ጀምሮ በማይጠገን መንገድ

2 ኖስቲሲዝም ከክርስቶስ ልደት በኋላ በ1ኛው እና በ2ኛው ክፍለ ዘመን የነበረ እምነትና ሀይማኖታዊ ልምምድ ነው። ከአይሁድ እምነት፣ ከግሪክ የሚስጥራዊ ነገር አሳቢዎች እና የሄለናዊ ፍልስፍናን ጨምሮ ከተለያዩ ሃይማኖታዊ እና ፍልስፍናዊ ባህል እና አስተሳሰብ ውስጥ የፈለቀ ፍልስፍናዊ ሃይማኖት ነው። "ኖስቲዝም" የሚለው ቃል የመጣው "ኖሲስ" ከሚለው የግሪክ ቃል ሲሆን ትርጉሙም እውቀት ወይም መረዳት ማለት ነው። ኖስቲሲዝም ጥንታዊ ኑፋቄ እምነት እና ልምምዶችን ያካተተ መንፈሳዊ እውቀትን መፈለግ ላይ ማተኮር የሚል ምልከታ ያለው የመጀመሪያዋ ቤተ ክርስቲያን ተግዳሮት የነበረ አስተሳሰብ ነው። ብዙ ጊዜ የሚያተኩረው ከመለኮት ጋር በግል እና በውስጣዊ ልምዶች መገናኘት በሚለው ላይ ነው። ባጠቃላይ ኖስቲዝም ከቤተ ክርስቲያን አስተምህሮ እና ከእግዚአብሔር በተገኘ መገለጥ ከተፃፈልን እውነት ይልቅ የግላዊ መንፈሳዊ እውቀት እጅግ አስፈላጊና ድነት በእውቀታችን ነው በማለት ያስተምራል። በኖስቲክ እምነት ዋነኛው ማዕከል ፍጽምና የጎደለው እና ብልሹ ሥጋዊ ዓለም (ምድር) እና የመለኮታዊ ጥበብ እና የእውነት የመጨረሻ ምንጭ በሆነው በመንፈሳዊው ዓለም መካከል መሠረታዊ የሆነ ልዩነት አለ የሚል አስተሳሰብ ነው። ነገር ግን ኖስቲክ እምነት መንፈሳዊው ዓለም የመለኮታዊ ጥበብ እና የእውነት የመጨረሻ ምንጭ ነው ብሎ ሲናገር አስቀድሞ ለነቢያት በኋላ ደግሞ በሐዋርያት በኩል የተገለጠው የእግዚአብሔርን ቃል ማለቱ አይደለም። ነገር ግን ግለሰቦች በራሳቸው ፍለጋ እና ጥረት የሚደርሱበት ጥልቅ የሆነ ድብቅ ሚስጥር ነው

ኖስቲሲዝም ይህን ክፉ እና መጥፎ ዓለም ከፈጠረ አምላክ ውጪ ያለ ልዕለ ኋያል አምላክ አለ ብሎ ያምናል። እንዲሁም የሰው ልጅ በሥጋዊው ዓለም (በምድር) ውስጥ የታሰረ መለኮታዊ ብርሃን ወይም ነፍስ አለው ነገር ግን እውቀትን በማግኘት ከመንፈሳዊው ዓለም ጋር እንደገና ሊገናኝ እንደሚችል ያምናሉ። ያስተምራሉ። ኖስቲክ ኑፋቄዎች በእምነት እና በልምዳቸው ምንም ወጥ የሆነ ነገር የሌላቸው ሲሆን የአንደኛው ኖስቲክ አስተሳሰብ እና ትምህርት ከሌላኛው ኖስቲክ አስተሳሰብና ትምህርት በስፋት ይለያሉ። ነገር ግን ሁሉንም ኖስቲክ አስተምህሮ ተከታይ ክፍሎች የሚያመሳስላቸው ነገር መንፈሳዊ ለውጥ ወይም አዲስ ወደሆነ ልምምድ ውስጥ መግባት እና ለግል የሚሆን መለኮታዊ መገለጥ ለማግኘት መፈለግ በሚል እምነታቸው ምክንያት ሁሉንም መንፈሳዊ ጽሑፎች ከጀርባቸው ያዘሉት መንፈሳዊ ምስጢር አለ በሚለው ላይ ያተኩራሉ። ይህ እምነትና ልምምድ የኑፋቄ ትምህርት ከቤተ ክርስትያን የመጀመርያው የታሪክ ዘመን ጀምሮ እስከ አሁን ድረስ በተለያየ ይዘትና ቅርፅ ተፅኖውን እያሳረፈ የሚገኝ ነው።

የተሰነጠቀ የሰው የማንነት አንዱ ገፅታ ነው። በሰዉ ልጅ ልምምድ ውስጥ የምንመለከተው እና በየዕለቱ የምናገኘው ፆታና ፆታዊነትን በተመለከተ ያለ ችግር፣ በሰው ልጅ ተፈጥሮ ውስጥ ያለ መሠረታዊ የሆነ መከፋፈል ወይም ግጭት ነፀብራቅ ነው። ይህ ግጭት ወይም ተቃርኖ በግልጽ የሚታየው በፆታና ፆታዊነት ልምምዶች እና ባሕርያት ውስጥ ነው።

ሁሉንም ፍቅር በተለይም ደግሞ ከልብ የሆነውን የሰው ልጆች ፍቅር ተከትሎ የሚመጣ ሁለት ተጨባጭ ሐቅ አለ። በተለይ ከልብ የሆነውን የሰው ልጆች ፍቅር ስንል በተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለውን ብቻ ለማመልከት ነው። ሴቷ ወንዱን፤ ወንዱ ሴቷን በሚፈላለጉበት ሂደት ሁለት ነገሮች ሁልጊዜ እግር ለእግር እየተከታተሉ ይመጣሉ። በሴቷ እና በወንዱ የፍቅር ሕይወት ውስጥ እነዚህ ሁለት ነገሮች መቼም አይወገዱም። ይህም ሁለት ተጨባጭ ሐቅ፦ መቼም የማይወገድ ሐፍረት እና መቼም የማይረካ ናፍቆት ነው። በሁሉም የሰው ልጆች የተቃራኒ ፆታ ግንኙነት ውስጥ ከመጀመሪያው ቀን ጀምሮ የማይጠፋ ሐፍረት አለ። ግን በቅፅበት ደግሞ፣ በተመሳሳይ ጊዜ፣ ለመገናኘት እና ለመተያየት ይነፋፈቃሉ። ጥልቀት የጎደለው የቁሳዊነት ጽንሰ ሐሳብ እንደሚለው በተቃራኒ ፆታ መካከል ባለ ግንኙነት ያለ ሐፍረት በሰው ሰራሽ መንገድ የሚፈጠር እና በሂደት ማህበረሰብ የሚያዳብረው ሳይሆን እውነተኛ የሆነ ሰው ከተፈጥሮ ያገኘው ስሜት ነው።

አሁን ዘመናዊው ዓለም ከፆታ እና ፆታዊነት ጋር ያለውን ሐፍረት ለማጥፋት የሚያደርገው ትግል እና የዚህ ሐፍረት መጥፋት ማለት ከፍተኛ ወደ ሆነ ሰብዓዊነት እና የነፃነት ጥግ መድረስ ሳይሆን ኅሊና ከመጉደል እና በሰው ጠባይ ውስጥ ያለ የሥነ ምግባር መዘቀጥ መጨመሩ ማሳያ ነው። ይህ በሴቷ እና በወንዱ መካከል ባለ ግንኙነት በተለይም በተቃራኒ ፆታ ፍላጎት ቅርርብ ያለ የሐፍረት ስሜት በፆታ እና ፆታዊነት ዙሪያ የተከለከለ ነገር ሲያደርግ ብቻ ሳይሆን፣ በተፈቀደ እና መብቱ በሆነ ሁለት ተቃራኒ ፆታዎች ሁለተናቸውን ከፍተው በሚጣመሩበት የትዳር ሕይወት እንኳን ተከትሎት ይመጣል። በዚህም የሚያበቃ አይደለም ነገር ግን አንድ ሰው እየበሰለ በመጣ ቁጥር፣ ግላዊ የሆኑ ባሕሪ እና ችሎታዎቹን ባዳበረ ቁጥር እና በመንፈሳዊ ሕይወቱ እየበረታ በመጣ ቁጥር ከጾታ እና ፆታዊነት ሐፍረት ነፃ ወደ መውጣት ሳይሆን፣ ይህን ሐፍረት ተፈጥሮአዊ እንደሆነ በደንብ እየተገነዘበ ይመጣል።

ለምሳሌ ጌታችን ኢየሱስ እንደኛ ቢበላ እና ቢጠጣም፣ ሰው ከሚያደርገው ነገር ሁሉን ቢካፈልም፤ አግብቶ ይሆን ብለን በአዕምሮአችን መሳል አንፈልግም።

የኢየሱስ ከድንግል ስለመወለዱ አስተምህሮ ዙሪያ ያሉት የተለያዩ አስተያየቶች ወይም አመለካከቶች እንዳሉ ሆነው ከድንግል ሴት ስለመወለዱ ያለን አስተምህሮ እንኳን ከዚህ የሀፍረት ተፈጥሮአዊ ሂደት ጋር የተገናኘ ነው። ከድንግል ስለመወለዱ ስናስብ የሆነ ንፅህና እና ቅዱስ ነገር ይሰማናል። ከፆታ እና ፆታዊነት ጋር ካለው ሐፍረት የወጣ መሆኑን እንፈልገዋለን። በሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊ ማንነት ውስጥ መሠረታዊ የሆነ የተሰበረ ከመስመር የወጣ ነገር እንዳለ በግልፅ ያሳየናል። ከመለኮታዊ እቅድ ጋር የሚቃረን መሠረታዊ ብልሽት እና የተሰበረ ነገር እንዳለ መረዳት ቀላል ነው። በሌላ አነጋገር በሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊነት ውስጥ ከመለኮታዊ ሥርዓት ጋር የሚጣረስ ወይም የማይጣጣም ከውስጥ እና ከተፈጥሮ የሆነ ገፅታ አለ ማለት ነው። የፆታ እና ፆታዊ ማንነታችን ከተፈጥሮ መስመር የሳተ ወይም ከመንፈሳዊ መርህ ወይም ከመለኮታዊ ሐሳብ ጋር የሚጋጫ ባሕሪ በውስጡ የያዘ ነው።

በሁሉም ዘመን እና ባህል የፍቅር ቅኔዎች፣ ዜማ እና ታሪኮች ውሰጥ የምናገኘው ወንዱ ለሴቷ፣ ሴቷ ለወንዱ ያላቸው የማያቆም ናፍቆትን የሚገልጡ ሥራዎች፣ በሁለቱ መካከል መሠረታዊ የሆነ መነጣጠል መለየየት ሌላው ጠቋሚ ነገሮች ናቸው። በመጀመሪያ ይህ ጥልቅ ናፍቆት ከሚወዱት ጋር ለመገናኘት ብቻ ያለመ ነው። ፍቅርን ለመግለጽ ነው። ነገር ግን እዚህ ጋ ያበቃል ማለት ነው? ከእያንዳንዱ ስኬት በስተጀርባ፣ ከእያንዳንዱ የፈለጉትን ነገር ከማግኘት ጀርባ የተሻለ ነገር፣ የበለጠ ፍጹም ወይም ሙሉ የሆነ ነገር ለማግኘት የመፈለግ ጉጉት የለምን? በዚህ ቦታ ላይ “አለ ማለት ይበቃል” ማለት አይደለም የሚለው አባባል ቦታው አይመስላችሁምን? ግኑኝነታቸው ሊኖረው የሚገባ የአዕምሮ፣ የአካል እና የመንፈሳዊ ነገር ጥንካሬ የሳይጎደለው፥ ነገር ግን የትኛውም አይነት ጥልቅ ትስስር የማያሰወግደው ከተፈጥሮ የሆነ መሰንጠቅ፣ መለየየት በዚህ ናፍቆት ውስጥ አይታያችሁም? በመጨረሻም ሴት እና ወንድ አንደ አንድ ውህድ ነገር መታየት ሲገባቸው እንደ ሁለት መታየታቸው የተሳሳተ ነው የሚለው ጥንታዊ አባባል እውነትነት ያለው አይመስላችሁም? በሁለቱ ተቃራኒ ጾታ መካከል ያለው መሳሳብ፥ ከማንኛውም የፆታ እና ፆታዊነት ልምምድ በላይ አልፎ የሚሄድ ጠንካራ ኀይል ሊሆን ይችላል፥ ሌላ አንዳች ጥልቅ ትርጉም የያዘ ነገር ሳይኖረው አይቀርም እርሱም፥ እና ምናልባት፣ ልክ ከሕይወት መጀመሪያ ጀምሮ፣ በሁለቱ መካከል ያለውን ዲበ ኣካላዊ ክፍፍል የሚያሳይ፥ የዲበ ኣካላዊ የተቃርኖ መርህ ሊሆን ይችላል?

መጽሐፍ ቅዱስ ሁሉም ሰው ሊረዳው በሚችለው በጣም ቀላል እና ግልጽ

በሆነ ቋንቋ፤ ሴት እና ወንድ አድርጎ ፈጠራቸው በማለት ይናገራል። የዚህ ሁለት የተለያየ ነገር አለ የማለቱ ትርጉም ምንድን ነው? የነገሩ ውስብስብነት፣ ክርስቲያን የሆኑትንም ጨምሮ ብዙ አሰላሳዮችን፥ የአንድሮጂንስ አፈ ታሪክ እንዲያምኑ ገፋፍቷቸዋል። ከዚህ ዕይታ ተነስተን፥ እግዚአብሔር ሰው በሚለው ፍጥረት ውስጥ ሁለት የተለያየ ነገር፣ ሴት እና ወንድ አድርጎ ከመፍጠሩ ጋር ተያይዞ ያለውን ውስብስብ ነገር እንዴት እንረዳዋለን? በመጀመሪያ በጊዜ ሂደት ከተፈጠረው፣ ነገር ግን ተገቢ ያልሆነውን አስተሳሰብ በማስተባበል እንጀምር። ጥሩ የሚሆነውም ከእርሱ ብንጀምር ስለሆነ። ይህ ተገቢ ያልሆነ አስተሳሰብ በወንድና በሴት መካከል ያለውን ልዩነት የማስወገድ ፍላጎት በግልጽም ሆነ በስውር ሁሉም ነገር በመጨረሻ አንድ ነው ብሎ ከሚያምን (ገዳማዊ ከሆነ) የአስተሳሰብ መንገድ ጋር የተገናኘ ነው።

በፕላቶኒስት ሃሳባዊነት ፍልስፍና ውስጥ የአንድሮጂን ጽንሰ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ ተቀባይነት አለው። ነገር ግን፣ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ በሚገኙ ሃሳቦች ውስጥ ይህ ሐሳብ ምንም አይነት ድጋፍ የለውም። ለምን? አንድ ነገር እንዲሁ በደፈናው ተፈጥሮአዊ ነው በማለት ተቀባይነት እንዲያገኝ የሚቀርብ ክርክር ተገቢ ያልሆነ ሲሆን፤ ክርክሩን በራሱ መቀበል አይቻልም። ማለትም በዓለም ላይ ወይም በአጽናፈ ዓለም ውስጥ፥ ተፈጥሯዊ ነው ተብሎ በሚታሰብ ነገር ላይ በመመስረት ክርክሮችን አቅርቦ ተቀባይነት ማግኘት የማይቻል ነገር ነው። የሃሳብን ትክክለኛነት ወይንም እውነተኛነት ለማረጋገጥ በአመክንዮ እና በመረጃ ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት።

እግዚአብሔር ሰውን በተለየ መንገድ ሊፈጥር ይችል ነበር። እንደሌሎች አጥቢ እንስሳ ሳይሆን መራባት ሳያስፈልገው ዘሩን የሚተካበት መንገድ ሊኖር ይችል ነበር።ሌሎች እንስሳትን ከሚገዙ ብዙ ሕጎች ነፃ እንዲሆን እንዳደረገው እንዲሁ ሰው ጥንድ ከመሆን፣ ከመውለድና ከመዋለድ ሥርዓት ወጥቶ ዘርያው እንዲቀጥል ማድረግ ይችል ነበር። ይህም ማለት እግዚአብሔር የሰውን ልጅ እንደ አብዛኛው አጥቢ እንስሳ የተለመደ ባሕሪ፣ በተቃራኒ ጾታ ጥምረት አማካኝነት የመውለድና የመዋለድ ሂደት ውስጥ ሳያልፍ ዘሩን የመተካት አቅምና ችሎታ ሊያስታጥቀው ይችል ነበር። በዚህም አማካኝነት ሰው ከእንስሳት ጋራ የሚካፈለው ማንነት የሌለው ፍጡር ሊሆን ይችል ነበር። በሌላ አነጋገር፣ በሥነ ሕይወታዊ አካሄድ እንስሳትን ከሚገዛው የተፈጥሮ ሕግ የተለየ እንደ አንድ ነጠላ፣ ልዩ ዘርያ ፆታ እና ፆታዊነት የሌለው አድርጎ ሊፈጥረው ይችል ነበር። ባጭር ቃል፣ የሰውን ልጅ እጅግ ብዙ ከሆኑ እንስሳትን ከሚገዙ እና ከሚወስኑ የተፈጥሮ ሕግጋት ስር

እንዳይሆን አድርጎ እንደፈጠረው እንዲሁ፣ ከእንስሳት ጋር የሚካፈለውን የመውለድ እና የመዋለድ ሂደትንም እንዳያልፍበት ማድረግ ይችል ነበር። የሆነውን ግን እንደዛ አይደለም። የእግዚያብሔር ፈቃድ ሰው በእግዚያብሔር አምሳል የመፈጠሩን እውነታ እንደያዘ፤ ደግሞ እንደማንኛውም አጥቢ እንስሳ ከሥነ ሕይወት ሕግ በታች እንዲሆን ፈቃዱ ሆነ። በርግጥ ይህ መንገድ ለሰው ልጅ የሚመች አይደለም። የሰው ልጅ መለኮታዊ ማንነት ያለው ሆኖ ተፈጥሮ፣ መልሶ ደግሞ ከእንስሳት ተፈጥሮ ተካፋይ መሆኑ ምቾት የሚሰጥ አይደለም። ነገር ግን ይህ የሆነው በተፈጥሮ ግዴታ፣ በተፈጥሮ መስፈርት ምክንያት አይደለም። ይልቁንም የእግዚአብሔር ፍላጎት እና ፍቃድ ስለሆነ እንጂ። የሰው ልጅ አሁን ባለው መንገድ የሚሄደው፣ የእግዚአብሔር ፈቃድ ሰው እንዲህ እንዲሆን በመፈለጉ ነው። እናም ይህ የእግዚያብሔር ፍቃድ መሆኑን ሙሉውን መጽሐፍ ቅዱስ በማጥናት ለመረዳት እንችላለን።

ራሳችን በራሳችን የምንችል ነፃ እና ሁሉ ያለው አድርጎ ከመፍጠር ይልቅ እግዚያብሔር ውስን እና እርስበርስ ከመደጋገፍ ውጪ አማራጭ የሌለን፣ ራሳችንን በራሳችን ችለን መቆም የማንችል ፍጥረት አድርጎ ፈጠረን። በተለይ በዚህ የመውለድ እና የመዋለድ፣ የፆታ እና ፆታዊነት ጥምረት አማካኝነት፣ በመፍጠር ሥራ ውስጥ አብዝተን እንድንሳተፍ የእግዚያብሔር ፈቃድ መሆኑን እናያለን። አንዳችን ለሌላችን እንደተፈጠርን እና አንዳችን በሌላችን እንደተደገፍን እንገነዘባለን። መፅሐፍ ቅዱስ ’ሰው ብቻውን ይሆን ዘንድ መልካም አይደለም” የሚለውን ቃል፣ ሰው ባለው አቅም ማለትም የማሰብ እና የመፍጠር ችሎታ ምክንያት ራሱ ሁሉን የማድረግ አቅም እንዳለው የማሰብ እብሪት ውስጥ በቀላሉ የመውደቅ እና ራስን የማምንት አደጋ ውስጥ የሚገባ መሆኑን ስናይ፣ አንዱ ያለ ሌላኛው መቆም የማይችል ተደጋጋፊ እና ተመጋጋቢ ሆኖ በዛ መነግድ መፈጠር ነበረበት። ለሰው ልጅ፣ በሁለት ግለሰቦች መካከል መደጋገፍን በሚፈጥር ግንኙነት ውስጥ የመሆን አስፈላጊነት ብቻዬን ሁሉን ማድረግ እችላለሁ ብሎ ከማሰብ ወጥቶ ራሱን ትሁት እንዲያደርግ የሚያደርግ መንገድ ነው። በዚህ መንገድ ለራሱ በቂ የሆነ ሙሉ ሰው ነኝ የሚል እብሪት ከሰው ልጅ ሊወገድ ችሏል። ሰው ራሱን ከመለኮት ጋር ከማስተካከል የማይመለስ መሆኑን ከግምት ውስጥ በማስገባት፣ እንደ ሥጋ ለባሽ እና እንደ ፍጡር፣ ሁለት የተለያዩ ሰዎችን በቅርበት በሚያገናኝ ሂደት ውስጥ መሳተፉ ጠቃሚ ነው። በዚህ መንገድ፣ አንዱ ያለው ሌላው የሌለ ስለሆነ እርስ በርስ አንደኛው የሌላኛውን እርዳታ ወይም ድጋፍ ይፈልጋል። በዚህ ሁኔታ አንድ ሰው ሁሉንም ነገር በራሱ ማድረግ ይችላል የሚል እምነት ውድቅ ሆነ ማለት ነው።

ስለዚህ በሁለቱ ግንኙነት ውስጥ ያለው የዚህ ሐፍረት እና ናፍቆት ምንጩ ምንድን ነው? መጽሐፍ ቅዱስ ይህንን በግልጽ እና በቀላሉ መልስ ይሰጣል። መልሱም ውድቀት ይባላል። በእግዚአብሔር በተፈጠሩ በሁለት ሰዎች ላይ በሐጢያት ምክንያት የወደቀው የመጀመሪያው ውጤት ሐፍረት ነው። ለመጀመሪያ ጊዜ፣ በሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊነት ውስጥ መለያየት እና ብልሽት የተፈጠረው ከውድቀት በኋላ ነው። ሴቷ እና ወንዱ የእግዚያብሔርን ሕግ ተላልፈው ሐጢያትን ከሰሩ በኋላ ነው። በፆታቸው መሐል መሰንጠቅ ተፈጠረ። ተቃራኒ ሆነው በመፈጠራቸው መተፋፈር ያልነበራቸው፤ ኃጢአት ከሠሩ በኋላ በጾታዊ ተፈጥሮአቸው አፈሩ። ሐፍረትን የመጣው ፆታ እና ፆታዊነት አይደለም። ከውድቀት በፊት በግልፅ ቋንቋ አይተፋፈሩም ነበር እንደሚል በቃሉ ውስጥ ተፅፎ እናነባለን። በአንድ ወቅት ባዋሃዳቸው የእግዚአብሔር የፍቅር ቃል ተደብቆ፣ ተሸፍኖ የነበረው እራቁትነት በኀጢአት ምክንያት ተገለጠ።

ይሄ ማለት የፆታ እና ፆታዊነት መኖር፣ ተቃራኒ ፆታ መሆናቸው፣ ሴቷ በአንድ ጥግ ወንዱ በሌላ ጥግ ሆነው መፈጠራቸው ሐጢያት አይደለም። ነገር ግን ኃጢአት በፆታ ግንኙነት ውስጥ በዚህ መንገድ መግባቱ ሁሉን ነገር አመሰቃቅሏል። በሐጢያት ምክንያት የሰው ልጅ ያለው የፆታ እና ፆታዊነት ተፈጥሮ፣ ግላዊ ሕይወቱ፣ እና የሕይወቱን ዓላማ ተጎድቷል። በጾታዊ እና በግላዊ ሕይወታችን፣ እንዲሁም በሥጋዊ ፍላጎቶቻችን እና በመንፈሳዊ ግቦቻችን መካከል መለያየት ፈጥሯል። ይህም በሥጋዊ እና በመንፈሳዊ ገጽታችን መካከል ግንኙነት እንዲቋረጥ አድርጓል። ሐፍረት የዚህ መለያየት መገለጫ ነው። በራሳችን ላይ ሁለት ገፅታ እንዳለን፣ ይሄኛውንም ያኛውንም እንደሆንን ስንገነዘብ የሚሰማን ስሜት ሐፍረት ይባላል።

ከዚህ ወድቀት በኋላ የሰው ልጅ መንፈሳዊ ጎኑ እና ጾታዊ ስሜቱ አብረው እንደማይሄዱ ይሰማው ጀመረ። በዚህም ልክ ነው። ሰው በተለይም እንደ ግለሰብ ሲኖር ያለው እይታ፣ እምነት፣ የሕይወት ልምምድ፣ ስሜት፣ እና የሕይወት ግብ ግምት ውስጥ በማስገባት ሲመለከት ፆታ እና ፆታዊነት ለእርሱ ትክክለኛ ሰዋዊ ማንነቱ የተገባ ተፈጥሮ እንዳልሆነ የሚነግረው ድምፅ በውስጡ አለ። የሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊነትን ዝቅተኛ፣ አሳፋሪ እና ተራ የሆነ በውስጡ ያለ እንስሳዊ ስሜት እንደሆነ ያስባል። ያምናል። ውድቀት በሰው ልጅ ፆታ እና ፆታዊነት ውስጥ ያስከተለው ውጤት ዝብርቅርቅ ያለ ነው። ሰው ቢዘህ የጾታ ሐፍረት ውስጥ መልሶ የሆነ የሚያስደንቅ እና የሚያስደስት እንግዳ የሆነ ነገር በፆታ ተፈጥሮ ምክንያት ይሰማዋል። መልሶ ደግሞ ያን ነገር ሲፈራ ይገኛል። ነገር ግን በተመሳሳይ ጊዜ

ሐፍረት የሆነውን ነገር የማወቅ እና ወደ እዛ ነገር የመሳብ ዝንባሌም አለው። ይህ ማለት ሐፍረት ሲሰማው ያ ያሳፈረው ነገር ምን ያህል አስፈሪ ወይም ሞቾት የማይሰጥ እና አስደንጋጭ እንደሆነ ይታወቀዋል። ነገር ግን የሆነ የእርሱነቱ ክፍል ደግሞ በሚያስገርም ሁኔታ ወደነገሩ ሊሳብ እና ያንን ነገር ሊፈልግ ይችላል።

ይህ ሁኔታ ወደ ሁለተኛ ነገረ ጉዳይ የምንሔድበትን ድልድይ ይሰራልናል። ይህ ሁለተኛ ጉዳይ ደግሞ የናፍቆት መኖር ነው። “ፍላጎትሽ ወደባልሽ ይሆናል” የሚለው ቃል ውድቀትን ተከትሎ የመጣ እርግማን ነው። በዚህ ቦታ እርግማን የሆነው በራሱ የፆታዊነት ዝንባሌ ወይም የሩካቤ ሥጋ ፍላጎት አይደለም። ምክንያቱም ባልና ሚስት በአንድ ላይ መጣበቅ እና አንድ አካል መሆን አለባቸው የሚለው እውነት ከውድቀት ታሪክ በፊት የነበረ ነው። አሁን በውድቀት ምክንያት የመጣው ስግብግብ ፍላጎት እና እርካታ የሌለው ናፍቆት ነው። ወንዱ የኔ የሚላትን፣ ሴቷ እኔ የምትለውን በማግኘት ውስጥ እንኳን ቢሆን በውስጣቸው ያለው ናፍቆት አይረካም።

የሰዉ ልጅ ብቻ በተሰጠው የማሰብ ኀይል ምክንያት ናፍቆት ምንድነው የሚለውን ያውቃል። በሁለት ተቃራኒ ፆታዎች መካከል ያለ ነገር ግን ከእውነተኛ ልብ ከሆነው ፍቅር ያፈነገጠ፣ ማለትም አንድ ሙሉ የሆነ ወንድ ሌላ ሙሉ ከሆነች ሴት ጋር ሁለንተናቸውን በመክፈት የማይቀባበሉበት ሕይወት ሊረካ አይችልም። እንደውም መሠረታዊ የሆነው ፍላጎት እንዳይረካ ምክንያት ይሆናል። ይህ መሠረታዊ ፍላጎት ደግሞ ሁለቱ ተቃራኒ ፆታዎች ለመጣመር ያላቸው ፍላጎት ብቻ ሳይሆን የማይረካው፣ በእነርሱ በኩል ሊፈጠር የሚገባው የተሻለ ማህበረሰብን የመምጣት ዓላማ በእንጥልጥል ይቀራል። በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ ግንኙነት እውነተኛ ፍቅር ሲያጣ፣ ለግለሰቡ እና ለግለሰቧ ትርጉም እና ዓላማ ከሚሰጥ መንገድ ሲወጣ እና ስሜትን ማእከል ያደረገ ሲሆን እርካታ ሊኖር አይችልም። ከሌሎች ጋር ላለ እውነተኛ አብሮነት እና የመቀራረብ ጥልቅ ፍላጎት እርካታን አያመጣም። መሠረታዊ የሆነ ፍላጎት ሳይረካ በባዶ ሜዳ እንዲቀር ያደርጋል። ያም የሁለቱ ፆታ ውህደት እንደግለሰብ ቸግር ውስጥ መውደቅ ብቻ ሳይሆን እውነተኛ እና ጤነኛ ማህበረሰብ እንዲኖር የመፈለግን ሂደትን መና ያስቀራል።

በእውነተኛ የሴቷ እና የወንዱ ጥምረት ውስጥ እንኳን ቢሆን፣ የሰው ልጅ በኀጢአት በመውደቁ ምክንያት የመጣ መካፋፈል አለ። ሁልጊዜ አንድ ነገር በተለያየ መንገድ የመፈለግ፣ ሁልጊዜ የአንዱ መንገድ ከሌላው መንገድ መለያየት

እና ያለ ተቀርኖ መኖር ያለመቻል ዝንባሌ አለ። ሁሌም የማይረካ ፍላጎትን ከኋላ አስከትሎ የሚሄድ መለያየት፣ አለመርካት ሙሉ አለመሆን አለ። ነገር ግን ሰው ሐጢያተኛ በመሆኑ ምክንያት፣ ይህንን በማንነቱ ውስጥ ያለ መዛባት በትክክል ሊረዳ አይችልም። ሐጢያት የማንነቱ አንድ አካል እና በማንነቱ ውስጥ ስር ከመሰደዱ ጥልቀት የተነሳ ይህን ሁኔታ ቢረዳም መረዳቱ ምንም አይጠቅመውም። ሀጢያት ትክክለኛ ነገር እንደናውቅ እንቅፋት መሆን ብቻ ሳይሆን፥ የምናቀውንም ትክክለኛ ነገር መኖር እንዳንችል አቅም የከለከለን ነገር ነው። በዚህ ምክንያት ግንዛቤ ብቻ የተሻለ እንዲሆን አይረዳውም። "ይህን መለያየት ለማስወገድ ብቸኛው መንገድ ወደ ፍቅር ሙሉ በሙሉ መመለስ ነው። ሆኖም ይህ በምድር ላይ በዕለት ተዕለት ሕይወታችን ውስጥ በፍፁምነት ሊፈጸም አይችልም። አንድ ሰው እምነት ቢኖረውም፣ አሁንም ኀጢአተኛ ነው። በክርስቶስ አዲስ ፍጥረት የሆኑ አማኞች እንኳን ቢሆኑ፥ በዚሀ አካል ሥጋና በዚህ በዚህ ምድር እስካሉ ድረስ፥ በማንነታቸው ውስጥ ያለ መነጣጠል አብሮአቸው ይሆናል። ልክ እንደማንኛውም ሰው በአንድ በኩል ከፍ ያለ ልዕልና የተላበሰ የመንፈስ ማንነት እንዳላቸው ይሰማቸዋል፥ በሌላ በኩል ፆትና ፆታዊነትን የተላበሰ ዝቅተኛ የሆነ ማንነት እንዳላቸው ይሰማቸዋል። ይህ መነጣጠል አይጠፋም።

ከጾታ ምንነት ጥያቄ ጋራ ተያይዞ ያለ ሁሉም ውስብስብ ችግሮ ምንጬ የሰው ልጅ ፆታዉን እንደ አንድ ሌላ ማንነት፥ እርሱነቱን ደግሞ ማለትም መንፈሳዊና አዕምሮአዊ ሕይወቱን ሌላ ማንነት አድርጉ ከመረዳት የመጣ ነው። ሌላው በሰው ልጅ ሕይወት ውስጥ ብዙ ምስቅልቅል የሚፈጥረው ነገር፥ ሴቷ ከወንዱ ወንዱ ከሴቷ፥ የሁለንተና ግኑኝነት ማለትም የሥጋ፣ የነፍስ እና የመንፈስ ውህደት የሌለበት ፆታዊ ግንኙነት መኖር ነው። በሰው ላይ ችግር የሚፈጥረው ሰውነትን ከውስጡ የወጣ የተቃራኒ ፆታ ፍላጎት ነው ማለት ነው። (በግብረ ሥጋ ግንኙነት ወይም በግንኙነቶች ውስጥ የግላዊ ትስስር ወይም ስሜቶች አለመኖር ወደ ችግር ሊያመራ ይችላል። በሌላ አነጋገር ያለ ምንም ስሜታዊ ግንኙነት ወሲብን እንደ አካላዊ እንቅስቃሴ አድርጎ መመልከት በጉዳዩ ውስጥ በተሳተፉ ሰዎች ላይ ችግር ሊፈጥር ይችላል። ይህ ስብዕና ከስብዕና፥ የአንደኛው ሰው ሁለንተና ከሌላው ሰው ሁለተና ጋር የማይዋሃድበት ፆታዊነት፥ በተለያዩ መንገዶች ሊገለጽ ይችላል። ፆታዊ ግንኙነት ስሜታዊ እና ግላዊ ገፅታዎች ከግምት ውስጥ ሳያስገባ በአካላዊ ድርጊት ላይ ብቻ ማተኮር ሰዎች በሕይወታቸው ውስጥ ግራ መጋባት፣ እርካታ ማጣት ወይም ስሜታዊ ባርነት ውስጥ እንዲገቡ ሊያደርጋቸው ይችላል። ስለዚህ በፆታዊ ግንኙነት ውስጥ የልብ ከልብ መቀራረብ እና ግላዊ ግንኙነቶችን አስፈላጊነት ማጉላት ከእነዚህ

ችግሮች መሀል አንዳንዶቹን ለማቃለል ይረዳል።

በተመሳሳይ ጊዜ ደግሞ ለሰው ልጅ ፍላጎት መነሳሳት ከፍተኛ ምክንያት የሚሆነው ይኸው ምንም አይነት የስሜት፣ የሃሳብና የማንነት ውህደት የሌለበት ፆታዊ ግንኙነት ነው። እንግዳ ስሜት፣ ሚስጥራዊ እና አስፈሪ ነው። ግን ደግሞ መስህብ ስላለው በሰው ልጅ ውስጥ የማወቅ ፍላጎት እንዲኖር ያደርጋል። የማየት እና የማድረግ ጉጉት እንዲኖር ያደርገል። ነገር ግን በተቃራኒ ፆታ ፍቅር (Eros) ውስጥ ያለ ህብርት በሕይወት ትርጉም፣ ዓላማ እና ሥነ ምግባራዊ መመዘኛ ሲዋሃድ ሚስጥራዊ ጉጉት እና ርሃብ፣ አስማታዊ ከሆነው ኋይሉ ጋር ብንን ብሎ ይጠፋል። ቀጥሎ የሚመጣው ምን ይሆን በሚል ድንግዝግዝ ውስጥ በወንዱ እና በሴቷ መካከል የነበረ ጥብቅ መፈላለግ መፈራረት፤ መቀራረብ እና መራራቅ ካለበት ቦታ ይጠፋል። በምትኩ ፍቅራቸው ሚዛናዊነትን፣ ምክንያታዊነትን እና የሰው ከሰው ግንኙነትን እያካተተ ምትሃታዊ የሆነው  የስሜት ውጥረት እየከሰመ ይሄዳል። ለዚህም ነው በወሲብ ንግድ ላይ የተሰማራች ሴት በተቻላት መጠን አብሯት ወሲብ ከሚፈፅመው ጋር የ“ማንነት ከማንነት” ሕብረት እንዲኖር የማትፈልገው። የእርሱም ሆነ የሌላኛው ደምበኛ የወሲብ ፍላጎት ሁሌም ባለበት እንዲሆን እና ሥራው እንዲሳካ ሚስጥራዊ እና ዘብርቅር ያለ ዓለም መሆን አለበት። ቪነስበርግ በሰው ሰራሽ ብርሃን ይደምቃል፣ የወሲብ አማልክቱ የምሽት፣ የጨለማ አማልክት ናቸው። ይህ ከግለሰባዊ፣ የሰው ለሰው ሁለንተናዊ ሕብረት፣ ጤናማ ሕይወት የተነጠለ የተቃራኒ ፆታ ፍቅር (ኢሮስ) ከዘብርቅርቀነቱ ጋር ከፍሎ የነቃውን (ኀሊና የኀደለውን ማንነት) የሰውን ማንነት ይፈልጋል። እናም ጥንካሬውን የሚያገኘው ከዚህ የሰው ማንነት አካባቢ ነው። ጤናማ ያልሆነ እና የልብ ከልብ የሆነ ሕብረት የሌለበት የፍቅር ፍላጎት ወይም የተቃራኒ ፆታ ፍቅር (ኤሮስ)፣ በአዕምሯችን እና በስሜታችን ከፊል ንቃተ ኀሊና እንዲኖረን ወይንም ግራ መጋባት ውስጥ የሆንን እንድንሆን ወይንም ስለሕይወት የአሁንና የወደፊት ግብ ጥርት ያለ ምስል እንዳይኖረን ይፈልጋል። ከዚህ ከጨለመ፣ ብዙም ካልተረዳነው የእኛነታችን ክፍል፥ በሰው ውስጥ ማድረግ የሚፈልገውን የሚያደርግበት ኀይል ያገኛል።

ውጊያው የሚካሄደው በብርሃን አምላክ፣ በአፖሎ (Apollo) [3] እና

---

3 አፖሎ በግሪክ እና በሮማውያን አፈ ታሪክ ውስጥ ማዕከላዊ ማእከላዊ ስፍራ የያዘ ታሪክ ነው። እንደ የፀሐይ፣ የብርሃን፣ የሙዚቃ፣ የትንቢት፣ የእውነት እና የፈውስ እና ሌሎች ባሕርያት ጋር ተደምሮ የነዚህ ነገሮች አምላክ ነው ተብሎ ይታመናል። የአማልክት ንጉሥ እንደ ዜኡስ ልጅ አፖሎ በጥንታዊው የአማልክት መቅደስ ውስጥ በጣም ኀይለኛ እና በሰፊው ከሚከበሩ አማልክት አንዱ ነበር።

በታችኛው ዓለም የጨለማ አማልክት (chthonic) [4] መካከል ነው። በነፍስ ብርሃን ማለትም በማሰብ ሓይልና እና ጨለማ በዋጠው ጠንካራ ስሜት መካል የሚካሄድ ፍትጊያ ነው። ይህ ፍትጊያ ከሰወ ልጅ እይታ ጎን ቆመን ካየነው መቆሚያ የለውም። በሰዎች መንፈስ አወንታዊ ገጽታዎች እና በኀይለኛ ስሜቶች ወይም ፍላጎቶች አሉታዊ ገጽታዎች መካከል ቀጣይነት ያለው ትግል ነው። ከሰው አንፃር ይህ ጦርነት በፍፁም ሊቆም ከቶ አይችልም ምክንያቱም የሰው መንፈስ ማለትም የሰው ውስጣዊ ማንነት የማሰብ ሀይል በራሱ ተጨባጭ የሆነ ነገር አይደለም። በሃሳብ ባሕር ውስጥ የሚዋልል ነገር ነው። ከአሁን በኋላ ግላዊ (አካል የለበሰ) እና ልዩ አይደለም፣ ነገር ግን በሃሳቦች እና በንድፈ ሀሳቦች ውስጥ ብቻ ያለ ረቂቅ ጽንሰ ሃሳብ ሆኗል። የልብ ከልብ፥ የሰው ከሰው፥ በሴቷ እና በወንዱ መካከል ያለ እውነተኛ ፍቅር፥ ከብርሃን አምላክ ከአፓሎ ነው ብለናል። መደማመጥ፣ መከባበር ያለበት እሱ ከእርሷ ጋር፤ እሷ ከእርሱ ጋር በዕራይ እና ግብ የተጣመሩበት ፍቅር የብርሃን ነው፤ ከአፖሎ ነው። በሌላ ጎኑ ደግሞ ከታችኛው ዓለም የፍቅር አማልክት (chthonic) የመጣ ፍቅር አለ። ይሄ የታችኛው ዓለም የፍቅር አማልክ የምትሰጠው ፍቅር ደግሞ የማይበርድ ናፍቆት ያለበት፣ በጥልቅ ስሜት የታጀበ፣ ምንም አይነት እንቅፋት እና ልዩነት ወንዱን ከሴቷ፤ ሴቷን ከወንዱ የመገናኘት ህልም እና ፍለጋ ማስቆም የማይችልበት ነው። ነገር ግን የብርሃን አምላክም ይሁን፣ የታችኛው ዓለም የፍቅር አማልክት በሐሳብ ባሕር ውስጥ የሚፈሱ ተማሳሌቶች ናቸው። የሁለቱን ሰፍራ በሰው ውሰጥ በትክክል ለይቶ የሚያሰምር ማን ነው። ማንም አይችልም። ከዚህ አንፃር አፖሎም ይሁን የምድር አማልክት ጉድለት አለባቸው። አንደኛው ልክ ሌላኛው የተበላሸ አይደሉም። አፖሎ በብዙ

---

በግሪክ አፈ ታሪክ መሠረት አፖሎ እና መንትያ እህቱ አርጤምስ የተወለዱት በዴሎስ ደሴት ነው።

4 “ቶኒክስ” የሚለው ቃል የሚያመለክተው በአፈ ታሪክ፣ እና በሃይማኖት ውስጥ ከምድር በታች የጨለማ ዓለም ገጽታዎች ጋር የተያየዘ ማንኛውንም ነገር ማለት ነው። “ቶኒዮስ” ከሚለው የግሪክ ቃል የተገኘ ሲሆን ትርጉሙም “መሬት” ወይም “ከምድር በታች” ማለት ነው። ቶኒክ የሚያመለክተው ከምድር በታች የሚኖሩ አማልክትን፣ መናፍስትን ወይም ፍጥረታትን፣ በፕላኔታችን ውስጥ ካሉ ጥልቅ ኀይሎች፣ እንዲሁም በሰው ንቃተ ኅሊና ወይም በሥነ ልቦና ውስጥ ያሉ ኀይሎችን ነው። “ቶኒክስ” አፈ ታሪክ በግሪክ ብቻ ሳይሆን በተለያዩ ባህሎችና ወጎች ውስጥ የሚገኝ ነው። እነዚህ አፈ ታሪኮች በታችኛውን ዓለም የሚገኝድብቅ ግዛት ያሳያሉ። ብዙን ጊዜ ከሞት ጋር፣ ዘርን ከመተካት ጋር እና አንዳች ነገር ወደ ሌላ ነገር ከመለወጥ ኀይል ጋር ይያያዛሉ። የሚስጥር እና የድብቅነት ተምሳሌትም ነው። በሌላ መልኩ ደግሞ ከፃታ ጋር በተያየዘ “ቶኒክስ” ሴት ይወክላል። ድብቅ ነች። በሚስጥር ና በመሸፈን ውስጥ ትኖራለች። ሞትንም ሕይወትንም ትሰጣለች። የፀደይ ና የበጋ ወቅቶችን እንዲፈራረቁ ታደርጋለች። ገበሬው ተስፋ ያደርጋታል። “ቶኒክስ” ከተፈጥሮ ትስስር ያላት የሴት ልጅ መገለጫ አፈ ታሪክ ነው።

መንገድ ምክንያታዊ ብቻ ስለሚሆን ምድረ በዳ ነው። ሙቀት የለውም። የምድር አማልክት ደግሞ ምክንያታዊነት የሚጎድላቸው ሙቀት ብቻ ናቸው።

## 1.3. ሴት እና ወንድ የመሆን ተፈጥሮአዊ ሚና

ሴት እና ወንድ ሆነው የመለያየታቸው ነገር ትልቅ ስፍራ መያዙ የሚያሳየው ፆታ ከተፈጥሮ በሰው ውስጥ የታተመ፥ ቁልፍ ጉዳይ የሆነ ነገር መሆኑን ነው። ለሰው ልጅ ወሳኝ የማንነቱ ክፍል ነው። በሁለቱ መካከል ያለው ልዩነት የሚያሳየው ጾታዊነት ከፍጥረት ጀምሮ በሰው ተፈጥሮ ውስጥ ምን ያህል አስፈላጊ እና ስር የሰደደ መሆኑን ነው። ነገር ግን ሰው ፆታዊ ፍጥረት ብቻ አይደለም ሌሎች ማንነቶችም አሉት። በሰው የፆታ ልዩነት ውስጥ፥ በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት በሁሉም የሕይወታቸው ገጽታ ላይ ተጽእኖ አለው። አጠቃላይ እነርሱነታቸውን እና ልምዳቸውን በጥልቀት ይነካል እና ይቀርጻል። ለወንዱ ሰው መሆን ማለት አካላዊ እና ጾታዊ ገጽታዎች ብቻ ሳይሆን በሕይወቱ ውስጥ ያሉትን ሁሉንም ሀሳቦች፣ስሜቶች እና ልምዶች ያካትታል። በእነዚህ ሁሉ ሙሉ ሰዉ ነዉ። ለወንዱ የምንለው በሙሉ ለሴቷም ተመሳሳይ ነው። ሴት ሴት የሆነችው በፆታዊ ተግባሯ ብቻ ሳይሆን፥ በሁሉም ሐሳብና ድርጊት ሙሉ ሰው ነች። ሆኖም በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው የሥነ ሕይወታዊ ጾታዊ ባሕርያት ልዩነት፥ በቀጥታ በአእምሯዊ እና በመንፈሳዊ ገፅታዎቻቸውም ላይ ይኸው ልዩነት አለ።

የሰው ልጅ አእምሮ በሁለት ክፍሎች የተገነባ እንደሆነ እናውቃለን። በንቃተ ኅሊና (conscious) እና ለእኛ ባልተገለጠ ኅሊና (unconscious) አካላት የተገነባ ነው። ይህ ለእኛ ያልተገለጠው ኅሊና (unconscious) የፆታ ፍላጎታችንን ጨምሮ ሁሉንም ደመነፍሳዊ ፍላጎት አካቶ የያዘ ነው። በወንድ እና በሴት መካከል ያለው ልዩነት በዚህ ደመነፍሳዊ ግፊት ጎልቶ ይታያል። ነገር ግን ሰዎች ግለሰባዊ ስብእናቸውን እየገነቡ በሄዱ ቁጥር ሥነ ሕይወታዊ ልዩነት እየደበዘዘ ይሄዳል። በዚህ ሥነ ሕይወታዊ ገደብ ውስጥ ሆኖ፥ ከሴቷ ጋር ያለው አእምሯዊና መንፈሳዊ ልዩነትም እንደተካተተ፥ ወንዱ የማምረት፣ መፍጠር የወንድነት ሚና ሲወክል። ሴቷ ደግሞ ዘር መተካትን፣ መመገብ እና መንከባከብን ትወክላለች። ከሚና አንፃር፣ ወንዶች ከፈጠራ እና ከምርታማነት ጋር የተቆራኙ ናቸው። ሴቶች ደግሞ ሌሎችን ከመደገፍ ከመንከባከብ እና ከመመገብ ጋር በተገናኘ ሚናቸውን ይወጣሉ። ወንድ ልጅ ብዙ ጊዜ በውጪው ዓለም ላይ ያተኩራል። ሴቶች ወደ ውስጣቸው ያተኩራሉ። ወንዱ የበለጠ ተጨባጭ እና አዳዲስ ልምዶችን ተደራሽ ግቦችን ያማትራል። ሴቶች፥

ሰው ላይ፣ ግንኙነት ላይ እና ግላዊ በሆኑ ነገሮች ላይ ያተኩራሉ። ወንዱ አዳዲስ ነገር ያስሳል። ሴቷ ነባሩን ነገር ታስቀጥላለች። ወንዱ እዚህ እና ዛ በማለት ይንከራተታል፤ ሴቷ ግን ቤትን ትፈጥራለች። የዚህ ዓይነቱ ልዩነት ወንዶች ከሴቶች ይልቅ ዘር በመተካት ሂደት ውስጥ በፆታዊ ሚናቸው ምክንያት የሚጫወቱት ሚና እጅግ ያነሰ እንዲሆን አድርጎታል። ሴቶች እንደ ሚስት እና እናትነት ባላቸው ተፈጥሮ የሰጠቻቸው ሚና፣ ወንዶች እንደ ባል እና አባት ካላቸው ሚና የበለጠ ኃላፊነት አለባቸው።

የአዲሱ ሰው እድገት (የምትወልደው ሕፃን) ከወንዶች ይልቅ ከሴት ሕይወት ጋር እጅግ የተቆራኘ ነው። አዲሱ ሰው ሲያድግ (ከእርግዝና ወቅት ጀምሮ) ተፅኖውን የሚያሳርፈው በሴቷ ላይ ነው። ሕይወቱ የተሳሰረውም ከሴቷ ጋር ነው። ነፍሰ ጡር ሴት በእርግዝና ወቅት አካላዊ እና ስሜታዊ ለውጦችን ታደርጋለች። ነገር ግን ወንዱ እነዚህን ቀጥተኛ ለውጦች በተመሳሳይ መንገድ አያጋጥመውም። ሴት ልጅ አዲስ ለተወለደው ህፃን ሁሉ ነገሯን ትሰጣለች። መሸከም አለባት፣ ወደዚህ ዓለም የምታመጣው እርሷ ነች። ግን ይህን ስታደርግ በምጥ እና ህመም ብቻ ሳይሆን በሕይወቷም ላይ አደጋን ጋርጣ ነው። በኋላም ወደዚህ ምድር ያመጣችውን በጡቶቿ መመገብ አለባት።

በዚህ ተፈጥሮ ሴቷን አብልጣ በሕይወት መፍጠር ውስጥ እንድትሳተፍ ማድረጓ፣ እሷ ከተፈጥሮ የሕይወት ፍሰት ጋር በቅርበት የተሳሰረች እንድትሆን ሆናለች። የምትፀንሰው እሷ ነች፣ በዚህም የተገደበች ነች። ግን ደግሞ በዛውም በተመሳሳይ በእሱ ትጠበቃለች። አንዲት ሴት በሕይወቷ ላይ ከባሏ ያነሰ ቁጥጥር አላት። በባሏ ድርጊት ሳይሆን እናት በመሆኗ የመጣ ነው። የእናትነት ሀላፊነቶች እና ፍላጎቶች በእሷ ላይ በጥልቅ ተጽእኖ ያሳድራሉ እናም ውሳኔዎችን የማድረግ እና ሕይወቷን እንደፈለገች የመቅረጽ ችሎታ ላይ ተጽእኖ ያሳድራሉ።

ወንዶችም ሴቶችም ፍጽምነት የጎደላቸው ናቸው፣ ልክ ሁለቱም በእግዚአብሔር አምሳል በመፈጠራቸውም የጋራ ትስስር እንዳላቸው እንዲሁ፥ ሁለቱም ኀጢአት ሰርተዋል። ይሁን እንጂ በጾታ እና በባሕርያቸው ውስጥ ባለው ልዩነት የሚሰሩት የሐጢያት ተግባራትንም በተለያየ መንገድ እንዲገልጹ ያደርጋቸዋል። የኀጢአታቸው ልዩነት በመካከላቸው ባለው ልዩነት ላይ የተመሠረተ ነው።

ያለ ምንም ገደቦች በነጻ የሚንቀሳቀሰው ወንዱ ነው። ዋነኛው ሐጢያት እና ድካሙ የሚመጣውም ነፃነትን ከመጠን በላይ በመጠቀም ነው። ይህም

እብሪተኛ፣ ልግዛ ባይ እና ሁሉን ተቆጣጣሪ ባሕርያትን እንዲኖሪው አድርጎታል። ማንም ሰው በመንገዱ ላይ እንዲቆም አይፈልግም። ራስን መስጠት አይችልበትም፥ ከሚገባው በላይ በራሱ ይተማመናል። ራሱን ከተፈጥሮ ነጥሎ፥ በእጆቹ ሰራ በሆኑት ስልጣኔ እና ማሕበረሰባዊ ግንኙነቶች ውስጥ ያሰምጣል። ሁሉን ነገር እንደቁስ ይመለከታል። በግንኙነቶች ውስጥ ሰዋዊ ሀዘኔታውን ከግምት አያስገባም። ርህራሄ ይጎድለዋል።ከፍጥረታት ጋር ባለው ግንኙነት ጨካኝ ነው። ፍጥረትን ከእግሮቹ በታች ረግጦ ይገዛል። እብሪተኛ በሆነ መንገድ ራሱን ከተፈጥሮ ሕግጋት በላይ ያስቀምጣል። እና ፍጥረትን ከሚገዙ ህጎች እንደሚበልጥ ያስባል። በተፈጥሮ ላይ የራሱን የዘፈቀደ ደንቦች ያስቀምጣል። በጉልበት ሌሎች የፈለገውን እንዲያደርጉ ያደርጋል እና አጥፊ ነው። ነገር ግን ለነፃነት እንደተፈጠረ ምድር ለመግዛት እንደተጠራ ለደቂቃ አይዘነጋም። ስለዚህም ምድርን ለማስገበር ማድረግ ያለበትን ነገር ሁሉ ያደርጋል። በሚያየው፣ በሚሰማው፣ በሚያሸተው፣ በሚቀምሰው እና በሚሰማው ነገር ቁጥጥር ስር በሚሆንበት ጊዜ እንኳን በቀላሉ ተስፋ አይቆርጥም። እጣ ፈንታዬ ይህ ነው ብሎ አያስብም። ብዙውን ጊዜ ወንዱ የሚያደርጋቸው ወይም የሚፈፅመው ሐጢያት ጉልበት የበዛበት፣ በጣም ነውጥ የሞላባቸው፣ አደገኛ እና ግልጽ ስለሆኑ ከሴት ይልቅ መጥፎ ሰው መሆኑን አምኖ ለመቀበል ይቀላል።

በሌላ በኩል ሴቷ በተፈጥሮ ላይ አንዳች ነገር ሳትጨምር እና ሳትቀንስ ከተፈጥሮ ጋር ተቆራኝታ ትኖራለች። በቻለችው ሁሉ ከተፈጥሮ ጋር ያላትን ትስስር ለመጠበቅ ትጥራለች። የተፈጠረውን ነገር አታጠፋም። የእርሷ ሐጢያት ደግሞ ብዙ ጊዜ ከቤት ዉጪ የማታገኘውን ነፃነት ምን ማድረግ እንዳለባት እና እንዴት መሆን እንዳለባት ምንም አይነት ከፍተኛ ኀይል ሳያስገድዳት ማለቂያ የሌለው ነፃነቷን ከመታው የሚመነጬ ነው። ንቁ እና አስቻይ የሆነ፣ ከቦታ ቦታ ተንቀሳቀሳ መሆን የምትፈልገውን ነገር የመሆን ነፃነቷትን በፈቃዷ ታጣለች። በራሷ ነፃነት እንዳላት ትረሳለች። በውስጧ ያለውን ነፃነት ትተዋለች። ከሁኔታው ጋር ለመስማማት ራሷን ትለውጣለች። በእሷም ሆነ በሌሎች ላይ የሚደርሱትን መጥፎ ነገሮች አትቃወምም። በተፈጥሮ የተሰጣትን ሚና ትቀበላለች እና ከተለመደው ወይም ከአማካይ ሕይወት በላይ ለመሄድ አትሞክርም። ከተፈጥሮ ጋር ባላት ትስስር፣ውበትን በማድነቅ እና በመፈለግ ውስጥ እራሷን ታጣለች። በሕይወቷ ውስጥ ያለውን ፆታዊ ግንኙነት ከምንም ነገር በላይ አስፈላጊ አድርጋ ታያለች። በእሷ እና በባሏ መካከል ያለው ግንኙነት፣ ለባሏ ካለው አስፈላጊነት በላይ ለእርሷ በጣም አስፈላጊ ነገር እንደሆነ ታስባለች። በዚህ ምክንያት በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ሰው

በመሆኗ ከተሰጣት ዓላማ እና ተልዕኮ ወደ ኋላ ትቀራለች። ቤቷ እንድትቆይ እንጂ ሌላ ነገር እንዳታደርግ ባሏ እንዲሳምናት ትፈቅዳለች። ሴት በመሆኗ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ሚናዋ ከሁሉ የላቀ አድርጋ ታስባለች። በዚህም የበለጠ ጭንቀት ውስጥ ትገባለች። በእሷ ውስጥ ያለው ስሜት፣ ከአካል እይታ አንፃር እንደ ወንዱ በጣም ጠንካራ እና አሁን ካልሆነ የሚል ባይሆንም፣በባሕሪ እና አስተሳሰቧ ውስጥ ከወንዱ የበለጠ የግብረ ሥጋ ግንኙነት ፍላጎት አላት።

ወንዱ በተሳሳተ መንገድ ነፃ ከሆነ፣ ለምሳሌ ራስ ወዳድ ወይም ኀላፊነት የጎደለው ከሆነ፣ እሷ ደግሞ በተሳሳተ መንገድ እራሷን ታሥራለች። ለምሳሌ ጥገኛ ወይም ታዛዥ ወደ መሆን ታዘነብላለች። ባልየው ከሰው ለሰው ግንኙነት ግድ የማጥሰጠው ደመ ቀዝቃዛ እና አዕምሮ የጎደለው ከሆነ፣ እሷ ደግሞ በተሳሳተ መንገድ ለግንኙነት ስፍራ የምትሰጥ እና ተፈጥሮአዊ የመሆን አዝማሚያ ይታይባታል። ልክ ባልሆነ መንገድ እጅግ ስሜታዊ እና ምክንያት የራቀው ሐሳቦችን በመቀበል ፈቃዱን ትፈፅማለች።

እነዚህ እየተወያየንባቸው ያሉት ሴቷን እና ወንዱን ለመለየት የተቀመጡ የጾታ ንድፈ ሃሳቦች እንደ ሁሉም ዓይነት ንድፈ ሐሳቦች በጥንቃቄ መርምረን መቀበል አለብን። ዘመናዊ ሴቶች በዚህ ጾንሰ ሃሳብ ውስጥ የእነርሱ ማንነት ተንፀባርቆ ላያዩት ይችላሉ። ነገር ግን ዘመናዊቷም ሴት ብትሆን መገንዘብ ያለባት ነገር፣ እየወራን ያለነው ከ1850ዎቹ ጀምሮ ስላለችው ዘመናዊ ሴት ብቻ ሳይሆን ከአደም ዘመን ጀምሮ እስካሁን፣ ባልሰለጠኑ እና በጥንታዊ ሕዝቦች መካከልም ስለነበረችው ሴት፣ ከታሪክ መቆጠር ጀምሮ ስለነበረችው ሴት በመካከለኛው ዘመን ስለነበረችው ሴት ስለምሥራቃዊቷ ሴት፣ በሁሉም አቅጣጫ ስላለችው ሴት፣ በአሁኑ ጊዜ እንኳን ነፃ ስላልወጣችው ሴት፣ በአሁን ጊዜ በሕይወት ካሉት ከ10 ሴቶች ስለ9ኙ ሴቶች ነው።

በአሁኑ ጊዜ መብቶችን እና ነጻነቶችን ያገኙ ብዙ ሴቶች በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለው ልዩነት አካላዊ ብቻ እንደሆነ ያምናሉ። የአዕምሮ እና የመንፈሳዊ ልዩነት ወንዶች የትምህርት ሥርዓቱን ስለተቆጣጠሩት የተፈጠረ ነገር ነው ብለው ያስባሉ። በአካላዊ ልዩነት ውስጥ ግልፅ ሆኖ የሚታየው ልዩነት በሴቷ የአስተሳሰብ እና መንፈሳዊ ዓለምም ልዩነት ያለ መሆኑን እና ይህ ልዩነት ተፈጥሮ ያመጣችው እንጂ በትምህርት የመጣ እንዳልሆነ ማመን አይፈልጉም። ይህ አይነቱ አመለካከት በሴቶች ነፃነት ዙሪያ የተነሱ ሁሉም ንቅናቄዎች የሚያመሳስላቸው ከአንድ አቅጣጫ ብቻ የሚያይ አመለካከት ነው። ነገር ግን ይህን መሰል አስተሳሰብ የታሪክ

እና የሁሉም ሐገሮች የሥነ ጽሑፍ መረጃ ድጋፍን አያገኝም።

ነገር ግን ከዚህ ሐሳብ ጀርባ እውነትነት ያለው ነገር ስላለ እርሱ ቸል ሊባል ከቶ አይገባም። እንደ እውነቱ ወንዶች ራስ ወዳድ እና የገዘያዋ ፍላጎታቸውን ብቻ ባማከለ መንገድ ስልጣናቸውን ተጠቅመው ታሪክን፣ ባህልን፣ ሕግን እና ትምህርትን ለእነርሱ ጥቅም እንዲሆን አድርገው ቀርፀዋል። የሴቶችን ነፃነት ገድበው አእምሮአቸውን እና መንፈሳቸውን እንዳያሳድጉ አግደዋቸዋል፣ ምንም እንኳን ሴቶች እንደ ወንዶች ሁሉ ለማደግ እና ለመማር የሚችሉ በእግዚያብሔር አምሳል የተፈጠሩ ቢሆኑም፤ ወንዶች ግን ሴቶችን ለራሳቸው ፍላጎት በምትሆን መንገድ ቀርፀዋል። ዛሬም ሴቶች ከምናውቀው በላይ በወንዶች ቁጥጥር ስር ናቸው። ሀብታም ወይም የተማሩ ሴቶች እንኳን ቢሆኑም ከዚህ እሥራት አልወጡም። በዚህ ምክንያት አሁንም የሴቶችን እውነተኛ ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ አልተረዳንም።

የሴት እውነተኛ ተፈጥሮ አሁንም ወንድ እንድትሆን ከሚፈልገው የሴት ምስል ጀርባ እና በወንዶች የብልሃት አካሄድ በወንዱ መልክ እና አምሳል በተቀረጹ ሴቶች በስተጀርባ የተደበቀ ነው። የሴቶችን የነፃነት መብት ጽንፍ ወይም የተጋነኑ የሴታዊነት እንቅስቃሴዎችን በማየት ተመልሷል በሚል ወይም ንቅናቄዎቹን በመጥላት ችላ ማለት አይገባም። ሴቶች እውነተኛ ነፃነታቸውን ለማግኘት ገና ብዙ ይቀራቸዋል። መጓዝ የሚገባቸው ብዙ መንገድ አለ። በአሁን ሰዓት ሴቶች ማናቸውንም ወይም ምን አይነት ስራ መሥራት ይችላሉ የሚለውን መገመት ብቻ ነው የምንችለው። ወንዱ እውነተኛ ማንነቱን፣ ችሎታውን እና አቅሙን የሚያሳይበት ሁሉንም እድሎች አግኝቷል።ሴቷን ተመሳሳይ እድሎችን በመከልከል የችሎታውን እና የአቅሙን አውጥቶ አሳይቷል። አሁን ሴቷን ከአቅም እና ከችሎታ አንፃር ለመናገር ግንዛቤያችን ጠባብ እና እርግጠኝነት የሚጎድለው ነው።

## 1.4. ፆታ እና ሰብዓዊነት

ወንዱ የሚያደርገው ነገር ሁሉ ቀቡልነት እንዲገኝ ስለ ሴትዋ ተፈጥሮ የሚገልጽ ንድፈ ሃሳብ ሳያዘጋጅ ምንም ነገር ማድረግ እንደማይችል ቀድሞ ተገንዝቧል። ይህ ንድፈ ሃሳብ ዲበ አካላዊ ንድፈ ሃሳብ ሲሆን፥ ሴቶች ከፍልስፍና ወይም ከመንፈሳዊ እይታ አንፃር ከወንዶች እኩል ጠቀሜታ ወይንም ዋጋ የላቸውም የሚል ነው። ይህ የተሳሳተ ንድፈ ሃሳብ ከመጀመሪያም ውልደቱን ያገኘው ወይንም የሚመነጨው ከወንዱ ራስን ካለ መረዳት ችግር ነው። የወንዱ

ራስን ያለመረዳት ችግር የሚመነጨው ደግሞ ቀድመን ከተነጋገርነው፣ ስለራሱ መንፈስ ወይም የአዕምሮ ሀይል ምንነት ካለው የተሳሳተ አስተሳሰብ ነው። ያን የመረዳት ችገር አካል ነው። እዚህ ጋ መንፈሳዊ ተፈጥሮ ስንል ከሰው ልጅ የመፍጠር የማሰብ እና የስልጣን አቅም ጋር የተያየዘ ነው። ይህን የሰው ሁሉ የጋራ የሆነ ነገር ወንዱ የብቻ እና የራሱ ማንነት መገለጫ አድርጎ ይመለከታል። ወንዱ ብዙ ጊዜ እንደሚያደርገው እኛም የሰውን አካላዊ ተፈጥሮ ሳይሆን (የሴቷ እና የወንዱን) ወንዱ የፈጠረውን ስልጣኔ፣ ባህል፣ ሥነ ህንፃ እና ቴክኖሎጂ ብቻ ከተመለከትን፣ እርግጥ ነው ሴቶች ከወንዶች ያነሱ ይመስላሉ። ምክንያቱም የሴቷ አእምሮ ከፈጠራ ስራዎች ጋራ በተያየዘ ከወንዱ ያነሰ ነው።

ይህ የሆነበት ምክንያት ተፈጥሮ ለሴቷ በመኖር ውስጥ ካስቀመጠችላት ዓላማ ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው። በአፖሎ አምላክ እና በምድር አማልክቶች መካከል ያለው ልዩነት መገለጫ ነው። ወንዱ የበለጠ በአፖሎ አምላክ የሚወከል ሲሆን፣ ሴቷ የምድር አማልክትን ትመስላለች። ሴትዋ ከግንባታ እና ፈጠራ ጋር በተያየዘ ያላት ያነሰ አስተወጽኦ፣ በአፖሎ እና በምድር አማልክት መካከል ባለው ቅራኔ ውስጥ እጣ ፈንታ ሴቷን ከምድር አማልክት ጋር ስላቆራኛት ነው። ፍላጎት እና ዝንባሌዋ የምድር አማልክት ካላቸው ፀባይና ዝንባሌ ጋር መሳ ለመሳ የሚሄድ ነው። በእነዚህ በሁለት አማልክቶች (ሴቷ እና ወንዱ በተመሰሉበት) ወይም ጣዖታት መካከል ሁልጊዜም ማቆሚያ የሌለው ትግል ይኖራል። ይህ ፈጽሞ አይቆምም። ምክንያቱም ደግሞ ኀጢአት ነው። ሐጢያት ጠላትነታቸውን አምጥቶታል። ይህ ማለት በእነዚህ ሁለት ኀያላን አማልክት መካከል ያለው ግጭት ዘላለማዊ ነው ማለት ነው።

ብዙ ጊዜ ወንዱ ከሰውነት እና ከሰው ለሰው ግንኙነት ይልቅ የአዕምሮ እና የመንፈስ ሥራ ውጤት በሆኑ ረቂቅ ሐሳቦች፣ እና ለእጆቹ ሥራ ስኬቶች ዋጋ ይሰጣል። በዚህ መመዘኛ ውስጥያልተገኘን ከሕይወት እንደወደቀ ይቆጥራል። ሴቷን በእነዚህ መለኪያዎች የምትወዳደርበት እድሎች ያልተገኘን ከሕይወት እንደወደቀ ይቆጥራል። ሴቷን በእነዚህ መለኪያዎች የምትወዳደርበት እድሎች ከነፈጋት በኋላ መልሶ ግን ዝቅ ባለ የአዕምሮ አቅም ውስጥ ይመድባታል።

ነገር ግን መፅሐፍ ቅደስ የሰው መነፈስ ምንድነው ለሚለው የሚሰጠውን መልስ፣ ከመፅሐፍ ቅዱስ የሰብዓዊት መመዘኛ አንፃር ብንመለከት ወይም ከዛ ብንጀምር የመኖር እውነተኛ ትርጉም በፈጠራ፣በስልጣኔ እና በስኬት ውስጥ ሳይሆን በፍቅር እና በማሕበረ ሰብ ውስጥ መሆንን ማዕከል ደርጋል። ከዚያም

ወንዶች እና ሴቶች እንዴት እርስ በርስ እንደሚገናኙ እና ስለ ሰው ልጅ የወደፊት ሁኔታ ያለን ግንዛቤ ይለወጣል። ይህ ማለት ፍቅርን እና በፍቅር ውስጥ የሚኖርን ማህበረሰብ እንደ ሰው ልጅ የመኖር ትርጉም እና የመኖሩ ግብ ዋና ገፅታዎች ብንመለከት ስለ ፆታ እና ስለ ወደፊት የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ምን እንደሚሆን የሚኖረን እይታ የተለየ ይሆናል።

በወንዶች እና በሴቶች መካከል ያለ ልዩነት ማን ይበልጣል ማን ያንሳል ከሚል ይወጣል። ስለ ልዩነታቸው ብቻ እንነጋገራለን። ሴቷ ሰው ነች ነገረ ግን የወንዱ አይነት ያልሆነች ሰው ነች። ነገር ግን ከወንዱ ሰውነት ያነሰ ሰው አይደለችም። በጥቅሉ ሲታይ የሴቷ የሕይወት ዝንባሌ በአዕምሯዊ ሥራዎች እና ረቂቅ ሀሳቦች ላይ ያተኮሩ አይደሉም። የሴቷ ስህተት እና አደጋ የሚመጣው አብዛታ በስሜት ላይ ያተኮረች መሆኗ ነው። በመንገደዋ እና በውሳኔዋ የስሜቷ ተፅዕኖ ከፍተኛ ነው። የወንዱ ስህተት እና አደጋ የሚመነጨው ሕይወቱን ከሚመራበት መርህ ነው። የወንዱ የሕይወት መርህ እንደልቡ መሻት (self willed) መሄዱ እና አመክኖዩዋ ብቻ መሆን የሚል ነው።

ከምክንያታዋ እና ከሥርዓት ጋር የተቆራኘ የወንድነት ዓለም (በግሪክ አፖሎ አምላክ የተወከለው) የመተዳደሪያ መርህ ከእግዚአብሔር ፈቃድ ያፈነገጠ ነው። ልክ እንደዚሁ ከደመ ነፍሳዊ ሥርዓተ ዓለም ጋር እንደተቆራኘው (በ chthonic አማልክት የተወከለው) የሴትነት ዓለምም ከመለኮት ፈቃድ ያፈነገጠ ነው። በሐሳብ እና የአዐምሮ ዓለም ላይ የማተኮር የወንዱ ዝንባሌ ይሁን፤ከውስብስብ ሐሳብ እና ከአዕምሮ ሥራዎች የሚሸሸው በራስ ላይ ብቻ የሚያተኩረው የሴቷ ዝንባሌ ሁለቱም ሐጢያት መሳሪያ ሊሆኑ ይችላሉ። ይህ ማለት በረቂቅ ሃሳቦች ላይ አብዝቶ ማተኮር ወይም በተጨባጭ ተሞክሮዎች ላይ ማተኮር ከትክክለኛው ነገር ሊያርቀን ይችላል። በወንዱ እና በሴቷ መካከል ሁሌም የማይጠፋ ማብቂያ የሌለው ትግል አለ፣ ምክንያቱ ደግሞ በሁለቱም ወገን ልክ የሆነ እና ያልሆነ አንዳች ነገር አለ። ሁለቱም ትክክል ስለሆነና ስላልሆነ ነገር የራሳቸው የሆነ ሃሳብ አላቸው። ሁለቱም በስሜታዊነት የተሞላ እና ሁለንተናቸውን ያካተተ ፍትሕ ያደርጋሉ። ነገር ግን በተለያየ መንገድ።

ወንድና ሴት በተለያዩ መንገዶች እርስ በርስ ይጣላሉ። ወንዱ ሴቷን ለመቆጣጠር እና ለመጨቆን ይሞክራል። ሴቷ ወንዱን በተለያየ ነገር በመያዝ ነፃነቱን ተነጥቀዋለች፣ ሊወጣው ከማይችለው ውጥንቅጥ ነገር ውስጥ ትከተዋለች። በሴቷ እና በወንዱ መካከል የሚደረገው ትግል እና ጦርነት በታሪክ

ውስጥ ከሰማናቸው ጦርነቶች ሁሉ የላቀ እጅግ ታላቅ ጦርነት ነው። ከዚህ ግጭት የተነሣ በወንድ እና በሴቷ ስብዕና ላይ ሚዛናዊ ያልሆነና የተሳሳተ ልዩነትን ተፈጥሯል። ወንዱ የመግዛት ፍላጎቱን በኀይል የመጫን አቅሙን በማሳደጉ ይቀጥላል። ሴቷ ደግሞ በግንኙነታቸው ውስጥ ጥቅሟን የምታስከብርበት የሴትነት ብልሃትን ታዳብራለች። በተገዢነት ቦታ ላይ ብትሆንም፥ ጌታውን መቆጣጠር ወደሚችል ባሪያ ዓይነት ማንነት ትለወጣለች። ሙሉ በሙሉ በቁጥጥሩ ውስጥ እንዳትገባ ለመጠበቅ ስኬታማ ሰልቶችን ፈጥራለች። ለወንዱ በመሸነፍ ውስጥ ድሏን ታሳካለች። ነገር ግን ይህ ስኬቷ መልሶ ወጥመድ ውስጥ ይከታታል። ዝቅ አድርጎ ስለሚመለከታት እና አነስተኛ ቦታ ስለሚሰጣት፥ እሱ እርሷን የሳለበትን ሥዕል፣ በመቀበል ትበቀለዋለች። ወንዱ እርሷን የሳልበትን ገጽታ በመቀበልና በዛ መንገድ በመመላለስ፥ የወንዱን ስልጣንና ኀይል የምትገዳደር አደገኛ ሴት ትሆናለች።

በዚህ ሁኔታ ውስጥ ማለትም በወንድና በሴት ግንኙነት መካከል የምንሰማውና የምናየው ተግባር በኀጢአት ምክንያት ከመጣ ማንነታቸው የወጣ እኩይ ነገር ብቻ ሳይሆን፥ በሌላ መልኩ ደግሞ  ለሰው ልጆች የታሰበው መለኮታዊ አላማ እርሱም የእግዚአብሔር መልክ ወንዱ በሴቷም ውስጥ በሥራ ላይ አለ። ሴቷ ከፍጥረት ጀምሮ እግዚአብሔር በውስጧ ያተመው "እውነተኛ ወንድ" ምን እንደሆነ ምስሉ ወይም ሃሣቡ ከውስጧ እንዳልጠፋ ሁሉ ወንዱም የ"እውነተኛ ሴት" መልክ ምስል በውስጡ አለ። በጭራሽ ከውስጡ አልጠፋም። በሀጢያተኛ ማንነቱ ምክንያት በእርሰዋ ላይ  የሚያደርገው ያልተገባ ድርጊት ባለበት ጊዜ ውስጥ እንኳን፣ ሐጢያተኛ ማንነቱ ከሳለለት ሥዕል ውጪ ሴቷ ብዙ ነገር እንዳላት ይገነዘባል። የሚፈለግ እና የሚፈራ ማንነቷን ያያል።

በወንዱ ውስጥ ያለ የእውነተኛዋ ሴት ምስል በሆነ ያህል መጠን የእኔ የሚላትን ሴት ለማግኘት ባለዉ ናፍቆትና ፍለጋ ውስጥ ይታያል። "ለእኔ ያላት ጸባየ ሰናይ ሴት ይህን ትመስላለች" የሚለው፥ በምናቡ ውስጥ ያለችውም" የእውነተኛዋ ሴት" ምስል ምናልባት አሁን በሚፈልጋት ሴት ይገለጣል። ወይም አግኝቷት ፍላጎቱን እያረካችው ባለችው ሴት እንዳይረካ የከለከለው ዋነኛ ምክንያት ይህ አእምሮ ውስጥ ያለው የእውነተኛዋ ሴት ምስል ዕውን የሆነ ስለማይመስለው ሊሆን ይችላል።በዚህም ምክንያት ሁሌም በናፍቆት ውስጥ እንዲቆይ ያደርገዋል። በወንዱ ፍላጎት እና ከሴቷ የሚጠብቀ መሟላት ያለበት እና የሌለበት ነገር ላይ ተጽእኖ ያደርጋል። በወንዱ አእምሮ ውስጥ ያለ "የእውነተኛዋ

ሴት” ምስል፥ የሚመኛት እና ሞኞቱን እያሟለች ባለች ሴት ሙሉ በሙሉ እንዲረካ እይፈቅድለትም። ባንድ በኩል የሴቷን እውነተኛ ምስል መቀበሉ ልክ ሲሆን፥ በሌላ በኩል ሃጢያተኛ ማንነቱ ተፈልጋ የማትገኝ ያደረግበታል። በምናቡ ውስጥ ያለች ሴት በተጨባጩ ዓለም ያለች ሴት መዳረሻ እንደሆነ በመቀበል፣ በተጨባጩ ዓለም ያገኛትን ሴት እርሷ እውነተኛዋ ከፍጥረት ጀምሮ ለእርሱ ያሰባት እንደሆነች እንዳይቀበል ይከለክለዋል። ይህ ሃሳብ በሚመኛት እና አካላዊ ፍላጎቱን እያሟላች ባለች ሴት እርካታ እንዳይኖረው ይከለክለዋል። ሆኖም ወንዱ ፈታኝ እና ለውድቀቱ ምክንያት የምትሆን ሴት ብቻ ሳትሆን፤ ንፁህ፣ ቅድስት እና ድንግል ሴት እንዳለች ያውቃል። የዚህች ሴት ምስል ሁልጊዜ በፊቱ አለ። አንዳንዴም የዚህች ሴት ሥጋ ለብሳ አለማግኘቱ ወይም እንደማያገኝ ማሰቡ ፍፁም ከሴት ውጪ የሆነ ሕይወትን እንዲኖር ያደርገዋል። ከሴቷ ያልተቆራኘ ሕይወትን እንደ ከፍተኛ የሕይወት ብቃት እና የሕይወት ንፅህና እንዲወስድ ያደርገዋል። የመታቀብ እና የገዳማዊ አኗኗር ጽንሰ ሃሳብ የመጣውም ከሴቶች ሳይሆን ከወንዶች ነው። ይህ ሁሉ የሚያሳየን ምንም እንኳን አሁንም የተዛባ እና በድንግዝግዝ ውስጥ ቢሆንም፣ የእውነተኛዋ ሴት ምስል፣ ሐሳብ በውስጡ እንዳለ ማሳያ ነው።

## 1.5. የፍጥረት ሥርዓት

መሠረታዊው እውነት ይህ ነው፦ እግዚያብሔር ሰውን በራሱ አምሳል ፈጥሯል፤ የፈጠራቸውም ወንድ እና ሴት አድርጎ ነው። ይህ እውነት ስለ ሴቷ የሚታመን ወይም የሚነገር ሴቷን ዝቅ አድርጎ የሚያይ የትኛውንም አስተሳሰብ ገደል የሚከት ነው። እግዚአብሔር ወንዶችንና ሴቶችን የፈጠረው የተለያየ እሴት ያላቸው አድርጎ አይደለም። ነገር ግን አንዳቸው በሌላቸው ላይ የሚደገፉ የተለያዩ ሆነው ተሰርተዋል። በተፈጥሮ ልዩነት ምክንያት እርስ በርስ አንዱ በጎደለው ሌላው ይሞላል። እና ይህ እውነት በቁም ነገር መታየት ያለበት እንጂ እንደ ተራ ነገር መመልከት የለብንም።

ሴቷ እና ወንዱ እንደ ሰው፥ በህብረተሰብ ውስጥ የተለያየ ሚና አላቸው። ይህም ከሌሎች ጋር ባላቸው ግንኙነት ላይ ተጽእኖ ያሳድራል። ሁለቱም እንደ ግለሰብ ራሳቸውን እንዲሆኑ፣ እና በፍቅር ውስጥ እንዲኖሩ ተጠርተዋል። በዚህ ሁለቱም እኩል ናቸው ነገር ግን ይህን የሚያሳኩት በተለያየ መንገድ ነው። ወንዱ ያመርታል እና የመሪነት ሚናውን ይወጣል። ሴቷ የተመረተውን ተቀብላ መልሳ ትመግባለች። ታሳድጋለች። ወንዱ አዳዲስ ሀሳቦችን እና ለውጦችን የማምጣት

ሃላፊነት አለበት። የሴቷ ሚና ግን ካለዉ ጋር ማገናኘት እና ማላመድ ነው። ወንዱ ወደ ውጪ መውጣት እና ምድርን ማስገበር ዓለምን መቆጣጠር አለበት። ሴቷ ግን በውስጣዊ ማንነታቸው ላይ ማተኮር እና ግንኙነታቸውን መጠበቅ አለባት። ወንዱ በተጨባጭ ነገሮች ላይ ማተኮር፣ በሰፊው እና ተንትኖ ማሰብ ይጠበቅበታል። ሴቷ በግል ስሜቷ ላይ እና ግለሰባዊ በሆነ ግንኙነቶች ላይ ታተኩራለች። ወንዱ መሠረት ይጥላል፣ ይገነባል። ሴቷ የተገነባውን ታሳምራለች፣ ታጠናቅቃለች። ውበት ትሰጠዋለች።

ወንዱ ማከናወን ወይም ፈተናዎችን በማሸነፍ ላይ ማተኮር አለበት፣ ሴቷ ግን በመናከባከብ እና በመመገብ ላይ ታተኩራለች። ወንዱ ሁሉንም ነገር በአመክንዮአዊ አስተሳሰብ ለመረዳት መሞከር ይጠበቅበታል፣ ሴቷ ሕይወትን መስጠት፣ ትርጉም እና ጣዕም መጨመር ይጠበቅባታል። ወንዱ ዕቅድ የመንደፍ እና የመቆጣጠር ሐላፊነት ሲወስድ፤ ሴቷ እነዛን የመረዳት እና የማዋኳድ ሐላፊነት አለባት።

በእነዚህ ልዩ ባሕርያት ውስጥ፣ አንደኛው ከሌላው ከፍ ያለ ወይም የላቀ ሐላፊነት ሌላኛው ያነሰ ንኡስ ሹመት እና የተወሰነ ተዋረድ አለ። ነገር ግን ይህ ሐላፊነት ከተግባር ጋር፣ ከሥራ ጋር የተያየዘ እንጂ ከማንነት ጋር ምንም ግንኙነት የለውም። የአንዱ ዋጋ ከፍተኛ ስለሆነ የሌላው ዝቅተኛ ስለሆነ የሆነ አይደለም። የእርሷ አዕምሮ እና ስብዕና ዝቅ ያለ የእርሱ ደግሞ እጅግ ከፍ ያለ ስለሆነ አይደለም። ፍቅርን እንደ የሕይወት ዓላማ ለተረዳ፣ እንደ ተሰጠው ድርሻ የማገልገለን የሕይወት ልዩ ጥሪ ‘’እንደ መታደል እና ጥቅም ለተቀበለ’’ ጥሪ እና ድርሻው ምንም ይሁን አዋራጅ እና ዝቅተኝነት አድርጎ አይወስድም። ይህ የተለያየ አመለካከት የፍጥረት ታሪክን ጨምሮ በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ይገኛል። ለወንዱ ‘እረዳት የምትሆንለት’ ተሰጥቶታል። በእኛ የወደቀ ዓለም ውስጥ ግን (ከውድቀት በኋላ ባለ ዓለም) ረዳት የምትሆንለት ተሰጥቶታል ማለት ‘ተገዢ፣ ጥገኛ፣ ብዙም ጠቃሚ ያልሆነች ግለሰብ” ማለት ነው። ነገር ግን የመጀመሪያው የመለኮት ዓለማ እንደዚያ አልነበረም። ነገር ግን በእግዚያብሔር ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ ሁሉን መቆጣጠር የሚፈልጉ ወንዶች የሚተረጉሙት በዚህ መንገድ ነው። ነገር ግን እርስ በርስ፣ አንዱ የሌላው፤ ሌላው የአንዱ አገልጋይ መሆን፣ የበሰለ እና በጤናማ መንገድ ያደገ የሰው ልጅ ሕይወት ምን ይመስላል የሚለውን ማሳያ ነው። ከዚህ ማዕከል በሚወጣ እውነት በሁሉም እሴቶች ላይ ለውጥ መምጣት አለበት። ይህ ለውጥ የሚመጣው ደግሞ “ለመገልገል ሳይሆን ለማገልገል” ከመጣው እና በዚያም

እውነት የሰው ልጅ የሕይወት ትርጉም ምን እንደሆነ ከገለጠ ከእርሱ ከክርስቶስ ነው።

ባልና ሚስት የተለያየ አወቃቀር እና ተግባር ቢኖራቸውም ነገር ግን በሩካቤ ሥጋ ግንኙነታቸው አንድ እንደመሆናቸው፣ በሁሉም የሕይወታቸው ዘርፍ አንድ መሆንን ማቀድ አለባቸው። የአስተሳሰብም ሆነ የመንፈስ ልዩነት ቢኖርም እርስ በርስ መደጋገፍ እና ለማህበረሰባቸው እና ለዓለም በጎ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው። ባል ብዘውን ጊዜ ከውጭው ዓለም ጋር ኋላፊነቱን ለመወጣት ሲንቀሳቀስ፣ ሚስትም ለህብረተሰብ እና ለሰው ልጅ ጠቃሚ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባት። ሆኖም፣ የእሷ አስተዋጽዖ የበለጠ ግላዊ ሊሆን ይችላል። ከእይታም አንፃር ከባሏ ያነሰ ሊሆን ይችላል። እሷም የወንዱ አይነት ሚና መጫወት ስለአለባት ውሎዋ አደባባይ ብቻ መሆን አለበት የሚለው እና አይ ሴት ድርሻ ጓዳ ብቻ ነው የሚለው ሁለቱም ፅንፎች የተሳሳቱ ናቸው። ግላዊ ለሆኑ እና የሰው ለሰው ቅርርብ የሚፈጥር ከባቢ በመፍጠር ሴቶች ለሕዝብ አገልግሎት (ለአደባባይ ሕይወት) ልዩ አስተዋፅኦ ማድረግ አለባቸው። ለምሳሌ ወንዱ በአብዛኛው ከቤት ውጪ ካለው ዓለም ጋር ስለሚገናኝ ከቤት ውጭ ካለው ዓለም ጋር ሁሉን ነገር መቆጣጠር ያለበት እርሱ አይደለም። ሴቷ ወይም ሚስት እኩል ዋጋ እንዳላት የቤተ ክርስቲያን፣ የቤተሰብ እና የማህበረሰብ አባል ስለሆነች ለሀገርና ለሰው ልጅ አጠቃላይ ደህንነት የበኩሏን አስተዋጽኦ ማድረግ አለባት።

እነዚህ ሁሉ የመለያየት ጥያቄዎችና በእነዚህ ልዩነቶች ምክንያት የተፈጠሩ ችግሮች ለአንዴና ለመጨረሻ ጊዜ የሚጠፉበት ቀን ይመጣል። መፅሐፍ እንደሚል፥ አንድ ቀን ሴት እና ወንድ"በሰማየት እንደሉ መላእክት ይሆናሉ" በወንዶችና በሴቶች መካከል ያለው የሥልጣን ተዋረድ ለዚች ዓለም እንጂ ለዘላለም አይደለም። ምክንያቱ ደግሞ ያኔ "ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።" ከፍጥረት መጀመሪያ የነበረውን እና ከውድቀት በኋላ የሰውን ልጅ መልሶ ወደ ቦታ ለማምጣት እየተሰራ ካለው የድነት ዓላማ ጋር ያለውን ልዩነት መረዳት አለብን። ፍጥረት ከጅማሬ መልካም የነበረ ቢሆንም፣ ከፍጥረት ጀምሮ መልካም የነበረው ነገር  በዉድቀት ውስጥ ሳያልፍ ራሱ ከጅማሬ በመልካምነት ሁኔታ ውስጥ በነበረ ጊዜ እንኳን የማይለወጥ እና ፍፁማዊነት አልነበረውም። የሁሉም ሰሪ እና ፈጣሪ የሆነው ብቻ በፍጹምነት ውስጥ "ፍጹም እና ፍፁም" ነው። ከጊዜ ወደ ጊዜ እየዳበረ እና በታሪክ አውድ ውስጥ እየተከሰተ ያለ ነገር ሁሉ፣ በነገረ ፍጻሜ ሙላቱን ፍፅምነቱን ያገኛል።

አዳኛችን የሆነው እርሱ ኢየሱስ ክርስቶስ በፆታ ልዩነት ውስጥ በመግባት አንደኛውን ሆኖ አልተሳተፈም። ከመጀመሪያ ጀምሮ በእግዚያብሔር ሐሳብ ውስጥ የነበረ ባል ወይም የሴቷ ተጣማሪ ምን አይነት ወንድ ነው የሚለውን በመኖር አላሳየንም። ይልቁንም ኢየሱስ ክርስቶስ የሁሉንም ነገር መደምደሚያ ምሳሌ ሆኖ ተገልጧል። በምድር ላይ ያሉ መልካም እና ጠቃሚ የሆኑ ሥርዓቶች እና አወቃቀሮች ምን መምሰል እንዳለባቸው እርሱ የመጨረሻው መገለጫ ነው። የጋብቻ እና የቤተሰብ ተቋማት ከሁሉም አይነት የፆታ ግንኙነት ገጽታዎች ጋር ከግላዊ እድገት እና ለውጥ ቀጣይ ሂደት ጋር የተገናኙ ናቸው። ነገር ግን ሰው ከመሆን ሙላት ጋር የተያያዙ አይደሉም። ጾታዊነት እግዚያብሔር ሰው ዘሩን እንዲተካ እና ሕይወትን እንዲያገኝ የነደፈው ዲዛይን ነው። ይህ የመብዛት እና ምድርን የመሙላት ሂደት አንድ ቀን ያበቃል። በሚያበቃበት ጊዜ ደግሞ ፆታዊ ተግባር፣ የፆታ መለያየቶች ተግባር እና ህልውና አብሮ ያበቃል። የፆታ ጽንሰ ሃሳብ ከምድራዊው ዓለም ጋር የተያያዘ ነው።ከሰማያዊው ዓለም ጋር የተቆራኘ አይደለም። እና ከዘላለማዊ ነገሮች ጋር ሳይሆን ከጊዜያዊ ነገሮች ጋር የተያያዘ ነው። ስለዚህ በጾታ መካከል ሊኖር የሚችለው ከሁሉ የተሻለው ሚዛን እንኳን የመጨረሻው እና በጣም አስፈላጊው ጉዳይ አይደለም።

## 1.6. ሥነ ሕይወታዊ (Biological origins) የጾታ እና ፆታዊ ግንኙነት አተያይ ምንድን ነው?

የፆታን ፅንሰ ሐሳብ ሙሉ በሙሉ እንድንረዳ ሥነ ሕይወታዊ (Biological origins) የጾታ እና ፆታዊ ግንኙነት አተያይ ምንድን ነው የሚለውን መመልከት መልካም ነው። የዘርፉ ምሁራን እንደሚነግሩን ጾታዊነትን (sexuality) ከሥነ ሕይወታዊ አተያይ (Biological origins) አንፃር መመልከት ማለት የጾታ እና ፆታዊ ግንኙነት ሥነ ሕይወታዊ አመጣጥ እና የጾታ እና ፆታዊ ግንኙነት ውስጥ ያሉትን ሥነ ሕይወታዊ ገፌ ኀይሎችን ሳይንሳዊ መረጃ ላይ በመመስረት፤ የፆታዊነትን ዝንባሌን፣ ባሕርያትን፣ አስተሳሰቦችን እና ምርጫዎችን መረዳት ማለት ነው ይላሉ።ይህ አተያይ የሰው ልጅን፣ የጾታ እና ፆታዊ ግንኙነት የተለያዩ ገጽታዎች ለማብራራት ጄኔቲክስ ላይ፣ በሆርሞኖች፣ በኒውሮባዮሎጂ እና በዝግመተ ለውጥ ላይ ብቻ ትኩረትን ያደርጋል።

ለምሳሌ በዚህ ጽንሰ ሐሳብ አተያይ መሠረት፣ የአንድ ሰው ወሲባዊ

ዝንባሌ የሚወሠነው በግለሰቡ የዘረመል ጠባይ ምክንያት ነው ይላል። የዘረመል ምክንያቶች አንድ ሰው ወደ አንድ የተወሰነ አይነት የግብረ ሥጋ ግንኙነት ዝንባሌ እንዲያጋድል ምክንያት ይሆናሉ በማለት ይሞግታል። ይህ ጽንሰ ሐሳብ ሳይንሳዊ እንደመሆኑ መጠን እንደ ፍልስፍና፣ ሥነ አዕምሮ እና ሥነ መለኮት የመሳሰሉ ዘርፎች የሃሳብ ሙግቶች እና አመክንዮአዊ አለመጣርስን እንደማስረጃ ይዞ የሚቀርብ ሳይሆን ተጨባጭ የሆኑ የዘረመል የላብራቶሪ ጥናት ውጤቶችን አስረጅ አድርጎ ስለሚያቀርብ፤ ተፅዕኖው እና ተቀባይነቱ ከፍተኛ ነው። በተለይም በምዕራቡ ዓለም የተመሳሳይ ፆታ፣ ፆታቸውን ለሚለውጡ እና ይህን መሰል መንገድ ለሚከተሉ ሰዎች መበራከት በር ከፋች የሆነ ጽንሰ ሐሳብ ነው።

ቀድሞ እነዚህን መሰል ወሲባዊ ዝንባሌዎች ከግለሰቡ አካላዊ፣ ሥነ ልቦናዊ፣ ማሕበራዊ እና ሃይማኖታዊ መመሰቃቀል የተነሳ የመጣ ዝንባሌ ነው ተብለው ይታመኑ ነበር። ነገር ግን የሥነ ሕይወታዊ አተያይ (Biological origins) ጽንሰ ሐሳብ ድንበሩን እያሰፋ በሄደ ቁጥር የትኛውም ፆታዊ ዝንባሌ (sexual Orientation) እንደማንኛውም ጤነኛ ሰው ከተፈጥሮ የሚገኝ እና ቀድሞ ይታመኑ ከነበሩ ነገሮች ጋር ምን አይነት ግንኙነት የሌለው፤ የትኛውም ፆታዊ ዝንባሌ ከምንም አይነት የማንነት መመሳቃቀል አንዳልመጣ እንዲታመን ከፍተኛ ሚና ተጫውቷል። የሥነ ሕይወታዊ አተያይ (Biological origins) የሚደግፉ ምሁራን እና ተመራማሪዎች፣ ሆርሞኖች የፆታዊነት እና የፆታ ግንኙነትን ባሕሪን እና ማንነትን በመቅረጽ ረገድ የሚጫወቱት ሚና ትልቅ እንደሆነ ያስገነዝባሉ።

የሆርሞን ደረጃዎች፣ በተለይም የቴስቶስትሮን እና ኢስትሮጅን፣ መብዛት እና ማነስ የወሲብ ፍላጎትን፣ ከወሲባዊ ዝንባሌያችን የተነሳ የምናሳየው የስሜት ሁኔታ እና የወሲብ ምርጫዎቻችን ላይ ከፍተኛ ተፅዕኖ ሊያሳድሩ ይችላሉ። በተጨማሪም ይህ አተያይ፣ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት፣ በቅድመ ወሊድ እድገት ውስጥ ያለ የሆርሞን ተጋላጭነት፣ ህፃኑ በኋለኛ እድገት ወቅት የሚኖረው ወሲባዊ ዝንባሌ እና ጾታዊ ማንነት ምን ይሁን የሚለው ላይ ተጽእኖ ሊያሳድር ይችላል ይላል። ሌላው በሥነ ሕይወታዊ አተያይ (Biological origins) ማዕቀፍ ውስጥ በሰው ልጆች ፆታዊነት ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጨወተው እና ወሳኝ ስፍራ የሚሰጠው የኒውሮባዮሎጂ ጥናት ነው።

ይህ አመለካከት ወይም ጥናት ከጾታዊነት ፍላጎቶች፣ ምላሾች እና ባሕርያት ጋር በተያያዘ የአንጎልን መዋቅር እና ተግባር ማጥናትን ያካትታል። ይህ ጥናት የፆታዊነት ኒውራል መሠረቶችን ለመረዳት በተቃራኒ ፆታ መሳሳብ ወይም በግብረ

ሥጋ ግንኙነት ወቅት ንቁ የሚሆኑ የአንጎል ክፍሎችን ለመለየት ጥረት ደርጋል። በተጨማሪም፣ እንደ ኦክሲቶሲን፣ ዶፓሚን እና ሴሮቶኒን ባሉ የነርቭ ኬሚካሎች ላይ የሚደረግ ጥናት እነዚህ ንጥረ ነገሮች ወሲባዊ ዝንባሌያችንን (ምርጫችንን) እና ለመጣመር የምናሳየውን ምርጫ ላይ ምን ያህል ተፅዕኖ እንደሚሳድሩ አብጠርጥሮ ለመረዳት ዓላማ ያደርጋል። የመጨረሻው እና በዚህ በሥነ ሕይወት አተያይ (Bilogical perspective) ውስጥ የምናገኘው ዝግመተ ለውጥ ፆታዊነትን እና የፆታ ግንኙነትን በተመለከተ ያለውን አተያይ ነው። ዝግመተ ለውጥ የሰውን ልጅ ፆታ እና ፆታዊ ግንኙነት ከሥነ ተዋልዶ ጥቅምና ከተፈጥሮ ምርጫ አንጻር ለማብራራት ይሞክራል።

የዚህ የዝግመተ ለውጥ አተያይ ፆታ እና ፆታዊነት መታየት ያለበት፣ ዘርን በመተካት ሂደት እና ከተፈጥሮ በሆነ (በአካለ ሥጋ) ግፊት ተጣማሪ የሚሆናቸውን በሚመርጡበት ሂደት ላይ ብቻ ነው ይላል። ለምሳሌ ዘርን በመተካት ሂደት ስላለ ኩነት የዝግመተ ለውጥ አተያይ ፆታ እና ፆታዊነትን ግንኙነትን ሲበይን፣ ሕይወት ያላቸው ነገሮች ዘራቸውን በሚተኩበት ሂደት ውስጥ ወይም ዘራቸውን ለመተካት የሚያስችላቸው ከተፈጥሮ የሆነ ከተመሳሳይ ዝርያዎቻቸው መሐል አንዳንዶቹ ተጣማሪያቸውን ለመምረጥ የተሻለ ሁኔታ እንዲያገኙ፣ የመዋለድ /ዘር የመተካት ችሎታ ከሌላው በተሻለ ሁኔታ እንዲኖራቸው እና የዘራቸውን የመኖር ዋስትና ለማረጋገጥ የሚያስችል አቅም በዘረመላቸው ውስጥ የይገኛል ይላል። ተፈጥሮ አንዳዶቹን ፊት ነስታቸዋለች።ሌሎቹን ደጥሞ ብቁ አሸናፊ አድርጋለች የሚለውን አስተሳሰብ ይደግፋል። የዚህ አስተሳሰብ ምንጭም ነው። የተፈጥሮ ማድላትን የመባዛት ቅድመ ተጠቃሚነት እድሎች (reproductive advantages) ባሕርያት በማለት ይጠራቸዋል።

በዚህ ምልክታ፣ ይህ ለመባዛት የሚያስችል የቅድመ ተጠቃሚነት እድሎች (reproductive advantages) ባሕርያት ሕይወት ያላቸው ነገሮች ጂኖቻቸውን ወደቀጣዩ ትውልድ ሳይጨነግፍ ለማስተላለፍ የሚጠቅማቸው መሠረታዊ ነገር ነው። በሥነ ሕይወታዊ አተያይ ውስጥ (Bilogical perspective) የምናገኘው፣ የዝግመተ ለወጥ በፆታዊነት እና ፆታ ግንኙነት መሐከል አንዳንድ ዝርያዎች ከሌላው የተለየ የቅድመ ተጠቃሚነት እድሎች (reproductive advantages) ባሕርያት አላቸው በማለት የተፈጥሮ ማድላት ከሚስተዋልባቸው ነገሮች መካከል አካላዊ ውበት (Physical Attractiveness) ከፊት ይቀመጣል። ብዙ ጊዜ አካላዊ ውበት ሰዎችን ጨምሮ በብዙ ዓይነት ዝርያዎች ውስጥ እንደ ጥሩ ጤንነት እና ጠንካራ

ጂኖች መኖር ምልክት ሆኖ ያገለግላል።

ሌላው የመራባት አቅም መኖር (Fertility) ነው፦ አንድ ሕይወት ያለው ነገር ብዙ ቁጥር ያለው ዘር የመውለድ ችሎታ ካለው፣ የዛ ሕይወት ያለው ነገር ጂኖች ለቀጣዩ ትውልድ የመተላለፍ እድል ይጨምራል።

የወላጅ እንክብካቤ (Parental care)፦ በአንዳንድ ዝርያዎች ወላጆች ለልጆቻቸው እንክብካቤ እና ጥበቃ ያደርጋሉ ይህም ዘራቸው ችግሮችን ተቋቁሞ የመኖር እና ዘርን የመተካት እድሉ ሰፊ እንዲሆን ያደርጋል።

ለተቃራኒ ፆታ ድምፅ ማሰማት እና የፍላጎት ምልክቶችን ማሳየት (Mating calls and displays)፦ እንደ ወፎች፣ እንቁራሪቶች እና ነፍሳት ያሉ እንስሳት የትዳር ጓደኛን ለመሳብ ብዙውን ጊዜ የመጥሪያ ድምፆችን ወይም ፍላጎታቸውን የሚያሳዩ ምልክቶች ይጠቀማሉ። እናም ተቃራኒው ፆታ እንዲህ አይነት ድምፅ የሚያሰማ እና ምልክት ማሳየት የሚችል ጤናማ እና ጠናካራ ነው ብለው ስለሚያምኑ ከሌላው የበለጠ ቀድመው ወደ እዛ ይሳባሉ።

ጠንካራ በሽታን የመከላከል ሥርዓት (Strong immune system)፦ ጠንካራ የበሽታ መከላከል ሥርዓት አንድ ግለሰብ በሽታን እና ኢንፌክሽኖችን እንዲቋቋም ይረዳዋል። ይህም የመራባት እና ጂኖቹን ወደቀጣዩ ትውልድ የማስተላለፍ ችሎታውን እንዲያሻሽል ይረዳዋል። የዘረመል ብዙኂነት (Genetic diversity)፦ ከተለያየ የዘረመል ዳራ የተገኙ ለበሽታ፣ ለፓራሳይቶች እና ለተለዋዋጭ የአካባቢ ሁኔታዎች ተጋላጭነታቸው አነስተኛ ስለሆነ ብዙውን ጊዜ የተሻለ የመዳን እና የመራባት ደረጃ አላቸው።

ከተወሰኑ አካባቢዎች ጋር መላመድ (Adaptations to specific environments)፦ ከአካባቢያቸው ጋር በጥሩ ሁኔታ የተላመዱ ፍጥረታት በሕይወት የመትረፍ እና የመራባት እድላቸው ሰፊ ሲሆን እነዚያን ጠቃሚ ባሕርያትን ለልጆቻቸው ያስተላልፋሉ።

ለምሳሌ ከእነዚህ ባሕርያት ውስጥ አካላዊ ውበት (Physical attractiveness) የሚለውን እንመልከት። አካላዊ ውበት የሰውን ልጅ ጨምሮ በብዙ አይነት ሕይወት ባላቸው ፍጥረታት ውስጥ አንድ ዝርያ ጥሩ ጤንነት እና ጠንካራ ጂኖች እንዳለው ማሳያ ሆኖ ያገለግላል። ከዚህም የተነሳ ተፈጥሮአዊ ውበት ወይም

መስህብነት ያላቸው ኦርጋኒዝምስ በቀላሉ ከተቃራኒ ፆታ ጋር ለመጣመር እና አጣማሪያቸውን ለማግኘት የቀረቡ ናቸው። ይህ ሂደት ደግሞ በሰው ልጆች መካከል ብቻ ሳይሆን በሁሉም ፍጥረታት ውስጥ አለ። እንደ ዝግመተ ለውጥ ኋሊዮት ትንታኔ፣ የመስብህነት ወይም ውበት ጽንሰ ሐሳብ ሥነ ሕይወታዊ ምክንያቶችን (Biological factors) እና ይህ ውበት በሰው ባሕሪ እና በማህበረሰብ መካከል እንዴት ነው የሚገለጠው በሚለው ላይ ይመሠረታል።

ከዝግመተ ለውጥ ንፅረተ ዓለም አንፃር፣ የአካለዋ ውበት ጽንሰ ሐሳብ ከተቃራኒ ፆታ ምርጫ (sexual selection) ጋር አያይዞ መረዳት ይቻላል። በመሠረቱ፣ አንዳንድ ባሕርያት የትዳር ጓደኛን የመሳብ ችሎታን በማሳደግ ወይም ተቀናቃኞችን በማሸነፍ የቅድመ ተጠቃሚነት እድሎችን ስለሚያበዘ ከጊዜ ወደ ጊዜ ስር በመስደድ ከጊዜ ወደጊዜ ጠንካራ እየሆኑ ይሄዳሉ። በዚህ ዘርፍ ላይ ጥናት የሚደርጉ ምሁራን ይህ ሐሳብ ለመጀመሪያ ጊዜ ወደ ወደ ምሑራዊ የአደባባይ ውይይት የመጣው በቻርለስ ዳርዊን ነው በማለት ፅፈው እናነባለን። እንደ ዳርዊን ሐሳብ፣ በመራባት ሂደት ውስጥ አንዳንድ ዝርዎች ከአምሳያ ዝርያቸው የተሻለ እድል መኖር ከተፈጥሮ መረጣ (natural selection) የተለያዩ ዝርያዎች በዝግመተ ለውጥ ውስጥ በማለፍ እንዲጎለብቱ ዋነኛ ገፌ ምክንያት ነው ይላል። ይህ ማለት አካላዊ መስህብ ለጠቅላላው ጤንነት እና በሁሉም አንግል ለሚታየው የሕይወት ንቃት እንደተወካይ ሆኖ ያገለግላል። ይህም ማለት አካላዊ መስህብ ያላቸው ግለሰቦች ጤነኛ ልጅ የመውለድ እድላቸው ከፍተኛ ነው። በዚህም ምክንያት የሚወልዱት ልጅ በሕይወት የመቆየት እና ዘሩን የመተካት እድሉ ከፍተኛ ነው። ይህም ወደ አንድ ተመሳሳይ መለያ ወዳለው ባሕርያት ወይም መገለጫዎች ያመራል። ለምሳሌ የፊት ቁንጅና፣ የቆዳ ጥራት እና በሰውነት ብልቶች መካከል መመጣጠን መኖር ተጠቃሽ ናቸው። ይህ ደግሞ የመልካም ጤንነት ባለቤት ከመሆን ጋር እጅጉን የተቆራኘ ነው። ከዛም አልፎ ይህን መሰል መገለጫ ዓለም አቀፋዊ በሆነ መልኩ ምስብህ ያለው ማንነት መገለጫ ነው። ከሥነ ሕይወት ደረጃ (biological level) የአካላዊ ቁንጅና እና ጤናማነት ልዩ ልዩ በሆኑ ምክንያቶች የሚመጣ ነው። ከነዚህም መካከል የሆርሞኖች ሚዛን መጠበቅ እና በሽታን የመቋቋም አቅም ዋነኞቹ ናቸው።

ለምሳሌ አንዳንድ የፊት ገጽታዎች ለምሳሌ ትልልቅ አይኖች እና ሙሉ ከንፈሮች በሴቶች ላይ ካለው ከፍተኛ የኢስትሮጅን መጠን ጋር የተቆራኙ መሆናቸውን በጥናት ተረጋግጧል። ይሄ ደግሞ በሌላ ቃል የወላድነት ሆርሞን በበቂ ሁኔታ

መኖር የሚያመለክት ነው። በተመሳሳይም በወንዶች ውስጥ የጠንካራ መንጋጋ እና ሰፊ ትከሻ መኖር ከፍ ያለ የቶስቶስትሮን መጠን ጋር ይያያዛል። ይህን በራሱ ጥንካሬን እና ወንዳወንድነትን መታደል ጠቋሚ ነው። ከዚህም በላይ ጥናቶች እንደሚያመለክቱት የተመጣጠነ የበሽታ መከላከያ ሥርዓት ያላቸው ግለሰቦች ይበልጥ የተመጣጠነ የፊት ገጽታ አላቸው። ይህም በውበት እና በጤናማነት መካከል ያለውን ግንኙነት የሚያጠናክር ነው። በሽታን ለመቋቋም ደግሞ እጅግ አስፈላጊ ነው።

ከሰው ባሕሪ እና ማሕበራዊ መስተጋብር (social dynamics) አንጻር የአካላዊ ማራኪነት አስፈላጊነት ምን ያህል እንደሆነ የሚነገር ነገር አይደለም። በተለያዩ ባህሎች ውስጥ አካላዊ ቁንጅና ያላቸው ግለሰቦች ብዙውን ጊዜ ከሌሎች በተሻለ ሁኔታ ይስተናገዳሉ። በነገር ሁሉ ቅድሚያ ያገኛሉ። ከፍ ያለ ማሕበራዊ ደረጃ ላይ ይቀመጣሉ። ለፍቅር እና ወሲባዊ ግንኙነት ብዙ እድሎች ይኖራቸዋል። ይህ ተፅእኖ በትምህርት፣ በሥራ እና በወንጀል መቅጫ የፍትሕ ሥርዓትን ጨምሮ በተለያዩ ቦታዎች በሰፋት የተጠና ሲሆን አካላዊ መስብህ ወይም ቁንጅና በበርካታ የሕይወት ዘርፎች ተጨባጭ ጥቅሞችን እንደሚያስገኝ ታይቷል።

ይሁን እንጂ አካላዊ ማራኪነት የትዳር ጓደኛን ምርጫ ብቻ የሚወስን አለመሆኑን እና ሌሎች በርካታ ምክንያቶችም እንደ ስብዕና፣ ብልህነት እና ተኳሃኝነት የመሳሰሉ ሌሎች ምክንያቶች እንዳሉ ልብ ሊባል ይገባል፡ ፡ በተጨማሪም፣ የአካላዊ ማራኪነት አስፈላጊነት ከግለሰቦች ግለሰቦች ይለያያል።የውበት ደረጃዎች የባህል ተጽዕኖ አለባቸው። ምንም እንኳን በዓለምአቀፍ ደረጃ ማራኪ ተብለው የሚታወቁ አንዳንድ መገለጫዎች ቢኖሩም ውብት እንደ ባህሉ ይለያያል። ሥነ ሕይወታዊው የፆታ እና የተቃራኒ ፆታ አተያይ አካላዊ ቁንጅና በዝግመተ ለውጥ፣ በሥነ ሕይወት እና በማህበራዊ መነፅሮች ልንረዳው የሚገባ ውስብስብ ክስተት ነው ይላል። ሰዎችን ጨምሮ በብዙ ዓይነት ዝርያዎች ውስጥ ማራኪነት ጥሩ ጤንነት እና ጠንካራ ጂኖችን የሚያመለክት አስፈላጊ ምልክት ሆኖ ያገለግላል። የአካላዊ ውበት ግንዛቤ እና አንድምታው በሰዎች ባሕሪ እና ማሕበራዊ መስተጋብር ውስጥ ቁንጅና የሚጫወተውን ሚና በመመልከት የተሻለ አድናቆት እንድንሰጥ የሚያደርግ ነው። ሌላው በዝግመተ ለውጥ ውስጥ የምናየው ሥነ ሕይወታዊ ፆታዊነት እና የተቃራኒ ፆታ ጉዳይ ብየኔ የተፈጥሮ መረጣ (natural selecetion) የምንለው ነው። በተፈጥሮ ዘርን የመተካት ሂደት ምርጫ (natural selecetion) ወይንም በሌላ አባባል

ተቃራኒ ፆታን መምረጥ የምንለው ነገር ራሱ፣ ተፈጥሮ የሚያመጣው ከራሱ ከተፈጥሮ የተገኘ ፀጋ ሲሆን በአንድ ማህበረሰብ ውይም ዝርያ ውስጥ ጥቂት ግለሰቦች ከአምሳያዎቻቸው በተሻለ ተቃራኒ ፆታን ወደራሳቸው በመሳብ እና ዘራቸውን በመተካት ሂደት ውስጥ ስኬታማና ናቸው። አንዳንድ ግለሰቦች ከሌሎች ይልቅ የትዳር ጓደኛን በመሳብ እና ዘር በማፍራት የበለጠ ስኬታማ ሲሆኑ ይህን ተፈጥሮአዊ ምርጫ (sexual selection) ብለን እንጠራዋለን።

## 1.7. ግለሰባዊነት እና መነሻው

ግለሰባዊነት እንደ ጽንሰ ሃሳብ በምዕራቡ ዓለም አስተሳሰብ እና ማህበረሰብ ውስጥ ስር የሰደደ ነገር ነው። ግለሰብን ማዕከል ያደርጋል። ግለሰባዊነት አንድ ሰው የግል ሕይወቱን የመቆጣጠር እና ለራሱ ሕይወት ራሱ የመወሰን መብት አለው ብሎ ማመን ነው። አንድ ግለሰብ ምን እንደሚያስብ፣ እንደሚያምን አንደሚያደርግ ለማወቅ ብቁ ስለሆነ ውጫዊ ኀይል ጣልቃ ሊገባበት፤ ማንኛውም ዓይነት ባለስልጣን ሊቆጣጠረው አይገባም የሚል ነው። የግለሰባዊነት አመጣጥ ከበርካታ ታሪካዊ እና ፍልስፍናዊ ሂደት ውስጥ አልፎ እየዳበረ የመጣ ነው። ለምሳሌ ኤሜል ብርነር በሌላ ሥራው ላይ ለብዙ ዘመን ሰዎች ግለሰባዊነትን በሃሳብ ደረጃ እንኳን ሳይረዱ እንደኖሩ ሲናገር "የሰው ልጅ ታሪክ በማህበር ተሰብስቦ በመኖር የተጀመረ ነው። ቀደምት ሰዎች እና ቀደምት ማሕበረሰቦች በራሱ ምርጫና ፍላጎት የሚኖር ግለሰብ የሚባል ስብዕና እንዳለ አያውቁም ነበር። ሰዎች ሁሉም ተመሳሳይ ነበሩ። ሁሉም ሰው ያደረገውን ሌላኛውም ሰው ያደርገዋል። ሁሉም ሰው የሚያስበውን ሌላኛውም ሰው ያስባል። ቀደምት ሰዎች ራሳቸውን ከእንስሳት በግልጽ እንደማይለዩ እንዲሁ ግለሰቡም በቡድን ውስጥ የተለየ አልነበረም። ጥንታዊውን ማህበረሰብ የተቆጣጠረው የመንጋ አስተሳሰብ ነው (The collective mind) እኛ የምናውቃቸው ጥንታዊ ስልጣኔዎች፣ የግብፅ እና የባቢሎን ስልጣኔዎች ሙሉ በሙሉ ግለሰባዊነትን የማያውቁ የጋርዮሽ ስልጣኔ ነበሩ። የባህልም ሆነ የሥነጽሑፍ፣ የእጅ ጥበብም ሆነ የግንባታ መጀመሪያ ሀሳቡን ያፈለቀው፣ ወደ ተግባር የቀየረው እና ያስጨረሰው እከሌ የሚባል ሰው የለበትም። ሁሉ ነገር የማህበረሰብ ነው። አንድ የተለየ እንደግለሰብ የሚጠራ ነገር ቢኖር ንጉሡ ብቻ ነው። ነገር ግን ንጉሱ ማንነታቸው ከማይታወቅ የሰዎች ስብስብ አኗኗር ተለይቶ እንደግለሰብ የተጠራው፣ ከፍ ብሎ የወጣው በባሕሪው ሳይሆን በማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ተግባሩ ነው። በዚህ ሁነኛ ምክንያት ብቻ ማለትም ከፍተኛውን የሕዝብ ስልጣን በመያዙ፣

የመለኮትን ባሕርያት የተላበሰ እና ከመለኮት የተላከ ተደርጎ ይከበራል። ይፈራል፥ ይመለካል። ከግለሰባዊነት የሚወጣ ምንም ነገር የለም። ከዚህ ራሱ የምናየው ከግለሰባዊነት በላይ የተቋም እና የጋርዮሽ አኗኗር የበላይነት ምን ያህል ከፍተኛ እንደነበረ ነው።” በማለት ይናገራል።

ይህንን የጋሪዮሽ አኗኗር አካሄድ በመስመበር ግሪኮች የመጀመሪያ ናቸው። ከግሪክ ፍልስፍና ቀጥሉ ለግለሰባዊነት እድገት ትልቅ ሚና የተጫወተው የህዳሴ ዘመን (Renaissance)፣ የተሐድሶ እንቅስቃሴ (Reformation) እና ዘመነ አብርሆት (Enlightenment) ነው። የጥንት ግሪክ የግለሰባዊነት መነሻ ከጥንታዊው የግሪክ ፍልስፍና በተለይም ከቅድመ ሶቅራጥስ ፍልስፍና ሥራዎች ውስጥ ነው። በዚህ ፍልስፍና ውስጥ ግለሰቡ ከዓለም ጋር ስላለው ግንኙነት አጽንኦት ተሰጥቶበታል። በዚህ ዘሪያ ያጠኑ ሙሁራን ይህ ሃሳብ የበለጠ የተገነባው በሶቅራጥስ ነው በማለት ይናገራሉ። በሶቅራጠስ ፍልስፍና ውስጥ አንድ ግለሰብ ራሱንና በዓለም ላይ ስላለበት ቦታ ለመረዳት እጅግ አስፈላጊው ነገር ራስን መመርመር እና ውስጥን መፈተሽ ግዴታ እንደሆነ ያስቀምጣል። በዚህም ግለሰቡን ከመንጋ ይነጥለዋል።

የህዳሴ ዘመን (Renaissance) ለግለሰባዊነት ትልቅ የእድገት ጊዜ ተደርጎ ይቆጠራል። በዚህ ጊዜ ውስጥ እንደገና የሰው ልጅ አእምሮን እና የግለሰብ ልዩ ችሎታዎች ለማጥናት ፍላጎት ማደግ ጀመረ። እንደ ሊዮናርዶ ዳ ቪንቺ፣ ማይክል አንጀሎ እና ፔትራች ያሉ ምሁራን እና አርቲስቶች የሰው ልጆችን ስኬት እና ነፃነት ማግነን ጀመሩ፣ አዲሱ ትውልድ ግለሰባዊነትን እንዲቀበልም አነሳስተዋል ይባላል። ሌላኛው ለግለሰባዊነት እድገት ተጠቃሽ ጊዜ ዘመነ አብርሆት (Enlightenment) ነው። ከ17ኛው መቶ ክፍለ ዘመን መገባደጃ እስከ 18ኛው ክፍለ ዘመን መገባደጃ ድረስ የነበረው ዘመነ አብርሆት፣ ግለሰቦች ራሳቸውን ችለው ማሰብና መተግበር የሚችሉ ምክንያታዊ ፍጡራን ናቸው የሚለውን ሃሳብ አስፋፍተዋል። በዚህ በዘመነ አብርሆት ወቅት፥ እንደ ጆን ሎክ እና ዣን ዣክ ሩሶ ያሉ ቁልፍ አሳቢዎች የግል ንብረት የማግኘት መብትን እና ሃሳቦችን የመግለጽ ነፃነትን ጨምሮ ለግለሰብ መብቶች ተከራክረዋል። በአሜሪካ እና በፈረንሣይ አብዮት እንደታየው የአብርሆት ዘመን ሀሳቦች ወደ ፖለቲካው ዓለም ተተርጉመዋል። ሁለቱም አብዮቶች ግለሰቦች ራሳቸውን በራሳቸው የማስተዳደር እና ጨቋኝ ገዥዎችን የመቃወም መብት እንዳላቸው የሚሰብኩና በዚህ የሐሳብ ግፊት የመጡ አብዮቶች ነበሩ። ሙሁራኑ እንደሚነግሩን በዚህ አብዮት ወቅት ቁልፍ ሥራዎች የነበሩት የቶማስ ጄፈርሰን

የነጻነት መግለጫ (Declaration of Independence) እና የፈረንሳይ “የሰው እና የዜጎች መብቶች” መግለጫ እነዚህን የግለሰባዊነት እና በፖለቲካ ራስን በራስ የማስተዳደር ጽንሰ ሀሳብን የሀሳባቸው ዋነኛ ማጠንጠኛ ያደረጉ ናቸው።

ሌላው ከአብርሆት ዘመን ቀደም ብሎ የተነሳው የተሃድሶ እንቅስቃሴ በግለሰባዊነት ግንዛቤ እና አረዳድ ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳርፏል። ተሐድሶው በምዕራቡ ዓለም የክርስትና ታሪክ ውስጥ ትልቅ ለውጥ ያመጣ ሲሆን፣ በግለሰባዊነት እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል ተብሎ ይታመናል። ከተሃድሶ በፊት የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያን በአውሮፓ ውስጥ የበላይ እና ግዢ ሃይማኖት ነበረች። ቤተ ክርስቲያን ትምህርትን፣ አምልኮን እና የሀይማኖት አስተምህሮን ጨምሮ ሁሉንም የሃይማኖታዊ ሕይወት ዘርፎች ትቆጣጠር ነበር። ይህ ማለት ግለሰቦች በሃይማኖታቸው ውስጥ የሚናገሩት ነገር በጣም ትንሽ ነበር ማለት ነው። በሚያዩት እና በሚሰሙት ነገር ስህተት የሆነ ነገር አግኝተው እንኳን ቢሆን ያንን ለመግታትና ለማስተካከል መብት አልነበራቸውም። ከካቶሊክ ሃይማኖት ውጪ ሌላ ሃይማኖት የመከተል መብት አልነበራቸውም።

ተሐድሶ የካቶሊክ ቤተ ክርስቲያንን ሥልጣን በመቃወም የግለሰብ እምነት ወሳኝ እንደሆነ እና አንድ ግለሰብ መጽሐፍ ቅዱስን ራሱ አንብቦ መረዳት እንደሚችል ያለውን አስፈላጊነት አጽንዖት ሰጥቷል። ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር በሚኖረውን ግንኙነት የግድ በቤተ ክርስቲያን እና በቄስ በኩል ካልሆነ የሚለውን ሃሳብ ውድቅ አድርጓል። ይህም ግለሰቡ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ግንኙነት ላይ አዲስ ትኩረት እንዲሰጥ አድርጓል። የበለጠ ግለሰባዊ ባህል ለመፍጠር ረድቷል።

ከተሐድሶው ዋና ዋና ገጽታዎች አንዱ የሁሉም አማኞች ክህነት ሐሳብ ነው። ይህ የተሐድሶ አስተምህሮ፣ ሁሉም ክርስቲያኖች በእግዚአብሔር ፊት እኩል እንደሆኑ እና መጽሐፍ ቅዱስን ለራሳቸው የማንበብ እና የመረዳት መብት እንዳላቸው ያስተምራል። ይህም በግለሰቦች ውስጥ አዲስ የስልጣን ስሜት እንዲፈጠር አድርጓል። እና የበለጠ ዴሞክራሲያዊ ማህበረሰብ ለመፍጠር ረድቷል። ተሐድሶው በትምህርት ዕድገት ላይ ከፍተኛ ለውጥ እንደመጣ ይነገራል። ከተሃድሶ በፊት፣ ትምህርትን በአብዛኛው የምትቆጣጠረው ቤተክርስቲያን ነበረች። ትምህርትም ለተወሰኑ ሰዎችና ለቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ብቻ ነበር። ይሁን እንጂ የፕሮቴስታንት ተሐድሶ አራማጆች ትምህርት ለሁሉም ክርስቲያኖች አስፈላጊ እንደሆነ ያምኑ ስለነበር፣ ትምህርት ቤቶችን እና ዩኒቨርሲቲዎችን በማቋቋም ለብዙሃኑ ትምህርት እንዲሰጥ አድርገዋል። ይህም የበለጠ ማንበብና መጻፍ

የሚችል ህዝብ እንዲኖር አስችሏል፣ እና የበለጠ መረጃ ያለው ዜጋ ለመፍጠር ረድቷል።

ይህም በሌላ መልኩ እንደግለሰብ ማን ነኝ ብለው የሚጠይቁ፣ ግለሰባዊነትን መረዳት የሚችሉ ሰዎችን ለመፍጠር ረድቷል። ተሐድሶ በግለሰባዊነት እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። እሱም የግለሰብ እምነትን፣ በመጽሐፍ ቅዱስን ትርጓሜ የግለሰቡ ሚና እና የትምህርትን አስፈላጊነት አጽንኦት ሰጥቷል። እነዚህ ለውጦች የበለጠ ዴሞክራሲያዊ እና በመረጃ የተደገፈ ማህበረሰብ ለመፍጠር ረድተዋል። እናም ተሐድሶ ለዘመናዊው ዓለም መሠረት ጥሏል እየሉ ያወድሱታል። የተሃድሶ እምነት እምነት የግልለሰብ እና የግለሰቡ የኀሊና ዳኝነት ነው ሚለውን አስርፃል። ሁሉም ሰዎች በመጽሐፍ ቅዱስ በኩል በቀጥታ ወደ ወደ እግዚአብሔር መቅረብ ይችላሉ በሚለው አስተምህሮ አማካኝነት፥ ከዚህ ፊት ያልነበረን ሰዎች እንደ ግለሰብም ሆነ እንደ ቡድን የፈለጉትን የማመን እና የማሰብ ነፃነታቸውን እንዲያገኙ ድጋፍ አድርጓል። የበለጠ ማንበብና መጻፍ የሚችል ህዝብ ለመፍጠር በመርዳቱ፥ ግለሰቦች ለራሳቸው እንዲያስቡ እና ባለስልጣኖች ተቋማትን ተገን አድርገው ለሚሠሩት ስህተት ተጠያቂ የሚያደርግ መሳሪያ አስታጥቋቸዋል። በግለሰብ ነፃነት መርህ ላይ የተመሠረቱ እንደ ዴሞክራሲያዊ እና ሰብአዊ መብቶች ያሉ አዳዲስ ፖለቲካዊ እና ማሕበራዊ አስተሳሰቦችን እንዲያዳብሩ አስተዋጽኦ አድርጓል። ተሐድሶ ውስብስብ እና ዘርፈ ብዙ እንቅስቃሴ ነበር፣ ነገር ግን በግለሰባዊነት እድገት ላይ ከፍተኛ ተጽዕኖ አሳድሯል። የበለጠ ነፃ፣ ታጋሽ እና የተለያየ አስተሳሰብን የሚያስተናግድ ማህበረሰብ ፈጥሯል። እና ግለሰቦች ለራሳቸው ራሳቸው እንዲያስቡ እና እጣ ፈንታቸውን እንዲቀርጹ የሚያስችል መሳሪያ ሰጥቷቸዋል።

## 1.8. የግለሰባዊነት ትርጉም

ግለሰባዊነት፣ ለግለሰብ በራሱ ጉዳይ ራሱ ወሳኝ ነው በሚለው እና ራስን መቻል ላይ ትልቅ ትኩረት ይሰጣል። ሰዎች ለራሳቸው ራሳቸው እንዲያስቡ ያበረታታል። ራሳቸውን እንዲችሉ፣ በራሳቸው ምክንያታዊነት ላይ እንዲደገፉ፣ የፈጠራ ሰዎች እንዲሁኑ እና በብዙ አማራጮች የተሞሉ እንዲሆኑ ያበረታታል። ከዚህም በላይ ግለሰባዊነት ለግለሰብ ሃላፊነት ትልቅ ስፍራ ይሰጣል። እያንዳንዱ ሰው ሕይወቱን መምራት እንዳለበት እና ለሚያደርጋቸው ነገሮች ራሱ ኃላፊነት መውሰድ እንዳለበት ያስገነዝባል። ሌላው በግለሰብነት ውስጥ ቁልፍ ነፃነት እና የግለሰቦች

መብት ነው፡፡ የግለሰባዊነት አስተሳሰብ አንድ ሰው መኖር ካለበት መኖር ያለበት በነፃነትና መብቱ በሚከበርበት ሁኔታ ውስጥ ነው በማለት ያስተምራል፡፡

ግለሰባዊነትን መሠረት ባደረገ ማህበረሰብ ውስጥ፣ ግለሰቦች ግባቸውን፣ ጥቅማቸውን እና ህልማቸውን ስልጣን አለኝ የሚል አካል ወይም ተቋም ጣልቃ ሳይገባ የመከተል ነፃነት አላቸው፡፡ ለግለሰብ መብት ቅድሚያ የሰጠ ማህበረሰብ መገለጫ ብለን የምንጠራቸው የመናገር ነፃነት፣ የእምነት ነፃነት፣ የመደራጀት ነፃነት፣ እና የመሳሰሉትን ናቸው፡፡ አሁን ባለንበት ዘመን ብዙ ሀገሮች እና ማህበረሰቦች እነዚህን ነገሮች ለማምጣት ብዙ ዋጋ እየከፈሉ ቢሆንም ማሳካት የቻሉት ግን ጥቂቶች ናቸው፡፡ የብዙ አገር መሪዎች እና ታጋዮች እነዚህን ነገሮች ለማክበርና ለማስጠበቅ ቃል ገብተው ወደ ስልጣን ቢመጡም ነገር ግን የበለጠ አፋሽኝ መንግስታዊ ሥርዓት ሲዘረጉ ይታያል፡፡

የግለሰባዊነት መብት የድሎት እና የምርጫ ጉዳይ ሳይሆን አንደ ማህበረሰብ ሊቀበለው እና ሊስተናግደው የሚገባ መሠረታዊ ነገር ነው፡፡ ግለሰባዊነት አንድ ማህበረሰብ ሊያዳብረው እና ሰፍራ ሊሰጠው የሚገደድበት ጽንሰ ሐሳብ ነው፡፡ በአንድ ማሕበረ ሰብ ውስጥ ግለሰባዊነት የሚጫወተው ሚና ይሄ ነው ተብሎ ተዘርዝሮ የሚያልቅ አይደለም፡፡ ግለሰባዊነት በሕብረተሰብ ላይ የሚያሳድረው ተጽእኖ በተለያዩ ደረጃዎች ማለትም በኢኮኖሚ፣ በማሕበራዊ እና በባሕላዊ ዘርፎች ላይ ሊታይ ይችላል፡፡ በመንጋ እና ከመንግስት ቀጥታ ትዕዛዝ ከሚመሩ የእድገት አካሄዶች በተሻለ ግለሰቦች ጥቅማቸውንና ፍላጎታቸውን ለማሳካት ነፃ ሲሆኑ፣ አዳዲስ ነገሮችን የመፍጠር እና ለዕድገት የሚጥሩ ሆነው ተገኝተዋል፡፡ ምንም እኳን ብዙ ሐገሮች ያለ ግለሰባዊነት መብት እና ባህል የኢኮኖሚ እድገት ቢያስመዘግቡም ሰዎች በሁሉም ዘርፍ የተሻለ እና ደስተኛ ኑሮ የሚኖሩበት ሐገር መሆን አልቻሉም፡፡ ግለሰባዊነት ሰዎችን በችሎታ እና ጥረታቸው ላይ ተመስርተው ጠንክረው እንዲሰሩ እና ስኬትን እንዲጎናጸፉ በማድረግ ብቃትን ያጎለብታል፡፡ ግለሰባዊነትን በመቀበል ሰዎች ጠንካራ የማንነት ስሜት እና ተግዳሮቶችን የመቋቋም ችሎታ እንዲያዳብሩ ያስችላቸዋል፡፡ ተግዳሮቶችን እና እንቅፋቶችን መቋቋምን ይማራሉ፡፡ እንደ ግለሰብ የሚያድጉ እና ችግሮችን ለመቋቋም የበለጠ ችሎታ ያላቸው ያደርጋቸዋል፡፡

# 1.9. ግለሰባዊነት በክርስትና ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ

ክርስቲያናዊ ባልሆኑ የግለሰባዊነት ጽንሰ ሃሳብ ውስጥ ስፍራ የማይሰጠው ነገር ግን ክርስትና ከፍተኛ ትኩረት የሚሰጠውን ሁለት ነገር እናገኛለን። አንደኛ ክርስትና ግለሰባዊነትን ከማህበረሰብ አያስበልጥም። በማህበረሰብ ኪሳራ ግለሰባዊነትን አይገነባም። በሌላ ጎኑ ደግሞ፣ በሁለተኛነት የምናገኘው፣ እንደ ጥንት ዘመን ሰዎች ግለሰባዊነትን የማያስተናግድ ማህበረሰብ እንዲኖር ደግሞ አይፈቅድም። በዚህም ምክንያት ክርስትና በግለሰባዊነት እና በማሕበረ ሰብ አያዎ (the paradox of selfhood and community) ውስጥ ቆሞ የሚገኝ ሀይማኖት ነው። ክርስትና ግለሰቦች ስለሕይወታቸው ራሳቸው የሚጠቀማቸውን የመወሰን መብት እንዳላቸው፣ ስለእምነት ምርጫቸው መገደድ እንደሌለባቸው እና ተጠያቂነታቸውም በእግዚያብሔር ፊት ብቻ እንደሆነ አፅንኦት ይሰጣል። ግለሰቦች ለሚወስኑት ውሳኔ እና ለሚያደርጉት ድርጊት ሃላፊነት ይወስዳሉ። በሌላ ጎኑ ደግሞ ክርስትና ግለሰቦች ለማህበረሰብ ደህንነት እና በጎነት አስተዋፅ የሚያበረክቱ ማህበረሰባዊ ኋላፊነት እንዳለባቸው የሚረዱ እንዲሆኑ ያሳስባል። ማህበረሰብን ያገለለ ግለሰባዊነት ትርጉም የሌለው እና “ውሸተኛ ግለሰባዊነት” ነው። በዚህም ምክንያት ክርስትና ግለሰባዊነትን የሚያስተናግድበት ማዕቀፍ ሄዶ ሄዶ ለግለሰቡም ለማህበረሰብ የሚጠቅም እንደሆነ ታይቷል።

ቀደም ብለን እንዳየነው የግለሰባዊነት ጽንሰ ሐሳብ መነሻ ቀደምት የግሪክ ፈላስፎች፣ በተለያየ ወቅት የተከሰተ የታሪክ እና የባህል ለውጥ እንደሆነ አይተናል። ነገር ግን ብዙዎች፣ እያንዳንዱ ሕይወት በእግዚያብሔር አምሳል ስለተፈጠረ ልዩ የሆነ ዋጋ አለው፣ ሕይወትም ክብር ነው፣ እግዚያብሔር በእያንዳንዱ ሰው ሕይወት ውስጥ ዓላማ አለው፣ ደግሞም እያንዳንዱ ግለሰብ በቀጥታ ከእግዚያብሔር ጋር ግንኙነት ማድረግ ይችላል የሚለውን ሐሳብ እንዳስተዋወቀን እንደ ክርስትና ያለ ለግለሰባዊነት ጽንሰ ሐሳብ ዋነኛ ምንጭ የሆነ ሌላ አስተሳሰብ የለም በማለት ይሞግታሉ። ክርስቲያናዊ የግለሰባዊነት ጽንሰ ሐሳብ ክርስትና ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ እና ከእግዚአብሔር ጋር ስላለው ግንኙነት ከሚያስተምረው መሠረታዊ አስተምህሮው የተገኘ ነው። የጋራ ወይም የተዋረድ አወቃቀሮችን አጽንዖት ከሚሰጡ ሌሎች ሃይማኖታዊ ሥርዓቶች በተለየ፣ ክርስትና እያንዳንዱ ግለሰብ ፆታ፣ ዘር እና ማሕበራዊ ደረጃቸው ግምት ውስጥ ሳይገባ “አይሁዳዊ ወይም የግሪክ ሰው የለም፥ ባሪያ ወይም ጨዋ ሰው የለም፥ ወንድም ሴትም የለም፤ ሁላችሁ በክርስቶስ ኢየሱስ አንድ ሰው ናችሁና።” በማለት በእግዚያብሔር ፊት እኩል

መሆናቸውን ያስተምራል።

ይህ የእኩልነት አስተሳሰብ ከብሉይ ኪዳን ጀምሮ እስከ አዲስ ኪዳን የዘለቀ ነው። የሰው እኩልነት ጽንሰ ሐሳብ ከአይሁድ-ክርስትና "እያንዳንዱ ሰው ለዘላለም በሚኖር ነፍስ፣ ዕኩይ እና መልካም ለመምረጥ በሚያስችል ነፃ ፈቃድ ተገንብቶ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ነው" ከሚል አስተሳሰብ ውስጥ ይቀዳል። በክርስትና ውስጥ ያለ ሌላው የግለሰባዊነት ወሳኝ አካል በግለሰብ እና በእግዚአብሔር መካከል ቀጥተኛ እና ግላዊ ግንኙነት አለ የሚለው ሃሳብ ነው። ክርስትና በሥጋ የተገለጠው አምላክ፣ ኢየሱስ ክርስቶስ፣ የሰውን ልጅ ከኃጢአት ለማዳን እና ወደ እግዚአብሔር መለኮታዊ ጸጋ እንደግለሰብ ሆኖ እንዲገባ ለማድረግ ወደ ምድር እንደመጣ ያስተምራል። ክርስቶስ በመስዋዕትነት ሞት እና ትንሳኤ፣ ሰውን ከእግዚአብሔር ጋር አስታረቀ፣ ይህም ግለሰቦች ከማንኛውም ሰው አስታራቂ ነፃ ሆነው ከእግዚያብሔር ጋር ሕብረት እንዲኖራቸው አስችሏል። ይህ በጊዜው ከነበሩት ተዋረዳዊ ሃይማኖታዊ ልምምዶች (Hierarchical religious practices) ፍፁም የተለየ ነው። ምክንያቱም እነዚህ ሃይማኖታዊ ልምምዶች በሰው እና በእግዚያብሄር መካከል አሸማጋይ ወይም አስታራቂ ሆኖ መግባት ያለበት ሌላ አካል መሆን እንዳለበት አጽንኦት የሚሰጡ ነበሩ። የግለሰቡ ሚና ብዙም አስፈላጊ አልነበረም።

ክርስቲያናዊ ግለሰብነት ግለሰቦች እጅግ ላቅ ያለ ሰብዕናን እና ሥነ ምግባርን በሕይወታቸው የመፈለግ ግዴታን ያስቀምጥባቸዋል። ክርስቲያናዊ ግለሰብነት ማለት በዋል ፈሰስ መሆን እና መርህ በሌለው መንገድ እንደልብ መሆን ማለት አይደለም። ከሁሉም በላይ ግን ክርስቲያናዊ ግለሰብነት አንድ ሰው በእዚያብሔር መልክ በመፈጠሩ፣ ግለሰባዊ ክብር እና ዋጋ ያለው በመሆኑ በእርሱ ላይ ያለውን ይህን መለኮታዊ ስጦታ ለማንም ሳያስረክብ እና ሳያስገዛ በተመሳሳይ መልኩ ሌሎች ሰዎች በእርሱ ልክ በእግዚያብሔር አምሳል የተፈጠሩ፣ ግለሰባዊ ክብር እና ዋጋ ያላቸው መሆናቸውን እውቅና የሚሰጥ ነው።

# 2. ቁጣ እና እርቀ

*"ተቆጡ ኀጢአትንም አታድርጉ፤*

*በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት።"*

*ኤፌ 4:26-27*

ቁጣ መልካም (ጽድቅ) ወይም መጥፎ (ኀጢአት) ውጤቶችን ሊያመጣ ይችላል። ውጤቱን የሚወሥነው በቁጣ ውስጥ ስንሆን የምንወስደው እርምጃ ነው። ሰዎች እንደሞኝ ቆጥረው የራሳቸውን ጥቅም በእኛ ኪሳራ ሲያገኙ እንቆጣለን። ሰዎች የሰውን ክበር ሲረግጡ እና አንዳች ያልተገባ ነገር ሲያደርጉ እንቆጣለን። ወይንም ደግሞ ግልፅ የሆነ ጥፋት በምናይበት ጊዜ እንቆጣለን። በፍትሕ መጓደል ላይ እንቆጣለን። ለምን እንቆጣለን? ምክንያቱም ከአፈጣጠራችን ስሜት እና አመክኒዮአዊ በሆነ መንገድ የማሰብ ችሎታ ስላለን ነው። እኩይ ነገር ስናይ ለዛ እኩይ ምግባር ያለን ምላሽ መላው ሁለንተናችንን ያካተተ ነው። አዕምሮአችን ብቻ ሳይሆን ስሜታችንም ይሳተፋል።

እኛ ስሜታዊ ደግሞም ምክንያታዊ ፍጡራን ነን። እኩይን ስንቃወም ስሜታችንም እንደ ሐሳባችን እኩል ድርሻ አለው። አንድ ሰው እኩይ ድርጊትን እያየ ነገር ግን በውስጡ ምንም አይነት ቁጣ የማይቀሰቀስ ከሆነ የ ሰው በቁሙ ሞቷል ማለት ነው። በአካል እና በስሜት "ሙሉ በሙሉ ከሌላው የተነጠለ ሰው ብቻ" በእኩይ ክስተት እና አድርጊት ላይ ምንም ዓይነት ቁጣ ሳይሰማ፣ እንደ ቴያትር ቤት ተመልካች "በእውን እየሆነ ያልን እኩይ ነገር" እንደ ድራማ እግሩን ዘርግቶ መመልከት ይችላል። በሥነ ምግባር የዘቀጠ እና ግድየለሽ ሰው ብቻ ምንም ስሜት ሳይሰማው እኩይ ነገር አይቶ ምላሽ አለመስጠት ይችላል። ማየት ብቻ አይደለም ምንም ጥሩም መጥፎም ስሜት ሳይሰማው እኩይ ድርጊቶችን ስለመፈጸም ሊያስብ ይችላል።

ምንም እንኳን መቆጣት ተገቢ ቢሆንም ብዙ ጊዜ ለብዙ እኩይ ነገሮች መፈጠርም ዋነኛ መንስኤ "ቁጠኝነት" ሆኖ እናገኛለን። ስሜታችን ለግላዊ ፍላጎታችን የተገዛ እና ከምክንያታዊነት የተፋታ ነው። ለተፈፀመብን በደል በከፍተኛ ቁጣ ተሞልተን ምላሽ የምንሰጥ ከሆነ፥ ምላሻችን እጅግ የተጋነነ

እና ከተደረገብን ባለይ የሄደ ነው። በጥንታዊ የማህበረሰብ ሥርዓት ይኖሩ የነበሩ ሰዎችን ከገጠማቸው ተግዳሮት አንዱ በቀል የት ድረስ ይሂድ የሚለውን ለመወሰን፣ ለማስቀመጥ መቸገራቸው ነው። በኋላ ግን በብዙ ባህሎች ውስጥ እንደምንመለከተው አንድ በደል የደረሰበት የአንድ ጎሳ አባል፣ በበደል አድራሹ ላይ “በቁጣ ተነሳስቶ” የከፋ በደል እንዳይፈፅም፣ በሀገር ሽማግሌ አማካኝነት በእርቀ ወይም በካሳ “ተበዳዩ ከቁጣ የሚበርድበትን” መላ አስቀምጠዋል። በጊዜ ሒደት እነዚህ በየባህሉ የነበሩ “በቁጣ የመጣ” ችግርን የመፍቻ ዘዴ፣ ዛሬ በዘመናዊ ማህበረሰብ ውስጥ ወደምናገኘው የሕግ ተቋምነት ተለውጧል። በነዚህም ተቋማት አማካኝነት፣ ማህበረሰብ የተበደለውንም ከቁጣ የሚረግብበት፣ በደል አድራሹም የሚቀጣበት ሥርዓት አበጅቷል። ይህም ማለት ህብረተሰቡ ተጎጂውን የመቆጣጠር እና ጥፋተኛውን የመቅጣት ሚናውን በአግባቡ መወጣት ችሏል ማለት ነው።

ሰዎች በራሳቸው ጉዳይ ላይ “አባቱ ዳኛ ልጁ ቀማኛ” በመሆን በራሳቸው ሚዛን መዝነው ላጠፋው ጥፋት የሚገባው ቅጣት ይህን ያህል ይሁን ብለው በበዳይ ላይ ቢወስኑ፤ ሁሌም ቢሆን የሚወስኑት ውሳኔ ፍትሓዊ እንዳልሆነ በብዞዎች ዘንድ ተቀባይነት አለው። ሰው አድሎአዊ ፍጡር እንደሆነ ስምምነት ላይ ደርሰናል። ሁሉም ሕብረተሰብ በዜጎች መካከል የሚነሱ ክርክሮችን እና አንዱ በሌላው ላይ የሚያደርሰውን ጉዳት ሚዛናዊ በሆነ መንገድ ከማየት ረገድ፣ በግጭት ውስጥ ያልተሳተፉ ሰዎች፣ በግጭቱ ውስጥ ከተሳተፉት ሰዎች በተሻለ መልኩ ፍትሃዊ ሆነው ማየት ይችላሉ የሚለውን መርህ ይቀበላል። በዚህ መንገድ እና ስምምነት ምክንያት የቁጣን አሉታዊ ተፅእኖዎች ለመቀነስ ማሕበራዊ ዘዴን ማበጀት ችለናል። ፈጥረናል። ይሁን እንጂ አሁንም ኀጢአትን ሳንሠራ በተፈፀመው በደል ላይ “መቆጣት” ን በተመለከተ ችግር እንደገጠመን አለ።

በምንናደድበት ጊዜ፣ ውስጣችን በቁጣ ሲሞላ ኀጢአት የምንሠራበት አንዱ ምክንያት፣ ትኩረታችን በራሳችን ስሜትና ጉዳት ላይ ብቻ ስለምናደርግ ነው። የእኛን ጉዳት አግዝፈን እናያለን። ሌሎች ላይ ያደረግነው ነገር ፍጹም አይታየንም። በቁጣ ተገፋፍተን የምናደርገው ነገር የሚያመጣው መዘዝ የከፋ መሆኑ ስለማይታየን ላደረጉብን በደል ሁለት እጥፍ አድርገን በቀሉን እንመለሳለን፤ እንከፍላለን። ይህ ቁጣ በቀልን ይወልዳል። በቀል ደግሞ በውስጣችን ያለውን የእግዚአብሔርን መልክ፣ ከፍጥረታችን ያገኘነውን የፍትሕ እሳቤ ከውስጣችን በማበላሸት፣ ፍትሕን

በራሳችን እጆች እንድናስፈፅም የሚያደርግ የራስ ወዳድነት ውጤት ነው። ሁሉም የማህበረሰብ ሕጎች እና ደንቦች ከጊዜ ወደጊዜ እየተሻሻሉ እና እየደረጁ የመጡበት ዋና ምክንያት፣ ይህን ግላዊ፣ ራስ ተኮር የሆነን ቂጠኝነት በመቆጣጠር ቢያንስ ሁሉም የሚስማማበት የፍትሕ ከባቢ ለመፍጠር ነው።

ሁለተኛው አግባብ የሌለው የቁጣ ፍሬ ጥላቻ ነው፡፡ የቁጣ አሉታዊ ውጤት ጥላቻ ነው። ጥላቻ ስር የሰደደ የቂጠኝነት ውጤት ነው። ጥላቻ የሚከሰተው ቁጣ ረጅም ጊዜ ሲቆይ ነው። በጥላቻ ውስጥ ምክንያታዊነት ያለው እና ምክንያታዊነት የሌለው አመለካከት የተደበላለቀ ነው። ጥላቻ የተሳሳተ የምክንያትና የስሜት ውህደትን ያካትታል። ስሜት ብዙ ጊዜ እንደጤዛ ተኖ የሚጠፋ ነገር ነው። እናም ይህ የስሜት ጊዜያዊነት ባሕሪ መላበስ፤ አንዳንድ ጊዜ ስለምንወስናቸው ውሳኔዎች እርግጠኛ እንዳንሆን ያደርገናል። ሆኖም ግን ቁጣ ቶሎ የሚጠፋ እና የሚተን መሆኑ እጅግ መልካም ነው።

የተደረገብንን በደል ለረጅም ሰዓት እና ቀናት እያብሰለሰልን የምንኖር ከሆነ በውስጣችን ያለ የቁጣ ስሜት እያየለ በመሄድ በበደለን ሰው ላይ ጥላቻ እንድናዳብር ያደርገናል። ይህንንም ታሳቢ በማድረግ ቅዱስ ጳውሎስ፣ መሽቶ እስኪነጋ፣ እስከ ቀኑ ፍጻሜ ድረስ፣ እንደተቆጣን እና ቁጣ በውስጣችን እንደ ነደደ እንዳይቆይ በመልዕክቱ ይመክረናል። ለዚህም ነው በመግቢያችን ላይ ባነበብነው የመፅሐፍ ቅዱስ ንባባችን ውስጥ ቅዱስ ጳውሎስ “ተቆጡ ኀጢአትንም አትሥሩ” የሚለውን ምክር ያቀመጠው። ቀጥሎ ደግሞ “በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ” የሚለውን ምክር አክሎ የነገረን።

አንዱ ህፃን ልጅ የመሆን ትልቁ ፀጋ እና በረከት የማስታወስ አቅማቸዉ አጭር መሆን ነው። ይህም የማስታወስ አቅማቸው አጭር መሆን ልጆች ቂም እንዳይዙ እና በደል እንዳይቆጥሩ እረድቷቸዋል። አዋቂዎች በልጆች ግጭቶች ውስጥ ካልተሳተፉ፣ ብዙውን ጊዜ “በቁጣችሁ መሃል ፀሀይ አይግባ የሚለው” ቃል ሙሉ በሙሉ ተተግብሮ የምናየው በልጆች ውስጥ ነው። የእለቱ ቀን ሳያልፍ ምንም እንዳልተፈጠረ ከተጋጨት ሰው ጋር በሰላም እና በደስታ መኖር ይጀምራሉ።

አዋቂዎች እንደ ልጆች አይደሉም። በተለይም ሁሉም ሀገሮች ወይም ጎሳዎች በሌላው ሀገርና ወይም በሌላ ጎሳ የተደረገባቸውን በደል በቀላሉ አይረሱም፥ “ሁሉንም አይነት የሰው ልጆች ግንኙነት  የሚያበላሽ ቁጣ” ለረዥም ጊዜ አምቀው ለልጅ ልጅ ያስተላልፋሉ። የጋራ የበደል ትውስታዎች በቀላሉ የሚረሱ

አይደሉም። ለምሳሌ በአንድ ወቅት እንግሊዝ በአየርላንድ ህዝቦች ላይ ለፈጸመችው በደል ካሳ የሚሆን ነገር ብታደርግም፣ አሁንም ያ የበደል ትውስታ በአይርላንድ ህዝቦች ውስጥ የጥላቻና የቁጣ ምንጭ ነው። በደቡባዊ የናይትድ ስቴትስ አንዳንድ ሰዎች በእርስ በርስ ጦርነት ወቅት የደረሰውን ጉዳት አሁንም ድረስ በቁጭት ያስታውሳሉ።

በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ ከሆነው ገጽታ አንዱ የተሸነፉ ሽንፈታቸውን ለረጅም ጊዜ ከአሸናፊዎች በላይ ማስታወሳቸው ነው። በሐሳብ ደረጃ እና ጥቅም የነበረው ነገር አሸናፊዎች ድላቸውን የማስታወስ ግዴታ እንዳለባቸው ቢያውቁ እና ተሸናፊዎች ደግሞ ያለፈውን ጊዜ ረስተው፣ የሽንፈት ታሪካቸውን ዘንግተው፤ ቁጣ ከውስጣቸው ማጥፋት ይጠበቅባቸው ነበር።

## 1.

“ተቆጡ ኀጢአትንም አትሥሩ” የሚለው ምክር ተፅፎ እንድናገኝ ዋነኛ ምክንያት የሆነውን መጽሐፍ ቅዱሳዊውን ንፀረተ ዓለምን፣ እጅግ ተጋነው እና ምክንያታዊነት የተላበሱ መስለው ከሚገኙ በሕይወት ትግል ውስጥ ስናልፍ የምናሳየውን ስሜታዊነት እና ስሜታዊ ምላሽን በራሱ እንደ እኩይ ከሚቆጥሩ ከሁሉም የሥነ ምግባር አስተሳሰብ ወይም ፍልስፍና መነጠል መቻል አለብን። መፅሐፍ ቅዱስ የማያስተምረውን የሚያስተምር፣ የትኛውም ከፍ ያለ እና ምክንያታዊነትን የተላበሰ የሚመስል አስተምህሮ ከእኛ አካባቢ ማራቅ፣ ማውጣት ግዴታችን ነው። ለምሳሌ ከመጽሐፍ ቅዱስ አስተምህሮ በተቃራኒ ከቆሙ አስተሳሰብና ፍልስፍናዎች መካከል አንደኛው በቁጣ ውስጥ እኩይ እንዳትፈፅሙ ከተፈለገ አንደኛውን ‘ኀጢአትን እንዳታደርጉ አትቆጡ’ የሚለው ይገኝበታል። የዚህ አስተሳሰብ መርህና አቋም ከሁሉም የሕይወት ውዝግቦች መራቅ እና በሕይወት ውስጥ ለብዙ ነገር ካለን ጥልቅ መሻት ራሳችንን መገደብ አለብን ብሎ ያስተምራል። በአጭሩ በዉስጣችን ቁጣን ከሚቀሰቅስ ማንኛውም ነገር መነጠል አለብን ይላል። ለዚህ አንዱ ሁነኛ ምሳሌ ከሁሉም ሞኞቶች እና በመኖር ውስጥ ለነገሮች ደመ ሞቃት ከሚያደርጉ ስሜቶች የመራቅ ሥነ ምግባር የሚያራምደው የስቶይክ ፍልስፍና አስተሳሰብ ነው። የዚህ አስተሳሰብ አስቸጋሪነት ወይም ቅቡልነት እንዲጎድለው የሚያደርገው የሰው ልጆች ከፍጥረታችን ለነገሮች ደመ ሞቃት ከሚያደርጉ ስሜቶች እና ፈቃድ ጋር አብሮ በአመክኒዮም የሚኖር አዕምሮ ይዘን ከመፈጠራችን ሐቅ ጋር ስለሚጋጭ ነው። እናም በሕይወት

እስካለን ድረስ ወይም በዚህ ምድር ስንኖር እንደ አንድ የመኖር ከፍታ እና ዝቅታ ተካፋዮች ከማይቀረው የሕይወት አለመግባባቶች እና ውዝግቦች ውስጥ እጃችንን እናስገባለን።

ከእኛ የሚጠበቀው ነገሮችን በኋላፊነት ለማድረግ መጣር ብቻ ነው። የተሰማንን ስሜት ወዲያውኑ እንዳናሳይ እና ቁጣችንን በውስጣችን እንድንውጥ መጫን እና እንዲህ አይነት ነገርን ማጣጣል ለሕይወት ያለንን ደመ ሞቃት የሆነ ፍላጎት ያጠፋል። ስሜትን ከሕይወት ውስጥ ችላ ማለት ጥሩም መጥፎም ስሜት የሌለን ደመቅዝቃዛ ያደርገናል። ከሕይወት ውስጥ ካለ ችግር መራቅ ማለት አንዳች የተሳሳተ ነገር ላለማድረግ የምናደርገው ጥንቃቄ የተሞላ እርምጃ ማለት አይደለም። ይልቁንም ፍትሕ ሲጓደል ልንቆጣ ይገባል። ነገር ግን ይህን ስናደርግ እኛው ራሳችን ሌላ ሐጢያት ሳንሰራ መሆን አለበት። ለክፋ ክፋ ሳንመልስ እንዴት ግን በእኩይ ሥራ ላይ ቁጣችንን እንገልፃለን የሚለውን መማር አለብን።

“አንድ ሰው በአንተ ላይ ቢቆጣ” ይላል ታላቁ የኢስቶይክ ፈላስፋ ኢፒክቴተስ “ወይም ስለአንተ ክፍ ነገር ቢናገር ልታስታውሰው የሚገባ አንድ ነገር፣ የሚያደርገውን እና የሚናገረውን ነገር፤ ማድረግ እና መናገር ከእርሱ የሚጠበቅ ግዴታ መሆኑ አውቀህ ሰውዬው ያን ግዴታውን እየተወጣ እንደሆነ አምነህ መቀበል አለብህ…ከዚህ ዕሳቤ በመነሳት ወይም ይህን መርህ የምትከተል ከሆነ፣ እንደዚህ አይነት ሰዎችን ያለ ስሜት መረበሽ ለመታገስ አይከብድህም” በማለት ያስተምራል። እንዲህ አይነት ሁኔታዎች በሚፈጠሩበት ጊዜ ሁሉ ‘ለእርሱ የመሰለው እንዲህ ነው’ በማለት ታልፈዋለህ “ይለናል።

ሆኖም ግን እንዲህ አይነት ምክር እጅግ ከሰው አቅም በላይ በሆነ እና ህልውናን አደጋ ላይ በሚጥል ሁኔታ፣ ለምሳሌ በጀርመን ናዚህ ማጎሪያ ካምፕ ውስጥ ላለ ሰው መምከር ምንም አይነት ትርጉም አይሰጥም። በሌላ ጎኑ ግን ሰዎች በትላልቅም ይሁን በጥቃቅን ነገሮች፣ በየጊዜው ከተከሰተ ክስተት ተነስተው በሚጋጩበት እና አንዱ በሌላው ላይ በሚቆጣበት ጊዜ፣ እንዲህ አይነቱ ምክር እጅግ ጠቃሚ ይሆናል። ስሜትን ለማርግብ እና ነገሩን ለጥጦ ከማየት ይጠብቃል። በእንደዚህ አይነት ሁኔታ ውስጥ ስንሆን እኔስ በእርሱ ቦታ ብሆን የማደርገው ነገር ምንድን ነበር ብሎ ራስን በሌላው ሰው ጫማ ውስጥ ማስቀመጥ የሌላውን ሰው ችግር ከማጥላላት ይጠብቃል። የተፈጠረውንም ግጭት እና አለመግባባት በቀላሉ መፍታት ይችላል። ነገር ግን ተጨባጭ የሆነ የአንድ ሰው ወይም ማህበረሰብን ህልውና አደጋ ላይ የሚጥል እኩይ ነገር ሲደፈረግ፣ “እኔም በእርሱ ቦታ ብሆን

የማደርገው ይህን ነው"፣ በሚል ለዘብተኝነት እኩይ አድራጊውን በቀና ለመመልከት መጣር በራሱ እኩይ የሆነ ጠባይ ነው። በሞራል መመዘኛዎች ተቀባይነት የሌለው አካሄድ ነው። በተጨባጭ ለተፈፀመ እኩይ ተግባር ትክክለኛው ምላሽ ቁጣ ነው።

በቁጣ ውስጥ ለምንሰራው ሀጥያት መድሀኒቱ "ከዚህ በኋላ በእንደዚህ ዓይነት ነገር ውስጥ እራሴን አልከትም" በማለት፣ በመኖር ውስጥ የሞት እና የህይወት ጉዳይ ከሆኑ ነገሮች ራሳችንን በመነጠል፥ በማራቅ አይደለም። ቁጣችን ገንፍሎ ከመስመር እስኪያልፍ ድረስ በማቆየት ምክንያት የምንሰራውን ሐጢያት የማሸነፊያው መንገድ፤ ስሜታችንን በማመቅ ልንጋፈጠው ከሚገባ የሕይወት ጉዳይ በመራቅ አይደለም። ከዚህ ይልቅ ማድረግ ያለብን በቁጣችን ውስጥ ካስቆጣን ነገር በላይ ሁኔታውን በማጋነን፣ "ተቆጡ ነገር ግን ኀጢያት አታድርጉ" የሚለውን እውነት የሚንድ ቁጣ ልንቆጣ እንደምንችል፣ ቁጣችን ከተገቢው መጠን አልፎ ሀጢያት ሆኖ ወደሚቆጠርበት ደረጃ እንደሚደርስ እና ቁጣችን ውስጥ ዕብሪት እንደማይጠፋ በመገንዘብ፤ ጥፋቱን የሚቀበልና ንስሃ የሚገባ የትሕትና ባሕርይ ማዳበር አለብን።

በሕይወት ትግል ውስጥ ያለብንን ሐላፊነት፣ ችግር በመፍራት ምክንያት ልንርቅ አንችልም። በእንዲዚህ አይነት የሕይወት ትግል ውስጥ ከራስ ጥቅም የፀዳ፣ በተጨባጭ መረጃዎች ላይ የተመሠረተ እና አድሎአዊነት የሌለበት አቋም ለመያዝ የሚደረግ የትኛውም ጥረት ኀላፊነትን ወደ መሸሽ ይወስደናል። ለራሳችን ፍላጎትና ስሜት ቅድሚያ እንደምንሰጥ ሳይታለም የተፈታ ነው። ነገር ግን ለራሴ ላደላ እችላለሁ በሚል ሥጋት ስለሁኔታው የተሰማንን ጉዳይ ከመግለጥ ወደ ኋላ ማለት የለብንም። ከዚህ ይልቅ ስሜታችን ሲጎዳና የሚያስቆጣ ነገር ሲገጥመን መቆጣታችን ተገቢ መሆኑን አውቀን፣ ቁጣችን ከገደብ እንዳያልፍ መጠንቀቅ፤ አሊያም ደግሞ ቁጣችን ከገደብ አልፎ ከሆነ ቶሎ ለማስተካከል ፈቃደኛ መሆን አለብን።

ሌላው ወደ ቁጣ የሚመሩ ወይም ቁጣ የሚቀሰቀሱ ነገሮች በሚኖሩበት ጊዜ፣ ያንን ቁጣ የሞላበት ሁኔታ በፈጠረው ክስተት ውስጥ በጉዳዩ ላይ እኛም እንዳለንበት፣ የራሳችንን አስተዋጽኦ አውቀንም ይሁን ሳናውቅ ያበረከትን፤ ሌላኛው አካል አርፈን ከተቀመጥንበት እንዲሁ ከመሬት ተነስቶ የሚያስቆጣ ነገር ውስጥ እንዳልከተተን ያለውን እውነታ በአዕምሮአችን መያዝ አለብን። እንደዛ ሲሆን ደግሞ በበደሉን ወይም ባስቆጡን ሰዎች ላይ ያለን ምላሽ እኛን ንፁህ ጠላታችን ግን ፍፁም አጥፊ አድርገን እንዳናስብ ይጠብቀናል። የበደሉንን ሰዎች ይቅር የምንልበት

መሠረት ያለው ፈላስፋው ኢፒክተተስ እንደሚለው “እነርሱም ማድረግ ያለባቸውን ነው ያደረጉት በቃ ስሜታዊ እና ደካሞች በመሆናቸው ነው ያደረጉት” ከሚል የአስተሳሰብ መርህ ውስጥ በመነሳት ሳይሆን፣ ነገር ግን ሁለታችንም የተቆጣነው “እኛ እና ያስቆጣን ሌላኛው አካል” ፤ ቁጣ ለቀሰቀሰው ነገር እኩል በደለኞች እንደሆንን እውቅና በመስጠት ውስጥ ነው።

በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሜሪካ፣ ከጃፓን ኢምፓየር እና ከጀርመን ናዚ ጋር ጦርነት ውስጥ በገባችበት የመጀመሪያዎቹ አመታት አካባቢ አንዳንድ ሰዎች፣ ለክርስትና ባዕድ የሆነ የፍልስፍና ጽንሰ ሃሳብን ከክርስትና የይቅርታ ሃሳብ ጋር አሳክረው፤ ጦርነት ውስጥ ከመግባት የሰላም መልዕክተኛ ብቻ መሆን አለብን ብለው ይናገሩ ነበር። “ክፉ ላለመሥራት ከቁጣ እና ግጭት ሽሽ” የሚለውን የኤፒዩክቲተስን ፍልስፍና አስተምህሮ፣ ይቅርታ ማድረግ ከሚለው የክርስትና አስተሳሰብ ጋር አንድ አይነት አድርገው በመቀላለቀል የሰሚዎቻቸውን ጆሮ ለመሳብ ይሞክሩ ነበር። በዚህ ውዥንብር ውስጥ የነበሩ ደግሞ እጅግ ብዙ ብሩህ አዕምሮ የነበራቸው ሰዎች ነበሩበት። አንድም እኛ እንደዚህ ስለመሰለን ወይም እኛ ከቆምንበት ቦታ ሆነን ስላየነው ነው እንጂ ነገሩ እኛ እንዳጋነነው አይደለም በማለት ከባዱን ነገር ቀላል አድርገው ያቀርቡ ነበር። ቀጠል አድርገውም እኛስ ማን ነን? ከእኛ ሐጢያት የሌለበት ናዚ ላይ ድንጋይ ይወርውር በማለት የናዚ ወንጀሎች ለማቃለልም ሞክረዋል። እንደውም አንዳንዶቹ እኛው ራሳችን በእኩይ ምግባር የጨቀየን ስለሆን ሌላኛውን እኩይ ሥርዓት ለመቃወም መብት የለንም የሚል ሃሳብ ይሰነዝሩ ነበር።

በራሳቸው ጉድለት ቢኖርባቸውም፣ በሃሳብና በድርጊታቸው ውስጥ እንከን ባይጠፋም፣ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ያለ መልካም ነገር ሁሉ የተገኘው ኢፍትሃዊ ድርጊት ለመወጋት ፈቃደኛ በሆኑ ሰዎች መሆኑን እንዳናይ እና እንዳንቀበል ፤ስሜት አልባ እና እጅግ የተለጠጠ የሃሳባዊነት ጽንሰ ሃሳብ ጋሬጣ አስቀጧል። በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ ምንም እንኳን የራሳቸው ጉድለት እና ጥፋት ቢኖርባቸውም፣ ከቁጣ እና በቀል የራቁ ሰዎች “አይን ያፈጠጠ፣ እና ጥርስ ያገጠጠ”፣ በእቅድ እና በዓላማ የሚሰራ፣ በተለይም በሰው ልጆች ላይ ዘርን እና ሃይማኖትን የመሳሰሉ የማንነት መገለጫዎችን እንደ ጠላት በመቁጠር የሚፈፀም ወንጀል መኖር የለበትም የሚለውን በማመናቸው፤ እንደ ናዚ አይነት ግፈኛ ሥርዓቶች ላይ ከፍተኛ የሆነ ቁጣ አሰምተዋል። ታግለውም አሸንፈዋል። በጣም ሃሳባዊ በመሆን በሰላም እና ጽድቅ ፈላጊነት ካባ በመደበቅ ሃላፊነትን ከመውሰድ ለማምለጥ ስንሞክር፣

ልብ ብለን ልናስታውሰው የሚገባ ነገር፣ በፍትሐ መጓደል ላይ መቆጣት ፅድቅ መሆኑን እና “ያ ግፍ ላይ የምናሰማው ቁጣ”ን ጠላቶቻችንን ለመፋለም እንደ ወኔ መቀስቀሻ ማዋል ተገቢ መሆኑን ነው።

ጠላታችንን ካሸነፍን እና የደቀነብን የህልውና አደጋ ከጠፋ በኋላ ወዲያውኑ የችግሩ ሌላኛውን ክፍል ላይ ማተኮር አለብን። ተደቅኖብን የነበረውን የህልውና ሥጋት ካስወገድን በኋላ፣ የእኛንም ጉድለት እና ሀጢያት ማየት፣ ለዛም እውቅና መስጠት እና ድሎቻችንን ተከትለው ከሚመጡ ትምክተኝነት እና በቀለኝነት ራሳችንን መገደብ ተገቢ ነው። ነገር ግን አሸናፊዎች ብዙውን ጊዜ መልካም ተግባራቸው ውስጥ ያለውን እኩይነት ሲገነዘቡ አይታዩም! በጠላቶቻቸው ውስጥ ያለው እኩይነት እነርሱም ውስጥ እንዳለ እና እነርሱም ሊፈቱት የሞከሩት ችግር አካል ሊሆኑ እንደሚችሉ ማመን አይፈልጉም! አሸናፊዎች እኩይን በመዋጋት መልካም ነገራቸው ውስጥ የተሸሸገውን ክፋት ሲያስተውሉ አናይም! ከሚዋጉት እኩይ ጋር እነርሱም ውስጥ ያው ክፋት እንዳለ በመቀበል የጋራ በደለኝነትን አይካፈሉም! በድላቸው ውስጥ ትምክህት፣ በቁጣቸው ውስጥ በቀለኝነት እንዳለ አይገነዘቡም! ቁጣ እንዴት ጨካኝ እና በቀለኛ እንዳደረጋቸው ማስተዋል ይሳናቸዋል! አሁን ሁሉን አድራጊ እና ፈጣሪ እንደሆኑ የሚሰማቸው ስሜት ከድሉ በፊት እንዳልነበረ እንደሄት ፈጥነው እንደሚረሱ እናያለን!በእኩይ ላይ በምንቀዳጀው ድል እኛኑ እብሪት ውስጥ ይከተናል! ቁጣችን በይቅርታ ስለማይለወጥ እኩይ የተዋጋንበትን መሳሪያ እኩይ መፈፀሚያ እናደርገዋለን!

ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል በኋላ አሸናፊ ሐገሮች ሰላም ወዳድ ስለሆኑ ሐገሮች እና ሰላም ወዳድ ስላልሆኑ ሐገሮች እንዴት መናገር እንደጀመሩ መመልከት እንችላለን!የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊ አገሮች ብዙ ጊዜ “ሰላም ወዳድ” ስለሆኑ ሐገሮች እና የዓለምን ሰላም ስላደፈረሱ ሐገሮች የሚነዙት ፕሮፓጋንዳ ማየት መልካም ነው። ብዙ ጊዜ አሸናፊ ሐገሮች ራሳቸውን ሰላምና ነጻነት ወዳጅ ሐገር አድርገው ይለፍፋሉ። በተቃራኒው ደግሞ ጠላቶቻቸው ሙሉ በሙሉ ለጦርነቱ ተጠያቂ አድርገው ያቀርቡ ነበር። ይሄ የጥቁር እና ነጭ ትንታኔ ትክክል የሆነ ትንታኔ አልነበረም! አሸናፊዎቹ አገሮች ሁልጊዜ ሰላም ወዳድ አልነበሩም። የራሳቸው ፍላጎትና አጀንዳ ነበራቸው።ግባቸውን ለማሳካት ያልተመጣጠነ ኃይልን ተጠቅመዋል። የበቀል ድርጊት ፈፅመዋል። አንዳንድ ሁኔታዎችን በጥልቀት ካየን አሸናፊ ሐገሮች ራሳቸው ለጦርነቱ መቀስቀስ ዋነኛ ተዋንያን ነበሩ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሸናፊዎቹ ሐገራት፣ ለዘለቄታዊ ሰላም የሚጠቅም በጋራ ጥቅም ላይ የተመሠረተ እውነተኛ ስምምነት ላይ መድረስ እንዲችሉ፣ ከድል ስሜት ስካር እና እብሪት ራሳቸውን መገደብ እንዳለባቸው ያለውን ተጨባጭ ሀቅ ለመሸሸግ ሲጥሩ ማየት ቀላል ነገር ነበር። ነገር ግን ከዚህ ይልቅ ለተቀረው ዓለም ለማሳየት የሞከሩት የዓለም ሰላም የበጠበጠው እኩይ ኋይል ከተሸነፈ እና ዳግም ተመሳሳይ ጥፋት የሚያደርስበት ኋይሉ ከተዳከመ ዳግም ዓለምን ለጦርነት ሥጋት የሚዳርጋት አይኖርም የሚል ነው። ጦርነት ከሚያመጣው አሳዛኝ የቁጣ ፍሬ መካከል አንዱ፣ እኛ የምንወስደው ጉድለት ያለበት አንፃራዊ የሆነ የፍትሕ እርምጃ ፍፁም እና እንከን አልባ ከሆነው የፍትሕ ጽንሰ ሐሳብ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ፣ አንድ አይነት አድርጎ ማቅረብ ነው። የእኛ ድርጊት ንፁህ ጠላቶቻችንን ደግሞ ከተፈጥሮአዊ እኩይ የሆኑ አድርጎ የመመልከት ዝንባሌ በጦርነት ምክንያት ከሚፈጠር ቁጣ የሚወለድ አደገኛ ውጤት መሐል ዋናው ሲሆን ይህም ሰዎች ትልቁን ምስል እንዳይመለከቱ አይናቸው ላይ ቀርፌት ያስቀምጣል። እውራን እንዲሆኑ ያደርጋል። በዚህ አይነት ቁጣ ወቅት ያለ እውርነት ነገን አሻግሮ ለማየት ይከለክላል!

ቁጣ የሚያመጣውን የእውርነት አሉታዊ ተጽእኖ በግለሰቦች መካከል በሚከሰቱ ግላዊ በሆኑ ግጭቶች ውስጥ ማየት እንችላለን። በቁጣ መሞላት የሚወልደው እውርነት እና ቁጣ የሚያመጣው የእውርነት መዘዝ አደጋ በሰው ልጆች የጋራ አኗኗር ውስጥ ባሉ የቡድን ግጭቶች መካከል የበለጠ ጎልቶ ይታያል። አንደኛው ምክንያት በቡድኖች፣ በጎሳዎች እና በሐገሮች መካከል የሚነሱ አለመግባባቶች እጅግ የከፋ የሚሆኑት በመካከላቸው የተፈጠረውን ችግር ለመፍታት ምንም ዓይነት አድልዎ የማያደርግ ኋይል አለመኖሩ ሲሆን፣ ይህ ሁኔታ እስከ ዓለም ፍጻሜ ሊቀጥል ይችላል። በዚህም ምክንያት ቡድኖች፣ ጎሳዎች እና ሐገሮች በራሳቸው ጉዳይ ፈራጅ ራሳቸው ይሆናሉ። በተሸናፊው ወገን ውስጥ ለሚጠነሰሰው የበቀል ስሜት ዋነኛ ምክንያት እና ምንጭ፤ አሸናፊው ወገን የሚወስደው እርምጃ በሙሉ ፍትሓዊ እና ተገቢ እንደሆነ ለማሳየት የሚያደርገው ድርጊት ነው። ይህ የሆነበት ምክንያት ለተሸናፊዎች እንጂ፣ ፍትሕ ፍትሕነቷ አብቅቶ የአሸናፊውን ኋይል ፍላጎት ለማርካት ጥቅም ላይ እየዋለች እንደሆነ ለአሸናፊዎች ሊታያቸው ስለማይችል ነው። የተሸነፋ ወይም የተወረሩ ቡድኖች፣ አሸናፊዎቹ የሚያነሷቸው እጅግ የተጋነኑ ወይም ውሸት የሞላባቸውን የይገባኛል ጥያቄዎች፣ ወይም በፍትሕ ስም የሚወስዷቸው እርምጃዎችን ፍትሓዊነት ከተጠራጠሩ ወይም በድርጊቱ ላይ ጥያቄ ካነሱ “ይህ ጥርጣሬ እና ጥያቄ በራሱ ተሸናፊዎቹ

እጅግ መጥፎ እና ተፈጥሮአዊ እኩይነት አለባቸው” ለሚለው የአሸናፊዎች ክስ እንደ ማረጋገጫ ሆኖ በአሸናፊዎች ይቀርባል።

ማንኛውም አስተዋይ ተመልካች በሁለተኛው የዓለም ጦርነት መጠናቀቅ ጋር ተያይዞ የሆነውን ሊገነዘብ እንደሚችለው፣ የአሸናፊ ሐገሮች የአንደኛው የሃይል ጥማት፣ የሌላኛው አሸናፊ ሐገር ክብር እና ጫንቀት፣ የሌላኛው አሸናፊ ሐገር ትምክህት፣ “የተሸነፈውን ህዝብ ፍትሃዊ ቅጣት ለመቅጣት እና ወደፊት ሌላ ጥቃት እንዳይፈፅም ለመከላከል” በሚል ሽፋን በተሸናፊዎች ላይ ለተወሰደዱ አግባብ የሌላቸው እርምጃዎች ከበስተጀርባ የነበረ እውነተኛ ገፄ ምክንያት ነበር። ክብር፣ ጥቅም እና ሃይል ፍትሕን የሚጋርዱ መሳሪያዎች ናቸው። ድል አድራጊዎቹ እና ራሳቸው ለራሳቸው ጉዳይ ዳኞች የሆኑት፣ በታላቅ ታሪካዊ ሙግት ውስጥ የራሳቸው ጥቅም እና ፍላጎት ያላቸው አካላት ነበሩ፡፡ ወገንተኝነት እና የራስ ጥቅም ለማስከበር እንዳልሆነ በመለፈፍ፣ ራሳቸውን የመለኮታዊ ፍርድ አስፈጻሚ፣ የፍትሕ መልክተኛ አድርገው በፍርድ ወንበር ላይ ቁጬ ብለው ነበር። ለጥቅማቸው የሚሆነውን ነገር እያደረጉ ነገር ግን ግልፅነት ያለበት እና ፍትሃዊ የሆነ ፍርድ እየሰጡ እንደሆነ ለማሳየት ይጥራሉ። “አለቆችንም እንዳልነበሩ፥ የምድርንም ፈራጆች እንደ ከንቱ ነገር የሚያደርጋቸው እርሱ ነው።” በሚለው መለኮታዊ ፍርድ አለማመናቸው በበረታ መጠን እግሮቻቸውን በእግዚያብሔር ቦታ የማስቀመጥ፣ በዚህ አይነት ወጥመድ ውስጥ የመውደቅ እድላቸው እየበዛ፣ የፍትሕ ሚዛን እኛ ነን ወደማለት ይመጣሉ።

ሌላው ቡድኖች፣ ጎሳዎች እና ሐገሮች በፈፀሙት ወንጀል ወይም በጣሱት ሕግ ምክንያት፣ አሸናፊው ወገን ፍርድ በሚያስፈፅምበት ወይም ሕግ በሚያስከብርበት ወቅት፣ ያልተገባ እና እጅግ የተጋነነ ቅጣት በመፈፀም ሐጢያት ውስጥ የሚወድቅበት ምክንያት፣ በተሸናፊው ወገን ያሉ ሰዎች የትኛዎቹ በተደረገው ወንጀል ውስጥ በቀጥታ በመሳተፍ ጥፋተኛ ናቸው፣ የትኛዎቹ ግለሰቦች ግን ስላልተሳተፉ ንፁህ ናቸው ብሎ በመበየን ሂደት ውስጥ ያለው ውስብስብ ችግር ነው። ማንም ሰው ሊክደው የማይችለው እውነት፣ አንድ ሐገር ወይም ቡድን ወይም ጎሳ አሸባሪ እና ወራሪ ወደ መሆን መበስበስ ውስጥ ሲገባ፣ የዚህ ችግር ምንጬ በከፊል በዛ ሐገር ውስጥ ያሉ ብዙ ሰዎች፣ ምንም እንኳን በሐገራቸው፣ በቡድናቸው ወይም በጎሳቸው ባሉ ሰዎች እየተፈፀመ ባለው እኩይ ምግባር ውስጥ ቀጥተኛ ተሳታፊ ባይሆኑም፣ የዜግነት የሞራል ሐላፊነታቸውን መወጣት ባለመቻላቸው ምክንያት ነው። ይህን በናዚ የአገዛዝ ዘመን ውስጥ በነበረችው

ጀርመን ውስጥ በናዚ ወንጀል ያልተሳተፉ ነገር ግን ተው ማለት ያልደፈሩ ብዙ ሰዎች በዛ ዝምታቸው ምክንያት ቀጥሎ የመጣውን አይተዋል። በአንድ ሐገር ውስጥ የሚፈፀም የእኩይ ምግባር ተፅእኖ ጤነኛ የሆነውን የሀገሪቱን ነገሮች እና ሕይወት ሁሉ እንደሚነካ እና ማንም ከእኩይ ድርጊት ተፅዕኖ እንደማያመልጥ መረዳት ተገቢ ነው።

ነገር ግን በሌላ ጎኑ ቁጥራቸው እጅግ ጥቂት ቢሆንም፣ በእንደዚህ ዓይነት ሕዝብ ውስጥ ሁል ጊዜ ክፋትን የሚዋጉ ሰዎች አሉ። እንደውም አንዳንድ ጊዜ ውጊያችን ፍትሓዊ ነው ብለው ከሚያምኑ እና ግፍ ከተፈፀመባቸው ሕዝቦች በላይ በገዛ ሐገራቸው ወይም ቡድናቸው አማካኝነት የሚፈፀመውን እኩይነት በጀግንነት የሚጋፈጡ ሰዎች አሉ። ከእነዚህ ነገሮች ውስብስብነት በተጨማሪ፣ በግልፅ ጥፋት በፈፀሙ፣ በእኩይ ምግባር ውስጥ በተሳተፉ እና ግን ደግሞ በግልፅ ይደረግ የነበረውን ወንጀል ይቃወሙ በነበሩ መሐል፣ ጥፋተኛ እና ንፁህ ብሎ ደረጃ የማውጣት ማብቂያ የሌለው አስቸጋሪ ሂደት፣ በአሸናፊ ወገኖች የሚደረገው ንፁን ከቆሻሻ ሳይለዩ ለመበቀል ያለው ፍላጎት ነገሩን የተምታታ እንዲሆን ያደርጋል። ምንም አይነት አድሎ እና ለራስ ጥቅም ብቻ መቆም የበቀል ፍላጎት በሌለበት ሁኔታ እንኳን፣ በአንድ ቡድን ወይም ሐገር የተፈፀመን ጥፋት በመቅጣት ሒደት ውስጥ ንፁኃንን የጥፋቱ እና ቅጣቱ ሰለባ ይሆናሉ።

ራሳቸውን በፍርድ ሚዛን ላይ ያስቀመጡ አሸናፊ ሐገሮች ወይም ቡድኖች፣ ተሸናፊው ሐገር ላይ በሚያስተላልፉት ፍርድ ወይም ቅጣት በሌላው ዳፋ አሳራቸውን ለሚበሉት ወገኖች ርህራሄ ሊኖራቸው ይገባ ነበር። ብዙ ጊዜ ግን የሚሆነው አሸናፊዎች ከአጥፊው ወገን ያሉ ሰዎች የጥፋተኝነት መጠን የተለያየ እንደሆነ እና ይህንንም የጥፋተኝነት ደረጃ መቀበል ተገቢ እንደሆነ እውቅና አይሰጡም። ጠላት ብለው የፈረጁት አካል ወይም ጥፋት የፈፀመውን ወገን ሕዝቦች ሙሉ በሙሉ ክፉ እና በሁሉም መንገድ የተገለጠ አረመኔ ናቸው የሚል አቋም ይይዛሉ። ቁጣ ይህን የህል እውር እና በበቀል የሚደሰት ጠባይ የተጠናወተው ያደርጋል። ቁጣ የበቀለኝነት ሐጢያት በውስጣችን ካዋለደ በኋላ እውነቱን የማይመለከቱ ጭፍኖች ያደርጋል።

አንዳንድ ሰዎች በፍትሕ እና በበቀል መካከል ግልጽ የሆነ መስመር ማስመር እና በዚህ ግልፅ መስመር ከበቀል መራቅ ይቻላል ብለው ያስባሉ።

ፍትሕን እና በቀልን የሚለይ ግልፅ የሆነ መስመር ማስመር እና በእዚህ በተሰመረ የመለያ መስመር አማካኝነት ከበቀል መራቅ ይቻላል ብለው የሚያስቡ ሰዎች አሉ። ሆኖም፣ አመክኒዮአዊ የሆነ ፍትህን ፣በፍትህ ስም ከሚፈፀም በቀል የመለያ መስመር ለብቻው፤ ፍትሕን የሚያዛባ እና የፍትሕን በትር ወደበቀል የሚቀይረውን ደመ ነፍሳዊ የሆነውን የሰውን ልጅ ራስ ወዳድነት ለመቆጣጠር ኋይል የለውም። በተሸነፋ ጠላቶቻችን ላይ እንዲተላለፍ የምንፈልገው ቅጣት፣ በፈፀሙት ወንጀል ምክንያት ሊቀበሉ የተገባ ፍርድ ስንፈርድ፣ እንደ አሸናፊ ኋይል እና ፈራጅ የተቀመጥንበት የፍርድ ወንበር፣ እርግጠኛ ያልሆነ እና አደገኛ በመሆኑ ማለትም ከበቀል ስሜት እና ከራስ ጥቅም ተነስተን ፍርድ ለመስጠት የሚከለክለን ሃይል የሌለበት ቦታ መሆኑን በመገንዘብ፣ የፍርድ አሰጣጣችን “በፍርሃት እና በመንቀጥቀጥ” ሃይላችንም ጊዜያዊ እንደሆነ በመገንዘብ፣ ደግሞም ከምንም በላይ “ፃድቁም ሐጢያተኛውም በደለኛ ሆነው የሚገኙበት” መለኮታዊ ፍርድ እንዳለ የሆነ ያህል መጠን እንኳን መቀበል አለብን። ይህ የማይሆን ከሆነ ግን የቱንም ያህል ምክንያታዊ ለሆነ ፍትሕ የፀና አቋም ቢኖረን፤ ፍትሕን ለማስፈን የምናደርገው ጥረት በበቀል ፍላጎት መበከሉን ይቀጥላል።

በምንቆጣበት ጊዜ የሚፈጠረውን ሐጢያት የምናስወግደው ራሳችንን ከሁሉ ነገር በመነጠል አይደለም። ነገር ግን ግለኛ እና አድሎአዊ ለሆነው ሰዋዊ ማንነታችን እውቅና በመስጠት እና ከእኛ ፍርድ በላይ ደግሞ በሁሉ የሚፈርድ አስፈሪው የመለኮት ፍርድ እንዳለ በማመን ነው። ሐገሮች ከራሳቸው አልፈው፣ በእነርሱም ላይ የሚፈርድ መለኮታዊ ፍርድ እንዳለ ስለመገንዘባቸው ማወቅ አስቸጋሪ ነው። አሸናፊ ሃይል ነገ ከነገ ወዲያ በጠላቶቻቸው ውስጥ ወደ በቀል የሚድግ ቁጣ ለማስቆም የሚያስችል ከፍ ያለ ስብዕና፣ የስልጣኔ ልዕልና እና የባሕሪ ትህትሃና ደረጃ ሊኖራቸው መቻሉ ጥያቄ ምልክት ውስጥ የሚገባ ነው። ቡድኖች እንዲህ አይነት ማንነት ላይ የደረሱበት ዘመን የለም። በምድራችን ላይ በተካሄዱ ጦርነቶች ውስጥ ከትላንት ጀምሮ እስከዛሬ ማብቂያ የሌለው የእኩይ ድርጊት ሰንሰለት ላለመበጠሱ ዋና ምክንያት ለአንድ ዓላማ የተሰባሰቡ ሰዎች (ቡድን፣ ጎሳ አልያም ሐገር ሊሆን ይችላል) ከራሳቸው ዓለም ወጥተው፤ ከእነርሱ በላይ ፈራጅ የሆነ እንዳለ ወደሚያውቁበት ከፍታ መሄድ ባለመቻላቸው እንደሆነ ግልፅ ነው። በሌላ አገላለፅ ሐገሮች ወይም ቡድኖች ተቀናቃኞቻቸው ሁልጊዜ ሐጢያተኞ ናቸው። እነርሱ ግን ሁልጊዜ ንፁሃን ናቸው። ሁሉም ቡድን እና ሐገር ጉልበት ባደረጀ፤ ሐይል ባገኘ ወቀት ለሚሰራው እኩይ ምግባር ፈራጅ የሆነ ሌላ ሀይል እንዳለ ማሰብ አይፈልግም።

ሆኖም ሁልጊዜም ቢሆን በአንድ ሐገር ውስጥ በቁጥራቸው ጥቂት የሆኑ የእግዚያብሔር ፍርድ ከዛች ሐገር ላይ እንዲከለከል የሚማልዱ ሰዎች አሉ። የእንደዚህ አይነት ሰዎች የመኖራቸው ዕድል ሁልጊዜም አለ። የብሉይ ኪዳን ነብያት በመልእክቶቻቸው ውስጥ ትውልድን ከጥፋት 'የሚታደጉ ቅሪቶች' የሚሏቸው ሰዎች ተግባር ይህ ነው። በሐሳብ ደረጃ፣ የአንድ ሕዝብ ወይም ሀገር ትውልድን ከጥፋት 'የሚታደጉ ቅሪቶች' መሆን የቤተ ክርስቲያን ድርሻ ነው። ነገር ግን ቤተ ክርስቲያን ስልጡን በሆኑ ሕዝቦች መሐል፣ ሃይማኖት የሌላቸው፣ ሆኖም አንድ ሐገር የምትሄድበት ያልተገባ እና እኩይ መንገድ የሚያሳስባቸው፣ በመርህ ደረጃ ግን መለኮታዊ ፍርድ አለ ብለው የማይቀበሉ፣ "ሰዎች በመለኮታዊ ፍርድ አመኑም አላመኑም ለሚሰሩት እኩይ ድርጊት ውጤቱን ይቀበላሉ" ብለው የሚያምኑ ሰዎች እንዳሉ እውቅና ልትሰጥ ይገባል። እንደውም ብዙ ጊዜ እንደታየው ከቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በላይ (ከክርስቲያኖችን በበለጠ) እኩይ ነገር ሲሆን ዝም የማይሉ፣ አንድ ሐገር በሃይሏ ወይም በአሸናፊነቷ ምክንያት የምትገባበትን የትምክህት ሐጢያት ተረድተው የሚያስጠነቅቁ ሃይማኖታዊ ያልሆኑ እና የትኛውንም ሃይማኖት የማይቀበሉ፣ ሃይማኖት የሌላቸው ሰዎች ሆነው ይገኛሉ።

በሐገሮች ትምክህት እና የአሸናፊነት እብሪት ላይ ገደብ የሚያስቀምጥ እና መስመር የሚያሲዝ ሥነ ምግባራዊ እና መንፈሳዊ የሆነ መረዳት ከየትም ይምጣ፤ ይህ መረዳት በሀገሮች እና በቡድኖች መሀከል ገንቢ የሆነ ሚና ይጫወታል። መልካም ተፅእኖም ይኖረዋል። እንደዚህ ካልሆነ ግን የሀገሮች ትምክህት እና የበቀል ፍላጎት ምንም ገደብ የለውም።የአሸናፊ ወገን ጭካኔ የተሞላ ስሜት በተሸናፊው ወገን ላይ ተከፍሎ የማያልቅ ጥያቄ በማቅረብ መልስ ይፈልጋል። ይህም ቀድሞ ጥፋት ወደ አጠፋው ወይም በጦርነት ወደ ተሸነፈው የጠላት የሞራል አዘቅት ውስጥ መግባትን ያመጣል። እኩይን ካሸነፉ በኋላ ወደ እኩይነት መቀየርን ይወልዳል። እና ተሸናፊው ላጠፋው ጠፋት እንዳይፀፀት ትልቅ ተግዳሮት ይሆናል።

## 2.

ከከንቱ ኩራት (egotism) ጋር የተቃየጠ ቁጣ በቀል ይወልዳል። ከትውስታ እና ነገሩን ይዞ ከማመንዠግ ጋር የተቀላቀለ ቁጣ፤ ጥላቻን ይፈጥራል። ምንም እንኳን ተግባራዊ የማይሆን እና ቃል በቃል ተርጉመን የማንከተለው ቢሆንም፣ ‘በቁጣችሁ መሐል ፀሀይ አይግባ’ የሚለው ትእዛዝ፤ ጥልቅ ከሆነ አሳላስሎት የወጣ ቃል እንሆነ እናያለን። እኩይ በመንገዳችን ሲገጥመን እና ከመጥፎ ነገር ስንላተም ንዴት ውስጥ እንገባለን። ሲበድሉን እና ያልተገባ ነገር ሲያደርጉብን እንቆጣለን። በዚህ ጊዜ እኩይ ተግባር የፌፅመብንን ሰው፣ ከፈፀመው እኩይ ተግባር ሙሉ በሙሉ ለይተን ማየት የምንችልበት፤ ምንም መንገድ የለም።

ሐጢያትን ጥላ ነገር ግን ሐጢያተኛውን ውደድ የሚለው ምክረ ሃሳብ ተግባራዊ የማይሆን አደናጋሪ ሀሳብ ነው። ክፋትን የመጥላት እና መጥፎ ድርጊት የፈፀመውን ሰው ደግሞ መውደድ የሚለው ሃሳብ ከሞራል አኳያ ፍጹም ትክክል አይደለም። አዕምሮአችንም ሊቀበለው አይቻልም። ከባድ ነው። ይህ አስተሳሰብ የተደገፈው መላምት፣ እኩይ ነገር የሚሰራ ሰው “እኩይ ምግባር እንዲፈጽም ያደረገው በቂ እውቀት ስላልነበረው እንጂ በክፋ ዓላማ ተሞልቶ አይደለም የሚል ነው”። ይህ መላ ምት “በሰው ልጆች ሁሉ የሚፈፀም እኩይ ስራ ከእውቀት እጦት የሚመነጭ እንጂ በመሠረታዊነት ሰው እኩይ ምግባር መፈፀም አይፈልግም” ብሎ ይሞግታል። ነገር ግን ብዙ መጥፎ ነገሮች በመጥፎ ዓላማ እና ፍላጎት ገፊነት ይከናወናሉ። ሰዎች ጥፋት እና ልማትን የሚያመጣውን ነገር ለይተው ጥፋት የሚያመጣውን መርጠው ያደርጋሉ። ስለዚህ ሰዎች እኩይ የሆነ ነገር ሲፈፅሙብን እነርሱን ከሥራቸው ሳንነጥል መቆጣታችን አግባብ አለው።

ነገር ግን እኩይ አድራጊ በፈቃደኝነት በእኩይ ሥራ ውስጥ የመሳተፋ ተጨባጭ ሐቅ፣ እኩይ አድራጊ ግለሰብን ፍፁም ሰብዓዊነት የሌለው፣ ከእኩይ ጋር የአንድ ሳንቲም ሁለት ገፅታ አድርጎ የመሳል ፣የመለወጥ ተስፋ እንደሌለው አድርጎ መውሰድ ትክክለኛ ያልሆነ የአመለካከት ፈተና ውስጥ ይጥለናል። አንድ ሰው በክፋ ምግባር ውስጥ የሚያደርገው ተሳትፎ ሌሎች ሰዎች ይህ ግለሰብ “ክፋ መንፈስ የሞላበት አንዳች መልካም ነገር የሌለው” አድርገው ወደ መመልከት እንዲያዘነብሉ ትልቅ ሚና ይጫወታል። በተለይም በጦርነት ወቅት እንዲህ አይነቱ አስተሳሰብ የጎላ ነው። በሁሉም ጦርነቶች ውስጥ፣ ተሳታፊ የሆኑ ሃይሎች ጠላቶቻቸውን፣ “ፍፁም እኩይ እና ጭራቅ” አድርጎ የማቅረብን ሥራ፣ ከአካላዊ

ጦርነት ባልተናነሰ መልኩ በፕሮፓጋንዳ ሲሰሩ ይታያል። ከየትኛውም ጦርነት በላይ ደግሞ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፣ የናዚህ ሃይል ከዚህ በፊት ታይቶ የማይታወቅ እጅግ የከፋ ጭካኔ በማሳየቱ፤ የምንዋጋው ጠላት 'ፍትሃዊ' ምክንያት የሌለው፣ "ከሰውነት የወጣ የእኩይ አካላዊ መገለጥ" (Demonic power) ነው፣ የሚለው እምነት ከፍተኛ ደረጃ የደረሰበት ወቅት ነበር።

ሆኖም ግን እነዚህም ሐልዮቶች ራሳቸው ፍትሃዊ አይደሉም። "በቁጣችሁ መሐል ፀሐይ አይግባ"፣ በሚለው ትዕዛዝ ውስጥ ያለው ማዕከላዊ መልዕክት፣ ቁጣችንን የቀሰቀሰው እኩይ ምግባር የጠላቶቻችን ብቸኛ ማንነት አድርገን አንቁጠር የሚል ነው። ቁጣችን ማብቂያ የሌለው እና ቋሚ አይሁን የሚል ነው። ተገዳዳሪያችን ተፈጥሮአዊ እኩይ ነው ብሎ ማመን እና በምንም ምክንያት የማይበርድ ቁጣ፣ ስር ወደ ሰደደ ጥላቻ ይቀየራል። የጠላቶቻችን ማንነት"እንደሚያደርጓቸው ድርጊቶች" እንዲሁ፣ እኩይ እና እኩይ ብቻ ነው የሚል ድምድሜ ዘንድ ያደርሰናል።

በረግጥ ሊስተካከል ወይም ምህረት ሊደረግለት ከሚቻለው መስመር በላይ አልፈው የሚሄዱ ወንጀለኞች አሉ። እንዲህ አይነት እኩይ ሥራ የሚሰሩ ሰዎች ቢያንስ ለማህበረሰብ ደህንነተ እና ጥቅም ሲባል በእድሜ ልክ እሥራት ወይም በሞት መቀጣት ይገባቸዋል። ልክ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት የናዚ መሪዎች በጦር ወንጀለኝነት እና በዘር ማጥፋት እንደተጠየቁት፣ አንዳንድ ሰዎች በቡድን በተሰሩ ጥፋቶች ውስጥ ከተጫወቱት ከፍተኛ ሚና የተነሳ ያሉበት ማህበረሰብ ፣ ከዚህ ቀደም ከሰሩት እኩይ ተግባር የተነሳ እንዲያስወግዳቸው ከመገደድ ውጪ ሌላ አማራጭ ያልሰጡትን ወንጀለኖች ባስተናገደበት መንገድ፣ ሊያስተናግዳቸው ይገባል።

የአንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ በደል፥አንድ ግለሰብ ከሚፈጽመው በደል ተለይቶ ሊቀል ወይም ሊከብድ አይገባም። አጥፊ እና የጥፋቱ መጠን ሳይሆን ማንኛውም ጥፋት ተጠያቂነትን ይዞ ይመጣል። በዚህም ፍትህ ለሀገር ሲሆን ዝቅ ወይም ከፍ አይልም። አንድን በደል ግለሰብም ይፈጸማው ወይም እንደ ሃገር ይፈጸም ፍትህ በሚከናወንበት ጊዜ መንገዱ የፍትህን ጥያቄ ብቻ ለማርካት መሆን አለበት። አንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ ጥፋት እና በደል ሲፈፅም፤ ያ ሐገር ወይም ማህበረሰብ ለምን እንዲህ አይነት በደል አደረሰ ተብሎ መጠናት አለበት። በደሉ የተፈፀመበት ምክንያት ሊመዘን፣ አውዱ፣ ነገሩን ያነሳሳው ነገር፣ አላማውን እና ለሎቹንም ምክንያቶች ግምት ውስጥ ማስገባት ይቻላል። እንዲያው በደፈናው የአንድን ሀገር ጥፋት በተመለከተ አጠቃላይ ግምቶችን ወይም ፍርዶችን

ማስቀመጥና አንድ ሀገር ወይም ማህበረሰብ ዘላለም ግፍ አድራጊ አድርጎ መሳል ተገቢ አደለም። በእያንዳንዱ ሰው ልብ ውስጥ፣ የተወሳሰቡ የፍላጎቶች ድር አለ።

እያንዳንዱ ድርጊት፣ ጥሩም ይሁን መጥፎ፣ በተለያዩ ገፊ ምክንያቶች እና ፍላጎቶች መካከል ያለ የተወሳሰበ የውስጥ ክርክር ውጤት ነው። አንዳንድ ጊዜ፣ በጣም መጥፎ ድርጊቶች የሚመነጩት እንደሌሎች ጎልተው የሚወጡ ተደጋጋሚ ወንጀሎችን ከሚፈጽሙ ክፉ ከሆኑ ሰዎች ሳይሆን ከዚህ ቀደም ምንም አይነት ወንጀል ካልፈፀሙ ሰዎች ነው። ድንገት እና በአጋጣሚ እዚህ ግባ የማይባል ጥፋት ካጠፉ መልካም ባሕሪ ካላቸው ሰዎች እኩል መልካም ባሕሪ ያላቸው ሰዎች እጅግ አደገኛ ወንጀል ፈፅመው ይገኛሉ። አንዳንድ ጊዜ በእስር ቤት ውስጥ ያሉ ነፍሰ ገዳዮች በተለያየ ወንጀል ከታሰሩ እስረኞች መካከል በመልካም ባሕሪቸው ከተመሰከረላቸው እስረኞች ከፊት የሚቀመጡ እነርሱ እንደሆኑ የታወቀ ነው። በእስር ቤት ውስጥ በመላካምነታቸው እና ትህትናቸው የተወደዱ ሰዎች ናቸው። እነዚህ ወንጀለኞች ብዙውን ጊዜ ወንጀላቸውን የሚፈጽሙት ድንገት ሊቆጣጠሩት በማይችሉት ስሜት ውሰጥ ሆነው ወይም በተስፋ መቁረጥ ስሜት ውስጥ ነው። እንደሌሎች ታስቦባቸው እና በዝግጅት እንደተፈፀሙ ወንጀሎች ስር በሰደዱ ተንኮል አዘል ዓላማ በእቅድ ያደረጓቸው ወንጀሎች አይደሉም።

ግለሰቦች ለብቻቸው በልባቸው የሚያውጠነጥኑት ሐሳብ እና ምኞት፣ የመላ ሀገሪቱን ዜጎች የሚያሳትፍ የድርጊት መመሪያ እና መተዳደረያ የመሆን አቅም አለው። የአንድ ግለሰብ ሐሳብ በማህበረሰብ ወይም በሐገሪቷ የሞራላዊ ሕይወት ውስጥ ትልቅ ሚና የሚጫወት የአደባባይ ሙግት ግብዓት ወደ መሆን ይመጣል። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመጀመሩ በፊት፣ የጀርመን ሕዝብ እንደ ናዚ ያለን ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ አጨብጭበው እንደተቀበሉት፣ አንባገነን መንግስት የሚፈልግ ማህበረሰብ በብዙ መልኩ የዘቀጠ መሆን አለበት። ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝ የሚቀበል ሐገር ማሕበረሰባዊ መዝቀጥ ውስጥ የገባ ነው። በሌላ አነጋገር ደግሞ በተሳካ ሁኔታ ፈላጭ ቆራጭ አገዛዝን ማስወገድ የማይችል ደካማ ማህበረሰብ ያለበት ሐገር ነው ማለት ነው። ሆኖም ግን በጀርመን ውስጥ እንደ ናዚ አይነት ጨካኝ እና አረመኔ አገዛዝን የወለደውን አይነት አሳዛኝ የባህል እና ስልጣኔ መዝቀጥ እና መበስበስ ውስጥ ያሉ ሐገሮች እና ሕዝቦች፤ እየሆነ ያለው ነገር እነዚህ ሐገሮች ሙሉ በሙሉ የመዝቀጣቸው እና ማሕበራዊ የሥነ ምግባር መበስበስ ውስጥ ስለመግባታቸው ማረጋገጫ አይደለም። ለምሳሌ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት የናዚ አገዛዝ በፈፀመው ወንጀል ምክንያት የዓለም ሕብ ለጀርመን

ያሳየው ጥላቻ ተፈጥሮአዊ እና እንደዛ አይነት ውጤት ከማምጣት ውጪ አማራጭ የሌለው ነገር ነው። ቢሆንም ግን ፍትሃዊ አይደለም። እንደዚህ መሰል ጥላቻዎች በወደፊቱ የጋራ ኑሮአችን ውስጥ የሚከሰቱ እኩይ ነገሮችን ይዘራሉ።

ክፋት በሚገለጥበት ጊዜ ወዲያው መዋጋት አስፈላጊ ነው፣ ግን ደግሞ የዚያ ክፋት ትውስታ የወደፊት ግንኙነቶችን እንዲያበላሽ አለመፍቀድ ብልህነት ነው። 'ቁጣህን በውስጥህ እንደያዝክ፣ በምሥራቅ የወጣችው ፀሀይ በምዕራብ እስክትጠልቅ አትጠብቅ' የሚለው ትዕዛዝ ቃል በቃል ለመተግበር የሚከብድ ሊሆን ይችላል። ነገር ግን ይህ ምክር ከጀርባው ያዘለው ዋናው ሐሳብ ከልብ ልንወስደው የሚገባ እና ጠቃሚ ነው። በጦር ሜዳ የሚካሄድ ውጊያ እየበቃ የጦርነት ትኩሳት እና ከፍተኛ መነሳሳት እየቀነሰ በሄደ ቁጥር፣ በጦርነት ወቅት ለጠላቶቻችን የነበረን አመለካከት በሰላም ጊዜ ከልባችን እንዳይወጣ የሚያደርግ ስለጠላቶቻችን በልቦናችን የያዝነው መራር የሆነ ጥላቻ እጅግ እየከፋ እና እየጨመረ ይሄዳል። ይህን ጥላቻ ለማስወገድ እና በመጨረሻም በማያልቅ የጥላቻ አዙሪት ውስጥ ተያይዘን እንዳንጠፋ፣ የግድ ከጠላቶቻችን ጋር ሰላም መፍጠር አለብን። ይህንን ለማድረግ ያለፈውን መርሳት አለብን።

መርሳት ለእርቅ ቅድመ ሁኔታ ነው። ያለፈውን ጊዜ በመርሳት ጠላት የነበሩ ኀይሎች አውንታዊ ባሕርያቸውን ለማሳየት እና ምናልባትም ወደ ተሻለ ሁኔታ ለመለወጥ እድል ይሰጣቸዋል። ይህም ጠላት የነበረ ከክፋ መንገድ ተመልሶ መልካም ግንኙነት እንዲመሰርት እድል እንዲያገኝ ያደርገዋል። ወደፊትደግሞ ቀድሞ ባላንጣ የነበሩ ወገኖች ጠንካራ እና መከባበር ያለበት ግንኙነት እንዲመሰርቱ ያደርጋል።

በእርግጠኝነት እንዲህ አይነት ወንጀልን መዘንጋት፣ እንዳልተፈፀመ ቆጥሮ መርሳት ሐላፊነት የጎደለው ተግባር ነው። ወንጀልን በመቅጣት ወደፊት የሚፈፀምን የሕግ ጥሰት ለማስቀረት እና የጋራ ደህንነትን ለመጠበቅ የሁሉም ማህበረሰብ የውዴታ ግዴታ እንደሆነ ግምት ውስጥ ማስገባት ያቃተው አስተያየት ነው የሚል ክርክር ሊነሳ ይችላል። አንድ የምንገነዘበው እውነት 'ተቆጡ .......... በቁጣችሁ መሐል ፀሐይ አይግባ' የሚለው ማስንጠቀቂያ እና ምክር ቃል በቃል ቀጥታ ወስደን ለመተግበር ከሞከርን አንድ ማህበረሰብ ወንጀልን ለመከላከል ማድረግ ያለበትን ጥረት እና ቅድመ ዝግጅት የሚቃረን ይሆናል። ማንኛውም ወንጀለኛ በአቋራጭ የሚገኝን ጥቅም እና የአጭር ጊዜ ትርፍን አስልቶ የፈፀመው ወንጀል ለዘለቄታው የማይጠቅም መሆኑን እንዲገነዘብ ማለትም ለራሱ

ለወንጀለኛው ትምህርት እንዲሆን እና ሌሎች ደግሞ በዚህ ወንጀለኛ አለመቀጣት ተማምነው ወደፊት ተመሳሳይ ወንጀሎችን እንዳይፈፅሙ ተስፋ ለማስቆረጥ ወንጀለኞች ሊቀጡ ይገባል።

ሆኖም ወንጀለኛን በመቅጣት የሚመጣን ውጤት አጋኖ የማይት ነገር አለ። የትኛውም ወንጀለኛ በከባድ ቅጣት ምክንያት ወደ ንስሐ እና ለውጥ አይመጣም። ወንጀል እና ወንጀለኛን በተመለከተ በሚደረግ የጥናት መስክ ውስጥ እንደምናገኘው፣ ማህበረሰብ የግለሰቦችን ጥፋት እና ልማት በተመለከተ በሚወስደው እርምጃ፣ በህመም እና እየተናነቀው የተማረው እውነት ቢኖር፣ እጅግ ከባድ የሆነ ቅጣት ወንጀለኛን ወደ ንስሃ እንደማያመጣ፣ በወንጀሉ እንዲፀፀት እንደማያደርገው እና ሌሎችም ተመሳሳይ ወንጀል ከመፈፀም ሞኞት ራሳቸውን እንዲያቅቡ የሚደርግ እንዳልሆነ ነው። ከባድ ቅጣት ወንጀለኛን ለመለወጥም ይሁን ወደፊት የሚፈፀም ወንጀልን ለማስቆም ዋስትና አይደለም። ስለዚህም ወንጀልን እና ወንጀለኛን በመቅጣት ሂደት ውስጥ፣ እጅግ ከባድ የሆነ ቀጣት በመቅጣት ወንጀልን ለማስቀረት የነበረው ጥረት ቆሟል። ለወንጀለኛ የሚራራ፣ ጥፋትን መቅጣት ብቻ ሳይሆን ለአጥፊም በማዘን ላይ ያተኮረ፣ በወንጀለኛ ማንነት ውስጥ ያለውን መልካምነት እና የሚያምንባቸውን ልክ የሆኑ የሥነ ምግባር አመለካከቶች እንዲያዳብር የሚረዳ፣ የወንጀለኛውን ስብዕና በመገንባት ላይ ያተኮረ አካሄድ ተመራጭ ሆኗል። እናም እጅግ የከፋ የቅጣት አይነትን ቀስ በቀስ እየተካ ሄዷል።

ለዚህ ለውጥ መምጣት በዋነኛነት ትልቅ ሚና የተጫወተው አስተሳሰብ በቁጣችሁ መሐል ፀሀይ አይግባ የሚለው ምክር እና ማስጠንቀቂያን ልብ ብሎ ከመስማት ነው። ምክንያቱም ወንጀለኛን ከባድ ቅጣት በመቅጣት ለውጥ ይመጣል የሚለው የተጋነነ አስተሳሰብ ውሃ የማይቋጥር እና ከባድ ቅጣት በራሱ የመጨረሻ መፍትሄ እንዳልሆነ ውስንነቱን ከመረዳት የመጣ ነው። ወንጀለኛን ከባድ ቅጣት በመቅጣት ለውጥ ይመጣል የሚለውን ሐሳብ ውስንነት መረዳት ማለት ደግሞ ፀሐይ ወጥቶ እስኪገባ ቁጣን አለመያዝ አስፈላጊ መሆኑን መቀበል ማለት ነው። እኩይ ሲፈፀም ስናይ መቆጣት እና በቁጣ የተሞላ ምለሽ መስጠት ተገቢ የሆነ እርምጃ ነው። ነገር ግን ዘለቄታዊ የሆነ መፍትሄ ለማምጣት የምናስብ ከሆነ እና በሰከነ መንፈስ እኩይ አድራጊውን ወደ ጤነኛ ሥነ ምግባር የሚመልስ የተሻለውን መንገድ ፈልጎ ለማግኘት ከቁጣ ውስጥ መውጣት አማራጭ የሌለው ነገር ነው።

‘በቁጣ ተሞልተህ እንደዋልክ ከቁጣህ ጋር አትደር’ የሚል ምክር እና ማስጠንቀቂያ አስፈላጊነቱ ጎልቶ የሚወጣው፣ በጠላቶቻችን ለተፈፀመብን ትንኮሳ እና እኩይ ድርጊት በቁጣ ተሞልተን በወሰድነው እርምጃ የመጣው ውጤት፣ ጠላቶቻችን ላጠፉት ጥፋት የሚገባ ወይም የተመጣጠነ ሳይሆን፣ በደህና ጊዜ ልናደርገው ሳይሆን ልናስበው እንኳን የማንፈልገውን አረመኔያዊ እርምጃ በምንወስድበት የጦርነት ወቅት ነው። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት በጃፓን እና ጀርመን ከተሞች የደረሰውን መፈራረስ እንደምሳሌ ማንሳት እንችላለን። በከፍተኛ ሁኔታ በኢንዱስትሪ አድገው የነበሩ ሐገሮች እና ማሕበረሰቦች ፈራርሰው ምንም ነገር ወደሌለበት ወደ ኋላ ቀር ዘመን ተመልሰዋል። ማህበረሰብ መሠረታዊ ነገሮች ወደሌሉበት እና ለሰው ልጅ ሁለተናዊ እድገት የሚስፈልጉ ነገሮች እጥረት ወደምላበት ወደ አሮጌው ዘመን ተለውጠዋል። ታላላቅ ከተሞች በፍርሥራሽ ህንፃዎች ተሞልተዋል። በአንድ ወቅት ኀያል የነበሩት ከተሞች የፍርሥራሽ ክምር ሆነዋል። በዘመናዊው ዓለም ያሉ ያደጉ ሐገሮች ወረራ እና ጥፋት ሲፈፅሙ የሚፈፅሙት የጦር ወንጀሎች ከዚህ ቀደም በባሕላዊ መንገድ ይካሄዱ ከነበሩ ጦርነቶች የከፋ እየሆነ በሄደ ቁጥር የሚደርስባቸው ቅጣት (በሚደርስባቸው ሽንፈት ምክንያት) ከመቼውም ጊዜ በላይ የከፋ ይሆናል።

ይህ ቅጣት የጠላትን ልብ ወደ ፀፀት እና ንስሐ ላያመጣው ይችላል። ቅጣታችን በጠላት ላይ የሚፈለገውን ለውጥ ስላላመጣ ብለን ደግሞ ከበፊቱ የከፋ ቅጣት ብናመጣ ያ ከመጀመሪያው የከፋው ቅጣትም ለውጥ አያመጣም። በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ወቅት አሸናፊዎቹ ሃያላን ሐገሮች ለብቻቸው ተሰብስበው፣ ተሸናፊዎቹ ሐገራትን ማብቂያ ለሌለው ጊዜ በእነርሱ ቁጥጥር ውስጥ እንዲወድቁ መወሰናቸው፣ በቅጣት ብቻ በአንድ ጊዜ ሁለት ተቃራኒ ነገር ለማድረግ ማለትም ተሸናፊዎቹ ሐገራት በጥፋታቸው እንዲፀፀቱ እና ወደፊት ተመሳሳይ ጥፋት እንዳያጠፉ ሃይላቸውን በበቂ ሁኔታ መንጠቅ ዓላማ ያደረገ ውሳኔ መወሰናቸው የሚያሳየን፣ የሰው ልጅ ምን ያህል በቀላሉ በከንቱ የአሸናፊነት ትምክህት ውስጥ እንደሚወድቅ ነው።

ሃይልን ስንጠቀምም ሆነ ፍትሕን ስናስፈፀም ምን ያህል ራሳችንን ሁሉን በሚችል አምላክ ወንበር ላይ ለማስቀመጥ እንደምንፈጥን ያሳያል። የአሸናፊነት ሥነልቦና የብዙ ችግር ምንጭ ነው። የጠላትን ሃይል ፈፅሞ ማድከም እና ከቅጣቱ ክብደት የተነሳ ጠላት በጥፋቱ እንዲፀፀት ማድረግ የሚለው ሐሳብ ምን ያህል አብረው የማይሄዱ ነገሮች መሆኑን አንገነዘብም። በአንደኛው ቢሳካልን

ማለትም ከእጁ ላይ ጥፋት የፈፀመበትን መሳሪያ ብንነጥቅ፤ በፀፀት እንዲመለስ ግን አናደርግም። በሌላው ግባችን እንቅፋት ይገጥመናል። የአሸናፊ አካል ጉልበት (ሰይፍ) በራሱ፣ በተሸናፊው ላይ የተገለጠ ፍርድ ነው የሚለው ሙሉ በሙሉ ልክ እንዳልሆነ መረዳት ይከብደናል። በርግጥ ወንጀለኛ ወይም አጥፊ አካል ወደ ነስሐ የሚመጣበት ብቸኛው መንገድ ሰይፍ ብቻ ቢሆንም። ነገር ግን እኛ ፍርድን ለማስፈፀም እና ጥፋተኛውን ለመቅጣት መብት የሚኖረን ጥፋቱ በተከሰተበት ወቅት ብቻ ነው። በተገኘው ድል ምክንያት የመጣውን ተቀባይነት በመጠቀም በፍትሕ ስም ተሸናፊውን ወገን ለረጅም ወይም ገደቡ ላልታወቀ ጊዜ ለመቆጣጠር መሞከር ፍትሕን ወደ ኢ ፍትሓዊነት ይቀይራል። ይህም የሚሆነው በቁጣችሁ መሃል ፀሀይ አይግባ የሚለውን ጥበብ መረዳት ከቻልን ብቻ ነው።

በሕይወት ትግል ውስጥ እንዳለን እንደ አንድ ተሳታፊ አካል እና እንደሰው ውስን መሆናችንን መገንዘብ ስለሚሳነን በወደረኞቻችን ላይ ፍትሕን እናዘገያለን፣ ቅጣታችንም ገደብ የለውም። ይህ ዝንባሌ ደግሞ የሚመጣው የሰው ልጅ ሁሌም ወድቆ ከሚገኝበት ሐጢያት ነው፥ ኀይል እና መልካምነት (የሥነ ምግባር ልዕልና አለኝ) አጣምሮ እንደያዘ የሚያስመስልበት መንገድ ነው። ጠላታችን እኩይ ስለሆነ ነገ ተመልሶ እንዳያጠቃን በሚል ኋይሉን ለመንጠቅ የምናደርገው ጥረት፣ ይሆናል ብለን ያላሰብነውን ቁጣ በጠላታችን ውስጥ ይቀሰቅሳል። ምናልባትም በዚህ ቁጣ ገፋፊነት የደከመውን እና የተሸነፈውን ኋይሉን የሚያድስለትን እና በሽንፈት የቀማነውን ኋይል የሚተካለት መሳሪያ የሚፈጥርበት ትጋት እና ቆራጥነት ውስጥ እንዲገባ ያደርገዋል። ዘላለም በጠላቶቻችን ላይ የበላይ ሆነን ለመኖር፣ ፍትሕ ሰጪ እና ቅጣት አስፈፃሚ ለመሆን የምናደርገው ጥረት፣ ዕለት በዕለት ለራሳችን ጥቅም ብቻ የምንቆም ስግብግቦች ተደርገን መታየታችንን ሲጨምር፣ ቂይማትንም የሚወልድ መንገድ ነው።

በዓለማችን ላይ ያሉ ሐገሮች ተሰባስበው የመሠረቷቸው ማህበሮች አድሎአዊ ያልሆነ የፍትሕ መሳሪያ ኖሮአቸው ቢሆን ኖሮ ይህ እኩይ አካሄድ መቆም የሚችል ነበር። ነገር ግን ያሉን ዓለም አቀፍ ሕጎች፣ ለረጅም ጊዜ ሰርፆ የቆየውን አድሎአዊነት ለማስወገድ የሚያደፍሩ አይደሉም። አሁንም ወደፊትም፣ ምናልባትም እስከ ምድር ፍጻሜ የአሸናፊዎች ፍላጎት ማስፈፀሚ እንደሆኑ ይቆያሉ። ያሉን ዓለም አቀፍ ሕጎች ከፍተኛ በሆነ ፍትሕ ስም እና ሃይል የአሸናፊዎቹን ትምክህት ለመቀነስ የሚያስችል አቅም እና ሃብት የላቸውም።

ከብሉይ ኪዳን ነብያት ጥልቅ እሳቤ መሐል አንዱ፣ የተለያዩ የዓለማችን

ሐገራት የመለኮት ፍርድ አፅፈፃሚ ሆነው እንደሚያገለግሉ መረዳታቸው ነው። እግዚአብሔር ሀገሮች የሚሰሩትን ኀጢያት ለመቅጣት ሌሎች ሀገሮችን ያሥነሳል ይጠቀማል። ሆኖም እያንዳንዱ በአንድ ወቅት የመለኮትን ፍርድ እንዳስፈፀመ እንዲሁ ያው ሐገር መልሶ በመለኮት ፍርድ ስር ይወድቃል። በአንድ ወቅት የመለኮት ፍርድ ሲያስፈፅም የነበረ ሐገር በተራው ደግሞ የመለኮት ፍርድ የሚፈፀምበት ሐገር የሚሆንበት ምክንያት ስኬታማ ሲሆኑ ኩሩ እና እብሪተኛ ስለሚሆኑ ነው። በእነርሱ በኩል የእግዚአብሔር ፍርድ በሌላው ህዘብ ላይ የተፈፀመበት ምክንያት እነርሱ ንፁህ ሆነው በመሆኑ ስለሚመስላቸው ነው። ከተሰጣቸው ተልዕኮ የተነሳ ምንም እኩይ ቢፈፅሙ ከሌላው የተለየ መለኮታዊ ጥበቃ እንደሚደረግላቸው ማሰባቸው እና በእግዚየብሔር ፊት ሞገስ ያስገኙላቸው ደግሞ ከሌላው የተለየ የሞራል ልዕልና እንዳላቸው ማመናቸው ተመልሰው እነርሱም በመለኮት የፍርድ እጅ ውስጥ እንዲወድቁ ያደርጋቸዋል። ስለዚህ፣ ማስመሰልን፣ ኩራትን እና እብሪተኙነትን የሚያሳዩ አስተሳሰቦችን እና ባሕርያትን ሊያዳብሩ ይችላሉ። በሌላ ቃል በአጭሩ ከተልዕኳቸው ባገኙት ስኬት ምክንያት በክፉ ምኞት ተፈትነው ይወድቃሉ። እናም እነርሱው ተመልሰው በመለኮት ፍርድ ስር ይወድቃሉ።

ብዙ ጊዜ አሸናፊዎች የሰው ልጅ ግብ ወይም ተልዕኮ ያለበትን የውስንነት ጠባይ እና የተጨበጠ ስኬትም ቢሆን እድሜው አጭር እንደሆነ መገንዘብ አይችሉም። ነገር ግን የደረሱበት ነገር ነገ ምን እንደሚሆን የተገለጠ ነው። ነገ ምን እንደሚሆን የሚናገረው ድምፅ ደግሞ ‘ተቆጡ ኀጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ፥ ለዲያብሎስም ፈንታ አትስጡት። ’ የሚለው ምክር ከፈለቀበት ቦታ የወጣ የጥበብ ቃል ነው። ፃድቅ ሰው አሁን እና ዛሬ እያየ ባለው ኢፍትሓዊነት ላይ የሚያሰማው ቁጣ እኩይ ተወግዶ መልካም ነገር እንዲመጣ ገፊ ኀይል ይሆናል። ነገር ግን ቁጣ ማቆሚያ የማይኖረው ከሆነ እና እንደውም ቁጣን መንፈሳዊ ካባ ለማልበስ በኩራት የሚያስስ ከሆነ፤ ይሄ የተሳሳተ ምልከታ በራሱ በአዲስ መልክ ለሚወለድ ኢ-ፍትሃዊነት መሠረት ይሆናል።

ሰው የአሁን እና የዛሬ ፍጥረት ነው። ነገር ግን ከአሁን እና ከዛሬ ተሻግሮ የመሄድ አቅም አለው። ማለትም ወደ ትላንት በመመለስ ከትላንት ሐሳቡ እና ድርጊቱ፣ ትምህርት መቅሰም ይችላል። ደግሞ ወደ መጪው ጊዜ በምናቡ ተሻግሮ ወደፊት ያለውን ተስፋ እና የወደፊት ጊዜ የያዘውን አደጋ ማየት ስለሚችል፣ የሰውን ልጅ “በአሁን እና በዛሬ፣ በቀን እና በሰዓታት” መገደብ አይቻልም። ደግሞም

ገደብ ለስቀመጥ ማንም መብት የለውም። ሆኖም ‘ተቆጡ ኀጢአትንም አታድርጉ፤ በቁጣችሁ ላይ ፀሐይ አይግባ’ የሚለው የተቀደሰው ምክር እና ‘ነገ ለራሱ ይጨነቃልና ለነገ አትጨነቁ’ የሚለው ማስጠንቀቂያ ቃል በቃል ወስደን የምንፈታው እና የምንተገብረው ሐሳብ ባይሆንም፣ በመሠረታዊ ይዘታቸው ትክክለኛ እና ጠቃሚ ምክር ናቸው። የሰው ልጅ ስለወደፊቱ ያለው እይታ ውስን፣ የሰው ልጅ “ፍትሕ” በተፈጥሮአዊ ይዘቱ ጎዶሎ እ እና የሰው ልጅ መልካምነት ወይም ፅድቅ እድሜው አጭር እንደሆነ የሚያስታውሱ፣ የሚያስጠነቅቁ ናቸው።

ብዙ ጊዜ የእግዚያብሔርን ፍርድ የምናስፈፅም እንድንሆን ተጠይቀናል። በእኩይ ላይ እንድንቆጣ ተጠርተናል። መጨረሻ ላይ የሁሉ ነገር መደምደሚያ ከሚሆነው አንፃር ስንመለከት ቀደም ሲል በመግቢያችን የጠቀሥነው የመፅሐፍ ቅዱስ ምንባብ እንዲፃፍ ካነሳሳው ከእምነት በሆነ ጥበብ የተገኘው ሌላው የቅዱስ ጳውሎስ ቃል እዚህ ውስጥ አካተን መገንዘብ ይገባናል። ቅዱስ ጳውሎስ፦ ‘ተወዳጆች ሆይ፥ ራሳችሁ አትበቀሉ፥ ለቍጣው ፈንታ ስጡ እንጂ፤ በቀል የእኔ ነው፥ እኔ ብድራቱን እመልሳለሁ ይላል ጌታ ተብሎ ተጽፎአልና። ’ ይለናል።

ይህ ቃል የነገር ሁሉ ፍጻሜ በማን እጅ እንዳለ የሚያሳይ እውነት ብቻ ሳይሆን፣ በክፉ አድራጊዎች ላይ የሰው አዕምሮ ሊያስበው ከሚችለው በላይ የሆነ አስደንጋጭ ቅጣት በሚፈፀምበት የጦርነት ወቅት አብቀቶ ሰላማዊ ሁኔታ ለመፍጠር ጥረት በሚደረግበት ጊዜ እጅግ አስፈላጊ የሆነ ቃል ነው።

# 3. የክብር መጎናጸፊያ

አጠገባችሁ ካሉ ወይም ከምታውቋቸው መሀል፣ ማስተዋል የሞላባቸውን እና ልበ ቀና የሆኑትን ሃያ የሚሆኑ ሰዎችን ፈልጋችሁ “ላቅ ያለ ስብዕና፣ የሥነ-ምግባር ሁሉ መለኪያ፣ የምስጉን ማንነት መታወቂያ ባሕሪ ምንድን ነው?” ብላችሁ ብትጠይቋቸው፣ በእርግጠኝነት አሥራ ዘጠኙ፣ ያማ “ራስን አለመውደድ ነው” በማለት መልስ ይሰጧችኋል። ነገር ግን ጥቂቶቹን፣እንደውም ሁሉንም ማለት ይቻላል፣ ቀደም ባሉት ዘመናት ከነበሩ ታላላቅ በህይወት ተመስክሮላቸው ያለፉ፣ ክርስቲያኖችን ብትጠይቋቸው “ከፍቅር ውጪ ምን አለ፣ ፍቅር ነው” በማለት መልስ ይሰጧችኋል። ምን እንደተፈጠረ ይታያችኋል? በጥንት ዘመን በነበሩ ክርስቲያኖች እና አሁን ባለንበት ዘመን ባለን ክርስትያኖች መካከል ከቃላት አጠቃቀም ጋር ተያይዞ የተፈጠረው ምንድን ነው? አሉታዊ ቃል የአዎንታዊውን ቦታ ወስዷል። ይህ ጉዳይ በዘፈቀደ አፋችን ላይ የሚመጣልን ያልታሰበበት የንግግር ጉዳይ ብቻ አይደለም። የቋንቋ አጠቃቀም ጉዳይ ብቻ አይደለም።

“ራስን አለመውደድ” የሚለው አሉታዊ ቃል የሚያመለክተው፣ ወይም “ራስን ያለ መውደድ ጽንሰ ሃሳብ” ከምንፈልገው ወይም ካለን ጥሩ እና ጠቃሚ ነገር ላይ መተው፣ መጣል፣ ሁሉንም ነገር አለማጋበስ፣ እና ራስን መቆጠብ የሚለውን ሐሳብ ነው። ጥሩ ነው። ነገር ግን ይሄ ለሌሎች የሚፈይደው ምንም ነገር የለም። ለሌላው ሰው የሚሰጠው ደስታ የለም። ባጭሩ “ራስን አለመውደድ” የሚለው አሉታዊ ጽንሰ ሃሳብ የሚያመለክተው የሌሎችን ደስታ ከማረጋገጥ ይልቅ ለራሳችን መልካም ነገርን በመተው ላይ ማዘንበል ነው። ይህም ከሌላው ሰው ደስታ ይልቅ “ከኔ የሚጠበቀውን ነገር ብቻ ላድርግ” የሚል አስተሳሰብ ነው። ይሄ ልክ አይመስለኝም። “ራስን አለመውደድ” የፍቅርን ክርስቲያናዊ እሴት ይወክላል ብዬ አላምንም። እውነት ነው፣ አዲስ ኪዳን ራስን መስዋዕት ስለ ማድረግ ብዙ ይናገራል። ነገር ግን “ራስን መስዋዕት” ማድረግ እንደመጨረሻ ግብ፣ “ራስን መስዋዕት” ማድረግ ብቻ በቂ እንደሆነ አያስተምርም። አዲስ ኪዳን ራስን መስዋዕት ስለማድረግ አስፈላጊነት ይናገራል፣ ነገር ግን የክርስትና ዋና ዓላማ እርሱ አይደለም።

ክርስቶስን መከተል እንችል ዘንድ ራሳችንን ካስቀመጥንበት ከፍታ ማውረድ እንዳለብን ትዕዛዝ ተሰጥቶናል፣ እኛነታችንን ዋነኛ አድርገን ማስቀመጥ መተው እንዳለብን ተነግሮናል። ራሳችንን እንድንክድ ምክር ቀርቦልናል። ምርጫ

ተሰጥቶናል። ይህን ምክር ሰምተን ራሳችንን መካድ ምርጫችን አድርግን እንደተባልነው የምንኖር ከሆነ፣ መጨረሻ ላይ ራስን በመካድ ሕይወት ውስጥ ይገኛል ተብሎ የቀረበው ማብራሪያ፣ ቢኖረን የምንፈልገው፣ ለፍላጎታችን የሚስማማ ነገር ነው። አሁን እኛ ባለንበት ዘመን ሰዎች አእምሮ ውስጥ፣ ለራሳችን የሚጠቅመንን ነገር ማሣደድና እና በምናገኘው ጠቃሚ ነገር ለመደሰት መጓጓት የተገባ ነገር አይደለም፣ የሚል እምነት ካለ ይህ እምነት፤ ከካንት እና ከስቶይኮች የመጣ ነው እንጂ ከክርስትና ጋር ምንም ግንኙነት እንደሌለው እከራከራለሁ። እንደውም ራሳችንን ብንክድ፣ ራሳችንን በመካድ ውስጥ ለከፈልነው ዋጋ ስለሚጠብቀን ሽልማት እና ስለሽልማቱ አስደናቂ ተፈጥሮ በወንጌላት ውስጥ በግልፅ እና በድፍረት የተጠቀሰውን ብንመለከት፤ ጌታ ኢየሱስ ሽልማቱን ለመውሰድ ያለን ፍላጎት እጅግ ጠናካራ ሳይሆን ልፍስፍስ ሆኖ የሚያገኘው ይመስላል።

እኛ ወላዋይ ነን። በዋል ፈሰስ የሆንን ፍጡራን ነን። ሁልጊዜም ልባችን የተከፈለ ነው። ልባችን እረግቶ አንድ ነገር ላይ አይቆምም። ቤተሰቦቹ ሊያዝናኑት ወደ ባሕር ዳርቻዎች እንደሚወስዱት ሲነግሩት በባሕር ዳርቻዎች መዝናናት ማለት ምን ማለት እንደሆነ ስለማይገባው በቆሻሻ ቦታ ላይ በጭቃ መጫዎትን እንደሚመርጥ ታዳጊ ልጅ፤ ማለቂያ የሌለው ደስታ፣ ቃላት የማይገልጡት ሐሴት ተዘጋጅቶልን ሳለ በመጠጥ፣ በወሲብ እና አይናችን አይቶ የማይጠግበውን፤ ጆሮአችን ሰምቶ የማይሞላውን ፍላጎት የምናሳድድ ፍጥረት ነን። በቀላል እና ትንሽ ነገር ቶሎ የምንፈነጥዝ ነን።

የማያምኑ ሰዎች ስለሚጠብቀን ሽልማት እና ያን ሽልማት ለመቀበል የምናደርገውን ተጋድሎን፣ "ይሄ የክርስቲያንን ሕይወት 'ይሄን አድርግ እኔ ደግሞ ያን አደርግልሃለሁ' የሚል የግብይት ሕይወት ያደርገዋል። ሰዎች በጥቅም እና በተስፋ ተታለው እንጂ፣ ክርስትና እውነት መሆኑ በርቶላቸው አይደለም" ብለው በሚያቀርቡት ሙግት ምክንያት ጭንቀት ውስጥ ልንገባ አይገባም። የተለያዩ አይነት ሽልማቶች አሉ። አንዳንድ ሽልማቶች፣ ሽልማቱን ለማግኘት ካደረጋችሁት ነገር ጋር ምንም አይነት ዝምድና የላቸውም። ላደረጋችሁት ነገር የሚገባ ሽልማት እና የማይገባ ሽልማት አለ።ካደረጋችሁት ድርጊት ጋር አብረው የማይሄዱ ሽልማቶች፣ ድርጊቱን ስታደርጉ ይሰማችሁ ለነበረው ስሜትም እንግዳ ናቸው። ትክክለኛውን የውስጣችሁን ፍላጎት የሚፃረሩ ናቸው። ለምሳሌ ገንዘብ ስላፈቀርን የሚሰጠን ተፈጥሮአዊ ሽልማት አይደለም። የፍቅር ሽልማቱ ገንዘብ አይደለም። ለዛም ነው አንድ ወንድ ወይም አንድ ሴት ሲያገቡ፤ የሚያገቡትን ሰው ያገቡበት ምክንያት

ስላለው ወይም ስላላት ገንዘብ ብለው ከሆነ ይሄ ግብይት ነው። ጥቅም ተኮር ነው። ፍቅር አይደለም። በአንጻሩ ግን ለፍቅር እውነተኛ ሽልማት አለው። ትዳር ለአፍቃሪ የሚሰጥ ሽልማት ነው። እናም አንድ ሰው የሚያፈቅረውን ሰው ለትዳር ቢመኝ ጥቅመኛ አያስብለውም። እና ለጋብቻ ያለ ፍላጎት እንደ ራስ ወዳድነት አይቆጠርም።

በማእረግ ላይ ማእረግ ለመጨመር፣ ለጥቅማ ጥቅም በቆራጥነት እና ብልሀት የሚዋጋና የሚያወጋ ጄኔራል የቱንም ያህል ስኬታማ ቢሆን ስግብግብ ነው። ከንቱ ጥቅመኛ ነው። ጠላቱን ድል ለማድረግ፣ ለማሸነፍ የሚዋጋ ጄኔራልን ግን ጥቅመኛ አንለውም። ለፍቅር እዉነተኛ፣ ተፈጥሮዋ እና ተገቢ ሽልማቱ ትዳር እንደሆነው እንዲሁ፤ በጦርነት ውስጥ ለሚጋደል እውነተኛ ወታደር ተገቢ ሽልማት ድል ነው። ለአንድ ጥሩ ድርጊት ወይም ሥራ የሚሰጥ ተገቢና እውነተኛ ሽልማት ከድርጊቱ ወይም ከጥሩ ሥራ የተነጠለ አይደለም። አንዳንድ ሽልማት፣ ሽልማቱ ፈለግን አልፈለግን የሥራው ቀጥተኛ እና ተፈጥሮአዊ ውጤት ነው ማለት ነው። እንደውም የ ጥሩ ድርጊት ወይም ሥራ ያመጣው ሽልማት፣ ሰራው ወይም ድርጊቱ ምን ያህል በሙሉ አቅም እና ሀይል የመሠራቱ ምልክት ነው! ለምሳሌ አንድ ወንድ አንዲትን ሴት በሃሳብና በድርጊቱ ካፈቀረት፤ እርሷም መልሳ ፍቅሩን ከተቀበለች እና ካፈቀረችው ቀጥሎ የሚመጣው ትዳር ነው። በትዳር ሲተሳሰሩ የሚያጡት ነገር ወይ የሚያገኙት ነገር በውሳኔያቸው ላይ ያን ያህል ለውጥ አያመጣም። ይህም ማለት ሥራችንን ተከትሎ የሚመጣ ተገቢ የሆነ ሽልማት አለ ማለት ነው። በሌላ ጎኑ ደግሞ ተገቢ ያልሆነ፣ ብናገኘው ክብር እና ደስታ የማይፈጥርልን እርሱን ለማግኘት ብለን ምንም አይነት ዋጋ መክፈል የሌለብን ሽልማት አለ።

ከላይ ሁለት አይነት ሽልማት ሊኖር እንደሚችል አየን። አንደኛው ተገቢ ያልሆነ እና ከምንሰራው ሥራ ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት የሌለው ነው። ዓላማችን ሥራው ወይም ድርጊቱ ሳይሆን፤ ሥራው ወይም ድርጊቱ የሚያመጣው ጥቅማጥቅም ነው። ይሄ ለሰው ልጅ የተገባ ሽልማት አይደለም። በተለይ በነገሩ ሁሉ ሙሉ ሆኖ ለማደግ የሚፈልጉ ከዚህ ዓይነት ሽልማት ራሳቸውን ያርቃሉ። ሁለተኛው ሽልማት፣ ሽልማቱን ፈለግን አልፈለግን፣ ሽልማቱን አሰብንም አላሰብን፤ ሥራችንን ተከትሎ የሚመጣ ሽልማት አለ። ተፈጥሮአዊ ሽልማት ነው። ለምሳሌ ጦርነት። ውርደትና ድል ጦርነትን ተከትሎ የሚመጣ ሽልማት ነው። አሁን ደግሞ ትንሽ የተወሳሰበ ሶስተኛ ዓይነት ሽልማትን እንመልከት።

በግሪክ ቅኔ መመሰጥ፣ ሀሴት ማድረግና መደነቅ መቻል ምንም ጥርጥር

እና ጥያቄ የሌለው የግሪክን ቋንቋ የመማር ትክክለኛ፣ ቀሳዊ ያልሆነ ውጤት ነው፤ ሽልማት ነው። የግሪክ ቋንቋ የተማረ ሰው የሚያገኘው ሽልማት ነው። ነገር ግን የግሪክን ቅኔ እና ግጥም በማንበብ የሚገኘውን ደስታ እና መመሰጥ የሚሸለሙት የግሪክን ቋንቋ ከመማር በተጨማሪ የግሪክን ቅኔ ለመረዳት እና ለማጣጣም የሆነ ደረጃ ላይ የደረሱ ሰዎች ናቸው። ከእውቀትና ከልምዳቸው ተነስተው በግሪክ ቅኔ ውስጥ ስላለው ውበት እና ደስታ ሊነግሩን የሚችሉት እነሱ ብቻ ናቸው። የግሪክን ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን ጥቅም የሚውቁት ተምረው ጥቅሙን ያጣጣሙ ብቻ ናቸው። የግሪክ ቋንቋን የተማረ ሁሉ በግሪክ ቅኔ ሐሴት ወደማድረግ አይሄድም!

አንድ አፍቃሪ ከሚያፈቅራት ጋር በትዳር ለመተሳሰር እንደሚናፍቅ፣ አንድ የጦር ጄኔራል ለድል እንደሚዋጋ፣ የግሪክን ቋንቋ ሰዋስው መማር የጀመረ፣ በአሥራዎቹ ዕድሜ ውስጥ የሚገኝ ታዳጊ የግሪክን ቋንቋ መማር፣ በኋላ በጎልማሳነት ዕድሜ በግሪክ ቅኔ ለመመሰጥ፣ ለመደሰት እንደሚጠቅም እና በሶፍክለስ ተውኔት ሐሴት ማድረግ እንደሚያጎናፅፍ አይገባውም። ይሄን መሰል ድንቅ ነገር እንደሚጠብቀው አውቆ፣ በትምህርቱ ላይ አንዳች ትጋት አይጨምርም። ለዚህ ታዳጊ አሳሳቢው ነገር ውጤት ነው። በየቀኑ በሚሰጠው ትምህርትና ፈተና ላይ ጥሩ በመሆን መንገዱን ይጀምራል። ወይም ደግሞ በጀመረው ትምህርት ላይ ወለም ዘለም ቢል የሚጠበቀውን ቅጣት ፈርቶ ይተጋል። ወይም በትምህርቱ ስኬት ወላጆቹን ደስ ለማሰኘት ይሰራል። ወይም ከምንም ነገር በላይ፥ አሁን በምናቡ ምን እንደሆነ ሊስለው ወይም በልቡ ሊመኘው የማይችለው፣ ነገር ግን የግሪክን ቋንቋ መማር የሚያስገኘውን መልካም ነገር እያሰበ ሊማር ይችላል።

አሁን ያለውን፣ የያዘውን ፍላጎት ከመዘንን፣ በጥቅማ ጥቅም መነዳት ጋር የተመሳሰለ ነው። እየተማረ ላለው ትምህርት የማይመጥን መሻት እየመራው ነው። የዚህ ተማሪ ሁኔታ እና ለማዕረግ እድገት፣ ጥቅማጥቅም የሚወጋ ወታደር ተመሳሳይ ናቸው። አንድ ናቸው። እንደዛም ሆኖ ግን፥ የግሪክን ቋንቋ በመማሩ ብቻ፥ ፈለገውም አልፈለገውም፥ ተፈጥሮአዊ የሆነ ሽልማት ከፊቱ ይጠብቀዋል። በየቱም ምክንያት ይማር የግሪክን ቋንቋ መማሩን ተከትሎ የሚመጣ የተገባ ሽልማት ይጎናፀፋል። የግሪክን ቋንቋ በመማሩ ብዙ ጥበብ ይሸለማል! ነገር ግን የግሪክ ቋንቋ በመማሩ የተገባውን ሽልማት ደርሶ እስኪያገኝ ድረስ ምንም አያውቅም። በእርግጥ፥ ቀስ በቀስ እያገኘ ይመጣል። ቀስ በቀስ የግሪክን ቋንቋ የመማር ደስታ፥ ለፈተና ውጤት፣ ለወላጆቹ ብሎ እና ከቅጣት ለማምለጥ

የመሳሰሉትን አሰልቺ ምክንያቶች መተካት ይጀምራል። እና ማንም ሰው እነዛ አሰልቺ ምክንያቶች እንደጨዛ የተነኑበትን እና የግሪክን ቋንቋ በመማር ውስጥ ያለውን ደስታ ማጣጣም የጀመረበትን ትክክለኛ ጊዜ ሊናገር አይችልም። ወደ ሽልማቱ በቀረበ መጠን፣ የግሪክን ቋንቋ መማር ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ማጣጣም ስለጀመረ ብቻ፣ ለየትኛውም ጥቅማጥቅም ብሎ ሳይሆን የግሪክን ቋንቋ፣ ቋንቋውን ለማወቅ ለሆነ ዓላማ መማር መፈለግን ይችል ይጀምራል። ቋንቋውን ለቋንቋ ዓላማ የመፈለግ ችሎታ ይኖረዋል። እሱ ስለወደደው ብቻ ነው። እንደውም የግሪክን ቋንቋ መማር ውስጥ የሚገኘውን ደስታ ማጣጣም በመጀመሩ ለመማር መፈለግ መቻል በራሱ የመጀመሪያ ሽልማት ነው።

ክርስቲያን መንግስተ ሰማያትን በተመለከተ ያለው አስተሳሰብና አካሄድ፣ ከዚህ ታዳጊ ተማሪ ሁኔታ ጋር ተመሳሳይ ነው። ወደ እግዚያብሔር የህልውና እቅፍ በመግባት፣ በመንፈሳዊ ልምምድ ጥልቀት፣ የዘላለም ሕይወት ምን ማለት እንደሆነ በአብርሆት የተረዱ ብቻ፣ የመንግስት ሰማይ ተስፋ ከንቱ ማባበያ እንዳልሆነ፣ ይልቁንም ዋጋ ከፍለው ላለፉበት የደቀመዝሙር ሕይወት፣ የጫጉላ ጊዜ፣ ከሙሽራው ጋር የሚገናኙበት ወቅት መሆኑን ይረዳሉ። በሌላ ጎኑ ደግሞ ወደዚህ መረዳት ያልመጣን ይህንን ልናውቅ አንችልም። እንደውም ከነጭራሹ ያንን የመረዳት አቅም የለንም። ያንን መረዳት የምንችለው በመታዘዝ ሕይወት በመቀጠል ብቻ ነው። የመታዘዛችን የመጀመሪያ ሽልማት በሕይወታችን ከተገኘ ብቻ ነው። የመታዘዛችን የመጀመሪያ ሽልማት ደግሞ በሰማይ የሚጠብቀንን ተስፋ፣ የመጨረሻውን ሽልማት ለማግኘት ያለን ርሃብ እያደገ መሄድ ነው። የዚህ ርሃብ መጠን እየጨመረ መሄድ፣ በሕይወታችን ውስጥ ከተገኘ ብቻ ነው። ይህ ከሆነ ብቻ የተስፋውን እውነተኝነት እንረዳለን። በሰማይ የተዘጋጀልንን ሽልማት ለማግኘት ያለን ረሃብ በጨመረ ቁጥር፣ “እግዚያብሔርን የፈለኩት ለዚህ ብቻ፣ ለራሴ ጥቅም ነው” የሚለው ፍርሃት ከላያችን ይወገዳል። ፍርሃታችንን እንደከንቱ ነገር እንቆጥረዋለን! መንግሥተ ሰማያትን ለማግኘት ያለን ፍላጎት ለእግዚአብሔር ካለን ፍቅር የተቀዳ ተፈጥሮአዊ ውጤት መሆኑን እንገነዘባለን። ምናልባት ይሄ የሕይወት ልምምድ፣ ለብዞዎቻችን ማለት እችላለሁ፣ በአንድ ጊዜ ከመቅፅበት የሚሆን አይደለም። በአንድ ማታ አይመጣም። ማዕበል መሬት ላይ የቆመውን መርከብ ቀስ በቀስ እንደሚያነሳ፣ ቅኄም ሰዋሰውን እንደሚተካ፣ ሕግም በወንጌል እንደሚለወጥ፣ ጥልቅ ርሃብም መታዘዝን እንደሚያመጣ እንዲሁ የእኛም ለውጥ ሂደታዊ ነው።

በእኛ እና በታዳጊ ተማሪው ልጅ መካከል አንድ ዓይነት ወይም ተመሳሳይ የሆነ ሌላ ዋና ነገር አለ። ለምሳሌ ይህ ታዳጊ ልጅ የምናቡ ስፋት ከፍተኛ ከሆነ፣ የግሪክ ሰዋስው መማር የእንግሊዝ ባለ ቅኔዎች እና ደራሲያንን በማንበብ የሚገኘውን ደስታ የሚመሳሰል ደስታ እንደሚያስገኝ መገንዘብ ከመቻሉ ቀደም ብሎ፣ ለእድሜው ተስማሚ በሆኑ የእንግሊዝ ባለቅኔዎች እና ደራሲያን ሥራ ማንበብና በነሱ መመጥሰ ጀምሮ ይሆናል። ምናልባትም የግሪክ ሰዋስው ትምህርቱን ማጥናት ትቶ ፤ ይልቁንም ሁለት ታዋቂ የእንግሊዝ ገጣሚዎች የሆኑትን የሼሊ እና ስዊንበርን ሥራዎችን በድብቅ እያነበበ ነው። በሌላ ቀላል አነጋገር፣ ይህ ታዳጊ ተማሪ የግሪክ ቋንቋ መማርን የበለጠ እንዲፈልግ የሚያደርግ ፍላጎት በውስጡ አለ። ነገር ግን ይህ ፍላጎት በግሪክ የሰዋስው ትምህርት ክፍለ ጊዜ ከሚማራቸው፣ የታላቁ የግሪክ ፈላስፋና የታሪክ ሙሁር ሥራዎች እና የግሪክ ግስ ትምህርቶች ጋር ግንኙነት ያላቸው አይደሉም። ክፍሉ ውስጥ የሚሰጠውን የግሪክ ሰዋስው ትምህርት ላይወደው ይችላል። በአጭር ቃል ወደፊት የግሪክ ቋንቋን በመማር የሚያገኘውን የግሪክን ባለቅኔዎች እና ደራሲዎችን ሥራ አንብቦ አእምሮውን የማስፋትና ሀሴት የማድረግን ነገር አስቀድሞ በሀገሩ ቋንቋ ሥራዎች ውስጥ ስለአገኛቸው፣ በክፍል ውስጥ የሚሰጠው የግሪክ ሰዋስው ትምህርት ባይመስጠውም፣ በሀገሩ ቋንቋ ያነበባቸው ቅኔዎች፣ ታሪኮችና አፈ ታሪኮች፤ ተመሳሳይ ቅኔዎች፣ ታሪኮችና አፈ ታሪኮች በግሪክ ቋንቋም የማንበብ ፍላጎት ውስጥ ከተውታል። ከክፍል ውስጥ የግሪክ ሰዋስው ትምህርት አላማ ጋር ባይገናኝም፤ የግሪክ ቋንቋን የመማር ርሃብ ውስጡ ገብቷል።

ያለምንም ጥርጥር ታዳጊውን ተማሪ ያነፃፀርኩበት መንገድ በአንድ ጉዳይ ጉድለት አለበት። የግሪክ ሰዋስው ትምህርቱን ማጥናት ሲገባው፣ በእንግሊዘኛ ቋንቋ የተፃፉ ቅኔዎችን ማንበቡ፣ በኋላ በትምህርት ቤት መማሪያ መጽሐፉ ላይ የግድ እንደሚያነባቸው የግሪክ ቅኔዎች፤ በተመሳሳይ መልኩ በእንግሊዘኛ የተጻፉትም ጠቃሚ ሊሆኑ ይችላሉ።ሚልተንን ቅድሚያ ሰጥቶ ኤሺለስ መተዉ ብቻ የተሳሳተ ነገር ነው ያደረገው አያስብለውም። በግሪክ ከተፃፉ የቅኔ እና የድርሰት ሥራዎች ይልቅ በሀገሩ ቋንቋ የተፃፉ የቅኔ እና የድርሰት ሥራዎችን ማንበቡ ዓላማውን ስቷል አያስብለውም። ነገር ግን የእኛ ጉዳይ የተለየ ነው። የእኛ ተጨባጭ መዳረሻ፣ ጊዜያዊ የሆነውን፣ ውስን የሆነውን መልካም ነገር ተሻግሮ የሚያልፍ ነው ካልን፣ ማንኛውም አይነት ፍላጎታችን የተጣበቀበት መልካም ነገር በሆነ ያህል መጠን የተሳሳተ ነው። ስለዚህ በተቻለ አቅም ሁሉ ፍላጎታችን፣ መጨረሻ ላይ ሲያገኘው በሙላት ከሚረካበት ነገር ጋር ቀጥተኛ ግንኙነት ያለው ነገር መሆን አለበት።

የመጨረሻ ግባችን ጊዜያዊ የሆነውን ዓለም የተሻገረ ገደብ የለሽ መልካም ነገርን ማግኘት ከሆነ ሌላ ዓይነት ርካታ እና ልብ እፎይ የሚያሰብል እርካታ አሳሳች ነው። የመጨረሻውን እርካታ ከፈለን እንኳን ላያክልም።

በሩቅ ስላለው ሀገራችን፣ ለመንግስተ ሰማይ ስላለን ፍላጎት እና ናፍቆት በምናገርበት ጊዜ፣ የተወሰነ ዓይን አፋርነት ይሰማኛል። አግባብ ያልሆነ ድርጊት እንደፈጸመ ሰው እራሴን አቆጥራለሁ። ይህ ስሜት በሁላችንም ውስጥ አለ። እኔ ስለዚህ ነገር በመናገር፣ እያንዳንዳችን ውስጥ ያለውን፣ በቃላት ለማፅናናት እንኳን የማይቻለውን እና በሚስጥር የያዝነውን ጥልቅ እና ድብቅ ህመም ለማጋለጥ እየሞከርኩ ነው። ሁላችንም በውስጣችን የተሸከምነው ጥልቅ፣ ድብቅ ሚስጥር የደረሰብን ጉዳት ከፍተኛ ከመሆኑ የተነሳ፣ ናፍቆት፣ በስሜት እና ምናብ ጥልቀት ውስጥ የመሆን አመለካከት (Romanticism)፣ ወይም አለመብሰል በሚሉ ስሞች በመተካት ህመማችን ለመሸሸግ እንሞክራለን። ይህ ሚስጥር ሁላችንም የምንጋራው ሚስጥር ነው። ደግሞም እጅግ ሀሴት የሚሞላ ሚስጥር ነው። ከሆነ የቅርባችን ሰው ጋራ በምንሆንበት ጊዜ ይሄን ሚስጥር የመናገር እድላችን ሰፊ ነው። ነገር ግን ከመናገራችን በፊት እንደ መርበትበት ስለሚያደርገን እና በራሳችን ላይ ስለምንስቅ፤ ለመናገርም ዝም ለማለትም በመፈለግ ስሜት ውስጥ እንሆናለን። ስለነገሩ ለመናገር አንፈልግም። በእኛ ተሞክሮ ውስጥ በጭራሽ ታይቶ የማያውቅ፣ ተጨባጭ በሆነ ነገር ልናሳየው የማንችለው ፍላጎት በመሆኑ ስለነገሩ ለመናገር አንፈልግም። ደግሞም ልንደብቀው አንችልም። ውስጣችን የመንግስቱ ወራሽ አይደለህምን ስለምን ዝም ትላለህ ስለሚለን ደግሞም ልንደብቀው አንችልም። አንድ አፍቃሪ የሚያፈቅሯትን ሴት ድምጽ ሲሰማ ድብልቅልቅ ያለ ስሜት ውስጥ እንደሚገባ ምንም እንዳልተፈጠረ እንደሚሆን እኛም እንዲሁ እንሆናለን። እውነተኛውን ስሜታችንን እንሸሽጋለን። ግም ደግሞ ውስጣችን ያለው ፍላጎት ግልጥ ነው። የተለመደው አካሄዳችን ‹ውብ› ብሎ መሰየም እና በዚህ ሁኔታ መጥራታችን ብቻ ከጉዳዩ ጋር ተያይዞ ያለውን ውስብስብ ነገር እንደፈታን ይሰማናል።

የዋርድስዎርዝ አካሄድ፣ ትላንትና ወደ አሳለፋቸው ትዝታዎች በመሄድ የናፍቆቱን ምንጭ ለማግኘት መሞከር ነው። ይህ አካሄድ ግን ስህተት ነበር። ወደ እነዛ የትዝታ ወቅቶች ወደኋላ መመለስ ቢችል እና ቢያያቸው፤ በዛ የሚያገኘው ትውስታውን እንጂ ተጨባጩን የናፈቀውን ነገር አይደለም። እርሱ ያስታወሰው ነገር በራሱ ትውስታን ብቻ ሆኖ ያገኘዋል። በውስጣቸው ውበትን ሸሽገዋል ብለን የምናስባቸው መፅሐፍት እና ሙዚቃን በተመለከተ ያለው ነገርም ተመሳሳይ ነው።

እነዚህ ነገሮች የምንናፍቀውን ነገር ሊሰጡን እንደሚችሉ ካሰብን ተሸውደናል። እነርሱ በራሳቸው ውበት አይደሉም! የውበት መገለጫ ሐሳብ የሚያልፍባቸው እንጂ! በእነርሱ በኩል የምናገኘው ብቸኛ ነገር ስለነገሩ ያለን ናፍቆት ነው። ውበት፣ ያለፈ ጊዜ ትውስታ እነዚህ ነገሮች የምንመኘውን ነገር የሚያስረዱልን ጥሩ ምስሎች ናቸው። ናፍቆታችን ከልምምዶቻችን አልፎ የሚሄድ ነገርን ማግኘት ነው። አሁን ሙሉ በሙሉ ልንረዳው ወይም ልንገልጸው የማንችለው ነገር ለመጨበጥ ነው። ቅኔ፣ ሥነ ጥበብ፣ ሙዚቃ እና ሌሎች የጥበብ ሥራዎች የፍላጎታችን ምስል ምን እንደ ሚመስል በጨረፍታ የምናይበት ነው። በቃ በእነዚህ ነገሮች ውስጥ ስለ ምንናፍቀው ነገር ዝርዝር ሐሳቦችን ውብ በሆነ መንገድ ስለተቀመጠ ዋናውን ነገር እንዳገኘ ሰው ከረካን፤ ወደ ጣዖትነት ይቀየራሉ። የምንፈልገውን ስለማናገኝም ተስፋ መቁረጥ ውሰጥ ድባቴ ውስጥ ይከቱናል። እነዚህ ነገሮች በራሳቸው የምንናፍቀውን ነገር አይደሉም፤ ገና ያላገኘነው የአበባ መዓዛ፣ ያልሰማነው ሙዚቃ፣ የሩቅ ድምፅ የሚያስተጋቡ የገደል ማሚቶዎች ወይም ጎብኝተነው የማናቀው ሐገር ዜና ናቸው።

የሆነ አስማት የሚመስል ነገር ለመሥራት እየሞከርኩ ይመስላችኋል። ምናልባት እየሞከርኩ ይሆናል። ነገር ግን በተረቶች ላይ ብዙ ጊዜ የሚባለውን እናስታውስ። ድግምት፣ ወይም አስማት እርግማንን ለማፍረስ እና መልሶ ደግሞ ለመፍጠር ጥቅም ላይ ሊውል ይችላል። እኔ እና እናንተ ለአንድ ምዕተ አመት ለሚሆን ዘመን በሙሉ ተጽዕኖ ያሳደረብንን፣ በአለማዊ ነገሮች ላይ አብዝቶ የማተኮር እርግማንን ለመስበር ኀይለኛ አስማት ያስፈልገናል። አብዛኛዎቹ ትምህርቶቻችን እና ዘመናዊ አስተሳሰባችን በዚህ ምድር ላይ ካለው ሕይወት የበለጠ ብዙ ነገር አለ የሚለውን የውስጣዊ ድምጽ ችላ እንድንል ተደርገው የተዘጋጁ ናቸው። በሌላ ጎኑ ደግሞ እነዚሁ ሁሉ ነገር እዚሁ ምድር ላይ ነው የሚያበቁት እያሉ የሚሰብኩ፣ የእድገት እና የዝግመተ ለውጥ ፍልስፍናዎች (philosophies of Progress or Creative Evolution) ራሳቸው እውነተኛ ግባችን ሌላ ቦታ መሆኑን ለእውነት ያለፍላጎት መመስከራቸው አስደናቂ ነው። መጀመሪያችንም መጨረሻችንም ምድር ብቻ እንደሆነች ሊያሳምኑን ሲሞክሩ የሚጠቀሙትን ቃል ልብ ብለን እንስማ! አንድ ቀን የሰዎች ኑሮ እየተለወጠ እና ሰላም እየበዛ ሲሄድ ምድር እራሷ መንግስተ ሰማይ ትሆናለች ይላሉ!ምድር እራሷ መንግስተ ሰማይ ትሆናለች ምን አመጣው!?የሚሰማችሁን የመፃተኝነት ስሜት ለማስረሳት ይህች ትንሽ ነች ውሎ አድሮ ወደፊት ወደ ፍጽምና እናደርሳለን የምትል ሾርባ ያጠጧችኋል። ምድር በሁሉ ነገር ተለውጣ ወደ ተሻለ ነገር እንደምትሄድ ተስፋ

ይመግባችኋል። በመጨረሻም፣ ጊዜያዊ ከሆነው ዓለም ያለፈ ምኞት በውስጣችሁ እንዳይነሳሳ እና ሁሉንም ነገር እንዳያበላሽ፣ ምንም እንኳን ተስፋ የገቡት ሁሉ ደስታ በምድር ላይ ቢመጣ፣ የሆነው ሆኖ፣ እያንዳንዱ ትውልድ የመጨረሻው ትውልድ ሳይቀር ማምለጥ በሌለው የሞት እጅ መጥፋቱ እንደማይቀር፣ በዚህ ምድር ላይ የሚሆነው ታሪክ ሁሉ ወደ አመድነት መቀየሩ ጥርጥር እንደሌለው፤ ምንም ታሪክ ሳይኖር ለዘላለም እንደሚጠፋ እንዳታስታውሱ ያሳምንልናል ያሉትን ቋንቋ ሁሉ ይጠቀማሉ። ለምሳሌ ሚስተር ሻው በሊልዝ ገጸ ባሕሪ በኩል በተውኔቱ መጨረሻ ንግግር ውስጥ ያካተተው የማይመስል ንግግር፤ ለምሳሌ በርግሰን የሕይወት ኋይል ማናቸውንም መሰናክሎች ምናልባትም ሞትንም ጨምሮ የማለፍ አቅም አለው በማለት ያቀረበልንን ንግግር ብንወስድ፣ በምድር ላይ በማሕበራዊም ሆነ በሥነ ሕይወት (biological development) መስኮች የሚደረጉ ማናቸውም መሻሻሎች የፀሐይን የማይቀር የእርጅና ሂደትን ሊያራዝሙ ወይም የሁለተኛው የቴርሞዳይናሚክስ ሕግ የሚያስከትለውን የማይቀር ውጤት ሊያስቀር እንደሚችል የምናምላቸው ይመስላቸዋል።

እነርሱ የፈቀዱትን፣ ማለት የፈለጉትን ይበሉ! በማንኛውም ምድራዊ ደስታ የማይሟላ፣ ከዚህ ምድር ውጪ የሆነ ነገርን የሚፈልግ ናፍቆት፣ በውስጣችን እንዳለ እናውቃለን። ነገር ግን በተጨባጭ፣ ይህ ናፍቆት ወደ ሙላት እንደሚመጣ ወይም የናፈቀውን ነገር እንደሚያገኝ እርግጠኛ የሚያደርገን፣ እምነታችንን መሠረት የምናደርግበት ምክንያት አለ? "ስለራበን ብቻ ምግብ እናገኛለን ወይም ምግብ እንዳለን ማረጋገጫ አይደለም።" ይሁን እንጂ አንድ ሰው ይህ አመለካከት ዋናውን ጉዳይ ሳይመለከት ድምዳሜ ላይ የደረሰ ነው ብሎ ሊከራከር ይችላል። እውነት ነው የአንድ ሰው በአካል ሥጋው መራቡ የሚበላውን ዳቦ እንደሚያገኝ ማረጋገጫ አይደለም። በአትላንቲክ ውቅያኖስ ጀልባ ላይ በርሃብ ተዝለፍልፎ እስከወዲያኛው ላይመለስ ሊያሸልብ ይችላል። ነገር ግን የአንድ ሰው በአካል ሥጋ መራብ የሚያረጋግጥልን ይህ ሰው የመጣው አካል ሥጋውን በመመገብ እንደገና ከሚጠግን እና ለምግብነት የሚውሉ ቁሳቁሶች በሚገኙበት ዓለም ውስጥ ከሚኖር ዘር እንደሆነ ማረጋገጫ ነው። በተመሳሳይ ሁኔታ፣ ወደ ገነት ለመግባት ያለኝ ፍላጎት ገነት እንደምገባ እና በዛ ሐሴት እንደማደርግ (ቢሆን ምኞቴ) ነው፡ ፡ ማረጋገጫ እንደሆነ ባላምንም፤ እንደማስበው ግን ገነት የሚባል ነገር እንዳለ እና አንዳንድ ሰዎች መኖሪያቸው በዛ እንደሚሆን በጥሩ ሁኔታ የሚያመላክት ነው። አንድ ሰው የሆነች ሴትን ሊያፈቅር ግን ያፈቀራትን ሴት ላያገኝ ይችላል። ነገር ግን ከተቃራኒ ፆታ ጋር "በፍቅር መውደቅ" የሚባል ኩነት፣ ተቃራኒ ፆታ የሚባል

ነገር በሌለበት ዓለም ውስጥ ቢከሰት ክው የሚያደርግ፤ ግራ አጋቢ ነገር ይሆን ነበር። አሁን እዚህ ፍላጎት እና ናፍቆት ብቻ አለ። ይሄ ይሆን ያ ይሆን፣ እያለ በሃሳብ የሚዋትት ፍላጎት እና ናፍቆት አለ። ስለሚናፍቀው ነገር እርግጠኝነት ግን የለውም። በዋናነት ዒላማው በትክክል ወደሚገኝበት አቅጣጫ ለማወቅ አቅም የጎደለው ናፍቆት! ቅዱሳን መጽሐፎቻችን ስለምንናፍቀው ቦታ የተወሰነ ዘገባ ይሰጡናል። እርግጥ ነው ስለቦታው ሙሉ መረጃ ሳይሆን ቢያንስ ካብራራው በሚል እንደ ምሳሌ የሆነ መለያ ያቀርባሉ። መንግስተ ሰማይ ማለት በመሠረታዊ ፍቺው ከእኛ ከሰው ልጆች መኖሪያ የጊዜ ክበብ እና ቦታ ውጪ ያለ ነገር ማለት ነው። ሆኖም ስለገነት፣ መንግስተ ሰማይ የሚሰጡ ማብራሪያዎች፣ ይህን ሊመስል ይችላል የሚሉ መግለጫዎች፣ ባጋጠመን ወይም በምናውቃቸው ነገሮች ላይ የተመሠረተ መሆን አለበት። ስለዚህ መፅሐፍ ቅዱሳዊው የመንግስተ ሰማይ፣ የገነት ምስል፣ ነፍሳችን ማንም እንዲህ አይነት ነው ብሎ ሳይነግራት መንግስተ ሰማይ ማለት እንዲህ አይነት ብላ የፈጠረችውን ምስል የሚደግፍ መሆን አለበት። በእውነቱ ገነት፣ መንግስተ ሰማያት ውስጡ በትክክለኛ እጅግ በሚያብረቀርቁ ድንቅ እንቁዎች የሞትላ አይደለም። በተፈጥሮ ውስጥ ያለውን ውብ ነገር ሆሉ ያካተተ ወይም ድንቅ የሙዚቃ ቅንብር የሚሰማበትም አይደለም። ልዩነቱ መፅሐፍ ቅዱሳዊው ስዕላዊ መግለጫ ለሰጠው መግለጫ ስልጣን አለው! ከእኛ ይልቅ ለእግዚያብሔር እጅግ ቅርብ ከሆኑ ጸሐፊዎች የመጣ ነው። ደግሞም በዘመናት መካከል በቅዱሳን ሕይወት ተፈትኖ የፀና እውነት ነው። ለዘመናት ክርስቲያኖች በወጥነት የታመነ እውነት ነው። ለእኔ፣ ለመጀመሪያ ጊዜ መፅሐፍ ቅዱስ ያቀረበው የገነት መስል ምንም እንኳን ስልጣን ያለው ብቸኛ እውነተኛ መግለጫ ቢሆንም ብዙም ስፍራ የሚሰጠው ሆኖ አላገኘሁትም። በመጀመሪያው እይታዬ ፍላጎቴን ከማነሳሳት ይልቅ እንደውም አቀዛቀዞት ነበር። በትክክል ልጠብቀው እና ልገምተው የሚገባኝ ያ ነው። ክርስትና በሩቅ ስላለው ሐገር፣ ገነት በራሴ ግምት እና መላምት እንዲህ ነው ብዬ ካሰብኩት የላቀ ነገር ሊነግረኝ ባይችል ኖሮ፤ ከፍ ያለ ቦታን አይይዝም ነበር። ሆኖም ግን ለእኔ በተጨማሪነት የሚሰጠኝ ነገር ካለ “ከራሴ መላምቶች” ዝቅ ያለ ማራኪነት እና አጓጉነት እንዲኖረው እጠብቃለሁ። የሼሊ ሥራዎችን ሲያነበር ለነበረ አንድ ወጣት፣ ለመጀመሪያ ጊዜ የሳፋክሊዝ ሥራዎች አግኝቶ ሲያነብ፣ ደረቅ እና አሰልቺ ሊሆኑበት ይችላል። ሃይማኖታችን እውነተኛ ነው፣ ከእኛ እውቀት እና ስሜት ውጪ በዘመናት በነገር ሁሉ ተፈትኖ የታመነ ነው (objective) ብለን የምናምን ከሆነ፤ እንግዲያውስ በሃይማኖታችን ውስጥ የሚገኙ እንቆቅልሽ የሆኑ እና አልፎ ተርፎም ደስ የማይሉ ጽንሰ ሐሳቦቸን እና ጉዳዮችን ለመመርመር መፍራት የለብንም። እንደውም ብዙ ጊዜ የማናውቀውን እና ልናውቀው የሚገባንን

የክርስትና እውነት ሸሽገው የሚይዙብን፣ በክርስትና ውስጥ ያሉ እንቆቅልሽ የሆኑ እና ትኩረት ሰጥተን ለመመርመር ምቾት የሚነሱን ጽንሰ ሐሳቦች ናቸው።

በቅዱሳት መጻሕፍት ውስጥ የሚገኙ የተስፋ ቃሎች እንዲሁ እንዳገኘናቸው ብንከፋፍላቸው በአምስት ዋና ዋና ጭብጦች ሊከፋፈሉ ይችላሉ። የተሰጠን የተስፋ ቃል፦ 1. ከክርስቶስ ጋር እንሆናለን 2. እርሱን ወደ መምሰል እናድጋለን 3. በብዙ ግልፅ እና ድንቅ ምሳሌዎች የ"ክብር" መጎናጸፊያን እንለብሳለን 4. ለእኛ አሁን በማይገባን መንገድ በሰማይ ድግስ፣ ምግብ እና ሐሴት ማድረግ ተዘጋጅቶልናል እና 5. በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ስልጣን እንይዛለን፤ ከተሞችን ማስተዳደር፣ በመላእክት ላይ መፍረድ እና በእግዚአብሔር ቤተ መቅደስ ውስጥ መጠቀሚያ አዕማድ ሆኖ ማገልገል። ስለነዚህ የተስፋ ቃሎች በመጀመሪያ ወደ አዕምሮዬ የሚመጣው ጥያቄ፣ "ከአንደኛው የተስፋ ቃል ውጪ ያሉት ሌሎች የተስፋ ቃሎች ለምን አስፈለጉ?" የሚል ነው። ከክርስቶስ ጋር ከሆንን በቂ አይደል ወይ፤ ከእርሱ ጋር እስካለን እንዳለን የምናስበው ሌላ ነገር፣ ወይ የሚያስፈልገን አለ? አንድ የጥንት ጸሐፊ እግዚያብሔር ደግሞም ሌሎች የሚታዩ እና የማይታዩ ሐብቶች ያሉት፣ እግዚያብሔር ብቻ ካለው ሰው የበለጠ ባለጠጋ አይደለም ያለው እውነት ነው። እግዚያብሔርም ሃብትም ካለው ጥሩ! እግዚያብሔር ብቻ ካለው ሌላ ምድራዊ ባለጠግነት ከሌለው፤ የሌለው ነገር እንደጎደለው አይቆጠርም።

እንደማስበው ከሆነ ይህን ነገር የበለጠ መረዳት መልሱ በምልክቶች አስፈላጊነት ዙሪያ የሚሽከረከር ይመስለኛል። ምንም እንኳን ነገሩን ለመጀመሪያ ጊዜ ስናውጠነጥን ወዲያውኑ ከትኩረታችን ሊሰወር ቢችልም፣ ብዙዎቻችን ልክ ስለሌሎቹ የተስፋ ቃሎች ያለን ሐሳብ ወይም ምስል ምልክታዊ እንደሆነው፤ ከክርስቶጋር ጋር መሆን ማለት ምን ማለት እንደሆነ አሁን በምናባችን ያለው ሐሳብ ወይም ምስል የው ምልክታዊ ነው። ካርታ እንጂ ትክክለኛው ነገር የለንም። ለምሳሌ ከክርስቶስ ጋር መሆን ማለት ምን ማለት ነው የሚለውን አካል ለአካል እንደ መቀራረብ እና ከአንድ ሰው ጋር በፍቅር ስንወያይ አይነት ያለ ውይይት ከእርሱ ጋር ስናደርግ ማለት እንደሆነ ወደ አዕምሮአችን ሽው ብሎ ይገባል። ከክርስቶስ ጋር ስለመሆናችን ስናስብ፣ ሰው በመሆኑ ላይ እናተኩርና፣ ደግሞ እርሱ አምላክ መሆኑን ልንዘነጋ እንችላለን። በመሠረቱ፣ በዚህ የመጀመሪያ ተስፋ ላይ ብቻ የሚያተኩሩ ክርስቲያኖች ብዙውን ጊዜ ከክርስቶስ ጋር መሆን የሚለውን ሐሳብ ምድራዊ ከሆኑ ነገሮች ጋር አያይዘው ሲያስቡት እናያለን። እንደእውነቱ፣ ሙሽሪት እና ሙሽራ በሰርጋቸው ቀን አብረው ሲሆኑ እንዳለው አይነት እና ለየት ያለ በፍቅር የተሞላ

ግንኙነት፣ እንዴት በፍቅር እንደሚተቃቀፉ አይነት ምስል ነው ያላቸው። እንደዚህ አይነት ምስል ስለኖራቸው አይፈረድባቸውም። እኔም ብሆን ለአንድ ደቂቃ እንኳን ለምን እንዲህ አይነት ምስል ኖራችሁ ብዬ አልነቅፋቸውም። እነዚህ ምስሎች የተሳሳቱ ወይም መጥፎ ናቸው እያልኩ አይደለም። ለአንዳንድ ሰዎች ከክርስቶስ ጋር ያላቸውን ግንኙነት ምን ሊመስል እንደሚችል እንዲረዱ ጠቃሚ ሊሆን ይችላል።

ከልቤ የምመኘው ነገር አሁን ከደረስኩበት መረዳት በላይ ጠልቄ መረዳት እንድችል ነው። ከክርስቶስ ጋር ስላለኝ ግንኙነት ጠለቅ ያለ ግንዛቤ እንዲኖረኝ እፈልጋለሁ እናም ወደ ፊት ይህን ለማድረግ እንድችል እጸልያለሁ። እኔ ግን ለማለት የፈለኩት ይህ ሁሉ ምልክት ብቻ ነው። ምሳሊያዊ፣ ምልክት ብቻ መሆኑን አፅንኦት መስጠት እፈልጋለሁ። በርግጥ በተወሰኑ ገጽታዎች ከክርስቶስ ጋር መሆን ምን ማለት እንደሆነ ያለን ምስል ከእውነታው ጋር ተመሳሳይነት አለው። ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት በአንዳንድ መንገዶች ከእውነታው ጋር ይመሳሰላል፣ በሌላ በኩል ግን የተለየ ነው። ስለሆነም በተሰጡት በሌሎች ቃል ኪዳኖች ውስጥ በሚገኙ ልዩ ምልክቶች ላይ በመመስረት ማስተካከያዎችን ማድረግ ያስፈልጋል። ከክርስቶስ ጋር ያለን ግንኙነት ያልተሟላ በመሆኑ፣ ይህን ጎደሎ ክፍተት ለመሙላት የሌሎቹ ተስፋዎችን እርዳታ እንፈልጋለን። ልዩ ልዩ ተስፋዎች መኖራቸው ከእግዚያብሔር ሌላ ደስተኛ የሚያደርገን ነገር አለ ማለት አይደለም። ከእግዚአብሔር ጋር ያለንን የመጨረሻ ደስታ የሚገልጹ የተለያዩ ተስፋዎች ስላሉ ብቻ፤ ከእግዚያብሔር ሌላ እውነተኛ ደስታ የሰጡን ናቸው ማለት አይደለም። እግዚያብሔር እንደ ሰው ስላይደለ፣ አሁን ካለን ግላዊ፣ ሰው ከሰው ጋር ያለው ደካማ የፍቅር ልምምዳችን፤ በእርሱ መገኘት ውስጥ ከምናገኘው ደስታ ጋር አንድ አይነት አድርገን እንዳንስል መጠንቀቅ አለብን። ጠባብ፣ አድካሚ እና ተደጋጋሚ ሊሆን ከሚችለው የሰው ፍቅር ልምዳችን አንፃር ብቻ እንዳናስበው እግዚአብሔር ፍቅሩን በተሻለ ለመረዳት እንድንችል የተለያዩ ምስሎችን ሰጥቶናል።

ቀጥዬ ክብር ወደሚለው ሐሳብ ልግባ። ይህ ሃሳብ በአዲስ ኪዳን እና በጥንታዊ የክርስትና ጽሑፎች ውስጥ በጣም ተደጋግሞ የተነሳ የታወቀ ሐሳብ ነው። ስለዚህ ልብ ልንለው የተገባ ሐሳብ ነው። ከዚህ ሐሳብ ልንሸሽ የምንችልበት ቦታ የለም። ድነት የሚለውን ሐሳብ በምስል ለማሳየት አዲስ ኪዳን መዳን ከዘንባባ ቅርንጫፎች፣ አክሊሎች፣ ነጭ ልብሶች፣ ዙፋኖች እና ታላቅ ብርሃናት ጋር ካሉ ነገሮች ጋር እያይዘ ያቀርብልናል። እንዲህ አይነት ምስሎችን መያዝ አዕምሮዬ ወዲያው ለመቀበል አልፈለገም። የሆነ ምክንያታዊ ሆኖ ለሚያስብ የሚመች

እይደለም። አልመሰጠኝም። እና በዚህ ረገድ እራሴን እንደማንኛው ዘመናዊ ሰው እቆጥራለሁ። ዘመናው ሰው (Modern age man) እንዲህ አይነት መግለጫዎች እንደ አፈታሪክ እና ተረት ይቆጥራቸዋል። “ክብር” የሚለው ቃል ሁለት ነገሮችን እንድመለከት ያደርገኛል። አንደኛው መጥፎ የሆነ ነገር ሲሆን፤ ሁለተኛው ሞኝነትን ነው። ወይም ደግሞ ክብር የሚለው ሐሳብ ዝነኝነት እና በጣም አይን የሚያጭበረብር ብርሃን ይመስለኛል። ቃሉን ስሰማ የሚመጣልኝ እርሱ ነው። እውነቱን ለመናገር፣ ዝነኛ ማለት ከሌሎች ሰዎች የበለጠ ታዋቂ መሆን ማለት በመሆኑ፣ ለእኔ ዝነኛ ለመሆን መፈለግ ጥሩ ያልሆነ ከሰው ጋር የመፎካከር አባዜ ስለሆነ ጤነኛ ከሆነ ልብ ሳይሆን ከክፋ የሚመነጭ ይመስለኛል። ሁለተኛው ደግሞ የሚያብረቀርቅ ብርሃን ይመስለኛል ብየለሁ። እና ማን ነው ዘላለም የሚኖር የመብራት አንፖል መምሰል የሚፈልግ?

ይህን ጉዳይ ጠልቄ በምመረምርበት ጊዜ እንደ ሚልተን፣ ጆንሰን እና ቶማስ አኩዊናስ ያሉ የተለያዩ ክርስቲያኖች ሰማያዊ ክብርን እንደ መልካም ስም ወይም መልካም እውቅና ማግኘት እንደሆነ ይረዱት እንደነበር ባወቅኩ ጊዜ እጅግ ተገረምኩ። ነገር ግን እንደኛው ፍጡር በሆኑ ሰዎች የሚሰጥ ዝና፣ ማረጋገጫ አይደለም። ደፍሬ መናገር እችላለሁ በእግዚያብሔር የሚሰጠን አድናቆት ነው። እና ከዚያ፣ በዛ ጉዳይ ላይ ካሰብኩበት በኋላ፣ ይህ ሃሳብ በመጽሐፍ ቅዱስ ላይ የተመሠረተ መሆኑን ተገነዘብኩ። እና በመክሊታቸው ነግደው ስላተረፉ እና መክሊታቸውን ስቀበሩ ሰዎች በሚያወሳው ታሪክ ላይ ያለውን አምላካዊ “መልካም፥ አንተ በጎ ታማኝም ባሪያ” የሚለውን ምሥጋና እና አድናቆት ማንም ሊፍቀው አይችልም። በዚህ የሕይወቴን አብዛኛውን ጊዜ ያቃጠልኩበት ሳስበው የነበረ ነገር፣ ለመጫወቻ በካርድ ተደርድሮ የተሰራ ቤት እንደሚናድ፣ በቀላሉ ተናደ። ወዲያው ማንም ሰው እንደ ልጅ ካልሆነ በቀር ወደ መንግስተ ሰማይ እንደማይገባ አስታወስኩ።ደግሞ በልበ ኩሩ እና ትእቢተኛ ልጅ ሳይሆን በመልካም ሥነ ምግባር ባደገ ልጅ ውስጥ እንደምናየው፣ ልጆች ሲመሰገኑ ሊደብቁት እስከማይችሉ ድረስ በመመስገናቸው ታላቅ እና ያልተሸፈነ ደስታቸውን ያሳያሉ። ልጆች ሲመሰገኑ ያላቸውን ደስታ ይደብቁም። ይህ ፀባይ ደግሞ በልጆች ውስጥ ብቻ አይደለም፣ ነገር ግን በውሾች እና በፈረሶች ውስጥም እናገኛለን።

ስለዚህ፣ ትህትና ነው ብዬ ያሰብኩት ነገር በዚህ ጊዜ ሁሉ በጣም ትሁት፣ እንደ ህፃን ልጅ ደስታ ያለ እና እጅግ ተፈጥሯዊ የሆነ ደስታን በሕይወቴ እንዳልለማመድ ከልክሎኛል ነበር። በእግዚያብሔር አንተ ጎበዝ ታማኝ ባሪያ የሚል

ሙገሳ ቃል መቀበል ብሎ ነገር አለ እንዴ ብዬ እራሴን እንደ ትሁት የቆጠርኩበት ነገር እጅግ ዝቅ ያለው ነገር እጅግ ከፍ ባለው ፊት፥ በሰው ፊት የእንስሳት መቦረቅ፣ የህፃን ልጅ በአባቱ ፊት መዝለል፣ ተማሪ በአስተማሪው ፊት መሳቅ ከመሰለ ፤ ንጹህ እና ተፈጥሯዊ የሆነውን ደስታ በሕይወቴ እንዳልለማመድ ከልክሎኝ ነበር። ነገር ግን ይህ እጅግ መልካም የሆነ የመመስገን ፍላጎት፣ በእኛ የማያባራ ሁሉ ነገር የራስ የማድረግ ሞኞት ምክንያት፣ እጅግ አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ተጠልፎ ላልተገባ ነገር እንደሚውል መረዳት ቀላል ነው። ወይም ከራሴ ልምድ ተነስቼ፣ በሕይወቴ ደስ ከማሰኛችው ሰዎች የሚቀርብልኝ ምሥጋና እና አድናቆት፣ እንዴት በፍጥነት አጥፊ እና ስብእናን አርካሽ በሆነው ራስን የመካብ ና የማድነቅ መርዝ እንደሚበከል ማየት ችያለሁ።

ነገር ግን ይህ ከመሆኑ በፊት፣ ለአፍታም ቢሆን፣ በጣም ለአጭር ጊዜም ቢሆን፤ በዚህ ጊዜ የእውነት ከልብ የምወደቸውን እና የምፈራቸውን ሰዎች በማስደሰት የሚገኘውን እርካታ ያየሁ ይመስለኛል። እና ያ እርካታ ንጹህ ነበር። እና ይህ ሁኔታ ማንም፣ ተስፋ ሊደርግ ከሚችለው በላይ ማለትም ተስፋ በማይደረግ መንገድ፣ ሊታመን በማይችል፣ ጭራሽ በማይታመን ሁኔታ በመጨረሻ፣ የዳነች፣ የተዋጀች ነፍስ ደስ እንደታሰኘው የተፈጠረችለትን እርሱን ደስ እንዳሰኘች ስታውቅ ሊሆን የሚችለውን ነገር እንድናስብ ካደረገን ከበቂ በላይ ነው። ከዚህ በኋላ ለከንቱነት ቦታ አይኖርም። ከዚህ በኋላ ኩራት አይሰማትም፡፡ ወይም ይህ የሆነው በድርጊቷ የተነሳ እንደሆነ አታስብም። ከዚህ ይልቅ እግዚያብሔር እንድትሆን አድርጎ በሰራት ማንነቷ ሐሴት ታደርጋለች። ቀድሞ የነበራት ለራስ ከፍ ያለ ግምት ይጠፋል። ወዲያው ቀድሞ የነበራት የበታችነት ስሜት ለዘላለም ሲፈወስ፤ በፕሮስፔሮ መጽሐፍ ውስጥ ካለው ኀይል እና ሚስጥር በላይ የነበራትን ኩራት እና እብሪትን ገደል ይከተዋል። ሰብሮ ትሁት ያደርጋታል። ፍፁም ትህትና አጉል ራሳችን ያበጀነውን ጨዋነት አይፈልግም። እግዚያብሔር የተሰራው ሥራ ልክ ነው ካለ፤ ሥራው በራሱ ደስተኛ ሊሆን ይችላል። እንደ አባባሉም “ከንጉስ ጋር እንመሰጋገን ብ፤ህ ሙገሳ ልትለዋወጥ መፈለግ የተገባ አይደለም”

አንድ ሰው መንግስተ ሰማይ ማለት እኛ ምሥጋና የምንቀበልበት፣ በእግዚያብሔር የምንወደስበት ቦታ ነው ማለቴን እንደማይወደው ሊነግረኝ እንደሚፈልግ መገመት እችላለሁ። ነገር ግን ይህን የእኔን ሐሳብ ካለመውደድ ጀርባ ሐሳቤን በትክክል እንዳይረዳ ያደረገው ዕብሪት አለ። በመጨረሻ፣ የአጽናፈ ዓለሙ ደስታ ወይም ጭንቀት የሆነው የመለኮት ፊት በእያንዳዳችን ላይ፣ ወይ

አንደኛውን ወይም ሌላኛውን ያንፀባርቃል፣ ወይ በቃላት ሊገለጽ የማይችል ክብር ያጎናጽፈናል ወይም የማይድን እና ለዘላለም የሚሆን ሀፍረትን ያለብሰናል። በቅርቡ እኛ እግዚአብሔርን እንዴት ነው የምናስበው የሚል ሐሳብ በጣም መሠረታዊ ነገር ነው በማለት የሚገልጽ አንድ መጣጥፍ አጋጥሞኛል። አንብቤ ነበር። “ይህ እውነት እንዳልሆነ በእግዚአብሔር እምላለሁ!” ይህ ትክክል አይደለም! ከዛ ይልቅ እግዚአብሔር ስለ እኛ ምን ያስባል የሚለው በጣም መሠረታዊ ነገር ብቻ ሳይሆን ነገር ግን ዘለዓለማችንን የሚወስን መሠረታዊ ነገር ነው። እንደ እውነቱ ከሆነ፣ እርሱ እኛን እንዴት ነው የሚያስበው ከሚል ሀሳብ ጋር በተያያዘ ምክንያት ካልሆነ በስተቀር፤ እኛ እርሱን እንዴት ነው የምናስበው የሚለው ሀሳብ ያን ያህል ጠቀሜታ የለዉም።

አንድ ቀን ሁላችን በፊቱ “እንደምንቆም”፣ በፍርድ ዙፋን ፊት እንደምንገኝ እና እንደምንመርምር ተጽፏል። የክብር የተስፋ ቃል፤ የተስፋ ቃል ነው፣ እጅግ አስገራሚ የሆነ፣ በክርስቶስ ሥራ ብቻ የሚቻል፣ አንዳንዶቻችን፣ እንዲያውም ሁላችንም በእውነት ይህን ለማድረግ የወሰንን በፍርድ ዙፋን ፊት የሚጠብቀንን ምርመራ አልፈን በቀኝ እንቆማለን፣ ተቀባይነትን እናገኛለን፣ እና እግዚአብሔርንም ደስ እናሰኛለን። እግዚአብሔርን ደስ ለማሰኘት... የመለኮታዊ ደስታ እውነተኛ አካል ለመሆን... በእግዚአብሔር ዘንድ ተወዳጅ ለመሆን፣ እንዲሁ ዝም ብሎ በሀዘኔታ ሳይሆን ነገር ግን አርቲስት በሥራው በእጆቹ ጥበብ እንደሚደሰት ወይም አባት በልጁ እንደሚደሰት እንደዛ ነው የሚሆነው! የማይቻል ይመስላል! አእምሮአችን ሊሸከመው ከሚችለው በላይ የሆነ የክብር መጎናጸፊያ ነው። ለእኛ ትልቅ ሸክም ነው። እውነታው ግን ያ ነው።

አሁን ምን እየተካሄደ እንዳለ ተመልከት። ስልጣን ያለውን እና መፅሐፍ ቅዱሳዊ የሆነውን የክብር ምስል አሽንቀጥሬ ጥዬ ቢሆን እና ምንም እንኳን ስለመንግስተ ሰማይ ያለኝ እውቀት ከዛ የተቀዳ ቢሆንም፣ ግልፅነት በሚጎድለው ከራሴ የመንግስተ ሰማይ ምስል ጋር ተጣብቄ ቢሆን ኖሮ፣ በእኔ ምኞት ውስጥ በነበረው የመንግስተ ሰማይ ምስል እና በክርስትና የተስፋ ቃል መካከል የነበረውን ግንኙነት በምንም ተዓምር ማየት አልችልም ነበር። አሁን ግን በቅዱሳን መጻሕፍት ውስጥ እንቆቅልሽ የሚመስሉትን እና ጥሩ ስሜት የማይሰጡትን ሐሳቦች ከመረመርኩ በኋላ፣ ወደ ኋላ መለስ ብዬ ሳስበው፣ ለራሴ በሚያስደንቀኝ ሁኔታ፣ ግንኙነቱ ጥርት ያለ እና ግልፅ ሆኖ አግኝቼዋለሁ። ትርጉም የሚሰጥ ሆኖ አግኝቼዋለው። ክርስትና ተስፋ እንዳደርግ የነገረኝ ክብር የመጀመሪያ ምኞቴን

የሚላ ነው። ስለ መንግስተ ሰማይ የምመኘውን ያካተተ ነው። እንደውም ከዚህ በፊት በምኞቴ ውስጥ የነበረ እኔ ግን ልብ ብዬ ያላየሁትን ነገሮች ሁሉ ገልጦልኛል። ስሆነ ያህል ጊዜ ስለ ምፈልገው ነገር ማሰብ በማቆም፣ አሁንም በተሻለ ሁኔታ በርግጥ የምፈልገው ነገር ምንድነው ብዬ መማር፣ መረዳት ጀምርኩ። ክላይ ክጥቂት ደቂቃዎች በፊት፣ ስለ መንፈሳዊ ነገር ርሀብ እና ናፍቆት ለማብራራት በሞከሩበት ጊዜ፣ አንድ እጅግ በጣም ትኩረት የሚስብ ፀባያቸውን አላካተትኩትም ነበር። ዘልዬው ነበር። ብዙውን ጊዜ ልዩ የሆነ ጊዜ ሲያልፍ፣ ሙዚቃ ሲቆም፣ ወይም ትዕይንቱ የሚያንፀባርቅ ድምቀቱን ሲያጣ እንዲህ ነበር ለካ እንላለን። ከዛ ቀጥሎ ስለሚሰማን ስሜት በደንብ የተገለጠው "ወደ መደበኛ፣ ትክክለኛ ማንነታችን የመመለስ ጉዞ" በሚለው የበኬት ሐሳብ ውስጥ ነው።

የምለው ነገር ተረድታችሁኛል። ስሆነ ደቂቃ ያህል እኛ ለዛኛው ዓለም የተገባን እንደሆንን የማሰብ ብዥታ ነበረን። አሁን እንዳልሆንን ተረድተናል። ዝም ብለን እየተመለከትን ነበር። ውበት ከተ ብላ ትስቅ ነበር ነገር ግን እኛ ለመቀበል አልነበረም። ፊቷ እኛ ወደ አለንበት መስመር አቅንቶ ነበር ነገር ግን እኛን ለማየት አልነበረም። ተቀባይነት አላገኘንም፣ የጋበዘን የለም ወይም ወደ ድግሱ፣ ጭፈራ ማንም አልወሰደንም። ደስ ካለን መሄድ እንችላለን ደስ ካላለን መቆየት እንችላለን። "ማንም ልብ አላለንም።" አንድ ሳይንቲስት እኛ ውበት ብለን የምንጠራቸው ነገሮች ስለማይንቀሳቀሱ ግዑዝ ስለሆኑ፤ ስለእኛ ግድ ባይኖራቸው አያስገርምም ሊል ይችላል። በርግጥ እውነት የሆነ ሐሳብ ነው። ነገር ግን እኔ እያወራሁት ያለሁት ግዑዝ ስለሆነው አካል አይደለም። ነገር ግን እነዚህ ግዑዝ ነገሮች በምንም ሊገለፅ የማይችል፣ ስሆነ ያህል ወቅት መልዕክት አድራሽ ሆነው ስለሚያስተላልፉት ነገር ነው። ስለ ግዑዝ ነገሮች ሳይሆን ከግዑዝ ነገሮች ስለምናገኘው ስሜት ነው የማወራው። ከመልዕክቱ ጣፋጭነት ጋር አብሮ የተቀላቀለ መራርነት የኖረበት ምክንየት መልዕክቱ ከመጀመሪያውንም ለእኛ ታስቦ የተዘጋጀ ስለማይመስል ነው። መራርነት ስል ህመም ማለቴ እንጂ የልብ መከፋት ቁጣ ማለቴ አይደለም።

ስለራሳችን ማንኛውንም ልዩ ትኩረት እንዲሰጡን ወይም እውቅናን ከሌሎች ለመጠየቅ ፍላጎት የሌለን መሆን አለብን። ግን እንደተገለልን ይሰማናል። በዚህ አጽናፈ ዓለም ውስጥ እንደ እንግዳ እንደተቆጠርን የሚሰማን ስሜት፣ እውቅና የማግኘት ፍላጎት፣ ምላሽ የማግኘት ፍላጎት፣ በእኛ እና በእውነታው መካከል ካለው ክፍተት ጋር የመገናኘት መሻት ማለቂያ የሌለው የምስጢራችን አካል ነው።

የነገሮች አካል መሆን እንፈልጋለን ነገር ግን፣ እንዳልሆንን ይሰማናል እና ይህ ደግሞ እኛ ሁላችን ሸሽገን የያዝነው አሳዛኝ ሚስጥር ነው። በእርግጠኝነት፣ በዚህ መንገድ የተብራራበትን ሁኔታ መሠረት አድርገን ስንመለከት ስለክብር የተገባው የተስፋ ቃል ጥልቅ ለሆነው መሻታችን የሚሰራ ነው። ክብር ማለት ስለእኛ በእግዚያብሔር የሚቀርብ ሪፖርት ማለት ነው። በእርሱ ተቀባይነት ማግኘት ማለት ነው። ምላሽ ማግኘት ማለት ነው። እውቅና ሲሰጠን ማለት ነው። ወደ ነገሮች ሁሉ አስኳል እንኳን ደህና መጣህ ተብለን አቀባበል የሚደረግልን! በመጨረሻም በሕይወት ዘመናችን ሁሉ ያንኳኳነው በር ይከፈታል።

ምናልባት ክብር ምንድን ነው ለሚለው ጥያቄ በእግዚያብሔር ዘንድ እውቅና ማግኘት ነው ብሎ መልስ መስጠት ሞኛት የማይሰጥ ነገር ሊሆን ይቸላል። ነገር ግን ይህ ሃሳብ እና ቋንቋ የአዲስ ኪዳን ሃሳብ እና ቋንቋ ነው። አዲስ ኪዳንም ተመሳሳይ ምላሽ እንደሚያቀርብ መመልከት እንችላለን። እኛ የምንፈልገው ወይም ቅዱስ ጳውሎስ ማለት አለበት ብለን የምንጠብቅበት እግዚአብሔርን የሚወዱ ሰዎች እግዚያብሔርን ያውቁታል እንዲል ነው፤ ነገር ግን በእርሱ ይታወቃሉ ይላል። (1ቆሮ. 8፡3) ይህ እንግዳ የሆነ ቃል ኪዳን ነው። እግዚአብሔር ሁል ጊዜ ሁሉንም ነገር አያውቅምን? ነገር ግን በሌላ በአዲስ ኪዳን ክፍል ውስጥ አስፈሪ በሆነ ሁኔታ ድጋሚ ይህ ሐሳብ ተጠቅሷል። በዛ ቦታ ላይ ከእኛ መካከል ማናችንም ልንሆን እንችላለን ግን በእግዚአብሔር ፊት ቆመን “ከቶ አላወቅኋችሁም ከእኔ ራቁ” የሚለውን አስፈሪ ቃል ልንሰማ እንደምንችል ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶናል። በሌላ አነጋገር እና ትርጉም አዕምሮአችን ሊረዳው የማይቻለው፤ ስሜታችን ደግሞ የማይቋቋመው፣ በሁሉም ቦታ ከሚገኝ ከእርሱ ህልውና ፊት ልንወገድ እና ሁሉን ከሚያውቅ ከእርሱ እውቀት ልንፋቅ እንችላለን። ለዘላለም ዘላለም ወደ ደጅ ተጥለን ልንተው፣ ልንገፋ፣ ልንሰደድ፣ ልንነጠል እና በንግግር ለማስረዳት በሚያዳግት ፣ ህመሙ በቃላት ሊገለጥ በማይችል ሁኔታ ይተወናል፣ እንዘነጋለን። በሌላ በኩል ደግሞ በልዑል እግዚአብሔር ወደ ውስጥ ልንጋበዝ፣ አቀባበል ሊደረግልን፣ ስፍራ እና እውቅና ሊሰጠን ይችላል። በየቀኑ፣ በእነዚህ ሁለት ትላልቅ አማራጮች መካከል እንገኛለን። በእውነቱ፣ በአጽናፈ ዓለሙ ውስጥ ካለ አንዳች ነገር ቆርጦ ጥሎን ከተለያየንበት፣ ሁልጊዜ ከበሩ አንዳች ጥግ ከደጅ ቆመን ወደ ውስጥ ከምንመለከተው አንዳች ነገር ጋር ዳግም የምንዋሃድበት ነው። በሕይወት ዘመናችን ሁሉ የነበረን ናፍቀት እና የነፍሳችን ርሃብ የአዕምሬሮ ቅዠት፣ አስቂኝ ነገር ፣ ስሜታዊነት ሳይሆን ነገር ግን የእኛ ትክክለኛ ሁኔታ ነጸብራቅ መሆኑ ይገለጣል። በተጨማሪም፣ መጨረሻ ላይ ወደ ውስጥ መጠራት፣ በሩ ተከፍቶልን

መግባት እና በምንም ሊገለጥ በማይችል፣ አእምሮን ሁሉ የሚያልፍ ክብር ማግኘት መዳረሻችን ነው። ልዩ ስፍራ ማግኘት ግባችን ነው። ይህ የሚሆንበት ሰዓትና ቀን ሲመጣ የሕይወት ዘመናችን ህመም ሁሉ ይፈወሳል።

ይህ ደግሞ ወደ ሌላኛው ክብር ማለት ምን ማለት ነው ወደሚለው ፍቺ ያመጣኛል። ክብር እንደ እንደሚያብረቀርቅ ብርሃን፣ እንደ ታላቅ ግርማ፣ እና ድምቀት! እንደ ፀሐይ ልናፀባርቅ ነው፤ የማለዳ ኮከብ ሊሰጠን ነው። ትርጉሙን መረዳት እንደጀመርኩ አምናለሁ። ይሄ ነገር ሳይገባኝ አይቀርም። በተወሰነ መንገድ፣ እግዚአብሔር የማለዳ ኮከብን አስቀድሞ ሰጥቶናል፤ ይህን ስጦታ በብዙ ውብ ጠዋት ማልደን ከተነሳን አይተን ማድነቅ እንችላለን። እንዲህ ብለን ልንጠይቅ እንችላለን፤ ከዚህ በላይ ምንድን ነው የምንፈልገው? ኦ! እረ ብዙ እንፈልጋለን! የበለጠ ነገር እንመኛለን! የሥነ ውበት መፅሐፍት ብዙ የማይናገሩለት እጅግ ብዙ ነገር፣ ተጨማሪ እንፈልጋለን! ነገር ግን ባለቅኔዎች እና የአፈታሪክ ጠበብቶች ስለዚህ ነገር በደንብ ያውቃሉ! እግዚያብሔር በሚያውቀው፣ ውበትን አይተን ብቻ ማለፍ፣ ምስክር ብቻ መሆን አንፈልግም! ምንም እንኳን ያ በራሱ ከበቂ በላይ ቢሆንም። በቃላት እንዲህ ነው ብለን ለማስቀመጥ የሚከብደን አንዳች ነገር እንፈልጋለን። ከምናየው ውበት ጋር አንድ ለመሆን፣ ራሳችንን በውስጧ ለማስገባት፣ ወደ እኛነታችን ጥልቀት ውስጥ ልንቀበላት፣ በእርሷ ልንታጠብ፣ እና የእርሷ አካል ለመሆን እንፈልጋለን! አንድ መሆን እንፈልጋለን! ለዛም ነው ! እንዲህ ጥልቅ መሻት ስላለን ! እንደ ሰው ለውበት እንዲህ አይነት ናፍቆት ስላለን፣ አየሩን እና መሬቱን እና ባሕር እና የብሱን በአማልት ብዛት የሞላነው! በጣኦታት፣ ኒሚፌስ እና ኤልቪስ የጥለቀለቅነው! ምንም እንኳን እኛ ባንችልም እነዚህ የእጆቻችን ሥራ ምስሉ ከተፈጥሮ የተገኘውን ውበት፣ ፀጋ እና ሃይል ማጣጣም ይችላሉ። ሊደሰቱበት እና ሊያሳዩ ይችላሉ። ለዚህም ነው ገጣሚዎች እንደዚህ አይነት አስማታዊ የፈጠራ ወሬዎችን የሚያውብለበልቡት። በብዕራቸው ጉልበት ሲገልጡት፣ እውነትም የምዕራብ ንፋስ ወደ ሰው ልጅ ነፍስ ውስጥ ከፍቶ የሚገባ ይመስላል። ነገር ግን አይችልም እኮ! እንዲህ ይሉናል “በሚያጉረመርም ድምፅ የተወለደ ውበት” ወደ ሰው ልጅ ይጋባል ላሉ! ነገር ግን አይችልም ! ወይም እስከምናውቀው ድረስ አሁን አልተጋባም።

በመጽሐፍ ቅዱስ ውስጥ ያለውን ተምሳሌታዊ እና ስዕላዊ መግለጫዎች በቁም ነገር ካጤን፣ አንድ ቀን እግዚአብሔር የማለዳ ኮከብ እንደሚሰጠን ፣የፀሐይን ብርሃን እንድንለብስ እንደሚያስችለን ካመን፣ ሁለቱም ማለትም ጥንታዊ

አፈ ታሪኮችም ሆኑ የዘመኑ ቅኔዎች የተሳሳቱ ሙሉ በሙሉ ልክ የሆኑ ባይሆኑም፣ የወደፊቱን ከመተንበይ አንፃር ወደ እውነት የቀረቡ ሊሆኑ ይችላሉ። በአሁኑ ጊዜ፣ እኛ የምንኖረው ከውጪኛው ክፍል፣ ትክክል ባልሆነው የመግቢያ በር ላይ ነው።የማለዳውን አዲስነት እና ንፅህና ልንገነዘብ እንችላለን። ነገር ግን ማለዳው አዲስ እና ንፁህ አያደርገንም! ከምናየው ግርማ ጋር መቀላቀል አንችልም። ሆኖም፣ የአዲስ ኪዳን ገፆች ይህ የማይሆንበትን እንዲህ መሆን የሚበቃበት ጊዜን በሹክሹክታ ይናገራሉ። የእግዚአብሔር ፈቃድ ከሆነ አንድ ቀን እንገባለን። ነገር ግን ግዑዛኑ ያለ ሕይወት ሆነው ሰጥ ለጥ ብለው እንደሚገዙ፣ የሰው ልጆች ነፍሶች በፈቃደኝነት በፍፁምነት ሲገዙ፣ መገዛታቸውን ተከትሎ የክብርን ካባ ይለብሳሉ። ተፈጥሮ የመጀመሪያዋ ረቂቅ የሆነችበት የበለጠውን እና ታላቁን የክብር ሸማ ይለብሳሉ። አንድ ነገር እንዳታስቡ ከወዲሁ ማስጠንቀቅ እፈልጋለሁ። እኔ እዚህ ምንም አይነት የአረማዊ ሕዝቦችን ከተፈጥሮ ጋር መዋህ እያሉ የሚሉትን ሐሳብ ይዤ አልመጣሁም። ተፈጥሮ የምትከስም ነገር ነች። እኛ ከእርሷ ይልቅ ዘላለም እንኖራለን። ሁሉም ፀሐይ፣ ከዋክብት እና በሰማይ እና በምድር ያሉ ነገሮች ሁሉ ተጠቅልለው ሲጠፉ እያንዳንዳችን ግን እንኖራለን። ተፈጥሮ እንደ ካርታ፤ ምስል ነው። ምልክት ነው። ነገር ግን ቅዱሳት መፅሐፍት እንድጠቀም የፈቀዱልኝ ምስል ነው። እርሷ ሙሉ በሙሉ ወደ ምታንፀባርቀው ክብር፣ ከእርሷ አልፈን በመሄድ፣ በተፈጥሮ ውስጥ እንድንጓዝ ተጠርተናል።

ከተፈጥሮ ዓለም ባሻገር ባለ ቦታ፣ ከሕይወት ዛፍ እንካፈላለን። አሁን በክርስቶስ ዳግም ከተወለድን በውስጣችን ያለው መንፈስ የሚኖረው በእግዚያብሔር ነው። አዕምሮአችን፣ በተለይም አካለ ሥጋችን ሕይወትን የሚያገኘው ከእርሱ ነው፤ነገር ግን አሁን ህይወትን የሚያገኘው በብዙ ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች ነው። ቀጥተኛ ባልሆኑ መንገዶች ስል በቅድመ አያቶቻችን፣ በአመጋገባችን እና በንጥረ ነገሮች ማለቴ ነው። ሥጋችን በዚህ ይኖራል። ሥጋዊ ደስታ እግዚአብሔር ዓለምን በፈጠረበት ጊዜ በግዑዝ ላይ ያስቀመጠው ኃያል ረቂቅ፣ ሩቅ ውጤቶች ናቸው። እግዚያብሔር በመፍጠር ውስጥ ካለው ታላቅ ደስታ ፈለቀ፤ እነዚህ ሃይሎች ዛሬ የምናውቃቸውን የአካላዊ ደስታ ልምዶችን አስከትለዋል። እንደዚያም ሆኖ፣ ተዳክመው እንኳን፣ አሁን ካለን አቅም በላይ ናቸው። ልናስተዳድራቸው ከምንችለው በላይ ናቸው። በዝቅተኛ ደረጃዎች ውስጥ እንኳን ያለ እንደዚህ አይነት ማራኪ እና አስደሳች የሆነበት፤ ከወንዙ ምንጭ በቀጥታ መቅመስ ምን ሊሆን ይችላል? አዎን! እንደማምነው ከፊታችን የተቀመጠው ነገር ይህ ነው! ሁሉም ሰው ከደስታ ምንጭ ደስታን ይጠጣል።

ቅዱስ አጎስጢኖስ እንደገለጸው የዳነች ነፍስ ስትነጠቅ የከበረውን አካል "ታጥለቀልቃለች" አሁን ካለን ልዩ እና ብልሹ ምኞቶች አንፃር፣ ይህንን የደስታ ጎርፍ ልንረዳው አንችልም፣ እናም ሁሉም ሰው እንዳይሞክር አጥብቄ አስጠነቅቃለሁ። ነገር ግን የበለጠ አሳሳች አስተሳሰቦችን ለማስወገድ ይህንን ጽንሰ ሐሳብ መጥቀስ አስፈላጊ ነው። ይህም አሳሳች ሐሳብ የዳነ ነፍስ ማለት ትርጉም የሌለው የሆነ መንፈስ ነገር ነው እና በዳግም ትንሳኤ ከሞት የተነሳ አካል ዝም ብሎ በደነዘዘ ሁኔታ የሚኖር ነው የሚል ነው። አካል የተፈጠረው ለጌታ ነው፣ እና እነዚህ ጨለምተኛ ምናቦች ዳግም ከሞት ስለሚነሳ የሰው አካል ያለን ምስል ከእውነት የራቀ ነው።

እስከዛ ድረስ ከአክሊል በፊት መስቀል ይቀድማል። እና በሚቀጥለው ቀን የሥራ ሳምንት መጀመሪያ ነው። ምህረት በሌለው የዓለም ግድግዳ ጠባብ ቦታ ተከፍቷል። በዚህ ጠባብ ቦታ መሪያችንን እንድንከተለው ተጠርተናል። በትክክልም እርሱን መከተል ዋናው ጉዳይ ነው! ይህን ግምት ውስጥ በማስገባት ሳቀርባቸው በነበሩ አስደሳች ሐሳቦች ውስጥ ምን ተግባራዊ ጠቀሜታ አለ ብሎ የሚጠይቅ ይኖራል። ቢያንስ ግን አንድ ጠቃሚ ነገር ማሰብ እችላለሁ። ለእያንዳንዱ ከሞት በኋላ ስለሚጠብቀው ክብር አብዝቶ ሊያስብ ይችላል። ነገር ግን አንድ ሰው ስለወዳጁ ወይም ጎረቤቱ ከሞት በኋላ ስላለ ክብር አብዝቶ እና በጥልቀት ማሰብ ይችላል ተብሎ አይታሰብም። የጎረቤቴ ክብር ሸክሙ፣ ቀንበሩ እና ግዴታው ግን በእኔ ጀርባ ላይ የወደቀ ነው። ትህትህና ብቻ የሚሸከመው ቀንበር ነው። የእብሪተኛ እና ኩራተኛ ጀርባ ላይ ግን ይሰበራል። አይሸከመውም። አንደኛው በክብር መጎናጸፊያ፤ ሌላኛው በዘላለም ውርደት ውስጥ መሆን ቀልድ አይደለም። አንድ ቀን ወደ አምላክ እና አማልክትነት በሚለወጡ ፍጥረታት መሐል መኖር ከምር የሚወሰድ ነገር ነው። ለማስታወስ ያህል፣ ድንገት ዛሬ በመንገድ የምታወራው አስቀያሚ እና ምንም ነገሩ የማያስደስት ሰው አንድ ቀን፣ የነገውን ዛሬ ማየት የምትችል ከሆነ፣ በግንባርህ ተደፍተህ ልታመልከው ግድ ወደሚል ወደምትፈተንበት ፍጥረትነት ይቀየራል። ወይም አሁን እንዳየህው ወደሚያስፈራ የተበላሸ የሞት መንፈስ ይለወጣል። እጅግ የሚስፈራ ፍጡር ይሆናል። ቀኑን ሙሉ፣ በሆነ ደረጃ ያህል ለክብር መጎናጸፊያ ወይም ወደሞት ጣር ፍጥረትነት ለምንቀየርበት ፍፃሚያችን አንዳችን ለሌላችን አስተዋፆ እናበረክታለን።

ይህን ከፍተኛ የሆነ የመሆን እድልን ግምት ውስጥ በማስገባት፣ ከእነዚህ አስደናቂ እድሎች አንፃር፣ ግንኙነታችንን፣ ጓደኝነትን፣ ፍቅርን፣ ጨዋታን፣ እና

ፖለቲካችንን በአክብሮት እና ጥንቃቄ በተሞላው መከባበር ማድረግ አለብን። በማሰብ መቅረብ አለብን። ተራ ሰዎች የሉም፣ የሰው ልጅ ዛሬ ታይቶ ነገ የሚጠፋ በልቶ ሟች አይደለም። እርስ በርስ ስናወራ እንዲሁ ነገ ሟች ከሆነ ፍጥረት ጋር አይደለም የምናወራው። ሐገሮች፣ ባህል፣ ጥበብ እና ስልጣኔ ጠፊ ናቸው። አንድ ቀን ከምድር ጋር ተጠቅልለው ይጠፋሉ። ከእኛ ዘላለም ጋር ሲነፃፀሩ፣ ከኛ ጋር ሲነፃፀር ትንኝ የሚመስል የሕይወት ዘመን ነው ያላቸው። ነገር ግን ስለ ሰው ልጆች ስንናገር ! ስለ ሰው ከሆነ የምናወራው ! የምንቀልደው፣ አብረን የምንሰራው፣ ትዳር የምንመሰርተው፣ የምናመናጭቀው፣ ያልተገባ ብዝበዛ የምናደርገው ሰው ወደ ማይሞት የሞት ጣር መንፈስ ወይም ወደ ዘላለም የክብር መጎናጸፊያ ከሚቀየር ፍጥረት ጋር ነው። ይህ ማለት ሁሌም በቁም ነገር መሆን አለብን ማለት አይደለም፤ ጨዋታ አስፈላጊ ነው። ነገር ግን ጨዋታ እና ደስታችን (በእውነቱ እጅግ የሚረካ እና የሚስደስት አይነት ነው) ከመጀመሪያው ጀምሮ ከቁም ነገር በሚተያዩ ሰዎች መካከል መሆን አለበት! አንደኛው ሌላኛው ላይ ማዋረድ የማያደርግበት፣ የማያፌዝበት፣ አንዱ በሌላው ላይ የበላይ የማይሆንበት፣ እና በግምት እና ይመስለኛል የሌለበት ግንኙነት ! እና እርስ በርስ ያለን ቸርነታችን እውነተኛ እና ዋጋ የተከፈለበት የፍቅር ስጦታ መሆን አለበት። አንድ ሰው ሐጢያትን ቢፈፅምም ነገር ግን ሐጢያትን ለሰራው ሰው ጥልቅ ፍቅር እና ለድካሙ በመራራት የሆነ ግንኙነት ሊኖረን ይገባል። ይጠበቅብናል! መቻቻላችን ለይምሰል የሆነ መቻቻል አይደለም!መሆን የለበትም! ወይም ለይምሰል ደስ የተሰኙ መስሎ በመገኘት እንደሚያላግጥ የኩረጃ ፍቅር እና እውነተኛ ደስታን ላይ እንደሚቀልድ ክብረቢሥነት ያለ ግንኙነት ሊኖረን አይገባም።

በቤተ መቅደስ ቅዱስ እና ክብር የሆነውን፣ ሥጋ እና ደሙን ፣ቅዱስ ቅርባን ከመውሰድ፣ ቀጥሎ፤ እጅግ ቅዱስ የሆነ ነገር በአጠገብህ ያለ ነገር ጎረቤትህ ነው። ይሄ ጎረቤትህ ደግሞ ክርስቲያን ከሆነ በእርሱ ውስጥ የክብርን መጎናጸፊ የሚያለብሰው እና የከበረው እርሱ ራሱ ክብር የሆነው! አዎን! በእውነት የተሰወረው፣ ክርስቶስ በውስጡ አለ። እናም በሁሉም ነገር ቅዱስ ነው!

# የጸሐፊዎቹ የሕይወት ታሪክ

## 1. ፖል ጀነኒስ ቲሊች

ፖል ጀነኒስ ቲሊች (እ.አ.አ. ነሐሴ 20፣ 1886 - ጥቅምት 22፣ 1965) ጀርመን አሜሪካዊ ክርስቲያን ፈላስፋ እና የሃይማኖት ምሁር ነበር። ቲሊች በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ከነበሩት እጅግ ተፅዕኖ ፈጣሪ እና ተደማጭ የነበረ የፕሮቴስታንት አግዚስተንሻሊስት ፈላስፋ እና የሥነ መለኮት ምሑር ነበር። እርሱ ይኖርበት የነበረው ዘመን በአውሮፓ ውስጥ ፖለቲካ እና ሃይማኖትን ጨምሮ በሁሉም ዘርፎች እጅግ ታላላቅ ለውጦች የተስተናገዱበት ዘመን ነበር። ለውጥ ብቻ ሳይሆን ከባድ ፈተናዎቹም የተደቀኑበት ዘመን ነበር። የክርስትና ትምህርት ለዘመናዊው ሰው አስፈላጊ ስላልሆነ ወደ ደጅ ወጥቶ እንዲጣል የሚል የዘመናዊነት ጽንሰ ሐሳብ ጋሬጣ የተደቀነበት ዘመን ነበር። ግን ክርስትና ብቻ ሳይሆን በአንደኛው እና በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ምክንያት እጅግ አስከፊ ሁኔታ ውስጥ ያለፈችው መላው አውሮጳ፣ ከ19ኛ ክፍለ ዘመን የወረሰችውን የሰው ልጅ በሳይንስ ከተደገፈ እና ከሃይማኖት እና አፈታሪክ ከተላቀቀ ስልጡን እና በሰላም የተትረፈረፈ ይሆናል የሚለውን የሳይንስ እና ሊብራሊዝም ተስፈኝነትን ጥያቄ ውስጥ የከተተችበት ወቅት ነበር።

ቲሊች ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ነገሮች በጀርመን በጣም አስቸጋሪ በሆኑበት ወቅት የራሱን አሻራ ማሳረፍ ጀመረ። ቲሊች በጊዜው ከነበሩት ጠቃሚ የነገረ መለኮት ሊቃውንት መካከል ሰፋ ያለ፣ ሁሉን አቀፍ እና ጥልቅ እውቀት የነበረው ፈላስፋ እና የሥነ መለኮት ሊህቅ ነበር። እርሱ ለነገሮች የነበረው አቀራረብ ሥነ መለኮትን፣ ፍልስፍናን፣ ባህል እና ሥነ ጽሑፍን እና ለሎችንም እውቀቶች አስተሳስሮ በመረዳት (interdisciplinary) ላይ እና ሁሉንም ሃይማኖቶች (interreligious) የሚስተሳሥራቸውን ነገር በመፈለግ ላይ ያተኮረ ነበር። በጊዜው የነበረው ስልጣኔ ያመጣው አስከፊ ገፅታ በዕለት ተዕለት ሕይወት ውስጥ ሃይማኖት ሊጫወት የሚችለውን ሚና የሚያሰፋ ታላቅ እድል ነው ብሎ ያምን ነበር። ይህንን ለማድረግ፣ የሃይማኖታዊው ዓለም ገጽታ፤ ሃይማኖታዊ ያልሆነው ዓለም ክፍል አካል መሆን እንዳለበት ያምን ነበር። እናም ሁለቱም አንደኛው ያለ ሌላው በእውነት ሊኖር እንደማይችል አስተምሯል። ሃይማኖት ሴኩላርዝም ከሚጋጩበት የሚተባበሩበት ብዙ ነገር እንዳለ አሳይቷል። ቲሊች፣ በሰው ልጆች ታሪክ ውስጥ

መንፈሳዊ ዓለም እና የሰው የሆነው ዓለም (the secular sphere) ትርጉም ባለው መልኩ ተገጣጥመው ሚናቸውን የተጫወቱት ኢየሱስ በሥጋ በነበረበት ወቅት እንደነበር ያምን ነበር፡፡የ ተመሳሳይ እድል ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ ወደ አውሮጳ መጥቷል ብሎ ሞግቷል፡፡

ቲሊች በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት በወታደሮች ካምፕ ውስጥ የሚያገለግል ቄስ ነበር፣ እና በዚያን ጊዜ ያጋጠሙት ገጠመኞች፣ ሌላኛውን የሀገሩን ልጅ ታላቅ ፈላስፋ ኒቼን እና ኒቼ ክርስትና ላይ ይሰነዝር የነበረውን ነቀፋ እና ስለ ክርስትና የነበረው ወሳኝ ሀሳቦችን እንዲያጠና ገፋፍቶታል፡፡ ቲሊች ለኒቼ ሙግቶች ሥነ መለኮት እና ፍልስፍና መልስ ሊሰጥ ይገባል የሚል እምነት ነበረው፡፡ ይህ ምልከታው እና ያለፈበት የሕይወት ልምድ ለፍልስፍና ሥራው ከፍተኛ መሠረት ሆኖታል፤ ልክ እንደ ሉተር እንዳሳለፈበት "የማማ ላይ የሕይወት ልምምድ" ሆኖታል:: ቲሊች በሕይወት ዘመኑ ሁሉ እግዚአብሔር የለሽ የሆኑ ሃሳቢዎች፣ ጸሐፊዎች እና ደርዝ ያለው መዋቅራቸው በሕይወት ጥያቄ ውስጥ የመጨረሻውን፣ የነገሮችን ነገረ ፍጻሜ (Ultimate) መልስ ከመስጠት አንፃር ከባሕላዊ ክርስትና በብዙ የተሻሉ መሆናቸውን ለማሳየት ጥሯል፡፡ የቲሊች ዋና አላማ እና ጥረት በክርስትና እና በዘመናዊው ማህበረሰብ መካከል ያለውን ግንኙነት ትርጉም ባለው መልኩ እንደገና መገንባት ነበር፡፡ ልክ እንደ ካርል ባርት፣ ክርስትናን ከሊበራል ፕሮቴስታንት እምነት ጋር ለማስማማት ከመሞከር ይልቅ፣ የእግዚአብሔርን ፍፁምነት እና የክርስትናን መልዕክት እንደገና ለማስተዋወቅ ሞክሯል፡፡ ሊብራል ፕሮቴስታንት ያደርግ የነበረው ሙከራ መጨረሻ ላይ መውደቁ እንደማይቀር ነገር ግን የክርስትናን አስኳል ማሳነሱን ማበላሸቱን እርሱም ካርል ባርትም አብራርተዋል፡፡ ቲሊች እና ባርት የክርስትናን መልዕክት ከማሕበራዊ ፍትሕ እና ማሕበራዊ ንቅናቄዎች ጋር አቆራኝተው አሳይተዋል፡፡ ነገር ግን ከባርት በተቃራኒ ፖል ቲሊች በእግዚያብሔር ላይ ያለ ፍፁማዊ እምነት፣ እርሱ እግዚአብሔር ከሰዎች ልጆች እና አለማቸው ፍፁም ሌላ፣ ("wholly other") የሚለው ጽንሰ ሐሳብ ትክክለኛ መፍትሄ ይሆናል ብሎ አያስብም ነበር፡፡ ሃይማኖት የማንኛውም ማህበረሰብ አስፈላጊ አካል እንደሆነ ለማሳየት የተለያዩ መንገዶች መዳሰስ አለበት የሚለውን አጉልቶ ለማሳየት ጥሯል፡፡ ደግሞም ፍፁም የሆነው እግዚያብሔር በተመሳሳይ ጊዜ አንፃራዊ በሆነ የሰው ልጆች የባህል ሕይወት ውስጥ እንደሚገኝ ማሳየት አስፈላጊ እንደሆነ ያምን ነበር፡፡

## ድንበር ከድንበር ማገናኛ መስመር ላይ

ምንም እንኳን የቲሊች አጽንዖት እና ዘይቤ፣ በተለይም በ 1933 ወደ አሜሪካ ከተሰደደ በኋላ እየተለወጠ የሄደ ቢሆንም፣ ነገር ግን የማንኛውም ጉዳይ ወይም ሁኔታ ሁለት ጎኖች አንድ ላይ ማስተሳሰር በሚል ያራምድ የነበረው የፍልስፍና መንገድ አልተቀየረም። ይህም ፖል ቲሊች በ1936 ባሳተመው የሕይወት ታሪኩ ላይ በጥሩ ሁኔታ ተገልፃ እናገኘዋለን። ቲሊች ሕይወቱ በነገረ መለኮት እና ፍልስፍና፣ በቤተ ክርስቲያን እና በሕብረተሰብ፣ በአውሮፓ እና በአሜሪካ፣ በፕሮቴስታንት እና በካቶሊካዊነት፣ በሊበራሊዝም እና በኒዮ ኦርቶዶክስ እና በመሳሰሉት መካከል ወደ ማናቸውም ፅንፍ ያልሄደ፣ እነዚህን በመካከለኛነት የሚያገናኝ ጽንሰ ሐሳብ የቱ ነው የሚለው መፈለግ እና ማወቅ የሚያስጨንቀው ሰው ነበር። ለትሊክ፣ በነዚህ ጉዳዮች አና ጽንሰ ሃሳቦች መሀል መሆን፣ ድንበሩ ጫፍ ሆኖ ሁለቱን ለማስታረቅ መሞከር፣ የሚያሳምም ወይም ደስታ የሚነሳ ነገር አልነበረም። ነገር ግን፣ በግል ዓለምን ከሚያይበት፣ ከሕይወት ዘንባሌው ጋር የሚጠጣም አጣ ፈንታው እንደሆነ ያስበ ነበር።

## የቲሊች ሕይወት በአጭሩ

እ.አ.አ. ኦገስት 20 ቀን 1886 በጀርመን በስታርዝድል፣ በበርድንበር፣ የሉተራን ፓስተር ከሆነ አባት የተወለደው ቲሊች በበርሊን፣ ቱቢን፣ ሃል እና በርስሎ ዩኒቨርሲቲዎች ትምህርቱን ተከታትሏል። የዶክትሬት ዲግሪውን በፍልስፍና በ1910 (በርስሎ) እና ሥነ መለኮት የማስተማር የፈቃድ ዲግሪውን በ1912 (ሃል) ተቀብሏል። ብዙም ሳይቆይ፣ በ1912፣ ቲሊክ የሉተራን ቤተ ክርስቲያን አገልጋይ ሆኖ ተሾመ። በአንደኛው የዓለም ጦርነት ወቅት፣ በእሱ ላይ ትልቅ ምልክት ያስቀመጠ እና ለወደፊት የሕይወት አቅጣጫው ከፍተኛ አስተዋጾ ያደረገ ልምድ ያገኘበት፣ በጀርመን የወታደሮች ጦር ካምፕ ውስጥ መጋቢ በመሆን አገልግሏል። በ1919 በጀርመን ውስጥ የናዚ አገዛዝ ወደ ስልጣን እስከመጣበት ጊዜ ድረስ የዘለቀ የማስተማር ሥራ ላይ ተሰማርቶ ነበር። ቲሊክ በርሊን፣ ማርበርግ ዴስደን እና ላፍይዝግ ዩኒቨርሲቲዎች የነገረ መለኮትን ትምህርት፣ በፍራንክፈርት ደግሞ ፍልስፍናን አስተምሯል። ይሁን እንጂ የናዚን አገዛዝ ይቃወም ስለነበር፣ በነበረው የማሕበረ ሰብአዊ ፖለቲካ አቋሙና ከአይሁዶች ጋር ያለው አጋርነት በዩንቨርስቲዎች ውስጥ የነበረውን ሥራውን እንዲያጣ ምክንያት ሆኗል። ቲሊክ የናዚ አገዛዝ እ.አ.አ.

በ1933 በአይኔ ላያቸው አልፈልግም ብሎ ከሥራ ገበታቸው ነቅሎ ካባረራቸው ከመጀመሪያዎቹ ጀርመናዊ ፕሮፌሰሮች አንዱ ነበር። ቲሊች ከዚያ በኋላ በዩናይትድ ስቴትስ በሚገኘው ዩኒየን ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ እንዲያስተምር ከራይንሆልድ ኒቡህር የቀረበለትን ግብዛ ተቀበለ፣ በመጨረሻም አሜሪካ ለማስተማር ጥሪ በቀረበለት በዛው አመት፣ ጓዙን ጠቅልሎ ወደ አሜሪካ ተሰደደ። ቲሊች በ1940 የአሜሪካ ዜግነት ማግኘት ችሏል።

ቲሊች የፕሮቴስታንት ክርስቲያናዊ ሥነ መለኮትን ከኤግዚስቴንሻልዝም ፍልስፍና ጋር ያላቸውን ልዩ ውህደት የሚገልጹ ተከታታይ መጽሐፎችን በማሳተም ከፍተኛ ተቀባይነት ስምና ዝና ያተረፈው በዩኒየን ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ ውስጥ ነው። ቲሊች በምዕራቡ ዓለም ከፍተኛ ተጽዕኖ ያሳረፋ ሙሁራን፣ አሳብያን እና ጸሐፊያን ተጋብዘው ንግግር በሚያደርጉበት በዝነኛው አበርዲን ዩኒቨርስቲ፣ ተጋብዞ የጊፎርድ ንግግሮችን (Gifford Lecturers) አድርጓል። የጊፎርድ ንግግሩ (Gifford Lecturers) ወደ መጽሐፋ ተቀይሮ፤ የሦስት ጥራዝ ስልታዊ ሥነ መለኮት መጽሐፍን አስገኝቷል። በኤግዚስቴንሻሊዝም ፍልስፍና ላይ ያለው አብዛኛውን ዕይታውን ያሰፈረበት በ1952 ዓመተ ምህረት የፃፈው Courage to Be የተሰኘው መፅሐፍ፣ ከመንፈሳዊ እና ሥነ መለኮት ከባቢ ውጪ ባሉ አንባብያን ጭምር የተወደደለት መፅሐፍ ሲሆን፤ ይህም ከፍተኛ አድናቆትን እና ተፅእኖን አስገኝቶለታል። ይሄ ሥራው እ.አ.አ.1957 በሃርቫርድ እንዲያስተምር በር የከፈተለት ሲሆን፣ በሃርቫርድ በነበረው ቆይታ ደግሞ ሌላ እጅግ ተወዳጅ እና አይነ ገላጭ የሆነ Dynamics of Faith የተሰኘ መፅሐፍን እ.አ.አ. 1957 ሊያሳትም በቅቷል። ለዘመናዊ የፍትሓዊ ጦርነት አስተሳሰብ በጣም ጠቃሚ አስተዋፅዖ አበርክቷል። እ.አ.አ. በ 1962 ወደ ቺካጎ ዩኒቨርሲቲ ተዛወረ፣ በ 1965 በቺካጎ እስከሞተበት ጊዜ ድረስ በቺካጎ ዩኒቨርዚቲ ሲያስተምር ቆይቷል።

## ሕላዌ፣ ኑባሬያዊነት (Existentialism)

የቲሊች አቀራረብ ኑባሬያዊነት (Existentialism) ተብሎም ሊጠራ ይችላል። ገና በመጀመሪያዎቹ ዓመታት፣ እግዚአብሔርን መገንዘብ እንደ “በምንም ቅድመ ሁኔታ መቀመጥ ውሰጥ የሌለ፣ ያልተከለለ” (the Unconditioned) ነው የሚል አቀራረቡ ከኑባሬያዊ ፍልስፍና ትንታኔ ጋር የተሳሰረ ነው። ምንም እንኳን ሄይድጋር በእግዚአብሔር መኖር የማያምን ቢሆንም፣ ቲሊች ከሄይድጋር Being and Time, 1927 ከሚለው ሥራ ጋር ከተዋወቀ በኋላ በእርሱ እና በሄይድጋር

ፍልስፍና መካከል መሠረታዊ የሆነ ቅርበት እንዳለ ማወቅ ችሏል። “ያለው እኛነታችን፣ የሆነውን ሆነን ያለንበት” (the being initself) ውስጥ ያለው፣ ምንም ያለመሆን ጭንቀት (non being) ወይም በኑባሬያዊነት ውስጥ ያለ ስቃይ (existential anguish) መሠረታዊ እና ከምንም ያልመጣ “ኑባሬያዊነት በራሱ” በተፈጥሮ ሆኖ የተገኘው ነገር ነው በማለት ተከራክሯል። በቀላል አነጋገር፣ ሰዎች የራሳቸውን አለመኖር ማለትም መሞታቸውን ይፈራሉ። ከኪርኬጋርድ እና ፍሮይድ ጋር የተያያዘውን መስመር በመከተል፣ ቲሊች በውስጣችን በጣም በምናስብባቸው፣ ወይም ራሳችንን አጥልቀን በምንመረምርበት ወቅት እና ጊዜያት ሁሉ፣ ከራሳችን አስፈሪ “ምንምነት ጋር” ፊት ለፊት እንጋፈጣለን ይላል። ማለትም፣ “የእኛን ሟችነት” እና “ውስን” ፍጡር መሆናችንን እንገነዘባለን ማለት ነው። ምንም የሌለበት የእኛነታችን ኩነት (non being) እጅግ ሰፊ ፍልስፍናዊ ሐሳብን የተሸከመ ሲሆን ያለውን እና ተጨባጭ የሆነው ነገር ወደ ምንምነት ሲለወጥ፣ ወይም የአንድ ነገር አለመኖር፣ ያለን ነገር ተቃርኖ የሚቆም፥ የምንም ነገርነት (non being) ጽንሰ ሃሳብን የመለክታል።

## ስለ ቲሊች ሥራዎች

የቲሊች ሥራ ጀርመን በነበረበት የሰራው ሥራ እና በኋላ አሜሪካ ከገባ በኋላ የሰራቸው ሥራዎች በሚል በግልፅ ለሁለት መከፈል ይችላሉ። በእነዚህ ሁለት የሥራ ወቅቶች ከላይ ከላይ ሲታይ ጉልህ ልዩነቶች ቢኖሩም ነገር ግን በነበረው አብዛኛው የፍልስፍና እና የሥነ መለኮት አቋም ላይ ትልቅ ያልተቋረጠ ቀጣይነት አለው።

## የጀርመን ጊዜ: የሃይማኖት እና የሶሻሊዝም ፍልስፍና

የጥንቱ በጀርመን የነበረው ቲሊች በዋነኝነት ያተኮረው ከሃይማኖት ፍልስፍና ጋር በተያያዙ ጉዳዮች፣ እንዲሁም በማሕበራዊ ጉዳዮች እና በክርስቲያን ሶሻሊዝም ጥያቄ ላይ ነበር። ሆኖም፣ በጀርመን የነበረው ሥራዎቹ ላይ አስቸጋሪ የአካዳሚክ ቋንቋ መግለጫዎች የሞላበት ቢሆንም፣ ቀደምት ሥራዎቹ ምናልባት የእሱን የመጀመሪያ አስተዋፅኦ የሚያሳዩ ናቸው። በእርግጠኝነት፣ እሱ በሕይወት ዘመኑ ሁሉ ያዳበራቸውን ቁልፍ ጭብጦች የያዘ ነበሩ።

## ካይሮስ እና ቲሊች፣ ክርስቲያን ሶሻሊዝም

ለቲሊች ሰው መሆናችን፣ እንደ ውስን ፍጡርነታችን፣ ከነገር ሁሉ ምንጭ፣ ፍፁም ከሆነው ከእርሱ (ultimate Being) ጋር ወደ መለያየት እንድናመራ አድርጎናል ብሎ ያምናል። ከተለምዷዊ የክርስትና እምነት በተቃራኒ የሰው ልጅ ከጸጋ መውደቅ የመነጨው ውሱን ፍጡር ሆኖ በመፈጠሩ ነው ይላል። ነገር ግን፣ እንደ ፖል ቲሊች ሐሳብ፣ በታሪክ ውስጥ መለኮት ወደ ሰው ልጅ ሕልውና ውስጥ ዘልቆ የሚገባበት እና ማሳካት የፈለገውን የሚያሳካበት፣ የሚዋሃድበት አጋጣሚዎችአሉ  ምንም እንኳን ፍጽምና ባይኖረውም። ቲሊች እንዲህ አይነት መለኮት ወደ ሰውልጆች ህልውና ጥሶ የሚገባባቸውን የታሪክ ወቅቶች የግሪክ ቃል ትርጉሙ "ትክክለኛው ጊዜ" ተብሎ ከሚተረጎመው "ካይሮስ" ከሚለው ሐሳብ ጋር ያዛምዳቸዋል። ለቲሊች ይህ "ትክክለኛው ጊዜ" የሆነው ደግሞ ክርስቶስ ወደ ምድር የመጣበት ከሁለት ሺህ ዓመታት በፊት እና እንዲሁም ክርስቲያን ሶሻሊዝም በጀርመን እንዲያብብ ወሳኝ ወቅት የነበረው በጀርመን አንደኛው የዓለም ጦርነት ማብቂያ ወቅት ነው። ቲሊች ምንም እንኳን ለማርክሲዝም ሐሳቦች ስስ ልብ ቢኖረውም ነገር ግን በማርክሲዝም ላይ የሚያነሳቸውን ሒሳዊ አቋም ያራምድ ነበር። ተጨባጭ የሕልውና ገደቦች ሊወገዱ የሚችሉት እና የካፒታሊዝምን ቁሳዊነት ተፅዕኖ በመቋቋም ፍትሓዊ ማሕበረ ሰብ ለመመስረት ሶሻሊዝም ሁነኛ የሆነ መፍትሄ ነው ብሎ ያስብ ነበር። ይህ ራዕይ "ሰማያዊ የሆነውን አገዛዝ" በምድር ላይ ከመመሥረት ጽንሰ ሐሳብ ጋር ይጣጣማል። የቲሊከ ሥራ የነበረው፣ "የሶሻሊስት ውሳኔ" የሚለው መጽሐፍ በናዚዎች ተቃጥሏል። በአሜሪካ ሀገር በነበረው ቆይታ ግን በሶሻሊስት ዩቶፒያ ላይ የነበረው እምነትና ትኩረት በከፍተኛ ሁኔታ ሊቀንስ ችሏል። ነገር ግን የካፒታሊዝምን የቁሳዊነት ፍቅር ከመተቸትና ከመንቀፍ ወደኋላ አላለም። በመሠረቱ የፖል ቲሊች እይታ የሰው ልጆች ውስን በሆነው ተፈጥሮአቸው ምክንያት ከሁሉ ነገር ምንጭ እና ፍጻሜ (ultimate Being) ከሆነው፣ የመነጠል እጣፈንታ ወድቆባቸዋል የሚል ነው። ይህም ትክክለኛ ማንነታቸውን አግኝተው ለመኖር የሚያደርጉትን ትግል አጣብቂኝ የሞላበት እንዲሆን አድርጎታል ብሎ ያስባል። ነገር ግን እንደ ፖል ቲሊች ሃሳብ፣ መለኮት ወደ ሰው ልጆች ሕይወት ጥሶ መግባት ወይም "ካይሮስ" እነዚህን ገደቦች የማለፍ እድልን እንዲያገኙ ያደርጋቸዋል።በእነዚህ የታሪክ ወቅቶች የሰው ልጆች ከትክክለኛው ማንነታቸው ጋር እርቅ ፈጥረው የመኖር አቅማቸውን አይተዋል ይላል። ክርስቲያናዊ ሶሻሊዝም ይህንን ዘመን ተሻጋሪ መንግስት (የሰው ልጆች ትክክለኛ ህልሞች የሚፈተኑበት) ለማሳካት እንደ አንድ አማራጭ መንገድ

ይመለከተዋል እና የካፒታሊዝምን ቁስ አካላዊ ገጽታዎችን አምርሮ ነቅፏል።

## እግዚአብሔር፣ በምንም ቅድመ ሁኔታ ያልተገደበ እና የአትኩሮት ሁሉ ግብ (God, the Unbound and Ultimate Concern)

ቲሊች የመጀመሪያ ሥራው፣ ስለሕልውና ጥልቅ ግንዛቤ እና ከሁሉ ከፍ ካለ፣ ቁሳዊ ካልሆነ እውነታ ጋር መገናኘት በሚለው (mystical approach) ጽንሰ ሃሳብ ላይ ተመስርቶ ሥነ መለኮት እና ፍልስፍናን ማጣመር በሚለው በስኬሊንግ ፍልስፍና ተፅዕኖ ያረፈበት፣ በሃይማኖት ፍልስፍና ላይ ያተኮረ ነበር። ነገር ግን በኋላ ላይ በካንት critical method መሠረት፣ እግዚአብሔርን በሰው የግንዛቤ ክበብ ውስጥ እንዳለ ሐሳብ (finite object of thought) ማሰብ ትክክል እንዳልሆነ ተገነዘበ። ይልቁንም ቲሊች እግዚአብሔር ሊብራራ እና ሊታወቅ የሚገባው ራሱ የሰውን ልጅ አዕምሮ በቀጥታ በመረዳት ነው። አዕምሮ ያሰበውን ሳይሆን፤ የሚያስበው ዐዕምሮ ላይ ትኩረት ማድረግ የሚለውን ያምን ነበር። ካንት ተጨባጭ ነገር (reality) በልምምድ ውስጥ የሚታወቅ ነው የሚለውን ተቀብሏል ነገር ግን ሃይማኖታዊ ልምምድን በተመለከተ ያለውን ጉዳዮች በሙላት ትኩረት በመስጠት በሥራው አላካተተም። በቲሊች አስተሳሰብ ዘዴ ውስጥ ግን ሃይማኖት የአዕመሮአችንን የአሁን እና "ቅድመ ሁኔታ የለሽ" ከሆነ ከህልውና ጋር የሚደርግ ግንኙነትን ያካትታል የሚል ነው። ይሄ መገናኘት ፍፁም ውስን የሆነውን የሐሳብ ገደብን የሚመለክት ሲሆን፤ ከመለኮት ጋር የሚኖረንን ግንዛቤ ልንረዳ የምንችለው በውስጥ ብርሃን እና በአሰላስሎት ብቻ ነው። ወይምን በሌላ አነጋገር የሚያስበው አዕምሮአችን ከመለኮት ጋር በሚያደርገው ግንኙነት ነው የሚል ነው።

ይህ ከምንጩ፣ ከመለኮት ጋር መገናኘት የማሰብ አቅም የመጨረሻ ወሰን ነው ብሎ ያስባል። መለኮትን መረዳት የምንችለው በውስጥ ብርሃን (mystical experience) ነው። ቲሊች ሃይማኖታዊ ነገርን በራሱ ክበብ መረዳትን ሂሳዊ ኢንቱዩቲቭ (በኋላ "ሜታሎጂካል") ብሎ ጠርቶታል። በዚህ ሂደት ውስጥ ፊት ለፊት የምናገኘው መለኮት ያልተወሰነ፣ ፍፁም እና በምንም ነገር ቅደመ ሁኔታ ያልተቀመጠበት ነው። ሩዶልፍ ኦቶን በመከተል ቲሊች፣ መለኮትን (The absolute being) አስፈሪም (ጣልቃ ገብነትን ለማይፈልገው አስተሳሰባችን ፈተና ስለሆነ) እና

ደግሞም ማራኪ እና የሚፈለግ (ትርጉም የሌለው ሐሳብ ብቻ የማይሰጠንን ሙላት ስለሚሰጠን) ነገር እንደሆነ ይገነዘብ ነበር። እግዚአብሔርን ሰለመረዳት በሚነሳው ፍልስፍናው ስለእግዚየብሔር ባለው መረዳት እግዚአብሔር በሰው አምሳል፣ መረዳት እና ግንዛቤ ልኬት ውስጥ ተቀርፍዶ ከመረዳት (objectifying God) ለመከላከል፣ በምንም እና በማንም ቅድመ ሁኔታ ያልተቀመጠበት (Unconditioned) የሚለውን ቃል እና ሃሳብ ይጠቀም ነበር። እንደውም በኋላ ላይ፣ አንድ ሰው በሕይወቱ ውስጥ የሞት እና የሕይወት ጉዳይ አድርጎ የሚይዛቸው አስፈላጊ እና ትልቅ ጉዳይ ኩነት፣ የአዕምሮአችንን ተግባር የሚያመለክት ቃል በመውሰድ የመጨረሻው የትኩረት ግብ (ultimate concern) በማለት ይጣራው ነበር። ይህም እግዚብሔርን በራሳችን መልክ እና አምሳል ከመረዳት ለመጠበቅ ነው።

ካርል ባርዝ የቲለክ እግዚአብሔርን በመረዳት ሂደት ውስጥ ባለው ፍልስፍናው ውስጥ ለመለኮት ጽንሰ ሐሳብ ምትክ “በምንም ቅድመ ሁኔታ የሌለበት” (“unconditioned”) የሚለውን መጠቀሙን ይነቅፍ እና እንደማይወደውም በግልፅ ያስቀምጥ ነበር። አደገኛ እና ቆሞ የቀረ ቃል ብሎ (frozen monstrosity) ይጠራው ነበር። ነገር ግን አንድ ሰው ፖል ቲለክ ባነሳው ሐሳብ ውስጥ ሊረዳ የሚገባው ነገር ቲሊች እየሞከረ ያለው እግዚአብሔር፣ የፍጻሜ መጨረሻ፣ እኔ ነኝ የሆነውን መለኮት ከማንኛውም የሃይማኖት አስተሳሰብ ጋር ከማያየዝ ለመነጠል እየሞከረ መሆኑን ነው። በዚህም ምክንያት ሃይማኖት ውስጥ ያለ እምነት (religious belief) በምንም ቅድመ ሁኔታ (the Unconditioned) ያልተያዘ የሚለውን ሃሳብ እንዲያካትት፣ ቲሊች፣ ሃይማኖታዊ ሆኑ ሃይማኖታዊ ያልሆኑ ግለሰቦች ከራሳቸው የላቀ ነገር ጋር ለመገናኘት በሚያደርጉት ጥረት የሚካፈሉት የጋራ ልምዶች፣ ሃሳቦች እና እሴቶች አሉ ለሚለው እውቅና ይሰጣል። ለእሱ፣ ሃይማኖት ማለት በዋናነት በሕብረተሰባችን ውስጥ ቦታ የተሰጠው ወይም ያልተሰጠው ነገር፣ የተለየ ጎራ አልነበረም። ይልቅ የእያንዳንዱ የሕይወት ተሞክሮ መሠረታዊ ገጽታ ነበር። ያለው ብቸኛ ነገር ቁስ ነው ብሎ የሚያምነው የቁሳዊነት ፍልስፍና ተከታይ እንኳን ቢሆን፣ እውነት ተጨባጭ የሆነ ነገር ምንድን ነው የሚለውን በአቶሞች ውስጥ ሊረዳ ይችላል ብሎ ያምናል። በዚህ መረዳት መሠረት የቁሳዊነት ፍልስፍና ተከታይም ሃይማኖተኛ ነው። እግዚአብሔር የለም የሚለውም “በፍፁም” አምላክ የለም ብሎ ያምናል፣ ስለዚህም እሱ በራሱ መንገድ ሃይማኖተኛ ነው። የዚህ አቀራረብ ጥንካሬ በጣም አካታች በመሆኑ ፣ኃይማኖትን ራሱ ከገነባው ጌቶ አውጥቶ ዓለም አቀፋዊ ያደርገዋል። የዚህ የቲሊች ሐሳብ ድክመቱ “እውነተኛ” ሃይማኖታዊ ተሞክሮ ከሌሎች ዓይነቶች ያልሆኑ

ግን የሚመስሉ ሃይማኖታዊ ቅርፆች እንዴት እንደሚለይ ግልጽ አለመሆኑ ነው። ሌላው እግዚአብሄርን የምንረዳው በእኛ ዓለም ስለሆነ በእርሱ ፍልስፍና ውስጥ የእግዚአብሔር ማንነት ከእኛ ሰብዓዊ አድማስ በላይ ሊሆን የሚችለው እንዴት ነው የሚለውን ግልፅ አድርጎ አይመልስልንም። ቲሊች እነዚህን ነጥቦች በሥነ መለኮት ፅሑፎቹ ለማብራራት ሞክሯል፣ ነገር ግን አንዳንድ ወጥነት የሌላቸው እንደሆኑ በስፋት ስምምነት አለ።

## የአሜሪካ ጊዜ፣ ሥነ መለኮት እና የህልውና ዳሰሳ (existential concerns)

ቲሊች፣ በ1933 ወደ አሜሪካ ከመጣበት ከሁለተኛው የሥራው ዘመን ጀምሮ፣ ቀደም ሲል በሃይማኖት ፍልስፍና ላይ ከሰጠው ትኩረት አይኑን አንስቶ፣ ከተለያዩ መስኮች ግብአቶችን በመውሰድ ሙሉ በሙሉ በሚባል ደረጃ በሥነ መለኮት ላይ አተኩሯል። ነገር ግን የቲሊች አቀራረብ እና ስለ ጭብጦች ያቀረበው ውይይት በጣም ፍልስፍናዊ ሆኖ ቆይቷል። እና ቀድሞ የነበረው ፍልስፍናዊ ግንዛቤው በእነዚህ የሥነ መለኮት ሥራዎቹ ውስጥ እየተደጋገሙ ብቅ ብለዋል። እውነትን (ultimate truth) በተመለከተ በሁለት ፅንፎች መካከል ያለ ግንኙነት መመርመር በሚለው አትኩሮቱ ውስጥ ያለው ፍላጎት፣ በፍልስፍና እና በባህል ለሚነሱ ጥያቄዎች ነገረ መለኮት መልስ እንዲሰጥ ያዘጋጀው የእርስ በእርስ ግንኙነት ዘዴ ብሎ የሰየመው ጽንሰ ሐሳብ የዚህ ዋና ማሳያ ነው።

## የነገሮች ተዛማጅነት ጉዳይ

“እምነት በዘመናዊ ባህል ውስጥ ተቀባይነት የሌለው መሆን የለበትም’’ እና ‘’ዘመናዊው ባህል በእምነት ውስጥ ተቀባይነት የሌለው መሆን የለበትም”። በማለት እምነት እና ባህልን ለማዛመድ ጥሯል። ይህ ጥረቱ የሚያሳየን የቲሊች ዝንባሌ በዋነኝነት አቀበተ እምነታዊ እንደሆነ ነው። ተጨባጭ ሥነ መለኮታዊ መልሶችን በዕለት ተዕለት እንቅስቃሴ ተፈጻሚ እንዲሆኑ ለማድረግ የተቻለውን አድርጓል። ይህም ውስብስብ ነገሮች ለሚገባቸው ብቻ ሳይሆን፣ ሐሳቡ ለማንኛውም አንባቢ ተደራሽ በመሆኑ ለታዋቂነቱ አስተዋጽኦ አድርጓል። ከሰፊ እና ሁሉን አቀፍ ምልከታ በመነሳት፣ መገለጥ የሃይማኖት ምንጭ እንደሆነ ተረድቷል።

በዚህም ቲሊች መገለጥን እና አመክንዮን ለማስታረቅ ሞክሯል። መገለጥ ከምክንያታዊነት ጋር ፈጽሞ አይቃረንም በማለትም ሞግቷል። ሆኖም ግን፣ ለእሱ ሁለቱ (መገለጥ እና አመክንዮ) እርስ በእርሳቸው በአዎአይ (paradoxical relationship) ግንኙነት ውስጥ እንደዋለሉ ይኖራሉ። አንዳቸውም ተረጋግተው፣ ያለቀ ጉዳይ ሆነው አይኖሩም።

ውስን የሆነውን ሰው ደግፎ የሚይዘው (finite beings)፣ መለኮት (be-

ing itself) ወይም የሆነው (being) እና ያልሆነው ነገር (non being) መነሻ እና መመለሻ የሆነው "ground of being" ነው። ይህንንም ፖል ቲሊች ከእግዚአብሔር ጋር አንድ አድርጎ ይተረጉመዋል። ሌላው የሆነው (being) ነገር እና ያልሆነው ነገር(በራሱ የሌለ ግን ያለን የሚፃረር ያም non being) የመነሻ እና መመለሻው "ground of being" ስም የማንነት ውስጠኛ ነገር (Essence) ይባላል። የአንድ ማንነት አስኳል የሆነውን ክፍል እና በተፈጥሮ የሆነውን እንዲሆን ያደረገውን ነገር Essence ልንለው እንችላለን። የማንነት ውስጠኛ ነገር (Essence) በመሆን ውስጥ ለሆነው ነገር (for being) ኀይል ነው። እና ደግሞ የማንነት ውስጠኛ ነገር (Essence በአዕምሮችን የማይደረስበት የእኛነታችን ክፍልም ነው ብለን ልንወስደው እንችላለን። እናም የእኛ የማሰብ አድማስ የማይደርስበት የእኛነታችን ክፍል ሲሆን ክርስትና ከሰማይ የሆነ መገለጥ ብቻ የሚደርስበት ብሎ የሚፈታው ማለት ነው።

## ስልታዊ ሥነ መለኮት

የቲሊች ለሥነ መለኮት ያለው የበሰለ አመለካከት በሶስቱ ስልተ መለኮት ጥራዞች ተገልጿል። ለእርሱ ክርስቶስ በራሱ ውስጥ የሕላዌን እና የማንነት ውስጠኛ ነገር (Essence) መካከል ያለውን መነጣጠል የሚያስተካክል አዲሱ አዳም "New Being," ነው። የማንነት ውስጠኛ ነገር (Essence) ሳይዛነፍ እና ሳይጎድል ሙላቱ የታየው በክርስቶስ ውስጥ ነው። ነገር ግን ክርስቶስ ከእኛ እንደ አንዱ ስለሆነ ውስን ነው። ይሄ ለቲሊች የሚያመለክተው፣ በመሆን ውስጥ ባለ ነገር (being) ላይ የተካሄደ አብዮት ነው። ስለዚህ ለቲሊች ክርስቶስ በራሱ አብ ሳይሆን ክርስቶስ የአብ መገለጥ ነው። ቲሊች ክርስቶስ፣ እግዚአብሔር ሰዎች እንዲሆኑ የሚፈልገው፣ የሰው ልጅ ከፍተኛ ግብ መዳረሻ እንደሆነ ያምን ነበር። ስለዚህ ክርስቲያን መሆን ራስን በሂደት "ክርስቶስን መምሰል" ነው፣ ይህም በቲሊች እይታ በጣም የሚቻል

ግብ ነው። በሦስተኛው እና በመጨረሻው ቅጽ ላይ፣ ቲሊች ስለ ካይሮስ ወይም ከእግዚአብሔር ጊዜ ካለው አመለካከት ጋር በቅርበት የተያያዘ ሐሳብ፣ “በመንፈስ ስላለ ሕይወት” እና ስለ “እግዚአብሔር መንግሥት” ያለውን አመለካከት ገልጿል። ለእርሱ የመንፈስ ሕይወት ፍፁም የሆነው የሚኖርበት የሕይወት ጥልቅ አቀጣጫ ነው። ይህም አንድ ሰው ግልፅ በሆነ ሁኔታ ከእግዚአብሔር ጋር ባለው ሕብረት የሚደርስበት ልምምድ ነው። የመንፈስ ሥራ አሁን ያሉትን መዋቅር አያፈርስም ነገር ግን አሁን ባለው መዋቅር የታመመውን ይፈውሳል። ነገር ግን ይላል ቲሊች፣ የነገረ ፍጻሜ ሙላት እስኪሆን ካለው እሳቤ ጋር በተያያዘ ምክንያት የዚህ የመንፈስ አሰራር የተቆራረጠ ሆኖ ይቆያል። በወጥነት እና በሙላት ላይገለጥ ይችላል።

## አጋንንታዊ ፈተና

በሕላዌ ውስጥ ያሉ ነገሮች የተበላሹ እና የተዘበራረቁ በመሆናቸው፣ የትኛውም ውስን ነገር በራሱ የማይወሰን ነገር መሆን አይችልም። ስለዚህ ውስን የሆነው ነገር መቻልን የሚያገኘው ውስን ላልሆነው ነገር መጠቀሚያ መሳሪያ በመሆን ነው። ነገር ግን ሁለቱ አንድ እንደሆኑ ተደርገው መታየት የለባቸውም። ለቲሊች አጋንንታዊ ፈተና ማለት ውስን የሆነው ነገር በምን ቅድመ ሁኔታ ያለመያዘን መብት የእኔ ነው ብሎ ጥያቄ ማንሳትን ያካትታል። ይህ ጽንሰ ሐሳብ በሁሉም የቤተ ክርስቲያን ሕይወት እና ባህል ላይ የሚሠራ ሲሆን፣ በተፈጥሮው ካለው የጽንሰ ሃሳብ ውስንነት እና ለብልሽት ተጋላጭነት ምክንያት፣ ሃይማኖትንም ከመጠን በላይ ቀኖናዊ ተደርጎ ሊወሰድ በማይችልበት ቦታ ላይ ያስቀምጣል። ትክክለኛ ሃይማኖት በምንም እና ማንም ያልተወሰነውን በትክክል መግለጥ መቻል ነው፣ ነገር ግን ይህን ማድረግ የሚችለው በዘይቤ እና በምልክት (metaphor and symbolism) አጠቃቀም ብቻ ነው። የትኛውም ሀይማኖት ከመታወቅ በላይ የሆነው እውነት (ultimate truth) ቀጥተኛ እይታ አለኝ ብሎ መናገር አይችልም። ቲሊች ይህንን ሃሳብ “የፕሮቴስታንት መርህ” በማለት ጠቅሶታል ይህም እያንዳንዱ ማረጋገጫ፣ “አዎ” (affirmation)፣ በተቃርኖ መግለጫ፣ “አይደለም” (opposing statement) ሚዛናዊ መሆን እንዳለበት ይደነግጋል። በውጤቱም፣ መላው መጽሐፍ ቅዱስ በምሳሌያዊ መንገድ መተርጎም አለበት። ሁሉም መንፈሳዊ እና ሥነ መለኮታዊ እውቀት ልንረዳው የምንችለው በምልክት ብቻ (symbolically) ነው ብሎ ያምናል። የሥነ መለኮት ሊቃውንቱ ይህን ጽንሰ ሐሳብ ብዘውን ጊዜ፣ ሃይማኖታዊ አክራሪነት (religious fundamentalism) ላይ እንደ መልሶ ማጥቂያ የሙግት መንገድ ይጠቀሙበታል። ቲሊች ከሁሉም ምልክቶች መካከል መስቀሉ

ራስን መካድ ስለሚያመለክት አላግባብ ጥቅም ላይ የመዋል ዕድሉ አነስተኛ እንደሆነም ያምን ነበር።

ፖል ቲሊች፣ በቤተ ክርስቲያን እና በባህል ወይም በማሕበረሰብ መካከል ሦስት አይነት ግንኙነት አለ በማለት ይናገራል። እነርሱም ቲኦኖሚ፣ ኦቶኖሚ እና ሄቶሮኖሚ ይባላሉ። ቲዎኖሚ ሃይማኖት በሰው አእምሮ እና በእግዚአብሔር መካከል እውነተኛ ግንኙነት የሚፈጥርበትን ሁኔታ ይወክላል። ማሕበረሰቡን ከውስጥ ዘልቆ በመግባት ሕይወቱን እና አወቃቀሩን ይቀርፃል። ይህ ጽንሰ ሃሳብ፣ የእግዚአብሔርን አገዛዝ የሚያመለክት፣ የመካከለኛው ዘመን አስተዳደር ባሕርይ ነው። ቀስ በቀስ፣ ቲኦኖሚ በመካከለኛው ዘመን መጨረሻ ወደ ሄትሮኖሚ ተለወጠ። ከሶስቱ አይነት ጽንሰ ሐሳቦች የመጨረሻው ተመራጭ ሐሳብ ነው። ሄትሮኖሚ ማለት ሃይማኖትን በጉልበት በሌላው ላይ መጫን ማለት ነው። በውጤቱም የሚሆነው ጭቆና ነው። ውሎ አድሮ፣ ዘመናዊነት ብቅ ሲል፣ የራስ ገዝ አስተዳደር ሕብረተሰቡን ማስተዳደር ጀመረ፣ ይህም የሰው ልጅ አእምሮ ከውጫዊ ሥልጣን ነፃ መሆኑን መጀመሩን አመላካች ነው።ቲሊች ራስን በራስ ማስተዳደር በሕብረተሰቡ ውስጥ ትክክለኛ ቦታ ሊይዝ እንደሚገባ፣ ተመራጭ ጽንሰ ሐሳብ መሆኑን ተከራክሯል። ነገር ግን ራስን በራስ ማስተዳደር ሊተገበር የሚገባው ለብዙ ዘመናት ከማሕበረሰብ እየጠፋ ካለው፣ በቲኤትኖመስ ጥላ ውስጥ ሆኖ ነው የሚል እምነት ነበረው።

## ስለ እግዚያብሔር መኖር አለመኖር በተመለከተ:-

## የእግዚብሔር አለመኖር (The non existence of God)

ቲሊች ስለ እግዚአብሔር መኖር አለመኖር በተመለከተ፣ እንደ አንድ ስልታዊ ነገረ መለኮት ሊሂቅ የራሱን “አያዎ” (paradoxical statement) የሆነ ጽንሰ ሐሳብ አዳብሮ አስቀምጧል። ቲሊች፣ ስልታዊ ነገረ መለኮት“Systematic Theology” በተሰኘው ሥራው፣ እግዚአብሔር የለም በማለት አስገራሚ ንግግሮችን ተናግሯል፣ ይህም እግዚአብሔር የለም የሚል ፍልስፍናን ተቀብሏል የሚል ውንጀላ አስከትሎበታል። እርሱ ግን፣ እግዚአብሔር የለም የሚለውን ፍልስፍና ለመንቀፍ፣ እግዚያብሔርን የሆነ ቦታ እንደ ተቀመጠ እቃ፣ ጽንሰ ሐሳብ ወይም ስፍራ “አለ የለም” በሚል ክርክር መጀመርን የኮነነበት ጽንሰ ሐሳብ ነው።በቲሊች ሐሳብ መሠረት እግዚያብሔር ከEssence እና Existence ያለፈ

ነገር ነው።ቲሊች “እግዚያብሔር የለም፤ ስለዚህ እግዚያብሔር አለ ብሎ ሙግት መግጠም እግዚአብሔርን መካድ ነው። “ከ Essence እና Existence ባለፈ እርሱ በራሱ እርሱ ነው። እግዚአብሔር ያለ ኩነት (isn’t an existing being) ሳይሆን ( የሕላዌ (Existence) መሠረት ነው ሲል ተከራክሯል። ይህ ጽንሰ ሐሳብ ቲሊች የቱንም ያህል ላቅ ያለ ሐሳብ እና የሙግት አቀራረብ ቢሆንም እግዚአብሔርን እንደ Object ልንገነዘበው አይገባም በማለት አስቀድሞ ከደረሰበት ድምዳሜ የቀጠለ ሐሳብ ነው። እግዚአብሔርን በጊዜ እና በቦታ እንዳለ Being ልናስበው አንችልም። ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ያለን መረዳት እንደ አንድ በጊዜ እና በቦታ ውስጥ ያለ Being ከሆነ፣ ያ ማለት እግዚአብሔርን ገደብነው ማለት ነው። በዚህ ሙግታችን መሠረት እግዚአብሔር ውስን ነው። ይልቁንም እግዚአብሔር ከሁሉም ገደቦች እና ድንበሮች ያለፈ የሕላዌ መሠረት ተደርጎ መታሰብ አለበት። ቲሊች የእግዚአብሄርን መኖር ጽንሰ ሐሳብ አለመቀበል እሱን በትክክል ለመረዳት አስፈላጊ መሆኑን በግልፅ ተናግሯል። ቢሆንም አንዳንዶች ይህንን የሕላዌን ጽንሰ ሐሳብ በተጠቀመበት መንገድ ምክንያት እግዚአብሔር የለም ብሏል ብለው ሊተረጉሙት ይችላሉ። የቲሊች መግለጫዎች በአድማጮቹ ላይ ድንጋጤ በመፍጠር የውሸት ሀሳቦችን በኃይል ለማረም እንደሚያገለግሉ ማስታወስ ጠቃሚ ነው።

## 2. ራይሆልድ ኒቦር

ካርል ፖል ራይሆልድ ኒቦር (ጁን 21, 1892 – ጁን 1, 1971) የፕሮቴስታንት ማሕበራዊ አሳቢ፣ የሥነ ምግባር ፍልስፍና አራማጅ፣ ሰባኪ፣ ጸሃፊ እና የክርስቲያናዊ ተጨባጭ ኩነት (Christian realism) ንጽረተ ዓለምን በመፍጠር የታወቀ ነበር። በዲትሮይት ሚቺጋን ለ13 ዓመታት አገልጋይ በመሆን አገልግሏል። እና በአሰሪ እና ሰራተኛ መካከል ያሉ አለመግባባቶች የመሰሉ ማሕበራዊ ችግሮችን መፍታት አስፈላጊ መሆኑን የተመለከተ እና እሱን ለመፍታት የጣረ ሰው ነበር። የፕሮቴስታንት ልዝብነት ፍልስፍና (Protestant liberalism) እነዚህን እና መሰል ጉዳዮች ለመፍታት ፍላጎት የሌለው እና ዳተኛ መሆኑን በማየቱ ደስተኛ ባለመሆኑ፣ የኀጢአትን ጽንሰ ሐሳባዊ አስተምህሮ ተጠቅሞ የሰውን ተፈጥሮ፣ እጣ ፈንታ እና ማኀበራዊ የሕይወት ገጽታዎችን ማጥናት ጀመረ። ኒቦር እምነት እና ማሕበራዊ ጉዳዮች፣ በሃይማኖት እና በፖለቲካ፣ እና በሰው መንፈስ እና ተፈጥሮ መካከል ሚዛኑ ምን እንደሆነ ለማግኘት እና ለመረዳት የሞከረ ሰው ነበር። የእሱ ሃሳቦች በእግዚአብሔር ፍቅር ፊት ያለውን የሰውን ኩራት የሚሞግቱ ነበሩ። ኒቦር በማሕበራዊ ወንጌል፣ በአንደኛው የዓለም ጦርነት፣ በፓሲፊዝም (በጦርነት ተቃዋሚ)፣ በማርክሲዝም፣ በታላቁ የኢኮኖሚ ድቀት፣ በአሜሪካ የተለየሁ ነኝ ባይነት ላይ፣ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት፣ በአቶሚክ በምብ እና በዲሞክራሲ ባሉ አርእስተ ጉዳዮች ላይ አትኩረቱን አድርጎ ሰርቷል። በኒውዮርክ ከተማ በዩኒየን ቲዎሎጂካል ሴሚናሪ ከ30 ዓመታት በላይ አስተምሯል።

ተቺዎች የኒቦር ሥነ መለኮታዊ የሥነ ምግባር ጽንሰ ሐሳብ የሰውን የኀጢአተኛነት እውነታ ትንሽ ከመጠን በላይ እንዳጋነነው በመንቀፍ ቅሬታ አቅርበዋል። ይህም አቀራረቡ በታሪክ ውስጥ ያለውን የኢየሱስን ፍቅር “የማይደረስበት ተደራሽ” (an impossible possibility) አድርጎ ማቅረብ ነው። ደግሞም የእግዚአብሔርን መንግሥት እውን ለማድረግ ታሪክን እና ዓለምን የሚቀይሩትን የእግዚአብሔርን ታላላቅ ሥራዎች በበቂ ሁኔታ አጽንዖት አይሰጥም በማለት ቅሬታቸውን ያሰሙ ነበር። ነገር ግን የእሱ ትንቢታዊ (ነገን የመተንተን) እና አስተዋይ አመለካከቶች በሃያኛው ክፍለ ዘመን የመጀመሪያ አጋማሽ ላይ በጣም ተደማጭነት ያለው አሜሪካዊ የነገረ መለኮት ምሁር እንዳደረገው ጥርጥር

የለውም። ትምህርቱን ማስተርስ ዲግሪ ላይ ያቆመ እና የዶክትሬት ዲግሪ ባያገኝም ኦክስፎርድ የሸለመውን ጨምሮ 18 የክብር ዶክትሬት ተሸልሟል። እ.አ.አ. በ1964 ደግሞ የፕሬዚዳንት የነፃነት ሜዳሊያ ተቀበለ።

## ሕይወት

ኒቦር የተወለደው በራይት ሲቲ፣ ሚዞሪ፣ የኤስኤ ከጉስታቭ እና ሊዲያ ኒቦር ነው። አባቱ ጉስታቭ ለዘብተኛ አስተሳሰብ ያለው የጀርመን ወንጌላዊ ፓስተር ነበር። የአባቱን ፈለግ በመከተል ወደ አገልግሎት ለመግባት ወሰነ። አሁን የእርሱ ትልቅ ሃውልት ተሰርቶ በቆመበት በኤልመረስት ኮሌጅ፣ ኢሎኒስ ትምህርቱን ተከታትሎ በ1910 ካጠናቀቀ በኋላ በሲቲ ለዊስ፣ ሚዞዮሪ በመዘዋወር በአዴን ሴሜናሪ ሥነ መለኮት ትምህርቱን ተከታትሏል። በመጨረሻም የሥነ መለኮት ድግሪ በ1914 እና በማስተር ኦፍ አርትስ በ1915 ወደተቀበለበት የል ዩኒቨርሲቲ ገብቷል። ወንድሙ ኤች. ሪቻርድ ኒቦርም በዬል ተምሮ የሥነ መለኮት ምሁር ሆነ። ልክ እንደ ቤተሰቡ እና አብረውት እንደሚማሩት አብዛኛዎቹ ተማሪዎች፣ ኒቦር በጊዜው በጣም ከፍተኛ ተፅዕኖ ፈጥሮ የነበረውን የማሕበራዊ ወንጌል (social gospel) አማኝ ሆኖ ጀመረ።

በ1915፣ ሬሆልድ በቤተ ክርስትያን ውስጥ መጋቢ ሆኖ ተሾመ። የጀርመን ወንጌላዊ ተልእኮ ቦርድ በዲትሮይት፣ ሚቺጋን በሚገኘው ቤቴል ወንጌላዊት ቤተ ክርስቲያን እንዲያገለግል ላከው። እርሱ ወደዛች ከተማ እንደመጣ የምእመናኑ ቁጥር 65 ያህል ሲሆኑ፣ በእርሱ፣ መሪነት ወደ ቁጥራቸው 700 አደገ። በአንድ በኩል የምእመኑ እድገት የጨመረው፣ እርሱ ያገለግልበት በነበረበት ከተማ በከፍተኛ ሁኔታ ተከማችቶ የነበረው የአውቶሞቢል ኢንደስትሪ ከፍተኛ እድገት ምክንያት ነው። ኒቦር ዲትሮይትን “የኢንዱስትሪ ከተማ ግንባር” በማለት ይጠራት ነበር። ለአዲሱ ቤተ ክርስቲያን ሕንፃ ክፍያ የረዱትን የኢንዱስትሪ ሠራተኞችን እና ሀብታም የንግድ መሪዎችን ያካተተ የነበረውን የራሱን ቤተ ክርስቲያን ምዕመናን በሚያገለግልበት ወቅት በኢንዱስትሪ ውስጥ የሚሰሩ ሰራተኞች ይጓደልባቸው የነበረውን ፍትሕ ለመገንዘብ በቃ። ለኒቦር ሄኔሪ ፎርድ የካፒታሊስት መደብ ሁነኛ ተወካይ ነበር። ኒቦር የማሕበራዊ ወንጌልን ሊበራል ሃሳባዊነት፣ እነዚህን ጉዳዮች ለመፍታት በጣም ሃሳባዊ ሆኖ ስላገኘው፣ በሞራል እድገት ላይ ባለው የዩቶፒያን እይታዎች ተስፋ ቆረጠ። እ.አ.አ. በ1920ዎቹ የጻፋቸው አብዛኛው ፅሁፎች፣ የፕሮቴስታንት ሊበራሊዝም ኢኮኖሚያዊ እና ፖለቲካዊ ስልጣንን አላግባብ መጠቀምን እና

ብዝበዛን ለማስቆም ያለው ማሕበራዊ ብቃት ማነስ የሚነቅፉ እና የሚያሳጡ ፅሑፎች ናቸው። በ1927 የፃፈው (Does Civilization Need Religion? (1927)) የመጀመሪያው መጽሃፉ ስልጣኔ ሃይማኖት ያስፈልገዋል? (1927) በዲትሮይት ከተማ የነበረው ልምድ ውጤት ነው። እ.አ.አ. በ1928 ባሳተመው ማስታወሻ ደብተር ላይ “ባሉበት ዘመን  አነታራኪ በሆኑ ጉዳዮች ላይ ምንም አይነት ግንዛቤ ሳይኖራቸው” የውርስ ሃይማኖታዊ አስተሳሰባቸውን በየዋህነት ያስተማሩትን ፓስተሮች ነቅፏል። ኒቡር በኢንዱስትሪ ሰራተኞች ላይ የሚደረገውን የጉልበት ብዝበዛ ቆሞ ፍትሕ እንዲሰፍን ሞግቷል። በሌሎች ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ መፃፍ እና መስበኩ በፍጥነት አገራዊ ዝናን አትርፎለታል። ይህም ዝናው በ1923 ከጦርነቱ በኋላ ስላለችው አውሮጳ ከምሁራን እና የሥነ መለኮት ሊቃውንት ጋር ለመወያየት ወደ አውሮጳ እንዲሄድ በር ከፍቶለታል። በፈረንሳይ ወረራ በጀርመን ያያቸው ሁኔታዎች አሳዘኑት። በዲትሮይት በተካሄደው አገር አቀፍ የተማሪዎች ስብሰባ ላይ፣ በኋላም የዩኒየን ሥነ መለኮት ሴሚናሪ ፕሬዘደንት ከሆነው እና ምንም እንኳን የዶክትሬት ዲግሪ ባይኖረውም እርሱ ብቻ እንዲያስተምርበት በተዘጋጀው ተግባራዊ ክርስትና ትምህርቶችን እንዲሰጥ በዩኒየን ሥነ መለኮት ትምህርት ቤት ካስገባው ከሄንሪ ስሎኔ ኮፊን ጋር ተዋወቀ። በ1928 የማስተማር ሥራውን ተቀበለ። በኒዮርክ የነበረው ሕይወቱ ሲያስተምር፣ ሲጓዝ፣ ሲጽፍ እና ብዙ ማሕበራዊ ድርጅቶች ውስጥ ተሳትፎ ያደረገበት አድካሚ ወቅት ነበር።

እ.አ.አ. በ1930ዎቹ መጀመሪያ ላይ ኒቡር በአሜሪካ የሶሻሊስት ፓርቲ ውስጥ በጣም ተጋፋጭ የነበረው አንጃ ቁልፍ መሪ በመሆን የኮሚኒስት ፓርቲ የዩኤስኤስ የተባበሩት ግንባር አጀንዳዎችን በመደገፍ ለአጭር ጊዜ አገልግሏል። ይህ የነበረው አቋም ከኋላ ካሉት አመለካከቶቹ በጣም የተለየ ነበር። የኒቡር ተቀናቃኝ ሉዊስ ዋልድማን በሕይወት ታሪኩ ውስጥ ኒቡር በወጣቶች ኮሚኒስት አባላት ጋር በመሆን ወታደራዊ ልምምድን እንደመራ ፅፏል። ሊበራሊዝምን ከማርክሲስት አንፃር ሲተች ነበር።

ይሁን እንጂ ኒቡህር በኮሚኒዝም ላይ የነበረው እምነት የቆየው ለአጭር ጊዜ ነበር። በኮሚኒስት ርዕዮተ ዓለም ተከታዮች ግትርነት እና ገንቢ ክርክሮች ውስጥ ለመሳተፍ ፈቃደኛ አለመሆን መንገዱን እንዲቀይር አድርጎታል። እ.አ.አ. በ1934 የስታሊንን ሶቪየት ሕብረትን ከጎበኘ በኋላ በአብዮት አማካኝነት ማሕበራዊ ፍትሕ ያለበት ማሕበረ ሰብ መገንባት ይቻላል በሚለው ፕሮፓጋንዳ መታለሉ ገባው። በኋላም የሰብአዊ መብቶችን ችላ የሚሉ እና የስልጣን ገደቦች የሌላቸው

የኮሚኒስት ሀሳቦች ጠንካራ ነቃፊ ሆነ። ከኮሚኒስት አብዮት ጋር ሲነጻጸር፣ ለታላቁ ዲፕሬሽን የበለጠ ተግባራዊ መፍትሄ ይሆናል ብሎ ወደመነበት ትኩረቱን ወደ ሩዝቬልት አዲስ እቅድ አደረገ።

ከኮሙኒስቶች ጋር ያለው ወዳጅነት የተቋጨው በአጭሩ ነበር። ለተወሰ ጊዜያት አብሮአቸው ውይይት ካደረገ በኋላ ትችት እና ሂስ የማይወዱ በመሆናቸው እና ምክንያታዊ ሙግት ባለመፍቀዳቸው ተሰላቸባቸው። እንዲሁም በ1934 ሶቪየት ሀብረትን ጎበኝቶ እና የስታሊንን የሶሻሊዝም ሙከራ አይቶ ከተመለሰ በኋላ፣ በኮሙኒስት አብዮት ፍትሀዊ እና እኩልነት የሰፈነበት ማሕበረ ሰብ መገንባት የሚቻል ስለመሆኑ ከልክ ያለፈ ፕሮፓጋንዳ እንደጠጣ ተገነዘበ። ከዚያ ወዲህ የኮሚስቶች ምናባዊ የቶፒያኒዝም ላይ ጠንካራ ትችቶችን መሰንዘር ጀመረ፤ ምክንያቱም ኮሚኒዝም በተግባር ለሰብዓዊ መብቶች ግድየለሽ እና ወደ አንባገነናዊነት የሚያጋድል ሥርዓት ነው። ከዚያም በጊዜው ለነበረው የኢኮኖሚ ቀውስ ከኮሚኒዝም ይልቅ አዲሱ ሩዝቬልት ያቀረበው አማራጭ ሃሳብ የተሻለና ተጨባጭ ለውጥ ሊያመጣ የሚችል ነው ብሎ ወደማመን መጣ። የጸረ ናዚ ቤተ ክርስቲያን አባል የሆነው ዲትሪች ቦንሆፈር በ1930 ወደ ዩኒዮን የሥነ መለኮት ሴሚናሪ መጣ። በዚያ ቦንሆፈር እና ኔቡር እምነት እና ሥራ ያላቸው ግንኙነት ምንድነው በሚል ርዕስ ጥልቅ ሙግት አድርገዋል። ኔቡር እምነት እና ሥራ ፈጽሞ የተለያዩ ናቸው የሚለውን ተለምዶአዊ የሉተራኖች እይታ አይቀበልም። «ግብረገብ ከእምነት ጋር በተያያዘ ብቻ ግብረገብ ሊባል አይገባም፤ ተጨባጭ የሆነ ማሕበራዊ ተግባር ሊታከልበት ይገባል» ብሎ ተከራክሯል። በዚያው አመት ጀርመን ውስጥ የካርል ባርትን ሥነ መለኮት እየጠና የነበረ ሪቻርድ የተሰኘ ወንድሙን ሊያገኘው ወደ ጀርመን አቀና። እዚያ እያለ «ከባርት ተከታዮች ጋር መከራከር ፍሬ አልባ እና ተስፋ ቢስ» ነው የሚል ደብዳቤ ጽፎ ነበር።

ሆኖም በሂደት በሰው ልጅ ሀጢያተኝነት ላይ አጽንኦት የሚሰጠው የባርት ትምህርት ኔቡር ላይ ተጽዕኖ አሳድሮበታል፤ በኋላም ይህንን የባርት ትምህርት ተቀብሎ ለማሕበራዊ እና ለፖሎቲካዊ ጉዳዮች ካለው እይታ ጋር አዋህዷል። ኔቡር Christian realism የተሰኘ ትምህርቱን ያዳበረው Moral Man and Immoral Society (1932) , Reflections on the End of an Era (1934) , An Interpretation of Christian Ethics (1935) , and Beyond Tragedy (1937) በተሰኙ በመጽሐፎቹ ሊበራሊዝምን በሚተችበት ጊዜ ነው። በተለይ መጨረሻ ላይ በተጠቀሱት በሁለት መጽሐፎቹ ላይ ስለሰው ልጆች ሀጢአተኝነት ያለው መረዳት

ጥልቅ እንደሆነ በግልጽ ይታያል። ኤዲንበርግ በተሰኘ ዩኒቨርስቲ ሌክቸር እንዲሰጥ ተጋብዞ ነበር፤ በዚህ መድረክ በተለያዩ ሰነመለኮታዊ ርዕሶች ላይ ያሉትን እይታዎች ሰብስቦ ስልታዊ በሆነ መንገድ አደራጅቶ የማቅረብ ችሎታውን አስመስክሯል። ኋላ ይህ ሌክቸር “The nature and destiny of man” በሚል ርዕስ በመጽሐፍ መልክ ታትሞ ሰፊ እውቅና አስገኝቶለታል። ሥነመለኮታዊ ርዕሶች ላይ ያሉት ድንቅ እይታዎች፣ ማሕበራዊ ጉዳዮች ላይ ያሰማቸው ነብያዊ ድምጾች እና በሀገር ደረጃ ያለው ቁልፍ ቦታ እጅግ ተፈላጊ የክርስትናዊ አና ማሕበራዊ ጉዳዮች አማካሪ ሊያደርገው ችሏል።

ፓሲፊዝም ጦርነት በየትኛውም ጊዜና ሁኔታ ትክክል አይደለም የሚል እሳቤ ነው። ኔቡር ወደዚያ የሚያጋድል እይታ ነበረው። የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ሲፈነዳ ያንን እይታ እርግፍ አድርጎ ተወ። ከፓሲፊስት ባልደረቦቹ ራሱን ማራቅ ጀመረ። ጦርነቱን በግልጽ መደገፍ ጀመረ። ብዙም ሳይቆይ እርቅ እና ሰላም ላይ ትኩረት አድርጎ ከሚሰራው የቲዎሎጂያን እና ሚንስትሮች ማሕበር ራሱን አገለለ፤ ከዚያም “Christians and crises” በተሰኘ መደበኛው ክርስትና ለመንካት የማይደፍራቸውን ጉዳዮች ለመዳሰስ በሱ በቋቋመው ጋዜጣ አማካኝነት ጠንካራ ሂሶችን እና ትችቶችን ይሰነዝርባቸው ጀመር። በ1940 ስለ ሂትለር እና ስለ ሁለተኛው የዓለም ጦርነት ያለውን እይታ ለመግለጽ “Christianity and power politics” የተሰኘ መጽሐፍ አሳተመ። Christian realism በተሰኘ እይታው በተቃኘ በዚህ መጽሐፉ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አሜሪካ ያላትን ሚና ደግፏል፤ ኮሙኒዝምን ተችቷል፤ ለሌሎች ሀገራት ኒኩሊየር መሳሪያ እንዳይጠቀሙባት ዋስተና ይሆናት ዘንድ አሜሪካ የራሷን ኒኩሊየር መሳርያ ማብላላቷን ደግፏል። ለሀይል ፖሊቲካ አጽንኦት የሚሰጠው Christian realism የሚሰኘው የኔቦር እሳቤ political realism የተሰኘ እይታ አባት በመባል በሚታወቀው ሀንስ ሞርገንት ላይ ትልቅ ተጽዕኖ አሳርፏል።

ኔቡር በ1952 “the irony of American history” የተሰኘ መጽሐፍ ጽፏል፤ በዚህ መጽሐፉ ፖሊቲካዊ፣ ሪዕዮታዊ፣ ሥነምግባራዊ እና ሀይማኖታዊ ትግሎች ላይ ያለውን ተሳትፎ ዳሷል። አሜሪካ በሁለተኛው የዓለም ጦርነት ድል መቀዳጀቷ እና የኒውክለር መሣርያ ባለቤት መሆኗ የአለማችን ሀያሏ ሀገር አድርጓታል፤ ኔቡር በሕይወት ዘመኑ ያየው በታሪክ የመጨረሻው የአሜሪካ ታሪክ ምፀት ይህ ነው። የአሜሪካ ታሪክ በምፀት የተሞላበት መንገድ ይህ ነው። በአንድ በኩል በክርስትና እምነትና አስተሳሰብ ተመርታ የብልጽግና እና የኀይል ከፍታ

ላይ የደረሰች ሲሆን፤ በሌላ መልኩ ደግሞ ይህን የደረሰችበትን ብልጽግናና ሀይል በሌሎች የፖለቲካ ኃይሎችና ሀገሮች ላይ እንዳሸት እንዳትሆን የሚከለከላት ወይ ሊቆጣጠራት የሚቻልበት መንገድ አለመኖሩ ነው። ኒቦር ይህን ሁኔታ የአሜሪካ የታሪክ ምጸት በማለት ይጠራዋል። ለሀገራት ሁሉ ምሳሌ እና የዓለም አዳኝ ተደርጋ የምትቆጠረው ሀገር በፍጥነት የአለማችን እጅግ አደገኛ ኢምፓየር እና ጨቋኝ ተደርጋ መታየት ጀመረች፤ ታዲያ ክርስቲያን አሜሪካውያንም የተቀረው ዓለም ዜጎችም በዚህ ላይ ያላቸው እይታ ተመሳሳይ ነው።

ኔቦር 18 የክብር ዶክተሬት ተሸልሟል፤ ከ18ቱ አንድ ከዬል፣ አንድ ከኦክስፎርድ፣ አንድ ደግሞ ከሀርቫርድ ነው። በ1964 ዓ.ም ከፕሬዝዳንት ሊደን ጆንሰን የነጻነት ሜዳልያ ተሸልሟል። የኒውዮርክ ከተማ አስተዳደር በስሙ ዩኒየን የሥነ መለኮት ሴሚናሪ የሚገኝበትን አከባቢ የምእራቡን 120ኛን መንገድ በስሙ ሰይሟል።

## የኔቦር ሥነ መለኮት

ኔቦር የሥነ መለኮት ሰው ከመሆኑ በላይ የማሕበራዊ ፍትሕ ታጋይነቱ የመዘናል። ነገር ግን የተረዳውን የክርስትና አስተምህሮ ወደ ማሕበራዊ ፍተህ እንቅስቃሴ ተግባራዊ የሚያደርግበት መንገድ ጥልቅ የሆነ የሥነ መለኮት አንድምታ አለው። ተጽእኖውም ከክርቲየኑ ማህቀረሰብ ያለፈና ጠቅላላ አሜሪካን የካለለ ነው። ስለዚህ ኔቡር በተጽእኖ ወደር የሌለው የ20ኛው ክ.ዘ የመጀመርያ አጋማሽ የሥነ መለኮት ሰው ነው ቢባል አንዳች ማጋነን የለበትም።

## ፖለቲካንና ማሕበራዊ ጉዳይ የሚዳሰስበት መንገድ (Christian realism)

Moral Man and Immoral Society (1932) ከሚለው መጽሀፋ ዕትመት ጋር በብዛት የሚተሳሰረው Christian realism የተሰኘው የኔቡር ትምህርት realism የተሰኘው በሁለት አግባብ ነው። የመጀመርያው በገሀዱ ዓለም ላሉ ፖለቲካዊ እና ማሕበራዊ ጉዳዮች አጽንኦት መስጠቱ ነው። Protestant liberalism የተሰኝ እይታ የሚከተሉ ክርስቲያኖችም ለሰው ተፈጥሮ ካላቸው አዎንታዊ አመለካከት እና

እግዚአብሔር ከምንም በላይ ቅርብ ነው ከሚል እይታቸው የተነሳ ማሕበራዊ እና ፖሊቲካዊ ጉዳዮች ውስጥ በሀይል ይሳተፉ ነበር። ነገር ግን የሰው ልጅ ሀጥያተኝነት እና ሰዎች ከእግዚአብሔር ፈጽሞ የራቀ ስለመሆናቸው አጽንኦት የሚሰጠው neo Orthodox የተሰኘው የkarl Barth ትምህርት በማሕበራዊ ጉዳዮች በቀጥታ ለመሳተፍ አመቻምቿል። ሁለተኛው ደግሞ፥ የኒቡር ጥንታዊውን ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በመከተል የኒቦር Christian realism አስተሳሰብ፣ የሰው ልጅ በሃጢአት ማጥ መዘፈቁን እና እግዚአብሔር ከሁሉ የሚልቅ መሆኑን ይቀበላል። በዚህም Christian Orthodoxን ይቀበልና በጊዜው እጅግ ገኖ የነበረውን Protestant liberalismን ይጥላል። የነበረው ኦርቶዶክስ እምነት ለማሕበራዊ እና ፖለቲካዊ ጉዳዮች ተግባራዊ መልስ እንዲሰጥ በር በመክፈቱ፣ ለChristian realism ልዩ እና አይነተኛ መልክ ሊሰጥ ችሏል። ኒቦር liberalism ምን በመቃወም ረገድ ከneo Orthodoxy አንጻር ለዘብተኛ ነው፤ ምክንያቱም ስለ እግዚአብሔር ልእለ ተፈጥሮነት ያለው እይታ የneo Orthodoxyን ያህል እጅግ የከረረ አይደለም። ሆኖም በሰው ልጅ ማሕበረ ሰብን የተሻለ በማድረግ ችሎታ እምነት የለውም። በዚህ ወደ neo Orthodoxy ያደላል። በአጠቃላይ Christian realism ከ liberalism እና ከ Orthodox መኻል ያለ እይታ ይመስላል። ከ2ኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአውሮፓ neo Orthodox በሀይል በማንሰራራቱ የተነሳ የ liberalism ተቀባይነት በፍጥነት አሽቆልቁሎ ነበር። በአሜሪካ ደግሞ በ1930ዎቹ liberal theology በChristian realism ተተክቶ ነበር፤ ይህ እይታ ከ neo Orthodoxy የተለየ ቢሆንም ለሰው ልጅ ሀጥአተኝነት ጥልቅ አጽንኦት ይሰጣል።

## ያልተሟላ ፍትሕ

ኒቦር ክርስቲያናዊ ባሕርይን በሚጻረር መልኩ ጥሩ የሚባሉ ክርስቲያኖች በብዙ እጅግ የተለያየ አቋም ያላቸው፣ እና እርስበርስ የሚታገሉ ቡድኖች አባላት እንደሆኑ አስተዋለ። በመጀመሪያው የዓለም ጦርነት የጀርመን ክርስቲያኖች ከአሜሪካ ክርስቲያኖች ጋር ተዋግተዋል። በዴትሮይት ደግሞ ክርስቲያን ኢንደስትሪያሊስቶች ክርስቲያን ሰራተኞችን በዝብዘዋል። እንዲሁም በቅርቡ idealist socialist ቶች አደገኛ የሆነ አብዮትን ሲያቀነቅኑ ተመልክቷል፤ ይህም የመጀመርያውን pacifism የተሰኘ እይታውን እንደገና እንዲፈትሽ ምክንያት ሆኖለታል።

እስከዛሬ የቀጠለው ይህ ርዕሰ ጉዳይ moral man and immoral so-

ciety የተሰኘ መጽሐፋ ዋና ርዕስ ነው። በዚህ መጽሐፋ በግለሰቦች ግብረገባዊና ማሕበራዊ ባሕርይ እና በማሕበራዊ ቡድኖችን መኻከል ልዩነት ስለመኖሩ አጽንኦት ሰጥቶ ሞግቷል። ግለሰቦች በዕለት'ለት ሕይወታቸው ከራሳቸው ጥቅም ይልቅ የሌሎችን ጥቅም እስካስቀደሙ ድረስ ግብረገባዊ ሊሆኑ ይችላሉ፤ በአንጻሩ ደግሞ ቡድኖች ሁልጊዜም ያልተገደበ ለራስ ጥቅም ብቻ ቅድምያ የመስጠት ባሕርይ አላቸው ብሎ ይሞግታል። ይህንን ሲል ግለሰቦች ሁልጊዜም ከራስ-ወዳድነት የጸዳ ግብረገባዊ ሕይወት ይኖራሉ ማለቱ እንዳልሆነ ልብ ልንል ይገባል። ግለሰቦች ሕብረተሰባዊ ቡድኖችን ለመመስረት ሲሰባሰቡ፣ የራስ ወዳድነት ስሜት በቀላሉ ይቆጣጠራቸዋል። ይህንን ችግር ለመቅረፍ ቡድኖች ከራስ ወዳድነት ነፃ መሆንን ከሥነ ምግባራዊ አስተሳሰብ ሁሉ የላቀ የሕይወት መመሪያ ማድረግ አለባቸው።አንድ ማሕበረ ሰብ ፍትሕን የሁሉ ነገር መጀመርያ አድርጎ መቀበል አለበት። ኒቦር በሥነ መለኮት በታገዘ መልኩ ዕይታዎቹን የበለጠ ያዳበረው በቅዱስ አውግስጢኖስ realism አማካኝነት ክርስትና ስለሀጢያት ያለውን ጽንሰ ሀሳብ በትክክል እንደገና ከተረዳ በኋላ ነበር።

An Interpretation of Christian Ethics (1935) and Beyond Tragedy (1937) በሚለው መጽሐፋ ውስጥ እንደ ለዘብተኛ ክርስቲያናዊ አስተሳሰብ፣ መለኮታዊ ፍቅር በታሪክ ውስጥ ራስ ወዳድ ባልሆነ ሁኔታ መኖር እንደሚቻል ፣ እና የሰው ልጅ ሁሉ አንዱ ለሌላው ሊኖር እንደሚችል የኢየሱስ በመስቀል መሰቀል መገለጫ ነው የሚለውን አቋም አይቀበልም። እንደ ኒቦር ሃሳብ እንዲህ አይነት ዕሳቤ በፖለቲካ ፍትሕ ላይ የሚተገበር አይደለም። ቢሆንም ለሰው ልጆች ሁሉ የተገባ የመጨረሻው የሕይወት ትክክለኛ ነገር መለኮታዊ ፍቅር ነው። ለኒቦር የሰው ልጅ ክቡርነት የሚመነጨው ከታሪክ ክስተቶች ከፍሎ በመሄድ እና ከፍተኛውን ሕላዌ ለመቀዳጀት ማለሙ ነው። ነገር ግን የሰው ልጅ ኃጢአተኝነት በተፈጥሮ ውስጥ ያለን ሁሉን ነገር ራሱን ጨምሮ ለመቆጣጠር የሚፈልግ (will-to-power) አድርጎታል። ይህ ሃጢያት የፈጠረው ተፈጥሮ ሰዎች ከሚገባው በላይ ሁሉ ነገር ለራሳቸው እንዲሉ አድርጓል።

## የሰው ተፈጥሮ

The Nature and Destiny of Man (1941) በተሰኘው የመጀመሪያ ጥራዝ ውስጥ ሥነ መለኮታዊ አንትሮፖሎጂ ምን እንደሆነ አሳይቷል። እያንዳንዱ ሰው በግጭት ውስጥ ያለ ሁለት የተለያዩ ገጽታዎች አሉት "ተፈጥሮ" እና "መንፈስ"።

የሰው ልጅ ተፈጥሮአዊው ገጽታ ስንል እንደማንኛውም እንስሳ የምንካፈለው፣ የተገደብንበት እና ውስን የሆንበት ማንነት ማለት ነው። የሰው ልጅ መንፈሳዊ ገጽታ ስንል ደግሞ በእግዚአብሔር አምሳል የተፈጠረ ሁሉ ነገር አሻግሮ ማየት የሚችል፣ በምንም ነገር ያልተገደበ ነፃና ማብቂያ የሌለው ማንነታችን ማለት ነው። እኛ ሰዎች ልዩ ነን ምክንያቱም የሰው ተፈጥሮ ከፍተኛ እና ዝቅተኛ ግምት ያለውን አያዎ (ፓራዶክስ) የሚያብራራ ውጥረት ነው። በተፈጥሮ እና በመንፈስ መካከል ያለ ውጥረት በራስ የመተማመን ስሜት እንዲሰማን ወይም ጭንቀት እንዲሰማን ማድረጉ የማይቀር ነው። ምንም እንኳን ይህ አለመተማመን ወይም ጭንቀት ከኃጢአት ጋር ተመሳሳይ ባይሆንም “የኃጢአት ቅድመ ሁኔታ” ነው።

ጭንቀት ወደ ሁለት የተለያዩ መንገዶች ሊያመራ ይችላል። 1) ጥሩ ዕድል፣ እሱም አዎንታዊ ነው፣ የሰው ልጅ የፈጠራ ችሎታ ሁሉ መሠረት መሆኑ ነው። እና 2) ሌላኛው ዕድል አሉታዊ ነው። ይህም ኃጢአትን ለመሥራት ፈተና ይሆናል። ከጥሩ ዕድል ወይም ከመሆን ተስፋዎች አንጻር ካየነው፣ የእግዚአብሔርን ፍቅር የመጨረሻ ዋስትና በእምነት ይገኛል። ነገር ግን በሌላ አጋጣሚ፣ ጭንቀት የእግዚአብሔርን የደህንነት ዋስትና ማግኘት የማይችል ይሆናል። ከዛ ይልቅ በጭንቀት ምክንያት ራስን ከፍ አድርጎ ራስን የሁሉ ነገር ወሳኝ ቦታ ወደ ማስቀመጥ ሊያመራ ይችላል። ራስን ከፍ ማድረግ ወደ ወሰን የለሽ የ”ትዕቢት” ኃጢአት ያስከትላል። ራስን ውስንና ዝቅ ማድረግ ደግሞ “ግብታዊና ስሜታዊ” ሕይወት ውስጥ ይዘፍቃል።

እንደ ኒቦር አባባል የትዕቢት ኃጢያት ባለን ሀይል እና ምሁራዊ እውቀት መመካትን ያካትታል። በመሠረቱ ይህ መጽሐፍ ቅዱስ ኃጢአትን የሚፈታበት መንገድ ነው። የስሜታዊነት ኃጢአት በተቃራኒው የጾታ ልቅነትን፣ ሆዳምነትን፣ ከመጠን ያለፈ ልፋትን፣ ስካርን፣ ተድላን፣ ዝሙትን እና ለተለያዩ አካላዊ ፍላጎቶች መከተልን ያጠቃልላል። ይህ አመለካከት ሪጀን፣ የአሌክሳንደሪያው ክሌመንት እና የኒሳ ጎርጎርዮስ ውስጥ እንደምንመለከተው ጥንታዊ የ Hellenistic ስለ ኃጢአት ያለ እይታ ነው። ትዕቢት ከስሜታዊነት የበለጠ መሠረታዊ እንደሆነ ያስረዳል። ምክንያቱም የኋለኛው ከቀድሞው የተገኘ ነው። ነገር ግን የስሜታዊነት ሀጢያት ከትዕቢት ሀጢያት ይልቅ ግልጽና ሁሉም ሰው በሚያየው መንገድ የሚሆን ስለሆነ፤ ለማሕበረ ሰብ ውግዘት የተጋለጠ ነው። ያም ሆኖ ግን ኒቡህር ራሱ እንደተናገረው የሁለቱ ግንኙነት አሁንም ግልጽ አይደለም።

## የሰው እጣ ፈንታ

ሁለተኛው የኒቦር መጽሐፍ The Nature and Destiny of Man የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ምን እንደሆነ የሚዳስስ መጽሐፍ ነው። የታሪክን ትርጉም የሚገነዘቡ የታሪክ አመለካከቶች፣ ከታሪክ ካልሆኑ አመለካከቶች ተለይተዋል። ከታሪክ የሚቃረኑ አመለካከቶች (Non historical)፣ ታሪክን አላማ በሌለው መንገድ ራሱን የሚደጋገም ክስተት አድርጎ የሚመለከተውን classical naturalism የሚያካትት ሲሆን፣ የዚህ አስተሳሰብ ፊት መሪዎች በዲሞክሪተስ፣ ሉክሪቲየስ፣ ወዘተ የመሳሰሉት ናቸው።

ሁለተኛው classical naturalism የሚያካትተው አስተሳሰብ ደግሞ ድብቅና ጥልቅ የሆኑ ነገሮችን የመረዳት ደረጃ classical mysticism የሚባለው ነው። ይህ አስተሳሰብ ተጨባጩ ታሪክ የሚፈጠርበት ዓለም በመሸሽ ወደ ማይዳሰስና ወደማይጨበጥ ራሱ ወደ ፈጠረው ዘላለማዊነት (mystical realm of eternity) ይገሰግሳል። እነዚህን ሀሳቦች በፕላቶ፣ ፕሎቲነስ፣ ሂንዱይዝም፣ ወዘተ ሥራዎች ውስጥ እናገኛለን። በተቃራኒው ታሪካዊ አመለካከት ግን የታሪክ ትርጉምና ፍጻሜ ፍትሕና ሰላም በማስፈን ውስጥ ነው ብሎ ያምናል። ይህም በታሪክ ሂደት ውስጥ በሚመጣው ድነት (Messiah) ይከናወናል የሚለውን ያስተምራል። ሦስት የተለያዩ የመሲሐዊነት ዓይነቶች አሉ፦ “egoistic-Nationalistic”፣ “Egoistic-Nationalistic”፣ “Ethical-Universalistic”፣ እና “Supra-ethical religion” ዓይነቶች ናቸው። የመጀመሪያው የአንድ ሀገር የበላይነትን፣ አሸናፊነትን በተመለከተ ያለውን እውነታ የሚዳስስ ነው። ሀገሮች እነርሱ ብቻ አሸናፊ እንዲሆኑ የሚፈልጉበት የራስ ወዳድነት መገለጫ ነው። ሁለተኛው አይነት ደግሞ በአጽናፈ ዓለሙ ላይ መልካም ነገር በእኩይ ላይ ድል ይቀዳጃል የሚለው አመለካከት ወደ ትዕቢትና ወደ ጣኦትን ማምለክ ይመራል ብሎ ያስባል። ሦስተኛው ዓይነት በአንፃሩ “ነቢያዊ ሲሆን” ለሁሉም እንደሥራው የሚከፍለውን” የእግዚአብሔርን የፍርድ ቃል ከፊት የሚያስቀድም አመለካከት ነው።

በታሪክ ውስጥ አንድ ቀን መዳን ይሆናል የሚለው ዕብራይስጣዊው ተስፋ (Hebrew Messianism) ከላይ የተጠቀሱትን ሦስት ዓይነት የመሲህነት ተስፋዎችን

ይዞዋል። በናዚዝም ውስጥ የነበረ ሁሉን አሸንፌ የራሴን ሥርዓት እዘረጋለሁ የሚል የድነት ተስፋ፤ የራስ ወዳድ ብሄርተኛነት ሁነኛ መገለጫ ነው። የባቢሎናውያንና የግብፅ መሢሕነት ደግሞ ሁለተኛው ዓይነት ነበር። በኢየሱስ ውስጥ የምናገኘው አንድ ቀን በታሪኩ ውስጥ ድነት (The Messianic claims of Jesus) ይሆናል የሚለው ተስፋ የሚመደበው በሶስተኛው አይነት መሲሃዊ መዋቅር ነው። የተጎሳቆለውን አገልጋይ ሃሳብ ከኢሳይያስ 53 በማከል በድጋሚ ተረጎመው። በመስቀል ላይ እንደተሰቃየ አገልጋይ፣ ኢየሱስ የዓለምን ኀጢአት ፍቅር ግድ ብሎት በራሱ ላይ አደረገ። ነገር ግን፣ የኢየሱስ ፍቅር ስቅዩ ፍቅር እንጂ የድል አድራጊ ፍቅር አይደለም። ስለዚህም "ኀጢአት" የተሸነፈው "በመርህ ደረጃ እንጂ በተጨባጭ አይደለም"። ቢሆንም፣ የመጨረሻው ዘመን መጽሐፍ ቅዱሳዊ ምልክቶች ቃል በቃል ሊወሰዱ አይችሉም።

የሁለተኛው ምጽአት የኢየሱስ ፍቅር የመጨረሻ ድል ማለት ነው። በዳግም ምጽአት የሚሆነው ድል ልክ እንደ ዩቶፒያኒዝም አንድ ቀን በምድር ላይ በታሪክ ውስጥ የሚሆን ነገር ነው ብሎ ወይንም ደግሞ ይች የምንኖርባት ምድር ና ዓለም ከንቱ ነው (other worldly view) እንደሚለው አመለካከት የምድርን ጉዳይ ወደ ጎን ያለ አይደለም። ነገር ግን ሁለቱንም እይታዎች የሚያልፍ ከታሪክ የተሻገረ ነገር ያመለክታል። የመጨረሻው ፍርድ ማለት የሰው ልጅ በታሪክ ውስጥ የተከናወኑ ስኬቶችን ሁሉ ውድቅ ማድረግ ማለት ሲሆን በሰው ልጅ ሕላዌ ውስጥ በተፈጥሮአዊው ማንነታችን እና በመንፈሳዊው ማንነታችን መካከል ያለው ውጥረት ዘለዓለማዊ ወሳኝነት አለው የሚለው እምነታችን በእግዚያብሔር ኋይል የሚጠበቅበት ነው።

## ህዳሴ እና ተሐድሶ (Renaissance and Reformation)፦ ከሁለቱ ጥምረት የተወለደ አዲስ መንገድ

ኒቡር The Nature and Destiny of Man በሚለው ሁለተኛ መጽሀፍ ቅጽ ላይ፣ የካቶሊክን ቤተ ክርስትያን የፀጋ አስተምህሮ፣ ህዳሴና ተሐድሶ እንዴት ተከፋፍለው እንደወሰዱት ያሳያል። ከሁለቱ ጥምረት የተገኘው እንዴት "አዲስ መንገድ" (a new synthesis) ተብሎ እንደሚጠራ ያመለክታል። የካቶሊክ ቤተ ክርስትያን የፀጋ አስተምህሮ ጎደሎ የሆነውን የእኛን ተፈጥሮ ሙሉ ለማድረግ ወደ ውስጣችን እየገባ ነው በማለት ያረጋግጣል። ይህ ቀዳሚውን የግሪኮ ሮማን

ሰብአዊነት እና መጽሐፍ ቅዱሳዊውን የጸጋ አስተምህሮ ከማዋሃድ የመጣ ትምህርት፣ ህዳሴ እና ተሐድሶ (Renaissance and Reformation) እንቅስቃሴ ሲመጣ ተቀባይነቱን አጥቶአል። ወይም አይቀበሉትም። በሰው ልጅ አቅምና ችሎታ ላይ ፍጹም የሚታመነው ህዳሴ (Renaissance) የሰው ልጅ ራስ በቅነት ወደፊት መሻሻል እንዲመጣ የሚያደርግ ትልቅ ዕድል ነው ብሎ ይሟገታል። ተሀድሶ (Reformation) ደግሞ በሌላ ጎን ሆኖ፣ የሰው ልጅ በራሱ ብቁ ነው የሚለው ከእውነት የራቀ ነው። የሰው ልጅ በተፈጥሮ ውስንና ደግሞም የወደቀ ማንነት (ሃጢያተኛ) አለው። የሰው ልጅ ብቸኛ ተስፋ እግዚአብሔር ለእኛ የሚሰጠን ፀጋ ብቻ ነው ብሎ ይሞግታል።

ይህ አዲስ ውህደት ሁለት አስፈላጊ ነገሮችን አስገኝቷል፦ መቻቻል እና ፍትሕ። በአዲሱ ውህድ መንገድ መቻቻል አያዎ (ፓራዶክሲካል) ባሕርይ አለው። አንድ ሰው ጥልቅ ከሆነ እና ከእውነተኛ መረዳት እውነትን ሊይዝ ወይም ሊያገኝ ይችላል። ይህንንም ሲያደርግ አለ መቻቻልን ከሚፈጥር እኔ የፍጻሜውን የመጨረሻውን እውነት አግኝቻለሁ ከሚል እብሪት በመራቅ መሆን አለበት። እዚህ ጋ ግልጽ የሆነ ልዩነት ተቀምጧል። አንደኛው እንደሰው ፈልገን እውነትን በማግኘት የምንደርስበት ስኬት ሲሆን። ሁለተኛው ግን እግዚአብሄር ጋ ብቻ ያለ ፍጹምና የመጨረሻው እውነት ነው። ይህ እውነት ጋ ማንኛውም የሰው ልጅ አይደርስበትም። ፍትሕ እንዲሁ አያዎ (ፓራዶክሲካል) ነው ምክንያቱም የፍትሕ የተለያዩ አወቃቀሮች እና ግኝቶች በትክክል ወደ እግዚአብሔር መንግስት ሊያመለክቱ ቢችሉም አሁንም ከእግዚአብሔር መንግስት ፍጹምነት ይጎድላሉ።

## አድናቆት እና ትችት

ኒቦር የኖረው በአሜሪካና በዓለም ታሪክ ውስጥ አሳዛኝ ክስተቶች በሚከናወንበት ወቅት ነበር። ዘርፈ ብዙ የሆኑ ማሕበራዊ ችግሮችን ለመፍታት፣ ክርስቲያናዊ አስተምህሮ በሰው ልጅ ኀጢአተኝነት ላይ የሚሰጠውን አጽንኦት ተጨባጩን እውነታ ግምት ውስጥ ያስገባ አቀራረብ (Christian realism) በተሰኘው ጽንሰ ሀሳቡ ላይ ተግባራዊ አድርጓል። ምንም እንኳን ፍጹም የሆነ ፍትሕ በምድር ላይ የሚሳካበት ጊዜ ባይመጣም ነገር ግን ቢያንስ አንጻት የሚያርስ ፍትሕ እንዲኖር ማድረግ ስለሚቻል (proximate justice) የ እንዲሆን መትጋት ይገባናል በማለት የሰጠው ማብራሪያ አሳማኝ ነበር። ምናልባትም የኒቦር ያህል በሀገር አቀፍ ደረጃ የሥነ ምግባር ተጽእኖ ማሳደር የቻለ አሜሪካዊ የሥነ መለኮት

ሊሂቅ የለም ማለት ይቻላል። በማሕበራዊ ሳይንስ እና በአሜሪካ የውጭ ፖሊሲ ላይ ይህን ያህል ጥልቅ ተጽዕኖ ያደረገ ሌላ የሃይማኖት ሊቅ አልታየም። ኒቦር አሜሪካዊያን ራሳቸውን በዓለም ውስጥ የፍትሕ ጠበቃ እንዲሆኑ አእምሮአቸውን ያነሳሳ ታላቅ ሰው ነበር። ምንም እንኳን በጊዜው እርሱ የነበረባት አሜሪካ እሱ ለአሜሪካ የሚያልመውን ባትመስልም፤ የእርሱ ህልም የነበረው ግን የተሻለ ፍትሐ የሰፈነባት እንድትሆን ነበር። በቤትናም ውስጥ ባደረገችው ጦርነት በውጭ ጉዳይ ፖሊሲ ውድቀት ቢገጥማትም እና በሀገር ውስጥ የዘር እኩልነት ባይኖርም ነገ የተሻለ ፍትሐ የሰፈነበት ማሕበረ ሰብ ለመገንባት በሚያስችል አቅጣጫ እየሄደች እንደሆነ አመላክቷል። ስለ መደብ እኩልነት ሲጽፍ፣ “የተደራጀ ኀይልን በተደራጀ ኀይል ላይ በማስቀመጥ በኢኮኖሚ ማሕበረ ሰብ ውስጥ የተወሰነ ሚዛን ማስጠበቅ የሚያስችል ሁኔታ ላይ ደርሰናል” ብሏል።

ምንም እንኳን የኒቦር ሰራ ይህን ያህል ታላቅ ቢሆንም፣ የእሱ አካሄድ በእግዚአብሔር ፈቃድ እና በሰው ልጅ ታሪክ መካከል ካለው ውጥረት የዘለለ እንደማይሆን ተቺዎቹ ጠቁመዋል። እርሱ ስለሀጢያት ያለው አስተምህሮ፣ ምንም እንኳን በማሕበረ ሰብ ውስጥ ኩራትና ትእቢት ያመጣውን የሞራል ውድቀት ገላልጦ የሚያሳይ ቢሆንም፤ ሰውና እግዚአብሔር እንዳይቀራረቡ የሚያደርግ አስፈሪ የሆነ ምስልም አስቀምጧል በማለት ይነቅፉታል። ስለ ነገር ፍጻሜ ያለው አስተምህሮ ለማስረዳት ተጨባጭ ያልሆኑ ምልክቶችና አፈ ታሪኮችን ተጠቅሟል በማለት ነቀፌታ ያቀርባሉ። የታሪክ ሙላት የሚሆነው (ful-fillment of history) በታሪክ ውስጥ ሳይሆን፣ ከታሪክ ውጪ ነው የሚለው አፅንኦቱ የማይጥማቸው ነበሩ። እንደ ኑቦር እሳቤ የእግዚአብሔር የመቤዠት እንቅስቃሴ በታሪክ ውስጥ የሚሆን አይደለም የሚል ይመስላል የሚሉት አሉ። ወይም ደግሞ መሆን የመቻሉን እድል እጅግ አጥብቦ (an impossible possibil-ity) ነው ያስቀመጠው ይላሉ። ስለዚህ፣ የክርስቲያን የሥነ ምግባር ምሁር የሆኑት ፖል ሌማን፣ ለምሳሌ፣ የኒቦር ነገረ ክርስቶስ አስመልክቶ ቅሬታቸውን አቅርበዋል። አሁን ተገልጦ የምናየው “የእግዚአብሔርን ኀያላን ሥራ አሮጌውን እንደ አዲስ አድሮጎ እንደሚለውጥ ክስተት አድርጎ አፅንኦት በመስጠት አላስቀመጠም። እነዚህ የእግዚአብሔር ሥራ በኀይል የተከሰተባቸው ኩነቶች የሰው ልጅ እጣ ፈንታ ፍጻሜውን የሚያገኝበትን መንገድ በማሳየት በታሪክ የለውጥ ባሕር ውስጥ አቅጣጫ እንደሚያሳይ መብራት ናቸው። በእርሱ ሥራ ውስጥ ግን በዚህ ጉዳይ በቂ ስፍራ ተሰጥቶት አናገኝም። አንዳንዶች ለዚህ ችግር ኒቦር የክርስቶስን ሥራ ለማስቀጠል እና በእግዚአብሔር እና በታሪክ መካከል ያለውን ክፍተት ለመሙላት

የመንፈስ ቅዱስ ትምህርት ላይ በቂ ትኩረት ባለማድረጉ ነው ይላሉ።

ቢሆንም በመጽሐፍ ቅዱሳዊው እምነትና በማሕበራዊ ጉዳዮች፣ በሀይማኖት በፖለቲካ ጉልበት፣ ሁሉም ነገር ተሻግሮ መሄድ በሚችለው የሰው ልጅ መንፈስና በሰው ልጅ በአካለ ሥጋ ውስጥ መወሰን፣ በህዳሴ እና፣ በክርስትና ሃይማኖት ውስጥ የተነሳው ተሀድሶ ባመጣው አስተምሮ መካከል የሚያስታርቅ መንገድ ለማሳየት ያደረጋቸው ጥረቶች ምን ያህል ጥልቅ የሆነ እይታና ነብያዊ የሆነ መረዳት እንደነበረው የሚያሳይ ነበር። ከዚህ አንፃር የእርሱ የሥነ መለኮት በተለያዩ የሙያ መስክ ላይ የተሰማሩ ሰዎች ትኩረት የሚሰጡት ታላቅ ሥራ ነው። ለምሳሌ ኒቦር እንደደረሰው የሚታመነው የልበ ቀኖች ፀሎት (serenity prayer) በአይአዎ (paradoxical) የተሞላ ነገር ግን ሁለት ተቃራኒ ሐሳቦችን ለማስታረቅ ስለሚሄድ ነው። ፈገግ የሚሰኘው ይህ ፀሎት ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ ያለባቸውን ችግር ለመፍታት የሚሰባሰቡ ቡድኖች (Alcoholics Anonymous) እና የአሜሪካ ወታደሮች በየእንቅስቃሴያቸው ሁሉ የሚጠቀሙበት ተወዳጅ ፀሎት ሆኗል።

ከአልኮል መጠጥ ጋር በተያያዘ ያለባቸውን ችግር ለመፍታት የሚሰባሰቡ

ቡድኖች ፀሎት እንዲህ አድርገው አሳጥረው በየእለቱ ይደግሙታል፦

“እግዚአብሔር ሆይ መለወጥ የማልችለውን እንድቀበል መረጋጋትን ስጠኝ። መለወጥ የምችለውን እንድለውጥ ብርታት፤ የሚለወጥ እና የማይለወጠውን እንድለይ ጥበብ ስጠኝ!” ይላል።

# 3. ኤሚል ብሩነር

## (ታኅሣሥ 23፣ 1889 - ኤፕሪል 6፣ 1966)

ኤሚል ብሩነር (ታኅሣሥ 23፣ 1889 - ኤፕሪል 6፣ 1966) ታዋቂ እና ከፍተኛ ተደማጭነት ያለው የስዊስ የሃይማኖት ሊቅ ነበር። ካርል ባርትን ጨምሮ ኤሚል ብሩነር በተለምዶ ከኒዮ ኦርቶዶክስ ወይም ከዲያሌክቲካል ሥነ መለኮት እንቅስቃሴ ጋር ስሙ በሰፋት ይነሳል። ብሩነር በአውሮፓ እና በአሜሪካ ከተማረ በኋላ በዙሪክ ዩኒቨርሲቲ የስልታዊ ሥነ መለኮት ፕሮፌሰር ሆነ እና ብዙም ሳይቆይ በዘመኑ የነበረውን የሊበራል ሥነ መለኮትን በመቃወም ትልቅ ስም አትርፏል። የወግ አጥባቂውን ጭፍን እምነት (the blind faith of fundamentalism) እየተቃወመም ቢሆን እንኳን፤ ብሩነር በግል ንስሐ መግባት እና ከእግዚአብሔር ጋር በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል መገናኘት አስፈላጊ መሆኑን አጽንኦት ሰጥቷል። ይህንንም በማድረግ የ ክርስትና መሠረታዊ እምነት ግራ ቀኝ በማይል አቋም እንደሚደገፍ አረጋግጧል።

መጀመሪያ ላይ የካርል ባርት የቅርብ ጓደኛ እና አጋር የነበረው ብሩነር ጸጋን በተመለከተና ውድቀት (original sin) በሰው ልጆች ላይ አምጥቷል ስለሚባለው መከራ ካርል ባርት አጠንክሮ ካቀረበው ይልቅ እርሱ አነስ ያለ ግምት በመስጠቱ ምክንያት ከካርል ባርት ጋር ሊራራቁ ችለዋል። በተለይ በመጀመሪዎቹ የአገልግሎት ዘመናቸው ብሩነር ከካርል ባርት ይልቅ በአሜሪካ ውስጥ ታዋቂ ነበር። ስለ ሰው ልጅ ተፈጥሮ ያለው ብሩህ ተሰፋ እና መፅሐፍ ቅዱስ ስህተት የለበትም የሚለውን አመለካከት አዎ ለማለት ፍላጎት አለማሳየቱ ወይም መቆጠቡ በኋላ ላይ በወንጌላውያን እና በወግ አጥባቂ ክርስቲያኖች ዘንድ እይታዎቹ እና አስተምህሮው ጥርጣሬ ላይ ወድቋል። ቢሆንም ግን ብሩነር በ20ኛው ክፍለ ዘመን እጅግ ተደማጭነትን ካተረፉ የሥነ መለኮት ምሁራን ዘንድ አንዱ ሆኖ ቀጥሏል።

## የሕይወት ታሪክ

ብሩነር የፍሬድሪሽ ሽላይማህርን ለዘብተኛ የሥነ መለኮት አስተሳሰብ (lib-

eral theology of Friedrich Schleiermacher) ከሚተቹት መካከል ዋነኛው ነበር። ኤሚል ብሩንነር በ1889 ዙሪክ አቅራቢያ ተወለደ። በሁለቱም፣ ዙሪክ እና የበርሊን ዩኒቨርሲቲዎች ተምሮ በ1913 ከዙሪክ በነገረ መለኮት የዶክትሬት ዲግሪውን ተቀብሏል። የዶክትሬት ዲግሪ ማሟያ ያቀረበው ጥናት በሃይማኖታዊ እውቀት ውስጥ ያለ የምልክት ቅንጣቶች (The Symbolic Element in Religious Knowledge) የሚል ነው። ብሩነር ከ1916 እስከ 1917 በኦብስታልደን ተራራ መንደር በግላሩስ ካንቶን ውስጥ በፓስተርነት አገልግሏል። በኒዮርክ በዩኒየን ሰሚናር ውስጥ ጥናቶችን በማካሔድ አንድ አመት (1919–1920) ቆይቷል። ወደ አሜሪካ የመጣውም ከአንደኛው የዓለም ጦርነት በኋላ በአሜሪካ እና በአውሮጳ መካከል የተካሔደ የተማሪዎች ልውውጥ አንድ አካል በመሆን ነበር።

በ1921 ብሩነር እንደ ሁለተኛ የመመረቂያ ጽሑፍ ያሰበውን ልምድ፣ እውቀት እና እምነት (Experience, Knowledge, and Faith) የሚለውን መጽሐፍን አቀረበ። ብዙም ሳይቆይ ሌላ ቃሉ እና ሚት (Mysticism and the Word) በሚል ርዕስ በከፍተኛ ሁኔታ የፍሬድሪሽ ሽላይማህርን ለዘብተኛ የሥነ መለኮት አስተሳሰብ (liberal theology of Friedrich Schleiermacher) የነቀፈበትን ሥራውን አቀረበ።

ብሩነር ለሥነ ጽሑፍ ያበረከተውን አስተዋጽኦ ግምት ውስጥ ያስገባው

የዙሪክ ዩኒቨርስቲ ሲስተማቲክ እና ተግባራዊ ክርስትና (Systematic and Practical Theology) ዘርፍ የሥነ መለኮት ፕሮፌሰር አድርጎ ሾመው። ይህም እንደ ፈረንጆቹ አቆጣጠር 1924-1955 ድረስ ማለት ነው። በነበሩት ቀጣዩ ዓመታትም ዝናው እና ተቀባይነቱ እየጨመረ ሊሄድ ችሏል። በተለይም ደግሞ the Philosophy of Religion from the Standpoint of Protestant Theology እና ሁለተኛው፣ አማላጅ የሚሉትን መጽሐፎቹን ካሳተመ በኋላ እጅግ ተደማጭ የሥነ መለኮት ሰው ለመሆን በቅቷል።

በ1932፣ በመላው አውሮፓ እና የናይትድ ስቴትስ እንዲጎበኝ እና ንግግር እንዲያደርግ ለተወሰኑ ዓመታት ግብዣ ሲቀርብለት እና ግብዣውን በተቀበለበት ጊዜ በዚህ መሀከል ላይ ሁለት God and Man and The Divine Imperative የተሰኙ ሁለት መጽሐፎችን ጻፈ። በዚህ ብቻ አልተወሰነም ነገር ግን በ1937 Man in Revolt and Truth as Encounter የተሰኙ ሰዎችን አበረከተ። በ1938-1939፣ በፕሪንስተን

ቲኦሎጂካል ሴሚናሪ እንደ ተመላላሽ ፕሮፌሰርነት ለመሥራት በመስማማቱ እንደገና አሜሪካን ጎበኘ።

የሁለተኛው የዓለም ጦርነት ከመቀስቀሱ በፊት ከአሜሪካ ወደአውሮፓ ተመለሰ። የናዚን ፓርቲ ከሚቃወሙ ሰዎች መካከል ከፊት የሚቀድም ነበር። ከሁለተኛው የዓለም ጦርነት ማብቃት በኋላ በሴንት አንድሪስ ዩኒቨርሲቲ (19461947) የጊፎርድ ትምህርቶችን እንዲሰጥ ተጋበዘ። በዛም ተወዳጅ የነበረውን ክርስትና ና ስልጣኔ (Christianity and Civilization) የተባለውን ሥራውን አቀረበ።

የማስተማር ሕይወቱ ያበቃው በ1953–1955፣ በጃፓን በቶኪዮ አዲሱ ዓለም አቀፍ የክርስቲያን ዩኒቨርሲቲ ነበር። ከዛ በማስቀደም ግን በሦስት ጥራዝ ዶግማ (Dogmatic) የተሰኘውን አበርክቷል።

ቅጽ አንድ እግዚአብሔር በክርስቲያናዊ አስተምህሮ (Christian Doc-

trine of God) ውስጥ ይሰኛል። ሁለተኛው ቅፅ ደግሞ በፍጥረት እና መቤዠት ጉዳይ የክርስትና አስተምህሮ (TheChristian Doctrine of Creation and Redemption) ይሰኛል፤ ሶስተኛው እና የመጨረሻው ደግሞ የቤተ ክርስቲያን፣ እምነት እና ክርስቲያናዊ ትዳር መልክ (The Christian Doctrine of the Church, Faith, and Consummation) ይሰኛል። ከጃፓን ወደ አውሮጳ በነበረው የመልስ ጉዞ ላይ ከፍተኛ ህመም አጋጠመው። አካሉም ተዳክሞ ነበር። እንደከዚህ በፊቱ በውጤታማነት የመሥራት አቅሙ አብሮት አልነበረም። በቀጣዮቹ ዘጠኝ ዓመታት ውስጥ ጥሩ ስሜት የተሰማው ጊዜ ቢኖርም ተጨማሪ የደም ስትሮክ ገጥሞት በመጨረሻም በ1966 እ.ኤ.አ በሞት ተለየ።

## ሥነ መለኮት

ብሩነር ለዘብተኛ የሥነ መለኮት አስተሳሰብ (liberal theology) ኢየሱስ ክርስቶስን ከሳለበት ምስል ጋር ሆድ እና ጀርባ ነበር። ኢየሱስ ክርስቶስ በሥጋ የተገለጠ እግዚአብሔር መሆኑን፣ የኢየሱስ አምላክ ሰው ሆነ ጽንሰ ሐሳብ እና ስለሐጢያታችን መስዋዕት ሆኖ ከሙታን መነሳቱ ለድነት ወሳኝ ነው የሚለውን ሽንጡን ገትሮ ተከራክሯል። ስለዚህም ከካርል ባርት ጋር ኒዮ ኦርቶዶክስን

በማቀንቀን እና በማስተዋወቅ፤ የሁለቱንም የሽሌማህር እና የሪትሽል ሃሳቦች ሞግቷል።

በኋላ ግን በፀጋ አስተምህሮ ዙሪያ ባላቸው ልዩነት ሊለያዩ ችለዋል። ብሩነር ሰዎች በሐጢያት ውድቀት (fall) ምክንያት ቀድሞ የነበራቸውን ነገር ሙሉ በሙሉ (totally depraved እንዳላጡ ያምን ነበር። በኢየሱስ በኩል የመዳን ጸጋ ባይኖርም እንኳ "የመገናኛ ነጥብ" (point of contact) በእግዚአብሔርና በሰዎች መካከል ያለው ሕብረት እንደቀጠለ የሚል ነበር። አንዳንድ ታዛቢዎች የብሩነርን የጸጋ ሥነ መለኮት ክርስቶስ እግዚአብሔር ለሰው ዘር ባቀረበው ሉዓላዊ አቀራረብ እና የእግዚአብሔርን የማዳን ስጦታ በነጻ በመቀበል መካከል ቆሟል የሚለውን በማስረፅ በመካሄድ ላይ ባለው የአርሚኒየ እና የካልቪኒዝም ክርክር ውስጥ መካከለኛ ቦታ ለማግኘት የሚሞክር ይሉታል።

ከ1937 በኋላ በነበረው የቡነር ሥነ መለኮት በአይሁድ የሥነ መለኮት እና ፍልስፍና ልሂቅ በማርቲን ቡበር ሥነ መለኮት ተፅዕኖ ውስጥ የወደቀ ነበር። ክርስቲያናዊ መገለጥ ከእግዚአብሔር ጋር የግላዊ ግንኙነት ምሳሌ እንደሆነ አበክሮ ተናግሯል። The Divine-Human Encounter (1937) , Man in Revolt (1938) , and Revelation and Reason (1941) የሚሉ መፅሐፎቹ እንዳለ ቡበር ያሳረፈበትን ተፅዕኖ የሚያሳዩ ናቸው።

የክርስትና እምነት በውስጡ የያዘውን ልዩ የሆነ ለድነት የሚሆን ዋጋ ትልቅ ስፍራ እንዲሰጠዉ እና ቸል እንዳይባል እየወተወተ፤ ሰዎች እንደ ሰው በሚኖራችው መስተጋብር ውስጥ በሚከሰቱ ክስተቶችና በክርስትና መካከል ውይይት እንዲካሄድ ከፍተኛ ፍላጎት ነበረው። ከዚህ ዕምነቱ የተነሳ። የናዚን ሥራአት በጥብቅ ይቃወም ነበር። ለኮሚኒዝም የነበረው ጥላቻ ግልጽ ነበር። ሁለቱም የፖለቲካ አስተሳሰብና ሥርዓት ለነፃነትና ለምእራባዊው ስልጣኔ አደጋ ናቸው ብሎ ያምን ነበር።

## ኒዮ ኦርቶዶክስ በብሩነር እይታ በአጭሩ

ብሩነር እ.አ.አ. 1928 በተከታታይ በዩኒቨርስቲ ውስጥ ያስተማረው ትምህርት The Theology of Crisis በሚል ርእስ ለህትመት በቃ። ይህ ሥራው ከኒዮ ኦርቶዶክስ ሥነ መለኮት ምርጥ ሥራዎች መካከል እጅግ ድንቅ ከሚባሉት መግለጫዎች አንዱ እንደሆነ በሰፊው ይታሰባል። እዚህ፣ ብሩነር የፕሮቴስታንት

ለዘብተኛ የሥነ መለኮት አቋም (Protestant liberalism) በመቃወም የጥንታዊ ተቃውሞ አምስት ዋና ዋና ጭብጦችን ለይቷል።

አደጋ የተጋረጠበት ስነ-መለኮት (The Theology of Crisis)፦ ይህ ሃሣብ የሚያመለክተው በ20ኛው ክፍለ ዘመን መጀመርያ አካባቢ የክርስትና ሃይማኖትን እና የክርስትና ሥነ መለኮትን የገጠመውን ተግዳሮት የሚያሳይ ነጥብ ነው። እጅግ ፈጣን በሆነ ሁኔታ እየፈራረሰ የነበረበት ጊዜ ነበር። ክርስትና የሥነ ምግባር ሥርዓት አይደለም። በሳይንስና አማካኝነት በክርስትና ላይ በሚቀርብ የታሪካዊ መረጃዎች ትችት አማካኝነት (historical criticism) መረዳትም አይቻልም። ያለው አማራጭ ራሱን የገለጠውን እግዚአብሔርን በእምነት መቀበል ነው ወይም ደግሞ መተው ነው። የለዘብተኛ ፕሮስታንትነትን ሥነ መለኮት ግን ይህን አልቀበልም ባይ ነው። ኢየሱስ አዳኝ ነው የሚለውን እምነት፣ ኢየሱስ ከሰዎች መካከል ከፍ ያለ ስብዕና እና የሰው ልጅ ሊደርስበት የሚገባ የስብዕና ልዕልና ነው በሚል እምነት በመተካት የክርስትናን ልዩ የሆነ እምነትነት፣ እውነት እና ሃይል መናኛ ነገር ተደርጎ እንዲወሰድ አድርጓል። ቢሆንም፣ ክርስቲያኖች በዘመናዊነት እና በወግ አጥባቂነት መካከል መምረጥ አያስፈልጋቸውም። ስለ መጽሐፍ ቅዱስ ያላቸውን ግንዛቤ በምክንያታዊነት እና ጥልቅ የሆነ ሒሳዊ አመለካከቶችን ግምት ውስጥ ባስገባ መንገድ ሊምርዱት ይችላሉ። ነገር ግን ይህንንም በሚያደርጉበት ጊዜ፣ በኢየሱስ በኩል እግዚአብሔር ራሱን ገልጧል የሚለውን እውነት አስፈላጊነት ላይ ሳያመቻምቹ መሆን አለበት።

መገለጥ (Revelation)፦ ሳይንስም ሆነ ሜታፊዚክስ የመጨረሻውን እውነት አይገልጡም። ይልቁንም መገለጥ የሚገኘው የእኛነታችን ሁለንተናን ባካተተ መልኩ በመሰጠት በምናደርገው ፍለጋ አማካኝነት ነው። ከዚህም በላይ እግዚአብሔርን በእኛ መንገድ እና መሻት አናገኘውም። ምክንያቱም እግዚአብሔር በማንነቱ ከእኛ መረዳት እና ማንነት ውጪ ነው (God is transcendent)። የማይታየው የእግዚአብሔር ተፈጥሮ ሙሉ በሙሉ ልናውቅ የምንችለው በሥጋ በተገለጠው አምላክ በኢየሱስ ክርስቶስ በኩል ብቻ ነው።

መዳን፦ የሰው ልጆች ሕይወት ከተቃርኖ ፍጭት የተገኘ የእርቅ መንገድ ነው (dialectical) እና አያዎ (paradoxical) ነው። ማንም ሰው የቱንም ያህል ቢጥር ከሞት ማምለጥ አይችልም። ከሁሉም በላይ እኩይ ማለት የሆኑ ጥቂት ሰዎች ወይንም የግለሰብ ጉዳይ ሳይሆን ሁሉም የሰው ልጅ ጥፋተኝነቱን የሚካፈልበት እውነታ ነው። ከመጀመሪያው ከእግዚአብሔር ጋር የነበረው ሕብረት

ስለተቋረጠ የሰው ልጅ ክፉ ስለሆነ እኩይ ድርጊት ያደርጋል። ይህን መፈወስ የሚችለው ንስሃ በመግባት እና ከህያው አምላክ ጋር በመታረቅ ብቻ ነው። ምንም እንኳን ክርስቲያኖች ከዳኑ በኋላ ኀጢአተኞች ሆነው ቢቀጥሉም፣ ከራሳቸው ፈቃድ ይልቅ የእግዚአብሔርን ፈቃድ ለማስቀደም ከወሰኑ በኋላ በእምነት የበለጠ ለመኖር አዲስ ጥንካሬ ያገኛሉ።

ሥነምግባር፦ ለሥነ መግባር ብቸኛ እርግጥ የሆነ መሠረት በእግዚአብሔር ቃል ላይ ያለ እምነት ነው። ምክንያቱም ለእውነተኛ የሞራል እድሳት አስፈላጊ የሆነውን ኀይል የምናገኘው ከእምነት ብቻውን ነው። በራስ በቅነት እና በራስ ስኬት ላይ በመደገፍ የምንገነባው የሥነ ምግባር ሥርዓት (self-esteem and self-realization) መጨረሻ ላየ ንፋስን እንደመከተል ይሆናል። ምክንያቱም እነዚህ አስተሳሰቦች ሐጢያት እና ሐጢያት በሰዎች ልጆች ውስጥ ስለሚያመጣው አደጋ መውጫው መንገድ ያዘጋጁት አይደሉም። እንደርሱ ሊያደርጉ አይችሉም። ስለጉዳዩ ለማንሳት ፍቃደኞች የሆኑ አይደሉም። ሁሉም ሰው ተስፋ በሌለው መልኩ ተሰብሯል። ድነትም ያስፈልገዋል። ነገር ግን መዳን እንዲሆንለት በመጀመሪያ ሐጢያተኝነቱን መናዘዝ እና ንስሀ መግባት አለበት። ያን ጊዜ ብቻ ለመታደስ ተስፋ ያደረገው ነገር ሥጋ ይለብሳል። ሆኖም፣ ይህ ተሐድሶ የእግዚአብሔር ተግባር ብቻ ሳይሆን፣ ከኀጢአት ወደ እግዚአብሔር ፈቃድ ለመመለስ ድፍረት የተሞላበት ውሳኔ ለመወሰን የሰዎች ትብብር ይጠይቃል።

እድገት፦ ዝግመተ ለውጥን ጨምሮ ሳይንስ ውድቅ ማድረግ ባይቻልም የዝግመተ ለውጥ ጽንሰ ሀሳቦች ለዕድገት በቂ መረጃ የላቸውም። የማይክል አንጄሎ ጥበብ፣ የባች ሙዚቃ፣ ወይም የዞራስተር ሃይማኖት እንኳ በሳይንስ ብቻ ሊገለጽ አይችልም ነገር ግን ከእኛ ዓለም ውጪ ያለ ልዕለ ኋይል ሊያበራልን ይገባል። ስለዚህ የእግዚአብሔር መንግስት የዝግመተ ለውጥ ሂደት ሳይሆን በቅዱስ መንፈሱ ጥሶ የገባበት የማዳን ሥራ ነው። የሰው ልጅ ቀስ በቀስ ወደ እግዚአብሔር የሚያደርገው እንቅስቃሴ ሳይሆን እግዚአብሔር ለሰዎች የገለጠው መገለጥ ነው። በመጨረሻ ግን፣ ክርስትና ከሃይማኖቶች የበለጠ ብሩህ ተስፋ የሚሰጥ እምነት ነው። ይህም በመጨረሻ፣ ሰዎች የእግዚአብሔርን ፊት እንደሚያዩት ያረጋግጣል።

## ከካርል ባርት ጋር የነበራቸው ግንኙነት

ምንም እንኳን በመጀመሪያ ብሩነር እና ባርት ጓደኛሞች እና የሥራ ባልደረቦች የነበሩ ቢሆንም በኋላ ግን በሥነ መለኮት አቋሟቸው ምክንያት ሊለያዩ ችለዋል። ባርት በአንድ ወቅት ግንኙነታቸውን ከዓሣ ነባሪ እና ከዝሆን ጋር እንደሚመሳሰል ገልጿል።

ከ 1934 በኋላ ባርት “ኒይን!” ብሎ አጽንዖት የሚሰጥ ጽሑፍ እንደጻፈ ጓደኝነታቸው ፈረሰ። ብሩነር በተራው በኋይለኛ ቃል በታጀበ አፃፋውን በመፅሐፍ መለሰ። ሁለቱ የቀድሞ ጓደኞች ከነዚህ ክስተቶች በኋላ ለ 30 ዓመታት አልተገናኙም።

የባርዝ ስም በዩኤስ ውስጥ ከመታወቁ ከረጅም ጊዜ በፊት ብሩነር በተለይም ኒዮ ኦርቶዶክስ በመባል በሰፋት ይታወቅ የነበረው የአዲሱ “ዲያሌክቲካል ሥነ መለኮት” ዋና ደጋፊ ተደርጎ ይወሰድ ነበር። በዩኤስ ውስጥ የብሩነር መጽሃፎች ከባርት ሥራዎች በበለጠ ፍጥነት ተተርጉመዋል።

ብዙዎች ዘንድ አስቸጋሪ በሆነው በሁለቱ ግንኙነት ውስጥ እንደ ትንሹ አጋር ተደርጎ የሚቆጠር፣ ብሩነር በአንድ ወቅት የሃያኛው ክፍለ ዘመን ብቸኛው የሥነ መለኮት ሊቅ ባርት መሆኑን አምኗል።

## ሌጋሲ

ብሩነር በ20 ኛው ክፍለ ዘመን በፕሮቴስታንት ሥነ መለኮት ውስጥ ሁነኛ ስፍራ ከነበራቸው የሥነ መለኮት ሊቃውንት መካከል ከፊት ረድፍ የሚቀመጥ የሰነ መለኮት ሊቅ ሲሆን በኒዮ ኦርቶዶክስ አስተምህሮ ውስጥ ትልቁን ሚና ከተጫወቱት መካከል አንዱ ነው። ሆኖም ግን ምንም እንኳን ብሩነር የክርስቶስን ማዕከላዊነት በሥራዎቹ ሁሉ አጽንኦት ሰጥቶ ያስቀመጠ ቢሆንም የሰው ልጆች ውድቀትን በተመለከተ ያለውን አስተምህሮ አሳንሶ በማየት፣ በቅዱሳት መጻህፍት ውስጥ ያሉ አንዳንድ ተአምራዊ ክስተቶች የምር የሆኑ ናቸው ብሎ ባለማመን እና መፅህፍ ቅዱስ በመንፈስ ቅዱስ መሪነት የተፃፈው (the doctrine of the inspiration of the Bible) የሚለውን አስተምህሮ ጠቃሚነት ጥያቄ ምልክት ውስጥ በማስገባቱ

ምክንያት በወንጌላዊያን እና በወግ አጥባቂ የሰነ መለኮት ሊቃውንት ዘንድ በጥርጣሬ አይን እንዲታይ እና ለ ሥራዎቹ ትኩረት እንዲነፍጉት ምክንያት ሆኗል።

ቢሆንም፣ እሱ እና ባርት የአሥራ ዘጠነኛውን ክፍለ ዘመን ሊበራል ሥነ

መለኮትን ፊትለፊት ተጋፍጠውዋል። ለዘብተኛ የፕሮቴስታንት ሥነ መለኮት (liberal Protestant theology) ክርስትና እግዚአብሔር የሰው ልጆችን ለማግኘት በተገለጠው በልጁ በክርስቶስ በኩል ወደ ሰው ልጆች የመጣበት መንገድ ሳይሆን፤ የሰው ልጆች ኢየሱስን እንደ አዳኝ ሳይሆን እንደ ሕይወት ሞዴል በማየት እግዚአብሔርን በመምሰል መኖር እንደሚቻል የሚያሳይ መንገድ መሆኑን ገልጦ በማሳየት ተሳክቶላቸዋል።

# 4. ክላይቭ ስታፕልስ ሉዊስ

## (November 29, 1898 – November 22, 1963)

በጽሑፎቹ ሲ ኤስ ሉዊስ እና በጓደኞቹ እና የሰራ አጋሮቹ ጃክ በመባል የሚታወቀው ክላይቭ ስታፕልስ ሉዊስ (November 29, 1898 – November 22, 1963)፣ እጅግ ዝነኛ ፀሀፊ፣ የልቦለድ ደራሲ፣ የ20ኛው ክፍለ ዘመን የክርስትና አቅበተ እምነት ከነበሩት መካከል አንዱ ነበር።

ገና በልጅነቱ ያጋጠመው የእናቱ ድንገተኛ ሞት፣ የትምህርት ቤት ጓደኞቹ ጭካኔ እና የአንደኛው የዓለም ጦርነት አሰቃቂ ክስተቶች የእግዚአብሔርን መኖር ጥያቄ ውስጥ እንዲያስገባ አደረጉት። እግዚአብሔር ቢኖር ኖሮ እንዲህ አይነት አሰቃቂ ነገር አይፈቅድም ነበር የሚለውን ሃሳብ በመቀበል የእግዚአብሔርን መኖር ካደ። ነገር ግን በ 1931 ወደ ክርስትና ተመለሰ። ሲ.ኤስ. ሉዊስ ዳግም ወደ ክርስትና ከተመለሰበት ሰዓት ጀምሮ፣ ልክ እርሱ በወጣትነቱ በእግዚአብሔር መኖር አለማመን ምክንያት መራር ዋጋ እንደከፈለው፣ በእግዚአብሔር መኖር አለማመን ምክንያት በጨለማ ውስጥ የሚዳክሩ ሰዎችን ዓይን የሚገልጡ እና ወደ እግዚአብሔር ዞር እንዲሉ የሚረዱ የጽሑፍ ሥራዎችን ማበርከት ጀመረ። በነበረው ቀሪ ዘመን ሁሉ፣ ለልጆች በጻፋቸው የልብወለድ ሥራዎች ውስጥ በተዘዋዋሪ መንገድ፣ ወይም በቀጥታ በአቀበት እምነት የጽሑፍ ሥራዎቹ አልያም በሬዲዮ የትምህርት ስርጭቶቹ በኩል፣ ሌሎች ወደ ሀይማኖት እንዲመለሱ በተለይም ኢየሱስ ክርስቶስን እንዲከተሉ በመርዳት አሳልፏል። የእርሱ የጽሑፍ ሰራዎች እስከ አሁን ድረስ ሰዎች በእምነታቸው እንዲበረቱ መርዳታቸውን ቀጥለዋል፣ እና ዛሬ ከመቼውም ጊዜ ይበልጥ ተወዳጅ ናቸው።።

## የሕይወት ታሪክ

ክላይቭ ስታፕልስ ሉዊስ የተወለደው November 29, 1898 በአየርላንድ ቤልፋስት ውስጥ ከአልበርት ጀምስ ሉዊስ እና ፍሎራ አውግስታ ሃሚልተን ሌዊስ ነው። ወላጆቹ ጠንካራ የአየርላንድ ቤተ ክርስትያን ኣባላት ነበሩ። ሌዊስን እና ታላቅ ወንድሙን ዋረን ሃሚልተን ሌዊስን (ዋርኒ) በክርስትና እምነት አንፀው አሳድገዋል።

አባቱ የሕግ አማካሪ ሆኖ ይሠራ ነበር እናቱ ደግሞ በጣም ድንቅ የሆነች የሂሳብ ሊቅ ነበረች። በተለይም ደግሞ እናቱ ፈሎራ፣ ግን ደግሞ ሁለቱም ወላጆቹ ከፍተኛ የሆነ የመጽሐፍት ፍቅር የነበራቸው አንባቢዎች ነበሩ። እናትየው ሁለቱንም ልጆቿን መጽሃፎችን ማንበብ እና መማር እንዲወዱ አስተምራቸዋለች፣ ላቲን እና ፈረንሳይኛ እንዲማሩ አበረታታቸዋለች። ወላጆቹ የነበራቸው እጅግ ብዙ መጽሐፍት አንድ መጽሐፍ ሲጨርስ ሌላኛውን መፀሀፍ እያማረጠ እንዲያነብ ሰፊ ዕድል ሰጥቶታል። ይህም የምናብ አድማሱ የሰፋ ሰው እንዲሆን አድርጎታል። ባንድ ወቅት እንደተናገረው እርሱ ይኖር ከነበረበት በቴክኖሎጂ እድገት ከፍተኛ ደረጃ በተደረሰበት በ20ኛው መቶ ክፍለ ዘመን ዓለም ውስጥ ከመኖር ይልቅ በተለያዩ ልቦለዶች ውስጥ በተገለጹት ዓለማት ውስጥ በምናብ መኖር ምቾት ይሰጠው ነበር።

ልዊስ ገና በለጋ እድሜው እንስሳት እንደ ሰው ሲናገሩና ሲኖሩ ከሚያሳይ የቢኤትሪክ ፖተር የልብ ወለድ ሥራዎች ጋር በፍቅር ወደቀ። እሱ እና ወንድሙ ዋርኒ እንስሳት የሚኖሩበት እና  ራሳቸውን በራሳቸው የሚያስተዳድሩበት የፈጠራ ዓለም በመጫወቻዎቻቸው ለመሥራት ብዙ ሰዓታትን በጋራ ያሳልፉ ነበር። ይህንን የፈጠሩትን ዓለም ቦክሰን ብለው ሰይመውት ነበር። ሉዊስ ጃኪን የቤታቸውን እንስሳ ልብስ ማልበስ ይወድ ነበር። በኋላም ቅጽል ስሙን ያገኘው ከዚህ እንስሳ ነበር። . ሌዊስ የአራት ዓመት ልጅ እያለ ውሻው በመኪና ተመትቶ ሞተ። ከዚህ በኋላ ሉዊስ ስሙ ጃክሲ እንደሆነ ለሁሉም ተናገረ። እና ለምን ለሚለው ጥያቄ መልስ ሳይሰጥ በዚህ ውሳኔ ላይ ጸንቷል። ይህ የቁልምጫ ስም በሂደት ጃክስ የሚለውን ሲይዝ በመጨረሻ ግን ጃክ ተብሎአል። እርሱ 6 ዓመት ላይ ሳለና ወንድሙ ዋርኒ ዘጠኝ ዓመት ሲሆነው ቤተሰባቸው መኖሪያቤት ቀይረው፤ በ Strandtown ውስጥ ወደሚገኘው አዲስ ቤት ወደ ሊቦሮው ወይም ትንሹ ሊያ ተዛወሩ።

ገና የዘጠኝ ዓመት ልጅ ሳለ የ ሲ ኤስ ሊዊስ ደስተኛ የልጅነት ጊዜ ባልተጠበቀ ሁኔታ ተረበሸ። እናቱ በካንሰር ሕይወቷ አለፈ። ከእናቱ ሞት በኃላ ሕይወት ዓላማ እና ትርጉም የለውም ወደማለት አዘነበለ። በመጨረሻም ይህ ዕይታው በእግዚአብሔር መኖር ወደ ዓለማመን እንዲያመራ አድርጎታል። አባትየው አልበርት ሉዊስን ወንድሙ ይማርበት ወደነበረበት በዋትፎርድ፣ ሄርትፎርድሻየር ወደሚገኘው አዳሪ የዋንየርድ ትምህርት ቤት በመላክ የደረሰበትን ጉዳት ለመርሳት ጥረት አድርጓል።

ከዚህ በፊት በእናቱ እና በተለያዩ አስተማሪዎች የተማረው ሉዊስ እናቱ ከሞተች ከጥቂት ወራት በኋላ ወደ አዳሪ ትምህርት ቤት ሄደ። በ እናቱ ሞት ምን

ያህል ጥልቅ የህመም ስሜት ውስጥ እንደገባ የሚማሩበት ትምህርት ቤት ርዕሰ መምህር መጥፎ ባሕርይ ጋር ተደማምሮ ጎልቶ ይታይ ነበር። "ሽማግሌው" በመባል የሚጠራው" ሮበርት ካፐሮን ጨካኝ፣ በጣም ተሳዳቢ እና እንዲህ ነው ተብሎ ለመገመት የሚያስቸግር ሰው ነበር። ብዙ የሚያውቁት ሰዎች ሰውየው እብድ ነው የሚለውን ያምኑ ነበር። በዚህ አስቸጋሪ ጊዜ ራሱን በጽሑፍ ሥራዎች ውስጥ ሸሸገ። ሥነ ጽሑፍ ደግሞ መጽናናትን ና ሞቶትን ሰጠው። ሰላም እና ደስታ የሞላበት፣ መከራ እና ችግር የማይገኝበት አዲስ ምድር እና በደጋግ ገጸ ባሕርያት የተሞሉ ሰዎች የሞሉበት ልብ ወለዶችን ፅፏል። በዚህም ሥራዎቹ በኩል በምናቡ ሞቶት ከነሳው የትምህርት ቤት ኑሮ በምናቡ ወጥቶ መሄድ አስችሎታል። ‹Surprised By Joy› በተሰኘው የሕይወት ታሪኩን በተረከበት መፅሐፍ ላይ ይህን የትምህርት ቤት ወቅት በሁለተኛው የዓለም ጦርነት አይሁዳውያን ይታሰሩበት እንደነበረው ቦታ የማጎሪያ ስፍራ በማለት ይጠራዋል (concentration camp)።

## ትምህርት

ራሱን በራሱ ለማስተማር በግል አስተማሪ ስር ቁጭ ብሎ መማር ከመወሰኑ በፊት የተለያዩ ትምህርት ቤቶች ውስጥ በመግባት ትምህርቱን ተከታትሏል። በህመም ምክንያት ትምህርቱን መከታተል እስኪያቅተው እስከደረሰበት ጊዜ ድረስ፣ በአቅራቢያው በሚገኘው የካምቤል ኮሌጅ ውስጥ ለጥቂት ወራት ትምህርቱን ሲከታተል ነበር። አስተማሪዎቹ እና ዶክተሮች ሉዊስ በጤና ሪዞርት ከተማ ማልቨርን፣ ዎርሴስተርሻየር ውስጥ ቢቆይ ለርሱ የተሻለ እንደሚሆን ተስምቷቸው ነበር። በኋላ ቼርበርግ ሃውስ ተብሎ በሚጠራው መሰናዶ ትምህርት ቤት ተመዘገበ። የክርስትና እምነትን እንደማይቀበልና በየትኛውም ሃይማኖት እንደማያምን በይፋ ያስታወቀው በዚህ ወቅት ነበር። ሌዊስ የ1913ቱን የትምህርት ዘመን በማልቨርን ኮሌጅ አሳለፈ። በመጨረሻ ወደ ቤት ወደ ቤልፋስት በመመለስ እስከ 1917 ድረስ እዚያው ቆየ። የቀድሞ የሉርጋን ኮሌጅ ዋና መምህር በሆነው በዊልያም ቲ. ኪርክፓትሪክ እግር ስር ቁጭ ብሎ ትምህርቱን በግል መከታተል ጀመረ። ውሎ እና አዳሩ የቤተሰቦቹ ላይብረሪ ውስጥ ነበር።

Surprised by Joy በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ "እኔ የረዥም ኮሪደሮች፣ በፀሀይ የተሞሉ ባዶ ክፍሎች፣፣ ፀጥታ በተሞሉ የፎቅ ክፍሎች፣ በብቸኝነት ውስጥ የሚዳሰሱ ሰገነቶች፣ ከውኃ ማጠራቀሚያ ጉድጓዶች እና ቧንቧዎች ከሩቅ

በሚሰሙ ጩኸቶች፣ እና ከጡቦች በታች የሚመጡ የንፋስ ጫጫታዎች ውጤት ነኝ። እንዲሁም ማለቂያ የሌላቸው መጻሕፍት። በጥናት ቦታ ብዙ መፅሀፍት አሉ፣ የሥዕል መሳያ ስፍራ ብዙ መጽሐፍት አሉ፣ መፃህፍት መደርደሪያው ላይ እጅግ ብዙ መጽሐፍት አሉ፣ በመኝታ ክፍል ውስጥ ብዙ መጽሐፍት አሉ፣ በገንዳው ሰገነት ላይ እንደ ትከሻዬ የተከመሩ መጻሕፍት፣ የወላጆቼን ፍላጎት ሁሉ የሚያንፀባርቅ ሁሉም ዓይነት መፃፍት፣ ሊነበቡ የሚችሉ እና የማይነበቡ መጻሕፍት፣ ለልጅ ተስማሚ የሆኑ መጽሃፎች፣ ለልጅ የማይሆኑ መፅሐፍት፤ ነገር ግን የሚከለክለኝ ምንም አልነበረም። ማለቂያ በሌለው ዝናባማ ከሰዓት በኋላ ከመደርደሪያው አንዱን መፅሐፍ ስጨርስ ሌላውን እየነሳሁ አነባለሁ።”

በእነዚህ የጉርምስና ዓመታት ውስጥ ሉዊስ ማንበብ ብቻ ሳይሆን በሪቻርድ ዋግነር ዘፈኖች እና ዋግነር በኦፔራዎቹ ውስጥ በገለጻቸው የሰሜን አፈ ታሪኮች ተማርኮ ነበር። የዋግነር ሙዚቃ በዙሪያው ካሉ የተፈጥሮ ውበት ጋር በመሆን በኋላ ላይ “ደስታ” ብሎ ለሚጠራው ነገር ከፍተኛ ጉጉት ሰጠው። ይህ ደስታ የሚለው ጽንሰ ሃሳብ በጥናቱ ገፍቶ እንዲሄድ ዋነኛው ገፊ ምክንያት ነበር።

በቤት ውስጥ የነበረው የብቸኝነት ጊዜ በቤት ውስጥ በመሆን የጽሑፍ ሥራውን እንዲቀጥል አስችሎታል። የተለያዩ መንገዶችን በመጠቀም ድንቅ ግጥም እና ኦፔራ ለመፃፍ እጁን ማፍታታት ጀመረ። እነዚህ ሁሉ ጥረቶቹ የሚያጠነጥኑት በኖርዲክ ሚት ዙሪያ ነው። ለግሪክ ሥነ ጽሑፍ እና አፈ ታሪክ ታላቅ ፍቅርን አዳበረ። በአስተማሪው በኪርፓትሪክ ድንቅ ክህሎት የተሞረደው ሊዊስ በክርክር የተካነ፣ ግልፅ እና ምክንያታዊነት ላይ ብቻ የሚያተኩር ሰው ነበር።

እነዚህን ሁሉ በርካታ የትምህርት ገጽታዎች ሰንቆ የያዘው ሊዊስ፣ እ.አ.አ. በ1916 ከኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ኮሌጅ የስኮላርሺፕ እድል አገኘ። በዚህ ወቅት ደግሞ የአንደኛው የዓለም ጦርነት የጀመረበት ወቅት ነበር። በዚህም ምክንያት ሊውስ ወዲያው ወደ ኦክስፎርድ ዩኒቨርሲቲ ገብቶ አልተማረም ይልቁኑ በ1917 በብሪቲሽ የመከላከያ ሰራዊት ውስጥ ተመዘገበ። በዛም በሶስተኛው ሻለቃ ሱመርሴትላይት እግረኛ ምድብ መኮንን ሆኖ ተሾመ።

## የወታደር ቤት ቆይታው

በወታደር ቤት በነበረበት ጊዜ የሊዋሰን ሕይወት እስከወዲያኛው የቀየረ አጋጣሚ ተከሰተ። ኤድዋርድ ፍራንሲስ ኮርቴናይ ሙር፣ በቅጽል ስሙ፣ "ፓዲ" ተብሎ ከሚጠራ ሰው ጋራ ጉዋደኝነት ፈጠረ። በወታደር ቤት በካምፑ ውስጥ በአንድ ምድብ አንድ ላይ የሚያድሩ ነበሩ። ፓዲ ሊዋስን ከእናቱ ጄን ኪንግ ሙር ጋር አስተዋወቀው። በኋላም በጉያዋ ሸሸጋ እንደ እናት የሆነችለት ሴት ሆነችለት። በ19 አመቱ ሊዋስ በፈረንሳይ ሶማ ቫሊ ተብሎ ወደሚጠራ ግንባር ተዘዋወረ። በዛም በኤፕሪል 15, 1917 በአራስ ጦርነት ላይ ጉዳት ደረሰበት።

በጦርነት ወቅት ከደረሰበት የአካል ጉዳት በተጨማሪ፣ ራሱን ከድባቴ እና ቤቱን ከመናፈቅ ስቃይ ጋር ሲታገል አገኘ። በሆስፒታል ሳለ የፓዲ ሙር እናት ጄን ልትጎበኘው ትመጣ ነበር። እና ከጓደኛው እናት ጋር እስከመጨረሻው የዘለቀ ወዳጅነት መሠረቱ። እርሱም በእናትነት ደግነቷ ውስጡ ተነክቶ ነበር። ከማንም በላይ ቅርቡም እርሷ ሆነች። አባቱ ሆስፒታል በነበረበት ወቅት መጥቶ ሊጎበኘው እንዳልፈለገ ያለውን መረጃ ስናይ በርግጥ ይህ መሆኑ አያስደንቅም። ሊዋስም እርሱ በውጊያ ላይ ቢሞት እስከ መጨረሻው እናቱን ጃኒን እንደሚንከባከባት እና የሚያስፈልጋትንም እንደሚያደርግላት ቃል ለፓዲ አንድ ቀል ገባለት።

በዚያው አመት በኦክቶበር ውስጥ፣ በጦርነት ውስጥ ከደረሰበት የመቁሰል አደጋ ሙሉ ለሙሉ አገገመ። ነገር ግን በውጊያ እና በጦርነት ውስጥ ያሳለፋቸውን ነገሮች ትዝታው በሙሉ አለቀቀውም። ፓዲ ሙር በጦርነት ተገደለ። ልዋስም የገባውን ቃል ኪዳን በማክበር የጓደኛውን እናት እስከመጨረሻው ተንከባክቧል። እንደ እናቱ ያየትም ነበር። ጄን እድሜዋ በጨመረ እና ባረጀች መጠን በሁለቱ ግንኙነት መካከል ያለው ግንኙነት እየሻከረ መጣ። ቢሆንም ሊዋስ ቃሉን እስከመጨረሻው ለመጠበቅ ችሏል። በአረጋውያን መንከባከቢያ ውስጥ በገባችበት ወቅት እንኳን በየእለቱ በሚባል ደረጃ ይጎበኛት ነበር።

## ትምህርት በተመለከተ

ዲሲምበር 1918፣ ከወታደር ቤት በክብር ተሰናብቶ ወደቤት መጣ። በመጨረሻም ወደ ትምህርቱ ተመለሰ። ሲ.ኤስ. ሉዋስ ቀጥለው በመጡት ጥቂት

አመታት የተለያዩ ሽልማቶችን በማግኘት የነበረውን ችሎታ አሳየ። በ1920 በግሪክ እና ላቲን ሥነጽሑፍ ዘርፍ፣ እና በእንግሊዘኛ ደግሞ በ1923 ሽልማት አግኝቷል። በዚሁ አመት ምንም እንኳን በኮሌጅ ውስጥ ያለውን መኖሪያውን የተወ ባይሆንም ወደ ጓደኛው እናት ጄን ቤት ተዘዋወረ። በዲሴንበር 1917 ዓ.ም ለጓደኛው አርተር ግሪቭስ፣ በፃፈው ደብዳቤ ላይ፣ ጂን እና ግሪቭዝ "በዓለም ላይ ለእኔ በጣም አስፈላጊ የሆኑት ሁለት ሰዎች ናቸው" በመጨረሻም በ1930 ሉዊስ እና ወንድሙ ዋርኒ በክሮኒክል ኦፍ ናሪያ ውስጥ ከተሳለው ቤት ጋር ተመሳሳይ ወደሆነ ቤት ተዘዋወሩ። ቤቱ ደግሞ የሚገኘው በሪሲንግኸርስት፣ ሄድንግተን (የኦክስፎርድ ከተማ ዳርቻ) ነው። ሊዋስ እና ወንድሙ አሮጊቷን ጄንን ወደቤታቸው አመጧት። እና ሦስቱም ለቤቱ ግዢ አስተዋፅኦ አድርገዋል። እ.አ.አ. በ 1973 ዋረን ሲሞት፣ ቤቱ ለጄን ሙር ሴት ልጅ፣ "የሄሞፕሪግሰ ደንባር" ተላለፈ።

## "የእኔ የአየርላንድ ሕይወት"

በባንጎር፣ ካውንቲ ዳውን ውስጥ በፓርክ አግዳሚ ወንበር ላይ ቁጭ ብሎ የአየርላንድ ማንነቱ ካሳደረበት ተፅዕኖ ተነስቶ... "ማንም እንግሊዛዊ ስለ እንግሊዝ ያለኝን የመጀመሪያ ግንዛቤ ሊረዳ አይችልም። የተከበብኩባቸው እንግዳ የእንግሊዘኛ ዘዬዎች የአጋንንት ድምጽ ይመስሉ ነበር። ነገር ግን የከፋው የእንግሊዝ መልክዓ ምድር ነበር... ከዛን ቀን ጀምሮ ግጭት ጀመርኩ። እንደውም ለሆነ ጊዜ ያህል ለኢንግላንድ ጥላቻ ሁሉ ነበረኝ። የ ጥላቻ ለመፈወስ ብዙ ጊዜ የወሰደ ነበር" በማለት Surprised by Joy በሚለው መፅሐፉ ላይ ስለኢንግላንድ ከትቧል።

ሲ.ኤስ ሊዋስ ለተወለደባት ምድር ለአየርላንድ የነበረው ፍቅር ከፍተኛ ነበር። አርበኛ የምንለው አይነት ሰው ነው። ለሐገሩ ከልብ የሆነ እና እጅግ ጠንካራ የአርበኝነት ስሜት ነበረው። ሉዋስ ከትንሽነቱ ጀምሮ የአየርላንድን አፈ ታሪክ አጥንቷል። ይህም ብቻ አይደለም ታላላቅ የአየርላንድ ደራሲያንን በጥልቀት ፈትሿል። በጥልቀት አጥንቷል። የኒቨርሲቲ በነበረበት ጊዜም የአየርላንድ ቋንቋ የመማር ፍላጎትም ነበረው። በዩኒቨርሲቲ በትምህርት ላይ በነበረበት ወቅት የሀገሩ ሰው የነበረው የደብሊው.ቢ. ዬትስ የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች አድናቂ ነበር። ሲ.ኤስ ሊዋስ በዝርዝር እና ግልፅ በሆነ ቋንቋ የአየርላንድን የሴልቲክ ባህል እና ትውፊት በግጥሞቹ ውስጥ መጠቀሙን እጅግ ይወድለት ነበር። ሉዋስ ለወዳጁ በጻፈው ደብዳቤ ላይ፣ "እዚህ እንደልቤ የሆነ ደራሲ አግኝቻለሁ። እጅግ የወደድኩት። የሚመስጠኝ። አንተም የደብሊውቢ.ቢ. ዬትስ ሥራዎች ደስታ እንደሚሰጡህ

እርግጠኛ ነኝ::ትገረምበታለህ። ደግሞ ስለ አሮጌው የአየርላንድ አፈ ታሪክ (mythology) ብርቅዬ መንፈስ እና ውበት የሚያንፀባርቁ ተውኔቶች እና ግጥሞችን ይጽፋል። “በማለት አስፍሯል። በዩኒቨርሲቲ ውስጥ ያሉ እግሊዛውያን የሥራ ባልደረቦቹ ለዬትስ ሥራዎች ቸልተኛ መሆናቸውን ባዬ ጊዜ ድንጋጤ ተሰማው። በጣም ግራ ተጋባ። እንደዛ ሊሆኑ የቻሉበት ምክንያትም ፍፁም ሊገባው አልቻለም። በኦክስፎርድ ያሳለፈውን ጊዜ ሲገልጽ እንዲህ ሲል ጽፏል፦ “ከተዋወቅኳቸው ሰዎች ዘንድ ዬትስ ምን ያህል ችላ እንደተባለ ሳውቅ በጣም ይገርመኛል፤ ምናልባት ለእርሱ ሥራዎች ያለው ቸልተኝነት ምንጩ አይሪሽ በመሆኑ ብቻ ነው፤ ግምቴ እውነት ከሆነ እኔ አይሪሽ በመሆኔ አማልክትን አመሰግናለሁ።”

ሉዊስ በኦክስፎርድ ውስጥ በነበረው የተደራረበ ሥራ ምክንየት ወደ አየርላንድ መመለስ አልቻለም። እና ሁል ጊዜ በዚህ ሁኔታ ይፀፀት ነበር። ነገር ግን እትብቱ የተቀበረባትን ምድር በየጊዜው ከመጎብኘት አልሰነፈም። በጽሑፍ ሥራው መጀመሪያ ላይ ሉዊስ ሥራዎቹን ወደ ዋና የደብሊን አሳታሚ ለመላክ አስቦ ነበር። ለጓደኛዬ በጻፈው ደብዳቤ ላይ፦ “የጽሑፍ ሥራዎቼን ወደ አሳታሚ የምልክ ከሆነ፣ ሲመስለኝ ወደ ማንሱል የዱብሊን ሰዎች ጋ መላክ ይኖርብኛል። በዚህም ራሴን ከአይሪሽ ሥነ ጽሑፋዊ ወግ ጋር ለማዛመድ መንገድ ይሆነኛል።” ሊዊሰ በእንግሊዛውያን ላይ በመቀለድ እና ስላቅ በመፍጠር የታወቀ ነበር። ከአንድ የአየርላንዳዊ ሰው ጋር የተገናኘበትን ሁኔታ ሲገልጽ “ልክ ሁሉም የአይርሽ ሰዎች በኢንግላንድ ውስጥ በሚገናኙበት ጊዜ እንደሚያደርጉት የአንግሎ ሳክሰን ዘር ምንም ቁም ነገር የማይገኝባቸው እና ደነዝ መሆናቸውን በማማትና በመተቸት ጊዜያችንን ጨረስን። ደግሞም አሚ፣ ምንም ጥርጥር የሌለው ነገር የአይርሽ ብቸኛ ማለቴ... ብቻ ለማንኛውም በሌላ ህዝቦች መካከል ደስ እያለኝ ኖሬ አልሞትም” ሲል ጽፏል:

ሊዊስ ሕይወቱን በሙሉ ብዙ ጊዜ በእንግሊዝ የሚኖሩ ሌሎች አይሪሽኖችን ሲያፈላልግ ነው የኖረው። እና ከብዙዎቻቸው ጋር የጠበቀ ወዳጅነት ነበረው። ይህንንም “የአይሪሽ ሕይወቴ” ሲል ጠርቶታል።

## የምትርነት ሥራ ሕይወቱ

የሉዊስ ጓደኛ ኦወን ባርፌልድ ሲ ኤስ ሌዊስን በሦስት በጣም የተለያዩ እና ልዩ ወደሆኑ ሊዊሶች ልንከፋፍለው እንችላለን ይለናል። የመጀመሪያው ታዋቂው

የኦክስፎርድ ምሁርና አስተማሪ የነበረው ሊዋሰ፣ ሁለተኛው የሳይንስ ልቦለድ እና የህፃናት ታሪክ ደራሲው፣ እና ሶስተኛው የክርስትና እምነት ተሟጋችና የአቀበት እምነት ጽሁፎችን ያበረከተዉ ሊዋስ ናቸው።

ሲ.ኤስ.ሌዊስ ከ1925-1954 በኦክስፎርድ ማግደላን ኮሌጅ አስተማሪ በመሆን አገልግሏል። በአስተማሪነት ያሳለፈው ጊዜ ውጤታማ የሚባል ነበር። በሁሉም አይነት መመዘኛዎች አስደሳች፣ ብዙ አክብሮትን ያስገኘለት እና የተዋጣለት ነበር። በኦክስፎርድ ማግደላን ኮሌጅ የነበረውን ቆይታ ከጨረሰ በኋላ፣ በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲም አስተምሯል። በካምብሪጅ ዩኒቨርሲቲም ውስጥ የመጀመሪያው የመካከለኛው እና የህዳሴ ዘመን እንግሊዘኛ አስተማሪ

ፕሮፌሰር (the first Professor of Medieval and Renaissance English) ሊሆን በቅቷል። የመካከለኛው እና የህዳሴ ዘመን እንግሊዘኛ እያስተማረ በነበረበት ጊዜ እና በዚህ የትምህርት አይነት ላይ ከነበረው ጥልቅ ፍላጎት የተነሳ ከሥራዎቹ መካከል አንዱ የሆነው The Allegory of Love (1936) የሚለው ሥራው ሊወለድ ችሏል። ይህ ሥራ በዋናነት የሚያተኩረው በኋለኛው የመካከለኛው ዘመን እና በዛ ዘመን የተምሳሌታዊ ዘይቤ (the use of allegory) አጠቃቀም ላይ ነበር። ቀጥሎ የነበረው የሥራ ድርሻ ለጥንታዊ የሥነ ጽሑፍ እና ሥነ ግጥም ሥራዎች መቅድም መፃፍ ነበር። መቅድም ከፃፈላቸው ሥራዎች መካከል የላይሞንስ Brut እና የጆን ሚልተን Paradise Lost የሚሉት ሥራዎች ይገኙበታል። ከዩኒቨርሲቲ የማስተማር ሙያው ጋር በተገናኘ የፃፈው የመጨረሻ ሥራው እ.አ.አ. በ1964 የታተመው The Discarded Image, an Introduction to Medieval and Renaissance Literature የሚለው ሥራው ነው።

በዩኒቨርሲቲ ውስጥ በአስተማሪነት ሙያ ተሰማርቶ በቆየበት ዘመን ብዙ ወዳጆችን አፍርቷል። ከአንዳንዶቹ ጋር እስከ ሕይወት ፍጻሜ የደረሰ ጓደኝነት እንዲመሠርት አስችሎታል። ምሁርነት ካወዳጃቸው ጓደኞቹ መካከል ጄ.አር. አር. ቶልኪን፣ ቻርለስ ዊሊያምስ እና ኦወን ባርፊልድ ተጠቃሾች ናቸው። እርሱና እነዚህ ጓደኞቹ ከ1930ዎቹ እስከ 1949 ባሉት ጊዜያት በየሳምንቱ ማክሰኞ Eagle and Child pub እና ተጨማሪ Bird and Baby ተብሎ በሚታወቅ መጠጥ ቤት እየተገናኙ ስለ ሥነጽሑፍ ይወያዩ ነበር። ሥነጽሑፍን እንዲወያይ የመሠረቱት ማሕበረ ሰብ Inklings በመባል ይታወቃል። ሉዋስ የግል ሕይወቱን በሚመለከት በፃፈው Surprised by Joy በሚለው መጽሐፍ ውስጥ በገጽ 173 ስለ ጓደኛው ጄ.አር.አር. ቶልኪን እንዲህ በማለት ፅፏል፡፡“በእንግሊዘኛ ፋኩልቲ ውስጥ ማስተማር

በጀመርኩበት ጊዜ ሌሎች ሁለት ጓደኞችን አፈራሁ። ሁለቱም ክርስትያኖች ነበሩ። ዩኒቨርስቲ ግቢ ውስጥ ሁሉም ቦታ የሚገኙ ሰዎች ናቸው። ወይም ይመስላሉ። እኔን በብዙ መንገድ ረድተውኛል። ብዙ አስቸጋሪ ነገሮችን እንዳልፍ ያደረጉልኝ ድጋፍ እንዲህ ነው ተብሎ የሚገለጽ አይደለም። እነሱም H.V.V. Dyson እና J.R.R. Tolkien ነበሩ። ከሁለተኛው ማለትም ከ J.R.R. Tolkien ጋር የፈጠርኩት ጥብቅ ወዳጅነት ቀድሞ የነበረኝ ተገቢ ያልሆነ አመለካከት መሰበሩን የሚያመለክት ነው። ገና ክፉና ደጉን ማወቅ እንደጀመርኩ በቀጥተኛ መንገድ ባይሆንም በተዘዋዋሪ የትኛውንም ፓፒስት እንዳላመን ማስጠንቀቂያ ተሰጥቶኝ ነበር። ሁለተኛው ተገቢ ያልሆነው አመለካከቴ፣ ገና ወደ እንግሊዘኛ የትምህርት ክፍል ተመድቤ ስመጣ በግልጽ እና በማያሻማ መንገድ በምንም ተአምር የፊሎሎጂ ባለሙያን ማመን እንደሌለብኝ ተነግሮኝ ነበር። እኔ ደግሞ ወዳጅ ያደረግኩት ቶልኪን ሁለቱንም ነበር።" የሚል ተጽፎ እናነባለን።

## የልብ ወለድ ፅሁፍ ሥራው

ምናልባት ሲ.ኤስ. ሉዊስ በደምብ የሚታወቀው በልቦለድ ደራሲነቱ ነው። ሉዊስ ለወጣቶች እና ለህፃናት በርካታ ታዋቂ ልብ ወለዶችን ጽፏል። እጅግ ዝነኛው እና በብዙዎች ዘንድ የተወደዱት የልቦለድ ሥራዎቹ የ ሳይንሳዊ ልቦለድ ዘርፍ የሆነው Space Trilogy የሚለውና ለህፃናት የፃፈው ተከታታይነት ያለው The Chronicles of Narnia የሚባለው ሥራው ነው።

## የሳይንሳዊ ልብወለድ ሥራዎቹ

በልጅነቱ የእናቱ ሞት ትቶበት ያለፈው ጠባሳ፣ በትምህርት ቤት ያሳለፈው መጥፎ ጊዜ፣ የአንደኛው የዓለም ጦርነት አስከፊ ገፅታ ተደማምረው፣ ሲ.ኤስ .ሊዊስ ስለዓለም ያለው ምልከታ ጨለምተኛ የሚባል ነበር። The Space Trilogy ወይም Ransom Trilogy ተብሎ የሚጠራው የሳይንሳዊ ልብወለድ ሥራው እርሱ እና የሥራ ባልደረባ ጓደኞቹ የሆኑ ሌሎች ምሁራንንም ሲያስጨንቅ የነበረውን በዘመናዊ የሳይንስ ልብወለዶች ውስጥ እንደባህል እየሆነ የመጣውን ሰብዓዊነት የጎደላቸው ገጸ ባሕርያት የመሳል አካሄድ ለመጋፈጥ የሰራቸው ሥራዎች ናቸው። ሉዊስ ስለ እነዚህ አዝማሚያዎች ከጓደኛው ቶልኪን ጋር ከፍተኛ ውይይት ካደረገ በኋላ የመጀመሪያውን የሳይንሳዊ ልብ ወለድ መፅሐፍ Out of the Silent

Plane የሚለውን ፃፈ። ሊዊስ እና ቶልኪን በጋራ ቁጫ ብለው ሊዊስ “space travel” በሚል ርዕስ፣ ቶልኪን ደግሞ “time travel” በሚል ርዕስ ሳይናሳዊ ልብወለድ ለመፃፍ ተስማሙ። የቶልኪን የፈጠራ ሥራ የሆነው The Lost Road፣ ቶልኪን ስለፈጠረው Middle-earth mythology and the modern world ስለሚለው ታሪክ የሚያስረዳ ነው። በርግጥ ይህን ሥራውን አልጨረሰውም። ሊዊስ ግን የራሱን የሳይንሳዊ ልብ ወለድ ታሪክ ፅፎ ጨረሰ። አንደኛው Ransom የሚለው ገፀ ባሕርይ ቶልኪን ነበር። በ That Hideous Strength በሚለው መፅሐፉ ውስጥ የምናገኘው Jules የሚለው ገጸ ባሕሪ ከ H. G. Wells. ሥራዎች ባገኘው አዲስ እይታ መሠረት የቀረፀው ነው።

## የናርኒያ ዜና መዋዕል (The Chronicles of Narnia)

የናርኒያ ዜና መዋዕል ያካተቱት ሰባት ነጠላ ልብ ወለዶች ነው። እነዚህ መጻሕፍት እንደ ልቦለድ ጸሐፊ ሉዊስ የደረሰበትን ከፍታ የሚያሳዩ መፅሐፍት ተደርገው ይቆጠራሉ። መጽሐፎቹ የሉዊስ ክርስቲያናዊ እሴቶችን በተዘዋዋሪ መንገድ የሚያፀባርቁ ናቸው። በዚህ የልብ ወለድ ሥራው ውስጥ ስለ ሰው ልጅ የሐጢያት ውድቀት፣ ለኀጢያት ስለተከፈለው ክፍያ እና ስለትንሳኤ (The Fall, The Atonement, and The Resurrection) ክርስቲያናዊ ጭብጦችን ተርኮበታል። ልብ ወለዶቹ ሊዊስ በምናቡ በፈጠረው ናርኒያ በሚባል ምትሃታዊ እና ምስጢራዊ (magical and mystical) ናርኒያ በተባለ ምድር ጀብደኛ የሆነ ተግባር ስለሚፈፅሙ ልጆች የሚያወሳ ነው። በጣም ታዋቂ እና ተወዳጅ ከሆኑት Lion, the Witch and the Wardrobe ከሚሉት መፅሐፍ ጀምሮ፤ የናርኒያ ተከታታይ የልብወለድ መፅሐፍ በ 1950 እና 1956 ውስጥ ታትመዋል። በኋላም ወደ መድረክ ቲያትር እና ወደ ፊልምነት ተቀይረዋል። ልብ ወለዶቹ ሲ.ኤስ. ሊዊስ ለግሪክ አፈ ታሪክ፣ የሮማውያን አፈ ታሪክ፣ የሴልቲክ አፈ ታሪክ፣ እና ባሕላዊ የእንግሊዝኛ እና የአየርላንድ ተረት ተረቶች (mythology, Roman mythology, Celtic mythology, and traditional English and Irish fairytales.) የነበረውን እውቀት እና ፍቅር የሚያንፀባርቁ ናቸው።

## ሌሎች ሥራዎች

ሉዊስ የበርካታ ሌሎች መፅሐፎች እና ልብወለድ ሥራዎች ደራሲ ነበር።

ከነዚህም መካከል አንድ ሰው በሰይጣን ሲፈተን የሚተርከው Screwtape Letters፣ እና Cupid and Psyche myth እንደገና የተረከበት Till We Have Faces የሚባሉ ሥራዎች ይገኙበታል። ሉዊስ ይህ በጣም የተዋጣለት ሥራው እንደሆነ የምን ነበር ነገር ግን እነዚህ ልብወለዶች ብዙ እውቅና አላገኙም።

## ክርስትና በተመለከተ የሰራቸው ሥራዎች!

ሲ ኤስ ሉዊስ ምሁር እና የልብ ወለድ ደራሲ ብቻ አልነበረም ነገር ግን እጅግ ተፅዕኖ የፈጠሩ የክርስትና አቀበተ ዕምነት ሥራዎችንም ያበረከተ ሰው ነበር። Mere Christianity የሚለው መፅሐፉ በአቅበተ እምነት ዘርፍ ከፃፋቸው ሁሉ እጅግ ታዋቂው እና ተፅዕኖ ፈጣሪው ነው። ሃይማኖትን በተመለከተ እጅግ ጥልቅ ትግል ሲያደርግ ቆይቷል። በወጣትነቱ አምላክ የለሽም ነበር። ነገር ግን 1931 በሃይማኖት ላይ የነበረው የማያቋርጥ ጥያቄ እና አምላክ የለሽነቱ ተሸንፎ ለክርስትና ሃይማኖት እጁን ሰጠ። ሃይማኖትን በተመለከተ ከሚነሱ ጥያቄዎች ጋር ታግሎ ስላለፈበት፤ በተቻለ መጠን የክርስትናን ጽንሰ ሐሳብ በአመክንዮ እና ሎጂክ (reason and logic) በመታገዝ ለማሰረዳት ጥልቅ ፍላጎት ነበረው። Mere Christianity፣ The Problem of Pain and Miracles የተሰኙ ሥራዎቹ በሁሉም ዘንድ የታወቁ በክርስትና ላይ የሚቀርቡ ትችቶችን በጥልቀት የዳሰሰበት ሥራዎች ናቸው። ሥራው በጽሑፍ ብቻ የተገደበ አልነበረም። በዩኒቨርሲቲ ሲያስተምር እና በሬዲዮ ፕሮግራም አቅራቢ ሳለ፤ አብዛኛዎቹን ሥራዎቹን ለሬዲዮ አድማጮቹ አቅርቧል። ሌዊስ በልጅነቱ ሃይማኖትን እንደ የቤት ውስጥ ሥራ እና ግዴታ አድርጎ ይመለከት ነበር። ሲኤስ ሊዊስ ሉክሪየስን (Lucretius) ስለ አምላክ የለሽነት (atheism) በጣም ጠንካራውን መከራከሪያ ያቀረበ በማለት ይጠቅሰው ነበር።

# ሉክሪየስ (Lucretius)

“እግዚአብሔር ዓለምን ቢሠራ ኖሮ፣ እንደምናየው ደካማ እና የተሳሳተ ዓለም አይሆንም ነበር።”

በሚለው ጠንካራ ሙግቱ ይታወቃል።

ስስለራሱ ሕይወት በተረከበት Surprised by Joy በተሰኘው ግለ ታሪክ መፅሐፋ ሲኤስ ሊዊስ “እግዚያብሔር ባለመኖሩ በጣም ተቆጥቼ ነበር። (I’m very angry with God for not existing” በማለት ፅፏል። ነገር ግን የጓደኞቹ ተፅዕኖ በተለይም ቶሊኪን የተጫወተው ሚና ክርስትናን በተለየ ዓይን እንዲያይ እረድቶታል።

“በማግዳሊን ኮሌጅ ባዶ ክፍል ውስጥ ብቻዬን ስዋልል ተመልከቱኝ። አንድ ምሽት አልፎ ሌላው ሲመጣ፣ እዕምሮዬ ለሰከንድ ከምሰራው ሥራ እንኳን ብድግ ካለ፤ ላገኘው ከቶም የማልፈልገው የእርሱ መገኘት በማያቋርጥ እና በማይሰለች ሁኔታ ይሰማኛል። በጣም የፈራሁት ነገር በመጨረሻ በእኔ ላይ መጣ። እ.አ.አ. በ1929 የሥላሴ ጊዜ ውስጥ፣ እጄን ሰጠሁ። እግዚአብሔር አምላክ መሆኑን አምኜ ተቀበልኩ፣ እናም ተንበርክኬ ጸለይኩ፤ ምናልባትም በዚያች ሌሊት፣ ደስ ሳይለው እና እያቅማማ እጁን የሰጠ ሰው ለውጥ የእኔ ለእግዚአብሔር መሸነፍ ይሆናል።”

እ.አ.አ. በ 1931 ከቶልኪን እና ከሌላ የቅርብ ጓደኛው ሁጎ ዳይሰን ጋር ረጅም ውይይት ካደረጉ በኋላ ሉዊስ እውነት መሆኑን የሚያውቀውን ነገር መካድ አልቻለም እና ወደ ክርስትና ተመልሶ የእንግሊዝ ቤተ ክርስቲያን አባል ሆነ።“በእርግጫና እየጮህኩ ወደ ክርስትና ገባሁ” ብሏል።

ብዙዎች ዘንድም ለተጠራጣሪዎች የተላከ (The Apostle to the Skep-

tics) ሐዋርያ በመባል ይታወቃል። ምክንያቱም ደግሞ ሃይማኖትን በተጠራጣሪ አይኖች ምን እንደሚመስል ደፍሮ ስለሚፅፍ እና ሁልጊዜ የተድበሰበሰ ሳይሆን መሠረት ያለው ሃደትን ስለሚደግፍ ነው። The Problem of Pain በተሰኘው ሥራው ከተጠራጣሪነት ጋር የተያያዙ ጉዳዮችን በስፋት ዳሷል።

## ከክርስቲያኖች ይቀርብበት የነበረው ትችት

ሊዊስ ከተቺዎች አፍ ያመለጠ ሰው አይደለም፡፡ በተለይም ደግሞ ወንጌላውያን ክርስቲያኖች አንዳንድ በሚናገራቸው ንግግሮች ይከፋ ነበር፡፡ ማጨስ እና መጠጣቱ እና በእድሜ 25 አመት ከምትበልጠው ካላገባች የጓደኛው እናት ጋር (ወደ ክርስትና ከመጣም በኋላ) በአንድ ቤት መኖሩ ብዙ ክርስቲያኖችን የሚጎረብጣቸው ነገር ነበር፡፡

የልብ ወለድ መፅሐፎቹ ግልፅ ባልሆኑ እና በተሳሳተ መንገድ በቀረቡ (in-

accurately based on biblical themes) መፅሐፍ ቅዱሳዊ ጭብጦች ላይ የተመሰረቱ እና ከአረማዊ ሚቶች ጋር የተደባለቁ ናቸው ብለው ይነቅፉታል፡፡ ወንጌል መስማት ሳይችሉ የሞቱ የጣዖት አምልኮ ተከታዮች ኢየሱስ ክርስቶስን እንደ ግል አዳኝ ባይቀበሉም ሊድኑ እንደሚችሉ ተናግሯል ብለው የሚሉ አሉ፡፡ Mere Christianity በተሰኘው ሥራው ላይ እንዲህ ሲል ጽፏል፣ “ነገር ግን እንደ እውነቱ ከሆነ እግዚአብሔር ስለሌሎች ሰዎች መዳን ያዘጋጀው እንዴት እንደሆነ አልነገረንም፡፡ በሌሎች ሐይማኖት ውስጥ ያሉ ሰዎች፣ በሃይማኖታቸው ውስጥ ከክርስትና ጋር በማይጋጨው ሐሳብ ላይ እንዲያተኩሩ እግዚአብሔር ለእኛ ሚስጥር በሆነ መንገድ እየሰራባቸው ይሆናል፡፡ ከዚህ ተነስተን ካየን ምንም እንኳን ክርስቶስን ባያውቁም፤ እነርሱ የክርስቶስ ናቸው፡፡”

ሊዊሰ መፅሐፍ ቅዱስ ምንም አይነት ስህተት የለበትም የሚለውን ሃሳብ (biblical inerrancy) አይቀበልም ነገር ግን ጊዜያዊ የቅጣት ቦታ እና በጥምቀት የሚገኝ ዳግም ዉልደት (purgatory and baptismal regeneration) አለ ብሎ ያምናል ብለው የሚነቅፉት አሉ፡፡ አንዳንድ ሐሳቦቹን በተገቢው መንገድ ለመረዳት ሲከብዳቸው፤ ተጨባጭነት የሌለው ክስ የሚያቀርቡ ሰዎችም አሉ፡፡ ለምሳሌ Mere Christianity በተሰኘው መጽሐፉ ውስጥ በክርስቶስ ደም ማመን የክርስትና አስፈላጊ አካል ነው ብሎ እንደማያምን ተናግሯል የሚል ሙግት ያመጣሉ፡፡ ነገር ግን ይህንን ክስ ያስረዳልኛል ብለው ለመረጃ የሚጠቅሱት ሃሳብ የሊዊስ ሃሳብ ሳይሆን እነርሱ እርሱን በትክክል አለመረዳታቸውን የሚያሳይ ነው፡፡ ሊዊስ “”ክርስቶስ ስለ ኀጢአታችን ሞቷል ልትል ትችላለህ፡፡ አብ ይቅር ብሎናል ልትል ትችላለህ ምክንያቱም ክርስቶስ ማድረግ የሚገባንን አድርጎልናልና በበጉ ደም ታጥበናል ልትል ትችላለህ፡፡ ክርስቶስ ሞትን አሸንፏል ልትል ትችላለህ፡፡

ሁሉም እውነት ነው።” ይልና “ነገር ግን ከእነዚህ አንዳቸውም አሳማኝ ሆኖው ካላገኘካቸዉ፣ ልትረዳው ባልቻልከው ነገር ላይ ጊዜህን አታጥፋ። ነገር ግን በትክክል ተረድቼዋለሁ ከምትለው ነገር ጋር ሁን። “ይህንን ያለበትን ዋና ዓላማ ሲያስረዳ ደግሞ “ምንም አይነት ነገር ስታደርግ፤ ከሌሎች ሰዎች ጋር በመጨቃጨቅ አይሁን። ምክንያቱም ሌሎቹ ደግሞ አንተ ከምትረዳበት በሌላ አንግል በኩል ሊረዱ ይችላሉ” በማለት ያስገነዝባል።

ሉዊስ ክርስትናን በተመለከተ ያለው አመለካከት ልዩነት ላይ በማተኮር ሳይሆን ክርስትናን አንድ በሚያደርጉ ሃሳቦች ላይ (ecumenical in his approach to Christianity) ያነጣጠረ ነው። Mere Christianity የሚለውን መፅሐፉን በፃፈበት ወቅት እንዲገመግሙለት ለአንግሊካን፣ ለሜቶዲስት፣ ለፕሬስባይቴሪያን እና ለሮማን ካቶሊክ አገልጋዮች ሰጥቶ ነበር። ሁሉም ክርስቲያኖች አንድ ቀን ወደ አንድነት እንደሚመጡ ያለውን ተስፋ ገልጿል፤ ነገር ግን ጽሑፎቹ የነባር ቤተ እምነቶችን የእምነት መግለጫዎች ለመተካት ያለመ እንዳልሆነም ገልጿል።

## የሉዊስ ሞት እና ለጋሲ

እ.አ.አ. በኤፕሪል 1956 ሲ.ኤስ. ሉዊስ የ57 አመት እድሜ ላይ ሳለ፣ ሁለት ትንንሽ ልጆቿን ለብቻዋ ታሳድግ የነበረውችን አሜሪካዊቷን ገጣሚ ጆይ ዴቪድማን አገባ። ሉዊስ እና ዴቪድማን ለአራት ዓመታት አስደሳች ትዳር አሳልፈዋል። እጅግ ደስተኞች ነበሩ። ጆይ በ1960 በካንሰር ህመም በ45 ዓመቷ ሞተች። የእርሷ ሞት ሊቋቋመው ከሚችለው በላይ የልብ ስብራት ውስጥ ከተተው። ከዛ ስብራት ለመውጣት ያደረገው ጉዞ A Grief Observed በሚለው መፅሐፍ ላይ ፅፎታል።

ሲ.ኤስ. ሊዊስ በዘመን መካከል የማይቀዘቅዝ አስተዋፅኦ ታላቅ የሆነ ሥራ (legacy) ሰርቶ ያለፈ ሰው ነው። ብዙ ደራሲዎች እና ጸሐፊዎች ዱካውን ተከትለው ፍሬያማ ሆነዋል። በእርሱ ሥራ ላይ ተመስርተው የራሳቸውን ሥራ አቅርበዋል። ከእነዚህ ውስጥ ሼልደን ቫኑኩን የፃፈው Severe Mercy ከፊት ይቀመጣል። የዚህም መፅሐፍ ሐሳብ በግማሽ የተወሰደው The Chronicles Of Narnia ከሚለው ከሊዊስ መፅሐፍ ነው። በዳንኤል ሃንድለር የተፃፈው A Series of Unfortunate Events፣ በኢዮን ኮልፈር የተፃፈው Artemis Fowl series፣ የፊሊፕ ፑልማን Dark Materials trilogy፣ እና የጄ.ኬ.ሮውሊንግ Harry Potter የሚለው መፅሐፍ በዚህ ውስጥ የሚካተት ነው። በኋላኛው ዘመን

የነበረው ሕይወቱ በፊልም ተሰርቷል። Sir Anthony Hopkins በዋና አክተርነት የተወነበት Shadowlands የተሰኘው ፊልም ምሁሩ፣ ደራሲው እና አቀበተ እምነቱ ለዊሰ ምን እንደሚመስል አሳይቶናል። ሉዊስ በሕይወት በነበረበት ዘመን የልብ ወለድ ሥራዎቹ ወደ ፊልምነት እንዲቀየር አይፈልግም ነበር። ፊልሞቹ ወደ ሲኒማ እንዳይመጡ ተቃውሟል። ምክንያቱ ደግሞ በጊዜው የነበረው የቴክኖሎጂ እድገት የልብ ወለድ ሥራዎቹን በትክክል ወደ ሲኒማ ለመቀየር ብዙ የሆኑ ስላልነበሩ ነው። በተለይ ደግሞ በልብ ወለድ ድርሰቶቹ ውስጥ የፈጠራቸው የእንስሳት ገጸ ባሕርያት በዘመኑ በነበረው ካሜራዎች ወደ ሲኒማነት ቢቀየሩ "ትርጉም የማይሰጡ ዝም ብለው የሚርመሰመሱ ቅዠት ነገሮች" ይሆናሉ የሚል ነበር።

አሁንም ድረስ በርሱ ሥራ ላይ የተመሠረቱ የሙዚቃና የሥነ ጽሑፍ ሥራዎች የብዙሃኑን የጥበብ ጥም እያረኩ አሉ። Thrice የተሰኘው ቡድን የተጫወተው The Earth Will Shake የሚለው ሙዚቃ እርሱ በጻፈው ግጥም ላይ የተመሠረተ ነው። Sixpence None the Richer የሚለው የሙዚቃ ባንድ ይህንን ስያሜ ለራሳቸው የሰጡት ሉዊስ Mere Christianity በማለት ከፃፈው መፃፍ ላይ ከወሰዱት ጥቅስ ነው።

ጆን ፓይፐር የተባለው አሜሪካዊው ሰባኪ ስለ ሲ.ኤስ .ሊዊስ ሲናገር "ሉዊስ በሁሉም ሥራዎቹ ምን እያደረገ ነበር? የተከደነውን ነገር ይገልጥ ነበር። በኢየሱስ ፊት የእግዚአብሔርን ክብር ይገልጽ ነበር። ሰዎችን ወደ ክርስቶስ ይመራ ነበር። ይህንን የሚያደርግበት መንገድ ደግሞ እጅግ በተካነበት ሮማንቲሲዝም እና አመክኒዮ ነበር። ስለዚህ በእነዚህ መንገዶች ሰዎች ሁሉ ወደክርስቶስ መንገዳቸውን እንዲያቀኑ ጠቁመዋል።" ይለናል።